# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ
# እና
# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

## ግእዝ እና አማርኛ

መስቀል ብሂል ዕፀ ሕይወት ብሂል ኢተሐሰወ ቃለ ነቢይ ዘይቤ ወፀዳሉኒ ከመ ብርሃን ውእቱ፡፡



መስቀል ማለት የሕይወት ዛፍ ማለት ነው፤ ብርሃኑም እንደ ፀሐይ ብርሃን ነው ያለው የነቢዩ ቃል አልታበለም፡፡

### ትርጉም
### መጋቤ ሐዲስ ኀይለ እግዚእ አሰፋ
### መምህር ኀይለ ሚካኤል ወ/ አምላክ
### መምህር ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል

ታኅሣሥ ፳፻፬ ዓ.ም

© ፳፻፬ ዓ.ም አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም

ይኽን የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል የገድል መጽሐፍ ወደ አማርኛ በመተርጐም ለንባብ ያበቃው የደብረ ባሕርይ ጋሥጫ ገዳም ሲሆን ገቢው ማኅበረ ቅዱሳን በከለላ ከተማ በማሠራት ላይ ለሚገኘው የገዳሙ ሁለገብ ሕንፃ ግንባታ የሚውል ነው፡፡

መጽሐፉን በድጋሚ የማሳተም፤ የማሰራጨትና፤ የመሸጥ መብት የቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና የአቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም ነው፡፡

**የደብረ ባሕርይ ጋሥጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፡፡**



አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሕይወትን ጽዋዕ በመልአኩ እጅ እንዳጠጣቻቸው፡፡

## ምስጋና

እነዚህን የገድል መጻሕፍትንና ሌሎችንም በየገዳማቱና አድባራቱ የሚገኙ የቀደምት አበው ሊቃውንት መጻሕፍት እንዳይጠፉ እጅግ ብዙ መከራዎችን አሳልፈው ለእኛ ላደረሱ የደብረ ባሕርይ ሊቃውንት፣ መምህራን፣ ገዳማውያን እና ማኅበረ መነኮሳት በሙሉ ላበረከቱት ታሪክን የመጠበቅ አስተዋጽኦ የአምላክ ቸርነት አይለያቸው እያልን፤ አሁንም የቀደሙት አባቶች በክብር ያቆዩትን ታሪክ በአግባቡ ለትውልድ እንዲተላለፍ ለሚደክሙ ሁሉ ብርታቱን ይስጥልን እንላለን፡፡

የእነዚህ ገድላት የትርጉም ዝግጅት ከተጀመረ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ቢሆንም ይህ ሥራ ደግሞ ለፍሬ እንዲበቃ በተለያየ ጊዜ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና የአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወዳጆች ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡

ገድላቱን ከተለያዩ ቦታዎች በማመሳከርና በመልቀም የመጀመሪያውን የትርጉም ሥራ ያዘጋጁት መ/ር ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል በመንበረ ፓትርያርክ  ጠቅላይ ቤተ ክህነት የቅርስ ጥበቃና ምዝገባ የቤተ መጻሕፍት ወመዘክር መምሪያ ሓላፊ ላደረጉት አስተዋጽኦ አምላካችን የቅዱሳኑን በረከት ይስጥልን እንላለን፡፡

የአባ ጊዮርጊስን ገድል ግእዙን ከእናቱ ላይ በእጃቸው በመጻፍ ደብረ ሊባኖስ ወስደው እንዲተረጎም የደከሙትን መ/ር ፈቃደ ሥላሴ ሣህሌ፣ እንዲሁም ረጅም ጊዜ ወስደው የትርጉም ሥራውን ለሠሩት መ/ር ኀይለ ሚካኤል ወ/አምላክ የደብረ ሊባኖስ ገዳም የመጻሕፍት ትርጓሜ መምህር፣ የእኒህን መምህር የትርጉም ሥራ ያስተባብር ለነበረው ዲ/ን ዳንኤል ክብረት የድካማችሁን ዋጋ ቅዱስ እግዚአብሔር ይክፈልልን፡፡

መጋቤ ሐዲስ ኀይለ እግዚእ አሰፋ የሊቃውንት ጉባኤ አባል የሁለቱንም ገድላት የአማርኛ ትርጉም በማረታት ያልተተረጎሙትንም በመተርጎም መልክና ቅርፅ በመስጠት፣ የተጣራ ሥራ እንዲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለፍሬ እንዲበቃ ስላደረጉ አምላካችን የአገልግሎት ዘመናቸውን እንዲባርክልን እንለምናለን፡፡

የተርጓሚዎቹን ሥራ በማቀናጀት፣ በማስተቸት፣ የኮምፒዩተር ሥራውን በመልቀም እንዲሁም መቅድሙን በማዘጋጀት የረዱንን ዲ/ን አረጋ ጌታነህ በማኅበረ ቅዱሳን የሙያ አገልግሎትና አቅም ማጎልበቻ ዋና ክፍል አስተባባሪ፣ ዲ/ን ደረጀ ግርማ የቅዱሳት መካናትና ማኅበራዊ ልማት ቦርድ የቅስቀሳና ገቢ አሰባሳቢ ክፍል ሓላፊ ሥራው ትኩረት ተሠጥቶት በማኅበሩ በኩል እንዲታተም ላደረጉት የጐላ አስተዋጽኦ የአባ ጊዮርጊስ ጸሎት ይጠብቅልን፡፡ የሁለቱን ገድላት የኮምፒዩተር ጽሑፍ እና ሌይ አውት ዲዛይኑን ለሠራችው የምስራች በላቸው፣ በአጠቃላይ ይህ ሥራ እዚህ ደረጃ እንዲደርስ አስተያየት በመሥጠት፣ በማበረታት የረዱንን፣ በመጨረሻም ለኅትመት እንዲበቃ ወጪውን በመሸፈንና ሥራውን በበላይነት በመከታተል ብሎም ገዳሙን በዘላቂነት ለመርዳት የሁለገብ ሕንፃ እየሠራ ያለውን ማኅበረ ቅዱሳንን የቅዱሳኑ በረከት አይለያችሁ እንላለን፡፡

የደብረ ባሕርይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና አባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም

***ታኅሣሥ ፳፻፬ ዓ.ም***

# መቅድም

መቅድም ማለት ቃሉ የግእዝ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም መጀመሪያ ወይም መግቢያ ማለት ነው፡፡ ወደ ቤት ለመግባት በሩን መክፈት እንደሚያስፈልግ ሁሉ መጽሐፍን ከማንበብ አስቀድሞ መጽሐፉን እና ባለ መጽሐፉን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ መቅድም የሚዘጋጀው በዚህ መሠረት ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ሁለት ገድላትን የያዘ ሲሆን የመጀሪያው ክፍል የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ሆኖ ይህ ክፍል በራሱ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ ተአምረ አባ ጊዮርጊስ እና መልክአ አባ ጊዮርጊስን የያዘ ሰፊ መጽሐፍ ነው፡፡

ሁለተኛው መጽሐፍ ደግሞ ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤልና መልክአ አቡነ በጸሎተ ሚካኤልን የያዘ ክፍል ነው፡፡ ሁለቱም ቅዱሳን በተጋድሎ የነበሩበት ዘመን ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ የሚራራቅ ቢሆንም ቦታው አንድ አካባቢ በመሆኑ በተለይም የአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ደብረ ጎል /ደብረ ግሽ/ በግራኝ መሀመድ ወረራ ከጠፋ በኋላ ታሪኩ ተጠብቆ የኖረው በአባ ጊዮርጊስ ገዳም በመሆኑ፤ አሁንም እንደገና ሲመሠረት ከፍተኛውን ጥረት ያደረጉት የአባ ጊዮርጊስ መነኮሳት በመሆናቸው፤ በአሁኑ ሰዓት በአንድነት እንዲተዳደሩ በመደረጉ ሁለቱ ገድላት በአንድ ላይ ተተርጉመው እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ የገድላቱ ጸሓፊ በዘመኑ የነበረው ሊቅ ወልደ አብ ስለመሆኑ በአባ ጊዮርጊስ ገድል የተገለጸ ቢሆንም ስለ አባ ጊዮርጊስ የተጻፉ በርከት ያሉ ታሪኮች በሌሎች አባቶችም ገድል ውስጥ ይገኛል፡፡ ከእነዚህም ገድል አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ ገድለ አቡነ ጽጌ ድንግል፣ ገድለ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ፣ ገድለ አቡነ ተክለ አልፋን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ ለትርጉም የበቃው የአባ ጊዮርጊስ ገድል ከደብረ ባሕርይ ጋሥጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳም የተገኘ ነው፡፡

ገድል ማለት ስለ መንፈሳዊ ሕይወት የተከፈለ ተጋድሎን የሚገልጽ፣ የሚተርክ ማለት ሲሆን ተጋድሎውም ከዓለም ከባሕርየ ሥጋና ከሰይጣን የሚሰነዘሩ የፈተና ወጥመዶችን ለማለፍ በጾም በጸሎት በትዕግሥት ተወስኖ አጋንንትን ድል መንሳት ማለት ነው፡፡

ተአምር ማለት ደግሞ ድንቅ ማለት ሲሆን እግዚአብሔር በቅዱሳኖቹ ላይ አድሮ በሕይወተ ሥጋም ሳሉ ከሞቱም በኋላ ድውያነ ሥጋን በመፈወስ ድውያነ ነፍስን በማንፃት

ዕዉራንን በማብራት ሀንካሳን በማርታት ሙታንን በማስነሣት የሚሠራው ድንቅ ሥራ ማለት ነው፡፡ አንድም ተአምር ማለት ምልክት ማለት ሲሆን ምልክትነቱም ድንቅ የሆነ የአምላክ ጥበብና ሁሉ የማይሳነው መሆኑን ለማሳየት ከተለመደው ወጣ ብሎ፤ ነገር ግን በቅዱሳት መጻሕፍት ከተገለጸው ድንቅ ሥ ሳይጣላና የመለኮትን ባሕርይ ሳይቃወም በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚደርግ ምልክት ነው፡፡

## አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

አባ ጊዮርጊስ የተወለዱት ጥንተ ስሙ ብሔረ አምሃራ፣ ከላስታና ከዛጒዌ ሥርወ መንግሥት በኋላ የአምሃራ ነገሥታት መናገሻ ከነበረው ከአምሃራ ሳይንት እና አካባቢው በአሁኑ ደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት በቦረና አውራጃ በከለላ ወረዳ በወለቃና በበቶ ወንዝ መካከል በምትገኘዋ ልዩ ስማ ሽግላ/ሰግላ/ ደብረ ማኅው በተሰኘች አካባቢ  በ፲፫፻፵፯ ዓ.ም ነው፡፡

የአባ ጊዮርጊስ አባታቸው ሕዝበ ጽዮን ከተከበሩ መምህራን ወገን የሆኑና የቤተ መንግሥት ባለሟል፣ መጻሕፍትን የሚያውቁ፣ ጥበብ የተመሉና የሽግላ ሀገር ገዥ የነበሩ ሲሆን፤ እናታቸው ደግሞ በወለቃና በበቶ ወንዝ መካከል ከሚገኙ ሹማምንቶች የተወለዱ እምነ ጽዮን የተባሉ ደግ እናት ነበሩ፡፡

የአባ ጊዮርጊስ ቤተሰቦቻቸው የካህናት ወገን የሆኑና ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸው እንደ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ በሕግ የጸኑ ደጋግ ሰዎች ቢሆኑም ልጅ ስላልነበራቸው ዘወትር ወደ ቤተ እግዚአብሔር በመመላለስ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም እና በመልአኩ ዑራኤል ሥዕል ፊት ተንበርክከው እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው ይጸልዩና ይማጸኑ ነበር፡፡

ሁሉን ማድረግ የሚቻለው እግዚአብሔር የለመኑትን የማይነሳ፣ የነገሩትን የማይረሳ ቸር አምላክ ነውና ልመናቸውን ሰምቶ ስእለታቸውን ተቀብሎ በ፲፫፻፵፯ ዓ.ም በወርኀ መስከረም የመላእክት አለቃ ቅዱስ ዑራኤል ተልኮ ልጅ እንደሚወልዱ ስሙንም በሰማዕታት አለቃ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም እንደሚሰይሙት ነገራቸው፡፡

እነሱም የደስታ ምስጋና ለፈጣሪያቸው ለእግዚአብሔር ካቀረቡ በኋላ ቅዱስ አባታችን ጥቅምት ፫ ቀን በ፲፫፻፵፯ ዓ.ም ተፀንሰው በዚያው ዓመት ሐምሌ ፯ ቀን ዕለተ ማክሰኞ ተወለዱ፡፡

አባ ጊዮርጊስም እድሜያቸው ለትምህርት እስከሚደርስ ድረስ እናታቸው በቤት ውስጥ ፈሪሀ እግዚአብሔር እያስተማሩ በጥበብና በዕውቀት ካሳደጓቸው በኋላ አባታቸው ሕዝበ ጽዮን በቤተ መንግሥት በንጉሡ ድንኳን ዙሪያ ከሚያገለግሉት ካህናት መካከል ስለነበሩ ልጃቸውን በመልካም አስተዳደግና ትምህርት በማስተማር አሳደጓቸው፡፡

ሕዝበ ጽዮን ልጃቸውን በዘመኑ ከነበሩት ጳጳስ ዘንድ በመውሰድ ዲቁና ካሾሟቸው በኋላ በጊዜው በኢትዮጵያ ታላቅ የትምህርት ማእከል በነበረችው ሐይቅ ደብረ ነጐድጓድ ገዳም ወደምትገኘው ትምህርት ቤት ይዘዋቸው በመሔድ ከታላቁ ሊቅ ዐቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃን ጋር እንዲማሩላቸው አድርሰዋቸው መጡ፡፡

አባ ጊዮርጊስ በማኅፀን የተመረጡና ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ናቸውና የአባታቸውን ትእዛዝ እንደ ይስሐቅ በደስታ ተቀብለው ያለ ዕረፍት የጉልበት ሥራ በመሥራት ገዳሙን ያገለግሉና አባቶችን ይረዱ ነበር፡፡ ሌሊት ሌሊት ደግሞ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ሥር  አብዝተው በመስገድ ፈጣሪያቸውን ይማፀኑ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ አባታቸው እንደተመኙት ትምህርት ለአባ ጊዮርጊስ በቀላሉ ሊገባቸው አልቻለም፡፡ ይህንን የተረዱት አባ ሠረቀ ብርሃን እንዳይወቀሱ ትምህርት ሊገባው አልቻለምና ሌላ ሙያ አስተምረው ብለው ወደ አባታቸው ላኳቸው፡፡ አባታቸውም መልሰው በማምጣት ልጄን የወለድኩት በስእለት ነውና ከዚሁ ገዳሙን እያገለገለና አባቶችን እየረዳ ይኑር ብለው ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም አድርሰዋቸው ተመለሱ፡፡



በዚያም ትምህርታቸውን እየተማሩ በቀን ዘጠኝ ዘጠኝ ቅርጫት እየፈጩ ማገልገል ቢጀምሩም ቅን አገልግሎት የሚያበረክቱላቸው መነኮሳትም ከማመስገን ይልቅ ትምህርት የማይገባው እያሉ ይሰድቧቸውና ይነቅፏቸው ጀመር፡፡ አባ ጊዮርጊስ ግን ጸጋ እግዚአብሔር ያደረባቸው ደግ ሰው ናቸውና እንደ ሰደቡኝ ልሳደብ እንደ ናቁኝ ልናቅ ሳይሉ የተለመደ አገልግሎታቸውን ሳያቋርጡ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም

ሥዕል ሥር በግንባራቸው ተደፍተው፤ እመቤቴ ሆይ መነኮሳቱ በእኔ ላይ እየፈጸሙብኝ ያለውን ነቀፋና ዘለፋ ተመልከተሽ ትምህርቱን እንዲገልጽልኝ ከልጅሽ ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ አማልጂኝ እያሉ ሲያለቅሱና ሲማፀኑ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በገሐድ ተገልጻ አይዞህ አታልቅስ ትምህርት ተከልክሎብህ ሳይሆን የምትጠቀምበት ጊዜው እስኪደርስ ነበር፤ አሁን ግን ጊዜው ደርሷልና እስከ ፯ ቀን በዚሁ በሱባዔው እንዳለህ ሆነህ ጠብቀኝ ብላቸው ተሰወረች፡፡

እሳቸውም ተስፋውን ተቀብለው በሱባዔ እንዳሉ በ፯ኛው ቀን እንደተለመደው በሥዕለ ማርያም ሥር ተደፍተው ሲያለቅሱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የመላእክት አለቃ ቅዱስ ዑራኤልን አስከትላና ጽዋዓ እሳት አስይዛ መጥታ የሕይወት ጽዋዕ አጠጣቻቸው፡፡



አባ ጊዮርጊስም የሕይወት ጽዋዕን ከጠጡ በኋላ የሰማይና የምድር ምስጢር ሁሉ ተገለጸላቸው፡፡ በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ተመልተው እግዚአብሔር በመዓልትና በሌሊት በዜማ የሚመሰገንባቸውን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በጸሎት የምትመሰገንበትን እና ሌሎችንም የምስጋናና የጸሎት ቅዱሳት መጻሕፍትን ደርሰዋል፡፡

አባ ጊዮርጊስ እንደ ሐዋርያት በሀብተ መንፈስ ቅዱስ የተመሉ አባት ስለነበሩ ዕውቀት ሳይወሰንባቸው ከቅዱስ ያሬድ የዜማ ትምህርት ሊቃውንት መካከል ፳ኛ የዜማ መምህር ናቸው፡፡ በዚህም የቅዱስ ያሬድን ዜማ በተለይም ድጓውን በዘመናት ከፋፍለውና በየበዓላቱ አደራጅተው ቅርፅ በማስያዝ ለቅዱሳኑ ሁሉ በየበዓላቶቻቸው የሚዜመውን አዘጋጅተው ለደቀ መዛሙርቶቻቸው በማስተማር እንዲስፋፋ አድርገዋል፡፡ አባ ጊዮርጊስ ድጓውን በደብረ ነጐድጓድ ሐይቅ ፯ ዓመት፤ በርእሰ አድባራት ተድባበ ማርያም ደግሞ ፯ ዓመት ካስተማሩ በኋላ ከእሳቸው ደቀ መዛሙርት መካከል እነ ልሳነ ዕፍረት ድጓውን ቤተልሔም ይዘውት በመሔድ ከግራኝ ጥፋት በኋላ እዚያው በመገኘቱ ቤተልሔም የድጓ ምስክር ሆኖ ቀርቷል፡፡

በዚህም በዜማው በኩል አባ ጊዮርጊስ ከያሬድ በኋላ የተነሡ ዳግማዊ ያሬድ ሲባሉ በዘመኑ የነበሩ መናፍቃንን በመከራከርና በመርታታቸው ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ የሚል ስም ተሰጥቷቸዋል፡፡

አባ ጊዮርጊስ ይማሩበት በኋላም ያስተማሩበትና ብዙ ደቀ መዛሙርትን ያወጡበት የነበረው ቦታ ደብረ እግዚአብሔር ይባል ነበር፡፡ ይህንንም ለማስረዳት የዜማ ሊቃውንት ሁሉ ዋና ምስክር መጽሐፍ የሆነው ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ በመቅድሙ ወተምህረ አባ ጊዮርጊስ እምደብረ እግዚአብሔር ይላል፡፡ ይህም ታላቅ ደብር እስከ ግራኝ መሀመድ ወረራ ድረስ ልክ እንደ ዛሬዋ ቤተልሔም የቅዱስ ያሬድ የዜማ ማእከል የነበረ፤ ብዙ ሊቃውንትን ያፈራ እንደነበርና  አፄ ዳዊትም አባ ጊዮርጊስን የደብረ ነጎድጓድ የዜማ ምስክር አድርገው ሾመውት እንደነበር በታሪክ የሚታወቅ  ሲሆን ከገድሉ ላይም ወይደምፅ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር ሲል ይገኛል፡፡ ይህ ታላቅ ቦታ በ፲፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበረው ወረራ በእሳት ቃጠሎ እንደጠፋ ቦታውም በሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም በምሥራቅ በኩል ወደ አውሳ መሔጃ እንደ ነበር በታሪክ ተመዝግቧል፡፡

**ደብረ ባሕርይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም**

ደብረ ባሕርይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም የተመሠረተው በታላቁ ሊቅ በአባ ጊዮርጊስ ቢሆንም ከዚህ ተራራ በምስራቅ የገደሉ ጫፍ ላይ ደብረ ጎል አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ይገኛል፡፡ ይህ ገዳም ከአቡነ ኢየሱስ ሞዓ አሠረ ምንኩስናን የተቀበሉት አቡነ በጸሎተ ሚካኤል የመሠረቱት ሲሆን በገድለ ተክለሃይማኖት ዐርባ ሁለተኛ ምዕራፍ ላይ እንደተጠቀሰው አቡነ ተክለሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ምናኔ ሲወጡ ምንኩስናን የተማሩበት ቦታ ነው፡፡ ይህ ገዳም በሰፊው የሚታወቀው በጻድቁ በአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ስምና ዘመን ሲሆን ይህ ታላቅ ቦታ በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት በከላላ ወረዳ ከአዲስ አበባ ፮፻፪ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

የገዳሙ አካባቢና አቀማመጥ እጅግ የሚማርክና አስገራሚ ግርማ ያለው ሲሆን በገዳምነት የተመሠረተበትና የነገሥታቱ መማሪያና መኖሪያ በመሆን የታወቀበት ዘመንም አባ ጊዮርጊስ ካስተማሯቸው ነገሥታት መካከል በዓፄ ይስሐቅ ዘመን ፲፫፻፺፱-፲፬፻፲፬ ነው፡፡

የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች ባለቤት የሆነው ይህ ገዳም፤ አባ ጊዮርጊስ ከ፺ በላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን የደረሱበት ታላቅ ቦታ ነው፡፡ ደብረ ባሕርይ እጅግ ታላላቅ ሊቃውንት የወጡበት ቦታ ሲሆን በአፄ ሠርፀ ድንግል ዘመን ታላቅ መምህረ ወንጌልና የብርብር ማርያም አለቃ የነበሩት አባ ባሕርይ የዚህ ቦታ ሊቅ ነበሩ፡፡ በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ዘመን የታተመው መዝሙረ ዳዊት የእኒህን ሰው ድርሰት ማለትም መዝሙረ ክርስቶስን የያዘ ሲሆን በመቅድሙ ላይ የአባ ጊዮርጊስ እኅት ልጅ እንደነበሩ ወልደ እኅቱ ለአባ ጊዮርጊስ በማለት ይናገራል፡፡ አባ ባሕርይ የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክን የጻፉ ሲሆን በሌሎች በርካታ ሥራዎችም ይታወቃሉ፡፡

አባ ጊዮርጊስ የእመቤታችንን ምስጋና በ፻፶ መዝሙረ ዳዊት ልክ እንዳዘጋጁ እሳቸውም የመድኀኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምስጋና ፻፶ መዝሙር ልክ መዝሙረ ክርስቶስ በማለት አዘጋጅተዋል፡፡

አባ ባሕርይ የሚለው ስማቸው መነኮስ ዘደብረ ባሕርይ ካለው የተወሰደ ነው፡፡

የአባ ጊዮርጊስ ገድል ጸሓፊ ወልደ አብም እንዲሁ ታላቅ የነበረ ሲሆን በሌሎች ሥራዎችም ይታወቃል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አባ ጊዮርጊስ አስተምረዋቸው ለንግሥና ከበቁት መካከል አፄ ዘርዓ ያዕቆብም ከንግሥናቸው በተጨማሪ በደረሷቸው ድርሰቶችና ለእመቤታችን ባላቸው ፍቅር በሳቸው ውስጥ አባ ጊዮርጊስና ትምህርታቸው ጎልተው ስለሚታዩ ከሊቃውንቱ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

ገዳሙ በ፲፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግራኝ መሀመድ ጥፋት ከአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ጋር ከፍተኛ ጉዳት ቢደርስበትም ብዙም ሳይቆይ እንደገና ተመሥርቷል፡፡

ወደ አምባው ለመውጣት አንድ በር ብቻ ሲኖረው የሚወጣውም በሁለት ታላላቅ ገደሎች መካከል በእርከን ተከፋፍሎ በተዘጋጀ ፵፮ ሜትር ርዝመት ባለው የእንጨት መሰላል በመጠቀም ነው፡፡

አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በአምባው ላይ ራሳቸው ፈልፍለው ያነፁት ቤተ መቅደስ ሲኖር ይህም ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስትና መቅደስን የያዘ በዐለት ምሰሶም የተከፋፈለ ነው፡፡

በገድላቸው ላይ ተጽፎ እንደሚገኘው ቤተ መቅደሳቸውን ከድንጋይ ከብርና ከወርቅ ስለ መሠራቱ በአእባነ ብሩር ወወርቅ ቤተከ ሐነፁ ሲል ይገኛል፡፡ በዚያም የእመቤታችን ጽላት እንደነበረበት ይነገራል፡፡ የኋላ ሊቃውንት ግን አሁን በአባ ጊዮርጊስ ስም እያገለገለ ያለውን ቤተ መቅደስ እየተገለገሉበት የቆዩ ሲሆን የጥንቱ ማለትም ከብርና ከወርቅ የተሠራው ቤተ መቅደስ ተሠውሯል የሚሉም አሉ፡፡

ይህ ቤተ መቅደስ አስገራሚ የሚሆኑ የብርሃን መስኮቶች ያሉትና አባ ጊዮርጊስ ድርሰት የደረሱባቸው ዋሻዎች፣ የክርስትና ቤትና የቅዱሳን መካነ ዓፅም ከዐለት ተፈልፍለው ተሠርተዋል፡፡

ከቤተ ክርስቲያኑ በተጨማሪ በአምባው ላይ ከ፲፪ በላይ የሚሆኑ የውኃ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶች፤ ቤተልሔም፤ የጸሎት ማድረሻ ዋሻዎችና የቅዱሳን ዓፅም የሚያርፍባቸው በርካታ ዋሻዎች ይገኛሉ፡፡

በአባ ጊዮርጊስ ገዳም ሌላው አስደናቂ ነገር ከአባ ጊዮርጊስ በኋላ የተነሡ ሊቃውንት ተመሣሣይ የውኃ ጉድጓዶችንና ዋሻዎችን መሥራት የማይችሉ መሆናቸው ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከስድሳ በላይ መነኮሳት በቦታው ላይ ሲኖሩ አባታችን ባዘጋጁት የውኃ ጉድጓድ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህ ውኃ ከ፮ወር በላይ ስለማያስጠቅም ከሁለት ሰዓት በላይ የእግር ጉዞ ተጉዘው ከሚያገኙት ወንዝ በትከሻቸውና በአህያ እያመላለሱ ይጠቀማሉ፡፡ በዚህም ከፍተኛ የውኃ ችግር ያለባቸው ሲሆን አካባቢው ለምንም ዓይነት ልማት መዋል የሚችል ቦታ ባለመሆኑ የቀለብ ችግርም በተደጋጋሚ ገዳሙን ሲፈትነው ይታያል፡፡

አባ ጊዮርጊስ በዘመኑ ከነበሩት ጻድቁ አባ ጽጌ ድንግል ጋር ለመገናኘት እንዲችሉ የወለቃን ድልድይ ያዘጋጁ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት የተነሡ መናፍቃንን በመከራከር የቤተ ክርስቲያን ጠበቃ ከመሆናቸውም በላይ ብዙ የጸሎት፣ የሥነ መለኮት የዜማ መጻሕፍትን አዘጋጅተው ቤተ ክርስቲያን እንድትገለገልባቸው በማድረግ ቀዳሚውን ቦታ ይይዛሉ፡፡

የአባ ጊዮርጊስ የድርሰት ሥራዎችን በተመለከተ ለጊዜው የታወቁትን በገድሉ ውስጥ የተገለጹትን ለመግለጽ ያህል፤

፩. መጽሐፈ ብርሃን የመዓልትና የሌሊት ሰዓታት
፪. አርጋኖነ ውዳሴ
፫. ኆኅተ ብርሃን
፬. ውዳሴ መስቀል
፭. ዕንዚራ ስብሐት
፮. ሕይወተ ማርያም
፯. ተአምኆተ ብርሃን /ተአምኆ ቅዱሳን/
፰. ውዳሴ ስብሐት
፱. ውዳሴ ሐዋርያት
፲. ፍካሬ ሃይማኖት
፲፩. ጸሎተ ፊትቶ /በቅዳሴ ጊዜ የሚጸለይ/
፲፪. መጽሐፈ ምስጢር
፲፫. መዓዛ ቅዳሴ
፲፬. ቅዳሴ እግዚእ ካልእ
፲፭. ውዳሴ ማርያም ካልእ
፲፮. ጸሎት ዘቤት ውስተ ቤት
፲፯. መዝሙረ ድንግል ሲሆኑ፤

በገድሉ ውስጥ በቀጥታ ካልተጠቀሱት መካከል መልክአ ውዳሴ፣ መልክአ ሥዕል፣ ይዌድስዋ ማርያም /የሰዓታት ክፍል/ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

ከአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ብዙዎቹን የውጭ ተመራማሪዎች ለተለያዩ አገልግሎቶች ሲጠቀሙባቸው  በአንፃሩ የሀገር ውስጥ ተማራማሪዎች እምብዛም አልተጠቀሙባቸውም፡፡ የጸሎትና የምሥጋና ድርሰቶቹን እንዲሁም የሥነ መለኮት ድርሰት የሆነውን መጽሐፈ ምስጢርን በተመለከተ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተለያዩ አንባቢዎች እየተገለገሉባቸው እንደሆነ ቢታወቅም ገዳሙ እነዚህን ገድላት ለንባብ ሲያበቃ አንባብያን የቅዱሳንን ተጋድሎ እንዲያውቁና ከበረከታቸው እንዲሳተፉ ብሎም ገዳሙን ለመጠበቅ በሚደረግ ጥረት ውስጥ ድርሻቸውን እንዲወጡ በማሰብ ነው፡፡

በዚህ የገድል መጽሐፍ ውስጥ የተካተተው ሁለተኛው ገድል ደግሞ  የአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሲሆን እኒህ ቅዱስ በዚያው በሀገረ ሸግላ በ፲፫ኛው ምእት ዓመት የተወለዱ ሰማዕትና

የሃይማኖት ጠበቃ የነበሩ ሊቅ ናቸው፡፡ የአቡነ በጸሎተ ሚካኤል አባት ከካህናት ወገን የሚሆኑ ማርቆስ የሚባሉ የእናታቸውም ስም እግዚእ ክብራ እንደሚባሉ በገድላቸው ተገልጾአል፡፡ ይህንንም እርሷም ከክቡራን ወገን ናት፤ እነርሱም ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለዱ በማለት አስቀምጦታል፡፡

አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገና በእናታቸው ማኅፀን እያሉ የሡሩትን ተአምር ገድላቸው እንዲህ በማለት ይናገራል፡፡ ያደጉት ልጆቿ ራሳችን ወይም ሆዳችን እያሉ ታመምን ካሉ በእጅዋ የሆዷን ፅንስ ይዛ የልጆቿን የታመመ አካላቸውን ትዳስሳቸዋለች፤ ያን ጊዜ በእግዚአብሔር ቸርነት ይፈወሱ ነበር በማለት በጥሩ ሁኔታ ገልጾታል፡፡

ጻድቁ አባታችን ገና በልጅነታቸው ወደ ገዳም በመሔድ ለገዳሙ አበምኔት እኔ መመንኮስ እፈልጋለሁ የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡም አበምኔቱ ግን ዕድሜያቸውን አይተው ፈተናው ይከብድሃል፤ የተወሰነ ጊዜ ቆይተህ እየው ብለዋቸው በገዳሙ ውስጥ መኖር ይጀምራሉ፡፡ የአቡነ በጸሎተ ሚካኤል አባት ልጃቸውን ለመፈለግ ወደ ገዳሙ በመሔድ እናትህ እግዚእ ክብራ ናፍቃለች ብለው ይዘዋቸው ወደ ቤት ተመለሱ፡፡ በጸሎተ ሚካኤል ግን የለመዱትን የጸሎትና የተጋድሎ ሥራ ቢቀጥሉም ቤተሰቦቻቸው ሚስት ማግባት አለብህ በማለት አስቸገሯቸው፡፡ አባ በጸሎተ ሚካኤል ግን እስከ መጨረሻ በመጽናታቸው የአባታቸው ዐሳብ አልተሳካም፡፡ በኋላም ይህ ፍላጐታቸው አይሎ ከመነኮሱ በኋላ በማስተማር፣ በዘመኑ የነበሩ ፍትሕን የሚያዛቡ ሰዎችን በመገሠፅ ተጋድሏቸውን ቀጠሉበት፡፡

በተለይም በዘመኑ የነበረውን ንጉሥና ሠራዊቱን እንዲሁም የአባቱን ሚስት አግብቶ ለፍርድ የቀረበ ወጣትን በተመለከተ የሰጡትን ፍርድ ስንመለከት መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በሄሮድስ ላይ የሰጠውን ፍርድ ያስታውሰናል፡፡ ጻድቁ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል በሀገረ ሲዋ፣ በትግራይ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች በመንቀሳቀስ ሰፊ ትምህርት ያስተማሩ መሆናቸውን በገድላቸው ላይ እንዲህ ሲል ይገኛል፡፡ "በመጀመሪያ በእንግድነቱ በኋላም በስደቱ ስለ ጐበኛት የትግራይ ምድር ዛሬ ትደሰታለች በአጥንቶቹ ስለ ቀደሳት የተንቤን ምድር ሐሤት ታደርጋለች"፡፡በመጨረሻም በሰማዕትነት ያረፉ ታላቅ አባት ናቸው፡፡

የእኒህ አባት ገድላቸው የሚነገርበትና ዓፅማቸው ያረፈበት ቦታ በበረከት የተመላ

የእኒህ አባት ገድላቸው የሚነገርበትና ዓፅማቸው ያረፈበት ቦታ በበረከት የተመላ ከመሆኑም በላይ ደቀ መዛሙርቱ ዝናም በሌለበት ቦታ ዓፅማቸውን በማንቀሳቀስ ይጠቀሙባቸው እንደነበር በገድላቸው ውስጥ ተፅፎ ይገኛል፡፡ ይህ የአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገድል እጅግ ማራኪና ሕይወት የሆነ ገድል ሲሆን የገድል ጸሓፊውም የአባ ጊዮርጊስን ገድል ጸሐፊ ራሱ ወልደ አብ ስለመሆኑ በጽሑፉ ይዘት ይታወቃል፡፡

በእኒህ ጻድቅ ስም የታነፀው ቦታ መካነ ዓፅማቸው የሆነው በደብረ ባሕርይ አባ ጊዮርጊስ ገዳም በስተምስራቅ በኩል መግቢያው ላይ ከታላቅ ዐለት ፈልፍለው ባነፁት ቤተ መቅደስ ውስጥ ነው፡፡

ቤተ መቅደሱ በተለያዩ ጊዜያት በሚነሱ ጦርነቶችና በክርስቲያን ምእመናን ቁጥር መመናመን ምክንያት ለረጅም ጊዜ ከተዘጋ በኋላ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ ደጋግ ምእመናን ተመልሶ አገልግሎት እንዲሠጥ ተደርጐ በአሁኑ ጊዜ ከአባ ጊዮርጊስ ገዳም ጋር ተደርቦ የደብረ ባሕርይ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም ይባላል፡፡ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል የካቲት ፲፪ ቅዳሴ ቤታቸው የከበረበትና ሐምሌ ፳፩ የዕረፍታቸው በዓል በደማቅ ሁኔታ ይከበራል፡፡

**የቅዱሳን አባቶቻችን ረድኤት ይድረሰን አሜን፡፡**

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

በስመ ሥሉስ ቅዱስ ሰማየ ሰማያት ዘኢያገምሮ ወዘባነ ኪሩብ ኢይጸውሮ ለዓለመ ኲሉ ፍጥረት በሐሳበ ልቡ ዘገብሮ ወለብርሃነ መዓልት በንባበ ቃሉ ዘፈጠሮ በከርሠ ደመና ረቂቅ ለግዘፈ ማይ ዘየዐቍሮ ወለዓንበሬ ባሕር ዘይመትሮ ኲሎ ኀይሎ ኢንክል ተናግሮ ወባሕቱ ንኅድግ ሎቱ አእምሮ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

ሰማየ ሰማያት በማይወስነው፣ የኪሩብ ጀርባ በማይሸከመው፣ የዓለምን ፍጥረት ሁሉ በልቡ ሐሳብ በፈጠረው የቀኑን ብርሃንም በቃሉ ንባብ በፈጠረው፣ በረቂቅ ደመና ሆድ የውኃውን ግዘፍ በሚቋጥረው፣ የባሕር ዐንበሪንም በሚቆርጠው ልዩ ሦስት በሆነ በሥላሴ ስም ኀይሉን ሁሉ መናገር አይቻለንም፤ ነገር ግን ዕውቀትን ለእርሱ እንተውለት ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፩

፩ ንዌጥን እንከ በረድኤተ እግዚአብሔር ወሠናይ ተሰናዕዎቱ ከመ ንጽሐፍ ገድሎ ወትሩፋቲሁ ጣዕመ ቃሉ ወሳዕስአ ከናፍሪሁ ለአቡነ ጊዮርጊስ ለባሴ እግዚአብሔር ድንግል ወንጹሕ፡፡

፪ ዘተመሰሎ ለእግዚእነ ክርስቶስ ከመ ይጹር መስቀሎ በኀይል ንጹሕ ወበልብ ፍጹም በከመ ይቤ ለሊሁ እግዚእነ በወንጌል ዘኢጾረ መስቀሎ ወኢተለወኒ ኢይክል ከዊነ ረድእየ፡፡ ወካዕበ ይቤ እስመ ኲሉ ዘይገብር ፈቃዶ ለአቡየ ዘበሰማያት ውእቱ እምየኒ ወእኁየኒ ወእኅትየኒ፡፡

ማቴ. ፲፥፴፰፣ ፲፪፥፶

## ምዕራፍ አንድ

፩ ንጹሕና ድንግል፣ የሚሆን እግዚአብሔርን የለበሰ የአባታችን ጊዮርጊስን የአንደበቱን ቅልጥፍና የቃሉን ጣዕም ገድሉንና ትሩፋቱን በመልካም መስማማት እንጽፍ ዘንድ በእግዚአብሔር አጋዥነት እንጀምራለን፡፡

፪ በንጹሕ ኀይልና በፍጹም ልብ መስቀሉን ይሸከም ዘንድ ጌታችን ክርስቶስን የመሰለው፤ እርሱ ጌታችን በወንጌል "መስቀሉን ያልተሸከመ ያልተከተለኝም የእኔ ደቀ መዝሙር መሆን አይችልም" እንዳለ፡፡ ዳግመኛም በሰማያት ያለ የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እርሱ እናቴ፣ ወንድሜ እኅቴም ነው አለ፡፡

ማቴ. ፲፥፴፰፣ ፲፪፥፶

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፫ | ዛቲኬ ተስፋ ሠናይት አጽሐቀቶ ለአቡነ ጊዮርጊስ ከመ ይትዐገሥ ቀኑስላቲሁ በሥጋሁ ወይጹር ትዕይርተ መስቀሉ፡፡ | ፫ | ይህች መልካም ተስፋ አባታችን ጊዮርጊስን በሥጋው ቁስልን ይታገሥ ዘንድ የመስቀሉንም ተግዳሮት ይሸከም ዘንድ አተጋቸው፡፡ |
| ፬ | ገደፋ ለነፍሱ ከመ ይርከባ ወመነና ከመ ያጥርያ፡፡ ገብረ አዕርክተ እምንዋየ ዓመፃ ዘውእቱ ምጽዋት ከመ አመ ኀልቀ ይትወከፍዎ ውስተ ምጽላላቲሆሙ ዘለዓለም እሉኬ ፍጻሜ ማኅበራ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡፡ | ፬ | ነፍሱን ያገኛት ዘንድ ጣላት፤ ይገዛትም ዘንድ ናቃት፤ በኀላፊውም ገንዘብ ወዳጁን ገዛ፤ ይኸውም ምጽዋት ነው፤ ባለቀ ጊዜ በዘለዓለም ቤታቸው ይቀበሉት ዘንድ የቤተ ክርስቲያን የአንድነቷ ፍጻሜ እኒህ ናቸው፡፡ |
| ፭ | ወዘልፈ ኮነ ይትቀነይ ለእግዚአብሔር እንዘ ይጐይይ እምነጽሮ ምግባራተ ከንቱ ዘዘዓለም ኃላፊ፡፡ ወፈተወ ምግባረ ሰማያዊተ ተዘኪሮ ቃለ ዘይቤ ብፁዕ ጳውሎስ እመሰ ሞትክሙ ምስለ ክርስቶስ ኅሡኬ እንተ ኀበ ላዕሉ ኀበ ሀሎ ክርስቶስ ዘይነብር በየማነ እግዚአበረሔር ወአኮ ዘውስተ ምድር፡፡ | ፭ | የኃላፊውን ዓለም ከንቱ ሥራ ከማየት እየሸሸ ለእግዚአብሔር ዘወትር የሚገዛ ሆነ፤ ብፁዕ ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው በክርስቶስ ምድራዊውን ያይደለ ሰማያዊውን ነገር ፈልጉ ያለውን ቃል አስቦ ሰማያዊውን ሥራ ወደደ፡፡ |
| ፮ | እስመ ሕሊና ያጌብራኒ ከመ አይድዕክሙ አ ፍቁራንየ ዜናሁ ለቅዱስ አቡነ ጊዮርጊስ አፈ በረከት ዘኮነ ዕረፍቱ አመ ፯ ለሐምሌ ወባሕቱ እፈርህ ከመ እወጥን ወእንግር ዕበያቲሁ ለዝንቱ ኀያል ወመዋዒ ኵሉ ተቃትሎቶ ለጸላኢ፡፡ እስመ ተቃትሎተ ነፍስ የዐፅብ እም ተቃትሎተ ሥጋ፡፡ ተቃትሎ ሥጋሰ ምስለ ሥጋውያን ወተቃተሎተ ነፍስሰ ምስለ መንፈሳውያን፡፡ | ፮ | ወዳጆቼ ሆይ ዕረፍቱ ሐምሌ ሰባት ቀን የሆነ የቅዱስ አፈ በረከት ጊዮርጊስን ዜናውን እነግራችሁ ዘንድ ኅሊናዬ ግድ ይለኛል፡፡ ነገር ግን የጠላት ዲያብሎስን ውጊያውን / ሰልፉን/ ሁሉ ያሸነፈ የዚህን ኀያል ክብር እጀምርና እናገር ዘንድ እፈራለሁ፡፡ በሥጋ ከመዋጋት በነፍስ መዋጋት ይከብዳልና፡፡ የሥጋ ውጊያ /ጦርነት/ ከሥጋውያን ጋር ነው የነፍስ ውጊያ ግን ከመናፍስት ጋር ነው፡፡ ኤፌ.፮፥፲ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፯ ወይእዜኒ እስመ አነ አአምር ድካመ ልቡናየ ወሕጸጸ አእምሮትየ ለነቢበ ውዳሴያቲሁ ወፈድፋደሰ ላዕለ ኀሊናየ ድኩም ወልሳንየ ጸያፍ። ወዳእሙ እሴፎ እም እግዚአብሔር ከመ ያብርህ ልቡናየ በፀዳለ ብርሃኑ ለዝንቱ ኮከብ ወየሀቦ ኀይለ ለልሳንየ ሕጹጽ ከመ እንግር ንስቲተ መንከራቲሁ ወገድሎ ጥዕመተ ለሕዝብ መፍቀርያነ ክርስቶስ እለ ጸውዖሙ ዮም ፍሥሓ በዐሉ ለአቡነ ጊዮርጊስ።

፯ አሁንም ምስጋናዎቹን ለመናገር የዕውቀቴን ጉድለት የልቡናዬንም ድካም እኔ ዐውቃለሁና። ይልቁንም ሐሳቤ ደካማ አንደበቴም ጸያፍ ነው። ነገር ግን በዚህ ኮከብ ብርሃን ልቡናዬን ያበራልኝ፤ ዕውቀት ለጐደለው አንደበቴም ኀይልን ይሰጠው ዘንድ የአባታችን ጊዮርጊስ የበዓሉ ደስታ ለጠራቸው ክርስቶስን ለሚወዱ ምእመናን የሚጣፍጥ ገድሉንና ድንቅ ተአምራቱን በትንሹ እናገር ዘንድ እግዚአብሔርን ተስፋ አደርጋለሁ።

፰ ወየሀበኒ እንግር በፍትወተ አእምሮ ህልወ ወአኮ ሐሰወ ወአኀሊ ዘይደሉ ወዘእትናገር። እስመ ለጥበብሂ መርሐ ውእቱ ወለጠበብት መርትዖሙ ከመ እዜኑ ግብሮ ለአቡነ ጊዮርጊስ ሥዕል አምላካዊ ወአይቀኑና ክርስቶሳዊ።

፰ ሐሰት ያይደለ እውነትን በዕውቀት መሻት እናገር ዘንድ ይስጠኝ፤ የሚገባውንና የምናገረውንም አስባለሁ፤ እርሱ ለጥበብ መሪ ለጠቢባንም መቅኖቻቸው ነውና፤ የአምላካችን ክርስቶስ ሥዕልና ማደሪያ የሆነ የአባታችን ጊዮርጊስን ሥራውን እናገር ዘንድ።

፱ ኮከበ ክብር ጽዱል ፀሐየ አግአዚ ብሩህ አቡነ ጊዮርጊስ ጥዑመ ስም ወሠናየ ግእዝ። መጋቤ ሃይማኖት ወመሠረተ ቤተ ክርስቲያን። ዘነሥአ ሞገሰ እምኀበ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ።

፱ አባታችን ጊዮርጊስ የሚያበራ የክብር ኮከብ፣ የኢትዮጵያ ብሩህ ፀሐይ፣ ስሙ የሚጣፍጥ፣ ምግባሩም የቀና ነው። ከአብ፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስም ሞገስን ያገኘ እርሱ የሃይማኖት መምህር የቤተ ክርስቲያንም መሠረት ነው።

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲ ወተወፈየ ወልታ መዊዕ እምኀቤሆሙ፡፡ ዝንቱ ውእቱ አቡነ ጊዮርጊስ ዘኀረዮ አብ ከመ ይኩን ላእከ ቤቱ ወአፍቀሮ ወልድ ከመ ይኩን ካህነ ምሥዋዑ ወአክበሮ መንፈስ ቅዱስ ከመ ይኩን መጋቤ ሕጉ፡፡

፲ ከእነርሱም ዘንድ የማሸነፍ ጋሻን ተቀበለ፤ የቤቱ አገልጋይ ይሆን ዘንድ አብ የመረጠው፣ የመሠዊያው ካህን ይሆን ዘንድ ወልድ የወደደው፣ የሕጉ አስተማሪም ይሆን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ያከበረው ይህ አባታችን ጊዮርጊስ ነው፡፡

፲፩ መፍትው ንጸውዖ ዮም ለኢያሱ ወልደ ሲራክ ከመ ይብለነ ንወድሶሙ ለእደው ክቡራን ለአበዊነ ዘበመዋዕሊሆሙ፡፡ እስመ ብዙኀ ክብረ ወሀቦሙ እግዚአብሔር፡፡ ወዕበዩኒ ዘእምፍጥረተ ዓለም፡፡ ሲራ.፵፬፥፩

፲፩ በዘመናቸው አባቶቻችንን እናመስግናቸው ይለን ዘንድ የሲራክ ልጅ ኢያሱን ዛሬ ልንጠራው ይገባናል፤ እግዚአብሔር ብዙ ክብርን ሰጥቷቸዋልና ክብሩም ከዓለም መፈጠር አስቀድሞ ነው፡፡ ሲራ.፵፬፥፩

፲፪ ወከማሁ ንሕነኒ ንወድሶ ዮም ለአቡነ ጊዮርጊስ ባሕረ ጥበባት ወአበ ልሳናት ካህን ዘበአማን ዘተሰምየ በአእምሮቱ ወመካሪ በጥበቡ ወይነግር በትንቢቱ ወጥበበ ቃሉ ዘውስተ ልቡ፡፡

፲፪ እኛም እንደዚሁ በዕውቀቱ እውነተኛ ካህን የተባለ የቋንቋዎች አባትና የጥበባት ባሕር አባታችን ጊዮርጊስን ዛሬ እናመስግነው፡፡ በጥበቡም መካሪ ነው በትንቢቱም በውስጡ ያለ የቃሉን ጥበብ ይነግራል፡፡

፲፫ እስመ ከመ መሰንቆ ሐዋዝ ጣዕመ ቃሉ፡፡ ወከመ ስቴ ወይን ያስተፌሥሕ ማኅሌተ ንባቡ፡፡ አሐዱ ውእቱ እምእደው ሥሉሳን ዘኢተረስዐት ሎቱ ጽድቁ ወትቀውም ምስለ ውሉዱ ለዝሉፉ፡፡

፲፫ የቃሉ ጣዕም እንዳማረ መሰንቆ ነው፡፡ የንባቡም ምስጋና እንደ ወይን መጠጥ ደስ ያሰኛል፡፡ ከተሳሉ አበውም አንዱ እርሱ ነው፡፡ ያልተረሳችበት ጽድቁ ለዘለዓለሙ ከልጆቹ ጋር ጸንታ ትኖራለች፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፬ ሠናይ ርስቱ በላዕለ ውሉዱ ወኀደገ ስመ ዘይትናገሩ ቦቱ፡፡ ተናገሩ ሕዝብ በጥበቢሁ፡፡ ጊዮርጊስ ካህን ወንጌላዊ ዘይሜህር ግጻዌ ሥላሴ ዘእንበለ ሌልዮ፡፡ ተዋሕዶ መለኮት ዘእንበለ ቶስሖ፡፡

፲፬ ርስቱ በልጆቹ ላይ መልካም ነው፡፡ የሚናገሩበት ስምን ተወ፤ ሕዝቡም በጥበቡ ተናገሩ፡፡ ወንጌላዊ ካህን ጊዮርጊስ ያለመለያየት የሥላሴን ሦስትነት ያለ መጨመርም የመለኮትን አንድነት የሚናገር ነው፡፡

፲፭ ቀዋሚ ወተዛዋዒ በማኅሌተ ድንግል እንተ ወለደቶ ለባሕርየ መለኮት በጠባይዐ ሰብእ፡፡ ጊዮርጊስ መስተባዕስ ምስለ ዓላውያን ዘይመትር በሰይፈ ቃሉ ርእሶሙ ለከሐድያን፡፡

፲፭ በሰው ባሕርይ መለኮትን በወለደች በድንግል ምስጋና /ማኅሌት/ የሚቆምና የሚያመሰግን ጊዮርጊስ ከዓላውያን ጋር የሚከራከር የከሐድያንንም ራስ በቃሉ ሰይፍ የሚቆርጥ ነው፡፡

፲፮ ጊዮርጊስ መጋቤ ኦሪት ከመ ሙሴ ወራእየ ኅቡኣት ከመ ሄኖክ፡፡ ቀናዒ ለሕገ አምላኩ ከመ ኤልያስ ወልዑለ ቃል ከመ ኢሳይያስ፡፡

፲፮ ጊዮርጊስ እንደ ሙሴ የኦሪት አስተማሪ፣ እንደ ሄኖክም የተሰወረውን የሚያይ፣ እንደ ኤልያስ ለአምላኩ ሕግ የሚቀና፣ እንደ ኢሳይያስም ቃሉ ከፍ ያለ ነው፡፡

፲፯ ዝንቱ ውእቱ ዳዊት ሐዲስ ዘቀተሎ ለጎልያድ ዘውእቱ ዲያብሎስ ወእሊአሁ ዝንቱ ውእቱ ጴጥሮስ ዘተወፈየ መራኁተ መንግሥተ ሰማያት ዝንቱ ውእቱ ጳውሎስ ልሳነ ዕፍረት ዘሰበከ እም ኢየሩሳሌም እስከ እልዋሪቆን ወበህየ ነጻራ ለእመ ብርሃን፡፡

፲፯ ጎልያድን የገደለው አዲሱ ዳዊት ይህ ነው፡፡ በጎልያድም የተመሰሉ ዲያብሎስና ሠራዊቱ ናቸው፡፡ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎች የተቀበለ ጴጥሮስ ይህ ነው፡፡ ከኢየሩሳሌም እስከ እልዋሪቆን ያስተማረ ልሳነ ዕፍረት ጳውሎስ ይህ ነው፡፡ በዚያም የብርሃን እናት እመቤታችንን አያት፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፰ ጽጉብ እም ጸቃውዐ ትንቢቶሙ ለነቢያት ወእም ዘትረ ትምህርቶሙ ለሐዋርያት፡፡ ጊዮርጊስ ቀላየ አእምሮ ወነቅዐ ኀሊና ጽድቅ ፈልፈለ ምክር ወውሒዘ ምስጢር፡፡ ቅሡም በፄወ መለኮት ወኅቱም በቅብዐ ሃይማኖት፡፡ ማኅሌታይ ከመ አሳፍ ወረአዬ ኅቡኣት ከመ ዮሴፍ ክቡደ ልቡና ከመ ዕዝራ ሱቱኤል ወመበይን ከመ ዳንኤል፡፡

፲፰ ከነቢያት የትንቢት ወለላ የጠገበ፣ ከሐዋርያትም የትምህርታቸው ምንጭ የጠጣ ነው፡፡ ጊዮርጊስ የዕውቀት ባሕር፣ የበጎ ኅሊና ምንጭ የምክር መገኛ፣ የምስጢርም ወንዝ ነው፡፡ በመለኮት ጨውነት የጣፈጠ በሃይማኖትም ቅባት የታተመ ነው፡፡ እንደ አሳፍ አመስጋኝ፣ እንደ ዮሴፍም የተሰውረውን የሚያይ፣ እንደ ዕዝራ ሱቱኤልም ልቡናው የጸና እንደ ዳንኤልም ፈራጅ ነው፡፡

፲፱ ዝንቱ ፀሐይ ብሩህ ዘያበርህ በጠፈረ ሰማዩ ለእግዚአብሔር እንተ ይእቲ ቤተ ክርስቲያኑ ቅድስት ከመ ወርኀ ምሉእ ዘዕለተ ገሀህ ወከመ ኮከብ ብሩህ በውስተ ደመና ከማሁ አሰርገዋ ለቤተ ክርስቲያን በዋካ ትምህርቱ፡፡

፲፱ ይህ ብሩህ ፀሐይ በእግዚአብሔር ሰማይ በጠፈር የሚያበራ ነው፡፡ ይችም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ በብርሃን ቀን እንደ ምሉዕ ጨረቃ በደመና ውስጥ እንደሚያበራ ኮከብም እንዲሁ ቤተ ክርስቲያንን በትምህርቱ ብርሃን አስጌጣት፡፡

፳ ዕፀ ገነት ምዑዝ ዘዘዚአሁ ጽጌሁ ወዘዘዚአሁ አስካለ ፍሬሁ አፈወ ርኄ ምዑዝ ዘይትዐቀብ በቀርነ ቅብዕ ዘጽዮን፡፡

፳ መዓዛውና ፍሬው ልዩ ልዩ የሚሆን የገነት ተክል ነው፡፡ በጽዮን የሽቱ መያዣ የሚጠበቅ ርኄ የተባለ ሽቱ ነው፡፡

፳፩ ዐምደ ወርቅ ጽሩይ ዘይቀውም ኀበ መከየደ ብሩር፡፡ እብነ ሕንደኬ ጽዱል ዘእጹብ ሥነ ሞገሱ ወመንክር ኅበሪሁ፡፡

፳፩ ከብር መድረክ ላይ የቆመ ንጹሕ የወርቅ ዐምድ ነው፡፡ የመልኩ ደም ግባት የሚያስደንቅ ኅብሩም ድንቅ የሚሆን የሕንድ ድንጋይ ነው፡፡

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፳፪ እብነ ባሕርይ ዘሰሩር ዲበ እብነ ሰንፔር፡፡ እብነ ጳዝዮን ዘአስተጣግዕዎ በወርቅ ጽሩይ ዘእምነፓሩሔም፡፡ ዕንቁ ሶፎር ወዕንቁ ሶም ዘአሰርገዋ ለምድረ ኢትዮጵያ በብርሃነ ትምህርቱ፡፡

፳፪ ሰንፔር በተባለ ዕንቁ ላይ የተሠራ የዕንቁ ድንጋይ ነው፡፡ በጠራ ወርቅ የተጠጋ እብነ ጳዝዮን ነው፡፡ በትምህርቱ ብርሃንነት የኢትዮጵያን ምድር ያስጌጣት ከፖሩሔም የተገኘ ሶፎርና ሶም የተባለ ዕንቁ ነው፡፡

፳፫ ወአስተመክሓ ለቤተ ክርስቲያን በጸዳለ ቃሉ ከመ ባዝግና ወርቅ ዘክሳደ መርዓት ወከመ አክሊለ ባሕርይ ዘዲበ ርእሰ መርዓዊ ከመ ጌራ ወርቅ ዘዲበ ርእሰ ነገሥት ወከመ ኅልቀተ ብሩር ዘውስተ አፃብዒሆሙ ለመሳፍንተ ምድር፡፡

፳፫ በሙሽራዋ አንገት ላይ እንዳለ ዝርግፍ ወርቅና በሙሽራው ራስ ላይ እንዳለ የዕንቁ አክሊል ቤተ ክርስቲያንን በቃሉ ብርሃንነት አስመካት በነገሥታት ራስ ላይ እንዳለ እንደ ወርቅ አክሊልና በገዥዎች ጣት ላይ እንዳለ የብር ቀለበት ነው፡፡

፳፬ አወፈያ ለቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ድርሳናቲሁ፡፡ ቀሰማ እመጻሕፍተ ሕጉ ለሙሴ ወእምቃለ ትንቢቶሙ ለነቢያት፡፡

፳፬ ለቤተ ክርስቲያን የድርሳኑን መጽሐፍ ሰጣት፤ በሙሴ የሕግ መጻሕፍትና በነቢያት ትንቢት አጣፈጣት፡፡

፳፭ አስተጻንዓ በትእዛዘ ትምህርቶሙ ለሐዋርያት ወበማኅሌተ ውዳሴሃ ለድንግል፡፡ አስተፍሥሓ በዜና ዕበዮሙ ለትጉሃን ወበነገረ ገድሎሙ ለሰማዕታት መዋዕያን ወመነኮሳት ገዳማውያን፡፡

፳፭ በሐዋርያት የትምህርታቸው ትእዛዝና በድንግል የምስጋና ማኅሌት አጸናት፡፡ በትጉሃን የታላቅነት ዜና፣ በአሸናፊዎች ሰማዕታትና በገዳማውያን መነኮሳት ገድልም አስደሰታት፡፡

፳፮ ጊዮርጊስ መሰንቆ ማኅሌት ዘቤተ ከብካብ ወቀርነ ስብሐት ዘቤተ በዓል፡፡ ወአርጋኖነ ማኅሌት ወፍሥሐ ሀገር ዘይደምፅ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር በእስትንፋሰ አፉሁ፡፡

፳፮ ጊዮርጊስ በሠርግ ቤት እንዳለ የምስጋና መሰንቆ፣ በበዓል ጊዜ እንደሚሰማ መለከትና በገናም ነው፡፡ በአፉ እስትንፋስ በደብረ እግዚአብሔር የሚሰማ የሀገር ደስታም ነው፡፡

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፺፯ ጊዮርጊስ ሐረሳዊ ጠቢብ ዘራዔ ሕግ ውስተ ገራህተ አልባብ ወተመከዐበ ፍሬ ቃላቲሁ ህየንተ አሐዱ ፻ ወ ፷ ወ ፴::

፺፯ ጊዮርጊስ በልቡና እርሻ ላይ ሕግን የሚዘራ ጥበበኛ ገበሬ ነው:: የቃሉም ፍሬ ስለ አንዱ ፈንታ ሠለሳ፣ ስድሳ መቶ እጥፍ አፈራለት::

፺፰ ወይእዜኒ ምንተ እንዕድ ዘእግዚአብሔር ንዕደ:: ጸሎቱ ወበረከቱ ወኀይለ ሃይማኖቱ ወላሕየ ፍቅረ አምላኩ ዘኀድርት ውስተ ልቡ ያዕርፍ ላዕሌነ እስመ ተአምነ በጸሎቱ ለዓለመ ዓለም:: አሜን::

፺፰ አሁንም እግዚአብሔር ያመሰገነውን ምን አመሰግናለሁ! ጸሎቱና በረከቱ፣ የሃይማኖቱ ኀይል፣ በልቡ አድራ ያለች የአምላኩ የፍቅር ወላፈን፣ በጸሎቱ ስለታመንን በእኛ ላይ ትኑር ለዘለዓለሙ አሜን::

፺፱ ይደልወነኬ አ አኀው ክርስቶሳውያን ከመ እንግርክሙ ዘከመ እፎ ኮነ ልደቱ:: ወኮነ አቡሁ እምዘመደ ክቡራን ዘስሙ ሕዝበ ጽዮን ጠቢብ ወማእምረ መጻሕፍት:: ወእሙኒ እምሥዩማነ ወለቃ ወስማ እምነ ጽዮን::

፺፱ ክርስቶሳውያን ወንድሞች ሆይ ልደቱ እንዴት እንደሆነ እንነግራችሁ ዘንድ ይገባል:: አባቱ ከተከበሩ ወገኖች ወገን የሆነ ስሙ ሕዝበ ጽዮን የተባለ መጻሕፍትን የሚያውቅ ነው:: እናቱም ከወለቃ ሹማምንት ወገን የሆነች ስሟ እምነ ጽዮን ነው::

፻ ወእምኔሆሙ ተወልደ ኮከብ ብሩህ በሀገር እንተ ስማ ሰግላ:: ወሐፀነቶ እሙ በፈሪሀ እግዚአብሔር ወጸንዐ በጥበብ ወኀይል ወየሐውር ምስሌሁ መንፈሰ እግዚአብሔር::

፻ ሸግላ በተባለች ሀገር የሚያበራ ኮከብ ከእነርሱ ተወለደ:: እናቱም እግዚአብሔርን በመፍራት አሳደገችው፤ በጥበብና በኀይልም ጸና፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ ከእርሱ ጋር ይሔድ ነበር::

፻፩ በከመ ይቤ መጽሐፈ መሳፍንት ወወለደት ይእቲ ብእሲት ወልደ ወሰመየቶ ሶምሶን:: ወባረኮ እግዚአብሔር ለውእቱ ሕፃን ወየሐውር መንፈሰ እግዚአብሔር ምስሌሁ ውስተ ትዕይንተ ዳን ማእከለ ስራሕ ወእስታሔል::

፻፩ በመጽሐፈ መሳፍንት እንደተነገረ "ያችም ሴት ልጅ ወለደች ስሙንም ሶምሶን ብላ ጠራችው:: ያንም ሕፃን እግዚአብሔር ባረከው የእግዚአብሔርም መንፈስ በስራሕና በእስታሔል መካከል ባለው በዳን ሰፈር ከእርሱ ጋር ይሔድ ነበር::" መሳ.፲፫፥፳፬

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፴፪ | ወከማሁ ባረኮ እግዚአብሔር ለዝንቱ ሕፃን ወሰመይዎ ስሞ ጊዮርጊስ በአማን በአማኅፅኖተ ሰማዕት ኅሩይ ጊዮርጊስ፡፡ አኮ ከመ ደቂቅ ዘይትሐወከ ወአኮ ምስለ ማሐዛኒሁ ዘይዛዋዕ አላ ይተሉ ዐሠረ ጠቢባን፡፡ | ፴፪ | እንደዚሁም እግዚአብሔር ይህን ሕፃን ባረከው የተመረጠ ሰማዕት ጊዮርጊስን በመማፀን ስሙን ጊዮርጊስ ብለው ጠሩት /ሰየሙት/፤ እንደ ልጆችም የሚታወክ አይደለም እንደ ጓደኞቹም አይጫወትም ነበር፤ የመምህራንን መንገድ ይከተል ነበር እንጂ፡፡ |
| ፴፫ | ወይገይሥ ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወአቡሁኒ መፍቀሬ እግዚአብሔር እምትልቁ ካህናት ደብተራ ዘውሣጤ ዐፀደ ቤተ ንጉሥ ወሐፀኖ ለወልዱ ሠናየ ሕፅነተ፡፡ ወሶበ ልህቀ ሕቀ ወሰዶ ኀበ ጳጳስ ወአሜሞ ዲያቆነ፡፡ | ፴፫ | ወደ ቤተ ክርስቲያንም ይሔድ ነበር፤ አባቱም እግዚአብሔርን የሚወድድ ቁጥሩ በቤተ መንግሥት በድንኳን ካሉ ካህናት ጋር ነበር፤ ልጁን በጥሩ አስተዳደግ አሳደገው፡፡ ጥቂት ባደገም ጊዜ ወደ ጳጳስ ወስዶ ዲቁናንም አሾመው፡፡ |
| ፴፬ | ወእምድኅረዝ ፈነዎ ውስተ መርጡለ እስጢፋኖስ እንተ ሀለወት በሐይቀ ባሕር በመዋዕለ ዳዊት ንጉሥ ወበሢመተ ሠረቀ ብርሃን ዓቃቤ ሰዓት ዘሐይቅ፡፡ | ፴፬ | ከዚህም በኋላ በንጉሥ ዳዊት ዘመንና የሐይቅ ዐቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃንም በተሾመበት ዘመን በሐይቅ ባሕር ወደ ምትገኘ የእስጢፋኖስ ገዳም ላከው፡፡ |
| ፴፭ | እስመ ካህናት ይእቲ ደሴት ጠቢባን ጥቀ ወማእምራነ መጻሕፍት ለአንብቦ ወለፈክሮ ወኄራን እሙንቱ፡፡ ወበእንተዝ ፈነዎ ኀቤሆሙ ወወሀብዎ ለመምህር ከመ ይምሀሮ፡፡ | ፴፭ | የዚያችም ደሴት ካህናት እጅግ ጠቢባን ለማንበብና ለመተርጐም መጻሕፍትን የሚያውቁ ደጋጎች ነበሩ፡፡ ስለዚህ ወደ እነርሱ ላከው፡፡ ያስተምረውም ዘንድ ለመምህር ሰጡት፡፡ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፴፮ ጊዮርጊስሰ ኮነ ጕንዱየ ለአጽንዖ ወኢተበውሆ ቃለ እግዚአብሔር፡፡ አኮ በእንተ ኀጢአቱ ወኢበስዒነ መከፈልት ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ ያስተርኢ ግብረ እግዚአብሔር ወስብሐቲሁ ላዕሌሁ፡፡ እስመ እንበለ መከራ ኢይትወሀብ ጸጋ ወእንበለ ተፈትኖ ኢይከውን አፈድፍዶ፡፡

፴፮ ጊዮርጊስ ግን ለማጥናት ዘገየ የእግዚአብሔር ቃልም አልገባውም፤ ይህም ስለ ኀጢአቱ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ሥራና ጌትነቱ በእርሱ ላይ ይገለጥ ዘንድ ነው እንጂ፡፡ ጸጋ ያለመከራ አይሰጥምና ያለመፈተንም ማብዛት አይቻልም፡፡

፴፯ በከመ ይቤ እግዚእነ ሶበ ተስእልዎ አርዳኢሁ ወይቤልዎ በኀጢአተ መኑ ተወልደ ዝንቱ ዕዉር በዘርእስኑ ወሚመ በአዝማዲሁ ወይቤሎሙ ኢውእቱ አበሰ ወኢአዝማዲሁ ዳእሙ ከመ ያስተርኢ ግብረ እግዚአብሔር በላዕሌሁ፡፡

፴፯ ደቀ መዛሙርቱ በጠየቁት ጊዜ ጌታችን እንደተናገረ፡፡ ይህ ዕዉር በማን ኀጢአት ተወለደ በራሱ ነውን ወይስ በወላጆቹ አሉት፡፡ እርሱ አልበደለም ወላጆቹም አልበደሉም የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ላይ ይገለጥ ዘንድ ነው እንጂ አላቸው፡፡ ዮሐ. ፱፥፩

፴፰ ሐዋርያትኒ ነበሩ በሕዳጥ አእምሮ እስከ አመ ወረደ ላዕሌሆሙ መንፈስ ቅዱስ፡፡ በከመ ጽሑፍ ዘይብል እስመ ዓዲ ኢየአምሩ ዘውስተ መጻሕፍት፡፡ ወከማሁ ጊዮርጊስ ነበረ በውኁድ አእምሮ ቃለ መጻሕፍት፡፡

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

፴፰ ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስ እስኪወርድላቸው ድረስ በትንሽ ዕውቀት ነበሩ፡፡ በመጻሕፍት ያለውን ገና ዐላወቁምና፡፡ ተብሎ እንደተጻፈ እንዲሁ ጊዮርጊስ የመጻሕፍትን ቃል በመጠኑ በማወቅ /ኖረ/፡፡

ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

## ምዕራፍ ፪

፩ ወሶበ ርእዮሙ ለካልኣኒሁ እንዘ ይቀድምዎ በትምህርት ኀዘነ ጥቀ። ወበአሐቲ እመዋዕል ሖረ ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወሰምዖ ለመድኀኒነ እንዘ ይብል በውስተ ወንጌል ኵሎ ዘሰአልክሙ እንዘ ትትአመኑ ትነሥኡ ወትረክቡ።

ማቴ. ፳፩፥፳፪

፪ ወዓዲ ሰምዖሙ ለአርዳኢሁ እንዘ ይብሉ ወኢትኩኑ ኑፋቃነ ሶበ ትጼልዩ ወኀሊ ዘተመነይከ ወይፌጽም ለከ። ወዓዲ ሰምዐ እምቃለ ኪዳን እንዘ ይብል ወይሰምዐነ እለ ዘእንበለ ኑፋቄ ንጼውዖ።

፫ ወምስለዝኒ አዘከሮ መንፈስ ቅዱስ ቃለ ሰሎሞን ዘይቤ ዝጥበብ ወአእምሮ እም አይቴ ሰከይኩ ኀበ እግዚአብሔር ወሰአልክዎ ወእቤ እምኵሉ ልብየ አምላከ አበው ወእግዚአ ለምሕረት ዘገበርከ ኵሎ በቃልከ ወበጥበብከ ፈጠርከ ሰብአ። ሀበኒ እንተ ኀበ መናብርቲከ ትነብብ ጥበበ ወኢትመንነኒ እምጽድቅከ እስመ አነ ገብርከ ወልደ አመትከ።

## ምዕራፍ ሁለት

፩ ሌሎች ጓደኞቹም በትምህርት ሲበልጡት /ሲቀድሙት/ ባየ ጊዜ እጅግ አዘነ። ከዕለታትም አንድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔደ። መድኃኒታችንም በወንጌል አምናችሁ የምትለምኑትን ሁሉ ታገኛላችሁ ትቀበላላችሁም። ያለውን ሰማ።

ማቴ. ፳፩፥፳፪

፪ ሁለተኛም ሐዋርያት በምትጸልዩ ጊዜ ተጠራጣሪዎች አትሁኑ የተመኘኸውን ለምን ይፈጽምልሃልም ሲሉ ሰማቸው። ዳግመኛም ከኪዳን ቃል ያለጥርጥር የምንለምነውን ይሰማናል ሲል ሰማ።

፫ ከዚህም ጋር መንፈስ ቅዱስ ይህ ጥበብና ዕውቀት ከወዴት ነው? ያለውን የሰሎሞን ቃል አሳሰበው፤ ወደ እግዚአብሔር አመለከትሁ ለመንኹትም፤ በፍጹም ልቤም ሁሉን በቃልህ የፈጠርህ በጥበብህም ሰውን የፈጠርህ የአባቶቻችን አምላክ የምሕረት ጌታ በጌትነትህ የምትኖር ጥበብን ስጠኝ። ከእውነትህም የተነሣ አትናቀኝ፤ እኔ አገልጋይህ የአገልጋይህም ልጅ ነኝና አልሁ።

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፬ ወእምዝ አኀዘ ይስአል ኀበ እግዚአብሔር እማዕምቀ ልቡ በከዊወ አንብዕ ቅድመ ሥዕላ ለእግዝእትነ ማርያም ለዘከሮ ስማ ሰጊድ፡፡ በጾም ጽፉቅ ወበጸሎት ምውቅ ወሰጊድ ከመ መንኰራኵር እንዘ ይብል ከመዝ፤

፬ ከዚያም ለስም አጠራሯ ክብር ይግባትና በእመቤታችን ሥዕል ፊት እንባንም በማፍሰስ፣ በጾምና በጸሎት፣ እንደመንኰራኩርም በስግደት ከልቡ እንዲህ እያለ ወደ እግዚአብሔር ይለምን ጀምር፡፡

፭ ክሥት ሊተ እግዚኦ ኅቡኣተ ጥበብከ ወመንፈሰ ቅዱሰ ወወሀበኒ መንፈሰ ልቡና ወምክር መንፈሰ ጥዒና ወኀይል ወፈሪሀ እግዚአብሔር፡፡ ክሥት ከናፍርየ ወአፉየ የይድኣ ስብሐቲከ ወምላእ አፉየ ስብሐቲከ ከመ እሰብሕ አኰቴተከ፡፡
ኢሳ. ፲፩፥፪ መዝ. ፶፥፲፭

፭ አቤቱ የተሰወረ ጥበብህን ግለጽልኝ የማስተዋልና የምክር መንፈስ፣ የጤናና የኃይል መንፈስ እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ የሆነ መንፈስ ቅዱስን ስጠኝ፡፡ ምስጋናህን ይናገሩ ዘንድ አፌንና ከንፈሮቼን ግለጥ፤ ጌትነትህንም አመሰግን ዘንድ ምስጋናህን በአፌ ምላ፡፡
ኢሳ. ፲፩፥፪ መዝ. ፶፥፲፭

፮ አብርሆን ለአዕይንተ ልብየ ለአእምሮ ቃላቲከ ወለጠይቆ ኅቡኣቲከ፡፡ ወደይ ውስተ አፉየ ስብሐቲከ ከናፍርየ እንዘ ፍሡሓት ይሴብሓ ለስምከ፡፡
መዝ. ፷፪፥፭

፮ ቃልህን ለማወቅ ምስጢርህንም ለመረዳት የልቡናዬን ዐይኖች አብራልኝ፤ ምስጋናህንም በአፌ ጨምር ከንፈሮቼ ደስ ብሏቸው ስምህን ያመሰግናሉ፡፡መዝ. ፷፪፥፭

፯ ፈጽም ሊተ እግዚኦ ኀሢሦትየ ዘውእቱ ኀሢሦተ ቃለ እግዚአብሔር ከመ እኩን ለባዌ ወማእምረ ለአንብቦ ወለተርጕሞ ቃለ መጻሕፍት፡፡ ወረስየኒ ቅሡመ በጼወ መለኮት በዘዚአከ ኂሩት፡፡

፯ አቤቱ የምሻውን /የምፈልገውን/ ፈጽምልኝ፡፡ ይኸውም የእግዚአብሔርን ቃል መሻት ነው፡፡ ለማንበብና ለመተርጎም ዐዋቂና አስተዋይ እሆን ዘንድ በቸርነትህም በመለኮትህ ጨውየጣፈጥሁ አድርገኝ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፰ ወካዕበ ጸለየ ጸሎተ ዘበድርሳን በከመ ሰምዐ እም ትምህርተ መፈክራን ወእኮ እምአእምሮ መጻሕፍት፡፡ ወይቤ ተወከፈኒ ጸሎትየ ወኢትትሐየየኒ ስእለትየ ዘተወከፍከ መሥዋዕተ አቤል የዋህ ወቍርባነ ኖኅ ጻድቅ፡፡

፰ ዳግኛም መጻሕፍትን ከማወቅ ሳይሆን ከተርጓሚዎች እንደሰማ በድርሳን ያለውን ጸሎት ጸለየ፡፡ የየዋህ አቤልን መሥዋዕትና የጻድቁ ኖኅን ቍርባን የተቀበልህ ሆይ ጸሎቴን ተቀበል ልመናዬንም ቸል አትበል አለ፡፡

፱ ስምዐኒ እግዚኦ ዘሰማዕከ ጸሎቶሙ ወተወከፍከ ቍርባኖሙ ለአበወ ዓለም ዘውእቶሙ አብርሃም፣ ይስሐቅ ወያዕቆብ

፱ አቤቱ የዓለም አባቶች ቍርባናቸውን የተቀበልህ ልመናቸውንም የሰማህ ስማኝ፡፡ እሊህም አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ ናቸው፡፡

፲ ስምዐኒ እግዚኦ ዘሰማዕኮ ለሙሴ በእንተ ሕዝብ ወለአሮን በእንተ ብድብድ ወለኢያሱ ወልደ ነዌ አመ ዐቀመ ፀሐየ በገባዖን ወለወርኀ በቈላተ ኤሎን፡፡ ወለዳዊት በዐውደ ኦርና ኢያቢሳዊ ለሰሎሞን በገባኦን፤ ዘፀ. ፴፪፥፴፪ ዘኍ. ፲፮፥፵፯ ኢያ. ፲፥፲፪ ፪ሳሙ. ፳፬፥፲፯ ፩ነገ. ፫፥፬

፲ አቤቱ ሙሴን ስለሕዝቡ አሮንንም ስለመቅሠፍት የነዌ ልጅ ኢያሱንም ፀሐይን በገባዖን ጨረቃንም በኤሎን ባቆመ ጊዜ ዳዊትንም በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ ሰሎሞንንም በገባዖን በጸለየ ጊዜ የሰማኸው ስማኝ፡፡ ዘፀ. ፴፪፥፴፪ ዘኍ. ፲፮፥፵፯ ኢያ. ፲፥፲፪ ፪ሳሙ. ፳፬፥፲፯ ፩ነገ. ፫፥፬

፲፩ ወለኤልያስ በደብረ ቀርሜሎስ ወለኤልሳዕ በኀበ አንቅዕት ወለሕዝቅያስ በእንተ ደዌሁ ወለዳንኤል በውስተ ግበ አናብስት ወለሠለስቱ ደቂቅ በውስተ እቶነ እሳት፡፡ ወለሐና በደብተራ ስምዕ፡፡

፲፩ ኤልያስን በቀርሜሎስ ተራራ፣ ኤልሳዕንም በውኃ ምንጮች፣ ሕዝቅያስንም ስለ ደዌው፣ ዳንኤልንም በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ፣ ሦስቱ ሕፃናትንም በእሳት ምድጃ፣ ሐናንም በምስክሩ ድንኳን የሰማኻት ስማኝ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፪ ወከማሁ ተከወፍ ጸሎትየ ወስእለትየ ወበከመ ሰማዕከ ጸሎቶሙ ወስእለቶሙ ለአበዊነ ሐዋርያት አመ ወደዩ እደዊሆሙ ላዕለ ድዉያን ከመ ይፈውስዎሙ ወለምዉታን ከመ ያንሥእዎሙ፡፡

፲፪ ሕሙማንን ይፈውሷቸው ሙታንንም ያስነሧቸው ዘንድ በሕሙማን ላይ እጃቸውን በጫኑ ጊዜ የአባቶቻችን ሐዋርያት ጸሎታቸውንና ልመናቸውን እንደሰማሃቸው ጸሎቴንና ልመናዬን እንዲሁ ስማ፡፡

፲፫ ወለሰማዕታት መዋዕያን አመ ቆሙ ቅድመ ነገሥት ኃያላን በዕለተ ኲነኔ ወምንዳቤ፡፡ ወለመነኮሳት ገዳማውያን ሶበ መጽአ ላዕሌሆሙ ተፈትኖ መከራ እምሕዝበ መናፍስተ ርኩሳን፡፡

፲፫ በፍርድና በመከራ ቀን በኃያላን ነገሥታት ፊት ድል የሚነሱ ሰማዕታትን ርኩሳን መናፍስት ካደሩባቸው ሰዎች የተነሣ የመከራ ፈተና በመጣባቸው ጊዜ ገዳማውያን መነኮሳትን የሰማሃቸው ስማኝ፡፡

፲፬ ወበከመ ተወከፍከ ጸሎቶሙ ወመሥዋዕቶሙ ለኲሎሙ ጻድቃን በበዘመኖሙ፡፡ ከማሁ ተወከፍ ጸሎትየ ወስእለትየ ሊተ ለኃጥእ በዘዚአከ ኂሩት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፲፬ አቤቱ በየዘመናቸው የሁሉንም ጻድቃን ጸሎታቸንና ልመናቸውን እንደተቀበልህ የእኔን የኀጢአተኛውን ጸሎትና ልመና በቸርነትህ ተቀበልልኝ፡፡ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

፲፭ ወምስለ ዝኲሉ ይውሕዝ አንብዑ ወያንጸፈጽፍ ሐፉ፡፡ ከመ ደም እምዋዕየ ጸሎት ወእምፍልሐተ ሃይማኖት ዘውስተ ልቡ፡፡ ወበጊዜሃ ቆመት ጸሎቱ ቅድመ ዕበየ ስብሐቲሆሙ ለኪሩቤል ወተቀድሐ ሞጻሕተ አንብዑ ውስተ ስያሆሙ ለሱራፌል፡፡

፲፭ ከዚህም ሁሉ ጋር በልቡናው ካለ ከሃይማኖቱ እሳትነትና ከጸሎቱ ማቃጠል የተነሣ እንባውና ወዙ እንደደም ይፈስስ ነበር፡፡ ያን ጊዜም ጸሎቱ ከኪሩቤል የምስጋና ባለሟልነት ጋር ቆመች የእንባውም መጠጥ በሱራፌል የመሠዊያ ጽዋ ተቀዳ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፭ ወናሁ ንግሥት ኵሉ ዓለም ተከሥተት ሎቱ በራእይ ወተናገረቶ እንዘ ትብል አንጽሕ ርእሰከ ወቀድስ ነፍሰከ ወአስተሐምም በትጋህ ዘእንበለ ንዋም ወወሀበቶ ዕድሜ በዘትገብእ ኀቤሁ ወተሰወረት እምኔሁ፡፡

፲፭ እነሆ የዓለም ሁሉ ንግሥት በራእይ ተገለጠችለት፡፡ እንዲህም ብላ ተናገረችው፡፡ ራስህን አንጻ ነፍስህንም ቀድስ ያለ እንቅልፍም በትጋት ተዘጋጅ፤ ወደ እርሱ የምትመለሰበትንም ቀጠሮ ሰጠችውና ከእርሱ ተሰወረች፡፡

፲፮ ወዘንተ ሰበ ትቤሎ ኮነ ሰቤሃ በመንፈስ ቅዱስ፡፡ ወተፈጸመ በላዕሌሁ ዘይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ወሪደከ ኰንን ሕዝበ ያንጽሑ ርእሶሙ ዮም ወጌሠመ፤ ወይሕጽቡ አልባሲሆሙ ወይጽንሑ ድልዋኒሆሙ እስከ ሣልሲት ዕለት ወይሪድ እግዚአብሔር ውስተ ደብረ ሲና፡፡ ዘፀ. ፲፱፥፲

፲፮ ይህንንም በነገረችው ጊዜ ያን ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ሆነ፤ እግዚአብሔርም ለሙሴ ወርደህ ሕዝቡን ሥራ / አስተዳድር/ ዛሬና ነገ ራሳቸውን ያንጹ፣ ልብሳቸውንም ይጠቡ እስከ ሦስት ቀንም ተዘጋጅተው ይጠብቁ እግዚአብሔርም ወደ ደብረ ሲና ይውረድ ያለው በእርሱ ተፈጸመ፡፡ ዘፀ. ፲፱፥፲

፲፯ ወከማሁ ለጊዮርጊስ አዘዘቶ እግዝእትነ ንግሥት ከመ ያንጽሕ ርእሶ ወወሀበቶ ዕድሜ በዘትገብእ ኀቤሁ ለፈጽሞ ስእለቱ ወለአጽምዖ ፈቃዱ፡፡

፲፯ እንዲሁም ንግሥት እመቤታችን ራሱን ያነጻ ዘንድ ጊዮርጊስን አዘዘችው፡፡ ልመናውን ለመፈጸም ፈቃዱንም ለማዳመጥ የምትመለስበትን ቀጠሮ ሰጠችው፡፡

፲፰ ወእምዝ በጽሐ ዕድሜ ዘወሀበቶ አመ ፲ወ፩ ለወርኀ አብ በሮማይስጥ ዘውእቱ አመ ፳ወ፮ ለወርኀ ነሐሴ በግእዝ፡፡ ወመጽአት ኀቤሁ እግዝእትነ ማርያም ድንግል በኵሉ ጊዜ ንግሥት ኵሉ ዓለም እሙ ለሕያው ፩ ዘእም ፫ ገጻት፡፡

፲፰ ከዚያም በሮማይስጥ የአብ ወር በተባለ ፲፩ኛው ቀን የቀጠረችው ቀጠሮ ደረሰ ይኸውም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ነሐሴ ፳፮ ቀን ነው፡፡ ሁል ጊዜ ድንግል የዓለም ሁሉ ንግሥት የምትሆን ከሦስቱ አካላት የአንዱ ሕያው አካል እናት እመቤታችን ማርያም ወደ እርሱ መጣች፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፳ ወምስሌሃ ኪሩቤል ወሱራፌል በበጾታሆሙ አርባብ ወረበዋት በድርገታቲሆሙ ወማኅበረ መላእክት በበሥርዐቶሙ እንዘ ይቄድስዋ ለውድስት ወይሴብሕዋ ለስብሕት፡፡

፳ ከእርሷም ጋር ኪሩቤልና ሱራፌል በየነገዳቸው፣ አርባብና ረበዋትም በአንድነታቸው፣ ማኅበረ መላእክትም በየሥርዐታቸው የተመሰገነች እርስዋን እየቀደሱ የከበረች እርሷዋን እያመሰገኑ ከእርስዋ ጋር ነበሩ፡፡

፳፩ ወሚካኤልኒ ሊቀ መላእክት ወውእቱ መልአከ ብሊት ይጸውር ውስተ እዴሁ በትረ ዘወርቅ በትእምርተ መስቀል ወይቀውም በየማና፡፡

፳፩ የመላእክት አለቃና መጋቤ ብሉይ ሚካኤልም የመስቀል ምልክት ያለበት የወርቅ ዘንግ በእጁ ይዞ በቀኝዋ ቁሞ ነበር፡፡

፳፪ ገብርኤልኒ አብሣሬ ትስብእት ዘተአመነ ላዕለ ምስጢራተ እግዚእነ ክርስቶስ ይቀውም በጸጋማ እንዘ ይጸውር ውስተ እዴሁ ጽዋዐ ምሉአ ዘኅብሩ ይመስል እሳተ፡፡

፳፪ በጌታችን ክርስቶስ ምስጢራት የታመነ የአምላክን ሰው መሆን ያበሠረ ገብርኤልም መልኩ እሳት የሚመስል ጽዋን በእጁ ይዞ በስተግራዋ ቁሞ ነበር፡፡

፳፫ ወጊዮርጊስኒ ሕፃን ሶበ ርእየ ለንግሥተ ኵሉ ዓለም ምስለ ሠራዊተ ኀይላት ወድቀ ውስተ ምድር በገጹ ወኮነ ከመ ምውት፡፡

፳፫ ሕፃኑ ጊዮርጊስም የዓለም ሁሉ ንግሥትን ከኀይላት ሠራዊት ጋር ባያት ጊዜ በግንባሩ ወደ ምድር ወደቀ እንደ ሞተም ሰው ሆነ፡፡

፳፬ ወበጊዜሃ ገሠሠቶ እግዝእትነ መስተ ምሕርት ወተንሥአ ሶቤሃ ወገብአ ልቡ ወኀሊናሁ ወቆመ በእገሪሁ፡፡

፳፬ ያን ጊዜም የምትራራ እመቤታችን ዳሰሰችው፣ ተነሣ፣ ኅሊናው ተመለሰለት በእግሩም ቆመ፡፡

፳፭ ወጸውዐቶ በስሙ እንዘ ትብል ጊዮርጊስ ኅሩይየ ወፍቁረ ወልድየ ንሣእ ስተይ ዘንተ ጽዋዐ ጽሩየ ዘተቀድሐ እምባሕረ መለኮት ዘውሕዘ እምፈለገ አእምሮ ወፈልፈለ እምነቅዐ ጥበብ፡፡

፳፭ የመረጥሁህና የልጄ ወዳጅ ጊዮርጊስ ብላ በስሙ ጠራችው፡፡ ከዕውቀት ወንዝ የመጣና ከጥበብ ምንጭ የተገኘ ከመለኮት ባሕር የተቀዳ ይህን ንጹሕ ጽዋ /እንካ/ ንሣ ጠጣ፡፡

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፷፮ ወመጠወቶ በየማነ እዴሃ እግዝእትነ ንግሥተ ኲሉ ዓለም ለዘክሮተ ስማ ሰጊድ፡፡ ወእምቅድመ ይስትዮ ነጸረ ኀበ ውስጡ ወረከበ መጽሐፈ ዘይብል ዘሰትዮ ለዝንቱ ጽዋዕ ኢይትኰነን እስመ ተቀድሐ እምቀላየ ሕይወት፡፡

፷፮ ለስም አጠራርዋ ሰጊድ ይሁንና የዓለም ሁሉ ንግሥት እመቤታችን ያን ጊዜ በቀኝ እጅዋ ሰጠችው፡፡ ሳይጠጣውም ወደ ውስጡ ተመለከተ ይህን ጽዋ የጠጣ አይኰነንም ከሕይወት ባሕር ተቀድቶአልና የሚል መጽሐፍን አገኘ፡፡

፷፯ ወሶቤሃ ሰትየ ብፁዕ ጊዮርጊስ አፈ በረከት ውእተ ስቴ መንፈሳዌ ወኮኖ ውስተ አፉሁ ዘይጥዕም እመዐር ወሶከር ወይኤድም እም ሐሊብ ወያጠልል እም ቅብዕ ወያስተፌሥሕ እምወይን፡፡

፷፯ ያን ጊዜም ብፁዕ አፈ በረከት ጊዮርጊስ ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጣ በአፉም ውስጥ ከመዐርና ከሦከር የሚጥምና ከወተትም የበለጠ የሚጣፍጥ ሆነው፤ ከቅባትም የሚያለመልም ከወይንም የሚያስደስት ሆነው፡፡

፷፰ ውእቱኬ ስቴ መንፈሳዊ ወስቴ ሰማያዊ ዘሰትይዎ አርድእት በጽርሐ ጽዮን ዘውእቱ ቤተ ዮሴፍ ወአልቦቱ ውሉጥ በዕለተ በዐለ፶፡፡ ውእቱኬ እሳት ነባቢ እሳት ማኅየዊ እሳት መለኮታዊ፡፡

፷፰ ይኸውም በዮሴፍ ቤት በጽርሐ ጽዮን ሐዋርያት የጠጡት መንፈሳዊና ሰማያዊ መጠጥ ነው በበዓለ ሃምሳ ከጠጡት ያልተለየ ነው፡፡ ይኸውም የሚናገር እሳት፣ የሚያድን እሳት፣ መለኮታዊ እሳት ነው፡፡

፷፱ በከመ ይቤ ሉቃስ ወንጌላዊ በመጽሐፈ ግብሮሙ ለሐዋርያት፡፡ ወአመ ተፈጸመ መዋዕለ ጳንጠቆስጤ እንዘ ሀለዉ ኅቡረ ኲሎሙ አሐተኔ መጽአ ግብተ እምሰማይ ድምፅ ከመ ድምፀ ነፋሰ አውሎ ወመልአ ኲሎ ቤተ ኀበ ሀለዉ ይነብሩ፡፡

፷፱ ወንጌላዊ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ እንደተናገረ፡፡ ፶ኛውም ቀን በተፈጸመ ጊዜ ሁሉም አንድነት በአንድ ቦታ ተሰብስበው ሳሉ ድንገትም ከሰማይ እንደአውሎ ነፋስ ድምፅ ያለ ድምፅ መጣ፣ የነበሩበትንም ቤት መላው፡፡

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፴ ወአስተርአይዎሙ ልሳናት እሳት ክፉላት ከመ እሳት ዘይትከፈል ወነበረ ዲቤሆሙ ወተመልኡ ኵሎሙ መንፈሰ ኀይል። ወአኀዙ ይንብቡ ዘዘዚአሆሙ በነገረ ኵሉ በሐውርት በከመ ወሀቦሙ መንፈስ ቅዱስ። ሎሙሰ አንበቦሙ በነገረ ኵሉ በሐውርት።ግብ.ሐዋ. ፪፥፬

፴ እየተጎረደ እንደሚሔድ እሳት የተከፋፈሉ የእሳት ላንቃዎች ታዩአቸው፤ በሁሉም ላይ አደረባቸው። ሁሉም ኀይል የሚሆናቸው መንፈስን ተመሉ። ይናገሩም ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እንደ አደላቸው መጠንም እየራሳቸው በአገሩ ሁሉ ቋንቋ ይናገሩ ጀመሩ። በአገሩም ሁሉ ቋንቋ አናገራቸው። ግብ.ሐዋ. ፪፥፬

፴፩ ወለአብኒ ጊዮርጊስ ከሠተ ሎቱ ኅቡኣተ ዘመጻሕፍት ቃለ ማኅሌት ወድርሳናት ወኵሎ ስብሐታተ። ዘአሰርገዋ ለቤተ ክርስቲያን።

፴፩ ለዚህም አባት ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን ያስጌጠበት የመጻሕፍትን ምስጢራት፣ የማኅሌትንና የድርሳናትን ቃል፣ ምስጋናዎችንም ሁሉ ገለጠለት።

፴፪ በከመ ይቤ ቅዱስ ጳውሎስ እስመ ዘዘዚአሁ ጸጋሁ በመንፈስ ቅዱስ ለለ፩ ወለኵሉ በበመክፈልቱ እንዘ እግዚእ ይረድእ ወለለ፩ ይሁቦ ገሀደ በከመ ይደልዎ ወበከመ ይበቍዖ።

፴፪ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረ ለየአንዳንዱ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ስጦታው ልዩ ልዩ ነውና ለሁሉም ጌታ እየረዳ እንደ ዕድሉ ይሰጠዋል። ለየአንዳንዱ እንደሚገባውና እንደሚጠቅመው በግልጥ ይሰጠዋል።

፴፫ ቦ ለዘይሁቦ ቃለ ጥበብ፤ ወቦ ለዘይሁቦ ቃለ አእምሮ በመንፈስ ቅዱስ፤ ቦ ለዘይሁቦ ሃይማኖተ በመንፈስ ቅዱስ፤ ወቦ ለዘይሁቦ አሶተ ዘያሐዩ ወቦ ለዘይሁቦ ምግባረ ረድኤት ወኀይል ወቦ ለዘይሁቦ ተነብዮ፤ ወቦ ለዘይሁቦ በመንፈስ ቅዱስ ያእምር ፍካሬ ዘነገረ ኵሉ በሐውርት በመንፈስ ቅዱስ። ወቦ ለዘይሁቦ ያእምር ፍካሬ ወለኵሉ ዝንቱ ውእቱ ፩ መንፈስ ቅዱስ ዘይረድኦሙ። ፩ቆሮ. ፲፪፥፯፡፲፩

፴፫ የጥበብ ቃል የሚሰጠው አለው፤ በመንፈስ ቅዱስም የዕውቀት ቃልን የሚሰጠው አለው። በመንፈስ ቅዱስ ሃይማኖትን የሚሰጠው አለው። ድዉይ የመፈወስ ሥልጣንንም የሚሰጠው አለው። የዕርዳታና የኀይል ሥራ የሚሰጠው አለው። ትንቢት መናገርን የሚሰጠው አለው፤ በመንፈስ ቅዱስም ትርጓሜን ማወቅ የሚሰጠው አለው። የየአገሩን ቋንቋ እንዲያውቅ ትርጓሜ የሚሰጠው አለው። በዚህም ሁሉ ሁሉንም የሚረዳቸው መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው። ፩ቆሮ. ፲፪፥፯፡፲፩

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፴፬ ወዘንተ ኵሎ ሀብታተ ወዘይመስሎ ተወፈየ አቡነ ጊዮርጊስ እምእደ እግዝእትነ ማርያም ንግሥተ ኵሉ ዓለም በፈቃደ ወልዳ ወበሥምረተ አቡሁ ወበሀብተ መንፈስ ቅዱስ፡፡

፴፬ ይህንና ይህን የመሰለውን ሀብት አባታችን ጊዮርጊስ የዓለም ሁሉ ንግሥት ከምትሆን ከእመቤታችን እጅ በልጅዋ ፈቃድ በአባቱም ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስም ፈቃድ ተቀበለ፡፡

፴፭ በመኑ አስተማስሎ ለአቡየ ጊዮርጊስ አፈ በረከት እምነ ቅዱሳን፡፡ አመ እሰምዮ ነቢየ እስመ ውእቱ ይትሌዓል እምነቢያት ወለእመ እቤሎ ሐጋጌ ሕግ እስመ ውእቱ ትሩፍ እምኔሆሙ፡፡

፴፭ አፈ በረከት አባቴ ጊዮርጊስን ከቅዱሳን በማን እመስለዋለሁ፣ ነቢይም ባልሁት ጊዜ ከነቢያት ይበልጣል፤ ሕግንም የሠራ ብለው ከእነርሱ እርሱ ይበልጣልና፡፡

፴፮ ዕዝራ ሱቱኤል ሰትየ ጽዋዐ በእደ ፩ እምሊቃነ መላእክት፡፡ በከመ ይቤ ለሊሁ ወበሳኒታ መጽአ ቃል ወጸውዐኒ ወይቤለኒ ዕዝራ ፍታሕ አፉከ ወስተይ ዘአሰትየከ፡፡

፴፮ ዕዝራ ሱቱኤል ከሊቃነ መላእክት በአንዱ እጅ ጽዋን ጠጣ፤ እርሱ ራሱ እንዳለ በማግሥቱም ቃል መጣ፤ ጠራኝም ዕዝራ አፍህን ግለጥ የማጠጣህንም ጠጣ አለኝ፡፡

፴፯ ወፈታሕኩ አፉየ ወአስተየኒ ጽዋዐ ዘምሉእ ማየ ወኅብሩ ይመስል እሳተ ወነሣእኩ ወሰተይኩ ወጐሥዐ ልብየ ጥቀ ጥበበ ወከብደ ዲበ እንግድዓ ልቡናየ ወመንፈስየ ተዐቅብ ወትዜከር፡፡ ወተከሥተ አፉየ ወኢተጋብአ እንከ፡፡

፴፯ አፌን ገለጥሁ /ከፈትሁ/ መልኩ እሳትን የሚመስል ውኃን የተመላ ጽዋንም አጠጣኝ፡፡ ተቀብልሁ ጠጣሁም፤ ልቤም ፈጽሞ ጥበብን ተናገረ፡፡ በልቤም ላይ በረታ፡፡ ነፍሴም ትጠብቀውና ታስበው ነበር፡፡ አፌም ተገለጠ /ተከፈተ/ ዝምም አላለም፡፡

፴፰ ወዝንቱሰ ጊዮርጊስ ሰትየ ጽውዐ በእደ እግዝእቶሙ ለሊቃነ መላእክት፡፡ ሄኖክኒ ይቤ ወበውእቱ መካን ርኢኩ ነቅዐ ጽድቅ ዘኢይትኌለቍ ወየዐውድዎ አንቅዕተ ጥበብ ወኵሎሙ ጽሙዓን ይሰትዩ እምኔሁ ወይትመልኡ ጥበበ፡፡

፴፰ ይህ ጊዮርጊስም በሊቃነ መላእክት በእመቤታቸው እጅ ጽዋን ጠጣ፤ ሄኖክም በዚያ ቦታ የማይቈጠር የጽድቅ ምንጭን አየሁ፤ የጥበብ ምንጮችም ይከብቡታል፡፡ የተጠሙትም ሁሉ በእርሱ ይጠጣሉ፤ ጥበብንም ይመላሉ አለ፡፡

፴፱ ወብፁዕሰ ጊዮርጊስ ሰትየ እምነቅዐ ጥበብ ዘውእቱ ራኆ እዴሃ ለጥበብ እንተ ወለደቶ ለገባሬ ጥበባት ወተመልአ ጥበበ ፈድፋደ፡፡

፴፱ ብፁዕ የሆነ ጊዮርጊስ ግን ከጥበብ ምንጭ ጠጣ፤ ይኸውም የጥበባትን ፈጣሪ ከወለደች መሃል እጅ ነው፡፡ ፈጽሞም ጥበብን ተመላ፡፡

፵ ኢሳይያስኒ ይቤ ወተፈነወ ኀቤየ እምሱራፌል ወውስተ እዴሁ ፍሕም ዘነሥአ በጉጠት እምሥዋዕ ወአልከፈኒ ከናፍርየ፡፡ ወይቤለኒ ናሁ አልከፍኩከ ከናፍሪከ ወአእተትኩ ኀጣውኢከ ወአበሳከኒ ያነጽሐከ፡፡ ኢሳ. ፮፥፯

፵ ኢሳይያስም አለ “ከሱራፌል አንዱ ወደ እኔ ተላከ ከመሠዊያው በጉጠት የወሰደው ፍሕም በእጁ ነበረ፡፡ ከንፈሮቼን ዳሰሰኝ አስነካኝ እነሆ ከንፈሮችህን አስነካሁህ፤ ኀጢአትህን አራቅሁልህ፤ በደልህንም ያነጻሐል አለኝ፡፡ ኢሳ. ፮፥፯

፵፩ ወለጊዮርጊስሰ አፈ በረከት አልከፈቶ ከናፍሪሁ እምጽዋዐ እሳት ወላዲቱ ለእሳተ መለኮት ዘየአኲትዎ ኪሩቤል ወይቄድስዎ ሱራፌል፡፡

፵፩ አፈ በረከት ጊዮርጊስ ግን ኪሩቤል የሚያመሰግኑት ሱራፌልም የሚቀድሱት እሳተ መለኮትን የወለደች እመቤታችን ከእሳት ጽዋ ከንፈሩን አስነካችው፡፡

፵፪ ሕዝቅኤልኒ ይቤ ወይቤለኒ ወልደ ዕጓለ እመሕያው አፉከ ይብላዕ ወከርሥከ ይጽገብ እምዛቲ መጽሐፍ እንተ ወሀብኩከ፡፡ ወበላዕክዋ፡፡ ወኮነተኒ ከመ መዐር ጥዕምተ በውስተ አፉየ ወሶበ ውኅጥክዋ አምረረታ ለከርሥየ፡፡

፵፪ ሕዝቅኤል አለ፤ የሰው ልጅ ሆይ ከሰጠሁህ ከዚች መጽሐፍ አፍህ ይብላ ሆድህም ይጥገብ አለኝ፤ በላኋት በአፌም ውስጥ እንደ ማር ጣፈጠችኝ በዋጥኋትም ጊዜ በሆዴ መራራ ሆነች፡፡

፵፫ ወጊዮርጊስኒ ሶበ ጥዕመ ዘንተ ስቴ በእዴሃ ለነቅዐ ሕይወት ኮነት ጥዕምተ በውስተ አፉሁ፡፡ ወሶበ ውሕጠ ጒሥዐ ልቡ ጥበበ ወምክረ ወከብደ ዲበ እንግድዓ ልቡናሁ እስመ ግብር ክሡት ገሀደ ከመ ውእቱ ይትሌዓል እምነቢያት

፵፫ ጊዮርጊስ ግን ከሕይወት ምንጭ እጅ ይህን መጠጥ በቀመሰ ጊዜ በአፉ ውስጥ የጣፈጠች ሆነችለት፤ በጠጣትም ጊዜ ልቡናው ጥበብንና ምክርን ተናገረ፡፡ በልቡናውም ላይ የጸና ሆነ፡፡ እርሱ ከነቢያት እንዲበልጥ የተገለጠ ሥራ ነውና፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፺፬ ሎሙሰ ተውህቦሙ ሀብት በእደ መላእክት ወለጊዮርጊስ በእደ እሙ ለገባሬ መላእክት በከመ ጽሑፍ ከመ መንፈሰ እግዚአብሔር ይኄይስ እመንፈሳቲሆሙ:: ወእግዚእነሂ ይቤ በወንጌል እስመ ብዙኃን ነቢያት ወጻድቃን ፈተዉ ይርአዩ አንትሙ ዘትሬእዩ ወኢርእዩ ወፈተዉ ይስምዑ አንትሙ ዘትሰምዑ ወኢሰምዑ:: ማቴ. ፲፫፥፲፯

፺፬ ለእነርሱ በመላእክት እጅ ሀብት ተሰጣቸው፤ ለጊዮርጊስ ግን መላእክትን በፈጠረ እናት እጅ ተሰጠው:: ከመንፈሳቸው የእግዚአብሔር መንፈስ ይበልጣል ተብሎ እንደተጻፈ ጌታችንም በወንጌል ብዙ ነቢያትና ጻድቃን እናንተ የምታዩትን ሊያዩ ተመኙ አላዩም፣ እናንት የምትሰሙትን ሊሰሙ ተመኙ አልሰሙም አለ:: ማቴ. ፲፫፥፲፯

፺፭ በሀብተ መክፈልትሰ ዘአበዊነ ሐዋርያት ወነቢያት እለ በልዑ መጻሕፍተ አእምሮ ወሰትዩ ጽዋዐ ሕይወት መለኮታዊ ተፈጸመ ላዕለ አቡነ ጊዮርጊስ በመክፈልት ዘእምኀበ እግዚአብሔር:: እስመ መንፈስ ቅዱስ ዘይረድኦሙ ለኲሎሙ በከመ ነገርነ ቀዳሚ::

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን::

፺፭ የዕውቀት መጻሕፍትን የበሉ መለኮታዊ ሕይወት ያለው ጽዋንም የጠጡ አባቶቻችን ነቢያትና ሐዋርያት የዕድላቸው ሀብት ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚገኝ ጸጋ /ዕድል/ በአባታችን ጊዮርጊስ ላይ ተፈጸመ፡ አስቀድመን እንደተናገርን የሚረዳቸው አንድ መንፈስ ቅዱስ ነውና::

ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን::

## ምዕራፍ ፫

፩ ንትመየጥኬ እንከ ኀበ ጥንተ ነገር እስመ ተጼወወ ኅሊናነ እምጣዕመ መጻሕፍት ዘአስተቃሰምዎ እምቃለ ነቢያት ወሐዋርያት::

## ምዕራፍ ሦስት

፩ እንግዲህ ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስ ከነቢያትና ከሐዋርያት ቃል ከጣፈጡት ከመጻሕፍት ጣፋጭነት የተነሣ ኅሊናችን ተማርኮ ነበርና::

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፪ ወእምድኅረ አስተየቶ ጽዋዐ እግዝእትነ ማርያም ለብፁዕ ጊዮርጊስ መሀረቶ ሶቤሃ ፭ ቃላተ ምስጢር እስመ ያበርሃ አዕይንተ ኅሊና ወይከሥታ አእዛነ አልባብ፡፡

፪ እመቤታችን ማርያም ለብፁዕ ጊዮርጊስ ጽዋውን ካጠጣችው በኋላ ያን ጊዜ አምስት የምስጢር ቃላትን አስተማረችው፡፡ የኅሊናን ዓይኖች ያበራሉና የልቡናንም ጆሮዎች ይከፍታሉና፡፡

፫ ወእምዝ ተሰወረት እምኔሁ ወዐርገት ውስተ ሰማያት ምስለ አእላፍ ትጉሃን እለ ኢይነውሙ፡፡ ስብሐት ይደሉ ለዘክሮታ ወግናይ ለክብረ ንግሣ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፫ ከዚህ በኋላ ከእርሱ ተሰወረች ከማይተኙ ከትጉሃን መላእክትም ጋር ወደ ሰማይ ዐረገች፡፡ ለስም አጠራርዋ ምስጋና ይገባል ለንግሥትነቷም ክብር ይገባል፡፡ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

፬ ወፍካሬ ፭ቱ ቃላተ ምስጢር በከመ አይድኡ አበው መንፈሳውያን ምሉኣነ አእምሮ፡፡ ዝ ውእቱ አጽንዖቱ ለመዝሙረ ዳዊት በአሐቲ ዕለት ዘእንበለ ትምህርት በሀብተ መንፈስ ቅዱስ ዘተውህበ እምእደ እግዝእትነ ማርያም፡፡

፬ የአምስቱ የምስጢር ቃላት ትርጉምም ዕውቀትን የተመሉ መንፈሳውያን አባቶቻችን እንደ ነገሩን ከእመቤታችን ማርያም እጅ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ትምህርት ሳይማር በአንድ ቀን የዳዊትን መዝሙር ማጥናት ነው፡፡

፭ እስመ ለመዝሙረ ዳዊትሰ ይሰርዕዎ ዕብራውያን ለኀበ ፭ ክፍል በአምጣነ ፭ ኊልቈ ሕዋሳት፡፡ ዘውእቶሙ ሰሚዕ ወርእይ አጼንዎ ወጥዒም ወገሢሥ፡፡

፭ መዝሙረ ዳዊትን ግን ዕብራውያን በአምስቱ የስሜት ሕዋሳት ቁጥር ለአምስት ከፍለውታል፡፡ እነዚህም መስማት፣ ማየት፣ ማሽተት፣ መቅመስና መዳሰስ ናቸው፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፮ ክፍል ቀዳማዊ ተፍጻሜቱ መዝሙር ፵፩፡፡ ወክፍል ዳግም ተፍጻሜቱ መዝሙር ፸ወ፪፡፡ ወክፍል ሣልስ ተፍጻሜቱ መዝሙር ፹ወ፱ ፡፡ ወክፍል ራብዕ ተፍጻሜቱ መዝሙር ፻ወ፮፡፡ ወክፍል ሐምስ ተፍጻሜቱ መዝሙር ፻፶፡፡ ወይኤምር ፍጻሜ እሉ ክፍላት ሶበ ይብል ለይኩን ለይኩን፡፡

፲፮ የመጀመሪያው ክፍል መጨረሻው ፵፩ኛው መዝሙር ነው፡፡ የሁለተኛው ክፍል መጨረሻው ፸፪ኛው መዝሙር ነው፡፡ ሦስተኛው ክፍል መጨረሻው ፹፱ኛው መዝሙር ነው፡፡ አራተኛው ክፍል መጨረሻው ፻፮ኛው መዝሙር ነው፡፡ አምስተኛው ክፍል መጨረሻው ፻፶ኛው ነው፡፡ የእነዚህም ክፍላት መጨረሻ ለይኩን ለይኩን ባለ ጊዜ ይታወቃል፡፡

፲፯ ወካልኣንሰ ይቤሉ በእንተ ፭ ቃላት ዘምስጢር እምድኅረ ተሰወረት እምኔሁ እግዝእትነ ጸሐፈ እልክቱ ፭ ቃላተ ምስጢር ከመ ይትመሀሮን ዳግመ፡፡ ለእመ ረስዖን እስመ ምስሌሁ ዘይትሐጥአ እም አፉሁ ከመ ኵሎን ቃላት

፲፯ ሌሎች ግን ስለ አምስቱ የምስጢር ቃላት እመቤታችን ከእርሱ ከተሰወረች በኋላ የእነዚህን አምስቱን የምስጢር ቃላት ዳግመኛ ይማራቸው ዘንድ እንደሌሎቹ ቃላት ከአፉ እንዳይረሱ ጻፈ ይላሉ፡፡

፲፰ ወእምድኅሬሁ ሶበ ነቅሐ እም ነዊም ብፁዕ ጊዮርጊስ ረከቦን ለእልክቱ ፭ ቃላተ ምስጢር፡፡ ወአንበቦን በአፉሁ አእመረ ከመ ኢይደምሰስ እምኅሊናሁ ደምሰሶን እምገጸ መጽሐፍ ዘጸሐፎን፡፡

፲፰ ከዚህ በኋላ ብፁዕ ጊዮርጊስ ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ እኒህን አምስት የምስጢር ቃላት አገኛቸው፡፡ በቃሉም አነበባቸው ከኅሊናውም እንደማይጠፉ ባወቀ ጊዜ ከጻፋቸው መጽሐፍ ደመሰሳቸው /አጠፋቸው/፡፡

፲፱ ወይትመርሑ በእንተ እልኩ ፭ ቃላተ ምስጢር ወይብሉ ብነ ስምዕ እምቃለ ጳውሎስ ላእክ፤ ዘይቤ ወአነ አእምር ብእሴ ምእመነ በክርስቶስ ወመሰጥዎ ለውእቱ ብእሲ እስከ ሣልስ ሰማይ ወሰምዐ በህየ ዘኢይተረጐም ወዘኢይከውኖ ለእጓለ እመሕያው ይንብብ፡፡ ፪ቆሮ. ፲፪፥፬

፲፱ ስለነዚያም አምስት የምስጢር ቃላት ተመርተው ከአገልጋይ ጳውሎስ ቃል ምስክር አለን ይላሉ፡፡ በክርስቶስ ያመነ የማውቀው ሰው አለ አለ፡፡ ያንን ሰው እስከ ሦስተኛው ሰማይ ነጥቀው ወሰዱት በዚያም ሰው ሊናገረውና ሊተረጉመው የማይቻለውን ነገር ሰማ፡፡ ፪ቆሮ. ፲፪፥፬

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲ | ምንተ እንከ ንብል በእንቲአሆን እንዳኢ እግዚአብሔር አብ የአምር ኅቡኣተ ምስጢሮን ለእልኩ ፭ቱ ቃላት፡፡ | ፲ | እንግዲህ ስለእነዚህ ቃላት ምን እላለሁ፤ የእነዚህ አምስት ቃላት የተሰወረ ምስጢራቸውን እግዚአብሔር ያውቃል፡፡ |
| ፲፩ | ወብፁዕሰ ጊዮርጊስ ኢነገሮን ወኢለመኑሂ ወኅብኦን በከመ ይቤ ሰሎሞን ጠቢባን የኀብኡ አእምሮ፡፡ ወዳዊትኒ ይቤ ዘኢይትነበብ ኅቡአ ጥበብከ አይዳዕይከኒ፡፡ ወለዮሐንስኒ ይቤሎ ሕትም ዘነበቡ ፯ ነጎድጓድ ወኢትጽሐፍ፡፡ መዝ. ፶፥፯ ራእ. ፲፥፬ | ፲፩ | ብፁዕ ጊዮርጊስ ግን ለማንም አልተናገረም ሰወራቸው እንጂ ሰሎሞን ጠቢባን ዕውቀትን /ጥበብን/ ይሰውራሉ እንዳለ፡፡ ዳዊትም የማይነገር ስውር ጥበብህን አስታወቅኸኝ አለ፡፡ ዮሐንስንም ሰባቱ ነጐድጓድ የተናገሩትን ስውር አትጻፍ አለው፡፡ መዝ. ፶፥፯ ራእ. ፲፥፬ |
| ፲፪ | ወከማሁ ብፁዕ ጊዮርጊስ ኅብኦን ለእልኩ ፭ ቃላት ውስተ መዝገበ ልቡ እስመ ኢያብሆ እግዚአብሔር ለከሢቶቶን፡፡ ወበጥዩቅሰ መዝሙረ ዳዊት ውእቱ እስመ መዝሙረ ዳዊትሰ አምሳለ ገነት ውእቱ ዘአስተጋብአ ኲሎ አቅማሃ ፍሬያተ ገነት ይሰድድ አጋንንተ ወያቀርብ መላእክተ፡፡ | ፲፪ | እንዲሁ ብፁዕ ጊዮርጊስም እነዚያን አምስት ቃላት በልቡ መዝገብነት ሰወራቸው፤ ሊገልጣቸው እግዚአብሔር አልፈቀደለትምና፤ በተረዳ ነገር ግን መዝሙረ ዳዊት ነው፡፡ የገነትን ፍሬዎች ሁሉ የሰበሰበ መዝሙረ ዳዊት የገነት አምሳል ነውና፤ አጋንንትን ያሳድዳል መላእክትንም ያቀርባል፡፡ |
| ፲፫ | ወዘያሌቡሰ እንበይነ ዝንቱ እስመ ሳኦል ንጉሥ በመዝሙረ ዳዊት ነበረ ያዓርፍ እም አጋንንት እለ ለመድዎ፡፡ ወካዕበ መዝሙረ ዳዊትሰ መንፈቁ ተነብዮ ወመንፈቁ ተግሣጽ ወመንፈቁ ጥበብ፡፡ | ፲፫ | ስለዚህም ነገር የሚያስረዳው ሳኦል ከለመዱት /ከተቆራኙት/ አጋንንት በዳዊት መዝሙር ዕረፍት ያገኝ ነበር፡፡ ዳግመኛም መዝሙረ ዳዊት ከፊሉ ትንቢት፣ ከፊሉ ተግሣጽ ከፊሉ ጥበብ ነው፡፡ |

፲፬ ንትመየጥኬ ኀበ ጥንተ ነገር፡፡ ወአመ ሰትየ ውእቱ ጽዋዐ አእምሮ እምእደ እግዝእትነ እመ ብርሃን ወተምህረ እምአፉሃ ውእተ ፭ ቃላተ፡፡ አማሕፀነቶ ኀበ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ ወትቤሎ ዕቀብ ድንግልናከ እስመ ኵሉ ዘዐቀበ ድንግልናሁ ይከውን እኁየ ወዘንተ ብሂላ ተሰወረት፡፡

፲፬ ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስ፣ ከብርሃን እናት ከእመቤታችን እጅ የዕውቀት ጽዋን በጠጣ ጊዜ ከእርሷ አንደበት እነዚህን አምስት ቃላት ተማረ፡፡ ለጌታ ወዳጅ ለዮሐንስም አደራ ሰጠችው ድንግልናህን ጠብቅ ድንግልናውን የጠበቀ ሁሉ ወንድሜ ይሆናልናል አለችው ይህንም ብላ ተሰወረች፡፡

፲፭ ወእምይእቲ ሰዓት ተከሥተ አዕይንተ ልቡ ወተመሰጠ ኅሊናሁ በአክናፈ መንፈስ ቅዱስ፡፡ ወበጽሐ ኀበ ኅሊናሁ ለአብ ወበህየ ረከበ ኢየሱስሃ እንዘ ይነብር በየማነ አቡሁ ወጰራቅሊጦስሃ ኀቡረ በህላዌሁ፡፡

፲፭ ከዚያችም ሰዓት ጀምሮ የልቡ ዓይን በራለት፡፡ ተከፈተለት ኅሊናውም በመንፈስ ቅዱስ ክንፎች ተመሰጠ፡፡ ወደ አብም ደረሰ፤ በዚያም ኢየሱስን በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ጰራቅሊጦስንም በአንድ አኗኗር አገኘው፡፡

፲፮ ወበእንተዝ ኮነ ብፁዕ ጊዮርጊስ እሱረ በሐብለ ሥላሴ ወተሞቅሐ በሰንሳሌሁ ዘኢይትሌለይ፡፡ ወተቀነወ በቅንዋተ ፍቅሩ ዘኢይትመላህ እምአልባቢሁ፡፡

፲፮ ስለዚህም ብፁዕ ጊዮርጊስ በሥላሴ ገመድ የታሰረ ሆነ፤ በማይለይም ሰንሰለት ታሰረ፤ ከልቡ በማይነቀል በፍቅሩ ችንካርም ተቸነከረ፡፡

፲፯ አስመከ ኀቤሁ በሃይማኖት ወኢተግሕሠ እምኔሁ ለይምን ወለጽግም፡፡ አንበሮ ከመ ሕልቀት ውስተ ልቡ ወከመ ማዕተብ ውስተ መዝራዕቱ፡፡

፲፯ በሃይማኖት ወደ እርሱ ተጠጋ፤ ከእርሱም ወደ ቀኝ ወደ ግራም አልሸሸም /አላለም/ እንደቀለበት በልቡ አስቀመጠው እንደ ማተብም በክንዱ አሰረው፡፡

፲፰ ወደዮ ከመ ባሕርይ ውስተ አስከሬነ ልቡ ወከመ መካልየ ወርቅ ውስተ መዝገበ ኅሊናሁ፡፡ ለብሶ ከመ ሞጣሕት ወተአጽፎ ከመ ሜላት፡፡ ቀነቶ ከመ ሰይፈ ሐራ ነገሥት ውስተ ሐቌ ልቡ፡፡

፲፰ እንደ ዕንቁም በልቡ ሳጥን ውስጥ ጨመረው፤ እንደ ወርቅም በኅሊናው መዝገብ አስቀመጠው፤ እንደ መጐናጸፊያ ለበሰው፤ እንደ ነጭ ሐርም ተጐናጸፈው፤ እንደነገሥታት ወታደር ሰይፍም በልቡ ወገብ ታጠቀው፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፱ ወተወልተዎ ከመ ወልታ መዊእ ዘድልው ለንዋየ ጸብዕ እስመ መልአ ውስተ ልቡ ፍቅረ ዚአሁ ከመ ተከዜ ግዮን በወርኀ ኤሎል ወከመ ተከዜ ዮርዳኖስ በጊዜ ማዕረር ወከመ ተከዜ ጤግሮስ ዘአሜ ክረምት፡፡ ወከመ ተከዜ ኤፍራጥስ አመ ይሰዊ፡፡ ሰቀዮ ለልቡ በአፍላገ ወንጌል ወአጽበቶ ለሐመረ ልቡ ውስተ ቀላየ ሃይማኖት፡፡

፲፱ ለሰልፍ እንደተዘጋጀ የድል ጋሻ አነገበው፡፡ የዐባይ ወንዝ በሐምሌ በነሐሴ የዮርዳኖስም ወንዝ በመከር ጊዜ የጤግሮስም ወንዝ በክረምት ጊዜ የኤፍራጥስም ወንዝ ስንዴ በሚሸት ጊዜ እንደሚመላ እንደዚሁ የፈጣሪው ፍቅር በልቡናው መልቶአልና፡፡ ልቡናውን ከወንጌል ምንጮች አጠጣው፤ የልቡን መርከብም በሃይማኖት ባሕር አስዋኘው፡፡

፳ ወእምዝ ገብአ ብፁዕ ጊዮርጊስ ኀበ መምህሩ፡፡ ወሶበ ወጠነ ይምሀሮ ፈጸመ ኩሎ ትምህርተ እንዘ ያነብብ ከመ ዘተምህረ ቀዳሚ፡፡ ወመምህሩሰ አንከረ ወአስተዐጸበ ወነገሮሙ ለሰብአ ይእቲ ደሴት ኩሎ ዘከመ ኮነ፡፡

፳ ከዚህም በኋላ ብፁዕ ጊዮርጊስ ወደ መምህሩ ተመለሰ፤ ያስተምረውም ዘንድ በጀመረ ጊዜ አስቀድሞ እንደተማረ ሰው እያነበበ ትምህርቱን ሁሉ ፈጸመ፡፡ መምህሩም ፈጽሞ አደነቀ፤ በሐይቅ ደሴት ለሚኖሩ ሰዎችም የሆነውን ሁሉ ነገራቸው፡፡

፳፩ ወእሙንቱሰ አንከሩ ወአስተዐጸቡ ወሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ዘይሁብ ጸጋሁ ለኅሩያኒሁ እለ ይግዕሩ ኀቤሁ መዓልተ ወሌሊተ ወምስጢሮሰ እለ ኢለበዉ፡፡ ወእምይእቲ ዕለት ለበወ አቡነ ጊዮርጊስ አንብቦ መጻሕፍት በጥእጣኤ ወፍካሬ ሆሙኒ ወኩሎ ቃላተ ዘበእንተ ክርስቶስ ጠየቀ ወፈጸመ፡፡

፳፩ እነርሱም ፈጽመው አደነቁ፤ በቀንና በሌሊት ለሚጮኹ ለተመረጡ ጸጋውን የሚሰጥ እግዚአብሔርን አመሰገኑት፤ ምስጢሩን ግን አላስተዋሉም፤ ከዚያችም ቀን ጀምሮ አባታችን ጊዮርጊስ የመጻሕፍትን ንባባቸውንና ትርጓሜያቸውን በጣፈጠ /ባማረ/ ሁኔታ አስተዋለ፡፡ ስለ ክርስቶስም ቃላትን ሁሉ ተረዳ ፈጸመም፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፳፪ ወኮኑ ያነክሩ እለ ያጸምዕዎ ወይብሉ እምአይቴ ሎቱ ዝንቱ ኵሉ ጥበብ ወኀይል፡፡ ወካልኣን ይብሉ ምንትኑ ይከውን እም ዝንቱ ሕፃን እስመ እደ እግዚአብሔር ላዕሌሁ፡፡

፳፪ የሚሰሙትንም አደነቁ፡፡ ይህ ሁሉ ጥበብና ኀይል ከየት መጣለት? አሉ፡፡ ሌሎችም ከዚህ ሕፃን የተነሣ ምን ይሆን? አሉ፡፡ የእግዚአብሔር እጅ / ሥልጣን/ በእርሱ ላይ ናትና፡፡

፳፫ ወእግዝእትነሰ ማርያም አኮ ባሕቲቶ ለብዎ መጻሕፍት ዘከሠተት ሎቱ አላ ዳእሙ አልበሰቶ ኀይለ ዘመንፈስ ቅዱስ፡፡ ወወሀበቶ ጥበበ ወአእምሮ በዘይድኀን እምዓለም ዘይትቃወም በእኩይ፡፡

፳፫ እመቤታችን ማርያምም የገለጠችለት የመጻሕፍትን ዕውቀት ብቻ አይደለም፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ኀይልንም አለበሰችው እንጂ፡፡ በክፉ ከሚቃወም ዓለም የሚድንበትን ጥበብና ዕውቀትን ሰጠችው፡፡

፳፬ ወእምዝ ረሰያ ለሥጋሁ ታቦተ መንፈስ ቅዱስ ዘይጸውር ቅድሳተ በመልያልይሁ፡፡ ወረሰያ ለነፍሱ ሠረገላ ለጸሎት፡፡ ዐቀባ ለሥጋሁ እምርኩስ ወለነፍሱ እምኀልዮ ዘበምድር፡፡

፳፬ ከዚህ በኋላ ሥጋውን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አደረጋት፡፡ በሕዋሳቱም ቅድስናን ተሸከመ፡፡ ነፍሱን ለጸሎት ሠረገላ አደረጋት፡፡ ሥጋውን ከርኩሰት ነፍሱንም በምድር ያለውን ከማሰብ ጠበቃት፡፡

፳፭ ወእደዊሁኒ እምገሢሠ ኵሉ ርኩስ ዘይጸልእ እግዚአብሔር፡፡ ወእገሪሁ እምነሶሳው ኀበ ዘኢይትበቍዕ፡፡ አዕይንቲሁ እምነጽሮ ከንቱ፡፡ ወእዘኒሁ እምሰሚዐ ሐሜት ወዛውዕ፡፡

፳፭ እጁንም እግዚአብሔር የሚጠላውን ርኩስ ነገር ሁሉ ከመዳሠሥ፣ እግሩንም ወደ ማይጠቅም ነገር ከመመላለስ፣ ዓይኑንም ከንቱ ነገር ከማየት፣ ጆሮውንም ሐሜትና አሉባልታ ከመስማት ጠበቀ፡፡

፳፮ በከመ ይቤ እግዝእነ በመጽሐፈ ኪዳን አጽምሙ እዘኒከሙ እለ ይትረአያ ወአዑሩ አዕይንቲከሙ እለ በገሐድ ከመ ታእምሩ ፈቃዶ ለእግዚአብሔር ወኵሎ ምስጢረ መድኀኒትከሙ፡፡

፳፮ ጌታችን በመጽሐፈ ኪዳን /ትምህርተ ኅቡኣት/ የሚታዩ ጆሮአችሁን አደንቁሩ፤ በግልጥ ያሉ ዐይኖቻችሁንም ሰውሩ የእግዚአብሔርን ፈቃድና የድኅነታችሁን ምስጢር ታውቁ ዘንድ እንዳለ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፷፪ ወዓዲ ዐቀበ ልሳኖ እምነቢብ ጽሩዕ ዘኢይደሉ ዘእንበለ ዳእሙ ለአንብቦ ቃለ መጻሕፍት ቅዱሳት ወደጊመ ቃለ መለኮት፡፡ ሰቀላ ለሥጋሁ በፍቅረ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ ወአሞታ ለነፍሱ እም ኀጢአት፡፡

፷፪ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል ከማንበብና የመለኮት ቃልን ከመድገም በቀር የማይገባ ነገር ከመናገር አንደበቱን ጠበቀ፡፡
ሰውነቱን በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር አጸናት ነፍሱን ከኃጢአት ለያት፡፡

፷፫ አስራራ ለኅሊናሁ በአክናፈ መንፈስ ቅዱስ ወአብጽሖ እስከ ሉዓሌ አእምሮ መጻሕፍት፡፡ አጽበታ ለሐመረ ልቡ ውስተ ባሕረ መለኮት፡፡ ወሞቅሐ ኲሎ መልያልይሁ በሐብለ ትእዛዛቲሁ ከመ መሀረቶ ወአለበወቶ ጥበበ እግዚአብሔር እንተ እምላዕሉ፡፡ እስመ አፍርሀቶ ወአደንገጸቶ በተግሣፃ ከመ ኢያንቀልቅል እምሕገ አምላኩ፡፡

፷፫ ኅሊናውን በመንፈስ ቅዱስ ክንፎች አመጣት መጻሕፍትንም እስከማውቅ ደረጃ አደረሳት፡፡ የልቡናውን መርከብ በመለኮት ባሕር አስዋኛት፤ ከላይ የተሰጠችው የእግዚአብሔር ጥበብ እንደ አስተማረችውና እንደ አስረዳችው በትእዛዛቱ ገመድ ሕዋሳቱን ሁሉ አሠረ፡፡ ከአምላኩ ሕግ እንዳይነዋወጥ በተግሣጽዋ አስፈርታዋለችና አስደንግጣዋለችምና፡፡

፷፬ በከመ ይቤ ኢያሱ ወልደ ሲራክ ወትቀድም ወተሐውር ምስሌሁ እንዘ ታፈርሆ ወትጌርሞ ወታደነግፆ፡፡ ትቀሥፎ ወትሜህሮ እስከ ታገርሮ ለነፍሱ፡፡ ወትሜህሮ በተግሣጸ፡፡ ወእምዝ ካዕበ ትትቄበሎ ወታስተፌሥሖ ወትከሥት ሎቱ ምክራ፡፡

፷፬ የሲራክ ልጅ ኢያሱ እንዳለ ፈጽማ እያስፈራችው ከእርሱ ጋር አስቀድማ ትሔዳለች፤ ታስደነግጠዋለች፡፡ ነፍሱን እስክታስገዛው ድረስ ትገርፈዋለች በተግሣጽዋም ታስተምረዋለች፤ ከዚያም ዳግመኛም ትቀበለዋለች፡፡ ታስደስተዋለች፡፡ ምክርዋንም ትገልጽለታለች፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፴ ወከማሁኬ ከሠተት ሎቱ ለብፁዕ ጊዮርጊስ ኵሎ ምክረ ወጥበበ አቅማሓ መጻሕፍት እሉ እሙንቱ መዛግብተ ጽድቅ። አብአቶ ውሳጤ አእምሮ። ወአዕረፈቶ ዓራተ ልቡና ከደነቶ ጽላሎተ ልዑል። ወአስተየቶ አፍላገ ማየ ሕይወት ዘውሕዘ እምገቦ ወልድ ወሴሰዮቶ ወአጽገቦቶ እከለ መንፈስ ቅዱስ።

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን።

## ምዕራፍ ፬

### ዘከመ ደረሰ ሞኀተ ብርሃን

፩ ወካዕበ በአሐቲ እምነ መዋዕል እንዘ ያወትር ጸሎተ በከመ ልማዱ ቅድመ ሥዕላ ለእግዝእትነ ማርያም ለዘክሮታ ሰጊድ አሥረረ ሕሊናሁ በጣዕመ ፍቅራ ወሮፀ ኀቤሃ ወሐቀፋ ወጠበወ አጥባተ ሥዕላ በሃይማኖት።

፪ ወውሕዘ ሎቱ እምአጥባቲሃ ሐሊብ ዘመንክር ጣዕሙ። አጽገቦቶ ወአርወዮቶ ወአብርሃት ገጾ በቅብዐ ሐሊብ ወይእተ ጊዜ ተፈሥሐ በመንፈስ ቅዱስ ወደረሰ ላቲ መጽሐፈ ዘይሰመይ ሞኀተ ብርሃን ዘይደሉ ለክብረ ውዳሴሃ።

፫ ወበበዐላትኒ ኵሎን የኀሊ ካዕበ ማኅሌተ መንፈስ ቅዱስ ጥዑመ ዜማ። ወይነግር በኀቡእ ለባዕዳን ከመ ይኅልዩ ቦቱ ወለሊሁሰ ይከብት ርእሶ ከመ ኢያእምርዎ።

፴ እንደዚሁም ለብፁዕ ጊዮርጊስ የመጻሕፍት ፍሬዎች ምክርንና ጥበብን ገለጠችለት፤ እኒህም የጽድቅ መዛግብት ናቸው። ወደ ዕውቀት ቦታም አስገባችው። በማስተዋል አልጋም አሳረፈችው። በልዑል መጋረጃ ሸፈነችው። ከወልድ ጐን የፈሰሰ የሕይወት ውኃንም አጠጣችው። የመንፈስ ቅዱስ እህልንም አብልታ አጠገበችው። ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን።

## ምዕራፍ አራት

### ሞኀተ ብርሃንን እንደ ደረሰ

፩ ዳግመኛም ከዕለታት አንድ ቀን እንደልማዱ ለስም አጠራርዋ ስግደት ይሁንና ከእመቤታችን ሥዕል ፊት ሲጸልይ በፍቅሯ ጣዕም ኅሊናው ተመሰጠ፤ ወደ ሥዕልዋም ሔደ አቀፋትም በሃይማኖትም የሥዕልዋን ጡቶች ጠባ።

፪ ከጡቶቿም ጣዕሙ ድንቅ የሆነ ወተት ፈሰሰለት። አጠገበችው አረካችውም፤ ያን ጊዜም በመንፈስ ቅዱስ ደስ ተሰኘ። ለምስጋናዋ ክብር የሚገባ ሞኀተ ብርሃን የተባለ መጽሐፍንም ደረሰላት።

፫ ዳግመኛ በበዓላቶቿ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ በአማረ ዜማ /ይደርሳል/ ይዘምራል። ለሌሎችም ያመሰግኑበት ዘንድ በስውር ይናገራል። እርሱ ግን እንዳያውቁት ራሱን ይሰውራል።

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፬ ወኢተከብተ አላ ተዐውቀ ለኵሉ ደሪሶቱ በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል ቅዱስ ኢትክል ተከብቶ ሀገር እንተ መልዕልተ ደብር ትነብር፡፡ ወኢያሐትዉ ማኅቶተ ከመ ያንብርዋ ታሕተ ከፊር አላ ያነብርዋ ዲበ ተቅዋማ ወታበርህ ለኵሎሙ እለ ውስተ ቤት፡፡ ማቴ.፭፥፲፬

፬ አልተሰወረም ድርሰቱ ለሁሉ ታወቀ እንጂ ጌታችን በወንጌል እንደተናገረ፡፡ "በተራራ ላይ የተሠራች ከተማ መሰወር አይቻላትም ከዕንቅብ በታች ሊያኖሯት መብራትን እያበሩም በመቅረዝዋ ላይ አኑረዋት በቤት ላሉት ሁሉ ታበራለች እንጂ፡፡ ማቴ.፭፥፲፬

፭ ከማሁኬ ቅዱስ ጊዮርጊስ ወእምዝ አኀዘ ይንብብ ገሃደ በቃለ ማኅሌት ወአብርሃ ለቤተ ክርስቲያን እንተ ተሐንጸት በሐይቀ ባሕር፡፡
ወእምአሜሃ አኀዙ ይሰአሉ እምኀቤሁ ኲሎሙ ሰብአ ሀገር ቃለ መጻሕፍት ወትርጓሜሁ ወኵሎ ቃለ ማኅሌት፡፡

፭ እንደዚሁም ቅዱስ ጊዮርጊስ የሚሠራው ሥራ አልተሰወረም ከዚያም የምስጋና ድርሰቱን በግልጽ ይናገር ጀመረ፡፡ በሐይቅ ደሴት የታነጸች ቤተ ክርስቲያንንም አበራት፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሀገሩ ሰዎች የመጻሕፍትን ቃልና ትርጓሜአቸውን የምስጋና ድርሰትንም ሁሉ ከእርሱ ይጠይቁ ጀመር፡፡

፮ ወሶበ ርእየ ዘንተ ስብሐተ ብጡለ ብፁዕ ጊዮርጊስ አኀዞ ፍርሀት ወሖረ ኀበ ሥዕላ ለእግዝእትነ ማርያም፡፡ ወጸለየ ወይቤ ኦ እግዝእትየ ዝንቱ ኲሉ በዕበየ ጸሎትኪ ተገብረ፡፡

፮ ብፁዕ ጊዮርጊስም ይህን ከንቱ ውዳሴ ባየ ጊዜ ፍርሀት ያዘው፡፡ ወደ እመቤታችን ማርያም ሥዕልም ሔዶ እመቤቴ ሆይ ይህ ሁሉ በምልጃሽ ኃይል ተደረገ ብሎ ጸለየ፡፡

፯ ወዝኒ ስብሐት እምአስራበ ክብርኪ ተቀድሐ በዘአፈልፈልኪ ሊተ ሐሊብ እምአጥባተ ሥዕልኪ፡፡ ኦ ንጽሕት ነቅዕ ንጹሕ ዘእምነቅዐ ቅድሳትኪ ውሕዘ ወተሰውጠ ውስተ አፉየ ለነዳይ ወአንጸፍጸፈ ውስተ ግምዔ ልህኵት ለምኑን፡፡

፯ ይህም ምስጋና ከሥዕልሽ ጡቶች ባፈለቅሽልኝ ወተትም ከክብርሽ ምንጭ ተቀዳ፡፡ ንጽሕት ሆይ ንጹሕ ምንጭ ከቅድስናሽ ምንጭ ፈሰሰ፡፡ በድኃው በእኔ አፍም ተጨመረ፡፡ በተናቅሁ በእኔም ማሰሮ ውስጥ ፈሰሰ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፰ አንጽሕኒ ኦ እግዝእትየ ለብእሲ ርሱሕ በነቅዐ ውእቱ ሐሊብ ቅዱስ ዘውሕዘ እምአጥባተ ሥዕልኪ ወአምዕዝኒ በመዐዛ ዕፍረትኪ ዘአንጻፈጻፈ እምቢረሌ ንጽሕኪ ኦ ንጽሕት ለኪ ይደሉ ስብሐት ወለወልድኪ ፍቁር ወለአቡሁ መሓሪ ወለመንፈስ ቅዱስ ማኅየዊ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፰ እመቤቴ ሆይ ከሥዕልሽ ጡቶች በፈሰሰ ወተትም የጉሰቆልሁ እኔን ንጹሕ አድርጊኝ፡፡ ከንጽሕናሽ ብርሌ በፈሰሰ የሽቱ መዓዛም አጣፍጭኝ፡፡ ንጽሕት ሆይ ለአንቺ ምስጋና ይገባል፤ ለተወደደው ልጅሽ ይቅር ባይ ለሆነ አባቱም ማኅየዊ ለሚሆን መንፈስ ቅዱስም ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

፱ ወሶበ ፈጸመ ጸሎቶ አስተርአየቶ እግዝእትነ ማርያም ለዘክሮታ ሰጊድ፡፡ ወምስሌሃ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ወአኀዘቶ በእዴሃ ወአማኅፀነቶ ኀቤሆሙ ለብፁዕ ጊዮርጊስ እንዘ ትብል እሉ ይኩኑከ ማሕፀንተ እስከ ለዓለመ ዓለም፡፡

፱ ጸሎቱንም በፈጸመ ጊዜ ለስመ አጠራርዋ ስግደት ይሁንና እመቤታችን ማርያም ተገለጸችለት፡፡ ከእርስዋም ጋር ጴጥሮስና ጳውሎስ ነበሩ፡፡ በእጇም ያዘችው፡፡ ብፁዕ ጊዮርጊስንም እሊህ ለዘለዓለሙ ጠባቂዎች ይሁኑህ ብላ አደራ ሰጠችው፡፡

፲ ናሁኬ ተወፈየ ማሕፀንተ ልደ ቤተ መቅደስ ለዐበይት ካህናት በቃለ እሙ ለሊቀ ካህናት፡፡ ናሁኬ ተወፈየ ማሕፀንተ ብእሲ ብሩሀ ሃይማኖት ለከዋክብት ጽዱላን በቃላ ለእመ ብርሃን፡፡

፲ እነሆ ለቤተ መቅደስ አገልጋይ / ቤተ ሰብእ/ ይሆን ዘንድ በካህናት አለቃ እናት ለታላላቆች ካህናት አደራን ተሰጠ፡ አሁን ሃይማኖቱ ብሩህ የሆነ ሰው በብርሃን እናት ቃል ለሚያበሩ ከዋክብት አደራ ተሰጠ፡፡

፲፩ ናሁኬ ተወፈየ ማሕፀንተ በግዐ የዋህ ለኄራን ኖሎት በቃለ እሙ ለሊቀ ኖሎት፡፡ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር ገብአ ወአተወ ውስተ ብሔረ ሙላዱ ሰግላ፤ ዘይሰመይ ጋስጫ፡፡

፲፩ እነሆ የዋህ በግ በእረኞች አለቃ እናት ቃል ለደጋግ እረኞች አደራ ተሰጠ፡፡ ከዚህም ነገር በኋላ ጋሥጫ ወደተባለች ወደ ተወለደበት አገር ሽግላ ተመለሰ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፪ ወእንዘ ሀሎ ህየ በአሐቲ ዕለት ርእየ ብእሲተ እምርሑቅ እንዘ ትሰፍሕ አፍታለ ለዝየ ወለዝየ ፈቂደ ከመ ይእንምዎ ለልብስ ወፌ አትረፈት ጐልቍ ፈትል እመፍቅዳ እንዘ ይመስላ ዘኢመልአ፡፡

፲፪ ከዚያም ሳለ ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ሴት ልብስ ልታሠራ ፈትል ስትፈትል ልቁ የማያበቃ መስሏት ከዚያ ከዚህ እያለች ለልብሷ እንዲበቃ ለማድረግ ቁጥሩን አትርፋ እየፈተለች መሆንዋን በሩቅ አያት፡፡

፲፫ አእመረ ብፁዕ ጊዮርጊስ በመንፈስ ቅዱስ ምልአቶ ወይቤ ለረድኡኒ በጽሐ በላ ጎድጊ ወኢትጻምዊ ወእስከ ይእዜ ተሰምየት ይእቲ ሀገር በዝንቱ ስም፡፡

፲፫ ብፁዕ ጊዮርጊስም በመንፈስ ቅዱስ መምላቱን ዐወቀ፡፡ ደቀ መዝሙሩን መልቷል አትድከሚ በላት አለው፤ ያችም አገር እስከ ዛሬ ድረስ በዚህ ስም ትጠራለች፡፡

፲፬ ወእምድኅረዝ አኀዝዎ ለአቡነ ጊዮርጊስ ወአብእዎ ውስተ ውሳጤ ዓጸድ ዘቤተ ንጉሥ። ወኰለቍዎ ምስለ ካህናት ደብተራ ህየንተ አቡሁ ዘመንኮሰ፡፡ ወእምድኅረ መንኮሰ አቡሁ ነበረ ኀዳጠ መዋዕለ እንዘ ይሜህሮሙ ለደቂቀ ንጉሥ ዘርዐ አብርሃም ወካልኣኒሁ፡፡

፲፬ ከዚህም በኋላ ብፁዕ ጊዮርጊስን ይዘው ወደ ንጉሥ ቤት ወሰዱት፡፡ ስለ መነኮሰው ስለ አባቱ ፈንታም በድንኳን /በቤተ መንግሥት/ ካሉ ካህናት ጋር ቈጠሩት፡፡ አባቱም ከመነኮሰ በኋላ የአብርሃምና የሌሎች ዘር የሚሆኑ የንጉሡን ልጆች እያስተማረ ጥቂት ዘመን ተቀመጠ፡፡

፲፭ ወእምድኅረዝ በአሐቲ ዕለት እምነ መዋዕል አስተርአዮ በራእየ ሌሊት ዮሐንስ ወንጌላዊ፡፡ ወይቤሎ እመ ይቤለከ ንጉሥ በእንተ ወለቱ በበይነ አውስቦ አሆ ኢትበሎ ወኢታውስብ ብእሲተ በዝ ብሔር፡፡

፲፭ ከዚህም በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን ወንጌላዊ ዮሐንስ ሌሊት በራእይ ተገለጸለት ንጉሡ ስለ ሴት ልጁን ጋብቻ አግባ ቢልህ እሺ አትበለው በዚህም ዓለም ሚስትን አታግባ አለው፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፭ ወእምድኅረዝ ተናገሮ ንጉሥ በበይነ ወለቱ በእንተ አውስቦታ ወይቤ ብፁዕ ጊዮርጊስ እንብየ ኢይክል ገቢሮቶ ለዝንቱ ነገር። ይበቀዓኒ ቃለ ኤርምያስ ነቢይ ዘይቤ ኢታውስብ ብእሲተ በዝ ብሔር ወኢትለድ ውሉደ።

፲፭ ከዚያም በኋላ ንጉሡ ልጁን ስለ ማግባት ተናገረው። ብፁዕ ጊዮርጊስም ይህን ነገር መሥራት አይቻለኝም አይሆንም አለ። በዚህ አገር ሚስትን አታግባ ልጅንም አትውለድ ያለው የኤርምያስ ቃል ይጠቅመኛል።

፲፮ አንሰ ሐፀይኩ ርእስየ ለእግዚአብሔር በከመ ይቤ ጳውሎስ አንሰ ፈኀርኩክሙ ለአሐዱ ምት ድንግል ወንጹሕ ክርስቶስ። ወለልየኒ ፈሐርኩ ሊተ መርዓተ በከመ ይቤ ሰሎሞን በእንተ ጥበቡ ዘንተ አፍቀርኩ ወሐሠሥክዋ እምውርዙትየ ወአፍቀርኩ አንሥአ ሊተ መርዓታ። ፪ቆሮ ፲፩፥፪

፲፮ እኔ ጳውሎስ "ለአንዱ ንጹሕ ድንግል ሙሽራ ለክርስቶስ አጭቻችኋለሁ" እንዳለ ራሴን ለእግዚአብሔር አጭቻለሁ። እኔ ለራሴ ሙሽራን አጭቻለሁ ሰሎሞን ስለ ጥበቡ ይህን ወደድሁ ከወጣትነቴ ጀምሮ ፈለግኋት። ለእኔም ሙሽራን ትሆነኝ ዘንድ ወደድሁ እንዳለ። ፪ቆሮ ፲፩፥፪

፲፯ ወስእነ ንጉሥ በብዙኅ ነገር አሆ አብሎቶ ወእምዕለት ዕለት ኢኀደገ ንጉሥ ተናገረቶ። ወሶበ ርእየ ብፁዕ ጊዮርጊስ ከመ ኢኀደጎ ንጉሥ ሖረ ኀበ ጳጳስ ወነሥአ ሢመተ ቅስና።

፲፯ ንጉሡም በብዙ ነገር እሺ ማሰኘት ተሳነው። ዕለት ዕለትም መናገሩን አልተወም። ብፁዕ ጊዮርጊስም ንጉሥ አልተወው ባለ ጊዜ ወደ ጳጳስ ሔዶ የቅስና /ሹመትን/ ሥልጣንን ተቀበለ።

፲፰ ወምድኅረዝኒ ኢኀደጎ በበይነ ወለቱ። ወሶበ ርእየ ካዕበ አቡነ ጊዮርጊስ ከመ ስእነ አምስጦ በኵሉ ወፅአ አፍአ ወነሥአ አልባሰ መነኮሳት ዘመከራ ወለብሰ በእዴሁ። ዝውእቱ ልብሰ ሐራ ዘኢኮነ ፍጹመ ከመ ያስተርኢ ለዓይነ ንጉሥ ከመ ዘመንኰሰ ወእምአሜሃ ኀደገ ንጉሥ ተናግሮቶ።

፲፰ ከዚህም በኋላ ንጉሡ ስለ ልጁ አልተወውም። ሁለተኛም አባታችን ጊዮርጊስ በሁሉም ነገር ማምለጥ እንደተሳነው ባየ ጊዜ ወደ ውጭ ወጣ። የመነኮሳትን የአመክሮ ልብስ በራሱ እጅ ለበሰ። ይኸውም የመጨረሻው ያልሆነ የአመክሮ ልብስ ነው። ለንጉሡ ዐይን የመነኮሰ መስሎ ይታይ ዘንድ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ንጉሡ መናገሩን ተወው።

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፳ ወእምድኅረዝ ኮነ አቡነ ጊዮርጊስ መምህረ ለነገሥት ወለካህናት ደብተራ ወለኩሉ ዐበይተ ቤተ መንግሥት፣ ለንቡራነ እድ ወለመኳንንት ለመሳፍንት ወለኩሉ ተዓይነ ቤተ መንግሥት፡፡

፳፩ ወነበረ እንዘ ይጸሙ በምህሮ ሕገ ኦሪት ወእንዘ ያደምፅ ነፍሖ ቀርነ አቅርንተ ትንቢት፡፡ ወእንዘ ያበሥር ወንጌለ መንግሥተ ሰማያት፡፡ ወይትጋደል በሕገ ቀኖና ዘአበዊነ ሐዋርያት ወበዘቢጠ መሰንቆ መዝሙር ዘዳዊት ወበመሐልየ ሰሎሞን ወልዱ ወይየብብ በማኅሌተ ያሬድ ብርሃነ ኢትዮጵያ፡፡

፳፪ እስመ ውእቱ ተምህረ እምኀበ አቡነ ሳሙኤል ዘጋርማ፡፡ ወለሊሁኒ ብፁዕ ጊዮርጊስ ያስተጋብእ ተቅራመ እምንባባተ ሐዲስ ወብሉይ ወየሐሊ በቀርነ ድርሳናት፡፡

፳፫ ሶበኒ ይዌጥን ቅዱስ ኀልዮታ ለቤተ ክርስቲያን ቅድስት ይትጋብኡ ኀቤሁ ኵሉ ሕዝብ ወይሰቀሉ በአጽምኦቱ፡፡ ወያነክሩ ጣዕመ ነገሩ ወሞገሰ ቃሉ ወስእሳኤ አፉሁ በከመ ይቤ ሲራክ ጠቢብ ቃለ ጠቢብ ይሰማዕ በውስተ እንግልጋ ወነገሩኒ ይበውእ ውስተ ልብ፡፡

፳ ከዚህ በኋላ አባታችን ጊዮርጊስ ለነገሥታት፣ ለካህናት ደብተራ፣ ለሁሉም የቤተ መንግሥት ሹማምንት፣ ለንቡራነ እድ ለመኳንንት፣ ለመሳፍንት፣ ለሁሉም የቤተ መንግሥት ሠራተኞች መምህር ሆነ፡፡

፳፩ የኦሪትን ሕግ በማስተማር፣ እየደከመ፣ የትንቢት መለከትንም እያሰማ፣ የመንግሥተ ሰማያት ወንጌልንም እያበሠረ ተቀመጠ/ኖረ/ በአባቶቻችን ሐዋርያት የቀኖና ሕግ በዳዊት መዝሙር በገና በመምታት በልጁ በሰሎሞንም ምስጋና ይጋደላል፡፡ የኢትዮትጵያ ብርሃን በሆነ በያሬድ ማኅሌትም ያመሰግናል፡፡

፳፪ እርሱ ከጋርማው ከአባታችን ሳሙኤል ተምሯልና እርሱ ብፁዕ ጊዮርጊስ ከብሉይና ከሐዲስ ንባባት ፍሬዎችን ይሰበስባል፡፡ በድርሳናት ቀንድም ያመሰግናል፡፡

፳፫ የተለየ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንንም ምስጋና በጀመረ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ፡፡ በመስማትም ይመሰጣሉ፡፡ የነገሩን ጣፋጭነት የቃሉ ተወዳጅነት የአንደበቱን ቅልጥፍና ያደንቃሉ፤ ሉቃ.፬፥፳፪ ጥበበኛው ሲራክ የጥበበኛ ሰው ቃል በጉባኤ ይሰማል፡፡ ነገሩም ወደ ልብ ይገባል እንዳለ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፷፬ | እስመ ድርሳኑኒ ለዝንቱ ብፁዕ ርቱዕ ወኢኮነ ጠዋየ፡፡ ከሡት ወኢኮነ ክቡተ፡፡ ክቡድ ወኢኮነ ቀሊለ፡፡ ይጥዕም እምዐር ወሦከር ወይኤድም እምሐሊብ፡፡ ያስተፌሥሕ እምወይን ወያጠልል እምቅብዕ፡፡ | ፷፬ | የዚህ ብፁዕ ጊዮርጊስ ድርሰትም ጠማማ ሳይሆን የቀና፣ የተሰወረ ሳይሆን የተገለጠ፣ ቀላል ሳይሆን ከባድ ነውና ከመዓር ከስኳር ይጣፍጣል፤ ከወተትም ያምራል፡፡ ከወይንም ያስደስታል፤ ከቅቤም ይልቅ ያለመልማል፡ |
| ፷፭ | ወፍቁር በልበ ካህናት ወነገሥት ወበኀበ ኲሉ ሰብእ፡፡ ወእንዘ ሀሎ አቡነ ጊዮርጊስ በቤተ ክርስቲያን አልቦ ዘይትሀበል ይንብብ በቅድሜሁ፡፡ | ፷፭ | በካህናትና በነገሥታት ልብ በሁሉም ሰው ዘንድ የተወደደ ነው፡፡ አባታችን ጊዮርጊስም በቤተ ክርስቲያን ሳለ በእርሱ ፊት ይናገር ዘንድ የሚደፍር የለም፡፡ |
| ፷፮ | ወእመኒ አርመመ ይጸንሑ እስከ ያወሥእ፡፡ በከመ ይቤ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት ሶበ አረምም ይጸንሑኒ ወሶበ አወሥእ ይቀርቡኒ፡፡ | ፷፮ | ዝም ቢልም እስኪናገር ድረስ ይጠብቁታል የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ዝም ባልሁ ጊዜ ይጠብቁኛል በተናገርሁም ጊዜ ይቀርቡኛል እንዳለ፡፡ |
| ፷፯ | ወእመ አብዛሕኩ ተናግሮ ይወድዩ እደዊሆሙ ውስተ አፉሆሙ እረክብ በእንቲአሃ ኢምንት ወዝከረ ለእለ እምድኅሬየ አኃድግ፡፡ አማንኬ ኀደገ አቡነ ጊዮርጊስ ዝከረ ጥዑመ ወስመ ዘይትናገሩ ባቲ፡፡ | ፷፯ | መናገርንም ባበዛ ስለ እርስዋ እጃቸውን በአፋቸው ላይ አድርገው አገኛለሁ፡፡ ከእኔም በኋላ ለሚነሡ መታሰቢያን እተዋለሁ፡፡ በእውነት አባታችን ጊዮርጊስ የጣፈጠ መታሰቢያንና የሚናገሩበት ስምን ተወ፡፡ |
| ፷፰ | ወካዕበ በአሐቲ ዕለት እመዋዕል መጽአ ሞተ ብድብድ ላዕለ ሕዝብ፡፡ ወተበውሁ መላእክተ መቅሠፍት ላዕለ ሠራዊተ ንጉሥ እስከ ለሊሁኒ ብእሴ እግዚአብሔር ተነድፈ በሐፀ ብድብድ፡፡ | ፷፰ | ዳግመኛም ከዕለታት በአንድ ቀን በሕዝቡ ላይ የመቅሠፍት ሞት መጣ የመቅሠፍት /አለቆችም/ መላእክት በንጉሡ ሠራዊት ላይ ታዘዙ፡፡ የእግዚአብሔር ሰው እርሱም በሕማሙ ጦር እስኪነደፍ ድረስ፡፡ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፷፱ ወአፀበት ነፍሱ ወአልፀቀት ለመዊት፡፡ ወገዐረ ኀበ እግዚአብሔር እማዕምቀ ልቡ እንዘ ይስእል ምሕረተ፡፡ ወበጊዜሃ አስተርአይዎ ጴጥሮስ ወጳውሎስ እንዘ ይለብሱ አልባሰ ብሩሃተ ወይትቄጸሉ አልባሰ መንግሥት ወማኅበረ ቅዱሳን ይተልውዎሙ፡፡

፷፱ ነፍሱ ተጨነቀች ለሞትም ደረሰች ምሕረትንም እየለመነ ከልቡ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፡፡ ያን ጊዜም የመንግሥት ልብሶችን ተቀዳጅተው የሚያበሩ ልብሶችንም ለብሰው ጴጥሮስና ጳውሎስ ተገለጹለት፡፡ የቅዱሳን ማኅበርም ይከተሏቸው ነበር፡፡

፸ ወሶበ ርእዮሙ ብፁዕ ጊዮርጊስ ፈርሀ ወደንገፀ ወይቤሎሙ እለ መኑ አንትሙ አጋእዝትየ፡፡ ወይቤልዎ ንሕነ እሙንቱ ጴጥሮስ ወጳውሎስ እለ ተወፈይናከ ምቅበና እምኀበ እግዝእትነ እመ ብርሃን፡፡

፸ ብፁዕ ጊዮርጊስም በአያቸው ጊዜ ፈራ ጌቶቼ እናንተ እነማን ናችሁ አላቸው፡፡ ከብርሃን እናት ከእመቤታችን አደራ የተቀበልንህ ጴጥሮስና ጳውሎስ ነን አሉት፡፡

፸፩ ወይእዜኒ መጻእነ ከመ ንንሣእከ እም ዓለመ ጽልመት ውስተ ዓለም ዘኢየኀልፍ፡፡ ወትኩን ምስሌነ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ወእሉኒ ኲሎሙ እለ ትሬኢ ማኅበረ ጻድቃን እሙንቱ እለ መጽኡ ለቀበላ ዚአከ፡፡

፸፩ አሁንም ከጨለማ ዓለም ወደማያልፈው ዓለም እንወስድህ ዘንድ መጣን፡፡ በመንግሥት ሰማያትም ከእኛ ጋር ትሆን ዘንድ፡፡ የምታያቸው እነዚህ ሁሉ አንተን ለመቀበል የመጡ የቅዱሳን ማኅበር ናቸው፡፡

፸፪ ወእምዝ ይቤሎሙ ብፁዕ ጊዮርጊስ ኀድጉኒ ንስቲተ እስከ እነግር ስብሐቲሁ ለአምላኪየ ወዘእሙ ድንግል፡፡ ወውዳሴ ዚአከሙ ወዘኲሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት ወይእተ ሶቤ ኀደግዎ ወሐሩ ወሶቤሃ ሐይወ እምሕማሙ፡፡

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

፸፪ ከዚያም ብፁዕ ጊዮርጊስ የፈጣሪዬን ጌትነት፣ የእናቱ የድንግልን ምስጋና፣ የእናንተን፣ የጻድቃንና የሰማዕታትንም ውዳሴ እስክናገር ድረስ ትንሽ ተዉኝ አላቸው፡፡ ያን ጊዜ ትተውት ሔዱ ከሕማሙም ዳነ፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

## ምዕራፍ ፭

### ዘከመ ደረሰ መጽሐፈ አርጋኖን

፩ ወካዕበ በአሐቲ ዕለት እመዋዕል ፈቀደ ከመ ይጽሐፍ መጽሐፈ ድርሳን። ወወዐለ እንዘ ይጽሕፍ አሐተ ዕለተ ወበሳኒታ ሶበ ፈቀደ ከመ ይዌስክ ላዕሌሁ ረከቦ ለውእቱ ጥራዝ ፀዓዲዎ።

፪ ወሐመ ልቡ በእንተዝ ወመሰሎ ዘተሰርቀ። ወሶበ ኈለቈ ጥራዛተ እለ ተቀፅአ ረከቦን ድኊናነ። ወካዕበ ደገመ ጽሒፈ ወበሳኒታ ረከቦ ከዊኖ ፅዕድወ ከመ ቀዳሚ ወእስከ ሣልስ ወራብዕ ዕለት፡

፫ ወእምድኅረዝ ወጠነ አቡነ ጊዮርጊስ ይትማሕለል ኀበ እግዝእትነ። ወይቤላ ከሥቲ ሊተ እመ በኀጢአትየኑ ኮነ ዝ አው አልቦ።

፬ ወበአሐቲ ዕለት እንዘ የሐውር ውስተ ቤተክርስቲያን ለጸሎት መንፈቀ ሌሊት ግብተ አስተርአየቶ እግዝእትነ ለጊዮርጊስ በስብሐት ዘኢይትነገር ወምስሌሃ ማኅበረ ኲሎሙ ቅዱሳን ወትእኅዝ በእዴሃ መጽሐፈ ዘይበርህ እምነ ፀሐይ ወወርኅ

## ምዕራፍ አምስት

### መጽሐፈ አርጋኖን እንደ ደረሰ

፩ ዳግመኛም ከዕለታት አንድ ቀን የድርሰት መጽሐፍን ይጽፍ ዘንድ ወደደ። አንድ ቀንም ሲጽፍ ዋለ። በማግሥቱም ሊጨምር በፈለገ ጊዜ ያን ወረቀት/ጥራዝ/ ነጭ ሆኖ አገኘው።

፪ ስለዚህም ልቡ አዘነ የተሰረቀም መሰለው። ጥራዞችም በቈጠረ ጊዜ ሳይጠፉ አገኛቸው። ሁለተኛም በድጋሚ ጻፈ። በማግሥቱም እንደ መጀመሪያው ጠፍቶ አገኘው። እስከ ሦስትና አራት ቀንም እንዲሁ ሆነ።

፫ ከዚያም በኋላ አባታችን ጊዮርጊስ ወደ እመቤታችን ይማለል /ይለምን/ ጀመረ። በኀጢአቴ ወይም በሌላ እንደሆነ ግለጭልኝ አለ።

፬ አንድ ቀንም ወደ ቤተ ክርስቲያን በእኩለ ሌሊት ለጸሎት ሲሔድ እመቤታችን በማይነገር ክብር ለጊዮርጊስ ድንገት ተገለጠችለት። ከእርስዋም ጋር ሁሉም የቅዱሳን ማኅበር ነበሩ። በእጅዋም ከፀሐይና ከጨረቃ የሚያበራ መጽሐፍን ይዛ ነበር።

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፰ ጊዮርጊስሰ ሶበ ርእያ ወድቀ ውስተ ምድር ወኮነ ከመ በድን፡፡ ወእግዝእትነሰ አንሥአቶ ወትቤሎ ለምንትኑ ደፈርከ ጽሒፈ መጽሐፍየ ዘእንበለ ትሰአለኒ፡፡ አኮኑ አነ አፍቀርኩከ ወቀደስኩከ እምከርሠ እምከ ወወሀብኩከ ምምሕፃነ ለጴጥሮስ ወጳውሎስ ወዮሐንስ፡፡

፰ ጊዮርጊስም ባያት ጊዜ ወደ ምድር ወደቀ፡፡ እንደ በድንም ሆነ፡፡ እመቤታችንም አነሣችው፡፡ ሳትጠይቀኝ መጽሐፌን መጻፍ ለምን ደፈርህ? አለችው እኔ ወድጄህ ከእናትህስ ማሕፀን መርጬህ የለምን? ለጴጥሮስ ለጳውሎስና ለዮሐንስም አደራ ሰጥቸሃለሁ፡፡

፱ ወይቤላ ጊዮርጊስ ስረዪ ሊተ ኦ እግዝእትየ እስመ በኢያእምሮ ገበርክዎ ለዝንቱ እንዘ ይመስለኒ ዘአሠምረኪ፡፡ ወእግዝእትነሂ ትቤሎ ሰረይኩ ለከ ኦ ፍቁርየ ወውእቱሂ መጽሐፍ ዘፈቀድከ ትጽሐፎ ናሁ እኁዝ ውስተ እዴየ፡፡

፱ ጊዮርጊስም እመቤቴ ሆይ ደስ የሚያሰኝሽ መስሎኝ ይህን ባለማወቅ አድርጌዋለሁና ይቅር በይኝ አላት፡፡ እመቤታችንም ወዳጄ ሆይ ይቅር ብዬሃለሁ አለችው፡፡ ልትጽፈው የፈለግኸው መጽሐፍም እነሆ በእጄ ተይዞአል፡፡

፲ እምይእዜሰ ሠምረ ወልድየ ፍቁር ከመ ይክሥቶ በአፉከ ወባሕቱ ኢትጉጉእ እስከ ትለብስ ኀይለ እምአርያም፡፡ ወዘንተ ብሂላ ተሰወረት፡፡

፲ ከአሁን በኋላ ግን የተወደደ ልጄ በአንደበትህ ይገልጠው ዘንድ ፈቅዷል፡፡ ነገር ግን ከሰማይ ኃይልን እስክትለብስ ድረስ አትቸኩል አለችው፡፡ ይህንም ብላ ተሰወረች፡፡

፲፩ ወሶቤሃ በርሀ ልቡ ከመ ፀሐይ ወኀተወ ውስተ ኀሊናሁ ባሕርየ መለኮት፡፡ ወነጸረ ኩሎ ኅቡኣተ በመጽሔተ መንፈስ ቅዱስ ወአኀዘ ይድርስ ወይጽሐፍ መጽሐፈ ዘይሰመይ አርጋኖነ ውዳሴ በመዋዕሊሁ ለዳዊት ንጉሥ መፍቀሬ እግዚአብሔር፡፡

፲፩ ያን ጊዜም ልቡ እንደ ፀሐይ በራ በኅሊናውም የመለኮት ዕንቍ አበራ፡፡ በመንፈስ ቅዱስም መስታወት የተሰወረውን ሁሉ አየ፡፡ እግዚአብሔርን በሚወድ በንጉሥ ዳዊት ዘመንም አርጋኖን ውዳሴ የሚባል መጽሐፍንም ይደርስና ይጽፍ ጀመረ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፱ | ወሰመዮ በሠለስቱ አስማት ዘውእቶሙ አርጋኖነ ውዳሴ ወመሰንቆ መዝሙር ወዕንዚራ ስብሐት:: ወእንበይነ ጣዕሙ ለውእቱ መጽሐፍ አጽሐፎ ንጉሥ በቀለመ ወርቅ:: | ፱ | በሦስት ስሞችም ሰየመው:: እነዚህም አርጋኖነ ውዳሴ፣ መሰንቆ መዝሙር፣ ዕንዚራ ስብሐት ናቸው:: ስለ ጣፋጭነቱም መጽሐፉን ንጉሡ በወርቅ ቀለም አጻፈው:: |
| ፲ | ወገባሬ ወርቀ ቀለምኒ ሶበ ኀጥአ እብነ በዘያጸድሎ ለወርቅ ነገረቶ እግዝእትነ ማርያም ለጊዮርጊስ በራእየ ሌሊት ከመ ሀሎ በሀገረ ዚማት ወአርአየቶ ኀበሪሁ:: | ፲ | የወርቅ ቀለም ሠሪውም የወርቅ ቀለሙን የሚያስጌጥበት ድንጋይ ባጣ ጊዜ እመቤታችን ዚማት በሚባል ሀገር እንዳለ ለጊዮርጊስ ሌሊት በራእይ ነገረችው:: ኀብሩንም አሳየችው:: |
| ፲፩ | ይቤ አቡነ ጊዮርጊስ እምኵሉ ድርሳናት ዘደረስክዎሙ ወዘተናገርክዎሙ ይጥዕም ወይትሌአል አርጋኖነ ውዳሴ:: | ፲፩ | አባታችን ጊዮርጊስ ከደረስኳቸው ድርሰት ሁሉ የአርጋኖን ምስጋና ይበልጣል አለ:: |
| | **ዘከመ ደረሰ መጽሐፈ ዘይሰመይ ውዳሴ መስቀል** | | **ውዳሴ መስቀል የተባለ መጽሐፍን እንደደረሰ::** |
| ፲፪ | ወካዕበ በአሐቲ እመዋዕል መጽኡ ኀቤሁ ጴጥሮስ ወጳውሎስ:: ወአምጽኡ መስቀሎ ወአንበሩ ወበጽሐ ቆሙ እስከ ርእሱ:: ወክልኤ አቅርንቲሁ ለመስቀል መልአ ኀበ ክልኤ መታክፍቲሁ:: | ፲፪ | ዳግመኛም ከዕለታት በአንድ ቀን ጴጥሮስ እና ጳውሎስ ወደ እርሱ መጡ መስቀሉንም አምጥተው ከፊቱ አስቀመጡ፤ የመስቀሉም ቁመት እስከ ራሱ ደረሰ የመስቀሉም ሁለት ክንፎች በሁሉቱ ትከሻዎቹ ልክ ሆኑ:: |
| ፲፫ | ወሶቤሃ ሰምዐ ቃለ እምሰማይ ዘይብል ልሳንከ ይኩን ከመ ልሳነ ጴጥሮስ ወጳውሎስ:: ወሥልጣንከ ከመ | ፲፫ | ያን ጊዜም ከሰማይ አንደበትህ እንደ ጴጥሮስና ጳውሎስ አንደበት፣ ሥልጣንህም እንደ ሥልጣናቸው ይሁን |
| ፲፬ | ወበጊዜሃ ኀተወ ውስተ ልቡ ማኅቶተ መንፈስ ቅዱስ:: ወደረሰ መጽሐፈ ዘይሰመይ ውዳሴ መስቀል:: | ፲፬ | ያን ጊዜም የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን በልቡ በራ:: ውዳሴ መስቀል የሚባል መጽሐፉን ደረሰ:: |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፫ | **ዘከመ ደረሰ መጽሐፈ ዘይሰመይ መጽሐፈ ብርሃን ወመጽሐፈ ሰዓታት ዘመዓልት ወዘሌሊት**<br>ወዓዲ ደረሰ መጽሐፈ ስብሐት ዘመዓልት ወዘሌሊት ዘለለሰዓቱ ወዘዘጾታሁ፡፡ ወዝ ሰመዮ መጽሐፈ ብርሃን፡፡ | ፲፫ | **መጽሐፈ ብርሃን የሚባል መጽሐፍንና የቀንና የሌሊት ሰዓታት መጽሐፍን እንደደረሰ፡፡**<br>ዳግመኛም በየሰዓቱና በየሥርዐቱ የሚጸለይ የምስጋና መጽሐፍን ደረሰ፡፡ ስሙን መጽሐፈ ብርሃን ብሎ ጠራው፡፡ |
| ፲፬ | እስመ ውእቱ ያበርህ ወያርኢ ፍናወ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር ወፍናወ ስብሐቲሆሙ ለትጉሃን ወለኲሎሙ ማኅበረ ቅዱሳን ልቡሳነ ብርሃን፡፡ | ፲፬ | እርሱ የእግዚአብሔርን የጌትነት፣ መንገድ የትጉሃንን ምስጋናና ብርሃንን የለበሱ የሁሉንም ቅዱሳን አንድነት መንገድ ያሳያልና፡፡ |
| ፲፭ | ወዓዲ ይነግር እንዘ ያስተሐውዝ ውዳሴሃ ለድንግል ንጽሕት ወሰመያ መርዓተ አብ ወእመ በግዑ ለታቦተ መንፈስ ቅዱስ ወአክሊለ ቅድስት ቤተክርስቲያን፡፡ | ፲፭ | ዳግመኛም የንጽሕት ድንግል ምስጋናን / እያሳመረ/ እያስማማ ይናገራል፡፡ የአብ ሙሽራ፣ የበግዑ እናት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘውድ ብሎ ጠራት፡፡ |
| | **ዘከመ ተሰይመ ንቡረ እድ ዘደብረ ዳሞ** | | **የደብረ ዳሞ ንቡረ እድ በመሆን እንደ ተሾመ** |
| ፲፮ | ወኮነ በአሐቲ እመዋዕል እንዘ ይጸውር አቡነ ጊዮርጊስ ምሥዋዐ ቊርባን ወፅአ ካህን ከመ ይመጡ ለሕዝብ፡፡ ወይቤሎ ለአቡነ ጊዮርጊስ ወንሑር ኀበ ንግሥት ከመ ንመጥዋ ቊርባነ፡፡ | ፲፮ | ከዕለታትም በአንድ ቀን እንዲህ ሆነ አባታችን ጊዮርጊስ የቊርባኑን መሠዊያ ይዞ ለሕዝቡ ያቀብል ዘንድ ካህኑ ወጣ፡፡ አባታችን ጊዮርጊስንም ንግሥቲቱን እናቆርባት ዘንድ እንሒድ አለው፡፡ |
| ፲፯ | ወአቡነሰ ጊዮርጊስ አበየ ወይቤሎ ትትነሣእ ወትምጻእ ዝየ እስመ ንጉሠ ነገሥታት ውእቱ ዝንቱ ቊርባን፡፡ እስመ ልማድ ኮነ እምቅድመ ዝ ይወስዱ ቊርባነ ለንግሥታት ኀበ ሀለዋ ነቢሮን፡፡ | ፲፯ | አባታችን ጊዮርጊስ ግን አይሆንም ይኸ ቊርባን ንጉሠ ነገሥት ነውና ተነሥታ ከዚህ ትምጣ አለው፡፡ ከዚያ በፊት ንግሥታቱ ካሉበት ወስደው የማቊረብ ልማድ ነበርና፡፡ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳ | ወነገርዎ ለንጉሥ ዳዊት መፍቀሬ እግዚአብሔር ወሠምረ በዝንቱ ወአዘዘ ከመ ትግበር ፈቃዶ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡ | ፳ | እግዚአብሔርን ለሚወድድ ለንጉሥ ዳዊትም ነገሩት እርሱም በዚህ ተስማማ፡፡ የአባታችን ጊዮርጊስም ፈቃድ ታደርግ ዘንድ አዘዘ፡፡ |
| ፳፩ | ወእም ይእቲ ዕለት ይመጽኣ ንግሥታት እምቅዋምን ከመ ይትመጠዋ ቍርባነ ምስለ ሕዝብ ወእምድኅረዝ ሤሞ ንጉሥ ለአቡነ ጊዮርጊስ ንቡረ እድ ዘደብረ ዳሞ፡፡ | ፳፩ | ከዚያችም ቀን ጀምሮ ንግሥቲቱ ከሕዝቡ ጋር ሥጋውንና ደሙን ይቀበሉ ዘንድ ከመቋሚያቸው ይመጡ ነበር፡፡ ከዚያም ንጉሡ አባታችን ጊዮርጊስን የደብረ ዳሞ ንቡረ እድ አድርጎ ሾመው፡፡ |
| ፳፪ | ወበአሐዱ ዕለት ሖረ አቡነ ጊዮርጊስ ኀበ ሳሙኤል ዘዋልድባ ከመ ይንሣእ በረከቶ፡፡ ወተለውዎ ፫ መስተፅዕናነ አብልቅት፡፡ | ፳፪ | አንድ ቀንም አባታችን በረከቱን ይቀበል ዘንድ ወደ ሳሙኤል ዘዋልድባ ሔደ፡፡ ፫ በቅሎዎችን የጫኑ ሰዎችም ተከተሉት፡፡ |
| ፳፫ | ወሶበ ርእዮ ሳሙኤል ጻድቅ በዝኩሉ ግርማ አምሰሎ ከመ ሰብአ ዓለም ውእቱ እስከ ኢተወከፎ፡፡ ወአቡነሰ ጊዮርጊስ ኮነ የዋህ ወትሑተ በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል ጹሩ አርዑትየ ላዕሌክሙ ወተመሀሩ እምኔየ ወአእምሩ እስመ የዋህ አነ ወትሑት ልብየ፡፡ | ፳፫ | ጻድቁ ሳሙኤልም በዚህ ሁሉ ግርማ ባየው ጊዜ አልቀበለውም እስከ ማለት ደርሶ እንደ ዓለም ሰው አስመሰለው፡፡ አባታችን ጊዮርጊስ ግን ጌታችን በወንጌል "ቀንበሬ በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔ ተማሩ፣ እኔ የዋህ እንደሆንሁ ልቤም ትሑት እንደሆነ ዕወቁ" እንዳለ የዋህና ትሑት ሆነ፡፡ ማቴ.፲፩፥፳፱ |
| ፳፬ | ወበእንተ ዝንቱ ቃል ኢተምዕዐ ወኢትቆጥዐ፡፡ ወባሕቱ ነገፈ ጸበለ እገሪሁ ወሖረ፡፡ በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል ወኀበ ቦእክሙ ቤት ቅድመ ወበሉ ሰላም ለሰብአ ዝንቱ ቤት፡ | ፳፬ | ስለዚህም ቃል አልተቆጣም፤ ነገር ግን የእግሩን ትቢያ አራግፎ ሔደ፡፡ ጌታችን በወንጌል "ወደገባችሁበት ቤት አስቀድማችሁ ለዚህ ቤት ሰዎች ሰላም ይሁን በሉ፡፡ |

፳፭ ወእመቦ በህየ ወልደ ሰላም ያዕርፍ ሰላምክሙ ላዕሌሆሙ ወእመ አኮሰ ይግባእ ሰላምክሙ፡፡ ወበይእቲ ሰዓት ከሠተ ሎቱ እግዚአብሔር ለአቡነ ሳሙኤል ኵሎ ትሩፋቲሁ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡

፳፭ ከዚያ የሰላም ልጅ ቢኖር ሰላማችሁ ይደርበት ያለዚያ ሰላማችሁ ይመለስላችኋል” እንዳለ ሉቃ.፲፥፭ በዚያችም ሰዓት እግዚአብሔር የአባታችን ጊዮርጊስን ትሩፋት ሁሉ ለአባታችን ሳሙኤል ገለጸለት፡፡

፳፮ ወተከዘ በእንተ ዘኢያብአ ወለአከ ረድኦ እንዘ ይብል ስረይ ሊተ ኦ እኁየ ገብረ እግዚአብሔር፡፡ አእመርኩ አነ ከመ ብእሴ እግዚአብሔር አንተ ወከመ ትፈርሆ ወፍቅረ ማርያምሂ ከመ ሀሎ ብከ፡፡ ወሰአሎ ከመ ይትመየጥ ኀቤሁ፡፡

፳፮ ስላላስገባውም አዘነ፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ወንድሜ ሆይ ይቅር በለኝ አንተ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆንህ እንደምትፈራውም የማርያምም ፍቅር እንዳለህ እኔ ዐወቅሁ ብሎ ደቀ መዝሙሩን ላከ፤ ወደ እርሱም ይመለስ ዘንድ ለመነው፡፡

፳፯ ወአቡነሰ ጊዮርጊስ ኢተመይጠ አኮ አስሕሮተ ሎቱ አላ ላዕለ ፍናው ጐጕአ ከመ ይስብክ ሃይማኖተ ለሰብአ ዳሞ፡፡

፳፯ አባታችን ጊዮርጊስ ግን አልተመለሰም፡፡ እርሱን ንቆት አይደለም ለዳሞ ሰዎች ወንጌልን ያስተምር ዘንድ ስለቸኮለ ነው እንጂ፡፡

፳፰ በከመ ይቤ እግዚእነ ለአርዳኢሁ ኢትትአምኁ መነሂ በውስተ ፍኖት፡፡ ወባሕቱ ለአከ ኀቤሁ እንዘ ይብል ይስረይ ለከ እግዚአብሔር ኦ አቡየ አንሰ ብእሲ ኀጥእ፡፡

፳፰ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን በመንገድ “ማንንም ሰላም አትበሉ” እንዳለ፡፡ ሉቃ.፲፥፬ ነገር ግን አባቴ ሆይ እኔ ኀጢአተኛ ነኝ እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ ብሎ ወደ እርሱ ላከ፡፡

፳፱ እምይእዜሰ ኢትስድዶሙ ለእለ ይመጽኡ ኀቤከ መሃይምናን ከመ ይንሥኡ በረከተከ፡፡ እስመ ይብል መጽሐፍ ጸሎተ ጻድቅ ትክል ወታሠልጥ፡፡ ወአነሂ እስከ እመጽእ ኀቤከ ኢትርስዐኒ በጸሎትከ፡፡ ወዘንተ ብሂሎ ሖረ፡፡

፳፱ ከአሁን በኋላ በረከትህን ይቀበሉ ዘንድ ወደ አንተ የሚመጡ ምእመናን አትመልሳቸው፡፡ መጽሐፍ “የጻድቅ ሰው ጸሎት ግዳጅ ትፈጽማለች ብሏልና፡፡ ያዕ.፭፥፲፮ እኔም ወደ አንተ እስከመጣ ድረስ በጸሎትህ አትርሳኝ፤ ይህንም ብሎ ሔደ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፴ | እምድኅረ ሞተ በጽሐ ኀበ መቃብሩ ተሳለመ ወአንገርገረ ወይቤ «በሠቀ ጸጕር ገዚፍ ያስሕከ ሥጋሁ አባ ሳሙኤል ዘምዑዝ ምንኩስናሁ አራዊተ ገዳም ሥንአሁ ይትጋነዩ ቅድሜሁ አካለ አንበሳ ግሩመ ይመጥን በእዴሁ፡፡»[1] | ፴ | ከሞተም በኋላ ወደ መቃብሩ ሔደ፤ ወድቆም ተሳለመ፤ ምንኩስናው የተወደደ አባ ሳሙኤል በማቅ ሥጋውን ያሻክራል /ያከሳል/ ከእርሱ ጋር የተሰማሙ የዱር አራዊትም በፊቱ ይገዛሉ የሚያስፈራ የአንበሳ አካልንም በእጁ ይለካል፡፡"[1] አለ፡፡ |
| ፴፩ | ወእምድኅረ ወደሶ ብዙኀ በዘከመዝ አርአያ ነገር አተወ ኀበ ማኅደሩ ነሢአ በረከተ እመቃብሩ፡፡ | ፴፩ | በዚህ ዓይነትም ብዙ ካመሰገነው በኋላ ከመቃብሩ በረከትን ተቀብሎ ወደ ቦታው ተመለሰ፡፡ |
| ፴፪ | ስምዑ እንከ አ አኃውየ ወበአሐተ ዕለት እንዘ ይትከሀን አቡነ ጊዮርጊስ ወረደ ደብተራ ብርሃን ከመ እንተ እሳት፡፡ | ፴፪ | ወንድሞቼ ሆይ ስሙ፤ አንድ ቀንም አባታችን ጊዮርጊስ ሲያገለግል የብርሃን ድንኳን እንደ እሳት ወረደ፡፡ |
| ፴፫ | ወከደና ለቤተ ክርስቲያን ቅድስት ወሰበ ርእዩ ሰብአ ይእቲ ሀገር መሰሎሙ ዘውእየት፡፡ ወሖሩ እንዘ | ፴፫ | ቅድስት ቤተ ክርስቲያንንም ሸፈናት፤ የዚያች ሀገር ሰዎችም ባዩ ጊዜ የተቃጠለች መሰላቸው፡፡ ውኃም ተሸክመው |
| ፴፬ | ወበጽሑ ኀበ ይእቲ ቤተ ክርስቲያን ወበጊዜሃ ተኀብአሙ ውእቱ ብርሃን፡፡ አንከሩ ወሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ወረከብዋ ለይእቲ ቤተ ክርስቲያን በከመ ኮነት ቀዳሚ፡፡ | ፴፬ | ወደዚያቺም ቤተ ክርስቲያን ደረሱ ያን ጊዜም ብርሃኑ ተሰወራቸው፤ አደነቁ፣ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ፡፡ ያቺንም ቤተ ክርስቲያን እንደ ቀድሞዋ ሁና አገኟት፡፡ |
| ፴፭ | ወነሥኡ ቊርባነ በእዴሁ ለጻድቅ ዘኢኀለዩ በልቦሙ እስመ ኢጋስተጋብአሙ በይእቲ ዕለት ኀይለ ጸሎቱ ለአቡነ ጊዮርጊስ ከመ ይንሥኡ በረከቶ፡፡ | ፴፭ | በልቡናቸው ያላሰቡት ሥጋውንና ደሙንም በጻድቁ እጅ ተቀበሉ፡፡ በዚያች ዕለት በረከቱን ይቀበሉ ዘንድ የአባታችን ጊዮርጊስ የጸሎቱ ኀይል ሰብስቧቸዋልና፡፡ |

*1. ድርሰቱ የማኅሌት ክፍል ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው አባ ጊዮርጊስ በቅዱስ ያሬድ የዜማ መሠረትነት ለአቡነ ሳሙኤል ዜማ መድረሱንና ለቅድስናውም ዕውቅና መስጠቱን ነው፡፡ በተለይ ከመካነ አጽሙ ደርሶ በረከትን መቀበሉ ለጻድቁ ለአቡነ ሳሙኤል ያለውን ታላቅ ከበሬታ ያሳያል፡፡ ይህንንም በመጽሐፈ ሰዓታቱ ላይ ገልጦታል፡፡*

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፴፯ ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘከፈሎሙ ሥጋሁ ወደሞ ለምእመናኒሁ በእደ ገብሩ ምእመን፡፡
ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፮
### ዘከመ ደረሰ ቅዳሴያተ

፩ ወበአሐቲ ዕለት እንዘ ይጼሊ አቡነ ጊዮርጊስ በከመ ያለምድ ግብተ አስተርአይዎ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ወይብልዎ ኤጺፋንዮስሃ መምህረ አሕዛብ ሜመከ ክርስቶስ፡፡

፪ አንበሩ እዴሆሙ ላዕሌሁ ወባረክዎ ወነፍሑ ውስተ ገጹ በከመ ይገብሩ ሥርዐተ ጳጳሳት ወእምድኅረዝ ዐርጉ ውስተ ሰማያት በስብሐት ዘኢይትነገር፡፡

፫ ወበአሐቲ እመዋዕል መጽአ አሐዱ አይሁዳዊ ወተዋሥአሙ ለክርስቲያን እንዘ ይብል ንግሩኒ ገጹ ለእግዚአብሔር መንገለ ዓይ ፍና ውእቱ፡፡ ወአልቦ ዘክህለ ተሰጥዎቶ፡፡

፬ ወአቡነሰ ጊዮርጊስ ከሠተ አፉሁ ወይቤ አኮ ዘቦቱ ለመለኮት ግድም ወኑኀ ላዕል ወታሕት የማን ወጸጋም አላ ምሉዕ ውእቱ በኵለሄ፡፡ ወአኮ ዘቦቱ እንግድዓ እንተ ፍጽም ወዘባን እንተ ድኅር፡፡ አላ ውስተ ኵሉ በሐውርት መለኮቱ በከመ ጽሑፍ፡፡

፴፯ በታመነ በአገልጋዩ እጅ ለምእመናን ሥጋውንና ደሙን /ላደለ/ ለሰጠ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡፡
ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን።

## ምዕራፍ ስድስት
### ቅዳሴያትን እንደ ደረሰ

፩ አንድ ቀንም አባታችን ጊዮርጊስ እንዳስለመደው ሲጸልይ ጴጥሮስና ጳውሎስ ድንገት ተገለጹለት ክርስቶስ እንደ ኤጺፋንዮስ የአሕዛብ መምህር አድርጎ ሾመህ አሉት፡፡

፪ እጃቸውንም በራሱ ላይ አስቀመጡ/ ጫኑ/፤ ባረኩትም በጳጳሳትም ሥርዐት እንደሚያደርጉ በፊቱ እፍ አሉበት፡፡ ከዚህም በኋላ በማይነገር ምስጋና ወደ ሰማያት ዐረጉ፡፡

፫ ከዕለታት አንድ ቀንም አንድ አይሁዳዊ መጣ፡፡ የእግዚአብሔር ፊቱ ወዴት ነው ንገሩኝ? እያለ ክርስቲያኖችን ተከራከራቸው፡፡ ሊመልስለት የቻለ ሰውም አልተገኘም፡፡

፬ አባታችን ጊዮርጊስ ግን አፉን ገልጦ ለመለኮት ወርድና ቁመት፣ ላይና ታች፣ ቀኝና ግራ፣ ያለው አይደለም፡፡ በአራቱ ማዕዘን ምሉዕ ነው እንጂ፡፡ ለመለኮት በፊቱ ደረት በኋላውም ጀርባ ያለው አይደለም እንደተጻፈ መለኮቱ በሁሉ የመላ ነው እንጂ አለ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፭ | ወእምብዝኃ ፍሥሓሁ አምኖ ጳጳስ ወባረኮ ወአብሖ ከመ ይድርስ ቅድሴያተ፡፡ | ፭ | ጳጳሱም ከደስታው ብዛት የተነሣ ሳመው ባረከው ቅዳሴንም እንዲደርስ ፈቀደለት፡፡ |
| ፮ | ወእምአሜሃ አኀዘ ይድርስ ጸሎተ ፈትቶ ዘዕውቅ በኀበ አኃው እስመ ተበውሐ እምሊቃነ ካህናት፡፡ በከመ ተበውሐ ሐናንያ ዲያቆን ለአጥምቆተ ጳውሎስ፡፡ | ፮ | ከዚያም ጀምሮ በወንድሞች ዘንድ የታወቀ ጸሎተ ፈትቶን /የፍታቴ ጸሎትን/ ይደርስ ጀመረ፡፡ ከሊቀ ካህናት ተፈቅዶለታልና፡፡ ዲያቆኑ ሐናንያ ጳውሎስን ለማጥመቅ እንደተፈቀደለት፡፡ |
| ፯ | ወበአሐቲ ዕለት ሶበ ሰምዐ አሐዱ ብእሲ በቤተ ክርስቲያን እንዘ ይቄድሱ ጸሎተ ፈትቶ ዘአቡነ ጊዮርጊስ፡፡ ናፈቀ በኀሊናሁ ወይቤ ምንትኑ ዝንቱ ቅዳሴ ዘኢተፈነወ እምኀበ ሐዋርያት ወኢእምሊቃነ ጳጳሳት፡ | ፯ | አንድ ቀንም አንድ ሰው የአባታችን ጊዮርጊስን ጸሎተ ፈትቶ በቤተ ክርስቲያን ሲቀድሱበት በሰማ ጊዜ በአሳቡ ተጠራጠረ፡፡ ከሐዋርያትና ከሊቃነ ጳጳሳት ያልተላከ ይህ ቅዳሴ ምንድን ነው? አለ፡፡ |
| ፰ | ወውእቱሰ ብእሲ ነበረ እንዘ ይጸልእ ወይጽዕሎ ወኢያከብሮ፡፡ ወተምዕዐ እግዚአብሔር በላዕለ ውእቱ ብእሲ፡፡ ወተከዕወ አማዑቲሁ ኀበ ነበረ ውስተ ቤተ ማይ በከመ ተከዕወ አማዑቲሁ ለአርዮስ፡፡ | ፰ | ያም ሰው እየጠላውና እየሰደበው ሳያከብረው ኖረ፡፡ በዚያም ሰው ላይ እግዚአብሔር ተቈጣበት፡፡ የአርዮስ አንጀት ተዘርግፎ እንደወጣ በመጸዳጃ ቤት በተቀመጠበት አንጀቱ ተዘርግፎ ወጣ፡፡ |
| ፱ | ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘይትቤቀል ፀሮሙ ለአግብርቲሁ ኄራን፡፡ | ፱ | የተመረጡ የአገልጋዮቹን ጠላት ለሚበቀል እግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡፡ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲ ወካዕበ ስምዑ አኀውየ ዜናሁ ለአቡየ ጊዮርጊስ ዘነገረኒ ፩ ብእሲ እስራኤላዊ ዘስሙ ዕዝራ እም አዝማዲሁ እለ በሥጋ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡ ወተምህረ ምስሌሁ ውስተ ፩ መካን ብእሲ ማእምር ለአንብቦ መጻሕፍት ወትርጓሜሆን፡፡

፲ ዳግመኛም ወንድሞቼ ሆይ በሥጋ ከአባታችን ጊዮርጊስ ወገኖች የሆነ ስሙ ዕዝራ የተባለ እስራኤላዊ ሰው የነገረኝን ነገር ስሙ፡፡ በአንድ ቦታም የመጻሕፍትን ንባባቸውንና ትርጓሜያቸውን ከእርሱ ጋር የተማረ ዐዋቂ ሰው ነበር፡፡

፲፩ ይቤ ውእቱ ብእሲ በአሐቲ ዕለት በዕለተ ሰንበት ጊዜ መንፈቀ መዓልት እንዘ ይነውም አቡነ ጊዮርጊስ ሰማዕኩ እንዘ ያነብብ ቃለ እግዚአብሔር ዘኢሀሎ ውስተ መጽሐፈ ብሉይ ወሐዲስ እም ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት እስከ ጊዜ ተሰዓቱ ሰዓት፡፡

፲፩ ያም ሰው አንድ ቀን በሰንበት ዕለት አባታችን ጊዮርጊስ በቀኑ እኩሌታ ተኝቶ ሳለ ከብሉይና ከሐዲስ መጽሐፍ የሌለውን በእግዚአብሔር ቃል ከሦስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ሲያነብብ ሰማሁት አለ፡፡

፲፪ ወሰሚዕየ ደንገፀኒ ልብየ ወርእደ ብረክየ እምኀይለ ነገሩ፡፡ ወሶበ ነቅሐ ወተንሥአ ተወለጠ ርእየተ ገጹ በከመ ተወለጠ ርእየተ ገጹ ለሙሴ ሊቀ ነቢያት እስከ ስእኑ ደቂቀ እስራኤል ነጽሮቶ፡፡ ዘፀ.፴፬፥፳፱-፴፩

፲፪ ሰምቼም ከነገሩ ኀይለ ቃል የተነሣ ልቤ ደነገጠብኝ፤ ጉልበቴም ተብረከረከ / ተንቀጠቀጠ/፡፡ በነቃና በተነሣ ጊዜም የእስራኤል ልጆች ማየት እስኪሳናቸው ድረስ የነቢያት አለቃ የሙሴ ፊት እንደተለወጠ የፊቱ መልክ ተለወጠ፡፡ ዘፀ.፴፬፥፳፱-፴፩

፲፫ ከማሁ አነኒ ፈራህኩ ወስእንኩ ነጽሮቶ ወጐየይኩ ንስቲተ፡፡ ወጸውዕኒ እንዘ ይብል ዕዝራ ወሶበ ተመየጥኩ ረከብኩ ገጾ ከመ ትካት፡፡ አኮ በይእቲ ዕለት ባሕቲቱ ዘይትናገር ነገረ እግዚአብሔር አቡነ ጊዮርጊስ አላ በኩሉ ዕለት ወበኩሉ ሰዓት፡፡ ኢያፀርእ ነቢበ ቃለ እግዚአብሔር

፲፫ እኔም እንዲሁ ፈራሁ፤ ማየትም ተሳነኝና ትንሽ ሸሸሁ፤ ዕዝራ! እያለም ጠራኝ በተመለስሁም ጊዜ ፊቱን እንደቀድሞው አገኘሁት፡፡ አባታችን ጊዮርጊስም የእግዚአብሔርን ነገር የሚናገር በዚያች ዕለት ብቻ አይደለም በሁሉም ዕለትና ሰዓት የእግዚአብሔርን ቃል ከመናገር አያቋርጥም ነበር፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፬ ወከመ ፈለገ ዐባይ ዘኢይነጽፍ ውሒዙ፡፡ ከማሁ ኢይነጽፍ ውኂዘ መንፈስ ቅዱስ እምአፉሁ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡

፲፬ የዐባይ ውኃ ምንጩ ከመፍሰስ እንዳያቋርጥ እንዳይደርቅ እንዲሁ የመንፈስ ቅዱስ ምንጭ ከአባታችን ጊዮርጊስ አፍ አይነጽፍም /አይቋረጥም/፡፡

፲፭ ሶበሰ ተጽሕፈ ኲሉ ዘነበቦ እምኢያግመሮ ዓለም፡፡ ስብሐት ለእግዚአብሔር ከሃሌ ኲሉ ወገባሬ ኲሉ ሠናያት ዘይሁብ መጠነዝ ጸጋ ለፍቁራኒሁ፡፡

፲፭ የተናገረው ሁሉ ተጽፎ ቢሆን ዓለም ባልቻለውም ነበር፡፡ ለወዳጆቹ ይህን ያህል ጸጋ የሰጠ ሁሉን ቻይና በጎ ነገርን ሁሉ ለፈጠረ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡፡

፲፮ ስምዑ ካዕበ ንንግርክሙ አኃዊነ መሃይምናን እስመ በ መናስዉ ዘይከውን እም ጸብዐ ሰይጣን፡፡ ወበአሐቲ ዕለት ተንሥአ ብእሲ አይሁዳዊ ርኩሰ ሃይማኖት ላዕለ ሰብአ ቤተ ክርስቲያን፡፡

፲፮ የምታምኑ ወንድሞቻችን ሆይ ከሰይጣን የሚሆን ፈተና አለና፡፡ እንነግራችሁ ዘንድ ስሙ፡፡ አንድ ቀንም ሃይማኖቱ የረከሰ አይሁዳዊ ሰው በቤተ ክርስቲያን ምእመናን ላይ ተነሣ፡፡

፲፯ ወይቤሎሙ ንዑ ንትዋሣእ በቃለ መጻሕፍት፡፡ እመ ሞእክሙኒ አብኡኒ ውስተ ሃይማኖትክሙ ወእመ ሞእኩክሙ ባኡ ውስተ ሃይማኖትየ፡፡ ወእሙንቱሂ ይቤልዎ እሆ፡፡

፲፯ ኑ በመጻሕፍት ቃል እንከራከር፤ ከረታችሁኝ ወደ ሃይማኖታችሁ አስገቡኝ፤ ከረታኋችሁም ወደ ሃይማኖቴ ግቡ አላቸው፤ እነርሱም እሺ አሉት፡፡

፲፰ ወሶበ ሰምዐ ዳዊት ንጉሥ መፍቀሬ እግዚአብሔር ነደ ልቡ በእሳተ ሃይማኖት፡፡ ወአስተጋብአ ኀቤሁ ኲሎ ሊቃነ ካህናት ወንቡራነ እድ ወኲሎ ማእምራነ መጻሕፍት ዘውስተ ኲሉ ሀገር፡፡

፲፰ እግዚአብሔርን የወደደ ንጉሥ ዳዊትም በሰማ ጊዜ ልቡ በሃይማኖት እሳት ተቃጠለ፡፡ የካህናት አለቆችን፣ ንቡራነ እድን፣ በአገሩ ሁሉ ያሉ መጻሕፍትን የሚያውቁትን ሁሉ ሰበሰበ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፱ ዐቀሞ ለአይሁዳዊ በባሕቲቱ ወለመሃይምናንሂ እንተ ባሕቲቶሙ፡፡ ወይቤሎ ለአይሁዳዊ ንብብ ቃለከ ከመ አስተኀፍርከ ፍጡነ፡፡

፲፱ አይሁዳዊውን ለብቻው ምእመናንንም ለብቻቸው አቆማቸው፡፡ አይሁዳዊውንም ፈጥኜ አሳፍርህ ዘንድ ቃልህን ተናገር አለው፡፡

፳ ወሶቤሃ ተሰጥወ አይሁዳዊ ወይቤ ዝንቱ ክርስቶስ ዘትብልዎ አንትሙ ወልደ እግዚአብሔር እስመ ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ እምአእምረኑ ኀበ ቀበርዎ ለአልአዛር፡፡

፳ አይሁዳዊውም መለሰ እናንተ የእግዚአብሔር ልጅ የምትሉት ይህ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነውና አልአዛርን የቀበሩበትን ባወቀ ነበር አለ፡፡

፳፩ እስመ በወንጌልከሙ ይቤ ወሶበ በጽሐ ኢየሱስ ቢታንያ ይቤ አይቴ ቀበርክምዎ ለአልዓዛር፡፡ ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ግብር ዘይትኀብኦ እስመ ኲሉ ስጡሕ ቅድመ አዕይንቲሁ፡፡ ናሁ ነበብኩከሙ ወእምገጸ ክፍል ዘወንጌልከሙ ወአኮ እምኦሪትየ በሉኬ አውሥኡኒ፡፡

፳፩ በወንጌላችሁ ኢየሱስ ቢታንያ በደረሰ ጊዜ አልዓዛርን ወደት ቀበራችሁት አለ፤ ይላልና፡፡ እግዚአብሔርን ግን የሚሰወረው ሥራ የለም፡፡ ሁሉ በዐይኖቹ ፊት የተገለጠ ነውና እነሆ በእኔ ኦሪት ያይደለ በወንጌላችሁ ክፍል ነገርኋችሁ፤ በሉ መልሱልኝ፡፡

፳፪ ወሶበ ሰምዑ ዘንተ አልቦ ዘክህለ ተሰጥዎቶ ቃለ ወኢአሐዱኒ እስመ ሰይጣን አፆረ አዕይንቲሆሙ ከመ ኢይርአዩ ስብሐተ እግዚአብሔር፡፡

፳፪ ይህንም በሰሙ ጊዜ አንዱ እንኳ ቃልን መመለስ የቻለ የለም፡፡ የእግዚአብሔርን ክብር /ጌትነት/ እንዳያዩ ሰይጣን ዐይናቸውን አሳውሮታልና፡፡

፳፫ ወእምድኅረዝ ኀሠሥዎ ማእከሌሆሙ ለአቡነ ጊዮርጊስ ወኢረከብዎ፡፡ እስመ ነበረ ውስተ ማኅደሩ እንዘ ይደዊ፡፡

፳፫ ከዚህም በኋላ አባታችን ጊዮርጊስን በመካከላቸው ፈለጉት አላገኙትም ታሞ በቤቱ ነበርና፡፡

# <u>ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ</u>

፳፬ ወነገርዎ ለንጉሥ በእንቲአሁ ወሶቤሃ ለአከ ንጉሥ ዐበይተ መንግሥቱ ከመ ያምጽእዎ፡፡ ወአብጽሕዎ ፍጡነ እንዘ ይጸውርዎ በዓራት ወአስከብዎ ማእከሌሆሙ፡፡

፳፬ ስለ እርሱም ለንጉሡ ነገሩት ያን ጊዜም ንጉሡ ያመጡት ዘንድ የቤተ መንግሥቱን ሹማምንት ላከ፡፡ በአልጋ ተሸክመው ፈጥነው አወጡት በመካከላቸውም አስተኙት፡፡

፳፭ ወሰሚዖ ቃሎ ለአይሁዳዊ ይቤ አቡነ ጊዮርጊስ አነሂ ኢይትዋሣእከ በወንጌልየ ዘእንበለ አላ በኦሪትከ፡፡ እስመ መጽሐፍሰ ለምኲራብ ወተዐውቆ ለቤተ ክርስቲያን፡፡ ምኲራብ ዘርዐት ወቤተ ክርስቲያን አረረት፡፡ ምኲረብ አነመት ፀምረ ወቤተ ክርስቲያን ተዐጽፈቶ፡፡

፳፭ አባታችን ጊዮርጊስ የአይሁዳዊውን ቃል ሰምቶ እኔም በእኔ ወንጌል አልከራከርህም፡፡ በአንተ ኦሪት ነው እንጂ አለ "ትንቢት ለምኲራብ ሃይማኖት ለቤተ ክርስቲያን ነውና ምኲራብ ዘርን ዘራች ቤተ ክርስቲያን ምርቱን ሰበሰበች፡፡ ምኲራብ ግምጃን ሠራች ቤተ ክርስቲያን ለበሰችው" ሃ. አበው ምዕ.፳፮፥፳፩

፳፮ በልኬ አውሥአኒ አ አይሁዳዊ መኑኬ ዘይቤሎ ለአዳም በውስተ ገነት አይቴ ሀሎከ አዳም መኑ ወዘይቤሎ ለአብርሃም አይቴ ሣራ ብእሲትከ፡፡

፳፮ አይሁዳዊ ሆይ እስቲ በል መልስልኝ አዳምን በገነት "አዳም ወዴት አለህ? አብርሃምንስ ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት? ያለው ማን ነው? ዘፍ.፩፥፱፣ ፲፰፥፱

፳፯ ወመኑ ዘይቤሎ ለሰይጣን እምአይቴ መጻእከ፡፡ ወበካልእኒ ገጸ መጽሐፍ ይብል መኑ ያስሕቶ ሊተ ለአክአብ ትብልኑ እግዚአብሔር ወሚመ አልቦ፡፡ ኢዮ.፩፥፮፣ ፩ነገ.፳፪፥፳

፳፯ ሰይጣንንስ "ከወዴት መጣህ?" ያለው ማን ነው? በሌላም የመጽሐፍ ክፍል "አክአብን ማን ያስትልኛል?" ይላል፡፡ እግዚአብሔር ነው ትላለህ? ወይስ የለም? /ሌላ/ አለው፡፡ ኢዮ.፩፥፮፣ ፩ነገ.፳፪፥፳

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፷፫ ወሶቤሃ ተኃፍረ አይሁዳዊ ወአኃዞ ፍርሀት ወረአድ፡፡ ወአቡነሰ ጊዮርጊስ እስራኤላዊ ሐዲስ ተንሥአ ዲበ ምስካቢሁ ወጸፍአ ገጾ ለአይሁዳዊ ወፈትሐ ንጉሥ ዳዊት ላዕሌሁ ፍትሐ ሞት ወቀተልዎ፡፡

ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘይትቤቀል ፀሮ በእደ አግብርቲሁ፡፡

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፯

### በእንተ ቢቱ

፩ ወበውእቱ መዋዕል አንሥአ ሰይጣን ለ፩ ብእሲ ዘስሙ ቢቱ እንዘ ይብል «ይመጽእ ወልድ ባሕቲቱ ዘእንበለ አቡሁ» ወዓዲ ይብሉ በእንቲአሁ ለውእቱ ብእሲ ከመ ይገብር ሥራያተ ወይትናገሮ ሰይጣን ወይዛዋዕ ምስለ ኢጋንንት፡፡

፪ ወንጉሥሰ ያፈቅሮ ወኢየአምር እከያቲሁ ዳእሙ ይመስሎ ማእምረ መጻሕፍት፡፡ ወአቡነሰ ጊዮርጊስ ሶበ ሰምዐ ዕልወቶ ለቢቱ አንገሥገሠ በመንፈስ ቅዱስ ወፈልሐ ልቡ በሃይማኖት ወተናግሮ ለቢቱ ወተዋሥአ በቃለ መጻሕፍት፡፡ ወስእነ አሆ አብሎቶ፡፡ ወመይጦቶ ውስተ ሃይማኖት ርትዕት፡፡

፷፫ ያን ጊዜም አይሁዳዊ አፈረ፤ ፍርሀትና መንቀጥቀጥም ያዘው፡፡ አባታችን ሐዲስ እስራኤላዊ ጊዮርጊስ ግን ከአልጋው ተነሣ የአይሁዳዊን ፊት በጥፊ መታው፡፡ ንጉሥ ዳዊትም የሞት ፍርድንም ፈረደበት፤ ገደሉትም፡፡

በአገልጋዮቹ እጅ ጠላቱን ለሚበቀል ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡፡

ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

### ስለ ቢቱ

፩ በዚያም ዘመን ስሙ ቢቱ የሚባል አንድን ሰው ሰይጣን “ወልድ ብቻውን ያለ አባቱ ይመጣል” ሲል አስነሣው፡፡ ዳግመኛም ስለዚያ ሰው ሥራይን እንደሚያደርግ ሰይጣን እደሚናገረውና ከኢጋንንትም ጋር እንደሚጫወት ይናገራሉ፡፡

፪ ንጉሥ ግን ይወደው ነበር ክፋቱንም ዐያውቅም፡፡ መጻሕፍትን የሚያውቅ ይመስለው ነበር እንጂ፡፡ አባታችን ጊዮርጊስም የቢቱን ክሕደት በሰማ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተነሣሣ፤ ልቡ በሃይማኖት ፈላ /ነደደ፡፡ ቢቱን በሃይማኖት ተናገረው፡፡ በመጻሕፍት ቃልም ተከራከረው፡፡ እሺ ማሰኘትና ወደ ቀናች ሃይማኖቱም መመለስ ተሳነው፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፫ ወእምዝ ሖሩ ክልኤሆሙ ኀበ ንጉሥ ወቆሙ ቅድሜሁ፡፡ ወይቤ አቡነ ጊዮርጊስ እግዚእየ ንጉሥ ናሁ ቢቱ ዐሥረፀ ዕልወተ እምልቡ፡፡ ወጐሥዐ ዘይመርር እምሐሞት ወአስተርአዮሙ ለመሃይምናን እምሕምዘ ቃሉ፡፡

፫ ከዚያም በኋላ ሁለቱም ወደ ንጉሡ ሔደው ከፊቱ ቆሙ አባታችን ጊዮርጊስም ንጉሥ ሆይ እነሆ ቢቱ ከልቡ ክሕደትን አበቀለ ከሐሞት የሚመርር ነገርን ተናገረ ለምእመናንም በቃሉ መርዝ ታይቶአቸዋል፡፡

፬ ወይቤ ኢይመጽእ አብ ምስለ ወልዱ ለኮንኖ ሕያዋን ወምውታን፡፡ኢተዘኪሮ ዘይቤ መድኃኒነ ዘሰ አምነኒ በቅድመ ገጸ ሰብእ አአምኖ አነኒ በገጸ አቡየ ዘበሰማያት፡፡ወዘሰ ክሕደኒ በገጸ ሰብእ እክሕዶ አነኒ በቅደመ አቡየ ዘበሰማያት።

፬ አብ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ ከልጁ ጋር አይመጣም አለ፡፡ መድኃኒታችን ያለውን ሳያስብ “በሰው ፊት ያመነብኝን እኔም በሰማያዊ አባቴ ፊት አምነዋለሁ፤ በሰው ፊት የካደኝ ግን እኔም በሰማያት ባለ በአባቴ ፊት እክደዋለሁ፡፡ ማቴ.፲፥፴፪

፭ ወዓዲ ይቤ አቡነ ጴጥሮስ ወእመሰ ለአብ ትጼውዕዎ ለዘይኴንን ጽድቀ እንዘ ገጸ ኢይነሥእ፡፡ በበምግባሪሁ ወባእደኒ ዐቀመ ስምዐ እምቃለ መጻሕፍት ዘሐዲስ ወዘብሉይ በእንተ ምጽአቱ ለአብ ምስለ ወልድ፡፡

፭ ዳግመኛም አባታችን ጴጥሮስ ”ለእያንዳንዱ በየሥራው ፊት ሳይነሳ እውነት የሚፈርድ አብን የምትጠሩት ከሆነ” አለ ፩ጴጥ.፩፥፲፯ ሌላም ከብሉይና ከሐዲስ መጻሕፍት አብ ከልጁ ጋር ስለ መምጣቱ ምስክር አመጣለት፡፡

፮ ወቢቱኒ ይቤ አኮኑ ጽሑፍ ዘይብል በወንጌል አብሰ ኢይኴንን ወኢመነሂ አላ ኵነኔሁ አወፈዮ ለወልዱ፡፡ ወሰሚዖ ንጉሥ ነገረ ክልኤሆሙ ይቤ ዝሰ ነገር ኢይኩን ለባሕቲትነ አላ ዳእሙ ንልአክ ኀበ ጳጳስ ወይጼውዕዎ ወትትዋሥኡ በቅድሜሁ፡፡

፮ ቢቱም በወንጌል “አብ ከቶ በማንም አይፈርድ ፍርዱን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ” የሚል ጽሑፍ የለምን? አለ፡፡ ንጉሡም የሁለቱንም ነገር ሰምቶ ይህ ነገር ለእኛ ብቻ አይሁን ወደ ጳጳሱ እንላክ ይጥሩትና በፊቱ ትከራከራላችሁ አለ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፯ ወፈነወ ንጉሥ ላእካነ ኀበ ጳጳስ ይጸውዕዎ፡፡ ወምእድኅረ ዝንቱ ነገር ተመየነ ቢቱ ወጸሐፈ መጽሐፈ ሐሰት ወፈነወ ምስለ ልኡካን እንዘ ይብል ይቤ ጊዮርጊስ ዐለወ ንጉሥ ሃይማኖተ፡፡ አ አቡየ ጳጳስ ኢትምጻእኬ ወኢትሰጠዎ፡፡

፯ ንጉሡም ይጠሩት ዘንድ ወደ ጳጳሱ መልእክተኞችን ላከ ከዚህም ነገር በኋላ ቢቱ በተንኮል የሐሰት መጽሐፍ ጽፎ አባቴ ጳጳስ ሆይ አትምጣ መልስም አትመልስለት ጊዮርጊስ ንጉሡ ሃይማኖቱን ካደ አለ ብሎ በመልእክተኞች ላከ፡፡

፰ ወካዕበ ቦአ ኀበ ንጉሥ ወአስተዋደዮ ወይቤ ለአከ ጊዮርጊስ ኀበ ጳጳስ በእንቲአከ እንዘ ይሰምየከ ዓላዌ፡፡ ወለእመ ኢአመንከኒ ፈኑ ኀበ ልኡካን ከመ ያግብእዎሙ እስመ እምኀቤሆሙ ሀሎ መጽሐፈ መልእክት፡፡

፰ ዳግመኛም ወደ ንጉሡ ገብቶ አጣላው፤ ጊዮርጊስ አንተን ከሐዲ ብሎ ወደ ጳጳሱ ልኳል አለ፡፡ ካላመንኸኝም የሐሰት መልእክት ከእነርሱ ዘንድ አለና ይመልሷቸው ዘንድ ወደ መልእክተኞቹ ላክ አለ፡፡

፱ ወፈነወ ንጉሥ መልእክተ ወአብእዎሙ ለልኡካን ፍጡነ፡፡ ወእሙንቱሰ ነሥኡ ኅልያነ እምኀበ ቢቱ በከመ ሐራ ዓቀብተ መቃብሩ ለእግዚእነ እለ ነሥኡ ሕልያነ እምኀበ አይሁድ፡፡ ወመጠውዎ መጽሐፈ ሐሰት ለንጉሥ፡፡

፱ ንጉሡ መልእክት ላከ መልእክተኞችንም ፈጥነው መለሷቸው፡፡ እኒያም የጌታችን መቃብር የሚጠብቁ ወታደሮች ከአይሁድ መማለጃ እንደተቀበሉ ከቢቱ መማለጃ ተቀብለው የሐሰቱን መጽሐፍ ለንጉሡ ሰጡት፡፡ ማቴ.፳፰፥፲፪

፲ ወሶበ ነጸራ ንጉሥ ለይእቲ መጽሐፈ መልእክቱ ለቢቱ አዘዘ ይቅሥፍዎ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡ ወቀሠፍዎ እስከ ይትከዐው ደሙ ከመ ማይ ዲበ ምድር፡፡

፲ ንጉሡም ያቺን የቢቱን መልእክት ባያት ጊዜ አባታችን ጊዮርጊስን ይገርፉት ዘንድ አዘዘ፡፡ ደሙ በምድር ላይ እንደ ውኃ እስኪፈስስ ድረስ ገረፉት፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፩ ወመጽአ አሐዱ እምነ አግብርተ ንጉሥ ወዘበጦ እንተ አፉሁ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡ ወወድቀ ስነኒሁ ውስተ ምድር ከመ ዲዮስቆሮስ በውእቱ መዋዕል፡፡ ዛቲ ጽፍአት ትመስል ዘተወክፉ መድኀኒነ እምኀበ ገብረ ሊቀ ካህናት፡፡

፲፩ ከንጉሡ አገልጋዮችም አንዱ መጣ፡፡ የአባታችን ጊዮርጊስን አፉን መታው በዚያም ቀን እንደ ዲዮስቆሮስ ጥርስ ወደ ምድር ወደቀ፡፡ ይህችም መመታት መድኀኒታችን ከሊቀ ካህናቱ አገልጋይ የተቀበላትን መመታት ትመስላለች፡፡ ዮሐ.፲፰፥፳፪

፲፪ ወብፁዕሰ ጊዮርጊስ አውከፎ ለደሙ ውስተ እደዊሁ ወዘረወ ውስተ ዓየር ወኢተመይጠ ውስተ ምድር፡፡ ወይቤ ረስዮ እግዚአብሔር ለደምየ ከመ ደመ አቤል ጻድቅ ዘተከዕወ በግፍዕ፡፡ ዘፍ.፬፥፲

፲፪ ብፁዕ ጊዮርጊስ ግን ደሙን በእጁ ተቀብሎ ወደ ሰማይ ረጨው ወደ ምድርም አልተመለሰም እግዚአብሔር ሆይ ደሜን በግፍ እንደፈሰሰ እንደ አቤል ደም አድርግልኝ አለ፡፡ ዘፍ.፬፥፲

፲፫ ወእንዘ ይቀሥፍዎ ይትናገር ዕበያቲሁ ለእግዚአብሔር፡፡ ወኅሊናሁ ላዕለ ውስተ አርያም፡፡ ወይቤ ለሊሁ ብፁዕ ጊዮርጊስ እመኒ ለዓይነ ሰብእ ተቀሠፍኩ ሊተሰ ኢያሕመመኒ ዝብጠተ ቅሥፈታቲሁ፡፡ እስመ መላእክቲሁ ለአምላኪየ ይሜግቡኒ፡፡ ወቅዱሳን ይትዌከፉ ቅሥፈታትየ፡፡

፲፫ ሲገርፉትም የእግዚአብሔርን ቸርነት ይናገራል፡፡ አሳቡም በሰማይ ነበር፤ እርሱ ብፁዕ ጊዮርጊስ ለሰው ዐይን ከመገረፍም የምገረፈው ግርፋት አይሰማኝም የአምላኬ መላእክት ይመግቡኛልና ቅዱሳንም ግርፋቴን ይቀበላሉ፡፡

፲፬ ወእምድኅረዝ ወደይዎ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ወውእቱሰ አኀዘ ይጸሊ ኀበ እግዚአብሔር እንዘ ይዜከሮሙ ለቅዱሳን በበአስማቲሆሙ፡፡

፲፬ ከዚህም በኋላ ወደ እስር ቤት አስገቡት፤ እርሱ ግን ቅዱሳንን በየስማቸው እየጠራ ይጸልይ ጀመር፡፡

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፭ | ወበይእቲ ሌሊት አስተርአይዎ ኵሎሙ ሐዋርያት እንበለ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ ወብዙኃን እምነ ጻድቃን ናዘዝዎ ወተሰወሩ እምኔሁ፡፡ | ፲፭ | በዚያችም ሌሊት ከጌታ ወዳጅ ከዮሐንስ በስተቀር ሁሉም ሐዋርያት ተገለጹለት፡፡ ከቅዱስንም ብዙዎቹ አጽናኑት ከእርሱም ተሰወሩ፡፡ |
| ፲፮ | ወበይእቲ ዕለት ኀደገ ብፁዕ ጊዮርጊስ ዘከሮቶ ለዮሐንስ እምውስተ ጸሎት ዘተዘከሮሙ ለካልኣኒሁ አርዳእ፡፡ ወበካልእት ሌሊት መጽአ ኀቤሁ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ወይቤሎ ለምንት አስተትከ ዘከሮትየ እምነ አብያጽየ አርዳእ፡፡ | ፲፮ | በዚያችም ዕለት ብፁዕ ጊዮርጊስ በጸሎት የሌሎቹን ሐዋርያት ስም ሲጠራ የዮሐንስን ስም ተወ፡፡ በሁለተኛይቱም ሌሊት ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ወደ እርሱ መጣ ከሌሎቹ ሐዋርያት ለይተህ ስሜን ለምን አቃለልህ? አለው፡፡ |
| ፲፯ | ወይቤሎ ብፁዕ ጊዮርጊስ በይነምንት አንተሂ ዘኢያስተርአይከኒ ከመ አኃዊከ ሐዋርያት ወኢናዘዝከኒ እንዘ ፈድፋደ አፈቅረከ፡፡ | ፲፯ | ብፁዕ ጊዮርጊስም አንተስ እጅግ ስወድህ እንደ ወንድሞችህ ሐዋርያት ያልተገለጽህልኝና ያላረጋጋኸኝ ለምድን ነው? አለው፡፡ |
| ፲፰ | ወአክሞሰሰ ብፁዕ ዮሐንስ ወይቤሎ ኢትፍራህ እምይእዜሰ ዐልፀቀት መድኀኒትከ ወፍጡነ ታስተርኢ ጽድቅከ፡፡ ወነገሮ ብዙኀ ምሥጢራተ እለ ይከውና በበመትልው ወተሰወረ እምኔሁ፡፡ | ፲፰ | ብፁዕ ዮሐንስም ፈገግ ብሎ እንግዲህስ ድኅነትህ ደርሳለችና አትፍራ፤ ጽድቅህም ፈጥና ትገለጻለች፡፡ በተከታታይ የሚፈጸሙ ብዙ ምስጢራትንም ነገረው፡፡ ከእርሱም ተሰወረ፡፡ |
| ፲፱ | ወእምዝ አደሞሙ ንጉሥ በሠለስቱ ዕለት ከመ ይፈጽሙ ነገሮሙ እንዘ ይትጋብኡ ኵሎሙ ሊቃነ ካህናት ወንቡራነ እድ ወኵሎሙ ካህናት፡፡ ወሶቤሃ ፈነወ እግዚአብሔር መልአኮ ወቀሠፎ ለቢቱ ወሞተ ሞተ እኩየ፡፡ | ፲፱ | ከዚህም በኋላ ንጉሡ ሊቃነ ካህናት ንቡራነ እድ ሁሉም ካህናት ሲሰበሰቡ ነገራቸውን ይፈጽሙ ዘንድ በሦስተኛው ቀን ቀጠራቸው፡፡ ያንጊዜም እግዚአብሔር መልአኩን ላከ ቢቱን ቀሠፈው፡፡ ክፉ ሞትንም ሞተ፡፡ |

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፹ ወአዕረፈት ቤተ ክርስቲያን ወእም ሐውከ እከዩ ወዕልወቱ። ወዝ ውእቱ ፍካሬ ቃሉ ዘይቤ በውስተ መጽሐፉ ሊተሰ ጸንሐኒ እግዚአብሔር ከመ እንግር ዘለፋሁ። ወሎቱሰ አስተፋጠነ ቀቲሎቶ በእድሜ ዘአደመነ ንጉሥ ከመ ኢይድብያ ለቤተ ክርስቲያኑ።

፹ ቤተ ክርስቲያንም ከክፋቱና ከክሕደቱ መታወክ ዐረፈች። በመጽሐፉ ውስጥ የተነገረው የቃሉ ትርጉም ይህ ነው። እኔን ግን ስድቡን እናገር ዘንድ እግዚአብሔር ጠበቀኝ እርሱን ግን ንጉሥ በቀጠረው ቀን ቤተ ክርስቲያንን እንዳያውካት ሞቱን አፋጠነው።

**ዘከመ ደረሰ ማኅሌተ ሐዋርያት ወውዳሴ ሐዋርያት**

**የሐዋርያትን ማኅሌትና ውዳሴ እንደ ደረሰ**

፹፩ ወእምድኅረዝ አኀዘ አቡነ ጊዮርጊስ ይወድሶሙ ለሐዋርያት በማኅሌተ ስብሐት ለጴጥሮስኒ ወለጳውሎስ ዐቀመ ሎሙ ስብሐተ ማኅሌት እምዕለተ ክላሌሆሙ እንተ ይእቲ እም ሐምስቱ ለሐምሌ እስከ ፲ወ፪ አውራኀ።

፹፩ ከዚህም በኋላ አባታችን ጊዮርጊስ ሐዋርያትን በምስጋና ማኅሌት ያመሰግናቸው ጀመረ። ለጴጥሮስና ለጳውሎስ ሰማዕትነት ከተቀበሉባት ዕለት ያችም ሐምሌ አምስት ቀን እስከ አሥራ ሁለት ወሮች የማኅሌት ምስጋና ወሰነላቸው።

፹፪ ወለዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ዐቀመ ሎቱ ውዳሴ መኀልይ ዘበአርያም ወበመዝሙር። እንዘ ያፈደፍድ ክብረ ለእሉ ሠለስቱ በእንተ ዘኮንዎ ምምሕፃነ።

፹፪ ለዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድም ክብሩን አብዝቶ በአርያምና በመዝሙር የሚደርስ የማኅሌት ምስጋናን አዘጋጀለት /ወሰነለት/ ለሦስቱም አደራ የተሰጡት ስለሆነ ደረሰላቸው።

፹፫ ወለካልኣንኒ ሐዋርያት ዐቀመ በበአስማቲሆሙ ስብሐታተ ዘዕውቅ በኀበ አበው። ወጸሐፈ ካዕበ መጽሐፈ ዘይሰመይ ውዳሴ ሐዋርያት[2]።

፹፫ ለሌሎቹም ሐዋርያት በየስማቸው በወንድሞች ዘንድ የታወቀ ምስጋናን አዘጋጀላቸው። ዳግመኛም ውዳሴ ሐዋርያት የሚባል መጽሐፍን ጻፈ።

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፳፬ ተብህለ ለውእቱሰ መጽሐፍ ዘይሰመይ ፈጸሞ እምድኅረ ሞቱ ወልዱ ለጊዮርጊስ ዘነሥአ ካዕበተ መንፈሱ ከመ ኤልሳዕ ዘተካዕበተት ላዕሌሁ መንፈሰ ኤልያስ፡፡

፳፬ ያንንም ውዳሴ ሐዋርያት[2] የሚባል መጽሐፍ ከሞተ በኋላ የኤልያስ መንፈስ በእጥፍ ሆኖ እንዳደረበት እንደ ኤልሳዕ የመንፈሱን እጥፍ የተቀበለ የጊዮርጊስ ደቀ መዝሙር ፈጸመለት ተባለ፡፡

፳፭ ወተብህለ ካዕበ በእንቲአሁ ለዝንቱ ረድአ ጊዮርጊስ ወበእንተ አኃዊሁ እንዘ ሀለወት እሙ ሕፃነ ርእየ አቡነ ጊዮርጊስ ወይቤ ከዋክብት ብሩሃን ይሠርቁ እምከርሠ ዛቲ ወለት፡፡

፳፭ ዳግመኛም ስለዚህ የጊዮርጊስ ተማሪና ስለ ወንድሞቹ ተናገረ፡፡ እናቱ ልጅ ሳለች አባታችን ጊዮርጊስ አያት፡፡ የሚያበሩ ከዋክብት ከዚህች ልጅ ይወለዳሉ አለ፡፡

**በከመ ተፈትሐ እምቤተ ሞቅሕ ወነሥአ አልባሰ ምንኵስና ውስተ ገዳመ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል**

**ከእስር እንደ ተፈታና ከአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ገብቶ እንደ መነኮሰ፡፡**

፳፮ ንግባእኬ ኀበ ጥንተ ነገር፡፡ ወእንዘ ሀሎ አቡነ ውስተ ቤተ ሞቅሕ አዕረፈ ዳዊት ንጉሥ ጻድቅ ወየዋህ፡፡ ወለሐዎ አቡነ ጊዮርጊስ ዐቢየ ላሐ፡፡

፳፮ ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስ አባታችን ጊዮርጊስ በእስር ቤት ሳለ ጻድቅና የዋህ ንጉሥ ዳዊት ዐረፈ፡፡ አባታችን ጊዮርጊስም ታላቅ ልቅሶን አለቀሰለት፡፡

፳፯ ወሶበ ርእዩ ጽንዐ ብካዩ ይቤልዎ ለምንትኑ መጠነዝ ትበኪ ዘእምተፈሣሕከ ወእምተኃሠይከ አኮኑ ቀሠፈከ ወሞቅሐከ፡፡

፳፯ የልቅሶውንም ጽናት ባዩ ጊዜ የገረፈህና የአሰረህ አይደለምን? በመደሰት ፈንታ ይህን ያህል ለምን ታለቅሳለህ? አሉት፡፡

፳፰ ወአውሥአሙ አቡነ ጊዮርጊስ ወይቤሎሙ አንሰ እምፈተውኩ ከመ ይሕየው ጉንዱየ ከራማተ እንዘ ይዌስክ ላዕሌየ ካዕበተ መቅሠፍት ካልአ እምዝንቱ እስመ ኮነ ያፈቅራ ለማርያም እግዝእትየ፡፡

፳፰ አባታችን ጊዮርጊስም ከዚህ ሌላ እጥፍ ግርፋት እየጨመረኝ ብዙ ዓመት ይኖር ዘንድ በወደድሁ ነበር፤ እመቤቴ ማርያምን ይወዳታልና አላቸው፡፡

2. ውዳሴ ሐዋርያት ድርሰቱ ዜማ ስለሆነ በጽሑፍ ያስቀመጠው ተማሪው ነው ለማለት ይሆናል፡፡

# <u>ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ</u>

፳፱ ወእምድኅረ አዕረፈ ዳዊት ንጉሥ ነግሠ ወልዱ ቴዎድሮስ ጻድቅ ወኄር ወፈራሄ እግዚአብሔር። ወተዘከሮ ለብፁዕ ጊዮርጊስ ወአውፅኦ እምቤተ ሞቅሕ።

፳፱ ንጉሥ ዳዊት ካረፈ በኋላ ጻድቅና ቸር እግዚአብሔርንም የሚፈራ ልጅ ቴዎድሮስ ነገሠ። ብፁዕ ጊዮርጊስን አሰበው። ከእስር ቤት አወጣው።

፴ ወሞተ ቴዎድሮስ በ፱ አውራኅ። ወነግሠ እምድኅሬሁ ይስሐቅ እኁሁ ወልደ ዳዊት ውእቱኒ አፍቀሮ ወአዕበዮ በካህናተ ደብተራ። ወፈነዎ እስከ ብሔረ ዳሞ ኀበ ሰበከ ቀዲሙ ከመ ያስተጻንዖሙ ላዕለ ሃይማኖት ርትዕት።

፴ ንጉሥ ቴዎድሮስም በዘጠኝ ወራት ሞተ። ከእርሱም በኋላ የዳዊት ልጅ ወንድሙ ይስሐቅ ነገሠ እርሱም ወደደው በካህናተ ደብተራ ከፍ አደረገው። በቀናች ሃይማኖት ያጸናቸው ዘንድ ቀድሞ እስከ አስተማረበት እስከ ዳሞ ድረስ ላከው።

፴፩ ወይቤ አቡነ ጊዮርጊስ ናሁ ተፈጸመ ላዕሌየ ቃለ ጸሎቱ ለኢያሱ ወልደ ሲራክ ዘይቤ እገኒ ለከ እግዚአ ንጉሥ ወእሴብሐከ አምላኪየ ወመድኅንየ ወእትአመን በስምከ እስመ ኮንከኒ ረዳእየ ወመሰውረ ወቤዘውኮ በሥጋየ እምነ ሞት እምነ መሥገርተ ውዴተ ልሳን ወእምአዕላፍ እለ ይትጌበርዋ ለሐሰት በቅድመ ኲሎሙ እለ ቆሙ ላዕሌየ ኮንከኒ ረዳእየ ወመሰውርየ ወእምልሳነ ዓማፂ ዘያስተደጉጽ ኀበ ንጉሥ ዘአብጽሓ ውስተ ሞት ለሕይወትየ። ሲራክ.፶፩፥፩

፴፩ አባታችን ጊዮርጊስም "አቤቱ ንጉሥ ሆይ! እገዛልሃለሁ፤ አቤቱ! አምላኪዬና መድኃኒቴ አመሰግንሃለሁ፤ በስምህም እታመናለሁ፤ ረድተኸኛልና ሰውረኸኝማልና ሰውነቴንም ከሚያሠሩአት ከብዙ ሰዎች ምላስ አድነኸኛልና፤ ከጠላትነትም ከተነሡብኝ ሰዎች ፊት የምትረዳኝና የምትሰውረኝ ሆነሃልና፤ ሰውነቴን ወደ ሞት ካደረሳት ወደ ንጉሥ ከሚያጣላ ከዐመፀኛ አንደበትም ሰውረኸኛልና፤ ያለው የሲራክ ልጅ ኢያሱ ጸሎት በእኔ ላይ ተፈጸመ አለ። ሲራክ.፶፩፥፩

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፴፪ | ወእምዝ የሐውር ፍኖተ በጽሐ ደብረ ሊባኖስ ምኔተ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በመዋዕለ አባ ዮሐንስ ከማ ፈቂዶ ከመ ይንሣእ ምንኵስና ፍጹመ፡፡ እስመ ነበረ እስከ አሜሃ በልብሰ መከራ፡፡ | ፴፪ | ከዚያም በኋላ ምንኩስናን ይቀበል ዘንድ ሲሔድ በዮሐንስ ከማ ዘመን ከአባታችን ተክለሃይማኖት ገዳም ደብረ ሊባኖስ ደረሰ፡፡ እስከዚያ ድረስ የአመክሮ ልብስ ለብሶ ይኖር ነበርና፡፡ |
| ፴፫ | ወመነኮሳተ ይእቲ ደብር ኄራን ወፍጹማን ከመ አቡሆሙ ፍጹም፡፡ ወባሕቱ ነበሩ ይስዕርዋ ለቀዳሚት ሰንበት፡፡ ወረከቦሙ እንዘ የሐንጹ ቤተ ክርስቲያን ባቲ፡፡ ወያመክንዩ በቃለ ሐዋርያ ጳውሎስ ዘይቤ በውስተ መልእክቱ ለሰብአ ቆላስይስ ዑቁኬ ኢያስሕቱክሙ ኢበበዓላት ወኢበሰናብት፡፡ | ፴፫ | የዚያችም ገዳም መነኮሳት እንደ ፍጹም አባታቸው ደጋጎችና ፍጹማን ነበሩ፡፡ ነገር ግን ቀዳሚት ሰንበትን ይሽሯት ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ሲያንጹባት አገኛቸው ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች በመልእክቱ "በበዓላትም በሰንበትም እንዳያስቱአችሁ ዕወቁ" ያለውን ምክንያት ያደርጋሉ፡፡ ቈላ.፪፥፲፮ |
| ፴፬ | ወሶበ ርእየ ዘንተ አቡነ ጊዮርጊስ ተዋሥዖሙ ብዙኀ በቃለ መጻሕፍት፡፡ ወእሙንቱሰ ኢተሰጠውዎ፡፡ ወበእንተዝ ግብር ሖረ እምህየ ወበጽሐ ኀበ መቃብሪሁ ለአባ በጸሎተ ሚካኤል ድንግል ወሰማዕት፡፡[3] | ፴፬ | አባታችን ጊዮርጊስም ይህን ባየ ጊዜ በመጻሕፍት ቃል ብዙ ተከራከራቸው፡፡ እነርሱ ግን አልተቀበሉትም፤ ስለዚህም ሥራ ከዚያ ሔደ፡፡ ድንግልና ሰማዕት ወደ ሆነው ወደ አባ በጸሎተ ሚካኤል መቃብር ደረሰ፡፡[3] |

*3. በአፄ አምደ ጽዮን መንግሥት ማብቂያና አካባቢው የመጡ የግብጽ ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ቀዳሚትንም እሑድንም ማክበራቸውን ተቃወሙ፡፡ ንጉሡም ቀዳሚትን ማክበር የአይሁድ ልማድ ነው፤ ክርስትያኖች እሑድን ብቻ ነው ማክበር ያለባቸው በማለት ትእዛዝ አስተላለፉ፡፡ ሆኖም ይህን በኢትዮጵያውያን ዘንድ ታምኖበት ለረጅም ጊዜ የቆየ ሥርዐትና በሐዋርያት ቀኖና የጸደቀ ጉዳይ የኢትዮጵያ ሊቃውንት በአንድ ጊዜ አልተቀበሉም፡፡ በተለይ የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ትምህርት ቤት ቀዳሚት በመጀመሪያ በሥነ ፍጥረት እግዚአብሔር ያከበራትና የቀደሳት ናት ዘፍ.፪፥፪-፫ በሁለተኛ ደረጃ በዐሥርቱ ሕግጋት ለሙሴ ሲሰጥ ሦስተኛ ሕግ ሆና ጸንታለች፡፡ ዘጸ.፳፥፰ በሐዲስ ኪዳንም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ሕግንና ሥርዐትን ልሽር አልመጣሁም ብሏል፡፡ ማቴ.፭፥፲፯ በታሪክም ኢትዮጵያውያን ሥርዐተ ኦሪትን ስንከተል ቆይተን በኋላ ክርስትናን የተቀበልን ስለሆነ ቀዳሚትን እንደ አይሁድ ሳይሆን እንደ ክርስቲያን ከሰንበተ ክርስቲያን ጋር ማክበር ይገባል፤ በማለት ጉዳዩን ወደ ክርክር ወሰዱት፡፡ ግብጻዊው ጳጳስ ግን ሁኔታውን ባለመቀበል ቀዳሚትን ለሚያከብሩት ሊቃውንት ክህነት አልሰጥም ብለው ከለከሉ፡፡ በዚህም የተነሣ በሊቃውንት መካከል ሠፊ ውይይት ቢደረግም ጳጳሱ ስለተቃወሙ በቶሎ መፍትሔ ሳይገኝለት ቆይቷል፡፡ በሊቃውንቱ መካከል በተደረገ ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ በፈጀ ክርክር በመጨረሻ መፍትሔ የሰጡት የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ትምህርት ቤት ደቀ መዝሙር የነበሩት አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ናቸው፡፡ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የነበሩበት ዘመን ይህ ክርክር በጣም አይሎ የወጣበት የአፄ ዳዊት ዘመን ነበር፡፡ በዚህም አባ ፊሊጶስ ዘደብረ ቢዘን ወደ ደብረ ሐይቅ ተወስደው በኢቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃን ቁጥጥር እየተማሩ እንዲቆዩ ሲደረግ መምህራቸው ኤዎስጣቴዎስ በዚሁ ጉዳይ ተሰደው ወደ አርመን ሒደዋል፡፡ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ መምህራቸው ኢቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃን ቢሆኑም በዚህ ጉዳይ ተጽእኖ ኣላደረጉባቸውም የአቡነ ጊዮርጊስ በሰንበት ላይ ያላቸው ትምህርት እንደ ኤዎስጣቴዎስ ሊቃውንት ከሰንበተ ክርስቲያን ጋር አብራ ትከበር ነገር ግን ሰንበተ ክርስቲያን የማታልፍ የትንሣኤ ዕለት ናት፤ ቀዳሚትንም ክርስቲያኖች እንደ አይሁድ በመጠናቀቅ ኢያከብሩም፣ ጌታችን እንዳዘዘ ለነፍስ የሚሆን የነፍስ ሥራን በመሥራት እናከብራለን እንጂ ብለዋል፡፡ ይህ ክርክር በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን በአባ ገብርእልና በአባ ሚካኤል በሚባሉ ጳጳሳት መፍትሔ አግኝቶ ከሰንበተ ክርስቲያን ጋር ትከበራለች፡፡ ከዚያ በኋላ ሊቃውንቱ ተስማምተው ውሳኔውን ጠብቀው ቆይተዋል፡፡*

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፴፫ | እስመ ፈድፋደ ያፈቅሮ እምንእሱ ወለብሰ በህየ አልባሰ ምንኲስና እምኀበ አበምኔት አባ ቴዎድሮስ ዘፍጹም በኲሉ ምግባረ ሠናይ፡፡ | ፴፫ | ከልጅነቱ ጀምሮ በጣም ይወደው ነበርና በዚያም በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹም ከነበረው የገዳም ሓላፊ አባ ቴዎድሮስ የምንኲስናን ልብስ ለበሰ፡፡ |
| ፴፬ | ወእምአሜሃ አፈድፈደ ጾመ ወጸሎተ፡፡ ቦ አመ ይበውእ ውስተ ቀላየ ማይ በቊር ወአስሐትያ ወይጼሊ በህየ፡፡ ወእምከመ ኮነ ዝናም ኃያል ወበረድ ይገድፍ አልባሲሁ ወይወፅእ አፍአ ወይቀውም ዕራቁ ከመ ያመንድብ ሥጋሁ፡፡ | ፴፬ | ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ጾምና ጸሎትን አበዛ፡፡ በብርድና በውርጭ ወደ ባሕር የሚገባበት ጊዜ አለ፡፡ በዚያም ይጸልያል፡፡ ከባድ ዝናምና በረዶ ከሆነ ልብሱን ጥሎ ወደ ውጭ ይወጣል፡፡ በሥጋውም መከራ ይቀበል ዘንድ ዕራቁቱን ይቆማል፡፡ |
| ፴፭ | ወበዕለተ ስቅለቱ ለእግዚእነ ወበተዝካረ ኲሎሙ ሐዋርያት ይትቀሠፍ እስከ ይውኅዝ ደሙ ውስተ ምድር ከመ ማይ፡፡ | ፴፭ | ጌታችን በተሰቀለበትና በሁሉም ሐዋርያት የመታሰቢያ ዕለት ደሙ በምድር ላይ እንደ ውኃ እስኪፈስ ድረስ ይገረፋል፡፡ |
| ፴፮ | ወበጾመ ፵ ቅድስት ይውዕል ኲሎ ዕለተ እንዘ ይጼሊ ውስተ ፀሐይ፡፡ ወጊዜ መንፈቀ ሌሊት ይበውእ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወይጸውር ዲበ ርእሱ ኦሪተ ወመልዕልቴሁ ወንጌለ መንግሥት ወየዐውድ አረፋቲሃ ፻ ፻ ጊዜ፡፡ | ፴፮ | በተመሰገነች በ፵ ጾም በፀሐይ ሁል ጊዜ ሲጸልይ ይውላል፡፡ የሌሊት እኩሌታ በሆነም ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይገባል፡፡ በራሱም ላይ ኦሪትን የመንግሥት ወንጌልንም ከላይ አድርጎ ይሸከማል፡፡ ቅጽሮቿንም መቶ መቶ ጊዜ ይዞራል፡፡ |
| ፴፯ | ወከመዝ ኮነ ልማዱ በኲሉ ለያልይ፡፡ ወዘእንበለ ዝኒ ካዕበ ነበረ በብዙኅ ጻማ ወገድል እስከ ዕለተ ሞቱ፡፡<br>ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡ | ፴፯ | በሁሉም ሌሊት እንደዚህ ልማድ ነበረው ዳግመኛም ከዚህ ሌላ እስከ ሞቱ ቀን ድረስ በብዙ ጾምና ገድል ኖረ፡፡<br>ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሆን አሜን፡፡ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

## ምዕራፍ ፰

**ከመ ደረሰ ፍካሬ ሃይማኖት ወበእንተዝ ሰመይዎ ለአቡነ ጊዮርጊስ ቁርሎስ ወዮሐንስ አፈ ወርቅ ዘኢትዮጵያ**

፩ ወበአሐቲ እመዋዕል ተስእሎ ፩ መስፍን ዘስሙ ቴዎድሮስ ዘይሰመይ ካዕበ ሊቀ ሐራ በእንተ ሃይማኖት ርትዕት ወደረሰ ሎቱ መጽሐፈ ዘይሰመይ ፍካሬ ሃይማኖት፡፡

፪ ወሶበ ርእይዎ ወአንበብዎ ለውእቱ መጽሐፍ ንጉሥ ወኲሎሙ ካህናተ ምስጢር ይቤሉ አማንኬ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ወቁርሎስ አፈ በረከት ተንሥኡ በመዋዕሊነ ኢትዮጵያ ተመሰለት በቁስጥንጥንያ ወተዐረየታ ለእለ እስክንድርያ፡፡

**በእንተ አባ ጊዮርጊስ ወአባ ጽጌ ድንግል**

፫ ወእምድኅረዝ ስምዑነ ካዕበ ንንግርክሙ ወሀሎ ፩ ጻድቅ አባ ጽጌ ድንግል ማእከለ ፈለግ ዘወለቃ በመዋዕለሁ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡ ወሐነጸ ለሊሁ ጻድቅ አባ ጽጌ ድንግል ሕንጻ ከመ አቡነ ጊዮርጊስ ዘይመስል ከመ ሕንጻ ላሊበላ ወስመ ደብሩ ደብረ ጽጌ ቅሩብ ውእቱ እምነ ፈለግ ዘወለቃ፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

**ፍካሬ ሃይማኖት የተባለ መጽሐፍን እንደ ደረሰና አባታችን ጊዮርጊስን ቄርሎስ እና ኢትዮጵያዊ ዮሐንስ አፈወርቅ ብለው እንደ ሰየሙት**

፩ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰው ቴዎድሮስ የተባለ የሠራዊት አለቃ ኀኘ ስለ ቀናች ሃይማኖት ጠየቀው ፍካሬ ሃይማኖት የተባለ መጽሐፍን ደረሰለት፡፡

፪ ያንንም መጽሐፍ ንጉሡና ምስጢር የሚያውቁ ሁሉም ካህናት ባዩትና በአነበቡት ጊዜ በእውነት ዮንሐስ አፈ ወርቅና የበረከት አፍ ቄርሎስ ተነሡ፤ ኢትዮጵያ በቁስጥንጥንያ ተመሰለች እስክንድርያንም ተካከለቻት አሉ፡፡

**ስለ አባ ጊዮርጊስና አባ ጽጌ ድንግል**

፫ ዳግመኛ እንነግራችሁ ዘንድ ስሙን በአባታችን ጊዮርጊስ ዘመን በወለቃ ወንዝ መካከል አባ ጽጌ ድንግል[4] የሚባል አንድ ጻድቅ ነበረ፡፡ ጻድቁ አባ ጽጌ ድንግልም የላሊበላ ሕንጻን የሚመስል እንደ አባታችን ጊዮርጊስ ያለ ሕንጻን አነጸ የደብሩ ስም ደብረ ጽጌ ሲሆን ለወለቃ ወንዝ ቅርብ ነው፡፡

---

4. *አባ ጽጌ ድንግል የማኅሌተ ጽጌ ደራሲ ናቸው፡፡ ከአባ ጊዮርጊስ ጋር የነበሩበት ዘመን ተቀራራቢ የነበረ ሲሆን የሁለቱም ቅዱሳን አባቶች በኣት በእግር ከ4፡00 በላይ አያስኬድም፡፡ ለዚህም በመካከላቸው የወለቃን ድልድይ ሠርተዋል፡፡ ወደፊት እንደምታገኙው እንደሚነገረው አባ ጊዮርጊስ በኣት /ሾማ/ ሳበራ ከአባ ጽጌ ድንግል በኣት ብርሃኑ ይታያል /ያገለግላል/ ይባላል፡፡*

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፡

፬ ወክልኤሆሙ አባ ጊዮርጊስ ወአባ ጽጌ ድንግል ይትራከቡ በበዕለቱ ላዕለ ፈለግ ዘወለቃ ወይትናገሩ ነገራተ እግዚአብሔር በቃዕያት፡፡ ወክቡራን እሙንቱ በኀበ አምላኮሙ ወበጊዜሁ ለክረምት ኢይትራከቡ እስመ ይከልዖሙ ማዕበለ ፈለግ፡፡ ወበእንተዝ የኀዝኑ ወይቴክዙ በበጊዜሁ ለክረምት፡፡

፬ ሁለቱም አባ ጊዮርጊስና አባ ጽጌ ድንግል በየቀኑ በወለቃ ወንዝ ይገናኛሉ፡፡ ዋጋ የሚገኝባቸው የእግዚአብሔርንም ምስጢራት ይነጋገራሉ፡፡ በፈጣሪያቸውም ዘንድ የከበሩ ናቸው፡፡ በክረምት ወራት ግን የውኃው ማእበል ስለሚከለክላቸው አይገናኙም፡፡ ስለዚህም በክረምት ጊዜ ያዝኑና ይተክዙ ነበር፡፡

፭ ወበአሐቲ እመዋዕል ኀለዩ ከመ ይግበሩ ተንከተመ ማእከለ ፈለግ ዘወለቃ በጥቡዕ ልብ ወበአሚነ እግዚአብሔር ወጠኑ ይግበሩ ወነዝሑ ጸበለ መሬት ላዕለ ፈለግ ወተገብረ ሎሙ በረድኤተ እግዚአብሔር ስፉሕ ተንከተም ዘያስተዐፅብ ሰብአ፡፡

፭ ከዕለታትም በአንድ ቀን በወለቃ ወንዝ መካከል ድልድይ ይሠሩ ዘንድ አሰቡ፡፡ በጠነከረ ልብና እግዚአብሔርንም በማመን ሊሠሩ ጀመሩ፡፡ በወንዙም ላይ የመሬቱን ትቢያ በተኑ በእግዚአብሔርም አጋዥነት ሰውን የሚያስደንቅ ሰፊ ድልድይ ተሠራላቸው፡፡

፮ ወካዕበ ንነግረክሙ ወበአሐቲ ዕለት ቀንዐ ቦሙ ጸላኤ ሠናያት አንሥአ እብነ ነዊኀ መጠነ ቆሙ በእመት ፬ቱ ወወጠነ ይስብር ተንከተመ እማእከል ከመ ኢይትራኩቡ ፪ቱ ጻድቃን፡፡ ወተርእዮ ለአቡነ ጊዮርጊስ ነቢሮ እምነ መካኑ እንዘ ይሰብር ሰይጣን ተንከተመ፡፡

፮ ዳግመኛም እንነግራችሁ አንድ ቀን የበጎ ሥራ ጠላት ሰይጣን ቀናባቸው፡፡ ቁመቱ አራት ክንድ የሆነ ረጅም ድንጋይን አንሥቶ ሁለቱ ጻድቃን እንዳይገናኙ ከመካከል ድልድዩን ይሰብር ጀመረ ለአባታችን ጊዮርጊስም ሰይጣን ከቦታው ተቀምጦ ድልድዩን ሲሰብር ታየው፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፯ ወበህየ ሖረ አባ ጊዮርጊስ ተጽዒኖ ላዕለ ነፋስ በረድኤተ እግዚአብሔር ወበጽሐ በቅጽበት ዘምሕዋረ ፫ቱ ሰዓት ፍኖት እምነ መካኑ፡፡ ወአኃዞ ለሰይጣን ወረገዞ በኲናት ወአሰሮ በሰናስለ ሐጺን ወአምጽኦ ኀበ መካኑ በጸዊረ ዝንቱ እብን ወሞቅሖ ፲ወ፪ ዓመተ ወኮነ ዝንቱ እብን ለመፍቅደ መነኮሳት እስከ ይእዜ፡፡

፯ አባታችን ጊዮርጊስም በእግዚአብሔር አጋዥነት በነፋስ ሠረገላ ተጭኖ ካለበት ቦታ ጀምሮ ሦስት ሰዓት የሚያስኬደውን መንገድ በቅጽበት ደረሰበት ሰይጣኑንም ይዞ በጦር ወጋው፡፡ በብረት ሰንሰለትም አስሮ ድንጋዩን አሸክሞ ወደ ቦታው አመጣው፡፡ አሥራ ሁለት ዓመትም አሰረው፡፡ ይህም ድንጋይ እስከ ዛሬ ለመነኮሳት መገልገያ ሆነ፡፡

፰ ንዑ ርእዩ ሰማዕያን ዘንነግረክሙ ትርአዩ ዘሰማዕክሙ በአእዛኒክሙ እሙነ ዘነገርናክሙ ቅድመ በእንተ ግብረ ተንከተም ወእብነሂ ዘኮነ መጥቅዐ ለግብረ ቤተ ክርስቲያን ናሁ ሀለዉ እስከ ይእዜ በማእከለ አፍላግ ወበውስተ ገዳም እንዘ ይትናገሩ ዘያስተፌሥሑ መንክረ ግብረ ዘገብረ እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ፡፡

መዝ ፷፯፥፴፭

፰ የምንነግራችሁን የምትሰሙ ሰማዕያን ሆይ አስቀድመን የነገርናችሁ ስለ ድልድዩ ሥራና ለቤተ ክርስቲያን ደወል ስለሆነው ድንጋይ በእውነት በጆሮአችሁ የሰማችሁትን ታዩ ዘንድ ኑ እነሆ ሰዎች ሲናገሩ ደስ የሚያሰኙ ሁነው ድልድዩ በወንዝ መካከል ድንጋዩም በገዳሙ ውስጥ አለ፡፡ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ሥራን አደረገ፡፡ መዝ ፷፯፥፴፭

፱ ወካዕበ በአሐቲ እመዋዕል ቀንዐ ላዕለ አቡነ ጊዮርጊስ መስፍን ወዘመዱ ውእቱ በሥጋ፡፡ ወሶበ ርእየ ክብሮ ወሞገሶ ለአቡነ ጊዮርጊስ ዘኀበ እግዚአብሔር ወዘኀበ ሰብእ አስተዋደዮ ኀበ ንጉሥ በሐሰት ወአኀበረ ምስሌሁ ሰብአ ሐሳውያነ፡፡

፱ ዳግመኛም ከዕለታት በአንድ ቀን አንድ ገዥ በአባታችን ጊዮርጊስ ላይ ቀናበት በሥጋም ዘመዱ ነው፡፡ በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ ያለውን የአባታችን ጊዮርጊስ ባለሟልነቱንና ክብሩ ባየ ጊዜ ከንጉሡ በሐሰት አጣለው ሐሰተኞች ሰዎችንም ከእርሱ ጋር አስተባበረ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲ | ወንጉሥሰ ኢያእመረ ትምይንቶ እስመ የዋህ ውእቱ ከመ ዳዊት፡፡ ወሰሚዖ ንጉሥ ነገሮ ሰደዶ ውስተ ብሔር ነኪር እምታዕካሁ፡፡ | ፲ | ንጉሡ ግን እንደ ዳዊት የዋህ ነበርና ተንኮሉን አላወቀም፡፡ ነገሩን ሰምቶ ከቤቱ አስወጥቶ ወደ ሌላ አገር ሰደደው፡፡ |
| ፲፩ | ወአዕረግዎ በሐብል ውስተ ደብር ነዋኅ ኀበ አልቦ ማይ ለሰትዩ ወእክለ ለሲሳይ፡፡ ወውእቱ ደብር ኰኵሕ ኵለንታሁ ወልሙጽ ወጥቀ ያመነድብ በህየ ሐሩረ ፀሐይ፡፡ ወሞቅሕዎ እደዊሁ ወእገሪሁ ወነበረ ህየ በብዙኅ ምንዳቤ ወተጽናስ፡፡ | ፲፩ | በገመድም እህል የሚጠጣ ውኃ ወደ ሌለበት ረጅም ተራራ አወጡት ያም ተራራ ሁለንተናው ልሙጥ ድንጋይ ነው፡፡ በዚያም የፀሐዩ ሙቀት ያሰቃያል፡፡ እጁንና እግሩን አሰሩት በብዙ ችግርና ስቃይ ተቀመጠ፡፡ |
| ፲፪ | ወሶቤሃ ሰአለ ወጸለየ ኀበ እግዚአብሔር መሓሪ ወጻድቅ ወኀበ እሙ ንጽሕት እግዝእትነ ማርያም፡፡ ወገብረ እግዚአብሔር ምሕረተ ውስተ ልበ ንጉሥ ወጸውዐ ሐራሁ ወተስእለ በእንተ አቡነ ጊዮርጊስ፡፡ ኀበ አይ መካን ሀሎ፡፡ | ፲፪ | ያን ጊዜ መሓሪና እውነተኛ ወደ ሆነ እግዚአብሔርና ወደ እናቱ ንጽሕት እመቤታችን ማርያም ለመነ፡፡ እግዚአብሔርም በንጉሡ ልብ ምሕረትን አሳደረበት፡፡ ወታደሮችንም ጠርቶ አባታችን ጊዮርጊስም ወዴት እንዳለ ጠየቃቸው፡፡ |
| ፲፫ | ወይቤሎ ውእቱ መስተዋድይ ሞተ በኀበ ተሰደ፡፡ ወተቀብረ በህየ፡፡ ወሰሚዖ ንጉሥ ኀዘነ ፈድፋደ ወመሰሎ ከመ እሙነ ሞተ፡፡ | ፲፫ | ያም ነገረ ሠሪ በተሰደደበት ሞተ፤ በዚያም ተቀበረ አለው፡፡ ንጉሡም ሰምቶ ፈጽሞ አዘነ፤ በእውነት የሞተም መሰለው፡፡ |
| ፲፬ | ወእግዚአብሔርሰ ማእምረ ኅቡአት ከሠተ ለአቡነ ጊዮርጊስ ዘንተ ነገረ ዘገብረ ውእቱ መስተዋድይ፡፡ ወዘከመ ነገሮ ለንጉሥ ሞቶ በሐሰት፡፡ | ፲፬ | የተሰወረውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ግን ያ ነገረ ሠሪ ያደረገውን ሞቱን በሐሰት ለንጉሡ እንደ ነገረው ገለጸለት፡፡ |

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፭ ወይቤሎ ለረድኡ ዘሀሎ ምስሌሁ ወይትለአኮ አምጽእ ሊተ ክርታሰ ወቀለመ፡፡ ወይቤሎ ውእቱ ረድእ እምከመ አምጻእኩ ለከ መኑ ይወስድ ለከ ወመኑ ያበውአ ኀበ ንጉሥ፡፡

፲፭ ከእርሱ ጋር ያለውን የሚያገለግለውን ደቀ መዝሙር ብራና/ወረቀትና ቀለም አምጣልኝ አለው፡፡ ያም ደቀመዝሙር ባመጣልህ ማን ይወስድልሃል ወደ ንጉሡስ ማን ያስገባዋል አለው፡፡

፲፮ ወይቤሎ አቡነ ጊዮርጊስ የአምር እግዚአብሔር አ ወልድየ ዘይገብር ሠናያተ ምስሌየ፡፡ ወሶበዝ አምጽአ ሎቱ ቀለመ ወክርታሰ ወጸሐፈ አቡነ ጊዮርጊስ እንዘ ያስተበቍዖ ለንጉሥ ከመ ያእትዎ እምስደቱ፡፡

፲፮ አባታችን ጊዮርጊስም ልጄ ሆይ በእኔ ላይ መልካም ነገርን የሚሠራ እግዚአብሔር ያውቃል አለው፡፡ ያን ጊዜ ቀለምና ብራና/ ወረቀት/ አመጣለት አባታችን ጊዮርጊስም ከስደቱ ይመልሰው ዘንድ ንጉሡን እየማለደ ጻፈ፡፡

፲፯ ወኀተመ ክርታሰ በሰምዕ ወጸለየ ወይቤ አ እግዚአ አምላከ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ኢኮንከ አምላከ ምውታን አላ አምላከ ሕያዋን እስመ ኵሎሙ ሕያዋን በኀቤከ አብጽሕ ሊተ ዘንተ ክርታሰ ኀበ ንጉሥ ከመ ይትኀፈር ጸላኢ ዘነገሮ በሞተ ዚአየ እስመ ለከ ስብሐት እስከ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፲፯ ወረቀቱንም /ብራናን/ በሰም አተመው እንዲህም ብሎ ጸለየ፡፡ አቤቱ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ የሙታን አምላክ አይደለህም የሕያዋን አምለክ ነህ እንጂ ሁሉም በአንተ ዘንድ ሕያዋን ናቸውና የእኔን ሞት የነገረው ጠላት ያፍር ዘንድ ይህን መልእክት ወደ ንጉሡ አድርስልኝ፡፡ ለአንተ ምስጋና ይገባልና ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

፲፰ ወሶበ ይቤ አሜን ወገረ ውእተ ክርታሰ ውስተ አየር፡፡ ወበጊዜሃ ጾሮ ነፋስ ዓውሎ ወአብጽሖ ኀበ ንጉሥ ይስሐቅ ወአንበሮ ማእከለ ብረኪሁ እንዘ ሀሎ ንቡረ ውስተ ደብተራሁ፡፡

፲፰ አሜንም ባለ ጊዜ ያን ደብዳቤ ወደ አየር ወረወረው፡፡ ያንንም ዐውሎ ነፋስ ተሸክሞ ከንጉሡ ይስሐቅ አደረሰው፡፡ በድንኳኑም ተቀምጦ ሳለ ከጉልበቱ መካከል አስቀመጠው፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፱ | ወርእዮ ንጉሥ ደንገፀ ወመሰሎ ዘገብሩ ላዕሌሁ ሥራየ ሰብአ እኩያን፡፡ ወሐተተ ሐራሁ ወመኳንንቲሁ በበ፩ እስከ እድ ወአንስት እስከ አእሩግ ወሕፃናት ወመኑ እምኔሆሙ ዘአብአ ለክርታስ ወኢረከበ፡፡ | ፲፱ | ንጉሡም አይቶ ደነገጠ ክፉ ሠዎችም መተት ያደረጉበት መሰለው ወታደሮቹን መኳንንቱን ከወንድ እስከ ሴት ከታላላቆች እስከ ሕፃናት ድረስ እያንዳንዱን መረመረ፡፡ ከእነርሱም ደብዳቤውን ማን እንዳስገባው አላገኘም፡፡ |
| ፳ | ወእምዝ ተሐዘበ ወገደፎ ለውእቱ ክርታስ ውስተ እሳት ወኢውዕየ ወውስተ ማይኒ ኢጠፍአ፡፡ ወእምድኅረዝ ፈንቀለ ማኅተሞ ወአንበቦ፡፡ | ፳ | ከዚያም በኋላ ተጠራጥሮ ያን ደብዳቤ ወደ እሳት ጣለው፡፡ አልተቃጠለም በውኃም አልጠፋም ከዚህም በኋላ ማኅተሙን ገልጦ አነበበው፡፡ |
| ፳፩ | ወሶበ ርእዮ ከመ ጊዮርጊስ ፈነዎ ደንገፀ ወጐድአ እንግድኣሁ ወበከየ፡፡ ወአኀዞ ለመስተዋድይ ወለእሊአሁ እለ ነገርዎ ሞቶ ወሞቅሖሙ፡፡ | ፳፩ | ጊዮርጊስም እንደ ላከው ባየ ጊዜ ደነገጠ፣ ደረቱንም መትቶ አለቀሰ፤ ነገረ ሠሪውን ያዘው ሞቱን የነገሩትንም አሰራቸው፡፡ |
| ፳፪ | ወፈነወ ላእካነ በጕጕዓ ኀበ አቡነ ጊዮርጊስ ያብጽሕዎ በክብር ምስለ በቅል ዘይጼዓን ቦቱ ንጉሥ፡፡ ወሶበ በጽሐ ተፈሥሐ ንጉሥ ወአምኆ፡፡ | ፳፪ | ንጉሡ በሚቀመጥበት በቅሎ በክብር ያደርሱት ዘንድ ወደ አባታችን ጊዮርጊስ በፍጥነት መልእክተኞችን ላከ፡፡ በደረሰም ጊዜ ንጉሡ ደስ አለው፡፡ እጅም ነሳው፡፡ |
| ፳፫ | ወእምድኅረዝ አእተተ ሰብአ ወይቤሎ እስእለከ በሕማማቲሁ ለክርስቶስ ከመ ትንግረኒ ለመኑ ወሀብከ ክርታሰ ዘለአኮ ኀቤየ ወመኑ አምጽአ ዝየ፡፡ | ፳፫ | ከዚያም በኋላ ሰዎችን ከእርሱ አራቀ ትነግረኝ ዘንድ በክርስቶስ መከራዎች እለምንሃለሁ፤ ወደ እኔ የላከኸውን ደብዳቤ ለማን ሰጠህ? ወደ እዚህስ ማን አመጣው? አለው፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፷፬ | ወአቡነሰ ይቤሎ አልቦ ለዘወሀብኩ ለአሐዱሂ እምሰብእ ወባሕቱ ወሀብክዎ ለነፋስ ወበሥምረቱ ለእግዚአብሔር አብጽሖ ኀቤከ ውእቱ ነፋስ ዓውሎ። በከመ ወሰደ ንስር መልእክተ ነቢይ እስከ ብሔረ ባቢሎን። | ፷፬ | አባታችን ግን ከሰው ወገን ለአንዱም የሰጠሁት የለም። ነገር ግን ለነፋስ ሰጠሁት ንስር የነቢይን መልእክት እስከ ባቢሎን አገር ድረስ እንደ ወሰደ በእግዚአብሔር ፈቃድ ዐውሎ ነፋስ ወደ አንተ አደረሰው አለው። |
| ፷፭ | ወበከመ ወሰደት ርግብ መልእክተ ንጉሥ እስከ ብሔረ አትሪብ። ወሰሚዖ ንጉሥ አንከረ ወወደሶ ለአቡነ ጊዮርጊስ። | ፷፭ | ርግብ የንጉሡን መልእክት እስከ አትሪብ አገር ድረስ እንደ ወሰደች ንጉሡም ሰምቶ አደነቀ አባታችን ጊዮርጊስንም አመሰገነው። |
| ፷፮ | ወዘንተ ኵሎ መንክራተ ዘገብረ ዝንቱ ቅዱስ ነገረኒ ውእቱ ቀሲስ ዘነበረ ምስሌሁ ዘከመ ርእየ በአዕይንቲሁ ወሰምዐ በእዘኒሁ ወዘአምጽአ ሎቱ ክርታሰ ወቀለመ ሊተ ለነዳይ ጸሐፌ ዝንቱ መጽሐፍ። | ፷፮ | ይህ ቅዱስ የሠራውን ይህን ሁሉ ድንቅ ተአምር በጆሮው እንደ ሰማ በዐይኑም እንዳየ ከእርሱ ጋር የነበረ ወረቀቱንና ቀለሙን ያመጣለት ቄስ ይህን መጽሐፍ ለጻፍሁ ለድኃው ለእኔ ነገረኝ። |
| ፷፯ | ወእምድኅረዝ ሰደዶ ንጉሥ ለውእቱ መስተዋድይ አምታዕካሁ ፍዳ ኀበ ስደቱ ለአቡነ ጊዮርጊስ። በከመ ጹሑፍ ዘይከሪ ግበ ለቢጹ ይወድቅ ውስቴቱ። ወዘያንኰረኵር እብነ ለእጉሁ ያንኰረኵር ላዕለ ርእሱ | ፷፯ | ከዚህም በኋላ ንጉሡ ያን ነገረ ሠሪ አባታችን ወደ ተሰደደበት ብድራቱን ከቤተ መንግሥት አስወጥቶ ሰደደው። "ለባልንጀራው ጉድጓድ የሚቆፍር ራሱ ይወድቅበታል ድንጋይንም የሚፈነቅል ራሱ ይቄስልበታል ተብሎ እንደተጻፈ። |
| ፷፰ | ወለአቡነሰ ጊዮርጊስ እምአሜሃ አንበሮ በክብር ከመ አሐዱ እምሐዋርያት። | ፷፰ | አባታችን ጊዮርጊዮስን ግን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከሐዋርያት እንደ አንዱ በክብር አስቀመጠው። |
| ፷፱ | ወእንዘ ሀሎ ቅድመ አቡነ ጊዮርጊስ በመካነ ስደቱ[5] አክረየ መቃብረ። እስመ መሰሎ ዘይትቀበር በህየ ወሶቤሃ አኅደጎ መንፈስ ቅዱስ። | ፷፱ | አባታችን ጊዮርጊስ ቀድሞ በስደት[5] ሳለ በዚያ የሚቀበር ስለመሰለው መቃብርን አስቆፍሮ ነበር። በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከለከለው። |

5. ሊቁ አባ ጊዮርጊስ የታሠሩበት ቦታ በመጽሐፈ ሰዓታትም አሰበው "እንዘ ንትቄከል ኪያኪ እምነ ኀሊና ወአፍ ውስተ አድባር አግብርትኪ ወርእሰ ጸድፍ እፎኑ ነአይል ከመ ዖፍ" እመቤታችን እኛ በነቢብም በኀሊናም በአንቺ ተአምነን ሳለ ወፍ ይመስል በየገደሉ ጫፍና በየተራራው ለምን እንከራተታለን ?በማለት ጸሎትን አቅርበዋል /ስብሐተ ፍቁር ዘእግዚእትነ/

፴ ወይቤሎ ዝየሰ ኢይከውን አላ መቃብሪከሰ ኀበ ተከዕወ ደሙ ለበጸሎተ ሚካኤል አቡከ ወመቃብሪሁኒ ሀለወ እስከ ይእዜ ወኢተከድነ፡፡

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

፴ የአንተ መቃብር በዚህ አይሆንም መቃብርህ የአባትህ የበጸሎተ ሚካኤል ደም በፈሰሰበት ነው እንጂ አለው፡፡ መቃብሩም እስከ ዛሬ ድረስ ሳይከደን አለ፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይኑር አሜን፡፡

## ምዕራፍፍ ፱

**ዘከመ ደረሰ መጽሐፈ ምስጢር**

## ምዕራፍ ዘጠኝ

**መጽሐፈ ምስጢርን እንደ ደረሰ**

፩ ወካዕበ በአሐቲ እመዋዕል እንበለ ይኩን መንፈቀ ሌሊት አንቅሖሙ ለደቂቁ ወይቤሎሙ ንዑ ንሑር ኀበ ቤተ ክርስቲያን፡፡

፩ ዳግመኛ ከዕለታት በአንደኛው የሌሊት እኩሌታ ሳይሆን ልጆቹን ቀሰቀሳቸው፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያንም እንሒድ አላቸው፡፡

፪ ወይቤልዎ ኢብጽሐ ጊዜ ወይቤሎሙ ኢትትኃከዩ ተንሥኡ ንሑር፡፡ ወእም ድኅረ ሖሩ ዐቀሞ መንፈስ ቅዱስ ማእከለ ፍኖት፡፡

፪ ጊዜው ገና ነው አልደረሰም አሉት፤ አትስነፉ ተነሡ እንሒድ አላቸው፡፡ ከሔዱም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ከመንገድ መካከል አቆመው፡፡

፫ ወመሠጠ ኀሊናሁ ውስተ ሰማያት ሰፍሐ እደዊሁ ወአንቃዕደወ ላዕለ፡፡ ወጐንደየ ጥቀ ወይቤልዎ ደቂቁ አ አቡነ ጊዮርጊስ ንባእ ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወእመ አኮ ንትመየጥ ውስተ ማኅደርነ፡፡

፫ ኅሊናውንም ወደ ሰማያት መሰጠው እጁንም ዘርግቶ ወደ ላይ አንጋጠጠ፤ እጅግም ዘገየ፡፡ ልጆቹ አባታችን ጊዮርጊስ ሆይ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንግባ ያም ባይሆን ወደ ቤታችን እንመለስ አሉት፡፡

፬ ወኢሰምዖሙ እስመ ከመ ተመሥጠ ልቡ ወኅሊናሁ ውስተ ሰማይ፡፡ ወሶቤሃ አስተርአየቶ እግዝእትነ ማርያም ወነገረቶ ፫ ቃላተ ዘእምከመ ሰመዮሙ ታድለቀልቅ ምድር፡፡

፬ ልቡም አሳቡም ወደ ሰማይ እንዲሁ ተመስጧልና አልሰማቸውም፡፡ ያን ጊዜ እመቤታችን ማርያም ተገለጸችለት፤ ጠራቸውም ምድር የምትነዋወጥባቸው ሦስት ቃላትን ነገረችው፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፳፮ በከመ ይቤ ዕዝራ ወሶበ ይነግረኒ በበህቅ ያድለቀልቅ መካን ኀበ እቀውም:: ወቶማስኒ ይቤ አንተ ውእቱ ዘፈለጥከኒ እምኲሉ ቢጽየ ወይቤለኒ ፫ ቃላተ ዘቦቱ ይትከሠት ኅሊናየ ወለባዕድሰ ነጊረ ኢያሆን ኢይክል::

፳፯ ወእንድርያስኒ ሐዋርያ ይቤሎ ለማትያስ ረሳእካኑ ለይእቲ ምስጢር ዘርኢነ እም ኀበ እግዚእነ እለ ሶበ ንትናገር ባቲ ታድለቀልቅ ምድር::

፳፰ ወለሐዋርያትኒ አመ ከልእዎሙ ሊቃነ ካህናት ከመ ኢይንግሩ ቃለ እግዚአብሔር አኀዙ ይጻልዩ ወእንዘ ይጻልዩ አድለቀለቀ ውእቱ ብሔር ኀበ ሀለዉ ይነብሩ ኅቡረ::

፳፱ ወከማሁ ለብፁዕኒ ጊዮርጊስ ሶበ ነገረቶ እግዝእትነ ማርያም ውእተ ፫ ቃላተ አድለቅለቀ ውእቱ መካን ኀበ ሀለወ ይቀውም:: ደንገፁ ንቁሓን ወተንሥኡ ንዉማን ወመሰሎሙ ዘንህለ መሠረታተ ምድር::

፴ ወእምዝ ተመይጠ ኅሊናሁ ውስተ ምድር:: ወይቤ ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘከሠተ ሊተ ኅቡኣቲሁ ወኢቦአ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወተመይጠ ውስተ ማኅደሩ:: ወይቤ አስተሳልም ሰማያውያነ ወምድራውያነ::

፳፮ ዕዝራ በየጥቂቱ በሚነግረኝ ጊዜ የቆምሁበት ቦታ ይነዋወጽ ነበር እንዳለ፤ ቶማስም ከወንድሞቼ ሁሉ የለየኸኝ አንተ ነህ አለ፤ ኅሊናየ የሚገለጥበት ሦስት ቃላትንም ነገረኝ ለሌላ ሰው ግን እነዚህን መናገር አይቻለኝም::

፳፯ ሐዋርያው እንድርያስም ማትያስን በእርሷ በምንነጋገር ጊዜ ምድር የምትነዋወጥበት ከጌታችን ያየናት ያችን ምስጢር እረሳሃትን አለው::

፳፰ ሐዋርያትንም የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይናገሩ የካህናት አለቆች በከለከሏቸው ጊዜ ይጸልዩ ጀመሩ:: "ሲጸልዩም በአንድነት ተሰብስበው የነበሩበት ቦታ ተናወጠ:: የሐዋ.ሥራ.፬፥፴፩

፳፱ እንዲሁ እመቤታችን ለብፁዕ ጊዮርጊስ እኒህን ሦስት ቃላት በነገረችው ጊዜ ቆሞበት የነበረው ቦታ ተናወጸ፤ የነቁት ደነገጡ፤ የተኙትም ተነሡ:: የምድርም መሠረት የፈረሰ መሰላቸው::

፴ ከዚህ በኋላ ኅሊናው ወደ ምድር ተመለሰ:: የተሰወረውን ለገለጸልኝ እግዚአብሔር ምስጋና ይሁን አለ:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ሳይገባ ወደ ቤቱ ተመለሰ:: ሰማያውያንና ምድራውያንንም አስማማ /አስማማለሁ/ አለ::

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲ ወሶቤሃ ለብፁዕ ጊዮርጊስ በሰሚዓ ውእቱ ቃል ፈድፈደት አእምርቱ ወተርኀወ አንቀጸ ልቡ። ወሀለዉ ሎቱ ጥራዛት ንቡራን ፈቂዶ ከመ ያጽሕፍ ቦን ኦሪተ።

፲ ያን ጊዜም ብፁዕ ጊዮርጊስ ያንን ቃል በመስማቱ ዕውቀቱ በዛችለት የልቡናው በርም ተከፈተለት የኦሪትን መጽሐፍ ያጽፍ ዘንድ ወድዶ ያስቀመጣቸው ጥራዞች ነበሩት።

፲፩ ወአዘዘ ያምጽእዎሙ ለ፭ ጸሐፍት ወአኅተወ ማኅቶተ ብዙኀ እስከ ይመስል መዓልተ። ወይቤሎሙ ለእሙንቱ ጸሐፍት አፍጥኑ ጽሒፈ ዘነገርኩክሙ።

፲፩ አምስቱንም ጸሓፊዎች ያመጥዋቸው ዘንድ አዘዘ። ሌሊቱም ቀን እስኪመስል ድረስ መብራት አበራ። እኒያንም ጸሓፊዎች የምነግራችሁን ለመጻፍ ፍጠኑ አላቸው።

፲፪ ወኀደሩ እንዘ ይጽሕፍ እስከ ይጸብሕ ወይነግሮሙ በበጾታሁ። ወወዐሉ እስከ ይመሲ እንዘ ይጽሕፉ ውእተ መጽሐፈ።

፲፪ በየክፍሉ እየነገራቸው እስኪነጋ ድረስ ሲጽፉ አደሩ። ያንም መጽሐፍ እስኪመሽ ድረስ ሲጽፉ ዋሉ።

፲፫ ወበሳኒታ ዕለት ጸሐፉ እስከ ይመሲ በመንፈቀ አሐዱ ሌሊት ወበ፪ቱ ዕለታት ፈጸምዎ ለውእቱ መጽሐፍ በረድኤተ እግዚአብሔር ዘያነቅህ ለወጢን ወያተግህ ለፈጽሞ።

፲፫ በማግሥቱም እስኪመሽ ድረስ ጻፉ። በአንድ ሌሊት እኩሌታና በሁለት ቀናትም ለመጀመር በሚያነቃ ለመፈጸምም በሚያተጋ በእግዚአብሔር አጋዥነት ያን መጽሐፍ ፈጸሙት።

ወሶበ አስተጋብእዎ እሙንቱ ጸሐፍት
፲፬ ለውእቱ መጽሐፍ አስተዐጸቡ ፈድፋደ። ወአቡነሂ ጊዮርጊስ ርእዮ አንከረ ጥቀ ወተፈሥሐ ልቡ ወይቤ አንሰ ኢነበብኩ ዘንተ መጽሐፈ አላ መንፈስ ቅዱስ ተናገረ በአፉየ።

፲፬ እኒያም ጸሐፊዎች ያን መጽሐፍ በሰበሰቡት ጊዜ እጅግ አደነቁ አባታችን ጊዮርጊስም አይቶ ፈጽሞ አደነቀ ልቡም ደስ ተሰኘ እኔ ይህን መጽሐፍ አልተናገርሁም መንፈስ ቅዱስ በአፌ ተናገረ እንጂ አለ።

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፭ | ስብሐት ለእግዚአብሔር አምላኪየ ዘከሠተ ሊተ ዘንተ ኵሎ ሠናያተ፡፡ ወሰመዮ ለውእቱ መጽሐፍ መጽሐፈ ምስጢር፡፡ እስመ ውእቱ ይነግር ምስጢራተ ዘመለኮት፡፡ | ፲፭ | ይህን ሁሉ መልካም ነገር ለገለጸልኝ ፈጣሪዬ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ያንም መጽሐፍ መጽሐፈ ምስጢር አለው የመለኮትን ምስጢር ይናገራልና፡፡ |
| ፲፮ | ዝሰ ነገር ይመስል ግብረ ዕዝራ ነቢይ ዘአጽሐፈ ኦሪተ ወነቢያተ በኅዳጥ መዋዕል፡፡ ወበእንተዝ ኵሉ ኮነ ስምዐ ፩ ቀሲስ ዘስሙ ገብረ ማርያም ዘፍጹም ወኵሉ ምግባረ ሠናይ ዘከመ ርእየ ወሰምዐ ዘጽድቅ ውእቱ ስምዑ ወእምአፉሁ አይድአኒ ሊተ ለነዳይ፡፡ | ፲፮ | ይህም ነገር በአጭር ጊዜ ኦሪትንና ነቢያትን ያጻፈ የነቢዩ ዕዝራን ሥራ ይመስላል፡፡ ስለዚህም ሁሉ በሥራው ሁሉ ፍጹም የሆነ ስሙ ገብረ ማርያም የሚባል አንድ ቄስ እንደ ሰማና እንዳየ ምስክርነቱም እውነት እንደ ሆነ ምስክር ሆነ፡፡ ለእኔም ለድኃው በአንደበቱ ነገረኝ፡፡ |
| ፲፯ | ተብህለ በ፩ እመዋዕል መጽኡ ነጋድያን እምሰብአ ኢየሩሳሌም፡፡ ወረከብዎ ለውእቱ መጽሐፍ ወአጥረይዎ በብዙኅ ንዋይ፡፡ | ፲፯ | ከዘመኑም በአንድ ወቅት ከኢየሩሳሌም ሰዎች ነጋድያን እንደ መጡ ተነገረ፡፡ ያንም መጽሐፍ አግኝተው በብዙ ገንዘብ ገዙት፡፡ |
| ፲፰ | ወእንዘ ይትመየጡ ውስተ ሀገሮሙ ሀለዉ በውስተ ፍኖት ወተማከሩ እንዘ ይብሉ ንዑ ንሕጽቦ ለዝንቱ መጽሐፍ ከመ ይትዐወቅ ለእመ እሙን ውእቱ ነገሩ ወለእመ ጽሩይ፡፡ | ፲፰ | ወደ አገራቸውም ሲመለሱ በመንገድ ሳሉ ቃሉ የታመነና ንጹሕ እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ ኑ ይህን መጽሐፍ እንጠበው ብለው ተማከሩ፡፡ |
| ፲፱ | ወቦኡ ውስተ ማይ ወሐጸብዎ ቀሊያሙ በበ፩ ክርታስ ከመ ዘያነብብ ወኢለከፎ ውእቱ ማይ፡፡ ወአንከሩ ጥቀ እሉ ነጋድያን ወአወፅእዎ ወአንበርዎ በክብር ወሰገዱ ሎቱ፡ | ፲፱ | ወደ ውኃውም ገብተው እንደ ሚያነብብም ሰው እያንዳንዱን ብራና ገልጠው አጠቡት ውኃውም አልነካውም እሊያም ነጋዴዎች እጅግ አደነቁ ከውኃው አውጥተው በክብር አስቀመጡት ሰገዱለትም፡፡ |

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፳ ወአብጽሕዎ ለውእቱ መጽሐፍ ኀበ ኢየሩሳሌም፡፡ ወዜነዉ ዘንተ ተአምረ ዘገብረ በውስተ ፍኖት ኀይለ ጸሎቱ ለአቡነ ጊዮርጊስ ወአንከሩ ጥቀ ሰብአ ኢየሩሳሌም፡፡

፳ ያንም መጽሐፍ ወደ ኢየሩሳሌም አደረሱት የአባታችን ጊዮርጊስ የጸሎቱ ኀይል በመንገድ ያደረገውን ይህን ተአምር ተናገሩ፡፡ የኢየሩሳሌምም ሰዎች እጅግ አደነቁ፡፡

፳፩ ወይእዜሰ ርቱዕ ሊተ እንግር ምሳሌያተ ግብሩ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡ወሶበ ይነግር ልደተ አበው ወይምህር አሪተ ወይመስል ከመ ዘሀሎ አሜሃ ምስለ ሙሴ፡፡ወሶበ ይነግር ቃለ ትንቢት ይመስል ከመ ፩ እምነቢያት፡፡

፳፩ አሁንም የአባታችን ጊዮርጊስ የሥራውን ምሳሌዎች እናገር ዘንድ ይገባል፡፡ የአበውን ልደት በተናገረና አሪትን ባስተማረ ጊዜ ያን ጊዜ ከሙሴ ጋር የነበረ ይመስላል፡፡ የትንቢትንም ቃል በተናገረ ጊዜ ከነቢያት እንደ አንዱ ይመስላል፡፡

፳፪ ወሶበሂ ይነግር ወንጌለ ይመስል ምስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመሀረ ወምስለ ሐዋርያት ዘአማኀበረ፡፡

፳፪ ወንጌልንም ባስተማረ ጊዜ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የነበረ ከሐዋርያትም ጋር አንድ ሁኖ ያስተማረ ይመስላል፡፡

፳፫ ሶበኒ ይነግር ግብረ ጻማሆሙ ለሰማዕት ይመስል ከመ ዘቆመ ምስሌሆሙ ቅድመ ነገሥት ከሓድያን በሰዓተ ኰነኔሆሙ፡፡

፳፫ የሰማዕታትንም የመከራቸውን ገድል በተናገረ ጊዜ በፍርድ ሰዓት ከከሓድያን ነገሥታት ፊት ከእነርሱ ጋር የቆመ ይመስላል፡፡

፳፬ ወሶበሂ ይዜኑ ጻማሆሙ ወምንዳቤሆሙ ለመነኮሳት ይመስል ከመ ዘተዓፅወ ምስሌሆሙ ውስተ ገዳም ወተመከረ ከማሆሙ በአጋንንት፡፡

፳፬ የመነኮሳትን ችግራቸውንና ድካማቸውን በተናገረ ጊዜ በገዳም ከእነርሱ ጋር የተዘጋ እንደ እነርሱም በአጋንንት የተፈተነ ይመስላል፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፷፫ ሶበ ይነግር ሥርዐተ ተክህኖ ዘሰማያውያን ይመስል ከመ ዘርእዮሙ ለሱራፌል፡፡ ወሶበኒ ይነግር ድምፀ ሑረቶሙ ለኪሩቤል ዘበግርማ ይመስል ከመ ዘሰምዖሙ፡፡

፷፫ የሰማያውያንን የክህነት ሥርዐት በተናገረ ጊዜ ሱራፌልን ያያቸው ይመስላል፡፡ የሚያስፈራ የኪሩቤልን ያካሔዳቸውን ድምፅ በተናገረ ጊዜ የሰማቸው ይመስላል፡፡

፷፬ ሶበኒ ይነግር ዜና ስብሐቶሙ ለመላእክት ትጉሃን ይመስል ቢጾሙ፡፡ ወሶበኒ ይትናገር ምስጢረ መለኮት ዘተዋሕዶ ዘእንበለ ቱሳሔ ወሥሉስ ዘእንበለ ቡዓዴ ወዕሩይ ዘበህላዌ ይመስል ካልኡ ለዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፡፡

፷፬ የትጉሃን መላእክት የምስጋናቸውን ዜና በተናገረ ጊዜ ባልንጀራቸው ይመስላል፡፡ ያለ ጭማሪ የመለኮትን ተዋሕዶ ያለ መለየትም በአኗኗር ትክክል የሆነ የሦስትነትን ምስጢር በተናገረ ጊዜ ሁለተኛው ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ይመስላል፡፡

፷፭ ሶበኒ ይዜኑ ትስብእተ ዋሕድ ይመስል ከመ ዘተልእከ ምስለ ገብርኤል፡፡ ወሶበኒ ይዜኑ ንጽሓ ወድንግልናሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል በኵሉ ጊዜ ወወሊዶታ ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ወኢሩካቤ ይመስል ከመ ዮሴፍ ወሰሎሜ እለ ህልዋን ምስሌሃ፡፡

፷፭ የወልድ ዋሕድ ሰው መሆንንም በተናገረ ጊዜ ከገብርኤል ጋር የተላከ ይመስላል፡፡ ሁል ጊዜ ድንግል የምትሆን የእመቤታችን ማርያም ድንግልናዋንና ንጽሕናዋን ያለዘርዐ ብእሲና ሩካቤ መውለዷንም በተናገረ ጊዜ ከእርሷ ጋር የነበሩ ዮሴፍንና ሰሎሜን ይመስላል፡፡

፷፮ እስመ አጥረየ አቡነ ጊዮርጊስ መጽሔተ አእምሮ ዘመንፈስ ቅዱስ ከመ ይርአይ ቦቱ ምሥጢረ ዘብሉይ ወሐዲስ ዘሰማይ ወምድር፡፡ ወተውህቦ አፈ ጥበብ በዘ ያረትዕ ፍኖተ ቃል ዘበአማን፡፡

፷፮ አባታችን ጊዮርጊስ የብሉይና የሐዲስ የሰማይና የምድር ምስጢርን ያይ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ የዕውቀት መስዎት አግኝቷልና እውነተኛ የወንጌል ጎዳናን የሚቀናበትም የጥበብ አንደበት ተሰጠው፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፷፱ | ወእንዘ ሀሎ አቡነ ጊዮርጊስ ውስተ ኢትዮጵያ ሀገሩ አንሶሰወት እግረ ኀሊናሁ ውስተ ኵሎን አህጉር ወበሓውርት እለ ፈጸመ እግዚእ በውስቴቶን ሥርዐተ ትስብእት ዘእንበለ ኀጢአት ባሕቲታ፡፡ | ፷፱ | አባታችን ጊዮርጊስ በሀገሩ ኢትዮጵያ ሳለ የእግሩ ኀሊና ከብቻዋ ከኀጢአት በቀር ጌታችን የሰውነትን ሥርዐት በፈጸመባቸው አገሮችና አውራጃዎችን ሁሉ ተመላለሰች፡፡ |
| ፸ | ወዓዲ ተውህቦ ለአቡነ ጊዮርጊስ ከመ ሄኖክ ወልደ ያሬድ ወከመ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት ከመ ያእምር ምሕዋረ ፀሓይ ወወርኀ ወከዋክብት ጥንተ ወተፍጻሜተ ማእከለ ወመዋዕለ መሳክወ ነፋሳት ወምርዋጸ ከዋክብት ወወርኃ ወኵሎ ምስጢረ ሚጠተ ብርሃናት፡፡ | ፸ | ዳግመኛም ለአባታችን ጊዮርጊስ እንደ ያሬድ ልጅ እንደ ሄኖክ፤ እንደ ዳዊት ልጅ እንደ ሰሎሞንም የፀሐይን፤ የጨረቃና የከዋክብትንም፤ መንገድ መጀመሪያውንና መጨረሻውን፤ መካከለኛውንና ዘመኑን፤ የነፋትን መስኮቶች፤ የከዋክብትና የጨረቃን መሮጫ የብርሃናትንም መመላሻ ምስጢር ሁሉ ያውቅ ዘንድ ተሰጠው፡፡ |
| ፸፩ | ወንፍሐተ ነፋሳት ለበረከት ወለድምሳሴ ወምስጢረ ደብተራ ዘሙሴ ወምስጢረ መቅደስ ዘሰሎሞን ወሕዝቅኤል፡፡ | ፸፩ | ለበረከትና ለጥፋት የሚነፍሱ ነፋሳትን የሙሴን የድንኳን ምስጢር የሰሎሞንና የሕዝኤልን የመቅደስ ምስጢር ያውቅ ዘንድ ተሰጠው፡፡ |
| ፸፪ | ወኮሎ ርእየ ወጠየቀ በዘሰትየ ጽዋዕ እምእዴሃ ለእመ ብርሃን ወበተምህሮ ፩ተ ቃላት[6] እምአፉሃ ወበለብዎ ፫ ቃላት እለ ነገረቶ ዘውእቶሙ ክፍላተ መዝሙር ዘዳዊት[7] በከመ ነገርነ ቅድመ እስመ አእምሮ ኀቡኣት ይሁብ እግዚአብሔር በመዝሙረ ዳዊት፡፡ | ፸፪ | በብርሃን እናት እጅ ጽዋዕ በመጠጣቱ ከአንደበቷም አምስቱን ቃላት[6] በመማሩ፤ የነገረችው ሦስቱንም ቃላት በመገንዘቡ ሁሉን አይቶ ተረዳ፡፡ እነዚህም አስቀድመን እንደተናገርን የዳዊት መዝሙር ክፍል ናቸው፡፡ እግዚአብሔር በዳዊት መዝሙር የተሰወረ ምስጢርን ይገልጣልና፡፡ |

6. ከቀድሞ ጀምሮ ካለው የሊቃውንት ትርጉም ትውፊት እንደምንረዳው እነዚህ ቃላት ከሞዋርት ወይም ከድብቅ አስማት ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከቅዱሳት መጽሐፍት ጋር የተገኙት ትምህርቶች ናቸው፡፡ በዚህ ገድል ላይ ጸሐፍቱ እንዳስገነዘቡት አምስቱን ቃላት በመዝሙረ ዳዊት ክፍሎች፤ ከሙሴ አምስት መጻሕፍት፤ ከአምስት የተግሳጽና የምክር መጻሕፍት ወይም ከትምህርተ ሃይማኖት አናቅጽ ጋር ሲሆን ሦስቱን ቃላት ደግሞ ከነቢያት ከሐዋርያትና ከሊቃውንት ሥርዐት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፴፫ ወፍካሬ ፫ቱ ቃላት እሉ እሙንቱ ቀዳሚ ትምህርተ ሥርዐት ዘሐዋርያት ወዳግም ዘነቢያት ወሣልስ ዘሊቃውንት። በከመ ንቤ ንሕነ።

፴፫ የሦስቱ ቃላት ትርጉምም እኛ እንዳልነው የመጀመሪያው የሐዋርያት ሥርዐተ ትምህርት፣ ሁለተኛው የነቢያት ሦስተኛው የሊቃውንት ነው።

፴፬ ወካልኣንሰ ይብሉ በእንተ እልኩ ፫ ቃላት ወ ፫ እለ ነገሮቶ እግዝእትነ ምስጢራት ካልኣት እማንቱ እምከመ ደገሞን ወትረ ታድለቀልቅ ምድር ኀበ ሀሎ።

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን።

፴፬ ሌሎች ግን እመቤታችን ስለ ነገረችው ስለ አምስቱ ቃላትና ሦስቱ ቃላት ሌሎች ምስጢራት ናቸው። ዘወትር ከጸለያቸው ምድር ካለችበት ትናወጣለች ይላሉ።

ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።

## ምዕራፍ ፲

## ምዕራፍ ዐሥር

፩ ንትመየጥኬ ካዕበ ኀበ ነጊረ ገድሉ። ሶበ ይነብር አቡነ ጊዮርጊስ ውስተ ማዕድ ወያቄርቡ ሎቱ መቃስማተ ጥዑማተ። ይቤሎ ለረድኡ ዮምሰ ኢያሠነይከ ወበዕለተ አሕሠመ ይቤሎ ሠናየ ገበርከ። ዘንተ ይቤ ከመ ኢይትዐወቅ ጾሙ።

፩ ዳግመኛ ገድሉን ወደ መናገር እንመለስ አባታችን ጊዮርጊስ በማዕድ በተቀመጠ ጊዜ የሚጣፍጡ ምግቦችን ሲያቀርቡለት አገልጋዩን ዛሬ ጥሩ አላደረግህም የማይጣፍጥ ባቀረበ ጊዜ ዛሬ ጥሩ ሠራህ ይለው ነበር።ይህንም የሚል ጾሙ እንዳትታወቅ ነው።

ወሶበኒ ያመጽኡ ሎቱ ሥጋ ወወይነ
፪ በመዋዕለ መከራሁ። ይኄንና
ለነፍሱ ወይቤላ ትፈትዊኑ አ ነፍስየ
ከመ ትጽገቢ በዝየ ወበከሐሰ
ትርኀቢ።

በተጋድሎውም ወራት ሥጋና
፪ ወይን ባመጡለት ጊዜ ነፍሱን
ይገሥጻታል። ነፍሴ ሆይ በዚህ
ልትጠግቢ በወዲያኛው ልትራቢ
ትወጃለሽን ይላታል።

# <u>ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፫ | ዘንተ ብሂሎ ኢይጥዕም ምንተኒ ወባሕቱ ያስተርኢ ለዓይነ ሰብእ ከመ ዘበልአ፡፡ ወእምድኅረ ፈጸመሰ ምንኩስና አግሀደ ሕርመተ ዘይደልዎሙ ለመነኮሳት፡፡ | ፫ | ይህንንም ብሎ ምንም አይቀምስም፤ ነገር ግን ለሰው ዐይን እንደሚመገብ ሰው መስሎ ይታይ ነበር፡፡ ምንኩስናውን ከፈጸመ በኋላ ግን ለመነኮሳት የሚገባውን ትርኅምት ገለጸ፡፡ |
| ፬ | ሶበኒ ይለብስ ሰቀ ይለብስ ታሕተ መልበሱ ከመ ኢያእምሮ ሰብእ ትጋሆ፡፡ ወኢይጥዕም በመዋዕለ ደዌሁ ዘእንበለ ዓሣ በከመ አዘዙ አበው፡፡ | ፬ | ማቅም በለበሰ ጊዜ ሰው ትጋቱን እንዲያውቅበት በልብሱ ውስጥ ይለብስ ነበር፡፡ በሕመሙም ጊዜ አበው እንዳዘዙ ከዓሣ በቀር አይቀምስም ነበር፡፡ |
| ፭ | ሶበኒ ይበውእ ውስተ ቤተ ክርስቲያን አኮ ዘይቀውም ጽሩዐ አላ ዳእሙ ይቀውም በገቦሁ ለካህን ዘይቄድስ፡፡ ወይነግሮ ሥርዐተ ምስጢር በጥንቃቄሃ፡፡ | ፭ | ወደ ቤተ ክርስቲያን በገባ ጊዜ ዝም ብሎ አይቆምም ነበር፡፡ በቀዳሹ ካህን ጐን ይቆም ነበር እንጂ የምስጢር ሥርዐትንም በጥንቃቄ ይነግረው ነበር፡፡ |
| ፮ | ወለዘኒ የዐጥን ይኤምሮ ሥርዓተ ዕርገተ ዕጣን፡፡ ወለሕዝብኒ ይኤምሮሙ ከመ ይቁሙ በጽማዌ ወይጸልዩ በአስተሐምሞ፡፡ ወይትመጠዉ እም ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ | ፮ | ዕጣን ለማያጥነውም የዕጣን ዕርገት ሥርዐትን ያሳየው ነበር፡፡ ሕዝቡንም በጸጥታ እንዲቆሙና በትጋት እንዲጸልዩ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሥጋና ደምም እንዲቀበሉ ያስተምራቸው ነበር፡፡ |
| ፯ | ወእምዝ ካዕበ አሐተ ዕለተ እምነ መዋዕል ቦአ አቡነ ጊዮርጊስ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወለብሰ አልባሰ ክህነት ወተክህነ፡፡ ወሶበ ፈጸመ ጸሎተ ቅዳሴ ተክህኖ ወተመጠዎ በእዴሁ ለእንፎራ ዘምስጢር ከመ ይሡዖ፡፡ | ፯ | ከዚህም በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን አባታችን ጊዮርጊስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገባ የክህነት ልብስን ለብሶ አገለገለ፡፡ የቅዳሴውን ጸሎት በፈጸመ ጊዜ የምስጢር መሥዋዕቱን ለመሠዋት በእጁ ተቀበለ፡፡ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፰ በጊዜሃ አስተርአየ ዓምደ ብርሃን ወወረደ እምሰማይ ወቆመ ዲበ ጠረጴዛ፡፡ ወእደዊ ሁኒ ኮና ከመ ፲ መኃትው እለ ያንበለብል ወኅብስትኒ[7] አስተርአየ በአምሳለ በግዕ ፀዓዳ ዘይሜጡ ክሳዶ ለተሐርዶ፡፡

፰ ያን ጊዜ የብርሃን ዐምድ ታየ፡፡ ከሰማይም ወርዶ በመንበሩ ላይ ተተከለ፡፡ እጆቹም ቦግ ቦግ እንደሚል ዐሥር መብራቶች ሆኑ፡፡ ኅብስቱም[7] አንገቱን ለመታረድ እንደሚሰጥ ነጭ በግ ሆኖ ታየ፡፡

፱ ሶቤሃ አጽነነ ርእሶ አቡሁ ሰማያዊ ከመ ይርአይ ጥብሐተ ወልዱ በእንተ ቤዛ ብዙኃን፡፡ ወዓዲ ቀነጸ መንፈስ ቅዱስ እምዲበ ሠረገላ ዘኪሩቤል ወወረደ ዲቤሁ በርእየተ ርግብ ጸዓዳ፡፡ ወጸለለ ዲቤሁ በአክናፊ ብርሃን ኃይለ ተንበሎ፡፡

፱ ያን ጊዜ ሰማያዊ አባቱ ስለ ብዙዎች የተሠዋ የልጁን መሥዋዕት ያይ ዘንድ ራሱን ዘንበል አደረገ፡፡ ዳግመኛም መንፈስ ቅዱስ ከኪሩቤል ሠረገላ ላይ በነጭ ርግብ አምሳል ወረደ፡፡ የብርሃንም ክንፎች በመሥዋዕቱ ላይ በኀይል ተጋረደ፡፡

፲ ወብርሃን ተደብተረ ውስተ ዐዘቅተ ጠፈራ ለቤተ ክርስቲያን፡፡ ኪሩቤል አንከረ ሶበ ርእዮ እንዘ ይጠብሖ ለበግዐ አርያም፡፡ ወሱራፌል ፈርሀ ሶበ ነጸሮ ለአቡነ ጊዮርጊስ ካህነ ወንጌል እንዘ ይፌትቶ ለፍሕም ዘእንበለ ጉጠት፡፡

፲ የብርሃንም ድንኳን በቤተ ክርስቲያኒቱ ጠፈር ዙሪያ ተተከለ፡፡ ኪሩቤል የአርያም በግን ሲያርደው ባየ ጊዜ አደነቀ ሱራፌልም የወንጌል ካህን አባታችን ጊዮርጊስ እሳትን ያለ ጉጠት ሲፈትተው ባየው ጊዜ ፈራ፡፡

፲፩ ወእለ ርእዩ እምርሑቅ መጽኡ እንዘ ይረውጹ ለረድኤት እስመ መሰሎሙ ዘውዕየት ቤተ ክርስቲያን፡፡ ወሶበ ርእዩ አንከሩ ወሰብሕዎ ለአቡነ ጊዮርጊስ ወይቤልዎ ዝንቱሰ አቡነ ብእሲ ሰማያዊ ወመልአክ ምድራዊ፡፡ እስመ ገሠሣ አእዳዊሁ እሳተ ዘመለኮት፡፡

፲፩ ከሩቅ ያዩ ሰዎችም ቤተ ክርስቲያኒቱ የተቃጠለች ስለመሰላቸው ለመርዳት እየሮጡ መጡ፡፡ ባዩም ጊዜ አደነቁ አባታችን ጊዮርጊስንም አደነቁት ይህ አባታችን ሰማያዊ ሰው ምድራዊ መልአክ ነው አሉት፡፡ እጆቹ የመለኮትን እሳት ዳስሰዋልና፡፡

---

7 ይህ በኦርቶዶክሳውያን እምነት ኅብስቱና ወይኑ ወደ ቅዱስ ሥጋውና ወደ ክቡር ደሙ የሚለወጥ መሆኑን የሚገልጽ ምስጢር ያለው አስደናቂ ተአምር ነው፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፪ ወለነኒ ብፁዓን አዕይንቲነ እለ ርእያ ወአእዛናቲነ እለ ሰምዓ ወአተዉ ውስተ ማኅደሮሙ እንዘ ያነክሩ፡፡ ወካዕበ አቡነ ጊዮርጊስ ጥንቁቅ በኵሉ ትእዛዛት በ፲ ቃላት ዘእምኦሪት ወለ፮ ቃላት ዘእም ወንጌል፡፡

፲፪ የእኛም ያዩ ዐይኖቻችን የሰሙ ጆሮቻችን ብፁዓን ናቸው፡፡ እያደነቁም ወደ ቤታቸው ገቡ፡፡ ዳግመኛም አባታችን ጊዮርጊስ ከኦሪት በዐሠርቱ ትእዛዛት ከወንጌልም በስድስቱ ቃላት የተጠነቀቀ ነበር፡፡

፲፫ ወፈድፋደሰ ይጠነቅቅ በእንተ አክብሮ ክልኤሆሙ ሰንበታት በከመ አዘዙ ሐዋርያት በሲኖዶሶሙ፡፡ ወዐቀመ ስብሐታተ ማኅሌት ወአስተቃሰመ ቃላተ ምድራሳት በአስተጋብኦ ሐዲስ ወብሉይ በእንቲአሆን፡፡

፲፫ በይበልጥም ሐዋርያት በሲኖዶስ እንዳዘዙ ስለ ሁለቱ ሰንበታት አከባበር ይጠነቅቅ ነበር፡፡ የማኅሌት ምስጋናዎችን አዘጋጀ፡፡ ስለ እነርሱም ከሐዲስና ከብሉይ በመሰብሰብ የድርሰት ቃላትን አስተካከለ፡፡

፲፬ ወባዕላተኒ ኵሎ ያከብር በተጠናቅቆ በከመ ሕገ ሐዋርያት፡፡ ወለጾመ አይሁድኒ ኢይጸውም በከመ ሕገ ሐዋርያት ሶበ ኢኮነ ረቡዐ ወዓርበ ወበዓለ ፶ ወርደተ መንፈስ ቅዱስሂ ሰቡዐ መዋዕለ ይገብር በከመ አዘዙ ሐዋርያት በዲድስቅልያሆሙ፡፡ ከመዝ ይሜህር ለደቂቁ

፲፬ በዓላትንም ሁሉ እንደ ሐዋርያት ሕግ በጥንቃቄ ያከብራል ረቡዕና ዓርብ ካልሆነ በስተቀር እንደ ሐዋርያት ሕግ የአይሁድን ጾም አይጾምም፡፡ መንፈስ ቅዱስ የወረደበት በዓለ ሃምሳን ሐዋርያት በዲዲስቅልያ እንዳዘዙ ሰባት ቀን ያከብራል፡፡ ለልጆቹ /ለተማሪዎቹ/ እንዲህ ያስተምራል፡፡

፲፭ ወይቤ ለኵሉ መነኮስ ዘይጸውም በጳንጠቆስጤ ወለዘሂ ይበልዕ በካልኣት መዋዕላት ኢይበጽሕ ጸሎቱ፡፡ ወባሕቱ ዘሰ ይጸውም አፈድፊደ ረባሐ እስመ ይቤሉ አበው አልቦሙ ፋሲካ ለመነኰሳት እስከ ዕለተ ሞቶሙ፡፡

፲፭ ለመነኮሰ ሁሉ በበዓለ ሃምሳ የሚጾም በሌሎች ቀናት የሚበላ ጸሎቱ አይደርስም ይላል፡፡ ነገር ግን ዘወትር የሚጾም ዋጋውን አበዛ፤ አባቶች ለመነኮሳት እስከ ዕለተ ሞታቸው ፋሲካ የላቸውም ብለዋልና፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፮ ጾመ ሥጋሰ ወወይን ስሩዕ ውእቱ ለመነኮስ ወከመ አዘዙ ፫፻ በሕንጻ መነኮሳት፡፡ ወለዝኩሉ ዘመሀረቶ ለብፁዕ ጊዮርጊስ ጥበብ እንተ እምላዕሉ ትትፌኖ እስመ አብደራ እምንእሱ፡፡

፲፮ የሥጋና የወይን ጾም ግን ሦለስቱ ምእት በሕንፃ መነኮሳት እንዳዘዙ ለመነኮሴ የተሠራ ነው፡፡ ይህንንም ለብፁዕ ጊዮርጊስ ሁሉ ያስተማረችው ከላይ የምትላክ ጥበብ ናት ከሕፃንነቱ ጀምሮ ወድዷታልና፡፡

፲፯ ወኀሠሣ በጸሎቱ ወተውህበቶ እም ኀበ እግዚአብሔር፡፡ በከመ ይቤ ኢያሱ ወልደ ሲራክ እንዘ ንኡስ አነ ዘአንበለ እስሐት ኀሠሥክዋ ለጥበብ ወአብደርክዋ በጸሎትየ፤ ወበቅድመ መቅደስ ሰአልኩ በአንቲአሃ ወለዝሉፉ አኀሥሣ፡፡

፲፯ በጸሎቱ ፈለጋት ከእግዚአብሔርም ተሰጠቸው፡፡ የሲራክ ልጅ ኢያሱ ታናሽ ሳለሁ ያለ ዕረፍት ጥበብን ፈለግኋት በጸሎቴም መረጥኋት፤ ስለ እርስዋም በመቅደሱም ፊት ለመንሁ፤ ለዘወትርም እፈልጋታለሁ እንዳለ፡፡

፲፰ ወሠረፀ ፍሬሃ ከመ ቆዓ ቀምሕ ወተፈሥሐ ልብየ ባቲ ወቆማ እገርየ በጽድቅ፡፡ እምንእስየ ተለውኩ ዐሠራ ወአጽማዕኩ በእዝንየ ወኀረይክዋ፡፡

፲፰ ፍሬዋም እንደሚበላ ተክል በቀለ፤ ልቤ ተደሰተባት እግረቼም በእውነት ቆሙ፡፡ ከታናሽነቴ ጀምሮ ፍለጋዋን ተከተልሁ፡፡ በጆሮዬም ሰምቼ መረጥኋት፡፡

፲፱ ወከማሁኬ ብፁዕ ጊዮርጊስ ብዙኀ ጥበበ ኀረየ ተምህረ ኀቡኣቲሃ ወተለወ ድኅሬሃ ዐሠራ ወዐቀበ ፍናዊሃ ሐወጸ እንተ መሳክዊሃ ወአጽምአ በውስተ አናቅጺሃ፡፡

፲፱ እንዲሁም ብፁዕ ጊዮርጊስ ብዙ ጥበብን መረጠ፤ ምስጢሮቿን ተማረ ፍለጋዋን ተከተለ፤ መንገዷን ጠበቀ፤ መስኮቶቿን ተመለከተ፤ በበሮቿም አዳመጠ፡፡

፳ ኀደረ ቅሩበ ቤታ ወተከለ መታክሊሁ ውስተ አረፋቲሃ ወዐቀመ ደባትሪሁ ወስተ አዕዋዲሃ ኀደረ ውስተ ማኀደራ ሠናይ ወቤተ ታሕተ አዕፁቂሃ አጽለለ እምነ መርቄ ታሕቴሁ፡፡

፳ በቤትዋ አቅራቢያ አደረ፤ በቅጽሮቿ ችካሎቹን ተከለ፤ በዐደባባይዋ ድንኳኑን አቆመ፡፡ በአማረ ቤቷም አደረ ከቆላ ሐሩርም በቅርንጫፎቿ ተጠለለ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፷፩ ወአዕረፈ በውስተ ክብራ ወዐቀበ ሕጋ ወረከባ ይእቲኒ ሐፀነቶ ከመ እሙ ወሐቀፈቶ ከመ ብእሲት ድንግል፡፡ ሴሰየቶ እክለ ጥበብ ወአስተየቶ ማየ አእምሮ፡፡ ተመርጕዞ ባቲ ወኢተንተነ አምነ ባቲ ወኢተሐፍረ፡፡

፷፩ በክብሯ ውስጥ ዐረፈ፤ ሕግዋንም ጠበቀ፤ እርስዋም እንደ እናት አሳደገችው፡፡ እንደ ድንግል ሴትም አቀፈችው፡፡ የጥበብ ምግብን መገበችው፡፡ የዕውቀትንም መጠጥ አጠጣችው፤ በእርስዋ ተመረጕዞ ከእርስዋም ለመውደቅ አልተፍገመገመም አላፈረም፡፡

፷፪ አዕበየቶ እምነ ቢጹ ወበማእከለ ማኅበር ብዙኅ ከሠተት አፉሁ፡፡ ወወሀበቶ አክሊለ ጥበብ ወትፍሥሕተ ወሐሤት፡፡ ወሀበቶ ስመ ዘለዓለም ወኮነቶ ወልታ ወተልዕለ ባቲ፡፡

፷፪ ከወንድሞቹ በላይ ከፍ ከፍ አደረገችው በብዙ ማኅበር መካከልም አንደበቱን ከፈተችለት፤ የጥበብ አክሊልንና ፍጹም ደስታንም ሰጠችው፤ የዘለዓለም ስምን ሰጠችው፤ ጋሻ ሆነችው በእርስዋም ከፍ ከፍ አለ፡፡

፷፫ ወአሐተ ዕለተ በጽሐ አቡነ ጊዮርጊስ ኀበ አባ ስምዖን ወአባ ሲኖዳ እንዘ ሀለዉ ውስተ በአተ ጽሙና ከመ ይንሣእ በረከቶሙ፡፡ ወተናገሩ ብዙኀ ነገራተ እግዚአብሔር፡፡

፷፫ አንድ ቀንም አባታችን ጊዮርጊስ በረከታቸውን ይቀበል ዘንድ አባ ስምዖንና አባ ሲኖዳ በበኣታቸው ተቀምጠው ሳለ ደረሰ፡፡ የእግዚአብሔርንም ምስጢራት ብዙ ተነጋገሩ፡፡

፷፬ ወእምደኅረዝ ተነበየ ሎሙ አቡነ ጊዮርጊስ ወይቤሎሙ ትወልዱ ብዙኀ ደቂቀ ወትከውኑ አእላፈ፡፡ ወይትሐነጻ ለከሙ አብያተ ክርስቲያናት ለለ፩ እምኔክሙ በከሐ ፈለግ፡፡ ወዘንተ ብሂሎ ነሥአ በረከቶሙ ወኀለፈ፡፡ ወእሙንቱሂ ነሥኡ በረከቶ፡፡

፷፬ ከዚህም በኋላ አባታችን ጊዮርጊስ ትንቢት ተናገረላቸው፤ ብዙ ልጆችን ትወልዳላችሁ፤ ብዙም ትሆናላችሁ ከእናንተም ለየአንዳንዱ አብያተ ክርስቲያናት ይታነጹላችኋል አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ በረከታቸውን ተቀብሎ ሔደ እነርሱም በረከቱን ተቀበሉ፡፡

፷፫ ወካዕበ ይቤ አቡነ ጊዮርጊስ ርኢኩ በራእየ ሌሊት ልብሰ ጸሊመ፤ ወ፪ ካህናት እንዘ ይትናገሩ ዕልወተ ሃይማኖት ቀርቡ ኀቤየ ወሞእክዎሙ በተዛልፎት አውደቅዎሙ ወኬድክዎሙ ወለልብሰ ጸሊም አውደቅዎ በማዕተበ መስቀል፡፡

፷፫ ዳግመኛም አባታችን ጊዮርጊስ ሌሊት በራእይ ጥቁር ልብስን አየሁ፡፡ ሁለትም ካህናት የሃይማኖት ክሕደትን እየተናገሩ ወደ እኔ ቀረቡ በክርክርም አሸነፍኳቸው፡፡ ከመሬት ጥዬ ረገጥኋቸው ጥቁሩንም ልብስ በመስቀል ዐማትቤ ጣልሁት አለ፡፡

፷፬ ወዘንተ ነገረ ራእይ ነገሮሙ ለደቂቁ ወይቤሎሙ ይመጽኡ እምድኅሬየ መስሕታን አለ ይዌልጡ ሃይማኖተ፡፡ ወአንትሙሰ ተዐቀቡ ርእሰክሙ፡፡ ወዝኮነ በመዋዕለ እንድርያስ ንጉሥ፡፡

፷፬ ይህንንም ራእይ ለልጆቹ ነገራቸው ከእኔ በኋላ ሃይማኖትን የሚለውጡ አሳቾች ይመጣሉ፤ እናንተ ግን ራሳችሁን ጠብቁ አላቸው፡፡ ይህም በንጉሡ እንድርያስ ዘመን ሆነ፡፡

፷፭ ወካዕበ ይቤሎ ለ፩ ብእሲ ዘስሙ ገማልያል ርኢኩ እንዘ ይወፅእ እምአፉከ ከይሲ ዘክልኤ ልሳኑ፡፡ ዝኒ ኮነ በመዋዕለ ዘርዓ ያዕቆብ ንጉሥ ርቱዐ ሃይማኖት፡፡

፷፭ ዳግመኛም ስሙ ገማልያል ለተባለ አንድ ሰው ሁለት ምላስ ያለው እባብ ከአፍህ ሲወጣ አየሁ አለው፡፡ ይህም ሃይማኖቱ በቀና በንጉሡ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ሆነ፡፡

፷፮ ወካዕበ መጽአ ፩ ብእሲ ወይቤሎ ለአባ ጊዮርጊስ አንሰ ርኢኩ በድነ ወላሕይት ብእሲት ትበክዮ ዐቢየ ብካየ፡፡ ወብዙኃን ሰብእ ተጋቢኦሙ ይበክይዎ ወይትቀሐዉ ለነሢአ በድኑ ለዝየ ወለዝየ፡፡ አ አባ ንግረኒ ፉካሬሁ ለዝንቱ ነገር፡፡

፷፮ ዳግመኛም አንድ ሰው ወደ አባ ጊዮርጊስ መጥቶ እኔ በድን አየሁ መልከ መልካም ሴት ብርቱ ልቅሶን ታለቅስለታለች፤ ብዙ ሰዎችም ተሰብስበው ያለቅሱለታል፣ በድኑንም ለማንሣት ወዲህና ወዲያ እያሉ ይከራከራሉ አባት ሆይ የዚህን ትርጉም ንገረኝ አለው፡፡

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፳፱ ወይቤሎ አቡነ ጊዮርጊስ በድንሰ ዘርኢከ አነ ውእቱ ወብእሲትኒ ቤተ ክርስቲያን ይእቲ። ዘትበኪ በሞተ ዚአየ። ወሕዝብኒ ዘርኢከ እለ ይትጋብኡ ወይበክዩ በሞትየ ወይትቀሐዉ ለነሢኦተ በድንየ። ሀለዎሙ ይግብሩ ከመዝ።

፳፱ አባታችን ጊዮርጊስም ያየኸው በድን እኔ ነኝ፤ ሴቲቱም በእኔ ሞት የምታለቅስ ቤተ ክርስቲያን ናት ያየሀቸውም ሕዝብ በሞቴ ተሰብስበው የሚያለቅሱና በድኔን /ሥጋዬን/ ለመውሰድ የሚከራከሩ እንደዚህ ያደርጉ ዘንድ አላቸው አለው።

፴ ወእምድኅረዝ ካዕበ ርእየ አባ ጊዮርጊስ እንዘ የዐውድዎ ምድረ ሰወን ወመጺአ አባ በጸሎተ ሚካኤል[8] እንዘ ይነሥእ መሬተ እምኀበ ተከዕወ ደመ ስምዑ ወደመ አበዊነ ቅዱሳን እለ አሥመርዎ ለእግዚአብሔር።

፴ ከዚህም በኋላ አባ ጊዮርጊስ የሰወንን ምድር ሲያዞሩት አባ በጸሎተ ሚካኤልንም[8] የሰማዕትነቱ ደምና እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙት ቅዱሳን ደም ከፈሰሰበት አፈርን ይዞ አየ።

፴፩ ወእምኍልቆሙ አባ ፊልጶስ አበምኔት ዘደብረ ሊባኖስ ወአባ ኤዎስጣቴዎስ ዘቢዘን ወደሚሮ ውእተ መሬተ ምስለ ማይ ጽሩይ እንዘ ይቀብዖ ውስተ ፍጽሙ። ወሶቤሃ አእመረ ከመ መከፈልቱ ይእቲ ምድረ ሰወን።

፴፩ ከእነርሱም መካከል የደብረ ሊባኖስ አበምኔት /የገዳም ሓላፊ/ አባ ሊባኖስ የቢዘኑ አባ ኤዎስጣቴዎስ ያንንም አፈር ከንጹሕ ውኃ ጋር አንድ አድርጎ በፊቱ ሲቀባው አየ። ያን ጊዜ የሰወን ምድር ዕድል ፈንታው እንደሆነች ዐወቀ።

፴፪ ወአምድኅረዝ ጸውዖ ንጉሥ ይስሐቅ ለአባ ጊዮርጊስ። ወወሀቦ ምድረ ሰወን እንበለ ይትናገሮ በቃሉ።

፴፪ ከዚህም በኋላ ንጉሥ ይስሐቅ አባ ጊዮርጊስን ጠራው። በቃሉም ሳይጠይቀው የሰወንን ምድር ሰጠው።

፴፫ ወተፈሥሐ በልቡ ወአእመረ ከመ እምኀበ እግዚአብሔር ተውህበት ሎቱ። ወሖረ ምስለ ልኡካነ ንጉሥ ኀበ ምድረ ሰወን ወአየድዎ ወአርአይዎ ኲለንታሃ።

፴፫ ከእግዚአብሔርም ዘንድ እንደ ተሰጣቸው ዐውቆ በልቡናው ደስ አለው። ከንጉሡም መልእክተኞች ጋር ሔደ። እያዞሩም ሁለንተናዋን አሳዩት።

8.አቡነ በጸሎተ ሚካኤል በ፲፫ኛው እና በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ጻድቅ ናቸው። አባታቸው ማርቆስ ሲባሉ እናታቸው እግዚእ ክብራ የንጉሥ ውድም ረዓድ /1291-1305/ ዘመድ ነበሩ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል በዘመናቸው የነበሩት ግብጻዊ ጳጳስ አቡነ ዮሐንስ ገንዘብ እየተቀበሉ ክህነትን መስጠታሕውን ስምዖናዊ ኀጢአት መሆኑንና ንጉሡ አምደ ጽዮን ያደረገውን ስህተት በመግለጻቸው ከሌሎች ቅዱሳን አበው ጋር ሰማዕእነትን ተቀብለዋል። አቡነ በጸሎተ ሚካኤል የመሠረቱት ገዳም ከአባ ጊዮርጊስ ገዳም ጋር በአንድነት ይገኛል።

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፴፬ | ወዓዲ አርአይዎ መካነ ገድሉ ለአባ በጸሎተ ሚካኤል ኀበ ተከዐወ ደመ ስምዑ፡፡ ወገብረ ውስቴታ ትእምርተ መስቀል፡፡ | ፴፬ | ዳግመኛም የሰማዕትነቱ ደም የፈሰሰበት የአባ በጸሎተ ሚካኤልን የገድሉን ቦታ አሳዩት፡፡ በውስጧም የመስቀል ምልክትን አቆመበት፡፡ |
| ፴፭ | ወንስቲተ ርሒቆ እምኔሃ ሐነጸ ቤተ ክርስቲያን እስመ ወሀቦ ንጉሥ ቤተ ምክራሙ ወፈጸማ ፍጡነ እንዘ ይፈቅድ ከመ በደኃሪ ይሕንጽ ኀቤሃ ሠናየ ሕንጸተ፡፡ | ፴፭ | ከእርስዋም ትንሽ ርቆ ቤተ ክርስቲያን አነጸ፡፡ ንጉሡ የሚኖርበትን ቤት ሰጥቶታልና፡፡ ኋላ ያማረ ቤተ መቅደሱን ሊሠራ አስቦ ፈጥኖ ፈጸማት፡፡ |
| ፴፮ | ወትንቢታቲሁሰ ብዙኃት እማንቱ ፈድፋደ እስመ ይነግሮሙ ለደቂቁ ዘይከውን ከመ ዘተገብረ ወዘ ይመጽእ ከመ ዘኀለፈ፡፡ ወሶበኒ ይጼሊ ወይብል ንዒ ኀቤየ አ ድንግል ትመጽእ ኀቤሁ ዘልፈ እግዝእትነ ማርያም በ አመ ታአስተርእዮ በአምሳለ ርግብ ፀዓዳ ወቦ በአምሳለ ወለት ንእስት፡፡ | ፴፮ | ትንቢቶቹም እጅግ ብዙዎች ናቸው፡፡ ለልጆቹ የሚሆነውን እንደተደረገ የሚመጣውንም እንዳለፈ ይነግራቸዋልና፡፡ ድንግል ሆይ ወደ እኔ ነይ እያለ በጸለየ ጊዜ እመቤታችን ማርያም ዘወትር ወደ እርሱ ትመጣለች፡፡ በርግብ አምሳል የምትገለጽለት ጊዜ አለ በትንሽ ሴት ልጅ አምሳልም የምትገለጽለት ጊዜ አለ፡፡ |
| ፴፯ | አእምሩ አ አኃውየ እስመ ለኵሉ ጸሎት ቦቱ ረባሕ፡፡ ለዘሂ ይጼሊ በስመ ነቢያት ይሔውጽዎ ነቢያት፡፡ ወለዘኒ ይጼሊ በስመ ሐዋርያት ይሔውጽዎ ሐዋርያት በከመ ርእየ አባ ሲኖዳ ዐምደ ግብፅ፡፡ | ፴፯ | ወንድሞቼ ሆይ ለጸሎት ሁሉ ዋጋ አለውና ዕወቁ፡፡ የግብጽ ዐምድ አባ ሲኖዳ እንደ አየ በነቢያት ስም የሚጸልየውን ነቢያት ይጐበኙታል፡፡ በሐዋርያትም ስም የሚጸልየውን ሐዋርያት ይጐበኙታል፡፡ |

፶፰ ወአሐተ ዕለተ ርእዮ ለአሐዱ ወልድ እንዘ ይደግም ደቂቀ ነቢያት፡፡ ወሶበ ይዌጥን ይመጽእ ኀቤሁ ነቢይ ዘዘከረ ስሞ ወበፍጻሜሁ ይኤምኖ ወየሐውር ወከማሁ ኩሎሙ በበ፩

፶፰ አንድ ቀንም አንዱን ልጅ የደቂቀ ነቢያትን መጽሐፍ ሲደግም አየው፡፡ በጀመረም ጊዜ ስሙን የጠራው ነቢይ ወደ እርሱ ይመጣል፡፡ በመጨረሻው ሰላምታን ሰጥቶት ይሔዳል፡፡

፶፱ ወሶበ በጽሐ ኀበ ሚልክያስ ነቢይ አኀዞ ንዋም ለውእቱ ወልድ ወኖመ፡፡ ወአባ ሲኖዳ አንቅሖ ወይቤሎ ፈጽም ፍጡነ ወኢታጽንእ ለሊቅ እስመ ይቀውም መንገሌከ፡፡

፶፱ ወደ ነቢዩ ሚልክያስም ትንቢት በደረሰ ጊዜ ያን ልጅ እንቅልፍ ይዞት ተኛ፡፡ አባ ሲኖዳም ቀስቅሶ ፈጥነህ ፈጽመው ነቢዩን አታስጠብቀው ከአንተ ዘንድ ቆሟልና አለው፡፡

፷ ከማሁኬ ኮነት ታስተርእዮ ለአቡነ ጊዮርጊስ እግዝእትነ ወላዲተ እምላክ ሶበ ይጼሊ በስመ ዚአሃ፡፡ ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

፷ እንዲሁም አምላክን የወለደች እመቤታችን በእርስዋ ስም በጸለየ ጊዜ ለአባታችን ጊዮርጊስ ተገልጻለት ነበር፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፲፩

**በእንተ ዕረፍቱ ለቅዱስ አቡነ ጊዮርጊስ**

፩ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር ሐመ አቡነ ጊዮርጊስ ዐቢየ ሕማመ እንተ ባቲ ይከውን ተፍጻሜተ ጽዋዔሁ፡፡

፪ ወእንዘ ሁሎ ውእቱ የሐምም ለአከ ኀቤሁ ንጉሥ ከመ ያምጽእዎ፡፡ ወኢሖረ እምብዝኀ ደዌሁ ወእምዝ ደገመ ንጉሥ ልኢኮ፡፡

## ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

**ስለ አባታችን ቅዱስ ጊዮርጊስ ዕረፍት**

፩ ከዚህም ነገር በኋላ አባታችን ጊዮርጊስ የመጠሪያው መጨረሻ የሚሆን ጽኑ ሕማምን ታመመ፡፡

፪ እርሱም ታመሞ ሳለ ንጉሡ ያመጡት ዘንድ መልእክተኞችን ላከ፡፡ ከሕመሙም ጽናት የተነሣ አልሔደም፤ ንጉሡም ዳግመኛ ላከ፡፡

# <u>ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ</u>

፫ ወሖረ ኀቤሁ እንዘ ሕሙም ውእቱ ወሶበ በጽሐ ሀገረ ንጉሥ ጸንዐ ላዕሌሁ ደዌ ወአልጸቀት ነፍሱ ለመዊት፡፡ ወሶበ ርእዮ ንጉሥ ወኲሎሙ ሠራዊቱ ኀዘኑ ጥቀ በእንቲአሁ፡፡

፫ ታሞ እያለ ወደ እርሱ ሔደ፡፡ ከንጉሡም ከተማ በደረሰ ጊዜ ሕመሙ ጸናበት ነፍሱ ከሥጋው ለመለየት ደረሰች ንጉሡና ሠራዊቱም ሁሉ ባዩ ጊዜ ስለ እርሱ እጅግ አዘኑ፡፡

፬ ወአዘዞሙ ንጉሥ ለሐራሁ ከመ ያዑድዎ ዐረፍተ ቤተ ክርስቲያን እንተ ሐነጸ ለሊሁ ንጉሥ እንዘ ይጸውርዎ በዐራት ከመ ይባርክ በአፉሁ ቡሩክ እምቅድመ ፍልሰቱ ወገብሩ ከማሁ፡፡

፬ ንጉሡም ሠራዊቱን ከዕረፍቱ አስቀድሞ በተባረከ አፉ ይባርክ ዘንድ በአልጋ ተሸክመው እርሱ ንጉሥ ያነጸውን ቤተ ክርስቲያን ዙሪያዋን ያዞሩት ዘንድ አዘዘ፡፡ እንዳዘዛቸውም አደረጉ፡፡

፭ ወእምዝ ጸውዖሙ አቡነ ጊዮርጊስ ለደቂቁ ወይቤሎሙ ደቂቅየ እምከመ ሞትኩ ቅብሩኒ ውስተ ቤተ ክርስቲያን አንተ ሐነጽኩ ለልየ ወእምከመ ተሐንጸት ድኅረ ኀበ ተከዕወ ደመ ቅሥፈታቲሁ ለበጸሎተ ሚካኤል አቡየ አፍልሱ ሥጋየ ህየ፡፡

፭ ከዚህም በኋላ አባታችን ጊዮርጊስ ልጆቹን ጠርቶ ልጆቼ ስሞት ራሴ ባነጽኋትና የአባቴ የበጸሎተ ሚካኤል የግርፋቱ ደም ከፈሰሰበት ቤተ ክርስቲያን ቅበሩኝ ሥጋዬንም አፍልሳችሁ ወደዚያ ውሰዱ አላቸው፡፡

፮ ወአንትሙኒ ስምዑኒ ናሁ እንሰ አልቦ ዘሰወርኩክሙ ወዘኢነገርኩክሙ ምግባሮ ለእግዚአብሔር ወኲሎ ስብሐታተ ወጸሎታተ ዘመዓልት ወዘሌሊት ኢትርሥኡ ወኲሎ ሰንበታተ ወበዓላተ፡፡

፮ እናንተም ስሙኝ ከእግዚአብሔር ሥራ የሰወርኋችሁ ያልነገርኋችሁም የለም ምስጋናዎችን ሁሉ የቀኑንና የሌሊቱን ጸሎቶች ሰንበታትንና በዓላትን ሁሉ አትርሱ፡፡

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፯ | ወፈድፋደሰ ዕቀቡ ሃይማኖተ አንተ አበዊነ ሐዋርያት ወሊቃነ ጳጳሳት ወዕቀቡ ካዕበ ትእዛዛተ ዘአበዊነ እንጦንዮስ ወመቃርዮስ ወሥርዓተ አቡነሂ ጳኲሚስ ወተፋቀሩ በበይናቲክሙ፡፡ | ፯ | ይልቁንም የአባቶቻችንን የሐዋርያትንና የሊቃነ ጳጳሳትን ሃይማኖት ጠብቁ፣ ዳግመኛም የአባቶቻችን የእንጦንስንና የመቃርስን ትእዛዛት፣ የአባታችን ጳኲሚስንም ሥርዐት ጠብቁ፡፡ እርስ በርሳችሁም ተፋቀሩ፡፡ |
| ፰ | ወናሁ ዘንተ ነገርኩክሙ ኢትወስኩ ዲቤሁ ወኢታንትጉ እምኔሁ ወንጹሕ አነ እምደምክሙ ወዘንተ ብሂሎ አዕረፈ በፍኖት፡፡ | ፰ | እነሆ ይህን ነገርኋችሁ ከዚህ ከነገርኋችሁ በላይ አትጨምሩ፤ ከእርሱም አታጉድሉ እኔም ከደማችሁ ንጹሕ ነኝ፡፡ ይህን ብሎ በመንገድ ዐረፈ፡፡ |
| ፱ | እንዘ ይወስድዎ ውስተ ማኅደሩ ወወፅአት ነፍሱ ክብርት መሥመሪተ እግዚአብሔር ወሖረት ኀበ እግዚአብሔር ዘአፍቀረቶ፡፡ | ፱ | ወደ መኖሪያውም ሲወስዱት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘች ክብርት ነፍሱ ከሥጋው ተለየች፡፡ ወደ ወደደችው እግዚአብሔርም ሔደች፡፡ |
| ፲ | ወሶቤሃ መጽአት ኀቤሁ እግዝእትነ ማርያም ለዘክሮታ ሰጊድ ወሐቀፈቶ ውስተ ሕጽና ወከደነቶ በአልባሲሃ ብሩሃት ወረሰየት ገጾ ምስብዒተ እምፀሐይ ዘይበርህ ወወሀበቶ ልብሰ ዘኢተገብረ በእደ ሰብእ፡፡ | ፲ | ያን ጊዜ ለስም አጠራርዋ ስግደት ይግባትና እመቤታችን ማርያም መጣች በእጆቿም አቀፈችው በሚያበሩ ልብሶችዋም አለበሰችው፡፡ ፊቱንም ከሚያበራ ከፀሐይ ሰባት እጅ እንዲያበራ አደረገችው፡፡ በሰው እጅ ያልተሠራ ልብስንም ሰጠችው፡፡ |
| ፲፩ | ዘይደምፅ ልሳነ ፈትሉ ወይብል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅዱሳተ ስብሐቲከ በከመ ኮነ ይሴብሕ በሕይወቱ፡፡ | ፲፩ | የልብሱ ዘርፍም በሕይወት ሳለ እንደሚያመሰግነው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የጌትነትህ ምስጋና በሰማይና በምድር መላ ሲል ይሰማ ነበር፡፡ ኢሳ.፮፥፱ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፪ ወዓዲ ወሀበቶ ክፍለ ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ወኲሎሙ ሊቃነ መላእክት እስመ ተሳተፈ ቅዳሴሆሙ ወምስለ ነቢያት ወሐዋርያት እስመ ኀብረ ስብሐቶሙ፡፡

፲፪ ዳግመኛም ከሚካኤልና ከገብርኤል ከሁሉም መላእክት ጋር ዕድልን ሰጠችው በምስጋና ከእነርሱ ጋር አንድ ሆኗልና፡፡ ከነቢያት ከሐዋርያትም ጋር በምስጋና ተባብሯልና ዕድልን ሰጠችው፡፡

፲፫ ወምስለ ጻድቃን ወሰማዕት እስመ ተዐገሠ ጻማሆሙ ምስለ ፫ መቃርስት አርእስተ መነኮሳት እስመ ተጸምደ ጾሞሙ ወጸሎቶሙ ወምስለ ሕፃናት ዘቤተልሔም እስመ ዐቀበ የውሀቶሙ ወንጽሐሙ፡፡

፲፫ እንደ እነርሱ መከራውን ታግሷልና ዕድሉን ከጻድቃንና ከሰማዕታት ጋር አደረገችለት፡፡ በጾማቸውና በጸሎታቸው ተወስኗልና ዕድሉን ከመነኮሳት አለቆች ከሦስቱ መቃርሶች /መቃርሳት/ ጋር አደረገችው፡፡ የውሃትንና ንጽሕናን ጠብቋልና ዕድል ፈንታውን ከቤተ ልሔም ሕፃናት ጋር አደረገችው፡፡

ምስለ ኲሎሙ ሊቃነ ጳጳሳት እስመ
፲፬ ተባየጸ ሃይማኖተ ምስሌሆሙ ወምስለ ኲሎሙ ማኅበረ በኲር እለ ተጽሕፉ አስማቲሆሙ በሰማያት እንዘ የኀብር ስባሔ ምስሌሆሙ፡፡

፲፬ ከእነርሱ ጋር በሃይማኖት ባልንጀራቸው ሁኗልና ዕድሉን ከጳጳሳት አለቆች ጋር አደረገችው፡፡ በምስጋና ከእነርሱ ጋር ሲተባበር /አንድ ሲሆን/ ስማቸው በሰማያት ከተጻፈ ከማኅበረ በኲር ሁሉ ጋር አደረገችው፡፡

፲፭ በከመ ሰብሐ ሙሴ ገብረ እግዚአብሔር ይወፅእ ነበልባለ እሳት እምአፉሁ፡፡ ትርሲቱኒ ከመ ትርሲቶሙ ወአክሊሉ ከመ አክሊሎሙ ቦ ፀዓዳ ከመ ዘበረድ ወቦ ከመ ዘሙብረቅ፡፡

፲፭ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ እንዳመሰገነ የእሳት ነበለባል ከአፉ ይወጣ ነበር፡፡ ሽልማቱ እንደ ሽልማታቸው አክሊሉም እንደ አክሊላቸው ነው፡፡ እንደ በረድ ነጭ የሆነ እንደ መብረቅም የሚያበራ አለ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፮ | በከመ ስምዐ ኮነ አሐዱ መነኮስ ለባሴ መንፈስ ቅዱስ ዘስሙ ማትያን ካህን ወማእመረ ኅቡኣት ዘከመ ርእየ በአዕይንቲሁ፡፡ | ፲፮ | መንፈስ ቅዱስን የለበሰ፣ ምስጢራትን የሚያውቅ ስሙ ማትያን ካህን የተባለ አንድ መነኩሴ በዐይኑ እንዳየ ምስክር ሆነ፡፡ |
| ፲፯ | ወእምድኅረዝ አዕረገት ነፍሶ እግዝእትነ ማርያም ውስተ ሰማያት በስብሐት ዘኢይትነገር፡፡ | ፲፯ | ከዚህም በኋላ እመቤታችን ማርያም በማይነገር ምስጋና /ክብር/ ነፍሱን ወደ ሰማያት ዐሳረገች፡፡ |
| ፲፰ | አእምሩ አ አኃውየ ኅበ ኵሉ ዘየዐርፍ ነፍስ ክርስቲያናዊ ትበጽሕ እግዝእትነ ማርያም ኀድጉሰ ኅበ ጊዮርጊስ ፍቁራ፡፡ ወዘንተ ነገርናክሙ አ አኃውየ ክብረ ዐቢየ እንተ ጸገዎ ባቲ እግዚአብሔር ለአቡነ ጊዮርጊስ በእደ ወላዲቱ፡፡ | ፲፰ | ወንድሞቼ ሆይ እመቤታችን ማርያም ከወዳጁዋ ከጊዮርጊስ ይቅርና በዕረፍት ከክርስቲያንዊ ነፍስ ሁሉ እንድትደርስ ዕወቁ፡፡ ወንድሞቼ ሆይ እግዚአብሔር ለአባታችን ጊዮርጊስ በእናቱ ማርያም እጅ የሰጠውን ታላቅ ክብር ነገርናችሁ፡፡ |
| ፲፱ | ንትመየጥኬ ወንንግርክሙ ዜና ሞቱ ወሶበ አዕረፈ አስቆቀዉ ደቂቁ እንዘ ይብሉ፤ አ መዝገበ የውሃት ወተራኅኖት አይቴኑ ኀደገነ፤ | ፲፱ | የሞቱን ዜና እንነግራችሁ ዘንድ እንመለስ፡፡ ባረፈ ጊዜ ልጆቹ የየዋሃትና የርኅራኄ መዝገብ ሆይ ወዴት ተውኸን? እያሉ አለቀሱ፡፡ |
| ፳ | አ ቀላየ መጻሕፍት ወምንሐረ ድርሳናት፡፡ አይቴኑ ኀለፍከ እምኔነ፡፡ አ ፈካሬ ኅቡኣት ወጸባቴ ባሕረ መለኮት፡፡ አይቴኑ ፈለስከ እማእከሌነ፡፡ | ፳ | የመጻሕፍት ወንዝ የድርሳናት ምንጭ ሆይ ከእኛ ወዴት ሔድህ? የተሰወረውን የምትተረጉምና የመለኮተን ባሕር የምትዋኘ ሆይ ከመካከላችን ወዴት ሔድህ?፡፡ |
| ፳፩ | ወሶበ ሰምዐ ንጉሥ ከመ ሞተ አቡነ ጊዮርጊስ ኮከበ ክብር ዘአሰርገዋ ለምድረ ኢትዮጵያ በብርሃነ ትምህርቱ ገደፈ እምላዕሌሁ ሰርጐ መንግሥቱ ወለብሰ ልብሰ ኀዘን ወበከየ ብካየ መሪረ፡፡ | ፳፩ | ንጉሡም የኢትዮጵያን ምድር በትምህርቱ ብርሃናት ያበራት የክብር ኮከብ አባታችን ጊዮርጊስ እንዳረፈ በሰማ ጊዜ ልብሰ መንግሥቱን አውልቆ የኀዘን ልብስን ለበሰ፡፡ መራራ ልቅሶንም አለቀሰ፡፡ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፷፪ ወከማሁ ሕዝብኒ ወመኳንንት ወኲሎሙ ካህናት ገደፉ አልባሰ ሰርጒ ወለብሱ ልብሰ ኀዘን፡፡ ወበከይዎ እንዘ ይብሉ

፷፪ እንዲሁም ሕዝቡና መኳንንቱ ሁሉም ካህናት የጌጥ ልብሳቸውን ትተው የኀዘን ልብስን ለበሱ፡፡ እንዲህም እያሉ አለቀሱ፡፡

፷፫ አባ አባ ኖላዊ ኄር ዘይርዒ አባግዐ ወንጌል በውስተ ሠናይ ፂያት፣ አባ አባ ዕፀ ገነት ሥሙር ዘኢይጸመሂ እምዋዕየ መርቄ፡፡ አባ አባ አፉሆሙ ለነቢያት ወልሳኖሙ ለሐዋርያት፡፡

አባ አባ አርጋኖነ ስብሐት ወመሰንቆ መዝሙር ዘቤተ ከብካብ፡፡
አባ አባ ጥእጡአ ስብሐት ከመ መላእክት ወጣዕመ ዜማ ከመ ትጉሃን፡፡
አባ አባ እፎ ያንቀለቅል ልበ ወየሃውክ አማዐውተ ዝክረ ሞትከ፡፡

አባ አባ አፈወርቅ ሐዲስ እፎ ተገደፍከ ውስተ ገጸ ምድር፡፡
አባ አባ ዕንቈ ቀይሕ ወዕንቈ ሐመልሚል እፎ ተዘረውከ ውስተ ገጸ ፍኖት፡፡ አባ አባ ብእሲ ሰማያዊ ወመልአክ ምድራዊ፡፡ አባ አባ ሐዋርያ ሐዲስ ዘይዜኑ በማኀበር ዐቢይ ወየዐቢ ቃሉ በውስተ ነገሥት፡፡

፷፫ አባት አባት በጥሩ መሰማሪያ የወንጌል በጎችን የሚጠብቅ ቸር እረኛ ነህ፡፡ አባት አባት ከቈላ ሙቀት የተነሣ የማይጠወልግ የገነት ተክል ነህ፡፡ አባት አባት የነቢያት አፋቸው የሐዋርያት አንደበታቸው ነህ፡፡

አባት አባት የምስጋና አርጋኖን የሰርግ ቤት መሰንቆ ነህ፡፡ አባት አባት ምስጋናህ እንደ መላእክት ምስጋናና እንደ ትጉሃንም ዜማ የጣፈጠና ያማረ ነው፡፡ አባት አባት የሞትህ ዜና ምንኛ ልብን ያናውጻል አንጀትንም ያውካል፡፡

አባት አባት አዲስ አፈ ወርቅ ስትሆን እንዴት በምድር ገጽ ተጣልህ፡፡
አባት አባት ቀይና ዝንጉርጉር ዕንቊ ስትሆን ምንኛ በምድር ላይ ተዘራህ
አባት አባት ሰማያዊ ሰው ምድራዊ መልአክ ነህ፡፡ አባት አባት በጉባኤ የሚያስተምር ቃሉም በነገሥታት ከፍ ያለ ሐዲስ ሐዋርያ አንተ ነህ፡፡

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

አባ አባ ዐምደ ሃይማኖት ዘኢይጸንን ወዘ ያጸንዓ ለቤተ ክርስቲያን ከመ ኢታንቀለቅል፡፡
አባ አባ ፀሐይ ብሩህ ዘብሔረ አግዐዚ ወገሀህ ወርኅ ምሉእ ዘጸልመተ ሌሊት፡

አባ አባ አባ ኮከበ ጽባሕ ዘያጸድል ውስተ ገጸ ሰማይ፡፡ አባ አባ ተቅዋመ ማኅቶታ ለቤተ ክርስቲያን ዘያበርህ ጸልመተ ኀሊናሆሙ ለውሉዳ፡፡

አባ አባ አማንኑ የብሳ አዕዳዊከ እለ ይገሥሣ ፍሕመ መለኮት ነባቢ፡፡
አባ አባ አማንኑ ተአስራ አእጋሪከ በማእሰረ ሞት እለ ይቀውማ ዲበ ኲኲሐ ሃይማኖት፡፡
አባ አባ አማንኑ ተከድና አዕይንቲከ እለ ይኔጽራ ኀበ ገጸ መጽሐፍ አምላካዊት፡፡

አባ አባ አማንኑ ተሐትማ አእናፊከ እለ ይትሜዓዛ አፈወ በመንፈስ ሃይማኖታዊ፡፡
አባ አባ አማንኑ ተፈጸማ አፉከ ወከናፍሪከ እለ ይነባ ምድራሳተ ጽድቅ አማናዊ፡
አባ አባ አማንኑ ጠግዐ ልሳንከ በጉርዔከ እንተ ትትናገር ቃለ ጽድቅ ማኅየዊ፡፡

አባት አባት ሆይ የማያዘነብል ቤተ ክርስቲያንንም እንዳትናወጥ የሚያጸናት የሃይማኖት ዐምድ /ምሰሶ/ አንተ ነህ፡፡
አባት አባት ኢትዮጵያን የሚያበራ ፀሐይና በጨለማ የሚበራ ምሉዕ ጨረቃ ነህ፡፡
አባት አባት በሰማይ የሚያበራ የንጋት ኮከብ ነህ፡፡

አባት አባት በሰማይ የሚያበራ የንጋት ኮከብ ነህ፡፡ አባት አባት የልጆችዋን የኅሊና ጨለማ የምታበራ የቤተ ክርስቲያን የብርሃን መቅረዝ ነህ፡፡

አባት አባት የነባቢ መለኮት ፍሕምን የዳሠሡ እጆችህ በእውነት ደረቁን?
አባት አባት በሃይማኖት ዐለት ላይ የሚቆሙ እግሮችህ በሞት ማሰሪያ በእውነት ታሰሩን፡፡
አባት አባት አምላካዊት መጽሐፍን የሚመለከቱ ዐይኖችህ በእውነት ተከደኑን?

አባት አባት በሃይማኖታዊ መንፈስ ሽቱን የሚያሸቱ አፍንጮችሁ እውነት ተዘጉን፡፡
አባት አባት እውነተኛ የጽድቅ ድርሳናትን የሚናገሩ አፍህና ከንፈሮችህ በእውነት ዝም አሉን፡፡
አባት አባት መድኅኒት የሆነ የእውነት ቃል የምትናገር አንደበትህ በጉረሮህ ተጣበቀን፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳፬ | እምይዜሰ መኑ ይረግሞሙ ለአርዮስ ወለሰባልዮስ ወመኑ ይፌጽም አፉሆሙ ጽዩአ ለንስጥሮስ ወለአቦርዮስ፡፡ | ፳፬ | ከእንግዲህ በኋላ አርዮስንና ሰባልዮስን ማን ይረግማቸዋል፡፡ የንስጥሮስንና የአቦርዮስን የሚሸት አፋቸውን ማን ይዘጋዋል፡፡ |
| ፳፭ | መኑ ይመትር ልሳኖሙ በሰይፈ ግዘት ለአርጌንስ ወለመቅዶንዮስ ወመኑ ያወቂ ቍልፈተ ልቦሙ በመጥባሕተ ወንጌል ለልዮን ወፎጢኖስ፡፡ | ፳፭ | የአርጌንሳንና የመቅዶንዮስን አንደበት በውግዘት ሰይፍ ማን ይቆርጠዋል፡፡ የልዮንንና የፎጢኖስን የልቡናቸውን ቈላፍነት በወንጌል ሰይፍ ማን ይቆርጠዋል? |
| ፳፮ | መኑ ይከሥት ኃሣረ እከዮሙ ለአውጣኪ ወፍልብያኖስ ወመኑ ይጼእሎሙ ለማኅበረ ኬልቄዶን ወለኩሎሙ አርሲስ መናፍቃን ዕልዋነ ሃይማኖት፡፡ | ፳፮ | የአውጣኪንና የፍልብያኖስንስ የክፋታቸውን ተዋርዶ ማን ይገልጠዋል? የኬልቄዶንን ማኅበርና ሁሉንም ሃይማኖትን የካዱ አርሲስ መናፍቃንን ማን ይነቅፋቸዋል? |
| ፳፯ | መኑ ይጸሐይዮ ለክርዳድ እማእከለ ስርናይ ወመኑ ይፈልጦ ለነገረ ሙሱናን እምቃለ ቅዱሳን፡፡ እስመ ኀለፈ አቡነ ጊዮርጊስ አስባብ ፩ እም ፯ ዓይን ዘቤተ ክርስቲያን፡ | ፳፯ | እንክርዳዱን ከሥንዴ መካከል ማን ይነቅለዋል? የጥፋተኞችን ነገር ከቅዱሳን ቃል ማን ይለየዋል፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ሰባት ዐይኖች አንዱ ኀያሉ አባታችን ጊዮርጊስ አልፏልና፡፡ |
| ፳፰ | ወእምዝ አሰርገዎ ንጉሥ በአልባስ ሠናያት ወአምዐዞ በርኄ አፈዋት ወአዘዘ ይቅብርዎ ወሶቤሃ መጽአ ፩ እምአዝማዲሁ ወአኀዘ ዓራቶ እንዘ ይፈቅድ ይሰዶ ውስተ ሀገሩ፡፡ | ፳፰ | ከዚህ በኋላ ንጉሡ ባማሩ ልብሶች ሸፈነው፤ ሽቱም ቀባው፡፡ ይቀብሩት ዘንድ አዘዘ፡፡ ያን ጊዜ ከዘመዶቹ አንዱ መጣ፡፡ ወደ ሀገሩ ሊወስደው ፈልጎ አልጋውን ያዘ፡፡ |
| ፳፱ | ወደቂቁኒ አኀዙ ዓራቶ እንዘ ይፈቅዱ ይንሥእዎ ኀቤሆሙ ወኮነ ጋዕዝ ማእከሌሆሙ ከመ ይትፈጸም ቃለ ራእይ ዘቀዳሚ፡፡ | ፳፱ | ልጆቹም ወደ እነርሱ ሊወስዱት ወደው አልጋውን ያዙ የመጀመሪያው የራእይ ቃል ይፈጸም ዘንድ ክርክር ሆነ፡፡ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፴ ወእምዝ ወፅአ ቃል እም ኀበ ንጉሥ ወነሥእዎ ደቂቁ ወአእተዉ ብሔሮሙ ወአንበሩ ሥጋሁ በንፍቅ ዘዕፅ ወወደዩ ውስቴቱ መሬተ እምድር እንተ ተቀሥፈ ባቲ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እስመ ከማሁ አዘዞሙ እንዘ ሀሎ በሕይወቱ።

፴ ከዚህ በኋላ ከንጉሡ ትእዛዝ ወጣ። ልጆቹ ተቀብለው ወደ ሀገራቸው ገቡ። ሥጋውንም በእንጨት ሳጥን አስቀመጡት። አባ በጸሎተ ሚካኤል ከተገረፈበት ምድር አፈርን በውስጡ ጨመሩ በሕይወቱ ሳለ እንዲሁ አዝዟቸው ነበርና።

፴፩ ወአብእዎ ውስተ ቤተ ክርስቲያን እንተ ለሊሁ ሐነጸ ወአንበርዎ ህየ እስከ አመ አፍለስዎ ውስተ ቤተ ክርስቲያን እንተ ተሐንጸት ውስተ ምድረ ቅሥፈቱ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል።

፴፩ ራሱ ባነጻት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስገቡት አባ በጸሎተ ሚካኤል በተገረፈበት ምድር ወደ ተሠራላቸው ቤተ ክርስቲያን እስኪያፈልሱት ድረስ ከዚያ አስቀመጡት።

፴፪ ወእምዝ ካዕበ ገብኡ ደቂቁ ውስተ ብካዮሙ ወይቤሉ። አባ አባ ለመኑ ኀደገነ። አባ አባ በአይቴ ንረክብ ዘከማከ ኖላዌ። አባ አባ በአይቴኑ ንረክበከ።

፴፪ ከዚህ በኋላ ልጆቹ ሁለተኛ ወደ ልቅሷቸው ተመለሱ። አባት አባት ለማን ተውኸን እንዳንተ ያለ እረኛን በየት እናገኛለን? አባት አባት ወዴት እናገኝሃለን አሉ።

፴፫ በኀበ ዐላውያንኑ እንዘ ትትዋቀሶሙ ወሚመ በኀበ ቅዱሳን እንዘ ትምዕዶሙ። በኀበ ተቀሠፍከኑ እስከ ይውሕዝ ደምከ ዲበ ምድር ወሚመ በኀበ ዘበጡከኑ እስከ ይዘረዉ አስናኒከ።

፴፫ ከዐላውያን ጋር ስትከራከር ነውን? ወይስ? ቅዱሳንን ስትመክራቸው? ደምህ በምድር ላይ እስኪፈስስ በተገረፍህበት ነውን? ወይስ? ጥርሶችህ እስኪረግፉ ድረስ በተደበደብህበት።

፴፬ በኀበ ሞቅሑከኑ በመዋቅሕት ወሚመ በኀበ ባሕተውከ እምኀበ ምኩናን። በአይቴኑ ንረክበከ ወኀበ ዓይኑ ነኀሥሠከ አ አባ እስመ ነደ ልብነ በላኀበ ፍቅርከ ወተከውሰ አማኡቲነ በኀዘነ ሞትከ።

፴፬ በታሰርህበት እስር ቤት ነውን? ወይስ? በፍርድ ቦታ ብቻኛ በሆንክበት ነውን? የት? እናገኝሃለን በወዴትስ? እንፈልግሃለን? አባት ሆይ! በፍቅርህ እሳት ልባችን ነድዷልና፤ አንጀታችንም በሞትህ ኀዘን ተናውጿል።

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፹፭ | ሶበ ንዜከርኑ ከመ ትዘልፎሙ ለከሐድያን ንትፌሣሕ ወሚመ ሶበ ትነግርኑ በማኅበር ዐቢይ ዖታ ሥላሴ በበገጽ ንትሐሠይ | ፹፭ | ከሐድያንን እንደ ዘለፍሃቸው ባሰብን ጊዜ ደስ ይለናል፤ ወይም በታላቅ ጉባኤ በየመልኩ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት በተናገርህ ጊዜ ሐሴት እናደርጋለን፡፡ |
| ፹፮ | ሶበ ንዜከርኑ ዝብጠተከ እምኀበ ገብር እስከ ይወድቅ አስናኒከ ውስተ ምድር ንበኪ ወሚመ ሶበ ንሔሊ ደመ ዘይውሕዝ እምአፉከ ናስቆቁ፡፡ | ፹፮ | ጥርሶችህ ወደ መሬት እስኪወድቁ ድረስ በአገልጋይ መደብደብህን ባሰብን ጊዜ እናለቅሳለን ዳግመኛ ከአፍህ የፈሰሰ ደምን ባሰብን ጊዜ እናንባለን፡፡ |
| ፹፯ | ሶበ ንዜከርኑ ቅሥፈታቲከ እስከ ይውሕዝ ደምከ ከመ ማይ ንበኪ ወሚመ ሶበ ትቤ ከለሉኒ መላእክት ወመገቡኒ ማኅበረ ቅዱሳን ንትፌሣሕ፡፡ | ፹፯ | ደምህ እንደ ውኃ እስኪወርድ የተገረፍኸውን ባሰብን ጊዜ እናለቅሳለን፤ ከዚህ ሌላ መላእክት ጋረዱኝ የቅዱሳንም ማኅበር መገቡኝ ባልህ ጊዜ ደስ ይለናል፡፡ |
| ፹፰ | ሶበ ንዜከርኑ ዝግኅታተከ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ንበኪ ወሚመ ሶበ ሐወጹ ማኅበረ ሐዋርያት ለናዝዞትከ ንትፌሣሕ፡፡ | ፹፰ | በእስር ቤት መታሰርህን ባሰብን ጊዜ እናለቅሳለን፤ ዳግመኛም የሐዋርያት ማኅበር ለማጽናናት የጐበኙህን ባሰብን ጊዜ እንደሰታለን፡፡ |
| ፹፱ | ኦ አባ ፀሐየ ቅዱሳን አማንኑ ዐረብከ፡፡ ኦ አባ ማኅቶተ ብፁዓን አማንኑ ተሰወርከ፡፡ | ፹፱ | የቅዱሳን ፀሐይ አባት ሆይ በእውነት ጠለቅህን? የብፁዓን መብራት አባት ሆይ በእውነት ተሰወርህን፡፡ |
| ፺ | ከመ ኢትንግሩ ሞቶ ለሰብአ አርዮስ እለ ጸሐፈ ተዝካረ ዕበዶሙ ወኢትዜንዉ ለሕዝበ ንስጥሮስ እንተ ለአከ በጦማሩ ባህለ ሐሰቶሙ፡፡ | ፺ | ስንፍናቸውን ለጻፈባቸው ለአርዮስ ሰዎች ሞቱን እንዳትነግሩ፡፡ የሐሰታቸውን ትምህርት በመልእክቱ ለገለጠባቸው ለንስጥሮስ ወገኖች እንዳታውሩ፡፡ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | |
|---|---|
| ፺፩ ኢይትፌሥሑ ማኅበረ ኬልቄዶን እለ መተሮሙ በሰይፈ ግዘቱ ወኢይትኃሠዩ ዓላውያን እለ አውቀዮሙ በመጥባሕተ ቃሉ:: | ፺፩ በግዚት ሰይፉ የቆረጣቸው የኬልቄዶን ማኅበር ደስ አይበላቸው በቃሉ ሰይፍነት የቆራረጣቸው ከሐዲያንም አይደሰቱ:: |
| ፺፪ ኦ አባ ጥዑመ ዝክር ከመ መዐር በውስተ አፍ ወከመ ቅብዕ ውስተ አዕጽምት:: ኦ አባ ጸልማ አዕይንቲነ እለ ይሬእያ በዘክሮ ሞትከ ወጠፍአ ሕሊናነ እምአእምሮ በኃጢኦትከ:: ወይ ለነ አሌ ለነ ድክትምና ዓገተነ ወእንዘ ውርዝዋን ንሕነ ርስዓን ፆደነ:: | ፺፪ አባት ሆይ የስም አጠራርህ በአፍ ውስጥ እንደ መዐር በአጥንትም ውስጥ እንደ ቅቤ ነው:: አባት ሆይ ሞትህን በማሰብ የሚያዩ ዐይኖቻችን ታወሩ:: ኅሊናችንም አንተን በማጣት ከዕውቀት ተለየ:: ወዮ ለኛ ወዮታ አለብን ድካም ከቦናል እኛ ጐልማሶች ስንሆን ሽምግልና አገኘን:: |
| ፺፫ ኦ አባ ብፁዕ አንተ ወሠናይ ለከ:: ወዓዲ ብፁዓን ኲሎሙ እለ ሥርግዋን በፍቅርከ:: | ፺፫ አባት ሆይ አንተ የተመሰገንህ ነህ:: መልካምም ነገር ለአንተ ይገባል:: ዳግመኛም በፍቅርህ የተሸለሙ ብፁዓን ናቸው:: ሲራክ ፵፫፥፲፩ |
| ፺፬ ስብሐት ለአብ ለዘኀረየከ:: ወሰጊድ ለወልድ ለዘሠምረከ አኰቴት ለመንፈስ ቅዱስ ለዘአፍቀረከ:: | ፺፬ ለመረጠህ ለአብ ምስጋና ይገባል፤ ለወደደህ ለወልድም ስግደት ይገባል፤ ለአፈቀረህ ለመንፈስ ቅዱስም አኰቴት ይገባል:: |
| ፺፭ ወፈጺሞሙ ብካዮሙ አተዉ ደቂቁ ውስተ ማኅደሪሆሙ በሰላም ለዓለመ ዓለም አሜን::<br>ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን:: | ፺፭ ልጆቹም ለቅሷቸውን ከጨረሱ በኋላ በሰላም ወደ ቤታቸው ተመለሱ:: ለዘለዓለሙ አሜን::<br>ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን:: |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

## ምዕራፍ ፲፪

፩ ንትመየጥኬ ወንንግርከሙ ክቡራተ ልቡሳተ ዘረከበ በውስተ ሰማያት ዝውእቱ ቅዱስ እም ኀበ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘርእየ ፩ ካህን መፍቀሬ ጾም ወጸሎት ወመፍቀሬ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡፡

፪ ይቤ ውእቱ ብእሲ ወአሐተ ዕለተ ሶበ ሰማዕኩ እንዘ ይትነበብ ቃለ መጻሕፍቲሁ ለአቡነ ጊዮርጊስ አስተዐጸብኩ ወአንከርኩ ፈድፋደ፡፡ ወእቤ በልብየ ሚመጠነ ይፈደፍድ ዕስቡ በመንግሥተ ሰማያት፡፡

፫ ወሰአልኩ ኀበ እግዚአብሔር እማዕምቀ ልብየ ከመ ያርእየኒ ጸጋሁ ወማኅደሮ ዘውስተ ሰማይ፡፡

፬ ወሶቤሃ አስተርአየኒ ብእሲ ብርሃናዊ ወተናገረኒ ከመ ቃለ ብእሲ ወይቤለኒ ምንተ ታነክር በእንተ ጊዮርጊስ ማኅሌተይ፡፡

፭ አኮ ውእቱ ዘአፍቀሮ ለእግዚአብሔር አምላክነ አላ ለሊሁ መፍቀሬ ሰብእ ኢየሱስ ክርስቶስ ኀረዮ ወአፍቀሮ ከመ ይኩኖ ሎቱ ለርስቱ ወቀደሶ እምከርሠ እሙ ከመ ኤርምያስ ካህን ወነቢይ፡፡

## ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

፩ ወንድሞች ሆይ በሰማያት ያገኘውን የክብር ልብስ እንነግራችሁ ዘንድ እንመለስ ይኸውም ጾምንና ጸሎትን የሚወድ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንንም የሚያፈቅር አንድ ካህን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሲቀበል ያየው ነው፡፡

፪ ያም ሰው እንዲህ አንድ ቀን የአባታችን ጊዮርጊስ የመጻሕፍት ቃል ሲነበብ በሰማሁ ጊዜ እጅግ አደነቅሁ በልቤም ዋጋው በሰማያት ምን ያህል ይበዛ ይሆን አልሁ፡፡

፫ በሰማያት የሰጠውን ጸጋውንና ማደሪያውን ያሳየኝ ዘንድ በጠለቀ ልብ ወደ እግዚአብሔር ለመንሁ፡፡

፬ ያን ጊዜ ብርሃንን የተጎናጸፈ ሰው ተገለጸልኝ በሰውም ቃል ተናገረኝ ስለ ማኅሌታዊው ጊዮርጊስ ለምን ታደንቃለህ አለኝ፡፡

፭ እርሱ እግዚአብሔር አምላካችንን የወደደው አይደለም፡፡ ሰውን የሚወድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለርስቱ ይሆን ዘንድ ራሱ መረጠው ወደደው እንጂ እንደ ካህኑና ነቢዩ ኤርምያስም ከእናቱ ሆድ ቀደሰው ኤር.፩፥፭

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፮ ወለሊሁ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ ተናገረ በአፉሁ ዘንተ ኵሎ መጻሕፍተ ዘታነክር አንተ፡፡ ወበእንተ አርጋኖነ ውዳሴሃኒ ለእግዝእትነ ንጽሕት ማርያም እመ አምላክ ምንተኑ ታነክር ወታስተ ዓጽብ

፮ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ አንተ የምታደንቃቸው መጻሕፍትን ሁሉ በአንደበቱ ተናግሮአል፡፡ የአምላክ እናት ስለሆነች ስለ ንጽሕት እመቤታችን ማርያም የምስጋና አርጋኖን የምታደንቀው ምንድን ነው?፡፡

፯ አኮ ውእቱ ዘተናገረ አላ ይእቲ ንጽሕት እመ አምላክ አልኖሰሰት ውስተ እዝኑ ወተናገረቶ ውዳሴያቲሃ ይንግር ወይጽሕፍ ተዝካረ ለካልኣን ለእለ ያፈቅርዋ እማዕመቀ ልቦሙ፡፡

፯ እርሱ የተናገረው አይደለም፡፡ የአምላክ እናት ንጽሕት እመቤታችን ከልባቸው ለሚወድዷት ሰዎች ውዳሴዋን ይነግርና ይጽፍ ዘንድ በጆሮው ነገረችው እንጂ፡፡

፰ ሰማዕ እንግርከ ኀሢሦተከ በእንተ ጊዮርጊስ ካህን ማኅሌታይ ይእቲ እሙ ለብርሃን ታፈቅሮ ፈድፋደ ከመ ወልዳ ፍቁር ወተዐቍሮ በአልባሲሃ ወትስእሞ በአፉሃ ወኢትትፈለጥ እምኔሁ አሐተ ሰዓተ በመዓልት ወበሌሊት በፍኖትኒ ወበገዳም በቤትኒ ወበኵሉ ገጸ መካን፡፡

፰ ስለ ማኅሌታዊው ጊዮርጊስ ለማወቅ የፈለግኸውን እነግርህ ዘንድ ስማ! የብርሃን እናት እርስዋ እንደተወዳጁ ልጅዋ ትወደዋለች በልብስዋ ትሸፍነዋለች በአፉም ትስመዋለች በቀንና በሌሊት በመንገድ፣ በገዳም፣ በቤት፣ በቦታው ሁሉ አንድ ሰዓት እንኳ ከእርሱ አትለይም፡፡

፱ ወዮምኒ ሀለወት ነፍሱ ንጽሕት ምስሌሃ በየማነ ወልዳ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ ክቡራትሰ ወጺጋ መንበርኒ ወሀገር ቅድስት ወተውህቦ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡

፱ ዛሬም ቢሆን ንጽሕት ነፍሱ በልጅዋ በኢየሱስ ክርስቶስ ቀኝ ከእርስዋ ጋር አለች ክብርና ጸጋ መንበር የተቀደሰች ሀገርም ለአባታችን ጊዮርጊስ ተሰጥቶታል፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲ | ኢመፍትው ይርአዮ ሰብእ እንዘ ሀሎ በሥጋ አንጻዒ ለእመ ተጋህከ ብዙኀ ወጻመውከ ፈድፋደ ወጻራሕከ ኀበ እግዚአብሔር ይከሥት ለከ በእንተ ጻማከ ትርአዮ ወትትፈሣሕ ቦቱ፡፡ | ፲ | ሰው በሕይወተ ሥጋ ሳለ ያየው ዘንድ የሚችል አይመስለኝም፤ ምናልባት ብዙ ከተጋህና ብዙ ከደከምህ ወደ እግዚአብሔርም ከጮኽ ስለ ድካምህ ታየው ዘንድ ይገልጥልሃል በእርሱም ደስ ይልሃል፡፡ |
| ፲፩ | በእንተ ውዳሴሆሙ ለጴጥሮስ ወጳውሎስ ብርሃናተ ዓለም ወካልኣን ሐዋርያት ስማዕ እንግርከ እስመ መንፈሶሙ ወጻማሆሙ ኅደረት ላዕሌሁ ወተሰውጠት ዲበ ርእሱ፡፡ ኢያእመርከኑ ከመ መራኁቱ ለጴጥሮስ እኁዝ ውስተ እዴሁ መስቀሉ ለእግዚእነ ክርስቶስ ትኩል ዲበ ርእሱ፡፡ | ፲፩ | ስለ ዓለም ብርሃናት ጴጥሮስና ጳውሎስ፣ ስለ ሌሎችቹም ሐዋርያት ምስጋና እነግርህ ዘንድ ስማ፡፡ መንፈሳቸውና ተጋድሎአቸው በእርሱ ላይ አድራለች፡፡ በራሱም ላይ ወርዳለችና፡፡ የጴጥሮስ ቁልፎች በእጁ እንደተያዘ የጌታችን ክርስቶስ መስቀልም በራሱ ላይ እንደተተከለ ዐላወቅህምን? |
| ፲፪ | ወኲሎሙ ሐዋርያት ይኤምኅዎ ከመ ዐርክ ወቢጽ ወከፍሉ ዘተውህበ ድሙር ምስለ ክፍሎሙ፡፡ ወውእቱ ያዓርግ ጸሎተ ኲሎሙ ቅዱሳን ቅድመ እግዚአብሔር በኲሉ ጊዜ ሌሊተ ወመዓልተ፡፡ | ፲፪ | ሁሉም ሐዋርያት እንደ ወዳጅና ወንድም ሰላም ይሉታል፡፡ የተሰጠውም ጸጋ እንደ እነርሱ ጸጋ ያለ ነው፡፡ እርሱም የቅዱሳንን ጸሎት በሁሉም ሰዓት በቀንና በሌሊት በእግዚአብሔር ፊት ያሳርጋል፡፡ |
| ፲፫ | ወካዕበ ይመጽእ ወያስተኃፍሮ ለሐሳዊ መሢሕ ወያወግዞ ወይትበአስ ምስሌሁ አኮ በሥጋ አላ በነፍሱ ንጽሕት፡፡ ወሶቤሃ አውሣእክዎ ለዘይትናገረኒ ወእቤሎ ለምንት ዘኢኮነ ዕረፍቱ ለዝንቱ ጻድቅ በዕለተ ዕረፍቶሙ ለጴጥሮስ ወጳውሎስ ፍቁራኒሁ፡፡ | ፲፫ | ዳግመኛም ይመጣል ሐሰተኛውንም ነቢይ ያሳፍረዋል፤ ከእርሱም ጋር ተከራክሮ ያወግዘዋል፤ የሚመጣም በአካለ ሥጋ አይደለም፤ በአካለ ነፍስ ነው እንጂ፡፡ ያን ጊዜ የሚያናግረኝን መለስሁለት /ጠየቅሁት/ የዚህ ጻድቅ ዕረፍቱ በወዳጆቹ በጴጥሮስና ጳውሎስ የዕረፍት ቀን ለምን ሳይሆን ቀረ አልሁት፡፡ |

## ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ወይቤለኒ እስመ ሠምረ እግዚአብሔር

ነፍሱ በፍጹማን መነኮሳት በአባ

፲፬ ትፍልስ ነፍሱ በዕለተ ዕረፍቶሙ ለአባ ሲኖዳ ወአባ መቃቢስ ፍጹማን መነኰሳት፡፡

፲፬ ሲኖዳና በአባ መቃርስ የዕረፍት ቀን ታርፍ ዘንድ እግዚአብሔር ወድዷልና አለኝ፡፡

፲፭ በከመ ኮነ አባ ሲኖዳ ዐምዶሙ ለሰብአ ግብጽ ከማሁ ውእቱኒ ዐምደሙ ለሰብአ ኢትዮጵያ ወለእለ የኀድሩ በሃይማኖተ ክርስቶስ እግዚእነ፡፡ አእምር ከመ አንተኒ ትመውት በዕለተ ሞቱ፡፡ ወዘንተ ብሂሎ ተሰወረ እምኔየ፡፡

፲፭ አባ ሲኖዳ ለግብጽ ሰዎች ዐምድ እንደሆነ እርሱም ለኢትዮጵያ ሰዎችና በጌታችን ክርስቶስ አምነው ለሚኖሩ ሁሉ ዐምዳቸው /ምሰሶ/ ነውና፡፡ አንተም እርሱ ባረፈበት ዕለት እንደምትሞት ዕወቅ ይህንም ብሎ ከእኔ ተሰወረ፡፡

፲፮ ወዘንተ ሰሚዕየ አፈድፈድኩ ፍቅሮ ለአቡየ ጊዮርጊስ ወእቤ ኢመፍትው በእንተ ኃጢአትየ ሊተሰ ከመ ይኩን ሞትየ በዕለተ በዐሉ ቅዱስ ለአቡየ ጊዮርጊስ፡፡

፲፮ ይህንንም ሰምቼ የአባቴን የጊዮርጊስን ፍቅር በእኔ ላይ አበዛሁ፡፡ እኔም ስለ ኀጢአቴ በአባቴ ጊዮርጊስ የተቀደሰ የዕረፍት በዓል ሞቴ ይሆን ዘንድ አግባብ አይደለም አልሁ፡፡

፲፯ ወእምድኅረ ዝንቱ በጽሖ ለዝንቱ መነኮስ በከመ ነገሮ መልአክ ወአዕረፈ በዕለተ በዓሉ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡ ወዘንተ አይዳዕናክሙ አ አኃውየ ፍቁራን ክቡራት ዐቢያተ ዘጸገዎ ባቲ እግዚአብሔር ለዝንቱ መስተጋድል አቡነ ጊዮርጊስ፡፡

፲፯ ከዚህም በኋላ መልአኩ እንደነገረው ለዚያ መነኩሴ ደረሰለት፤ በአባታችን በጊዮርጊስ በዓለ ዕረፍትም ዐረፈ፡፡ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ለዚህ ተጋዳይ አባታችን ጊዮርጊስ እግዚአብሔር የሰጠውን ታላቅ ክብር ነገርናችሁ፡፡

፲፰ ወዘተርፈ ስብሐቲሁ ወዕበየ ክብራቲሁ ህልው በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ሀገረ ንጉሥ ክርስቶስ፡፡

፲፰ ከዚህ የተረፈው ምስጋናውና የክብሩም ብዛት ደግሞ የንጉሥ ክርስቶስ አገር በሆነች በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ይገኛል፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፲፱ ወይእዜኒ ኦ አኃውየ ፍቁራን ናሁ አእመርነ ከመ አቡነ ጊዮርጊስ ቅሩብ ውእቱ ኀበ እግዚአብሔር መጠነዝ፡፡ ወቦቱ ሞገስ ከመ ይባእ ቅድመ ሥሉስ ቅዱስ ኵሎ ጊዜ ወይተነበል ለለ ፩ ፩፡፡

፲፱ አሁንም የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ እነሆ አባታችን ጊዮርጊስ ይህን ያህል ለእግዚአብሔር ቅርብ እንደሆነ ዐወቅን፡፡ ሁል ጊዜ ከሥሉስ ቅዱስ ፊት በመቆም ለያንዳንዱ ይማልድ ዘንድ ባለሟልነት አለው፡፡

፳ ወንሕንኒ ንረስዮ ተንባለ እንዘ ንመጸውት ለአኃዊነ ነዳያን ወነጋድያን ወንትፋቀር በበይናቲነ ወናጥሪ ንጽሐ ከመ ይትንብል በእንቲአነ ለነ ለኵልነ ቅድመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይሠሃል ላዕሌነ ወይስረይ ኃጣውኢነ፡፡

፳ እኛም ለወንድሞቻችን ነዳያንና እንግዶች ምጽዋትን እየመጸወትን አማላጅ እናድርገው፡፡ እርስ በርሳችንም እንፋቀር፡፡ ሁላችንን ይቅር እንዲለንና ኀጢአታችንም እንዲያስተሰርይልን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ይለምንልን ዘንድ ንጽሕናን ገንዘብ እናድርግ፡፡

፳፩ ወይባርክ ላዕለ ተጋብኦተ ሕዝብነ ዐቢያን ወንኡሳን አእሩግ ወሕፃናት መበለታት ወአዋልድ፡፡ ወይባርክ ዓዲ ላዕለ ዘአስተሐመመ በጽሒፈ ዝንቱ መጽሐፍ ክርስቶስ ኢየሱስ እግዚእነ ዘኪያሁ ንስእል ከመ ይስረይ ኀጣውኢነ ወይደመስስ አበሳነ፡፡

የታላላቆቹንና የታናናሾቹን የሽማግሌዎችንና የሕፃናቱን የመበለታቱንና የልጆችንም አንድነት ይባርክ፡፡ ዳግመኛም ተስፋ የምናደርገው ኢየሱስ ክርስቶስ ኀጢአታችን ያስተሠርይልን በደላችንንም ይደመስስልን ዘንድ ይህን መጽሐፍ ለመጽሐፍ የተጋውን ይባርክ፡፡

፳፪ ወይክድን ዳኅፃቲነ ወይርድአነ ላዕለ ኵሉ ገቢረ ሠናይ እምቅድመ ተፍጻሜተ መዋዕሊነ፡፡ ወለኵልክሙ እለ ተጋባእክሙ በዕለተ ተዝካሩ ያልህቅ ሕፃናቲክሙ ወይመግብ ዕቤራቲክሙ፡፡

፳፪ ስሕተታችንን ይሰውርልን፤ ከዘመናችን መጨረሻ በፊት መልካም ሥራ ለመሥራት ይርዳን፤ በመታሰቢያው ቀን ለተሰበሰባችሁ ለሁላችሁም ሕፃናቶቻችሁን ያሳድግ ድሆቻችሁንም ይመግብ፡፡

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፷፫ | ወይሚጥ ተአንግዶተ ነጋድያኒክሙ ወያራኅርኅ ለክሙ አልባበ ሥዩማን ወያብጽሕክሙ በከመ ዛቲ ዕለት ዓመታተ ብዙኀ ወመዋዕለ ነዊኀ ወይረስየክሙ ድልዋነ ለመጥዎ ሥጋሁ ንጹሐ ወደሙ ክቡር ለሥርየተ ኀጣውኢክሙ ነፍሳዊ ወሥጋዊ፡፡ | ፷፫ | ለንግድ የወጡትን ይመልስላችው፤ የሹማምንቱን ልቡና ያራራላችሁ፤ ለዚህች ዕለት እንዳደረሳችሁ ብዙ ዓመትና ረጅም ዘመንን ይስጣችሁ፡፡ የነፍስና የሥጋ ኀጢአታችሁን የሚያስተሠርይ ንጹሕ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበል የተዘጋጃችሁ ያድርጋችሁ፡፡ |
| ፷፬ | ወያስምዕክሙ ቃለ ፍሥሓ ዘይብል ንዑ ኀቤየ ቡሩካኒሁ ለአቡየ ትረሱ መንግሥተ ዘድልው ለክሙ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፡፡ በትንብልናሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል በኵሉ ጊዜ ዘወፅአ እማሕፀና ፍሬ መድኃኒት ዘኢተዘርዐ፡፡ | ፷፬ | ያለ ወንድ ዘር የድኅነት ፍሬ ከማሕፀኗ በተገኘ ሁል ጊዜ ድንግል በሆነች በእመቤታችን ማርያም አማላጅነት ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥተ ሰማያት ትወርሱ ዘንድ የአባቴ ቡሩካን ወደ እኔ ኑ የሚል የደስታ ቃልን ያሰማችሁ፡፡ |
| ፷፭ | ወበትንብልና አጋእዝቲነ ሐዋርያት ዘአጸወት ጸዋዔሆሙ አብያተ ጣዖታት ወአርኀወት አናቅጸ አብያተ ክርስቲያናት ወአጽረዩ በትምህርታቲሆሙ አልባበ ከሓድያን መስተቃርናን፡፡ | ፷፭ | በስብከታቸው የጣዖትን ቤት በዘጉ፣ የአብያተ ክርስቲያናትን በር /ደጃፍ/ በከፈቱ፣ በትምህርታቸውም የከሐድያንንና የተቃዋሚዎችን ልቡና፣ ባጠሩ /ንጹሕ ባደረጉ/ በጌቶቻችን ሐዋርያት አማላጅነት የደስታ ቃልን ያሰማችሁ፡፡ |
| ፷፮ | በትንብልና ኵሎሙ ሰማዕት ወጻድቃን ወኵሎሙ እለ አሥመርዎ ለእግዚአብሔር አምላክ እምዘርዐ አዳም ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወእስከ ለዓለመ ዓለም አሜን አሜን ወአሜን፡፡ | ፷፮ | ከአዳም ልጆች ጀምሮ እግዚአብሔር አምላክን ደስ ባሰኙት በሰማዕታትና በጻድቃን ምልጃ የደስታ ቃልን ያሰማችሁ፡፡ ዛሬም ዘወትርም እስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሜን ይሁን ይደረግ፡፡ |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳፯ | ወኮነ በዘአዕረፈ እግዚእየ አባ ጊዮርጊስ አመ ፩ ለወርኃ ተሙዝ በሐሳበ ሮም ወበቅብጢ አቢብ ወበዐረቢ ዲእል ቀአድ ወበግዕዝ አመ ፯ ለሐምሌ በ፳፻ወ፳፻፶ወ፯ እም አቡነ አዳም በሐሳበ ሮም ወበሐሳበ ኢትዮጵያሰ በ፳፻ወ፳፻፲ወ፯። | ፳፯ | ጌታዬ አባ ጊዮርጊስ ያረፈው በሮማውያን ተሙዝ በተባለ ወር በ፩ኛው ቀን በቅብጥ አቢብ በተባለ ወር በዓረብ ዲእልቀኡድ በተባለ በግእዝ ሐምሌ ፯ ቀን አዳም በተፈጠረ በ፳፻ ሺህ ፳፻፶፯ በኢትዮጵያና በሮም አቆጣጠር በ፯ ሺህ ፳፻፲፯ ነው። |
| ፳፰ | ወንሕነሰ ንብል እምአቡነ አዳም ፳፻ ወ፲፻ወ፭ እስከ አሜሃ። ወዓመተ ምሕረትሂ ፫፻ወ፭ ወበቀመረ ገብረ መስቀል ንጉሥ ዝውእቱ ዓሥር ወሣልስ እምነ አቅማር ወበትግራይሰ በ፸፯ ወበካህናተ ደብተራሂ በ፩ ዓመተ ምሕረት በ፲ወ፭ ዓመተ እንድቅትዮን | ፳፰ | እኛ ግን ከአባታችን አዳም ጀምሮ እስከዚያ ድረስ ፯ሺህ ፲፻፭ ነበረ እንላለን። ዓመተ ምሕረቱም በንጉሥ ገብረ መስቀል አቈጣጠር ፫፻፭ /በሦስት መቶ አምስት/ ነበር፤ ይኸም ዐሥራ ሦስተኛው አቈጣጠር ነው። በትግራይ ግን በ፸፯ /በሰባ ሰባት/ ነው። በካህናተ ደብተራም በ፩ ዓመት ምሕረት በ፲፭ኛው ዓመተ እንድቅትዮን ነው።/በስድስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ሰባት/ |
| ፳፱ | ወበኢትዮጵያ በ፪ እንድቅትዮን በአልቦ ዓበቅቴ በ፯ ጥንተ ዮን በዓመተ ማቴዎስ ወንጌላዊ በዕለተ ረቡዕ ወበ፲፻ወ፩፻ወ፵ወ፪ እምዓመተ ሰማዕታት ንጹሓን በ፲ወ፩ ዓመተ መንግሥቱ ለይስሐቅ | ፳፱ | በኢትዮጵያ በሁለት እንድቅትዮን አበቅቴ አልቦ በነበረበት በሰባት ጥንተ ዮን በወንጌላዊው ማቴዎስ ዘመን ረቡዕ ቀን ከሰማዕታት ዓመት በአንድ ሺህ አንድ መቶ አርባ ሁለት ይስሐቅ በነገሠ በዐሥራ አንድ ዓመት ነው። |
| ፴ | ወአዕረፈ እንዘ ወልደ ፷ ዓመት አሜን። | ፴ | ስድሳ /ሰልሳ/ ዓመት ሲሆነው ዐረፈ። አሜን። |

# ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

፴፩ ወዘተርጐማሰ ለዛቲ መጽሐፍ አባ ያዕቆብ ወልደ ኤዎስጣቴዎስ ዘቢዘን፡፡ ወእምዝ ጽሕቀ በአርትዖ ዝንቱ መጽሐፍ ፩ ብእሲ ነዳይ ወምስኪን፡፡

፴፩ ይህችን መጽሐፍ የተረጐማት የአባታችን ኤዎስጣቴዎስ ዘቢዘን ልጅ አባ ያዕቆብ ነው፡፡ ከዚህም በኋላ ይህን መጽሐፍ ለማቅናት አንድ ድሀና ምስኪን ሰው ተጋ፡፡

፴፪ በዝየ ንምትር ቃለነ ወንኅድግ ንባበነ ወንስአሎ ለእግዚአብሔር ከመ ይክብት ነውረነ ወይክድን ጻኅፃቲነ ለዓለመ ዓለም አሜን ወአሜን ሃሌ ሉያ ለይኩን ለይኩን፡፡

፴፪ በዚሁ ቃላችንን እንግታ ንባባችንን እንተው ነውራችን እንዲሰውርልን ስሕተታችንንም እንዲሸፍንልን እግዚአብሔርን እንለምነው፡፡ ለዘለዓለሙ አሜን አሜን ሃሌ ሉያ ይሁንልን ይደረግልን፡፡

፴፫ ተፈጸመ ገድለ አቡነ ጊዮርጊስ አመ ፲፫ ለወርኅ ኅዳር በጊዜ ፱ ሰዓት፡፡ ናሁ ፈነውነ ለክሙ ገድለ አቡነ ጊዮርጊስ ለደሴተ ፍቅር በትእዛዘ አቡነ ፊቅጦር ወበትጋሁ ለሥነ ድንግል ፈቂዶ ከመ ይብጻሕ ኀቤክሙ እስመ አጽሐቆ ዜና ፍቅርክሙ፡፡

፴፫ የአባታችን ጊዮርጊስ የገድል መጽሐፍ ኅዳር ዐሥራ አምስት ቀን በዘጠኝ ሰዓት ተጽሕፎ ተፈጸመ፡፡ የአባታችን ጊዮርጊስን የገድል መጽሐፍ በአባታችን ፊቅጦር ትእዛዝና በሥነ ድንግል ትጋት የፍቅራችሁ ዜና ግድ ስላላችሁ ከእናንተ ይደርስ ዘንድ በወደደ ጊዜ በፍቅር ደሴት ለምትኖሩ ለእናንተ ልከንላችኋል፡፡

፴፬ አበዊነ ደቂቀ ኢየሱስ ሞዓ ኢትርስኡነ በጸሎትክሙ፡፡ ለነሰ አልብነ ተስፋ ዘእንበሌክሙ ምስለ ጸሓፊሁ ወልደ አብ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡ ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

፴፬ የኢየሱስ ሞዓ ልጆች አባቶቻችን በጸሎታችሁ አትርሱን ከጸሓፊው ወልደ አብ ጋር ለእኛ ያለ እናንተ ተስፋ የለንምና፡፡ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

# ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

## ተአምር ፩

ተአምሪሁ ለቅዱስ አቡነ ጊዮርጊስ ሊቀ ወማእመረ ኵሉ መጻሕፍት ምሉአ ጸጋ ወሀብት ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም፡፡ አሜን፡፡

ሶበ ይጼሊ በስመ ዚአሃ ወእምአሜሃ ይቤላ አቡነ ጊዮርጊስ እግዝእትነ ማርያም እም ከመ አባሕክኒ ሰአሊዮ ለፍቁር ወልድኪ ከመ የሀበኒ ዐሥራተ እለ ይመጽኡ ለስኢመ መርጡልየ ወይትቀበሩ በውስቴታ ወይነብሩ ባቲ እስመ ይፀንዕ ላዕሌሃ ሐሩረ ፀሐይ

ወሰአለት በጽፋቅ እግዝእትነ ኀበ ወልዳ እንዘ ትብል ሰማዕ ስእለቶ ወፈጽም ጻሕቆ ለፍቁርየ ዐሥራተ ለእለ መጽኡ በንጽሐ ልጊዮርጊስ ወይቤሎ መድኀኒነ ወሀብኩከ ብ ለስኢመ መርጡልከ ወዘተቀብረ ውስቴታ በዛቲ ወበዕለተ ተዝካርከ ዘአብአ ዕጣነ አው ስንዳሌ አው ማኅቶተ እምሕር ለከ ወዘንተ ብሂሎ ዐርገ እግዚእነ ውስተ ሰማያት ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን፡፡

## አንደኛ ተአምር

መጻሕፍትን የሚያውቅ ጸጋንና ሀብትን የተመላ አባታችን ቅዱስ ጊዮርጊስ ያደረገው ተአምር ይህ ነው፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይኑር ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

በእርስዋ ስም ሲጸልይ በዚያን ጊዜ አባታችን ጊዮርጊስ እንዲህ አላት፤ እመቤታችን ማርያም ከፈቀድሽልኝስ ገዳሜን ለመሳለም የሚመጡትን በውስጧም የሚቀበሩትን፣ የፀሐዩ ሐሩር ይጸናባታልና ይህን ሁሉ ችለው የሚኖሩበትን ዐሥራት አድርጎ ይሰጠኝ ዘንድ የተወደደው ልጅሽን ለምኚልኝ፡፡

እመቤታችን የወዳጇ የጊዮርጊስን ልመናውን ሰማ፤ ምኞቱንም ፈጽም አያለች በፍጹም ልብ ወደ ልጅዋ ለመነች መድኀኒታችንም በንጹሕ ልብ ሆነው ገዳምህን ለመሳለም የመጡትን በውስጧም የተቀበሩትን ዐሥራት አድርጌ ሰጥቸሃለሁ፡፡ በመታሰቢያህም ቀን ዕጣኑን ስንዴውን /መገበሪያውን/ ወይም መብራቱን ያስገቡትን ሁሉ እምርልሃለሁ አለው፡፡ ይህንም ብሎ ጌታችን ወደ ሰማያት ዐረገ፤ ለዘላለሙ አሜን ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

# ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

## ተአምር ፪

ተአምሪሁ ለቅዱስ አቡነ ጊዮርጊስ ሊቅ ወማእመረ ኵሉ መጻሕፍት ምሉአ ጸጋ ወሀብት ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም፡፡ አሜን፡፡

ወካዕበ በአሐቲ እምነ መዋዕል እንዘ ያወትር ጸሎተ በከመ ልማዱ ቅድመ ሥዕላ ለእግዝእትነ ማርያም ለዘክሮታ ሰጊድ አስረረ ሕሊናሁ በጣዕመ ፍቅራ ወሮፀ ኀቤሃ ወሐቀፋ ወጠበወ አጥባተ ሥዕላ በሃይማኖት፡፡ ወውሕዘ ሎቱ እምአጥባቲሃ ሐሊብ ዘመንክር ጣዕሙ፡፡ አጽገበቶ መና ወአርወየቶ፡፡ ወአብርሃት ገጾ በቅብዐ ሐሊብ ወይእተ ሶበ ተፈሥሐ በመንፈስ ቅዱስ ወደረሰ ላቲ መጽሐፈ ዘይሰመይ ኆኅተ ብርሃን ዘይደሉ ለክብረ ውዳሴሃ፡፡ ወለዛቲኬ መጽሐፍ ዘቀዳሚት ድርሰቱ ይእቲ፡፡ ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

## ሁለተኛ ተአምር

መጻሕፍትን የሚያውቅ ጸጋንና ሀብትን የተመላ ቅዱስ አባታችን ጊዮርጊስ ያደረገው ተአምር ይህ ነው፡፡ ልመናውና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

ከዕለታትም በአንዳቸው እንዳስለመደው ለስም አጠራርዋ ስግደት ይሁንና ከእመቤታችን ሥዕል ፊት ሲጸልይ በፍቅሯ ጣዕም ኅሊናው ተመሰጠ፡፡ ወደ እርስዋም ሮጠ አቀፋትና በሃይማኖት የሥዕለቱን ጡት ጠባ፤ ከጡቶቿም ጣዕሙ ድንቅ /ልዩ/ የሆነ ወተት መነጨለት፡፡ አጠገበችው አረካቸው በወተት ቅቤም ፊቱን አበራችለት፡፡ ያን ጊዜም በመንፈስ ቅዱስ ደስ አለው፡፡ ለምስጋናዋ ክብር የሚገባ ኆኅተ ብርሃን የተባለ መጽሐፍንም ደረሰለት፡፡ ይህችም መጽሐፍ የመጀመሪያ ድርሰቱ ናት፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

# ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

## ተአምር ፲

ተአምሪሁ ለቅዱስ አቡነ ጊዮርጊስ ሊቅ ወማእመረ ኵሉ መጻሕፍት ምሉአ ጸጋ ወሀብት ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም፡፡ አሜን፡፡

ወካዕበ በአሐቲ ዕለት እመዋዕል ፈቀደ ከመ ይጽሐፍ መጽሐፈ ድርሳን፡፡ ወወዐለ እንዘ ይጽሕፍ አሐተ ዕለተ ወበሳኒታ ሶበ ፈቀደ ከመ ይዌስክ ላዕሌሁ ረከቦ ለውእቱ ጥራዝ ፀአዳዎ፡፡ ወሐመ ልቡ በእንተዝ ወመሰሎ ዘተሰርቀ፡፡ ወሶበ ኈለቈ ጥራዛተ እለ ተቀፅአ ረከቦን ጽኑናነ፡፡ ወካዕበ ደገመ ጽሒፈ ወበሳኒታ ረከቦ ከዊኖ ጽዕድወ ከመ ቀዳሚ እስከ ሣልስ ወራብዕ ዕለት፡፡ ጊዮርጊስ ወእምድኅረዝ ወጠነ አቡነ ጊዮርጊስ ይትማሕለል ኀበ እግዝእትነ ወይቤላ ክሥቲ ሊተ እመ በኃጢአትየ ኮነዝ አው አልቦ፡፡

ወበአሐቲ ዕለት እምዘ የሐውር ውስተ ቤተክርስቲያን ለጸሎት መንፈቀ ሌሊት ግብተ አስተርአየቶ እግዝእትነ ለጊዮርጊስ በስብሐት ዘኢይትነገር ወምስሌሃ ማኅበረ ኲሎሙ ቅዱሳን ወትእኅዝ በእዴሃ መጽሐፈ ዘይበርህ እምነ ፀሐይ ወወርኀ፡፡ ጊዮርጊስ ሶበ ርእየ ወድቀ ውስተ ምድር ወኮነ ከመ በድን፡፡ ወእግዝእትነሰ አንሥአቶ ወትቤሎ ለምንትኑ ደፈርከ ጽሒፈ መጽሐፍየ ዘእንበለ ትስእለኒ፡፡

## ሦስተኛ ተአምር

መጻሕፍትን የሚያውቅ ጸጋንና ሀብትን የተመላ ሊቁ ቅዱስ አባታችን ጊዮርጊስ ያደረገው ተአምር ይህ ነው፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

ዳግመኛም ከዕለታት አንድ ቀን የድርሰት መጽሐፍ ሊጽፍ ወደደ፤ አንድ ቀንም ሲጽፍ ዋለ፡፡ በማግሥቱ በዚያው ላይ ሊጨምር በወደደ ጊዜ የተጻፈበት ጥራዝ ቀለሙ ጠፍቶ ነጭ ሆኖ አገኘው፤ ስለዚህም የተሰረቀ መስሎት ልቡ አዘነ፡፡ የተስተካከሉ ጥራዞችንም በቈጠረ ጊዜ ደኅና ሆነው አገኛቸው ሁለተኛም በድጋሚ ጻፈ፡፡ በማግሥቱም እንደ መጀመሪያው ነጭ ሆኖ አገኘው እስከ ሦስትና ዐራት ቀንም /ተደጋገመ/ እንዲህ ሆነ፡፡ ከዚህ በኋላ አባታችን ጊዮርጊስ ወደ እመቤታችን ይማለል /ይጸልይ/ ጀመረ፤ ይህ የሆነ በኀጢአቴ ነውን? ወይስ አይደለም? ግለጭልኝ አላት፡፡

አንድ ቀንም በሌሊት እኩሌታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎት ሲሔድ እመቤታችን በድንገት በማይነገር ክብር ለጊዮርጊስ ተገለጸችለት ከእርሷም ጋር የቅዱሳን ማኅበር ሁሉ ነበሩ፡፡ በእጅዋም ከፀሐይና ጨረቃ የበለጠ የሚያበራ መጽሐፍን ይዛ ነበር፤ ጊዮርጊስም ባየ ጊዜ ወደ መሬት ወደቀ፤ እንደ በድንም ሆነ፡፡ እመቤታችንም አነሣችውና ሳትጠይቀኝ መጽሐፌን ትጽፍ ዘንድ ለምን ደፈርህ አለችው፡፡

# ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

አኮኑ አነ አፍቀርኩከ ወቀደስኩከ እምከርሠ እምከ ወወሀብኩከ ምሕፃነ ለጴጥሮስ ወጳውሎስ ወዮሐንስ፡፡ ወይቤላ ጊዮርጊስ ስረዩ ሊተ እግዝእትየ እስመ በኢያእምሮ ገበርክዎ ለዝንቱ እንዘ ይመስለኒ ዘአሠምረኪ፡፡

ወእግዝእትነሂ ትቤሎ ሰረይኩ ለከ አ ፍቁርየ ወውእቱሂ መጽሐፍ ዘፈቀድከ ትጽሐፎ ናሁ እትኀዝ ውስተ እዴየ፡፡ እምይእዜሰ ሠምረ ወልድየ ፍቁር ከመ ይክሥቶ በአፉከ ወባሕቱ ኢትጕጕእ እስከ ትለብስ ኃይለ እምአርያም፡፡ ወዘንተ ብሂላ ተሰወረት፡፡

ወሶቤሃ በርሀ ልቡ ከመ ፀሐይ ወኀተወ ውስተ ኀሊናሁ ባሕርየ መለኮት፡፡ ወነጸረ ኲሎ ኀቡኣተ በመጽሔተ መንፈስ ቅዱስ ወአኀዘ ይድርስ ወይጽሐፍ መጽሐፈ ዘይሰመይ አርጋኖነ ውዳሴ በመዋዕሊሁ ለዳዊት ንጉሥ መፍቀሬ እግዚአብሔር፡፡

ወሰመዮ በሠለስቱ አስማት ዘውእቶሙ አርጋኖነ ውዳሴ ወመሰንቆ መዝሙር ወዕንዚራ ስብሐት፡፡ ወእንበይነ ጣዕሙ ለውእቱ መጽሐፍ አጽሐፎ ንጉሥ በቀለመ ወርቅ፡፡ ሶበ ኃጥአ እብነ በዘያጸድሎ ለወርቅ ነገረቶ እግዝእትነ ማርያም ለጊዮርጊስ በራእየ ሌሊት ከመ ሀሎ በሀገረ ዚማት ወአርአየቶ ሕበሪሁ፡፡ ይቤ አቡነ ጊዮርጊስ እምኲሉ ድርሳናት ዘደረስክምዎ ወዘተናገርክምዎ ይጥዕም ወይትሌአል አርጋኖነ ውዳሴ፡፡

እኔ ወድጄህ ከእናትህስ ማሕፀን መርጬህ ለጴጥሮስ፣ ለጳውሎስና ለዮሐንስ አደራ ሰጥቼህ የለምን አለችው፡፡ ጊዮርጊስም እመቤቴ ሆይ ይቅር በይኝ፤ ደስ የሚያሰኝሽ መስሎኝ ይህን ባለማወቅ ሠርቼዋለሁና አላት፡፡

እመቤታችንም ወዳጄ ሆይ ይቅር ብየሃለሁ አለችው ልትጽፈው የወደድኸው መጽሐፍም እነሆ በእጄ አለ፤ ከአሁን በኋላ የተወደደ ልጄ በአንደበትህ ሊገልጸው ወድዷል፡፡ ነገር ግን ከአርያም ከሰማይ ኀይልን እስክትለብስ ድረስ አትቸኩል፤ ይህንም ብላ ተሰወረች፡፡

ያን ጊዜም ልቡ እንደ ፀሐይ በራ የመለኮትም ባሕር በኅሊናው አበራ፡፡ በመንፈስ ቅዱስም መስታወት የተሰወረውን ሁሉ አየ፡፡ እግዚአብሔርን በሚወድ በንጉሥ ዳዊት ዘመንም አርጋኖነ ውዳሴ የተባለ መጽሐፍን ይደርስና ይጽፍ ጀመር፡፡

በሦስትም ስሞች ጠራው እነዚህም አርጋኖና ውዳሴ፣ መሰንቆ መዝሙር፣ ዕንዚራ ስብሐት ናቸው፡፡ ስለ መጽሐፉም ጣፋጭነት ንጉሡ በወርቅ ቀለም አጻፈው፡፡ ወርቁን የሚያንጸባርቅበት ድንጋይ /ዕንቍ/ ባጣ ጊዜ እመቤታችን ማርያም በሌሊት ራእይ ዘማት በሚባል አገር እንዳለ ለጊዮርጊስ ነገረችው ኅብሩንም አሳየችው፡፡ አባታችን ጊዮርጊስም ከደረስኳቸውና ከተናገርኋቸው ድርሳናት ሁሉ አርጋኖን ውዳሴ ይጣፍጣል? ይበልጣል አለ፡፡

# ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ወከመዝ ደረሰ ብዙኀተ ድርሳናተ ወመጻሕፍተ ጸሎታት በረድኤተ አምላኩ ወበረድኤታ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም፡፡ ወአስማቲሆሙ ለእሉ ድርሳናት ወኍላቌኖሙ ዕውቅ በኀበ ሊቃውንት ዘውእቶሙ ውዳሴ መስቀል ወመጽሐፈ ብርሃን ወመጽሐፈ ሰዓታት ዘመዓልት ወዘሌሊት ወመጻሕፍተ ቅዳሴያት

ወጸሎተ ፈትቶ ውዳሴ ወማኅሌት ዘሐዋርያት፣ መልክአ ቊርባን ፣ወፍካሬ ሃይማኖት፣ ወመጽሐፈ ምስጢር፣ ወሕይወታ ለማርያም፣ ወተአምኖ ቅዱሳን፣ ወጸሎት ዘቤት ውስተ ቤት፣ ወውዳሴ ስብሐት ወሰላምታ፣ ወጸሎተ ማዕድ፣ ወቅዳሴ እግዚእ ካልእ፣ ወውዳሴ ማርያም ካልእ፣ ወመዝሙረ ድንግል፣ ወዘይመስሎ፡፡ ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

እንደዚሁም በፈጣሪው ቸርነት በእመቤታችን ረድኤት ብዙ ድርሳናትንና የጸሎት መጻሕፍትን ደረሰ፡፡ የእሊህም ድርሳናት ስማቸውና ቁጥራቸው በሊቃውንት ዘንድ የታወቀ ነው፡፡ እሊህም ውዳሴ መስቀል፣ መጽሐፈ ብርሃን፣ መጽሐፈ ሰዓታት የመዓልትና የሌሊት፣ መጻሕፍተ ቅዳሴያት ናቸው፡፡

ጸሎተ ፈትቶ /የፍታቴ ጸሎት/ የሐዋርያት ማኅሌት መልክአ ቊርባን፣ ፍካሬ ሃይማኖት፣ መጽሐፈ ምስጢር፣ ሕይወታ ለማርያም፣ ተአምኖ ቅዱሳን፣ ጸሎት ዘቤት ውስተ ቤት፣ ውዳሴ ስብሐት፣ ሰላምታ፣ ጸሎተ ማዕድ፣ ቅዳሴ እግዚእ ካልእ፣ መዝሙረ ድንግልና የመሳሰለው ነው፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

## ተአምረ ፬

ተአምሪሁ ለቅዱስ አቡነ ጊዮርጊስ ሊቀ ወማእመረ ኵሉ መጻሕፍት ምሉአ ጸጋ ወሀብት ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም፡፡ አሜን፡፡

## ዐራተኛ ተአምር

መጻሕፍትን የሚያውቅ ጸጋንና ሀብትን የተመላ አባታችን ቅዱስ ጊዮርጊስ ያደረገው ተአምር ይህ ነው፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

## ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ጸጋ ወኀይል መንክር ወመድምም ዘገብረት እግዝእትነ ማርያም ዘበእብራይስጥ ማሪሃም ጸሎታ ወበረከታ ወምሕረተ ፍቁር ወልዳ ወጸሎቱ ለዝንቱ ጻድቅ አባ ጊዮርጊስ የሀሉ ምስለ ኲልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

በዕብራይስጥ ደሪሃም የምትባል እመቤታችን ማርያም ያደረገችው ድንቅ ተአምርና ጸጋ ይህ ነው፡፡ ልመናዋና ክብሯ የተወደደ የልጅዋም ቸርነት የጻድቁ አባ ጊዮርጊስም ጸሎት ከሁላችን ሕዝበ ክርስቲያን ጋር ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

ወሀሎ ፩ መምህረ ደብር ዘፍጹም በኲሉ ምግባረ ሠናይ ወበሃይማኖት ወፍቁረ ዚአሃ ወፍቁረ ወልዳ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወባሕቱ ኮነ ይጸልዕ ወይሜንነ ማኅሌተ አቡነ ጊዮርጊስ ወያስተሐቅሮሙ ለእለ ይትቀነዩ ሰዓታተ ዚአሁ
ወለእለሰ ያነብቡ መጻሕፍተ ምድራሳቲሁ ይከልዖሙ ከመ ኢያንብቡ ወያወግዞሙ በጽኑዕ መሐላ ወአጽርዖ በውስተ ኲሉ መካናቲሁ

በሁሉም በጎ ሥራና ሃይማኖት ፍጹም የሆነ የእርስዋና የልጅዋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወዳጅ የሆነ አንድ የደብር መምህር ነበር፡፡ ነገር ግን የአባታችን ጊዮርጊስን ማኅሌት ይጠላና ይንቅ ነበር፡፡ በሰዓታቱም የሚያገለግሉትን ያቃልላቸው ነበር፡፡
የደረሳቸውንም መጻሕፍት የሚያነብቡትን እንዳያነብቡ ይከለክላቸዋል፡፡ በጽኑ መሓላም ያወግዛቸዋል፡፡

ከመ ኢይትቀነዩ ሰዓታቲሁ ወከመ ኢያንብቡ መጻሕፍቲሁ ዘከሠተ ሎቱ እግዚአብሔር እሎንተ መጻሕፍተ ቅዱሳተ ወአስማቲሆሙ መጽሐፈ ምስጢር ወአርጋኖነ ስብሐት ወዓዲ መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘመዓልት፡፡ ወኖኅተ ብርሃን ወብዙኃተ ምድራሳተ ዘብሉይ ወዘሐዲስ ዘከመ አንበበ መንፈስ ቅዱስ ወዘንተ ኲሎ ከመ ኢያንብቡ ወኢይትቀነዩ አብጠለ ወአጽርአ በኲሉ ስብከታቲሁ፡፡

በሰዓታቱ እንዳያገለግሉ እግዚአብሔር የገለጠለት እነዚህን የተቀደሱ መጻሕፍትንም እንዳያነብቡ በቦታው ሁሉ አስቀረ፡፡ ስማቸውም መጽሐፈ ምስጢር አርጋኖነ ስብሐት፣ የመዓልትና የሌሊት መጽሐፈ ሰዓታት፣ ኆኅተ ብርሃን፣ ናቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስ እንደገለጸለት ከብሉይና ከሐዲስ እያውጣጣ የደረሳቸውን ብዙ ድርሰቶች ይህን ሁሉ እንዲያነብቡ እንዲያገለግሉም በስብከቱ ቦታ ሁሉ ከለከለ፡፡

## ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ባዕደኒ ካልአ ነገረ የሐምዮ ወይጸርፎ ዘበቃለ ጽዕለት ዓቢይ ዘኢይትከሃል ለተናግሮ በከመ ትቤ ነቢይት ሐና ኢትትመክሁ ወኢትንብቡ ዓቢያተ ወኢይፃዕ ዓቢይ ነገር እምአፋክሙ፡፡ እስመ እግዚአብሔር አምላክ ማእምረ አልባብ ውእቱ፡፡ እግዚአብሔር አስተዳለወ መንበሮ በሰማያት ወኲሎ ይኴንን፡፡ ወበዝንቱ ኲሉ ነገር እንዘ ሀለወ ውእቱ መምህረ ደብር ወአቡነሂ ጊዮርጊስ እንዘ ይትናገር ግፍዖ ወይትመሐፀን ግፍዖ በቅድመ እግዚአብሔር በሰማያት ወበቅድመ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል በ፪ ማርያም ወላዲተ አምላክ፡፡

ዳግመኛም በሌላ ነገር ያማዋል፤ ሊናገሩት በማይቻል፤ ነቢይቱ ሐና "አትመኩ የኩራት ነገሮችንም አትናገሩ ጽኑዕ ነገርም ከአፋችሁ አይውጣ፤ እግዚአብሔር አምላክ ልቡናን ይመረምራልና እግዚአብሔር በሰማያት ዙፋኑን አዘጋጀ፤ ሁሉንም ይገዛ" እንዳለች፡፡ ፩ሳሙ.፪፥፫

ያም የደብር መምህር በዚህ ሁሉ ግፍ ሳለ አባታችን ጊዮርጊስ ዳግም በእግዚአብሔር ፊት በሰማያት ግፉን እየተናገረ አምላክን በወለደች በሁለት ወገን ድንግል በሆነች በእመቤታችንም ፊት እየተማፀነ እመቤታችንን የልቤን ምስጢር እንደምታውቂ እዩ አላት፡፡

ወይቤላ ለእግዝእትነ ርእዪኬ በከመ አእመርኪ አንቲ ኅቡአተ ልብየ ወአንቲ ትጠይቂ ለእመ ኮነ ዝንቱ ኲሉ አእምሮ ምድራሳትየ ወዘሰብሕዎ ቃለ መጻሕፍትየ በተጥባበተ ሰብእ ዘበቃለ አስማት ወበመቲረ ዕፅዋት ወአቁጽላት ወበከመ ፈተንክኒ አንተ ንግሥትየ እምቀዳሚ እስከ ደኅሪ ለእመ አጥረየኩ ባእደ እግዝእተ ዘእንበለ አሐቲ ቤዛዊትየ፡፡

ይህ ሁሉ ድርሰት በዕውቀት ሰዎች የሚያመሰግኑባቸው መጻሕፍት፣ በሰው ጥበብ፤ በአስማት፣ ሥር በመማስ ቅጠል በመበጠስ እንደሆነ አንቺ ታውቃያለሽ አላት፤ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ /ንግሥቴ/ እመቤቴ አንቺ እንደ መረመርሺኝ ቤዛዊት ከሆንሽኝ ከአንቺ በቀር ሌላ እመቤት ከተከተልሁ አንቺ ታውቂያለሽ ሥራዬን እንደምታውቂና እንደምትረጂ አንቺ እስኪ ፍረጂልኝ፡፡

# ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ወዘከመ ተአምሪ ወትጠይቂ ኵሎ ምግባራትየ ፍትሒ እስኩ አንቲ ወአስተኰንኒ ምስለ ዝኩ መምህረ ደብር ዘይጽእለኒ ወይዘነጉገኒ በቅድመ ደቂቁ እንዘ ሀለዉክኒ አንቲ ዘታጸድቅኒ ወትኰንንኒ አ እግዝእትየ፡፡ ወበእንተ ግፍዑ ለአቡነ ጊዮርጊስ መጽአ ቃለ ትዕዛዝ እምኀበ ፍቁር ወልዳ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይምስጥዋ ለነፍሰ ውእቱ መምህረ ደብር በጕጕኣ፡፡

ወእምዝ መሠጥዋ ለነፍሰ ውእቱ መምህር ግብተ ዘአንበለ ፃዕር ወደዌ፡፡ ወአዕረግዋ በከመ ሥርዐተ ዕርገቶሙ ለነፍሳተ ጻድቃን ኅሩያን፡፡ ወበጊዜ በጽሑ መላእክተ ብርሃን መጽአ ምስለ ፀቱ ሊቃናት ከመ ይትቀበልዋ ለነፍሰ ውእቱ መምህር፡፡ ወማእከለ እሙንቱ ሊቃናት ከዊኖ ዕሩየ ወሥርግወ ከማሆሙ መጽአ ዝኩ አዛል አቡነ ጊዮርጊስ በክብር ወበሞገስ፡፡

ወፈቀደ ከመ ይትአማኅ ምስሌሆሙ ውእቱ መምህረ ደብር እስመ ንጹሕ ውእቱ በምንኵስናሁ ወምዑዝ በቅድስናሁ ወፍጹም በድንግልናሁ ወፍድፉድ ገድለ ፃማሁ፡፡ ወሶበ ቀርበ ለተአምኆቶሙ አውሥእዎ መንፈሳውያን ሊቃውንት ለውእቱ መምህር፡፡

እመቤቴ ሆይ በአማላጅነትሽ የምታጸድቂኝና የምትፈርጂልኝ አንቺ ሳለሽኝ በልጆቹ ፊት ከሚሰድበኝና ከሚያሽሟጥጠኝ ከዚህ ከደብር መምህር ጋር አፋርጂኝ፡፡ ስለ አባታችን ጊዮርጊስም ግፍ የሚናገር የደብር መምህርን ነፍስ በፍጥነት ነጥቀው ይወስዷት ዘንድ ከተወደደ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ መጣ፡፡

ከዚያም በኋላ የዚያን መምህር ነፍስ ያለጻዕርና ሕማም ድንገት ነጠቀው ወሰዷት፤ እንደ ተመረጡ የጻድቃን ነፍሳት ሥርዐትም ወደ ሰማይ ዐሳረጓት የብርሃን መላእክትም በደረሱ ጊዜ የዚያን መምህር ነፍስ ይቀበሏት ዘንድ ከዘጠኙ ሊቃናት ጋር መጣ፡፡ በእነዚያም ሊቃናት መካከል እንደ እነርሱ የተካከለና የተሸለመ ሆኖ ይህ ብርቱ አባታችን ጊዮርጊስ በክብርና በባለሟልነት መጣ፡፡

ያም የደብር መምህር በምንኩስናው ንጹሕ፣ በቅድስናው ያማረ በድንግልናው ፍጹም፣ ተጋድሎውም ብዙ ነውና፡፡ ከእነርሱ ጋር እጅ ሊነሳ ወደደ እጅ ሊነሣውም በቀረበ ጊዜ ታላላቆቹ መንፈሳውያን ለዚያ መምህር መለሱለት፡፡

## ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ወይቤልዎ እስመ ናሁ ጊዮርጊስ ይትመሐፀነከ እንዘ ይዜከር ግፍዖ ወዘንተ ብሂሎሙ አበይዎ ተአምኖ ወኃደግዎ ወሖሩ ኀበ ሥርዓቶሙ፡፡ ወእምዝ አዕረግዎ ላዕለ እለ ይቄድሱ እለ ሱራፌል በዐውደ መንበሩ ለእግዚአብሔር ወጊዮርጊስኒ ሀሎ ምስሌሆሙ ድርገተ እንዘ የዓጥን ወሶበ ቀርበ ለእማኄሆሙ ውእቱ መምህር አበይዎ በእንተ ግፍዑ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡ ወካዕበ አዕረግዎ ኀበ ሀለዉ ይቄድሱ እለ ኪሩቤል በገበዋተ መንበሩ ወምስሌሆሙ ድርገተ ረከቦ ለጊዮርጊስ እንዘ ይፀውር መንበሮ ለመኰንነ ጽድቅ ወሶበ ቀርበ ለእማኄሆሙ ውእቱ መምህር አበይዎ እለ ኪሩቤል ወይቤልዎ ናሁ ይትመሐፀነከ ጊዮርጊስ እንዘ ይዜከር ግፍዖ፡፡

እነሆ ጊዮርጊስ ግፉን እያሰበ ይከራከርሃል አሉት፤ ይህንም ብለው እጅ መንሣቱን አይሆንም አሉት፤ ወደ ሥርዐታቸውም ሔዱ፡፡ ከዚያም በኋላ በእግዚአብሔር ዙፋን ቆመው ወደሚያመሰግኑ አወጡት፡፡ ጊዮርጊስም ከእነርሱ ጋር አንድ ሆኖ ያጥን ነበር፡፡ ያም መምህር እጅ ለመንሣት በቀረበ ጊዜ ስለአባታችን ጊዮርጊስም ከእነርሱ ጋር አንድ ሆኖ የእውነት ፈርጅ መንበርን ተሸክሞ አገኘው፡፡ ያም መምህር እጅ ለመንሣት በቀረበ ጊዜ ኪሩቤልም እነሆ ጊዮርጊስ መገፋቱን እያሰበ ተማፅኖብሃልና አይሆንም አሉት፡፡

ወበከመዝ አምሳል በጽሑ ኀቤሁ ከመ ይተቀበልዎ ለውእቱ መምህረ ደብረ ማኅበረ ነቢያት በበሥርዓቶሙ እም አቡነ አዳም እስከ አብርሃም ወእም አቡነ አብርሃም እስከ ሙሴ ወእሙሴ እስከ ዮሐንስ ወእም ዮሐንስ እስከ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ እለ ገነዙ ሥጋሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወምስሌሆሙ ከዊኖ ዕሩየ በዕበይ ወበሞገስ አባ ጊዮርጊስ ወሶበ ቀርበ ዝኩ መምህር ከመ ይትአምኖሙ አውሥእዎ ከመ ቀዳሚ እንዘ ይዜክሩ ግፍዖ፡፡

በዚህም አምሳል ያን የደብር መምህር የነቢያት ማኅበር በየሥርዐታቸው ከአዳም እስከ አብርሃም ከአብርሃምም እስከ ሙሴ ከሙሴም እስከ ዮሐንስ፣ ከዮሐንስም የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ እስከ ገነዙ እስከ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ድረስ አባታችን ጊዮርጊስም በክብር ከባለሟልነት የተካከለ ሆኖ ይቀበሉት ዘንድ ወደ እርሱ መጡ፡፡ ያም መምህር እጅ ሊነሣቸው በቀረበ ጊዜ እንደ ቀድሞው ግፉን እያሰቡ መለሱለት።

## ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ወድኅሬሆሙ ለነቢያት መጽኡ ሐዋርያቲሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ እምአቡነ ጴጥሮስ እስከ አቡነ ማትያስ፣ እም አቡነ ጳውሎስ እስከ ኲሎሙ አርድእት ወሊቃውንት እሉ እሙንቱ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ ወዮሐንስ ልሳነ ወርቅ ወምስሌሆሙ ደርገ ከዊኖ ዕሩየ በሢመት ወበሥልጣን አቡነ ጊዮርጊስ ወከልዖሙ ከመ ኢይትአምኃዎ ለዝኩ መምህር እንዘ ያዜክሮሙ ግፍዖ፡፡ ወእምድኅሬሆሙ ለሐዋርያተ እግዚአነ መጽኡ ሰማዕታቲሁ ለልዑል እሉ እሙንቱ ቅዱስ እስጢፋኖስ ወንጉሠ ሰማዕታት ብፁዕ ወቅዱስ ጊዮርጊስ ወዘአንጾኪያ ፋሲለደስ ወምስለ ቴዎድሮስ ወገላውዴዎስ ወብፁዕ ዮስጦስ ወወልዱ አቦሊ ወቅዱስ ፊቅጦር ወመርቆሬዎስ ወብፁዕ ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳሳት ወተፈጻሚተ ሰማዕት ወኲሎሙ ሕፃናተ ገሊላ እለ ተክዕወ ደሞሙ በእንተ ስምዐ ጽድቅ ወምስሌሆሙ ከዊኖ ዕሩየ አባ ጊዮርጊስ በሥን ወበሞገስ ወበአክሊለ ስብሐት ወከመ ሕፃናት ኅሩያን በተሠርግዎ አልባስ ወሶበ ፈቀዱ ከመ ይትአምኃዎ ከልዖሙ አባ ጊዮርጊስ እንዘ ያዜክር ግፍዖ፡፡

ከነቢያትም በኋላ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ደቀ መዛሙርት ከአባታችን ጴጥሮስ እስከ አባታችን ማትያስ፣ አባ ጳውሎስና አባ እንጦንዮስ አባ መቃርዮስና አባ ሲኖዳ የንጉሡ ልጅ አባ ኪሮስና ከአባታችን ጳውሎስ እስከ ሁሉም አርድእትና ሊቃውንት መጡ፡፡ እሊህም ባስልዮስ ጎርጎርዮስ ልሳነ ወርቅ የተባለ ዮሐንስ ናቸው ከእነርሱም ጋር አባታችን ጊዮርጊስ በሹመትና በሥልጣን የተካከለ ሆኖ ግፉን እያሳሰበ ያን መምህር እጅ እንዳይነሡት ከለከላቸው፡፡ ከጌታችን ሐዋርያትም ቀጥሎ የልዑል እግዚአብሔር ሰማዕታት መጡ፤ እሊህም ቅዱስ እስጢፋኖስ የሰማዕታት አለቃ ብፁዕና ቅዱስ ጊዮርጊስ የአንጾኪያው ፋሲለደስ ቴዎድሮስና ገላውዴዎስ፣ ብፁዕ ዮስጦስና ልጁ አቦሊ፣ ቅዱስ ፊቅጦር መርቆሬዎስ የሰማዕታት መጨረሻና የጳጳሳት አለቃ ብፁዕ ጴጥሮስ እውነትን ለመመስከር ደማቸው የፈሰሰ የገሊላ ሕፃናት ሁሉ መጡ፡፡ አባ ጊዮርጊስም ከእነዚህ ጋር በመልክ፣ በባለሟልነት፣ በክብር አክሊል እንደተመረጡ ሕፃናትም በልብስ /አጊጦ/ ተሸልሞ ነበር፤ እጅ ለነሡትም /ሰላምታ/ ሊሰጡትም በወደዱ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ መገፋቱን አሳስቦ ከለከላቸው፡፡

## ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ወእምዝ መጽኡ አበዊነ ቅዱሳን አባ ጳውሎስ ወአባ እንጦንዮስ ወአባ መቃርዮስ ወአባ ሲኖዳ ወአባ ኪሮስ ወልደ ንጉሥ ወአባ ብሶይ ዘሐፀበ ለኢየሱስ ዘምስለ ኲሎሙ መነኮሳት እለ ሀለዉ በበአታት ወእለ በጾማዕት ወምስሌሆሙ መጽአ አባ ጊዮርጊስ ከዊኖ ሥርግወ በንጽሕና ወበቅድስና አምሳለ መላእክት፡፡ ወሶበ ቀርበ ዝኩ መምህረ ደብር ከመ ይትአምኆሙ ለእሉ መነኮሳት ወአውሥእዎ ወይቤልዎ ይትመሐፀነነ ወልድነ ጊዮርጊስ እንዘ ይዜከር ግፍዖ፡፡

ከዚህም በኋላ አባቶቻችን ቅዱሳን አባ ጳውሎስ፣ አባ እንጦንዮስ፣ አባ መቃርስ፣ የንጉሥ ልጅ አባ ኪሮስና የጌታችን ኢየሱስ እግር ያጠበው አባ ብሶይ በዋሻና በፍርኩታ ከሚኖሩ ሁሉም መነኮሳት ጋር አባ ጊዮርጊስ እንደ መላእክት በንጽሕና እና በቅድስና የተሸለመ ሆኖ መጣ፤ ያም የደብር መምህር እሊያን ቅዱሳን መነኮሳት እጅ ሊነሣቸው በቀረበ ጊዜ ልጃችን ጊዮርጊስ ግፉን እያሰበ ይማፀነናል ብለው መለሱለት፡፡

ወእምዝ እምድኅረ ኲሎሙ መጽአት እግዚእትነ ድንግል በ፪ኤ ማርያም በወላዲተ አምላክ ወምስሌሃ ኅቡረ ሐና ወአልሣቤጥ ምእመናቲሃ ወኲሎን ደናግል ቅዱሳት እለማርያ ወማርታ ወማርያም እንተ ቀለዮጳ ወማርያም መግደላዊት ወሰሎሜ ወቅዱሳት እለ ሶፍያ ወኢዮጵራቅስያ ወአንጦልያ ወታውክልያ ወብፁዓት፤ እለ በርባራ ወዮልያና ወእንባ መሪና ወብፅዕት ቴክላ እኅቱ ለአባ ኤሲ ወበህየ ሀለዋ እምነ ሔዋን ወእምነ እድና እምነ ባረካ እምነ ሳራ ወርብቃ ራሄል ወልያ ወዲና ወዲቦራ ወዮዲት ዘምስለ አስቴር ወአሰኔት፡፡

ከእነዚህ ሁሉ በኋላ አምላክን የወለደች በሁለት ወገን ድንግል የሆነች እመቤታችን ማርያም መጣች፤ ከእርስዋም ጋር የታመኑ ሐናና ኤልሳቤጥ፣ ሁሉም ቅዱሳት ደናግል፣ እነ ማርያም ማርታና የቀለዮጳ ሚስት ማርያም፣ መግደላዊትና ሰሎሜ የተቀደሱ እነ ሶፍያና ኢዮጳራቅስያ፣ እነ አንጦልያና ታውክልያ፣ የተመሰገኑ እነ በርባራና ዮልያና እንባ መሪናና የአባ ኤሲ እኅት ብፅዕት ቴክላ ከእርስዋ ጋር ነበሩ፡፡ በዚያም እናታችን ሔዋንና እናታችን እድና፣ እናታችን ባረካና እናታችን ሣራ፣ ርብቃና ራሔል፣ ልያና ዲና፣ ዲቦራና ዮዲትም ከአስቴርና ከአስኔት ጋር ነበሩ፡፡

# ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ወመጽአት እግዝእትነ ማርያም እንዘ የዓውድዋ ወይኬልልዋ ኲሎሙ ማኅበረ መላእክት ወእንዘ የአኲትዋ ነቢያት ወይባርክዋ ሐዋርያት ወያስተበፅዕዋ ኲሎሙ ማኅበረ ጻድቃን ወሰማዕት ወአቡነ ጊዮርጊስ እንዘ ይዜምር ወየኀሊ በቅድሜሃ በአርጋኖነ ወዳሴ ወበእንዚራ ስብሐት እስከ ያነክሩ እምዕበየ ክብሩ ኲሎሙ ሠራዊተ ሰማያት፡፡ ወበጺሖ ውእቱ መምህረ ደብር ሰገደ በቅድሜሃ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል በ፪ኤ ርያም ወላዲተ አምላክ፡፡

ወሶበ ፈቀደ ለተአምኖታ ወአውሥአቶ ወትቤሎ ይትመሐጸነከ ፍቁርየ ጊዮርጊስ እንዘ ይብለከ ገፋዕከኒ ወጸላእከኒ ወባሕቱ በከመ አእመርኩ ወጠየቁ ኲሎ ኅቡዓቲሁ ለጊዮርጊስ እገብር ሰላመ ማእከሌከ ወማእከሌሁ፡፡ ወእምዝ ትቤሎ ለጊዮርጊስ ፍቁራ ነዋ ውእቱ ዘትቤሎ ገፍዓኒ ወጸአለኒ ወሐመየኒ ዘምስለ ደቂቁ፡፡ ወናሁ አዘዝክዎ በእንቲአከ ከመ ይፍዲከ በሕቁ ህየንተ ዘሐመየከ ወጸዓለከ በኢያእምሮቱ፡፡ ወአዘዞ ለውእቱ መምህረ ደብር ከመይትጋነይ ሎቱ ለአባ ጊዮርጊስ ወገብረት እግዝእትነ ማርያም ሰላመ ወፍቅረ ማዕከለ ፪ኤሆሙ፡፡

እመቤታችን ማርያምም ሁሉም የመላእክት ማኅበር አጅበዋትና ከበዋት፣ ነቢያት እያመሰገኗት፣ ሐዋርያት እያከበሯት የጻድቃንና የሰማዕታት ማኅበር ሁሉ እያደነቋት አባታችን ጊዮርጊስም ከክብሩ ገናንነት የተነሣ የሰማይ ሠራዊት እስኪያደንቁ ድረስ በፊቷ በአርጋኖነ ውዳሴ /በምስጋና አርጋኖንና /በእንዚራ ስብሐት እያመሰገነ መጣች፡፡ ያም የደብር መምህር ቀርቦ አምላክን በወለደች በሁለት ወገን ድንግል በሆነች በእመቤታችን ቅድስት ማርያም ፊት ሰገደ፡፡

እጅ ሊነሣትም በወደደ ጊዜ ወዳጄ ጊዮርጊስ ገፍተኸኛል ጠልተኸኛል እያለ ተማፅኖብሃል አለችው፡፡ ነገር ግን የጊዮርጊስን ምስጢሩን ሁሉ እንዳወቅሁ በእርሱና በአንተ መካከል ስለምን አደርጋለሁ? ከዚህ በኋላ ወዳጅዋ ጊዮርጊስን ገፋኝ ሰደበኝ ከልጆቹም ጋር አማኝ የምትለው እነሆ እርሱ ነው አለችው፡፡ እነሆ ባለማወቁ ስለ አማህና ስለሰደበህ በጥቂቱ ይከፍልህ ዘንድ አዝዘዋለሁ፡፡ ያንም የደብር መምህር ለአባ ጊዮርጊስ ይታዘዝ ዘንድ አዘዘችው፡፡ እመቤታችን ማርያም በሁለቱ መካከል ሰላምንና ፍቅርን አደረገች፡፡

# ተአምረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ወእምድኅረዝ በትእዛዘ እግዝእትነ ማርያም ተመይጠ ውእቱ መምህረ ደብር ኀበ ዘትካት ህላዌሁ ወገብአ ውስተ መካኑ ወአስተጋብኦሙ ለኲሎሙ ደቂቁ ወነገሮሙ ኲሎ ዘረከቦ ኀዘነ ወምንዳቤ በሰማያት በእንተ ዘጸአሎ ወሐመዮ ለአቡነ ጊዮርጊስ፡፡ ወእምዝ አዘዞሙ ለኲሎሙ ከመ ይትቀነዩ ሰዓታተ ዚአሁ ወመጻሕፍተ ኲሎን ድርሳናቲሁ ኀበ ዘተሐንጸ ውስተ ኲሉ መካናቲሁ፡፡

ከዚህ በኋላ ያ የደብር መምህር በእመቤታችን ትእዛዝ ወደ ቀድሞ ደረሰ፡፡ ልጆቹን ሁሉ ሰብስቦ አባታችን ጊዮርጊስን ስለ ሰደበውና ስለ አማው በሰማያት ያገኘውን ኀዘንና ችግር ነገራቸው፡፡ ከዚያም በኋላ ልጆቹን ቤተ ክርስቲያን በታነጸበት ሁሉ በሰዓታትና በመጻሕፍቱ በድርሰቶቹ ሁሉ እንዲያገለግሉ አዘዛቸው፡፡

ወውእቱኒ መምህር እምአሜሃ አኀዘ ከመ ይትቀነይ ሰዓታተ ዘሌሊት ወዘመዓልት ወከመ ያንባብ መጽሐፈ አቡነ ጊዮርጊስ ዘእንበለ ጽርዓት ወነበረ እንዘ ይሰብክ ወይነግር ውስተ ኲሉ በሐውርት ዘከመ ርእየ በዐይኑ ወዘከመ ሰምዐ በእዝኑ ዕበዮ ወክብሮ ለአቡነ ጊዮርጊስ ዘተውህቦ በሰማያት፡፡ ወዝንቱ ኲሉ ዘኮነ ላዕለ ውእቱ መምህር በእንተ ኂሩቱ ወሠናይቱ ወበእንተ ተአምሪሃ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል በ፪ኤ ማርያም ወላዲተ አምላክ፡፡

ያም መምህር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሌሊትና በመዓልት ሰዓታት ያገለግልና የአባታችን ጊዮርጊስም መጽሐፍ ያለማቋረጥ ያነብብ ጀመር፡፡ በሰማያት የተሰጠውን የአባታችን ጊዮርጊስን ገናንነቱንና ክብሩን በዐይኑ እንዳየ በጆሮውም እንደሰማ በሀገሩ ሁሉ ሲሰብክና ሲናገር ኖረ፡፡ ይህ ሁሉ ነገር በዚያ መምህር ላይ የተደረገ ስለ ቸርነቱና ስለ በጎነቱ ነው፡፡ አምላክን ስለ ወለደች በሁለት ወገን ድንግል ስለሆነች ስለ እመቤታችን ማርያምም ተአምር ነው፡፡

ጸሎታ ወበረከታ የሀሉ ምስለ ኲልነ ሕዝበ ክርስቲያን ሰማዕያን ወአንባቢ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

ጸሎቷና በረከቷ ከምንሰማ ከሁላችን የክርስቲያን ወገኖችና ከአንባቢውም ጋር ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

# መልክአ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ይትፌሣሕ ልሳንየ በጽድቀ ዚአከ ዘልፈ፡፡
እንዘ አየድእ ዘስብሐቲከ ተረፈ፡፡
ጊዮርጊስ ዘኮንከ ለኀሊና ኵሉ መጽሐፈ፡፡
እስመ አኀዝኩ ሐረሳዌ በገራህተ ዚአከ ዕርፈ፡፡
ኀጠተ ውዳሴከ ዝራዕ ዘይፈሪ እልፈ፡፡

ሰላም ለዝክረ ስምከ ምሉአ ጸጋ ወሞገስ፡፡
ከመ ዝክረ ስሙ ዐባይ ለፀሐየ ልዳ ወፋርስ፡፡
ጊዮርጊስ ዕንቊ ዘወለደከ ተርሴስ፡፡
በጊዜ ንፍሐቱ ውስተ ገጸ ቀላይ ወየብስ፡፡
ለዘእምደቡብ ተንሥአ ነፋስ፡፡

ሰላም ለሥዕርተ ርእስከ በቅብዐ ሃይማኖት ስቁይ፡፡
ከመ እንተ ስኂን ምዑዝ ወከመ ቄድሮስ ኀሩይ፡፡
ጊዮርጊስ ትርሲት ወማኀቶተ ዓለም ባሕርይ፡፡
እምጸዳልከ ነጸብራቅ ወብርሃንከ ውኩይ፡፡
ኢይትፈቀድ ወርኀ ወምኑን ፀሐይ፡፡

ሰላም ለርእስከ ዘተረሰየ አክሊለ፡፡
እምዕንቊ ክቡር እንተ ቦ ጸዳለ፡፡
ጊዮርጊስ ዘብከ በውስተ ኵሉ ክሂለ፡፡
አስተዳሉ ለምእመናን ምሕረተ ወሣህለ፡፡
ወለዓላውያን ድምሳሴ ወኀጕለ፡፡

ሰላም ለቀራንብቲከ እለ ሐተታ ለነጽሮ፡፡
ፍኖተ ኢየሱስ ክርስቶስ ወኵሎ ዐሥሮ፡፡
ጊዮርጊስ ጥዑም አርጋኖነ ስብሐት ወዘምሮ፡፡
ድምፅከ ድምፀ ጥበብ ወከላህከ አእምሮ፡፡
እስከ ይእዜ በውስተ ኵሉ ይደምፅ ለምህሮ፡፡

ሰላም ለአዕይንቲከ ዘዘልፈ ይጸድላ፡፡
እምነ ቶማስስ ወእብላ፡፡
ጊዮርጊስ ጽጌ ወመድምመ ስን ሄላ፡፡
እንተ አሰርገውከ ለገነተ ወንጌል ማእከላ፡፡
ወመዐዛከ ነፈርአጽ ወጼናከ ተድላ፡፡

ሰላም ለአእዛኒከ እለ ዘልፈ ኮና፡፡
ለቤተክርስቲያን ህየንተ እዝና፡፡
ጊዮርጊስ ሰሎሞን በዕፀ ቄድሮስ ወዕፀ ጸውቄና፡፡
እም አመ አቅዘዝከ ውስተ ሰማያዊት ጸቆና፡፡
ብዙኃን ሰረቅት ኢረከቡ ፍና፡፡

ሰላም ለመላትሒከ አፈዋተ ዘፈረያ፡፡
እለ ይሜስላ አምሳለ ዘዕፀ ገነት አርአያ፡፡
ጊዮርጊስ መምህር ወሠላጤ መልእክት ሐዋርያ፡፡
ወአንተኬ ለባሕረ ሃይማኖት ጌልያ፡፡
ወአንተኬ ማእምር ኖትያ፡፡

# መልክአ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ሰላም ለገጽከ ውስተ ገጸ ክርስቶስ ዘአንጸረ፡፡
እንዘ ኢይትመየጥ ድኅረ፡፡
ጊዮርጊስ ዘኮንከ ለቤተ ክርስቲያን ሐመረ፡፡
በነፊሖቶሙ ሶበ ጐድኡ ባሕረ፡፡
አበርዮስ ወአውጣኪ ዘዐረዩ ምክረ፡፡

ሰላም ለአዕናፊከ እለ ይነፍሓ ለጥዒና፡፡
ነፋሰ መዐዛ ወጼና፡፡
ጊዮርጊስ ዕንቍ ጥሪተ ማርያም ወሕፃና፡፡
ዝክርከ ኃሤተ ልብ ወጣዕመ ፍቅርከ መና፡፡
ከመ ሞገደ ባሕር ጽኑዕ የሐውክ ኅሊና፡፡

ሰላም ለከናፍሪከ ዘመለኮተ ይትናገራ፡፡
ዘኢይትረሳእ ለዝላፉ ወኢይትኃደግ ለግሙራ፡፡
ጊዮርጊስ መምህር ወነቢይ ከመ ዕዝራ፡፡
ሶበ ትዘብጥ በዜማ አርጋኖነ ስብሐት መዝሙራ፡፡
ማርያም ትትፌሣሕ ወይትኃሠይ በኲራ፡፡

ሰላም ለጉርዔከ ለመቅደሰ ስብሐት አንቀጹ፡፡
መደንግፀ ክላሑ ወድምፀ ነጐድጓድ ድምፁ፡፡
ጊዮርጊስ ምዑዝ ለልሳነ ዕፍረት ቢጹ፡፡
ነገሥታተ (በእንቲአከ) ምድር እለ በመዐዛከ ሮፁ፡፡
በአእባነ ብሩር ወወርቅ ቤተከ ሐነፁ፡፡

ሰላም ለአፉከ ዘተሰውጠ ቦቱ፡፡
ለሙሴ ትንቢቱ ወለጳውሎስ ዕፍረቱ፡፡
ጊዮርጊስ ብርሃን በመልዕልተ ተቅዋም ዘተኀቱ፡፡
ሶበ ኪያከ ይጼዕሉ ወመጽሐፈከ ያሰትቱ፡፡
ነአምሮሙ ለአይሁድ በዝንቱ፡፡

ሰላም ለክሳድከ ሐብለ ሥላሴ አኒቆ፡፡
ይትቀሠፍ ድኅረ ሃይማኖተ ለአጠይቆ፡፡
ጊዮርጊስ ፍትው ለቤተክርስቲያን መሰንቆ፡፡
ለድምፀ በዐልከ እንዘ ይጸንሖ ተዐውቆ፡፡
እምዮሐንስ ባቲ ዘዘልፈ ናፍቆ፡፡

ሰላም ለአስናኒከ ከመ መራዕይ እለ ተቀርፃ፡፡
ወእለ እምሕጻብ ሐወፃ፡፡
ጊዮርጊስ መሰንቆ ለዝክርከ ቃለ ተግሣፃ፡፡
ጊዜ አንሶሰዉ በውስተ ኲሉ ወበጊዜ ተሰምዓ ድምፃ፡፡
ነገሥታተ ምድር ይሁብዋ ሞፃ፡፡

ሰላም ለመትከፍትከ እለ አንሐ ተወከፎ፡፡
አርዑተ ኢየሱስ ቀሊለ ለዓለም ዘየዐርፎ፡፡
ጊዮርጊስ ክሥት ለጥበብከ መጽሐፎ፡፡
ከመ ትሰብሐ ለማርያም ወከመ ለቢቱ ትዝለፎ፡፡
እስመ ዓይነ ኵሉ ዘሥጋ ኪያከ ይሴፎ፡፡

# መልክአ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ሰላም ለልሳንከ ልሳነ ጥበብ ወልባዌ፡፡
ማእከለ ከናፍር ወአፍ እንተ ረሰየ ህላዌ፡፡
ጊዮርጊስ መድኅን መትልወ ኢያሱ ዘነዌ፡፡
እስከ እትቤቀሎ ለፀርየ ወለእደወ ደምየ አርዌ፡፡
ዐቅም ሊተ ፀሐየ ሥጋዌ፡፡

ሰላም ለቃልከ ከመ ቀለመ ጸሓፊ ዘሐፈጣ፡፡
ኖኅያተ ወንጌል ሐዲስ ወነገረ ብሉይ የውጣ፡፡
ጊዮርጊስ ጴጥሮስ ወኤልሳዕ ዘትዝቤጣ፡፡
ለቃልከ ዕፍረተ ተድላ ዘእደ ኢየሱስ ፀዐጣ፡፡
ክበደ ሰማያት ወምድር ኢይከውን ሄጣ፡፡

ሰላም ለእስትንፋስከ ዘይነፍሕ ርጢነ፡፡
እመንፈስ ቅዱስ ነሢአ ሥልጣነ ፡፡
ጊዮርጊስ ቀርን እንተ ትሰብክ ግዕዛነ ፡፡
ቃለ ትግሣጽከ ያጠብብ አብዳነ፡፡
ወሕገ አፉከ ይሴብሕ ጻድቃነ፡፡

ሰላም ለአዕዳዊከ እለ ያጸንዓ መርኖ፡፡
አንቀጸ ማኅሌት ወሰብሖ፡፡
ጊዮርጊስ ጻሙ ዐስበ ከናፍርየ ለአጽንሖ፡፡
እመ ተከለ ኃረሣዊ በዐፀደ ወፍሩ ተጊሆ፡፡
የኃድግኑ ለበለስ ቀሞሖ፡፡

ሰላም እብል ለዘዚአከ ኩርናዕ፡፡
ስርግው በኅይል ወርሱይ በጽንዕ ፡፡
ጊዮርጊስ ገነት ገነተ ተድላ ወፍግዕ፡፡
በውሒዝከ ነፈርዓጽ ጥዒና እንስሳ ወሰብእ፡፡
ይትፌሥሑ ጥቀ መዐዝን ዘርብዕ፡፡

ሰላም ለዘባንከ እንተ ኪያሁ ለበጡ፡፡
ዐጽፈ ቅድስና በላዕሉ ወልበ ንጽሕና በውስጡ፡፡
ጊዮርጊስ ባሕርይ ዘዕፁብ ሤጡ፡፡
ለቁስለ ዚአየ እምርጢነ ፈውስከ መጡ፡፡
እስመ ዘባንየ ኃጥአን ዘበጡ፡፡

ሰላም ለእንግድዓከ ዘተዐጽፈ ብርሃናተ፡፡
በአብዝኖቱ ስብሐተ፡፡
ጊዮርጊስ ጸሐፊ ትእዛዝ ቃላተ
እንዘ ታስተፋጥን አእዳዊከ ክልኤተ፡፡
ፍቁረ ማርያም ድንግል ወብፁዕ አንተ

ሰላም ለሕፅንከ ዘረሰየቶ ምንባራ፡፡
ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ፡፡
ጊዮርጊስ ቅዱስ መሥዋዕተ ስብሐት ጽርስፎራ፡፡
በመዐዛከ ዘዘልፍ ወበጼናከ ለግሙራ፡፡
ትትፌሣሕ ጥቀ አግአዚት ደብተራ፡፡

ሰላም ለከርሥከ ዘብዕለ በርኅራኄ፡፡
ወተልዐለ በይዋሄ፡፡
ጊዮርጊስ ብርሃን የዐውደከ ሡራኄ፡፡
ሥነ ጸዳልከ ጸዳለ ኢየሱስ ኤሎሄ፡፡
ዓለመ ዓለማት መልአ ወነግሠ ኵለሄ፡፡

ሰላም ለልብከ ዘኢያብደረ የኀሊ፡፡
መንበርተ ዓለም ኀላፊ ወፍቶቶኒ ዘይበሊ፡፡
ጊዮርጊስ ሰንቃዊ በአርአያ ዳዊት አርከ በርዘሊ፡፡
በገጸ ድንግል ወበገጸ ወልዳ ከሃሊ፡፡
ምሕረተ ወፍትሐ ለውሉድከ ጸሊ፡፡

# መልክአ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ሰላም ለእመትከ ከመ ይመጥን ዘሰፍሐ፡፡
ለመቅደሰ ስብሐት ግድማ ወለቤተ ጸሎት ኑኃ፡፡
ጊዮርጊስ ዝክርከ ሶበ ናየድያሙ በፍሥሓ፡፡
ንፉቃነ ልብ እለ ኢየአምሩ ፍትሐ፡፡
ይፀንሱ ፃዕረ ወይወልዱ ላሐ፡፡

ሰላም ለእራኅከ እለ ስፉሐት ለውሂብ፡፡
ሐሊበ ልቡና ወእክለ ጥበብ፡፡
ጊዮርጊስ ነፋስ ሞጣሕተ ሞቅሕ ወላሕብ፡፡
ጊዜ ንፍሐትከ እምገጸ አዜብ ርሒብ፡፡
ተንሥአ ሰሜን ወመጽአ ደቡብ፡፡

ሰላም ለአፃብዒከ እንተ በዲቤሆን ሀለዋ፡፡
አጽፋረ ማኅቶት ዐሥር እለ የኅትዋ፡፡
ጊዮርጊስ ጻድቅ ለጥበብ ሥርዋ፡፡
ዘስብሐት ምህርካ ወዘማኅሌት ዜዋ፡፡
መልአከ ፍቅርከ ያስተጋብእ ነዋ ፡፡

ሰላም ለገቦከ ለሰኪብ ዘተደለወ፡፡
ዘቤተ መጻሕፍት ቅድወ፡፡
ጊዮርጊስ ወሬዛ እንተ አርታዕከ ፍናወ፡፡
ነቢብከ ነደ እሳት አመ በዓላውያን ተከዕወ፡፡
አፉሆሙ የብሰ ወልቦሙ በድወ፡፡

ሰላም ለአብራኪከ ለሰጊድ ዘያስተኤድማ፡፡
ለክብረ ፩ዱ አምላክ በአብዝኖ ሥራኅ ወጻማ፡፡
ጊዮርጊስ መምህር ወምሁረ ሕግ ፌማ፡፡
ወሰከኒ ዓመተ ተድላ እንተ ኢይትዌዳዕ ዐቅማ፡፡
እመ ለሕይወትየ በጽሐ ወቀርበ ተፍጻማ፡፡

ሰላም ለኵልያቲከ እንተ ቦ በኑባሬ፡፡
ሰሌዳ ሥጋ ቅድው ወመንጦላዕተ ደም ዘሰዋሬ፡፡
ጊዮርጊስ ካህን ምሉአ ጥበብ ወፍካሬ፡፡
ሶበ ትዘብጥ መሰንቆ ወታስተናሥዕ ዝማሬ፡፡
ያገብኡ ቃለ ደቂቀ ለቆሬ፡፡

ሰላም ለኅሊናከ አድያማተ ልብ ዘያዳ፡፡
ከመ የኀልያ ጽድቀ በእንተ ማርያም ወወልዳ፡፡
ጊዮርጊስ ጽሌ ወዘቃላተ ሕግ ሰሌዳ፡፡
ባርከነ ለውሉድከ ተውላጠ አምኃ ወጋዳ፡፡
በበረከቶሙ ለሌዊ ወይሁዳ፡፡

ሰላም ለኅንበርትከ ዲበ ሰሌዳ ከርሥ ግቡር፡፡
ንዋያተ ወስጥ ኩሉ እንተ በውስቴቶን ዕሡር፡፡
ጊዮርጊስ ቀርን ሰባኬ ሰላም ወፍቅር፡
ደመና ቃልከ ጸለለ ለደብር፡፡
ወጊሜ ሣህልከ ከደና ለባሕር፡፡

ሰላም ለሐቌከ በቅንዓተ ሃይማኖት ቅኑት፡፡
ዘማዕዘንቱ ጥበብ ወኪነ መቁጸሩ ሥርዓት፡፡
ጊዮርጊስ እግዚእ ዘምልክናከ ዕለት፡፡
እምሥርቀትከ ጥዒና ወሩጸትከ ሕይወት፡፡
ደመና ኅለፈ ወጉየ ጽልመት፡፡

ሰላም ለቆምከ ማየ መንፈስ ቅዱስ ዘአጥለሎ፡፡
ሠናይ ለርእይ ወአዳም ለአጽልሎ፡፡
ጊዮርጊስ ስምከ እምነ ልዑላን ተልዒሎ፡፡
በውስተ ሀገር ከመ እንተ ንጉሥ ሀሎ፡፡
እንዘ ሥልጣኑ ያስተራትዕ ኩሎ፡፡

## መልክአ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ሰላም ለአኢጋሪከ በእብነ ኃጢአት ዘኢትአቅፋ።
ፍኖተ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ የኀልፋ።
ጊዮርጊስ ጠቢብ ለቤተ ክርስቲያን ዘትኄድፋ።
እንበለ ሕጸጽ ሰበከ ከመ ጳውሎስ ወኬፋ።
አጽናፈ ዓለም ረሰይከ ተስፋ።

ሰላም ለሰኮናዊከ ዘአንሳህለለ መድረከ መኀልይ።
ወእለ ኢድኅፃ በፍኖተ ዓለም ጠዋይ።
ጊዮርጊስ እግዚእ ወመልአከ ሀገር ዐባይ።
ኢይኀጥኡ እምዘፈቀዱ እለ ሐፀኖሙ ማይ።
አንጠብጠበ መና ቃልከ ሰማይ።

ሰላም ለመከየድከ በፍኖተ መጻሕፍት ዘመረዳ።
አቅራበ ወከይሴ እንዘ ይከይዳ።
ጊዮርጊስ ባሕርይ ፍቁረ ማርያም ወወልዳ።
ማኅበረ ቀያፋ ወሱቱፋኒሁ ለይሁዳ።
ጽዕለተ ዚአከ ይትፈደዩ ፍዳ።

ሰላም ለአፃብዒከ ዘአኢጋሪከ ፪።
ጊዮርጊስ ዘኮንከ ለክርዱዳነ ልብ መስዔ።
መጽንዔ ምእመናን አንተ ወዘመናፍቃን ገፍታዔ።
መጽሐፈ ሕግከ ትምክሕተ ቅድስት ጉባኤ።
ለአርዮስ ወለቢቱ አጸወሙ ጉርዔ።

ሰላም ለመልክእከ ዘበበገጹ ወርእየቱ።
ዘበበሐሳቡ ወመሌሊቱ።
ጊዮርጊስ ኰኵሕ ለእግዚአብሔር መሠረተ ቤቱ ።
ዘኢተኃየሉ ሕንጻ ዚአከ ይንስቱ።
አናቅጸ ሲኦል አርዮስ ወቢቱ።

ሰላም ለፀአተ ነፍስከ እንዘ ይማስን ኀበ ኢማሰነ።
በትእዛዘ አምላክ ዘቦቱ ሥልጣነ።
ጊዮርጊስ ቃልከ ቀኖተ ዓለም ዘኮነ።
በጊዜ ደጐጸ እንበለ ያስተርኢ ዐይነ።
እስከ ያስተርኢ አማዑቱ አርዮስ ፈጸነ።

ሰላም እብል ለበድነ ሥጋነ ባሕርይ።
ማእከለ ሀገር ዘየሐቱ ከመ ሥነ ስቡሕ ፀሐይ።
ጊዮርጊስ ውዱስ የዐውደከ ዕበይ።
ለቤተ ሥጋከ ውስተ አድያሚሃ ጥዑይ።
አልቦ ሕመም ወአልቦ ድውይ።

ሰላም ለግንዘተ ሥጋከ በአፈወ ዕፍረት ዘምዕዘ።
ወልብሰ ገርዜን ብሩህ እንተ ይመስል አብያዘ።
ጊዮርጊስ ያም እንተ ፈረይከ ሐዋዘ።
ለማኅሌተ ስምከ እንተ ያረስእ ትካዘ።
ዘያስተሐቅር በመንኖ ይመስል እንቡዘ።

## መልክአ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ሰላም ለአጽፋረ እግርከ መልዕልተ አፃብዕ ዘአስራው፡፡ ይጸድላ ዘልፈ ከመ ማኅትው፡፡
ጊዮርጊስ ራእዩ ወሐዋርያ ፍንው፡፡
ይገንዩ ነገሥታተ ምድር በጸሎትከ ፍትው፡፡
እስመ ሐወዞሙ እምኲሉ አፈው፡፡

ሰላም ለመቃብሪከ ወለኲሎን አድያማ፡፡
ሰዋስወ ጸሎት ኑኃ ወምዕራገ ስብሐት ግድማ፡፡
ጊዮርጊስ ማኅፈድ ወዘኢትንህል ጥቅማ
እምኵሎን ካልኣቲሃ ሶበ አፈድፈደት ግርማ፡፡
ደብረ ባሕርይ ሰመይዋ ስማ፡፡

ሰላም ለፍልሰተ ሥጋከ እምድኅረ መዋዕል ጉንዱየ፡፡ ውስተ ሙላዱ ሰግላ እንተ ኪያሃ ኅረየ፡፡
ጊዮርጊስ አእምሮ እንተ ታብዕል ነዳየ፡፡
ሶበ ሰምዑ ደቂቅከ ቃለ ተናብቦ ሲሳየ፡፡
አንከሩ መንክራቲከ ወርእዩ ዐቢየ፡፡

ኦ ጊዮርጊስ ለእምነትየ ርድኦ፡፡
በከመ ዕበይከ አኮ ዘአብፃዕኩከ አብጽዖ፡፡
በብዝኃ ኂሩትከ አላ ተወከፈኒ እግዚኦ፡፡
እመ ተቀንየ ለሊቁ በአምጣነ ኃይሉ ጠቢኦ፡፡
መኑ ውእቱ ዘያቴክዝ ረድኦ ፡፡

## ሰላምታ

ዓምደ ኢትዮጵያ አንተ ከመ ለምድረ ግብጽ ዓምዳ፡፡
ናስምከ ብከ ለመርዓት ውሉዳ፡፡
ጊዮርጊስ ቢጸ ሲኖዳ፡፡

ሰላም ለከ ፍቅረ ማርያም ትኄይስ ለአሮን እሰርጉ፡፡
ሊቀ ካህናት ዐቢይ ለክርስቶስ ዘውጉ፣
ጊዮርጊስ መጋቤ ሕጉ፡፡

ሰላም ለከ ዕበያቲከ እዜኑ አፈ ወርቅ መምህር፡፡
ልስሐተ ልሳንየ ቅስም በጥዑም ነገር፡፡
ጊዮርጊስ አፈ ሶከር፡፡

ሰላም ለከ እንበለ ጽርዓት ወትረ ጊዜ ትሴብሕ ሥላሴ፡፡
ሱራፌልሃ ትመስል ወአኮ ብእሴ፡፡
ጊዮርጊስ ነቅዓ ቅዳሴ፡፡

ሰላም ለከ ኖላዌ ክርስቲያን አእላፍ፡፡
ወክበበ አርባዕቱ አጽናፍ፡፡
አርእስተ ረሲኣን ዘትመትር በቃለ መጽሐፍ፡፡
ጊዮርጊስ ልሳነ ሰይፍ፡፡

ሰላም ለከ በምህሮ ወንጌል ጊዮርጊስ ሐዋርያ፡፡
ምስለ ኢየሱስ ወእሙ ማርያም፡፡
ዘነበርከ በቢታንያ፡፡

## ሰላምታ

ሰላም ለከ ቀናዒ ኤልያስ ሐዲስ፡፡
ዘታነድዶሙ በእሳት ወባዕስ፡፡
ለአይሁድ ወለአርሲስ፡፡

አርጋኖነ ድንግል ሰሚዓ ወውዳሴ መስቀል ብርሃን፡፡
በፍሥሐ ትብለከ ቤተ ክርስቲያን እንዚራ ከናፍርየ ወይን፡፡
ጽጌ ሃይማኖት ትጽገይ በአፀደ ወይንከ ከርሣ፣
እንበለ ያማስንዋ በአበሳ፣
ቆናጽለ ታሥግር እም እንስሳ፣
ንቃህ ጊዮርጊስ ወጥሐር አንበሳ፡፡

ሰላም ለከ እንዘ ትነውም ጊዮርጊስ ዘደብረ ባሕርይ ትሔ፡፡
መጽሐፈ ምስጢር ይሰብከ ጥበብከ ስባሔ፡፡
ዘየዐውድ ውስተ ኲለሄ፡፡
ዘአፍቀረከ በልቡ ለማርያም አፍቀራ፣
ወዘጸልአከ በአማን ፀራ፣
ጊዮርጊስ መሰንቆ ለቤተ ክርስቲያን ክብራ፡፡
አፍቅረኒ አባ ወባርከኒ ባርኮ፣
እስመ ኲሉ ያፈቅር ለዘተዐረኮ፣
ወያደሉ ለዘተልእኮ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል
# ዘደብረ ጎል /ግሸ/

ታኅሣሥ ፳፻፬ ዓ.ም

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

በስመ እግዚአብሔር ዋሕድ ዘይሤለስ በተዋሕዶቱ፣ ወይትዋሐድ በትሥልስቱ፣ አኀዜ ዓለም በመንግሥቱ መላኤ ኲለሄ በመለኮቱ፣ አበ ኲሉ በኂሩቱ ርሑቀ መዓት በትዕግሥቱ መጽደቄ ኀጥአን በሥምረቱ መቅለሌ ዕጹብ በከሂሎቱ ጠቢበ ጠቢባን በተኬንዎቱ፣ ወአልቦ ዘይትቃወማ ለጽንዐ መዓቱ ዘእንበለ ኀይለ አድኀኖቱ አልቦ ዘያቈርራ ለእሳተ ቅንኣት ዘእንበለ ጠለ ሣህሉ ወምሕረቱ ዘይወርድ እመዝገበ ቤቱ፡፡

በሦስትነት አንድነት በአንድነት ሦስትነት ባለው በአንድ እግዚአብሔር ስም በመንግሥቱ ዓለምን የያዘ፣ በመለኮቱ ሁሉን የመላ፣ በቸርነቱ የሁሉ አባት የሆነ፣ በትዕግሥቱ ከቁጣ የራቀ፣ በፈቃዱ ኀጥአንን የሚያጸድቅ፣ በከሃሊነቱ ጭንቅ ነገርን የሚያቀል፣ በጥበቡ የጥበበኞች ጥበበኛ የሆነ፣ ከማዳኑ ኀይል በስተቀር የመዐቱን ጽናት የሚቃወማት የሌለ፤ ከርኅራኄ ቤቱ ከሚወርድ ከይቅርታውና ከምሕረቱ ጠል በስተቀር የቅንኣቱን እሳት የሚያቀዘቅዛት የለም፡፡

## ምዕራፍ ፩

፩ ንቀድም እንከ በረድኤተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለጽሒፈ ሥነ ምግባር ለአብ ክቡር በጸሎተ ሚካኤል ዘስርግው በኲሉ ገድል ወጻማ፡፡

፪ የዋህ ከመ አቤል ጻዋዒ ስመ አምላክ ከመ ሄኖስ መፍቀሬ እግዚአብሔር ከመ ሄኖክ ምሉአ ሞገስ ከመ ኖኅ ፍቁረ እግዚአብሔር ከመ አብርሃም ንጹሐ ምግባር ከመ ይስሐቅ ዐሥራተ እግዚአብሔር ከመ ያዕቆብ፡፡

## አንድ ምዕራፍ

፩ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አጋዥነት በገድልና በድካም ሁሉ የተሸለመ የክቡር አባት የበጸሎተ ሚካኤልን በጎ ሥራ ለመጻፍ እንጀምራለን፡፡

፪ እንደ አቤል የዋህ፣ እንደ ሄኖስም የአምላክን ስም የሚጠራ፣ እንደ ሄኖክም እግዚአብሔርን የሚወድ፣ እንደ ኖኅም ባለሟልነትን የተመላ፣ እንደ አብርሃምም የእግዚአብሔር ወዳጅ፣ እንደ ይስሐቅ በሥራው ንጹሕ እንደ ያዕቆብም የእግዚአብሔር ድርሻ ነው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፫ መጋቤ ሕግ ከመ ሙሴ ማኅሌታይ ከመ ዳዊት ልዑለ ቃል ከመ ኢሳይያስ ሠናየ ትንቢት ከመ ኤርያምስ ለሕገ አምላኩ ቀናኢ ከመ ኤልያስ ገባሬ መንክራት ከመ ኤልሳዕ፡፡

፫ እንደ ሙሴ የሕግ መምህር፣ እንደ ዳዊት ዘማሪ፣ እንደ ኢሳይያስ ቃሉ ከፍ ያለ፣ እንደ ኤርምያስ ትንቢቱ ያማረ፣ እንደ ኤልያስ ለአምላኩ ሕግ የሚቀና፣ እንደ ኤልሳዕ ተአምራትን የሚሠራ ነው፡፡

፬ ስኩረ መንፈስ ከመ ዕዝራ ሱቱኤል ራእዬ ኅቡኣት ከመ ሕዝቅኤል ለባሴ ጸማ ከመ ዮሐንስ መጥምቅ ኰኵሐ ሃይማኖት ከመ ጴጥሮስ ልሳነ ዕፍረት ከመ ጳውሎስ ንጹሕ ወድንግል ከመ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ፡፡

፬ እንደ ሱቱኤል ዕዝራ በመንፈስ የተቃኘ፣ እንደ ሕዝቅኤል የተሰወረውን የሚያይ፣ እንደ ዮሐንስ መጥምቅ ገድልን የለበሰ፣ እንደ ጴጥሮስ የሃይማኖት መሠረት፣ እንደ ጳውሎስ ነገሩ እንደ ሽቶ ደስ የሚያሰኝ እንደ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ ንጹሕና ድንግል ነው፡፡

፭ ዐምደ ሃይማኖት ከመ እስጢፋኖስ ኮከበ ክብር ከመ ጊዮርጊስ መፍቀሬ ጽሙና ከመ እንጦንዮስ ጥዑመ ልሳን ከመ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ነባቤ መለኮት ከመ ኤጲፋንዮስ መስተቃትል በሰይፈ ሥላሴ ከመ ቄርሎስ ጸዋሬ መከራ በእንተ ጽድቅ ከመ ዲዮስቆሮስ

፭ እንደ እስጢፋኖስ የሃይማኖት ዐምድ፣ እንደ ጊዮርጊስ የክብር ኮከብ፣ እንደ እንጦንዮስ ብሕትውናን የሚወድድ፣ እንደ ዮሐንስ አፈ ወርቅ አንደበቱ የተወደደ፣ እንደ ኤጲፋንዮስ የመለኮትን ምስጢር የሚናገር፣ እንደ ቄርሎስ፣ በሥላሴ ሰይፍ የሚጋደል፣ እንደ ዲዮስቆሮስ ስለ ጽድቅ መከራን የሚቀበል ነው፡፡

፮ ዕጉሥ በስደት ወጥቡዕ ለሙቃሔ ወቁሱል በቅሥፈታት ወጽዑል በዘንጓጊ፡፡

፮ በስደት የሚታገስ፣ በእስራት የበረታ፣ በግርፋትም የቆሰለ በስድብም የተነቀፈ ነው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፯ ወይጼሊ ዘእንበለ ጽርዐት ወይሴብሕ ዘእንበለ አርምሞ ይቀውም ከመ ዐምድ፣ ወይሰግድ ከመ መንኰራኵር ይተግሀ ከመ መላእክት ወይጸውም ከመ ዘአልቦቱ ሥጋ፡፡

፯ ያለማቋረጥ ይጸልያል፣ ዝምም ሳይል ያመሰግናል፣ እንደ ዐምድ ይቆማል፤ እንደ መንኰራኵር ይሰግዳል፣ እንደ መላእክት ይተጋል፤ ሥጋም እንደሌለው ይጾማል፡፡

፰ ይበውእ እንተ መጽብብ ወይጸዐቅ እንተ መቅዐን ወያጠውቃ ለሥጋሁ በገድል ወጻማ መፍርህ፡፡

፰ ወደ ጠባብና የማያስጨንቅ ገድል ይገባል፡፡ ሥጋውንም በገድልና በሚያስፈራ መከራ ያስጨንቃታል፡፡

፱ ዮም ትትሜካሕ ምድረ ሰግላ በእንተ ዘወለደት ኪያሁ ዮም ትትሬሣሕ ደብረ ሲዋ በእንተ ዘከለላ በትምህርተ ዚአሁ፡፡

፱ እርሱን ስለ ወለደች የሰግላ ምድር ዛሬ ትመካለች፡፡ በእርሱ ትምህርት ስለ አከበራት የሲዋ ደብርም ዛሬ ትደሰታለች፡፡

፲ ዮም ትትፌሣሕ ምድረ ትግራይ በእንተ ዘሐወጻ ቀዳሚ በንግደቱ ወደኃሪ በስደቱ ዮም ታንፈርዕጽ ምደረ ተንቤን በእንተ ዘተቀደሰት በአዕፅምቲሁ፡፡

፲ በመጀመሪያ በእንግድነቱ በኋላም በስደቱ ስለ ጐበኛት የትግራይ ምድር ዛሬ ትደሰታለች በአጥንቶቹ ስለ ቀደሳት የተንቤን ምድር ሐሤት ታደርጋለች፡፡

፲፩ አንሰ እብል መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ፣ አምላከ እስራኤል ውእቱ ይሁብ ኀይለ ወጽንዐ ለሕዝቡ፡፡ መዝ ፷፯፥፴፭

፲፩ እኔ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው የእስራኤል አምላክ ለሕዝቡ ኀይልንና ጽንዐትን ይሰጣል እላለሁ፡፡ መዝ ፷፯፥፴፭

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፪ ወካዕበ ይቤ መዝሙረ ዳዊት አንተ አትጽናዕኮሙ ለአድባር በኀይልከ ወቅኑታን እሙንቱ በኀይልከ አድባረ ይሰምዮሙ ለቅዱሳን ወእምዝ ይነግር ከመ በቀኒተ ኀይለ እግዚአብሔር ውእቱ ጽንዐ ገድሎሙ፡፡ መዝ ፷፯፥፯

፲፪ ዳግመኛም የዳዊት መዝሙር አንተ በኀይልህ ተራሮችን አጸናሃቸው፡፡ እነርሱም በኀይል ታጥቀዋል አለ፡፡ ቅዱሳንን ተራራዎች ይላቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የእግዚአበሔርን ኀይል በመታጠቅ ገድላቸው እንደ ጸና ይናገራል፡፡ መዝ ፷፯፥፯

፲፫ ወይእዜኒ ኢንበል እፎ ይክል ዘመጠነ ዝ ጸዊመ ወጸልዮ ዘመጠነዝ ሰጊደ ወዘመጠነዝ ትጋህ ወዓዲ ኢንበል እፎ ይገብር ዘከመዝ ተአምረ ወዘከመዝ መንክረ፡፡

፲፫ አሁንም ይህን ያህል መጾምና መጸለይ ይህን ያህል መስገድ ይህንም ያህል መትጋትን እንዴት ይችላል አንበል፡፡ ዳግመኛም እንደዚህ ያለ ተአምርና ድንቅ እንዴት ይሠራል አንበል፡፡

፲፬ ስማዕ ዘይቤላ ቅዱስ ገብርኤል ለማርያም ድንግል ናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ወትቤሎ ድንግል ለመልአክ እፎኑ ይከውነኒ እንዘ ኢየአምር ብእሴ ወይቤላ መልአክ መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወኀይለ ልዑል ይጼልለኪ፡፡ ሉቃ ፩፥፴፭

፲፬ ቅዱስ ገብርኤል ድንግል ማርያምን እነሆ ትፀንሻለሽ ልጅም ትወልጃለሽ ያላትን ስማ፤ ድንግልም መልአኩን ወንድ ሳላውቅ እንደምን ይሆንልኛል አለችው፡፡ መልአኩም መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል የልዑል ኀይልም ይጋርድሻል አላት፡፡ ሉቃ ፩፥፴፭

፲፭ እምከመሰከኬ ክህለት ድንግል ፀኒሰ ቃል በርደተ መንፈስ ቅዱስ ወወሊዶተ መለኮት በኀይለ ልዑል እፎኬ ንብል ኢይክሉ ቅዱሳን ጻማ ወገድለ በረድኤተ መንፈስ ቅዱስ ወገቢረ መንክራትሂ በኀይለ ልዑል፡፡

፲፭ ድንግል በመንፈስ ቅዱስ መውረድ አካላዊ ቃልን መፅነስ ከቻለችና በልዑል ኀይልም መለኮትን መውለድ ከቻለች ቅዱሳን በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ድካምንና ገድልን ከልዑል ኀይልም ተአምራት መሥራትን አይችሉም እንዴት እንላለን፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፮ እስመ የሐጽጽ ፈድፋደ ጸዊረ ጻማ ገድል እምፀኒሰ ቃል ወገቢረ መንክራት እምወሊደ መለኮት ወዝንቱሰ ብእሲ ረሰያ ለሥጋሁ ታቦተ ለመንፈስ ቅዱስ ወለመንፈሱኒ ሠረገላ ለጸሎት፡፡

፲፮ አካላዊ ቃልን ከመፅነስ የገድልን ድካም መሸከም፣ መለኮትንም ከመውለድ ተአምራትን መሥራት እጅግ ያንሳልና፡፡ ይህ ሰው ግን ሥጋውን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነፍሱንም የጸሎት ሠረገላ አደረጋት፡፡

፲፯ ይትሔረም በሥጋሁ እምርኩሰ ፍትወተ ዝንቱ ዓለም ይትሔረም በነፍሱ እምኀልዮ ዘበምድር ይትሔረም በእዴሁ እምገሢሠ ጽሉእ በኀበ እግዚአብሔር፡፡ ይትሔረም በእገሪሁ እምአንሶስዎ ረባሔ ኵሉ ንዋየ ዓለም ይትሔረም በአዕይንቲሁ፣ እምነጽሮ ከንቱ ዘይሔውዞ ለኀሊና ሥጋ፡፡

፲፯ በሥጋው ከዚህ ዓለም የርኵሰት ምኞት ይከለከላል፤ በነፍሱም ከምድራዊ አሳብ ይርቃል፤ በእጁም እግዚአብሔር የጠላውን ከመዳሠሥ ይለያል፡፡ በእግሩም በዓለም ገንዘብ ትርፍ ከመመላለስ በዐይን የሥጋን አሳብ ደስ የሚያሰኘውን ከንቱ ነገር ከማየት ይርቃል፡፡

፲፰ ይትሐረም በልሳኑ እምንባበ ጽሩዕ ዘኢይደሉ ለግብረ ቅዱሳን ይትሐረም በአፉሁ እምበሊዐ ሥጋ ወቅብዕ ወሐሊብ ዘይኤድሞ ለከርሥ ወእምሰሪበ ወይን ወሜስ ዘያስተፌሥሖ ለልብ ወያጠልሎ ለአዕፅምት፡፡

፲፰ በአንደበቱ ለቅዱሳን የማይገባ ከንቱ ነገር ከመናገር ይለያል፡፡ በአፉ ሆድን ደስ የሚያሰኘው ሥጋና ቅቤ ከመብላት ከወተትም ልብን ደስ ከሚያሰኘው አጥንትንም የሚያለመልም ወይንና ጠጅም ይከለከላል፡፡

፲፱ ሰቀላ ለሥጋሁ ምስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወአሞታ ለነፍሱ እምኀጢአት አሥረራ ለኀሊናሁ በአክናፈ መንፈስ ቅዱስ ወአንበራ ኀበ ኢየሩሳሌም ዘላዕሉ፡፡

፲፱ ሥጋውን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሰቀላት፤ ነፍሱንም ከኀጢአት ለያት፤ /ገደላት/ ኅሊናውን በመንፈስ ቅዱስ ክንፍ /ሥልጣን/ አበረራት በሰማያዊት ኢየሩሳሌምም አኖራት፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳ ወይእዜኒ ስምዑ እንግርክሙ ጥንተ ዜናሁ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ዘተሰርገወት ቅድስናሁ በገድለ ጻማሁ ወተከለለት ድንግልናሁ በቅድስናሁ ወትሕትናሁ ወተጽዕጠት ዕፍረተ ክህነቱ በደመ ስምዑ ዘይምዕዝ እምቅብዐ ጽጌ ቅድው፡፡

፳ አሁንም ቅድስናው በገድሉ ያጌጠች፣ ድንግልናውም በቅድስናውና በትሕትናው የከበረች የአባታችን የበጸሎተ ሚካኤልን የዜናውን ጥንት እነግራችሁ ዘንድ ስሙ፡፡ የክህነቱ ሽቶም ካማረ አበባ ሽቶ ይልቅ በምስክርነቱ ደም ጣፈጠች፡፡

፳፩ ለዝንቱ ብእሲ ስመ አቡሁ ማርቆስ እምዘመደ ካህናት ወስመ እሙ እግዚእ ክብራ ወይእቲኒ እምዘመደ ክቡራን ወወለዱ ውሉደ ወአዋልደ፡፡

፳፩ የዚህ ሰው አባት ስሙ ከካህናት ወገን የሚሆን ማርቆስ የሚባል ነው፡፡ የእናቱም ስም እግዚእ ክብራ ይባላል፡፡ እርሷም ከክቡራን ወገን ናት፤ እነርሱም ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለዱ፡፡

፳፪ ወእምድኅረዝ ሖረት እሙ ኀበ አዝማዲሃ ወከልእዎ ኪያሃ እንዘ ይብሉ ኢንሁበከ ለከ ኪያሃ አላ ናስተዋስባ ለአሐዱ እመኳንንት ወሖረ ማርቆስ ኀበ መነኮስ ዘይነብር ውስተ ደብር ዘቤተ ክርስቲያን ዘሚካኤል ሊቀ መላእክት ወነገሮ ዘከመ ከልእዎ ብእሲቶ

፳፪ ከዚህም በኋላ እናቱ ወደ ዘመዶቿ ሔደች ከመኳንንት ለአንዱ እናጋባታለን እንጂ ለአንተ አንሰጥህም እያሉ እርሷን ከለከሏት ማርቆስም በመላእክት አለቃ በሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ወደሚኖር መነኩሴ ሔዶ ሚስቱን እንደ ከለከሉት ነገረው፡፡

፳፫ ወጸውዖሙ ውእቱ መነኮስ ለአዝማዲሃ ወይቤሎሙ ይደልወክሙኑ ትክልእዎ ብእሲቶ ለካህነ እግዚአብሔር ወገሠጾሙ በቃለ ተግሣጽኒ ወበቃለ መጻሕፍት ወበዝኒ ስእነ ዐሪቆቶሙ፡፡

፳፫ ያም መነኩሴ ጠርቶ የእግዚአብሔርን ካህን ሚስት ትከለክሉ ዘንድ ይገባችኋል አላቸው፡፡ በምክርና በመጻሕፍትም ቃል ገሠጻቸው በዚህም ማስታረቅ ተሳነው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፷፬ ወተመይጠ ማርቆስ ካዕበ በሣልስ ወአጽሐቦ ለውእቱ መነኮስ በእንተ ብእሲቱ ወእንዘ ይትዋቀስ ምስለ አዝማዲሃ ሶበ አብዝኁ አዝማዲሃ ተሰናነ ይቤሎሙ እትዉ ለለማኅደሪክሙ ኅድግዎ ለክልኤሙ ይቢቱ ኅቤየ ወአተዉ ለለማኅደሪሆሙ፡፡

፷፬ ማርቆስም ዳግመኛ ለሦስተኛ ጊዜ ተመልሶ ስለ ሚስቱ ያን መነኩሴ አስቸገረው፡፡ ከዘመዶቿም ጋር እየተከራከረ ሳለ ዘመዶቿ ጥላቻን ባበዙ ጊዜ እናንተ እየማደሪያችሁ ሒዱ ሁለቱን ከእኔ ያድሩ ዘንድ ተዋቸው አላቸው፡፡ እየ ማደሪያቸው ሔዱ፡፡

፷፭ ወተርፉ ማርቆስ ወብእሲቱ ኅበ ውእቱ መነኮስ ወይቤሎሙ ለማርቆስ ወለብእሲቱ ውእቱ መነኮስ ቢቱ ዮም ውስተ ማኅደርየ አምሕለክሙ በጸሎቱ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ኢታጽርዑ ትድምርተ ሥጋ በዛቲ ሌሊት፡፡

፷፭ ማርቆስና ሚስቱም ከዚያ መነኩሴ ዘንድ ቀሩ፤ ያም መነኩሴ ማርቆስንና ሚስቱን በማደሪያዬ እደሩ በዚህችም ሌሊት ሩካቤ ሥጋ ሳትፈጽሙ እንዳትቀሩ በመላእክት አለቃ በሚካኤል ጸሎት አምላችኋላሁ አላቸው፡፡

፷፮ ወቤቱ ውስተ ማኅደሩ በከመ አዘዞሙ ወአስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር በሕልም ለማርቆስ ወይቤሎ እግዚእ ክብራ ብእሲትከ ትወልድ ለከ ወልደ ወወሊዳ ትሰምዮ ስሞ በጸሎተ ሚካኤል ወይከውን ዐምደ ለቤተ ክርስቲያን፡፡

፷፮ እንዳዘዛቸውም በቤቱ አደሩ የእግዚአብሔርም መልአክ ለማርቆስ በሕልም ተገለጸለት ሚስትህ እግዚእ ክብራ ወንድ ልጅ ትወልዳለች፡፡ በወለደችም ጊዜ ስሙን በጸሎተ ሚካኤል ትለዋለች ለቤተ ክርስቲያንም ዐምድ ይሆናል አለው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳፪ | ወነቂሆ እምንዋሙ ማርቆስ ተደመረ ምስለ ብእሲቱ ወበዝየ ፀንሰቶ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል በረሀ ገጻ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ወኮነት እንከ ትትፌሣሕ በልባ ከመ ዘሰትየ ወይነ ከራሜ ወለሊሃኒ ትቤ ምንትኑ ውእቱ ዘሀሎ ውስተ ከርሥየ እም አመ ፀነሰክዎ ይበርህ ጎሊናየ ወገጽየ ከመ ማኅቶት፡፡ | ፳፪ | ማርቆስም ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ ከሚስቱ ጋር ተገናኘ፡፡ በዚያም አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ፀነሰችው በፀነሰችውም ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ፊቷ በራ፡፡ የከረመ ጠጅም እንደ ጠጣ በልቧ ትደሰት ነበር፡፡ እርሷም በሆዴ ውስጥ ያለው ምንድን ነው? ከፀነስኩት ጀምሮ ልቤና ፊቴ እንደ መብራት ያበራል አለች፡፡ |
| ፳፫ | ወእምከመ ደወዩ ደቂቃ ዘይልህቁ ወይብሉ ሐመምነ ርእሰነ አው ከርሥነ ትእኅዝ ፅንሰ ከርሣ በእደዊሃ ወትገሥሦሙ ለደቂቃ ኅበ ዘይደውዩ መካነ ሥጋሆሙ ወይትፌወሱ ሶቤሃ በጸጋ እግዚአበሔር | ፳፫ | ያደጉት ልጆቿ ራሳችን ወይም ሆዳችን እያሉ ታመምን ካሉ በእጇዋ የሆዷን ፅንስ ይዛ የልጆቿን የታመመ አካላቸውን ትዳስሳቸዋለች ያን ጊዜ በእግዚአብሔር ቸርነት ይፈወሱ ነበር፡፡ |
| ፳፬ | ወበጽሐ ዕለተ ወሊዶታ አስተርአየ ቀስተ ደመና በውስተ ቤታ በጊዜ ሰዓት እንተ ባቲ ወለደቶ ለሕፃን ወሰመየቶ ስሞ በጸሎተ ሚካኤል በምኔተ ሚካኤል ፀንሰቶ በከመ ትቤ ቀዳሚ፡፡ | ፳፬ | የመውለጃዋ ቀን በደረሰ ጊዜ ሕፃኑን በወለደችበት ሰዓት በቤቷ ውስጥ ቀስተ ደመና ታየ አስቀድሞ እንደ ተናገረ በሚካኤል ገዳም ፀንሳዋለችና ስሙንም በጸሎተ ሚካኤል አለችው፡፡ |
| ፴ | ወእምዝ ሐፀነቶ እስከ አኀደገቶ ጥባ ወሶበ ልህቀ ንስቲተ ወይቤሎ አቡሁ በል በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወይቤ ሕፃን በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ | ፴ | ከዚህም በኋላ ጡቷን እስኪተው ድረስ አሳደገችው፤ ትንሽም ባደገ ጊዜ አባቱ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ በል አለው፡፡ ሕፃኑም በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አለ፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፩ ወይቤሎ ካዕበ በል ብፁዕ ብእሲ ዘኢሖረ በምክረ ረሲአን ወአንበበ ሕፃን ዘንተ መዝሙረ እስከ ተፍጻሜቱ ወአንከረ አቡሁ በእንተ ዘአንበበ ዘኢተምህረ ለለጥንተ መዝሙር እስከ ይነግሮ አቡሁ አሐደ ቃለ ወይፌጽም ሕፃን አንብቦ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡፡

፴፩ ዳግመኛም በዝንጉዎች ምክር ያልሔደ ምስጉን ነው በል አለው፤ ሕፃኑም ይህን መዝሙር እስከ መጨረሻው አነበበ፣ አባቱም ያልተማረውን ስለ አነበበ አደነቀ፤ አባቱ የመዝሙሩን መጀመሪያ አንዱን ቃል እስኪነግረው ድረስ ሕፃኑ በመንፈሰ ጸጋ አንብቦ ይፈጽመው ነበር፡፡

፴፪ ወእምዝ ፈጸመ እምጥንተ መዝሙር እስከ ተፍጻሜቱ ወማኅሌተ ሙሴ ገብረ እግዚአብሔር እስከ ጸሎተ ስምዖን ካህን ወነቢይ ወሶበ ፈጸመ መዝሙረ ዳዊት መሀሮ አቡሁ ዮኅያተ ወእምዝ መጽሐፈ መልእክተ ሐዋርያት፡፡

፴፪ ከዚያም ከመዝሙር መጀመሪያ ጀምሮ እስከ መጨረሻ፤ የእግዚአብሔር አገልጋይ የሙሴን ምስጋና እስከ ካህኑና ነቢዩ ስምዖን ጸሎት ድረስ ፈጸመ፡፡ የዳዊትንም መዝሙር በፈጸመ ጊዜ አባቱ ፊደልን አስተማረው፤ ከዚያም የሐዋርያትን መልእክት አስተማረው፡፡

፴፫ ወለለ ጽባሑ ይትዌሰኮ ቃለ እግዚአብሔር ውስተ አፉሁ ወትርጓሜሁኒ ውስተ ልቡ አዳም ምገሰ ቃሉ ወቅሱም በጼወ መለኮት ንባበ ልሳኑ፡፡

፴፫ በየዕለቱም የእግዚአብሔር ቃል በአፉ ትርጓሜውም በልቡ ውስጥ ይጨመርለት ነበር፡፡ ቃሉ ያማረ የአንደበቱም ንባብ በመለኮት ጨው የጣፈጠ ነው፡፡

፴፬ ወእምዝ ይቤላ አቡሁ፣ ለእሙ ንሰዶ ኀበ ጳጳስ ከመ ይንሣእ ዲቁና ወትቤሎ እሙ ይመውተነ በረኀብ ወኢይክል ጸዊመ፡፡

፴፬ ከዚህ በኋላ አባቱ እናቱን ዲቁና ይቀበል ዘንድ ወደ ጳጳስ እንውሰደው አላት፤ እናቱም በረኀብ ይሞትብናል ጾምም አይችል አለችው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፻፯ ወሶበ ሰምዐ ሕፃን ዘተማከሩ አኀዘ ይጹም ዐርበ ወረቡዐ ወአበየ በሊዐ ወዘበጦ አቡሁ ወአሕመሞ ወበዝኒ ስእነ ኦሆ አብሎቶ ወሶበ አበዮ ነሥአ መብልዐ ወወደየ ውስተ አፉሁ ለሕፃን ወይቤሎ አቡሁ ናሁ ሰአርከ ጾመከ፡፡

፻፯ ሕፃኑም የተማከሩትን በሰማ ጊዜ ዓርብና ረቡዕን ይጾም ጀመር፡፡ መብላትንም አይሆንም አለ፤ አባቱም ገረፈው አሳመመውም በዚህም እሺ ማሰኘት ተሳነው፤ አይሆንም ባለውም ጊዜ ምግቡን ይዞ በሕፃኑ አፍ ጨመረው አባቱም እነሆ ጾምህን ሻርህ አለው፡፡

፻፰ ወይቤ ሕፃን ወሶበሁ ወደይኩ በፈቃድየ ውስተ አፉየ እምሰአርክዎ ለጾምየ ወእመሰ አንተ ወደይከ ውስተ አፉየ ኢሰአርኩ ወይእዜኒ ኢይሰአር ጾምየ ወሶበ አድከሞ ኀደጎ አቡሁ ከመ ይጹም፡፡

፻፰ ሕፃኑንም እኔ በፈቃዴ በአፌ ውስጥ ብጨምረው ጾሜን በሻርኹት ነበር አንተ በአፌ ውስጥ ከጨመርኸው ግን ጾሜ አይሻርም አለ አባቱም ባደከመው ጊዜ ይጾም ዘንድ ተወው፡፡

፻፱ አንከርዎ ለዝ ሕፃን ዘሐጸያ በጾም ለክህነት ወአሰርገዋ በንጽሐ ሥጋሁ ለማኅደረ መለኮት አንከርዎ ለዝ ሕፃን እምከርሠ እሙ ቅዱስ ከመ ኤርምያስ ወከመ ዮሐንስ ወከመ ሳሙኤል ዘተሐፅነ ውስተ ቤተ መቅደስ አንከርዎ ለዝ ሕፃን ዘአብጠለ ሐገ ደቂቅ በልቡናሁ ዘጸንዐ እም አፅሩግ በጽሙናሁ፡፡

፻፱ በጾም ክህነትን ያጫት የመለኮት ማደሪያ ሥጋውንም በንጽሕና ያስጌጣት ይህን ሕፃን አድንቁት፡፡ እንደ ኤርምያስ፣ እንደ ዮሐንስና በቤተ መቅደስ እንዳደገ እንደ ሳሙኤልም ከእናቱ ማሕፀን የተለየ ይህን ሕፃን አድንቁት፤ የልጆችን ሕግ በልቡናው ያስቀረ ከታላላቆቹም በብሕትውናው የጸና ይህን ሕፃን አድንቁት፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፰ ወአንክርዎ ለዝ ሕፃን ዘምስለ ጎበ እሙ ሐፀነቶ ጥበበ እግዚአብሔር ወዘ እምንእሱ አልሀቀቶ ቃለ መጽሐፍት አንክርዎ ለዝ ሕፃን እምነ አቡሁ ዘአፍቀሮ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወእምነ እሙ ዘአፍቀራ ለቤተ ክርስቲያን፡፡
ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

፴፰ ከእናቱ ጡት ጋር የእግዚአበሔር ጥበብ ያሳደገችው ከታናሽነቱም ጀምሮ የመጻሕፍት ቃል ያሳደገችው ይህን ሕፃን አድንቁት ከአባቱ ይልቅ ኢየሱስ ክርስቶስን የወደደው ከእናቱም ቤተ ክርስቲያንን የወደዳት ይህን ሕፃን አድንቁት፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይኑር አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፪

፩ ንግባእኬ ጎበ ጥንተ ነገር ከመ ንንግርክሙ ዜናሁ ለአቡነ ለባሴ መንፈስ ቅዱስ ወእምዝ ወሰደ አቡሁ ጎበ ጳጳስ ወኮነ ዲያቆነ ወተመይጠ ውስተ ሀገሩ ምስለ አቡሁ፡፡

፪ ወመልአ ፍቅረ እግዚአብሔር ውስተ ልቡ አሰራ ለሥጋሁ በሐብለ ወንጌሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወቀነዋ በቅንዋተ ፍቅር ከመ ኢያንቀልቅል እምኔሁ ኢለየማን ወኢለጸጋም፡፡

## ሁለት ምዕራፍ

፩ መንፈስ ቅዱስን የለበሰ የአባታችን ዜና እንነግራችሁ ዘንድ ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስ ከዚህ በኋላ አባቱ ወደ ጳጳስ ወሰደው ዲያቆን ሆነ (ዲቁና ተሾመ) ከአባቱም ጋር ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

፪ የእግዚአብሔር ፍቅር በልቡናው መላ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል ገመድ ሥጋውን አሰራት ከእርሱም ወደ ቀኝም ወደ ግራም እንዳይናወጥ በፍቅሩ ችንካር ቸነከራት፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፫ ወአርሰና ለኅሊናሁ፣ በእሳተ ቅንአቱ ወኢያቀኍረራ እስከ አመ ነደት ፍጡነ ወተፈጸመ ላዕሌሁ ቃለ እግዚአብሔር ዘይቤ በወንጌል "እሳተ አምጻእኩ ለብሔር ወምንተ እፈቅድ ዘእንበለ አንድዶታ ቃለ እግዚአብሔር ንጹሕ ቃለ እግዚአብሔር ርሱን፡፡ ሉቃ ፲፪፥፵፱

፫ በመንፈሳዊ የእሳት ቅንኣትም ኅሊናውን አቃጠላት፡፡ ፈጽማ እስክትነድ ድረስም አላቀዘቀዛትም በወንጌልም "ለሀገር እሳትን አመጣሁ እስዋን ከማንደድ በቀር ምን እሻለሁ ያለው የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ ላይ ተፈጸመ የእግዚአብሔር ቃል ንጹሕ ነው የእግዚአብሐርም ቃል የሚያቃጥል ነው፡፡ ሉቃ ፲፪፥፵፱

፬ ወሶበ ይበውእ ውስተ ልበ ቅዱሳን ያረስኖሙ ለኅሊናሆሙ እምውስተ ምንሃብ ብዙኅ ምብኳሕ ወበእንተዝ ይቤ በመዝሙር ቃለ እግዚአብሔር ርሱን ወምእመኖሙ ውእቱ ለኵሎሙ ለእለ ተወከሉ ቦቱ፡፡

፬ በቅዱሳንም ልብ በገባ ጊዜ በወናፍ ውስጥ እንደገባ እሳት ኅሊናቸውን ያግለዋል፣ ስለዚህም በመዝሙር የእግዚአብሔር ቃል የጋለ ነው፤ ተስፋ ላደረጉትም መታመኛቸው ነው አለ፡፡

፭ ወካዕበ ይቤ ርሱን ቃልከ ፈድፋደ ወገብርከሰ አፍቀሮ እስመ አኮ በኀበ ኵሉ ዘይሬስያ ቃለ እግዚአብሔር ወእምከመሰ ቦአ ውስተ ልበ ረሲእ ይቈርር በከመ ይቤሎ ያዕቆብ ለሮቤል ወልድየ ቈረርከ ከመ ማይ እስመ ዐረገ ዲበ ምስካበ አቡከ፡፡ ዘፍ ፵፱፥፬

፭ ዳግመኛም ቃልህ ፈጽሞ የጋለ ነው፤ ባሪያህም ወደደው የእግዚአበሔር ቃልም በሁሉ ዘንድ እንዲህ የምትሆን አይደለም በዝንጉ ሰው ልብ ከገባ ያዕቆብ ልጁ ሮቤልን ልጄ እንደ ውኃ ቀዘቀዝህ ወደ አባትህ አልጋ ወጥተሃልና እንዳለው ይቀዘቅዛል፡፡ ዘፍ ፵፱፥፬

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፺፮ እስመ ንዴት በፍትወተ ሥጋ ቍረት በኀበ እግዚአብሔር ወቍረት በኀበ ሰብእ ንዴት በኀበ እግዚአብሐር እስመ ዘይትፈቀድ በዝየ ኢይትፈቀድ በህየ ዘይትመነን በኀበ ሰብእ ይከብር በኀበ እግዚአብሔር ልዑል።

፺፮ በሥጋ ምኞት መቃጠል በእግዚአብሔር ዘንድ መቀዝቀዝ ነውና፤ በሰውም ዘንድ መቀዝቀዝ በእግዚአበሔር ዘንድ መቃጠል ነው። በዚህ የሚወደድ በዚያ አይወደድምና በሰው ዘንድ የሚናቅ በልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ይከብራል።

፺፯ ወዘይትነፋኀ በትዕቢት ወየኀሥር በጉባኤ መላእክት ወሰብእ ዘይለብስ ሲራያተ ወዘይትሜካሕ ዲበ ዘይለብስ አጽርቅተ ይከውን ዕሩቀ ዘበሰማያት።

፺፯ በትዕቢት የተወጠረ በመላእክትና በምእመናን ጉባኤ ይዋረዳል፤ ግምጃን ለብሶ ጨርቅ በለበሰው የሚመካ በሰማያት የተራቆተ ይሆናል።

፺፰ ወዘይትቀባዕ መዓዛ አፈው ለአሰሕቶ ውስተ ሞት ጽዩዕ በኀበ አምላከ ንጹሓት ነፍሳት በከመ ይቤ ጳውሎስ ልሳነ ዕፍረት እስመ ቦ እለ ይደልዎሙ መዓዛ ሞት ለሞት ወእለ ይደልዎሙ መዓዛ ሕይወት ለሕይወት። ፪ቆሮ ፪፥፲፮

፺፰ ሰውን ለማሳት ሽቱ የሚቀባ በንጹሓት ነፍሳት አምላክ ዘንድ በሞት ፍዳ ተይዞ ይከረፋል። የሞት መዓዛ የሚገባቸው ለሞት ናቸውና የሕይወት መዓዛ የሚገባቸውም ለሕይወት ናቸውና። ፪ቆሮ ፪፥፲፮

፺፱ ወዝንቱሰ ብእሲ ጸገየ ጽጌ መዓዛ ዘዘዚአሁ ኀብሩ ወዘዘዚአሁ ጽጌ ደንጐላት ንጹሕ ዘአልቦ ርስሐት ዘበርደተ መንፈስ ቅዱስ ወአጽደልደለ ወጽጌ ተከህኖ ቅድመ ዘበመዓዛ ዕፍረቱ ለክርስቶስ ተቀስመ ጽጌ ስብከት ዘነቢያት ብሩህ ሠረጸ ዘበሐዋርያት ጼነወ።

፺፱ ይህ ሰው ግን በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ርኵሰት የሌለበት ኅብሩ ልዩ ልዩ የሆነና እንደ ሱፍ አበባም መዓዛው ልዩ ልዩ የሆነ መዓዛን አፈራ አስቀድሞ በክርስቶስ የሽቱ መዓዛ የጣፈጠ ክህነት አበባው አበራ፤ በነቢያት የስብከት አበባ ጣፈጠ፤ በሐዋርያት የነበረ ትምህርቱም የሚያበራ ሆኖ ወጣ።

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲ ዘበወንጌለ ጸጋ ተምዕዘ ወጽጌ ስምዕ ቀይሐ ዘበደመ ቅሥፈቱ ተቀልመ ወይትሜካሕ በደመ ሕማሙ ለክርስቶስ በከመ ይቤ ጳውሎስ ወእፌጽም ተሕጻጸ ሕማሙ ለክርስቶስ፡፡ ቈላ ፩፥፳፬

፲ በወንጌል ጸጋ ጣፈጠ፤ በግርፋቱ ደምም ቀይ የሆነ የምስክርነቱ አበባ ታለለ፡፡ /ተጻፈ/ ጳውሎስ የክርስቶስን የመከራውን ቅሬታ በሥጋዬ እፈጽማለሁ እንዳለ ክርስቶስ መከራ በተቀበለ ጊዜ በፈሰሰው ደም ይመካል፡፡ ቈላ ፩፥፳፬

፲፩ ወካዕበ ይቤ ጳውሎስ እምከመ ተሳተፍናሁ ለመርዓዊ በሞቱ ንትሜሰሎ በሕይወቱሂ እምከመ ዐረይነ መዊተ ንዔሪ ሕይወተ ወእምከመ ዐረይነ ትዕግሥተ ንዔሪ ነጊሠ ወጴጥሮስኒ ይቤ ወእመሰ ክርስቶስ ተሰቅለ በሥጋሁ በእንቲአነ ወአንትሙኒ ተወልተዉ በይእቲ ኀሊና እስመ ዘሐመ በሥጋሁ ድኅነ እምኀጣውኡ
፪ጢሞ ፪፥፲፩ ፤ ፩ጴጥ ፬፥፩

፲፩ ዳግመኛም ጳውሎስ መርዓዊን በሞቱ ከመሰልነው በሕይወቱም እንመስለዋለን በሞት ከተካከልን በሕይወትም እንተካከላለን በትዕግሥትም ከተካከልን በመንግሥ እንተካከላለን አለ፡፡ ጴጥሮስም ክርስቶስ ስለ እኛ በሥጋው ከተሰቀለ እናንተም ይህችን አሳብ ጋሻ አድርጋችሁ ኑሩ፡፡ በሥጋው መከራ የተቀበለ ከኀጢአቱ ድኖአል አለ ፪ጢሞ ፪፥፲፩ ፤ ፩ጴጥ ፬፥፩

፲፪ ወዝንቱሰ አብ ክቡር ወንጹሕ ስርግው በኵሉ ምግባረ ሠናይ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ዘቀደመ ከዊነ ስምዕ በእደ አቡሁ ማርቆስ ወሶበ ኀለየ አቡሁ ከመ የሀቦ ብእሲተ አእመረ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወሐረ ኀበ ምኔተ መነኮሳት፡፡

፲፪ ይህ የከበረ፣ ንጹሕ የሆነና በአባቱ በማርቆስም እጅ ምስክርነቱን ያስቀደመ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል በበጎ ሥራ ሁሉ የተሸለመ ነው፡፡ አባቱም ሚስት ያጋባው ዘንድ ባሰበ ጊዜ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ዐውቆ ወደ መነኮሳት ገዳም ሔደ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፫ ወሶበ በጽሐ ይቤሎሙ ለመነኮሳት አብኡኒ ኀበ ምኔት ወይቤሎ አበምኔት ምንተኑ ትፈቅድ አ ወልድየ ወይቤ በጸሎተ ሚካኤል እፈቅድ እኩን መነኮሰ ወይቤሎ አበምኔት ኢትክል አ ወልድየ ከዊነ መነኮስ እስመ ሕፃን አንተ ወባሕቱ ንበር ዝየ ኀቤየ ወአመክር ርእሰከ፡፡

፲፫ በደረሰም ጊዜ መነኮሳቱን ወደ ገዳሙ አስገቡኝ አላቸው፡፡ የገዳሙም ሓላፊ ልጄ ሆይ ምን ትሻለህ አለው፡፡ በጸሎተ ሚካኤልም መነኩሴ መሆን እፈልጋለሁ አለ፡፡ የገዳሙም ሓላፊ/አበምኔት/ ልጄ ሆይ ሕፃን ነህና መነኩሴ መሆን አትችልም ነገር ግን ከእኔ ዘንድ ተቀመጥ ራስህንም ፈትን አለው፡፡

፲፬ ወእምድኀረዝ ሰምዐ አቡሁ ኀበ ሀሎ ምኔት ወሖረ ኀበ ውእቱ መነኮስ ወይቤሎ ሀበኒ ወልድየ ወይቤሎ አበምኔት አንሰ ኢይሁበከ ኪያሁ አላ ለሊከ በቃልከ ተናገሮ ወይቤሎ ማርቆስ ለወልዱ ነዐ ንሑር ኀበ እምከ ወአኀዊከ፡፡

፲፬ ከዚህም በኋላ አባቱ ገዳም እንዳለ ሰምቶ ወደዚያ መነኩሴ ሔዶ ልጄን ስጠኝ አለው፤ አበምኔቱም እኔ እርሱን አልሰጥህም እራስህ በቃልህ ተናገረው አለው፡፡ ማርቆስም ልጁን ወደ እናትህና ወደ ወንድሞችህ እንሒድ አለው፡፡

፲፭ ወይቤሎ ወልዱ አንሰ ኢየሐውር እምዝየ አላ እከውን መነኮሰ ወሖረ ማርቆስ ኀበ እግዚእ ክብራ ወነገራ ኵሎ ዘከመ ይቤሎ ወልዱ ወሐዘኑ ክልሆሙ ዐቢየ ሐዘነ በእንተ ወልዶሙ፡፡

፲፭ ልጁም እኔ ከዚህ አልሔድም መነኩሴ እሆናለሁ እንጂ አለው፡፡ ማርቆስም ወደ እግዚእ ክብራ ሔዶ ልጁ እንደ ነገረው ሀሉን ነገራት ሁለቱም ስለ ልጃቸው ታላቅ ኀዘን አዘኑ፡፡

፲፮ ወሖረት እግዚእ ክብራ ኀበ ውድም ረአድ ንጉሥ እስመ ዘመዳ ውእቱ በሥጋ ወነገረቶ በእንተ ወልዳ ወደመረ ላቲ አሐደ እምሐራሁ ዘይጸውር ጥብጣቤ ወሖረ ወበጽሐ ሐራ ንጉሥ ኀበ አበምኔት ወነሥኦ ለሕፃን እምኔሁ ወሀባ ለእግዚእ ክብራ፡፡

፲፮ እግዚእ ክብራም በሥጋ ዘመዷ ስለሆነ ወደ ውድም ረአድ ንጉሥ ሒዳ ስለ ልጇ ነገረችው፡፡ እርሱም ከወታደሮቹ አንዱን አለንጋ ይዞ እንዲሔድ ጨመረላት፤ የንጉሡም ወታደር ከአበምኔቱ (የገዳሙ ሓላፊ) ወስዶ ለእግዚእ ክብራ ሰጣት፡፡

፲፯ ወይቤላ ለእመ ወፅአ እምኔኪ ዝ ሕፃን ጸውዕኒ ወአነ እዘብጦ በዝንቱ ጥብጣቤ ወነበረ ሕፃን ኀበ አቡሁ ወእሙ ወይትኤዘዝ ሎሙ ወይትለአኮሙ

፲፯ ይህ ሕፃን ከአንቺ ከወጣ ጥሪኝ፤ እኔ በዚህ አለንጋ እገርፈዋለሁ አላት፤ ሕፃኑም ከአባቱና ከእናቱ ዘንድ ተቀመጠ ይታዘዝና ያገለግላቸውም ነበር፡፡

፲፰ ወበአሐቲ ዕለት ለአኮ አቡሁ ኀበ ካልእ መካን ወእንዘ ይትመየጥ እምኅበ ዘለአኮ ረከበ በፍኖት ኖሎተ አብቅልት ዘንጉሥ በውስተ ፂያት፡፡

፲፰ አንድ ቀንም አባቱ ወደ ሌላ ቦታ ላከው ከላከውም ቦታ ሲመለስ በመሰማሪያ የንጉሥን በቅሎዎች የሚጠብቁ እረኞች አገኘ፡፡

፲፱ ወእንዘ የኀልፍ ተሠግረ ገመደ በቅለ ንጉሥ ወአኀዝዎ ወወሰድዎ ኀበ ሊቆሙ ወርእየ ሊቆሙ ፊቃረ ዘውስተ ከሳዱ ለሕፃን ይቤሎሙ ኅድግዎ እስመ ውእቱ ካህን ወኢትዝብጥዎ ወእምዝ ኅደግዎ፡፡

፲፱ የንጉሡንም የበቅሎ ገመድ ተራምዶ ሲሔድ ይዘው ወደ አለቃቸው ወሰዱት፡፡ አለቃቸውም በአንገቱ ያለ ቀሚሱን አይቶ ካህን ነውና ተውት አትምቱት አላቸው ከዚያም ተውት፡፡

፳ ወኀለየ ሕፃን በልቡ እንዘ ይብል መዋትያን አግብርተ ንጉሥ መዋቲ በእንተ ገመደ በቅል ዘተዐደውኩ ዘመጠነዝ ድንጋፄ አደንገፁኒ እፎ እንከ ያደነግፁኒ መላእክተ እሳት ዘመፍርህ ግርማሆሙ በእንተ ዘተዐደውኩ ትእዛዞ ለንጉሠ ስብሐት፡፡

፳ ሕፃኑም በልቡ ሟቾች የሆኑ የሟች ንጉሥ አገልጋዮች ስለ አለፍሁት የበቅሎ ገመድ ይህን ያህል ድንጋፄ ካስደነገጡኝ ግርማቸው የሚያስፈራ የእሳት መላእክት የክብር ንጉሥ ትእዛዝን ስለተላለፍሁ እንዴት /ምንኛ/ ያስደነግጡኝ ይሆን? አለ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳፩ | ወሖረ ኀበ ደብር ዘመነኮሳት ወነበረ ህየ በጻማ ወበጸሎት ወሰምዐ አቡሁ ኀበ ሀሎ ወልዱ ወሖረ ህየ ወአኀዘ ይእስሮ ወአብጽሖ ኀበ እሙ ወይቤልዎ አቡሁ ወእሙ ንሣእ እክለ ወብላዕ፡፡ | ፳፩ | ወደ መነኮሳትም ደብር ሔዶ በዚያም በገድልና በጸሎት ተቀመጠ፡፡ አባቱም ልጁ ያለበትን ሰምቶ ወደዚያ ሔደ፡፡ አስሮ ያዘውና ወደ እናቱ አደረሰው፡፡ አባቱና እናቱም እንካ ምግብ ብላ አሉት፡፡ |
| ፳፪ | ወአውሥአ ወይቤሎሙ አንሰ ኢይበልዕ እክለ ለእመኢኀደግሙኒ እኩን መነኮሰ ወይቤልዎ አቡሁ ወእሙ ኢነኀድገከ ትኩን መነኮሰ ወይቤሎሙ አነሂ ኢይበልዕ እክለ፡፡ ወዘበጦ አቡሁ ዐቢየ ዝብጠተ እስከ የሐምም ሥጋሁ፡፡ | ፳፪ | መለሰላቸው እኔ መነኩሴ እንድሆን ካልተዋችሁኝ እህል / ምግብ/ አልበላም አላቸው አባቱና እናቱም መነኩሴ ትሆን ዘንድ አንተውህም አሉት፡፡ እኔም ምግብ አልበላም አለው አባቱም ሥጋው እስኪታመም ድረስ ታላቅ አመታትን መታው፡፡ |
| ፳፫ | ወካዕበ ይቤሎ አቡሁ ንሣእ ብላዕ ወስተይ ከመ ኢትሙት በበትር ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ ኢይበልዕ ወኢይሰቲ እስከ አመ እመውት ለእመ ኢኀደግሙኒ እኩን መነኮሰ፡፡ | ፳፫ | ዳግመኛም አባቱ በበትር እንዳትሞት ብላ ጠጣ አለው፡፡ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም መነኩሴ እሆን ዘንድ ካልተዋችሁኝ እስከሞት ድረስ እኔ አልበላም አልጠጣም አለው፡፡ |
| ፳፬ | ወመልአ አቡሁ መዐተ ወተወሰከ ቍጥዓሁ ወነሥአ በትረ ወዘበጦ እንዘ ይብል አነኒ ኢይኀድግ ዘቢጦተከ ለእመ ኢገበርከ ዘእቤለከ ወደገመ አቡሁ ዘቢጦቶ ለወልዱ፡፡ | ፳፬ | አባቱም ቁጣን ተመላ ቁጣውም ተጨመረ፤ በትርም ይዞ እኔም የምልህን ካላደረግህ መማታቴን አልተውም እያለ መታው አባቱም መልሶ ልጁን መታው፡፡ |

፷፭ ወኀደነ እሡሮ አሜሃ በገዳም ወቤተ ኀበ ቍር በይእቲ ሌሊት ወበሣኒታ ነሥአ አቡሁ በትረ ወዘበጦ እንዘ ይብል ኢይኅደግ ዘቢጦተከ እስከ ትመውት ለእመ ኢኀደገ ከዊነ ምንኵስና፡፡

፷፭ ያን ጊዜም በገዳም እንደታሰረ ተወው በዚያችም ሌሊት በውርጭ አደረ በማግሥቱም አባቱ በትር ይዞ ምንኩስናን ካልተውህ እስክትሞት ድረስ መማታትን አልተውም እያለ መታው፡፡

፷፮ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ እመውት በእንተ እግዚአብሔር ወኢይኅድግ ከዊነ ምንኵስና ወሶበ ሰእነ አቡሁ አሆ አብሂሎቶ ኀደጎ ካዕበ እሱረ ይቢት ውስተ ቍር ወአሰሐትያ፡፡

፷፮ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እኔ ስለ እግዚአብሔር እሞታለሁ ምንኩስናንም አልተውም አለው፤ አባቱም እሺ ማሰኘት በተሳነው ጊዜ በቅዝቃዜና በውርጭ ያድር ዘንድ እንደ ታሰረ ተወው፡፡

፷፯ ወበሳኒታሁ ካዕበ ሖረ አቡሁ ኀበ ሀሎ እሱረ ወይቤሎ ስማዕ አ ወልድየ ዘእቤለከ ከመ ኢትሙት በእዴየ ወይቤሎ ወልዱ እመውት በእንተ እግዚአብሔር ወኢይኅድግ ፍቅሮ ለክርስቶስ አምላኪየ፡፡

፷፯ በማግሥቱም ዳግመኛ አባቱ ወደ አለበት ሔዶ ልጄ ሆይ በእጄ እንዳትሞት የምልህን ስማ አለው፡፡ ልጁም ስለ እግዚአብሔር እሞታለሁ የአምላኬ የክርስቶስንም ፍቅር አልተውም አለው፡፡

፷፰ ወሶበ ሰምዐ አቡሁ ተምዐ ዐቢየ መዐተ ወነሥአ በትረ ወዘበጦ በዐቢይ ኀይል ዝብጠተ እስከ ይየብስ ሥጋሁ ከመ እብን ወከመዝ ነበረ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ እንዘ ይዘብጦ አቡሁ በኑኀ መዐልት ወይበይት በዋዕየ ፀሐይ ወሌሊተ በቍር ወበአሰሐትያ እንዘ ኢይበልዕ እክለ ወኢይሰቲ ማየ እንዘ ሕሙይ እደዊሁ ድኅሬተ ወእገሪሁ ውስተ ጒንደ ዕፀው፡፡

፷፰ አባቱም በሰማ ጊዜ ታላቅ ቁጣን ተቈጣ፤ በትርም አንሥቶ ሥጋው እንደ ድንጋይ እስኪደርቅ ድረስ በታላቅ ኀይል መታው፡፡ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እንደዚህ ቀን አባቱ እየገረፈው ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ተቀመጠ፡፡ ቀን በፀሐዩ ሐሩር ሌሊትም በቅዝቃዜና በውርጭ እህል ሳይበላ ውኃም ሳይጠጣ እጁንና እግሩን የኋሊት ከእንጨት ግንድ ጋር ታስሮ ያድራል፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳፱ ወውእቱሰ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ቀደመ ስምዐ በእደ አቡሁ ወተፈጸመ ላዕሌሁ ቃለ እግዚአብሔር ዘይቤ በወንጌል “ኢይምሰልክሙ ዘአምጻእኩ ሰላመ ለምድር አላ መጥባሕተ ወመጻእኩሰ እፈልጥ ብእሴ እምአቡሁ ወወለተኒ እምእማ ወመርዓተኒ እምሐማታ”፡፡ ማቴ. ፲፥፴፬

፳፱ እርሱ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም አስቀድሞ በአባቱ እጅ ሰማዕትነትን ተቀበለ፤ በወንጌልም ለምድር ሰላምን ያመጣሁ አይምሰላችሁ ሰይፍን ነው እንጂ የመጣሁስ ሰውን ከአባቱ ልጅንም ከእናቷ ምራትንም ከአማትዋ ልለይ ነው ያለው የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ ላይ ተፈጸመ፡፡ ማቴ. ፲፥፴፬

፴ ወዝንቱሰ ብእሴ እግዚአብሔር አፍቀረ ንጽሐ ከመ መላእክት ወመነነ ሰብሳበ ከመ ደናግል መነኮሳት ተመሰለ በኢያጥርዮ ንዋይ ከመ ሐዋርያት ወለብሰ ጻማ ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ፡፡

፴ ይህም የእግዚአብሔር ሰው እንደ መላእክት ንጽሕናን ወደደ እንደ ደናግል መነኮሳትም ጋብቻን ተወ /ናቀ/፤ ገንዘብንም ባለመፈለግ እንደ ሐዋርያት ተመሰለ እንደ ዘካርያስ ልጅ እንደ ዮሐንስም ተጋድሎን ለበሰ፡፡

፴፩ ለከዊነ ስምዕ ተደለወ ከመ ይኩን ሱታፌ ለሕማማቲሁ ለወልደ እግዚአብሔር ቀነተ ሰይፈ መለኮት ወአጥብዐ ለከዊነ ሐራሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ አኀሠራ ለሥጋሁ በጾም ወበትሕርምት ከመ ትኩን ልምልምተ በዐጸደ መርዐሁ ለክርስቶስ፡፡

፴፩ የወልደ እግዚአብሔር የመከራዎቹ ተሳታፊ ይሆን ዘንድ ሰማዕት ለመሆን ተዘጋጀ የመለኮትን ሰይፍ ታጠቀ የኢየሱስ ክርስቶስ ወታደር ለመሆን ጨከነ፡፡ በክርስቶስ በሙሽርነቱ ቦታ የለመለመች ትሆን ዘንድ ሥጋውን በጾምና በትርሕምት አጐሰቆላት፡፡

<u>ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል</u>

፻፪ አይበሳ ለጉርዔሁ በጽምዕ ከመ ትኩን ጥልልተ በማየ ገነት ንጹሕ አስተናሥኣ ለኀሊናሁ ምስለ ግዕዘ ሥጋ ከመ ይኩን ረድኦ ለወልደ እግዚአብሔር ወአሰራ ውስተ ኊንደ ፍቅሩ ወአንበራ ለማኅቶት ዲበ ተቅዋመ መስቀል ከመ ታብርህ ለኲሉ ዓለም፡፡

፻፪ በንጹሕ የገነት ውኃ የለመለመች ትሆን ዘንድ ጉረሮውን በጥም አደረቃት የወልደ እግዚአብሔር ደቀ መዝሙር ይሆን ዘንድ ኅሊናውን ከሰውነቱ ጠባይዕ ጋር አነሣሣት በፍቅሩም ግንድ አሰራት፤ መብራቱንም ለዓለም ሁሉ ታበራ ዘንድ በመስቀል መቅረዝ አስቀመጣት፡፡

፻፫ ቀሰማ ለክህነቱ በጼወ መለኮት ወአሰርገዋ በባሕርየ ወንጌል ነሥአ አፈወ እምነቢያት ወቅብዐ ዘይት እምሐዋርያት ወአምዐዛ ለዓለም በዕፍረተ ትምህርቱ፡፡

፻፫ ክህነቱንም በመለኮት ጨውነት አጣፈጣት በወንጌል ዕንቍም አስጌጣት ከነቢያት ሽቱን፣ ከሐዋርያትም ዘይትን ወሰደ ዓለምን በትምህርት ሽቱ አጣፈጣት፡፡

፻፬ ንትመየጥኬ ኀበ ነገረ ዜናሁ ለብእሴ እግዚአብሔር ወእምዝ ሶበ ስእነ አቡሁ መዪጦ ኅሊናሁ እምፍቅረ እግዚአብሔር በአብዝኆ ቅሥፈታት አዘዞ አቡሁ ለአሐዱ እም አግብርቲሁ ከመ ይሰዶ ኀበ መነኮስ ወየሀቦ ኪያሁ እንዘ ይብል ንሣእ ዘንተአ ወልደአ ከመአ ይኩንከአ ገብረአ እስከ ዕለተ ሞቱአ፡፡

፻፬ የእግዚአብሔርን ሰው ዜናውን ወደ መናገር እንመለስ ከዚያም በኋላ አባቱ በግርፋት ብዛት ዐሳቡን ከእግዚአብሔር ፍቅር መመለስ በተሳነው ጊዜ አባቱ ከአገልጋዮቹ አንዱን ወደ መነኰሴው ይወስደውና እስከ ዕለተ ሞቱ ባሪያ ይሆንህ ዘንድ ይህን ልጅ ውሰድ ብሎ ይሰጠው ዘንድ አዘዘው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፭ ወይቤሎ ውእቱ መነኮስ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ትነብርኑ ኀቤየ ከመ እኩንከ መምህረ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ ኢይፈቅድ ትኩነኒ መምህረ ወይቤሎ ውእቱ መነኮስ ለላእከ አግብኦ ኀበ አቡሁ ወነገሮ ዘከመ ይቤሎ መነኮስ ወዘከመ ይቤሎ በጸሎተ ሚካኤል፡፡

፴፭ ያም መነኩሴ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን መምህር እሆንህ ዘንድ ከእኔ ጋር ትቀመጣለህን? አለው አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እኔ መምህር እንድትሆነኝ አልፈልግም አ ለ ው ፡ ፡ ያ ም መ ነ ኩ ሴ መልእክተኛውን ወደ አባቱ መልሰው አለው፡፡ መልእክተኛውም ወደ አባቱ ወስዶ መነኩሴውም የነገረውንና በ ጸ ሎ ተ ሚ ካ ኤ ል ም ያ ለ ው ን ነገረው፡፡

፴፮ ወሶበ ሰምዐ አቡሁ ነደ ልቡ በመዐት ወይቤልዎ ካልአን ኢትቅትል ዘንተ ወልደ በእዴከ ከመ ኢትኀዝን ድኅረ ወእምዝ ኀለየ አቡሁ በልቡ ከመ ይሰዶ ኀበ ካልእ መነኮስ ወይቤሎሙ ለአግብርቲሁ ሰድዎ ኀበ እገሌ መንኮስ ወይቤልዎ ንሣእ ይኩንከ ገብረ፡፡

፴፮ አባቱም በሰማ ጊዜ ልቡናው በቁጣ ነደደ፤ ሌሎችም ሰዎችም ኋላ እንዳታዝን በእጁ ይህን ልጅህ አትግደል አሉት፡፡ ከዚያም በኋላ ወደ ሌላ መነኩሴ ይወስደው ዘንድ አሰበ፤ አገልጋዮቹንም እገሌ ወደ ሚባል መነኩሴ ውሰዱት አላቸው እነርሱም አገልጋይ ይሆንህ ዘንድ ውሰድ አሉት፡፡

፴፯ ወይቤሎ ውእቱ መነኮስ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ትፈቅድኑ ትንበር ኀቤየ ከመ እኩንከ መምህረ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ ኢይፈቅድ ትኩነኒ መምህረ ዳእሙ አስትየኒ ማየ በእንተ እግዚአብሔር እስመ ጸማዕኩ፡፡

፴፯ ያም መነኩሴ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን መምህር እንድሆንህ ከእኔ ዘንድ ልትቀመጥ ትወዳለህን? አለው፡፡ አባታችንም እኔ መምህር እንድትሆነኝ አልፈልግም ነገር ግን ጠምቶኛልና ስለ እግዚአብሔር ብለህ ውኃ አጠጣኝ አለው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፫ ወእምዝ አግብእዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኀበ አቡሁ ወተምዐ አቡሁ ወሰዶ ኀበ ቤተ ክርስቲያን ዘሚካኤል ኀበ ተጋብኡ ካህናት ወዲያቆናት እድ ወአንስት ነሥአ መላጼ ወበጥሐ እዝኖ እንዘ ይብል ንሣእ ሚካኤል ይኩንከ ገብረ ይትለአክ ለቤተ ክርስቲያን እስከ ዕለተ ሞቱ፡፡

፴፬ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ ኢኮንኩ ገብሮ ለሚካኤል አላ አነ ገብሩ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ዘወሀብክዎ ሎቱ ነፍስየ ወሥጋየ ወሶበ ሰምዐ አቡሁ ኀዘነ ዐቢየ ኀዘነ ወሖረ ኀበ እግዚእ ክብራ ብእሲቱ ወይቤ አስአነኒ አንሰ ደከምኩ በእንተ ዝንቱ ወልድኪ ምንተ እግበር፡፡

፴፭ ወይቤሉ በበይናቲሆሙ ሀለወት ብእሲተ እኁሁ ዘላሕየ ገጽ ንእስሮ ምስሌሃ ከመ ታስሕቶ በዝሙት ወነገርዋ ለብእሲተ እኁሁ ዘንተ ምክረ ወተፈሥሐት ይእቲ ፈድፋደ ወትቤሎሙ አምጽእዎ ኀቤየ ፍጡነ ወኢትቅትልዎ በረኀብ፡፡

፴፫ ከዚህ በኋላ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ወደ አባቱ መለሱት አባቱም ተቆጥቶ ካህናትና ዲያቆናት፣ ወንዶችና ሴቶችም ወደ ተሰበሰቡበት የሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ወሰደው፡፡ ጆሮውንም በጥቶ ሚካኤል ሆይ እስከ ዕለተ ሞቱ አገልጋይ ይሆንህ ዘንድ ለቤተ ክርስቲያንም ይላላክ ዘንድ ውሰድ አለው፡፡

፴፬ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እኔ የሚካኤል ባሪያ አይደለሁም ነፍሴንና ሥጋዬን የሰጠሁት የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነኝ እንጂ አለ፡፡ አባቱም በሰማ ጊዜ ታላቅ ኀዘን አዘነ፤ ወደ ሚስቱ እግዚእ ክብራም ሔዶ አደከመኝ ስለዚህ ልጅህ ደከምሁ ምን ላድርግ አለ፡፡

፴፭ እርስ በርሳቸውም የወንድሙ ሚስት መልከ መልካም አለች፡፡ በዝሙት ታስተው ዘንድ ከእርስዋ ጋር እንስረው አሉ፤ ለወንድሙም ሚስት ይህን ምክር ነገሯት፤ እርስዋም ፈጽሞ ደስ አላት፤ ወደ እኔ ፈጥናችሁ አምጡት በረኀብም አትግደሉት አለች፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፻፲፩ ወወሰድዎ ኀቤሃ ወአሰርዎ ምስሌሃ ወጸለየ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል በለኆሳስ ዘንተ ጸሎተ እንዘ ይብል አድኅነኒ እግዚኦ እመሥገርተ ዝሙት እንተ ታወርድ ውስተ ገሃነም አድኅነኒ እግዚኦ እመሥገርተ ጸላኢ ዘርቡብ መሣግሪሁ ውስተ ዓለም፡፡

፻፲፩ ወደ እርስዋም ወስደው ከእርስዋ ጋር አሰሩት፤ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ይህን ጸሎት እንዲህ ብሎ በለኆሳስ ጸለየ፤ አቤቱ ወደ ገሃነም ከምታወርድ ከዝሙት ወጥመድ አድነኝ፤ አቤቱ በዓለም ከተዘረጋ ከጠላት ወጥመድ አድነኝ፡፡

፻፲፪ አድኅነኒ እግዚኦ እምእደ ብእሲት ወእም ሂጠተ ቃል ዘያነድድ ልበ ወራዙት አድኅነኒ እግዚኦ እምሥነ ላሕይ ዘያሠግሮ ለዐይን ወእምሐብለ ሙስና ዘይስሕብ ውስተ ጸድፍ

፻፲፪ አቤቱ ከሴት እጅ የጎልማሶችንም ልብ ከሚያናድድ የቃል ማታለል አድነኝ፤ አቤቱ ዐይንን ከሚያጠምደው ደም ግባትና/ውበትና/ ወደ ገደል ከሚስብ የጥፋት ገመድ አድነኝ፡፡

፻፲፫ አድኅነኒ እግዚኦ ዘአድኅንኮ ለያዕቆብ እምእደ ኤሳው እኁሁ ወለሙሴ እምእደ ፈርዖን አድኅነኒ እግዚኦ ዘአድኅንኮ ለዳዊት እምእደ ሳኦል ወለኤልያስ እምእደ አክአብ ወኤልዛቤል አድኅነኒ እግዚኦ ዘአድኅንኮ ለዳንኤል እምአፈ አናብስት ርኁባን ወለሠለስቱ ደቂቂ እምዕቶነ እሳት ዘባቢሎን፡፡

፻፲፫ አቤቱ ያዕቆብን ከወንድሙ ከኤሳው ሙሴንም ከፈርዖን እጅ ያዳንኸው አድነኝ፤ አቤቱ ዳዊትን ከሳኦል እጅ ኤልያስንም ከአክአብና ከኤልዛቤል እጅ ያዳንኸው አድነኝ፡፡ አቤቱ ዳንኤልን ከተራቡ አናብስት አፍ ሦስቱ ልጆችንም ከባቢሎን እሳት ያዳንካቸው አድነኝ፡፡

፻፲፬ አድኅነኒ እግዚኦ ዘአድኅንካ ለሶስና እምእደ ረበናት ወለመርዶክዮስ እምእደ ሐማ ወአውፅአኒ እግዚኦ እምስሕተታ ወእምድኅፀታ ለዛቲ ብእሲት፡፡ ዘአውፃእኮ ለዮናስ እምከርሠ አንበሪ፡፡

፻፲፬ አቤቱ ሶስናን ከረበናት እጅ ያዳንሃት መርዶክዮስንም ከሐማ ያዳንኸው አድነኝ አቤቱ ዮናስን ከአንበሪ ሆድ ያወጣኸው ከዚህች ሴት ድቀትና ስሕተት አውጣኝ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፶፭ አውፅአኒ እግዚኦ እምከረ ጻላኢ ዘአምከሮሙ ለአቡየ ወለእምየ ከመያንብሩ ሣዕረ ምስለ እሳት አንሰእብል ወአውፅአኒ እምዛቲ መሥገርት አንተ ኅብኡ ሊተ እስመ አንተ ረዳእየ እግዚኦ ውስተ እዴከ አመሐፅን ነፍስየ፡፡

፶፭ አቤቱ አባትና እናቴን ሣርን ከገለባ ጋር ያስቀምጡ ዘንድ ከመከራቸው ከጠላት ምክር አውጣኝ፡፡ እኔን ለማጥመድ ከሸመቋት ከዚህች ወጥመድ አውጣኝ እላለሁ አቤቱ አንተ ረዳቴ ነህና ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ፡፡

፶፮ መኑ ዘየዐቍር ፍሕመ ውስተ ሕፅኑ ወኢይውዒ ወመኑ ዘይእኅዝ አቅራበ በእደዊሁ ወኢይሐምም ወመኑ ዘየዐንቅ አፍዖተ ውስተ ክሳዱ ወኢይደነግፅ ወመኑ ዘይቀንት ከይሴ ውስተ ሐቌሁ ዘኢይትነሰክ፡፡

፶፮ ፍሕምን ቋጥሮ የማይቃጠል ማን ነው? እፉኞችን በአንገቱ የሚያስር የማይደነግጥ፣ እባብን በወገቡ የሚታጠቅ የማይነከስስ ማን ነው?

፶፯ ሡቀኒ እግዚኦ እንበለ እደቅ ዕቀበኒ ንጹሐ እንበለ እርሳሕ ረስየኒ ጽኑዐ እንበለ እጽበስ ለከ ኀይል ወለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፶፯ አቤቱ ሳልወድቅ ደግፈኝ ሳልረክስ በንጽሕና ጠብቀኝ ሳልደክምም የበረታሁ አድርገኝ ለአንተ ኀይል ምስጋና ይገባል ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

፶፰ ወእምዝ ትቤሎ ብእሲተ እኁሁ ኢትቤለኒኑ አፈቅረኪ ጥቀ ወይቤላ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ፍቅረሰ አፈቅረኪ እምነ አቡየኒ ወእምየኒ ወፈድፋደ አፈቅሮ እምኔኪ ለእግዚአብሔር ወትቤሎ ብእሲተ እኁሁ እመሰ ታፈቅረኒ ነዐ ንደመር በሥጋነ ምንትኑ ፍቅረ ብእሲ ወብእሲት ዘእንበለ ሩካቤ

፶፰ ከዚህ በኋላ የወንድሙ ሚስት እወድሻለሁ አላልኸኝምን አለችው፤ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም መውደድስ ከአባቴና ከእናቴ አብልጬ እወድሻለሁ፤ ከአንቺ በበለጠ ደግሞ እግዚአብሔርን እወደዋለሁ አላት፤ የወንድሙም ሚስት እምትወደኝ ከሆነ በሥጋ አንድ እንሁን ያለ ሩካቤስ የወንድና የሴት ፍቅር ምንድን ነው? አለችው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፺፱ ወይቤላ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ይትመዐዐ እግዚአብሔር ላዕሌየ ለእመ ሐጸጽኩ ፍቅረ ዚአሁ እምፍቅረ ዚአኪ ወገበርኩ ምስሌኪ ኀጢአተ ወትቤሎ ይእቲ ብእሲተ እኁሁ እመሰ አበይከ ተደምሮ ምስሌየ ኢይፈትሐከ ትነብር ሙቁሐከ፡፡

፺፱ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ከአንቺ ፍቅር የእርሱን ፍቅር ካሳነስሁ ከአንቺም ጋር ኀጢአት ከሠራሁ እግዚአብሔር በእኔ ላይ ይቆጣል አላት፤ የወንድሙም ሚስት ከእኔ ጋር ካልተገናኘህ እንደታሰርክ ትቀመጣለህ አልፈታህም አለችው፡፡

፻ ወእምዝ ኀለየ በጸሎተ ሚካኤል ከመ ኢትፈትሖ ዘእንበለ አሆ ይቤላ አውሥአ ውእቱኒ በቃለ ጥበብ እንዘ ይብል እመሰ አፍተወኪ ትድምርተ ዚአየ ፍትሕኒ እመዋቅሕትየ እስመ ኀሣር ውእቱ ሩካቤ ብእሲ ወብእሲት እንዘ እሱራን እሙንቱ፡፡

፻ ከዚያም በኋላ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል እሺ ሳይላት እንደማትፈታው አስቦ እርሱም በጥበብ ቃል ከእኔ ጋር መገናኘት ደስ ካሰኘሽ ታስረው የወንድና የሴት መገናኘት ተዋርዶ ነውና ከእስራቴ ፍችኝ አላት፡፡

፻፩ ወዘንተ ዘይቤ ያምስጥ እም እዴሃ ወመሰላ ላቲሰ ዘይገብር ፈቃዳ ወዘያጸርዕ ምንኵስና ወተፈሥሐት ፈድፋደ ወፈትሐቶ ፍጡነ እመዋቅሕቲሁ ወሖረት ኀበ አቡሁ ወእሙ ወነገረቶሙ ዘከመ አሆ ይቤላ ወተፈሥሑ እሙንቱሂ ዐቢየ ፍሥሓ፡፡

፻፩ ይህንም ያለ ከእጅዋ ያመልጥ ዘንድ ነው፤ ለእርስዋ ግን ፈቃዷን የሚያደርግ ምንኵስናውንም የሚተው መሰሏት ነበር፡፡ ፈጽሞ ደስ አላት ፈጥናም ከእስራቱ ፈታችው ወደ አባቱና እናቱም ሒዳ እሺ እንዳላት ነገረቻቸው እነርሱም ታላቅ ደስታ ተደሠቱ፡፡

፻፪ ወበይእቲ ሌሊት ተግኅሠ ጽሚተ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እምቤተ አቡሁ ወእሙ እምሀገረ ሙላዱ ወድኅነ በጸጋ እግዚአብሔር አመሥገርት እንተ ረበቡ ሎቱ አምሰጠ በግዕ እምአፈ ተኵላ ወርግብ ንጹሕ እምአፈ አንቄ፡፡

፻፪ በዚያችም ሌሊት አባታችን በጸሎተ ሚካኤል በቀስታ ከተወለደበት ሀገር ከአባቱና ከእናቱ ሸሸ፡፡ በእግዚአብሔርም ቸርነት ከዘረጉበት ወጥመድ ዳነ፤ በግ ከተኩላ አፍ ንጹሕ ርግብም ከጭልፊት አፍ አመለጠ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፶፫ ወእምዝ ጸለየ ወይቤ መሥገርትሰ ተቀጥቀጠት ወንሕነሰ ድኅነ ረድኤትነሰ በስመ እግዚአብሔር ወካዕበ ይቤ ሰበርከ መዋቅሕትየ ለከ እሠውዕ መሥዋዕተ ስብሐት መዝ.፻፳፫፥፯፤ መዝ.፻፲፭፥፯
ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፶፫ ከዚህም በኋላ እንዲህ ብሎ ጸለየ፡፡ ወጥመድ ተሰበረች እኛ ግን ዳን ረድኤታችንም ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር ስም ነው፡፡ ዳግመኛም እስራቴን ሰበርህ ለአንተ የምስጋና መሥዋዕት እሠዋልሃለሁ አለ፡፡ መዝ.፻፳፫፥፯፤ መዝ.፻፲፭፥፯
ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይኑር ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፫

፩ ወእምዝ በጽሐ ኀበ ደብረ ጕል ዘውእተ ደብረ ጽሙና ለአኖርዮስ ቀሲስ ዘይነብር ግኁሠ ወይትጋደል በጽምው ወነገሩሰ በእንቲአሁ ለዝ መነኮስ ከመ አስተርአየቶ እግዝእትነ ማርያም ወአዋልደ ንግሥት ቅድሜሁ ወተናገረቶ ቃለ በቃል፡፡

፪ ወነሥአ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ልብሰ ምንኩስና አምእደ ውእቱ መነኮስ ወኮነ ጽሙደ ለአርዑተ ቅዱሳን ወለቃለ መጻሕፍትኒ ያበዝኀ ጾዊመ ወያፈደፍድ ትሕርምተ ወያወትር ጸልዮ ወያፈጥን ሰጊደ ወውእቱ የሐርጽ መባአ ቤተ ክርስቲያን ውእቱ የእቱ ፺ ጾረ ፍልጸ አውልዕ አሐደ ጾረ ለግብ ቤተ ክርስቲያን ወ፺ ጾረ ለአበምኔት፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

፩ ከዚያም ወደ ደብረ ጕል ደረሰ ይኸውም ቀሲስ አኖርዮስ በብቸኝነት ሸሽቶ የሚጋደልበት ደብረ ጽሙና ነው፡፡ ስለዚህም መነኩሴ እመቤታችን ከመንግሥት ልጆች ጋር በፊቱ ቃል በቃል እንደ ተገለጸችለት ይናገራሉ፡፡

፪ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ከዚያ መነኩሴ እጅ የምንኩስና ልብስን ተቀበለ፤ በቅዱሳን ተጋድሎና በመጻሕፍት ቃልም የተጠመደ ሆነ፡፡ ጾምና ትሕርምትም ያበዛል፤ ዘወትር ይጸልያል፤ ስግደትንም ያፋጥን ነበር፡፡ የቤተ ክርስቲያንንም ግብር ይፈጭ ነበር፤ ዘጠና ሸክም የወይራ ፍልጥም ፈልጦ አንዱን ሸክም ለቤተ ክርስቲያን ዘጠናውን ለአበምኔቱ ያመጣ ነበር፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፫ ወካዕበ ወፈሮ የአቱ ፩ዱ ጕንደ ለባሕታውያን ወኢይሴጽር ዕፀ ወጕንዳ በጕድብ ወበምሣር ዘእንበለ በመክርየ ሐጺን ዘይከርዩ ቦቱ መሬተ፡፡

፫ ዳግመኛም ለባሕታውያን ከተሰማራበት አንድ ግንድ ያመጣላቸዋል፡፡ እንጨቱንና ግንዱንም መሬት በሚቆፍሩበት በብረት መቆፈሪያ ነው እንጂ ምሣርና በመጥረቢያ አይፈልጠውም ነበር፡፡

፬ ወዘንተ ዘይገብር ከመ ይድክም ሥጋሁ እም ኀይለ ውርዙት ዘንተ ኲሎ እንዘ ይትቀነይ ጾመሂ ኢያበጥል ጸሎተሂ ኢያፀርዕ ወሰጊደሂ ኢያውኅድ ወማየኒ ዳግመ ውእቱ ይቀድሕ፡፡

፬ ይኸንንም የሚያደርግ ከወጣትነት ኀይል ሥጋው ይደከም ዘንድ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ሲሠራ ጾምን አይሽርም፤ ጸሎትንም አያስታጉልም፤ ስግደትንም አያጐልም ነበር፤ ዳግመኛም ውኃ ይቀዳ ነበር፡፡

፭ ወቦ አመ ይጸውም በበሠሉስ ወቦ አመ ይጸውም በበረቡዕ ወቦ አመ ይጸውም በበሰዱስ ወነበረ እንዘ ይገብር ከመዝ ፲ወ፫ ዓመተ በግብረ ዲቁና ወበዝኒ ስእነ አድክሞ ሥጋሁ፡፡

፭ ሦስት ሦስት ቀን የሚጾምበት ጊዜ አለ፣ አራት አራት ቀንም የሚጾምበት ጊዜ አለ፤ ስድስት ስድስት ቀንም የሚጾምበት ጊዜ አለ፤ እንዲህም እያደረገ ዐሥራ ሦስት ዓመት በዲቁና ሥራ ሲያገለግል ኖረ፡፡ በዚህም ሥጋውን ማድከም ተሳነው፡፡

፮ ወበመንፈቀ መዐልት ሶበ ያውዒ ፀሐይ ወትልህብ ምድር ወይረስን ኰኲሕ ይሰክብ በዘባኑ ውስተ ውእቱ ኰኲሕ እስከ ይበስል አነዳ ሥጋሁ ወካዕበ ይትመየጥ በእንግድዓሁ ወይሰክብ በከርሡ ዲበ ኰኲሕ ርሱን እስከ ይበስል ማእሱ ወእንግዳዓሁ ወከርሡ ወይሰክብ ወበዝኒ ስእነ አድክሞ ሥጋሁ፡፡

፮ በቀትርም እኩሌታ ፀሐይ ሲያቃጥል ምድርም ስትሞቅ ዐለቱ ሲግል በጀርባው የሥጋው ቈዳ እስኪበስል ድረስ በዐለቱ ላይ ይተኛ ነበር፡፡ ዳግመኛም በደረቱ ተደፍቶ ቈዳው፣ ደረቱ፣ ሆዱ እስኪበስል ድረስ በጋለው ዐለት ላይ ይተኛ ነበር በዚህም ሥጋውን ማድከም ተሳነው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፯ | ወእምድኅረዝ ሖረ ኀበ ጳጳስ ወኮነ ቀሲሰ ወአተወ ኀበ ማኅደሩ ወገብረ ሎቱ ንስቲተ ጸማዕተ ወቦአ ውስቴታ ወነበረ ህየ በፈሪሀ እግዚአብሔር ወኲሎሙ ቅዱሳን ይሬስይዎ መልአከ እግዚአብሔር፡፡ | ፯ | ከዚህ በኋላ ወደ ጳጳስ ሔዶ ቅስና ተሹሞ ወደ ማደሪያው ተመለሰ፤ ትንሽ ዋሻ ሠርቶ በውስጥዋ ገባ በዚያም እግዚአብሔርን በመፍራት ተቀመጠ፤ ቅዱሳንም ሁሉ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ያደርጉታል፡፡ |
| ፰ | ወእምዝ ሖረ ኀበ አሐዱ መካነ ጽሙና ወከረየ ግበ እስከ ይውኅጦ ኲለንታሁ ኀደገ ተናግሮ ምስለ ሰብእ ወተመሰለ ከመ በሐም ወኢይትናገር ወኢምንተኒ ዘእንበለ አንብቦ መጻሕፍት ወጸሎት፡፡ | ፰ | ከዚህ በኋላ ወደ አንድ የብቸኝነት ቦታ ሔዶ ሁለንተናውን እስኪውጠው ድረስ ጉድጓድ ቆፈረ፡፡ ከሰው ጋር መነጋገርን ትቶ እንደ ዲዳ መሰለ፤ መጻሕፍትን ከማንበብና ከጸሎት በቀር ምንም አይናገርም ነበር፡፡ |
| ፱ | ወእምዝ እምጉንዱይ መዋዕል መጽኡ ኀቤሁ ቅዱሳን ወይቤልዎ ነዐ ፃእ እምዝ ግብር ከመ ትኩን በቊዔተ ለብዙኃን፡፡ | ፱ | ከብዙ ዘመን በኋላም ቅዱሳን ወደ እርሱ መጥተው ለብዙዎች ጥቅም ትሆን ዘንድ ከዚህ ሥራ ውጣ አሉት፡፡ |
| ፲ | ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኅድጉኒ እብኪ በእንተ ኀጢአትየ ከመ እርባሓ ለነፍስየ በከመ ይቤ በወንጌል ምንት ይበቊዖ ለሰብእ ለእመ ኲሎ ዓለመ ረብሐ ወነፍሶ ሐጒለ ወምንተ እምወሀበ ሰብእ ቤዛሃ ለነፍሱ እስመ ትኄይሰኒ ዛቲ ግብ እምግባ ለሲኦል ማቴ.፲፮፥፳፮ | ፲ | አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ነፍሴን እጠቅማት ዘንድ ስለ ኀጢአቴ ላልቅስ ተዉኝ አላቸው፡፡ በወንጌል ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ ነፍሱንም ቢያጠፋ ለሰው ምን ይረባዋል? ሰውስ ለነፍሱ ቤዛ ምን በሰጠ ነበር! እንዳለ፡፡ ከሲኦል ጉድጓድ ይህች ጉድጓድ ትሻለኛለችና ፡፡ ማቴ.፲፮፥፳፬ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፩ | ወይቤልዎ ቅዱሳን እመሰ ነበርከ ውስተ ግብ ትረብሕ ነፍሰከ ባሕቲታ ወእመሰ ወፃእከ እምዝ ግብ ወመሀርከ ለብዙኃን ርእሰከ ታድኅን ወዘሂ ይሰምዐከ፡፡ | ፲፩ | ቅዱሳንም በጉድጓድ ብትቀመጥ ነፍስህን ብቻ ትጠቅማለህ ከጉድጓዱ ወጥተህ ግን ለብዙዎች ብታስተምር ራስህን የሚሰማህንም ታድናለህ አሉት፡፡ |
| ፲፪ | ተመሰልኬ ከመ ሐዋርያት ወመሀር ከመ ጳውሎስ ስብከ ውስተ አንሕስት ወአስምዕ ቃለከ በቅድመ ጉባኤ በከመ ይቤ ወንጌል "ኢትክል ተከብቶ ሀገር እንተ ተሐንጸት መልዕልተ ደብር ወኢያኅትዉ ማኅቶተ ከመ ያንብርዋ ታሕተ ከፊር አላ ያነብርዋ ዲበ ተቅዋማ ወታበርህ ለኵሎሙ እለ ውስተ ቤት፡፡ ማቴ.፭፥፲፬ | ፲፪ | እንደ ሐዋርያት ምሰል እንደ ጳውሎስም አስተምር፤ በሰገነት ላይ ስበክ በጉባኤም ቃልህን አሰማ፤ ወንጌል እንዳለ፡፡ በተራራ ላይ የተሠራች መንደር መሰወር አይቻላትም ዕንቅብም ሊደፉባት መብራትን አያበሩም በመቅረዝዋ ላይ አኑረዋት በቤት ላሉት ሁሉ ታበራለች እንጂ፡፡ ማቴ.፭፥፲፬ |
| ፲፫ | ወሶበ አስተብቍዕዎ ብዙኀ ወአጽሐብዎ ፈድፋደ ወፅአ እምግብ ወተአምኃዎ ኵሎሙ ቅዱሳን ወነበረ ምስሌሆሙ በፈሪሀ እግዚአብሔር እንዘ ይሬኢ ኅቡኣተ ከመ ነቢያት ወይገብር ተአምራተ ከመ ሐዋርያት፡፡ | ፲፫ | ብዙ በማለዱትና እጅግ ባስቸገሩት ጊዜ ከጉድጓዱ ወጣ፤ ቅዱሳኑም ሁሉ እጅ ነሱት እንደ ነቢያት የተሰወረውን እያየ እንደ ሐዋርያም ተአምራት እየሠራ ከእነርሱ ጋር እግዚአብሔርን በመፍራት ኖረ፡፡ |
| ፲፬ | ወመነነ አጥርዮ ንዋይ ከመ መዘምር ዳዊት ወኢገብረ ሎቱ አዝርዕተ እስከ ኅጠተ ሰናፔ ወኢይኄሊ በእንተ ሲሳየ ከርሡ ወኢይንህከ በእንተ አማዑቲሁ ወኢይቴክዝ በእንተ ስታዩ ወኢይኅዝን በእንተ አልባሲሁ፡፡ | ፲፬ | እንደ መዝሙረኛው ዳዊትም ገንዘብ መሰብሰብን ናቀ፡፡ ከሰናፍጭ ቅንጣትም ድረስ ለራሱ ዘርን አልዘራም፤ ስለ ሆዱም ምግብ አያስብም፤ አንጀቱ ስለሚርስበት ነገርም አያዝንም፤ ስለሚጠጣውም አይተክዝም ስለ ልብሱም አይጨነቅም፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፫ የሐጽባ ለሥጋሁ በማየ አንብዑ ወያረስና ለልቡ በላህበ መለኮት ወሀሎ እኁሁ ዘይልህቆ ካህን ወመነኮስ መምህረ ቅዱሳን ዘስሙ ኀረዮ ክርስቶስ አስተብቍዖ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል እንዘ ይብል ኅቡረ ንነብር በፍቅር ወበሰላም ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ አፈቅር ነቢረ እንዘ ባሕቲትየ፡፡

፲፫ ሥጋውን በእንባው ውኃ ያጥባታል በመለኮትም እሳት ልቡን ያቃጥላታል፤ ስሙ ኀረዮ ክርስቶስ የሚባል የቅዱሳን መምህር ካህንና መነኩሴ የሆነ ታላቅ ወንድም ነበረው አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን በፍቅርና በሰላም በአንድነት እንቀመጥ ብሎ ለመነው አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እኔ ብቻዬን መኖር እፈልጋለሁ አለው፡፡

፲፬ ወእምዝ ገብሩ ሎቱ ጾማዕተ ወነበረ ውስቴታ እንዘ ይተግህ በጾም ወበጸሎት ወይሰግድ በኑኀ መዐልት ፰፻ ወበኑኀ ሌሊት፰፻ ወእምዝኀ ሰገድ ተዐምቅ ምድር ወተውኅጠ እስከ ብረኪሁ ወኀበዘሰገደ ገጸ መካን ያንጸፈጽፍ ሐፋ ከመ ማይ እስከ ይሬስያ ጽቡረ ለመሬት ወትትሌለይ እመሐ ስዐተ አጣሊ ዘይለብሳ፡፡

፲፬ ከዚህም በኋላ ዋሻ ሠራለት፤ በውስጥዋም በጾምና በጸሎት እየተጋ ኖረ፤ በቀን ስምንት እልፍ በሌሊትም ስምንት እልፍ ይሰግድ ነበር ከስግደቱም ብዛት የተነሣ ምድር ጐድጉዳ እስከ ጉልበቱ ትውጠው ነበር፡፡ ከሰገደበትም ቦታ ወዙ መሬትን ጭቃ እስኪያደርጋት ድረስ እንደ ውኃ ይፈስስ ነበር፡፡ የሚለብሳት የፍየል ሌጦም ሲሰግድ ከሰውነቱ ትለይ ነበር፡፡

፲፭ ወቦ ዘይቤ እንዘ ይትገሀረት አሐተ ዕለተ በሰጊድ ውስተ ቤተ መቅደስ ላህበ እስትንፋሰ አፉሁ አሕመማ ለሥጋየ ከመ ላህበ እሳት ይተግህ ኵሎ ሌሊተ እንዘ ይብል ወኢይሁቦን ንዋመ ለአዕይንትየ ወኢድቃሰ ለቀራንብትየ ወኢዕረፍተ ለመላትሕየ እስከ እረክብ መካኖ ለእግዚአብሔር ወማኀደሮ ለአምላከ ያዕቆብ፡፡ መዝ.፻፴፩፥፬

፲፭ አንድ ቀንም በቤተ መቅደስ ውስጥ እየተፋጠነ ሲሰግድ የአፉ እስትንፋስ እንደ እሳት ነበልባል ሥጋዬን አሳመማት ሌሊት ሁሉ እንዲህ እያለ ይተጋል፤ ለዐይኖቼ ምኝታን ለቅንድቦቼ እንቅልፍን ለጕንጮቼም ዕረፍትን አልሰጥም፤ የእግዚአብሔርን ቦታ የያዕቆብ አምላክን ማደሪያ እስካገኝ ድረስ የሚልበት ጊዜ አለ፡፡ መዝ.፻፴፩፥፬

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፰ ወአሐተ ዕለተ እንዘ ይኄሊ በእንተ ፀአቱ እምዝ ዓለም ወፍልሰቱ ውስተ ሰማያት አስተርአዮ መድኅን እንዘ ይብል ምስለ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ረሰይኩ ለከ ማኅደረከ ወዘንተ ብሂሎ ተሰወረ እምኔሁ፡፡

፲፰ አንድ ቀንም ከዚህ ዓለም ስለ መውጣቱና ወደ ሰማያትም ስለ መሔዱ ሲያስብ መድኀኒታችን ክርስቶስ ማደሪያህን ከጴጥሮስና ከጳውሎስ ጋር አደረግሁልህ ሲል ተገለጸለት ይህንም ብሎ ከእርሱ ተሰወረ፡፡

፲፱ ወእምዝ ነበረ እንዘ ይገብር ተአምረ ወመንክረ ያበዝኅ ጾመ ወጸሎተ ወይትዔገሥ ምንዳብያተ በእንተ እግዚአብሔር፡፡

፲፱ ከዚህም በኋላ ተአምርንና ድንቅ ሥራን እየሠራ ጾምንና ጸሎትንም እያበዛ ኖረ፤ ስለ እግዚአብሔርም ብዙ መከራዎችን ይታገሥ ነበር፡፡

፳ ወእምዝ ወፅአ እምቤተ አቡሁ ወተግኅሠ ውስተ ካልእ መካን ወገብረ በህየ ምኔተ ሠናየ ገደፋ ለነፍሱ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይርባሕ ዘበሰማያት ተዘኪሮ ቃለ እግዚእ ዘይቤ በወንጌል ዘገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ ይረከባ፡፡

፳ ከዚህም በኋላ ከአባቱ ቤት ወጥቶ ወደ ሌላ ቦታ ሔደ፤ በዚያም ጥሩ ዋሻ ሠራ በወንጌል ስለ እኔ ነፍሱን የጠላት ያገኛታል፤ ያለውን የጌታ ቃል አስቦ በሰማያት ባለው ይጠቀም ዘንድ ነፍሱን በእግዚአብሔር ጠላት፡፡

፳፩ ወካዕበ ይቤ "አማን አማን እብለከሙ እመ ኢወድቀት ኅጠተ ስርናይ ውስተ ምድር ወኢሞተት ባሕቲታ ትነብር ወእመሰ ሞተት ብዙኀ ፍሬ ትፈሪ ወዘሰ ያፈቅራ ለነፍሱ ለይግድፋ ወዘሰ ገደፋ ለነፍሱ ይረከባ፡፡ ዮሐ.፲፪፥፳፭

፳፩ ዳግመኛም እውነት እውነት እላችኋለሁ የስንዴ ቅንጣት በምድር ላይ ካልወደቀችና ካልሞተች ብቻዋን ትኖራለች ከሞተች ግን ብዙ ፍሬን ታፈራለች፡፡ ነፍሱን የሚወዳት ይጣላት ነፍሱንም የጣላት ያገኛታል አለ፡፡ ዮሐ.፲፪፥፳፭

# <u>ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል</u>

፳፪ ወዘንተ ቃላተ ተዘኪሮ ብእሴ እግዚአብሔር ረሰያ ለነፍሱ ምዉተ በኀበ ዓለም ወዓለምኒ ምውቱ በኀበ ነፍሱ በከመ ይቤ ጳውሎስ "ወበኀቤየሰ ምዉት ዓለም ወአነሂ ምዉት በኀበ ዓለም፡፡ ገላ.፮፥፲፬

፳፪ የእግዚአብሔርም ሰው ይህ ቃል አስቦ ሰውነቱን በዓለም የሞተች ዓለምንም በእርሱ ዘንድ የሞተች አደረጋት ቅዱስ ጳውሎስ በእኔ ዘንድ ዓለሙ የሞተ ነው፤ እኔም በዓለሙ ዘንድ የሞትሁ ነኝ እንዳለ፡፡ ገላ.፮፥፲፬

፳፫ ወተቀንየ በትሕትና በትጋሀ ቅዱሳን አኀዘ ዕርፈ ወኢተመይጠ ድኀረ ከመ ኢይጽንን ትልሙ ወነሥአ መስቀለ ሞቱ ወተለዎ ለወልደ እግዚአብሔር እንዘ ኢያስቆቁ እምንዋየ ዝዓለም፡፡

፳፫ ከዚህ በኋላ በወንገል ሥርዐት በትሕትና በቅዱሳን ትጋት የተጠመደ ሆነ እርፍ ይዞ ትልሙ እንዳይጸንበት ወደ ኋላው አልተመለሰም፡፡ የሞቱን መስቀል ተሸክሞ ከዚህ ዓለም ገንዘብ የተነሣ ሳያዝን የእግዚአብሔርን ልጅ ተከተለው፡፡

፳፬ ወተመሰሎሙ ለአዕዋፈ ሰማይ በኢያጥርዮ አዝርዕት ወለአራዊተ ገደምኒ ተመሰሎሙ በኢኀልዮ ለአራዘ ሥጋሁ፡፡

፳፬ ዘር/ ምግብ/ ባለመሰብሰብም የሰማይ ወፎችን መሰላቸው ለሥጋውም ልብስ ባለማሰብ የዱር አራዊትን መሰላቸው፡፡

፳፭ ወተመሰላ ለንህብ በአስተጋብኦ ጽጌያት ለገቢረ ጸቃውዕ፡፡

፳፭ የማር ወለላን ለመሥራት አበባዎችን በመሰብሰብ ንብን መሰላት፡፡

፳፮ ነሥአ ንጽሐ ኀሊና እምነቢያት ወመንኖ ዓለም እምሐዋርያት፡፡

፳፮ ከነቢያት ኅሊናን ንጹሕ ማድረግ፣ ከሐዋርያትም ዓለምን መናቅን ተማረ፡፡

፳፯ ወነሥአ ንጽሐ ሥጋ እምደናግል መነኮሳት ወአፍቀረ ጽሙና እምገዳማውያን ወእለ በጾማዕት፡፡

፳፯ የሥጋን ንጽሕና ከደናግል መነኮሳት ተማረ፤ ከገዳማውያንና በዋሻ ከሚኖሩም ብቸኝነትን ተማረ፡፡

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፷፰ ወነሥአ ምህሮ ሠናይ እምጳውሎስ ልሳነ ዕፍረት ወገቢረ መንክራት እምጴጥሮስ ኰኵሐ ሃይማኖት፡፡

፷፰ መልካም ነገር ማስተማርን ነገሩ እንደ ሽቱ ደስ ከሚያሰኝ ከጳውሎስ ተአምራት ማድረግንም የሃይማኖት መሠረት ከሆነ ከጴጥሮስ ተማረ፡፡

፷፱ ወነሥአ ተደንግሎ እምዮሐንስ ቴዎሎጎስ ወአብዝኆ ቀዊመ በጸልዮ እምያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ፡፡

፷፱ ድንግልናን ከነባቤ መለኮት ዮሐንስ በጸሎት አብዝቶ መቆምን ከጌታችን ወንድም ከያዕቆብ ተማረ፡፡

፸ ነሥአ ትዕግሥተ እምኢዮብ ምኩር ወትዕግሥተ ጻማ እምጳውሊ ኮከበ ሐቅል፡፡

፸ ትዕግሥትን ከተፈተነ ከኢዮብ በተጋድሎ መጽናትንም ከበረሃው ኮከብ ከጳውሊ ተማረ፡፡

፸፩ ነሥአ ትግሀ እመላእክት ወአብዘኆ ስብሐት እምሊቃነ መላእክት፡፡

፸፩ ትጋትን ከመላእክት ምስጋና ማብዛትንም ከመላእክት አለቆች ተማረ፡፡

፸፪ ነሥአ ትዕግሥተ ቅሥፈት ወሙቃሔ እምሰማዕታት ወስደታተ ከመ አበው ቅዱሳን ወፈላስያን፡፡

በግርፋትና በእስራት መታገሥን ከሰማዕታት ተማረ እንደ አበው ቅዱሳንም መሰደድን መረጠ፡፡

፸፫ ወዘንተ ኵሎ አቅማተ ጽጌ አስተጋቢኦ እምገድለ ቅዱሳን ገብረ ሎቱ ጸቃውዐ ዘይጥዕም ለዘአንበቦ ወይኤድም ለዘይሰምዖ፡፡

፸፫ ይህን ሁሉ የተጋድሎ አበባ ፍሬዎች ከቅዱሳን ገድል ሰብስቦ ላነበበው የሚጣፍጥ ለሰማውም ያማረ ወለላን ሠራለት፡፡

፸፬ በከመ ይቤ በመዝሙር ጥዑም ለጉርዔየ ነቢብከ እመዐር ወሶከር ጥዕመኒ ለአፉየ መዝ.፻፲፰፥፻፫

፸፬ በመዝሙር ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ እንዳለ፡፡ መዝ.፻፲፰፥፻፫

፸፭ ወካዕበ ይቤ "ወይትፈተው እምወርቅ ወእምዕንቍ ክቡር ወይጥዕም እመዐር ወሦከር ወገብርከሰ የዐቅቦ ወበዐቂቦቱ ይትዐሠይ ብዙኅ ወበዝኅ እንከ ፍሬ ምግባር ዘፈረየ በውስተ ውእቱ መካን፡፡ መዝ.፲፰፥፲ ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፸፭ ዳግመኛም ከወርቅና ከክቡር ዕንቍ ይልቅ ይወደዳል፤ ከስኳር ከመዐር ወለላም ይልቅ ይጣፍጣል፤ ባሪያህ ይጠብቀዋል በመጠበቁም ብዙ ዋጋ ይቀበላል አለ ፤ ስለዚህ በዚያ ቦታ ያፈራው የሥራ ፍሬ በዛ፡፡ መዝ.፲፰፥፲ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይኑር ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

## ምዕራፍ ፬

፩ ወእምድኅረ ጕንዱይ መዋዕል ተከዘ አኀው በእንተ ዘርሕቀ ፍኖት ዘመቅድሐ ማይ እስመ አልቦቱ ማይ ለውእቱ ደብር ወይቤሎሙ በጸሎተ ሚካኤል ንዑ ክርዩ ኀበ ዝንቱ መካን ወይቤልዎ አኀው እፎኬ ንከሪ ኀበ ኰኵሕ ይቡስ ሕቀ ንወርድ ውስተ ምድር ሠናይ ዘቦ ሣዕር፡፡

፪ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እስመ በይቡስ ይሴባሕ እግዚአብሔር ቀዳሚኒ በአውፅአ ማይ እምኰኵሕ በኮሬብ በእደ ሙሴ ቍልዔሁ ወካዕበ በአውፅአ ማይ እምሰሌዳ እብን በውስተ ቤተ ሞቅሕ በእደ እንድርያስ ወማትያስ አርዳኢሁ ወእምዝ ነሥአ አብ ክቡር ምርጕዘ በእደዊሁ ወደጐጸ ለውእቱ መካን፡፡

፫ ወእምዝ አኀዙ ይከርዩ አኀው መነኮሳት ወአኮ እንዘይትአመኑ ለአውፅኦማይ አላኢይትዐደዉ ትእዛዞ ዘይመስሎሙ ዘበከ ይጸምዉ፡፡

## ምዕራፍ አራት

፩ ከብዙ ዘመንም በኋላ የውኃ መቅጃው መንገድ ስለራቀ ወንድሞች አዘኑ፡፡ ያ ደብር ውኃ አልነበረውምና አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ኑ ከዚህ ቦታ ቆፍሩ አላቸው ወንድሞችም ከደረቅ ዐለት ላይ እንዴት እንቆፍራለን? ሣር ወደ አለበት ወደ መሬት እንወርዳለን አሉት፡፡

፪ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እግዚአብሔር መጀመሪያ በወዳጁ በሙሴ እጅ በኮሬብ ከዐለት ውኃ በማፍለቅ ዳግመኛም በእስር ቤት በደቀ መዛሙርቱ በእንድርያስና በማትያስ እጅ ከድንጋይ ዐምድ / ምሰሶ/ በደረቁ በማፍለቁ ይመሰገናልና አላቸው፡፡ ከዚያም ክቡር አባታችን መቋሚያውን አንሥቶ ያን ቦታ መታ መታ አደረገው፡፡

፫ ከዚህ በኋላ ወንድሞች መነኮሳይት ይቆፍሩ ጀመር የሚቆፍሩም ውኃ ለማውጣት አምነው አይደለም፤ በከንቱ የሚደክሙ ስለ መሰላቸው ትእዛዙን እንዳይተላለፉ ነው እንጂ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፬ ወከረይዎ በኀይል እንዘ ይትፈነቀል ኰኵሕ እምኰኵሕ ወአሚቆሙ መጠነ እመት ረከቡ መሬተ ፀዐዳ ይቡሰ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኀድግዎ ወኅደግዎ ወተከለ ውስቴቱ መስቀለ ወሰቀለ ላዕሌሁ ወንጌለ፡፡

፭ ወመሬቱሰ ይቡስ ከመሐመድ ዘአልቦቱ ጠል፡፡ ወአተወ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ውስተ ማኅደሩ፡፡ ወአኀውኒ አተዉ ለለ ማኅደሮሙ እንዘ ያንጐረጕሩ ወይቤሉ አጻመ ወነ በከንቱ፡፡

፮ ወእምዝ ፈጺሞ ጸሎቶ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሖረ በመንፈቀ ሌሊት ጽሚተ ኀበ ውእቱ መካን ዘአከረየ ወረከበ ማየ ጥዑመ ዘምሉእ እስከ አፉሁ ለግብ ወሦጠ ኰራሁውስቴቱ ወቀድሐ ማየ ወአተወ ውስተ ቤተ ክርስቲያን፡፡

፯ ወእምዝ ጸቢሖ ይቤሎሙ ለአኀው ነዑ ከመ ትርአዩ በረከተ እግዚአብሔር ወወሰዶሙ ኀበ ይእቲ ግብ ዘምልእት ማይ ወርአዩ አኀው ወሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ወለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገነዩ ሎቱ፡፡

፬ ድንጋይ በድንጋይ ላይ እየተፈነቀለም በኀይል ቆፈሩት፡፡ አንድ ክንድ ያህል ከቆፈሩ በኋላ ደረቅ የሆነ ነጭ አፈርን አገኙ፡፡ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ተውትም አላቸው በተውትም ጊዜ በውስጡ መስቀልን ተከለ በላዩም ወንጌል ሰቀለበት፡፡

፭ መሬቱም ርጥበት የሌለው እንደ አመድ ደረቅ ነበር አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ወደ ማደሪያው ተመለሰ፤ ወንድሞችም በከንቱ አደከመን ብለው እያዘኑ እየቤትአቸው ሔዱ፡፡

፮ ከዚህም በኋላ አባታችን በጸሎተ ማካኤል ጸሎቱን ፈጽሞ በሌሊት እኩሌታ ወደአስቆፈረበት ወደዚያ ቦታ በቀስታ /ብቻውን/ ሔደ፡፡ በጉድጓዱ አፍ ልክም የሞላ የሚጣፍጥ ውኃ አገኘ፡፡ ጽዋውንም ወደ ውስጥ አስገብቶ ውኃውን ቀድቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገባ፡፡

፯ ከዚያም ከነጋ በኋላ ወንድሞችን የእግዚአብሔርን በረከት ታዩ ዘንድ ኑ አላቸው፡፡ ውኃ ወደ ተመላበት ወደዚያች ጉድጓድም ወሰዳቸው ወንድሞችም አይተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ ለአባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ታዘዙለት፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፰ ወሰበሂ ይቄድስ ቍርባነ ሶበ ነጸረ ርደተ መንፈስ ቅዱስ ይኬልሐ ወይብል ይምጻእ መንፈስ ቅዱስ ወወፂዖ እምቍርባን ኢይሬእዮ ሰብእ በአፍኣ ወኢይትናገር ምስለ መኑሂ ኢይፈቀዶ ለሙቀተ ፀሐይ ወፍጡነ ይበውእ ውስተ ማኅደሩ፡፡

፰ ቅዳሴ ሲቀድስም የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ባየ ጊዜ አሰምቶ በመጮህ መንፈስ ቅዱስ ይምጣ ይል ነበር ከቍርባኑም ከወጣ በኋላ ሰው እያየውም ከማንም ጋር አይነጋገርም ነበር የፀሐይን ሙቀት አይሻውም፤ ፈጥኖ ወደ ቤቱ ይገባል እንጂ፡፡

፱ ወማኅደሩኒ ሙሱን ከመልጕተ ዐቀቤ ቀምሕ አልቦቱ መስኮት ዘይሬኢ ብርሃነ እሳት ወአልቦቱ መንጸፍ በዘይዴቅስ ወእምአመኮነ መነኮሰ ኢሰከበ በገቦሁ ለንዋም ዘእንበለ በእደዊሁ፡፡

ማደሪያውም እንደ ፍሬ ጠባቂ ጐጆ ደሳሳ ነበር የእሳት ብርሃንን የሚያይበት መስኮት የለውም፤ የሚተኛበት ምንጣፍም አልነበረውም፤ ከመነኮሰ ጀምሮ በእጁ ላይ እንጂ በጐኑ አልተኛም፡፡

፲ ወአመ መጽአ ድካም ይነውም ንስቲተ እንዘ ንቡር ወእምዝ ይተግህ ኵሎ ሌሊተ ወኢያፀርዕ ቃለ መጻሕፍት እምአፍሁ ወኢያነትግ ጸልዮ ዘምስለ አንብዕ፡፡

፲ ድካም በተሰማው ጊዜ ተቀምጦ ትንሽ ይተኛል፡፡ ከዚያም ሌሊቱን ሁሉ ለጸሎት ይተጋል፤ የመጻሕፍትን ቃል ከአፉ አያቋርጥም ከእንባም ጋር ጸሎትን አያስታጉልም ነበር፡፡

፲፩ ወእምዝ ኀለየ በልቡ ቃለ እግዚእነ ዘይቤ "ዘኢኀደገ አባሁ ወእሞ ወውሉዶ ወብእሲቶ ወኢይደሉ ሊተ ወኢይክል ይጸመደኒ ዘኢያጥብአ ወዘኢነሥአ መስቀለ ሞትየ ኢይክል ከዊነ ረድእየ፡፡
ማቴ.፲፥፴፯፤ ሉቃ.፲፬፥፳፮

፲፩ ከዚህም በኋላ በልቡ አባቱንና እናቱን፣ ሚስቱንና ልጆቹን ያልተወ ለእኔ አይገባም ሊያገለግለኝም አይችልም ያልጨከነ ለሞት የሚያበቃውንም መከራ ተቀብሎ ያልተከተለኝ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም ያለውን የጌታን ቃል አሰበ፡፡ ማቴ.፲፥፴፯፤ ሉቃ.፲፬፥፳፮

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፪ ወዘንተ ኵሎ ተዘኪሮ ወረደ ምድረ ትግራይ ኀደገ አባሁ ወእሞ ከመይርአዮ ለአብ ኢየሱስ ክርስቶስ ኀደገ አዝማዲሁ በሥጋ ከመይኩንዎ ዘመደ ሰራዊተ ብርሃን፡፡

፲፪ ይህን ሁሉ አስቦ አባቱ ኢየሱስ ክርስቶስን ያየው ዘንድ አባትና እናቱን ትቶ ወደ ትግራይ ምድር ሔደ፡፡ የብርሃን ሠራዊት ዘመድ ይሆኑት ዘንድ የሥጋ ዘመዶቹን ተወ፡፡

፲፫ ኀደገ ርስተ ዘበምድር ከመትኩኖ ርስተ ኢየሩሳሌም ዘበሰማያት ኀደገ ንዋየ ዘዓለም ከመያጥሪ አክሊለ ዕንቌ ባሕርይ ዘበላዕሉ፡፡

፲፫ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ርስት ትሆነው ዘንድ በምድር ያለ ርስትን ተወ፡፡ በላይኛው ዓለም ያለ የዕንቍ አክሊልን ገንዘብ ያደርግ ዘንድ የዚህን ዓለም ገንዘብ ተወ፡፡

፲፬ ኀደገ አልባሰ ዘይኤድሞ ለዐይን ወለብሰ አጽርቅተ ርሱሐ ወማዕሳተ ጥቁባተ ከመ ይልበስ ልብሰ መርዓ ወይትዐጸፍ ሜላተ ብርሃን ወመነነ ሰብሳበ ምድር ከመይርአይ ከብካበ ዘበሰማያት፡፡

፲፬ ለዐይን ደስ የሚያሰኘውን ልብስ ትቶ የሙሽራ ልብስና የብርሃን ሐር ይጐናጸፍ ዘንድ ያደፈ ጨርቅንና የተሰፋ ቁርበትን ለበሰ፡፡ በሰማያት ያለ የክብር ሙሽርነትን ያይ ዘንድ ምድራዊ ሙሽርነትን ናቀ፡፡

፲፭ ተአንገደ እመካን ውስተ መካን ዘእንበለ መስነቅት ወኢኀብሰት ለሲሳየ ዕለቱ ወየዐውድ መካናተ ቅዱሳን ወቀዲሙ በጽሐ መካነ ዳሞ፡፡

፲፭ ለዕለት ምግቡ እንጀራና የስንቅ መያዣ ሳይዝ ከቦታ ወደቦታ ተንከራተተ፡፡ በቅዱሳንም ቦታ ይዞራል አስቀድሞ ደብረ ዳሞ ደረሰ፡፡

፲፮ ወነበረ ህየ እንዘያነብብ መጻሕፍተ ሐዲስ ወብሉይ ወያበይን ፍካሬሆሙ፡ኒ በጽሒቀ ልብ ወእምብዝኀ አንብቦ መጻሕፍት ተመልሐ አነዳ ልሳኑ ከመ ቀቀበ መጥባሕት ወበዝኒ ኢኀደገ አንብቦ መጻሕፍት፡፡

፲፮ በዚያም የብሉይና የሐዲስ መጻሕፍትን እያነበበ ተቀመጠ ከልቡም በትጋት ትርጉማቸውን ይመለከት ነበር፡፡ መጻሕፍትንም ማንበብ ከማብዛቱ የተነሣ የአንደበቱ ቆዳ እንደ ሰይፍ ማጎደር /ሰገባ/ ተላጠ፡፡ በዚህም መጻሕፍትን ማንበብን አልተወም፡፡

፲፯ ወእምዝ ተግኅሠ ወበጽሐ ቤተ አባ መጣዕ ወነሥአ በረከቶ ለብፁዕ ሊባኖስ ወነበረ ኀዳጠ መዋዕለ እንዘ ይተግህ በአንብቦ መጻሕፍት፡፡

፲፯ ከዚያም ተነሥቶ ወደ አባ መጣዕ ቤት ደረሰ፤ የብፁዕ ሊባኖስ በረከትንም ተቀበለ፤ መጻሕፍትንም በማንበብ እየተጋ በዚያ ጥቂት ተቀመጠ፡፡

፲፰ ወእምዝ ፈለሰ ወበጽሐ መካነ ቅፍርያ ወእምዝኒ ፈለሰ መካነ ቋአት ወእመካነ ቋአት ውስተ መካነ በአልተቤሐት ወእመካነ በአልተቤሐት ውስተ መቀሌ ወእመካነ መቀሌ ውስተ መካነ ጌፆ ኀበ ገብረ ናዝራዊ ፍቁሩ ወኀበ በጽሐ መካን ይገብር ሎቱ ጾማዕተ ወይተግህ መዐልተ በአንብቦ መጻሕፍት ወይትማሕለል በጾም ወበጸሎት ከመ ይክሥት ሎቱ እግዚአብሔር ምስጢረ ስዋሬሆን ለመጻሕፍት፡፡

፲፰ ከዚያም በኋላ ወደ ቅፍርያ ሔደ፡፡ ከዚያም ቋአት ወደሚባል ቦት ሔደ ከቋአትም ወደ በአልተቤሐት ከበአልተቤሐትም ወደ መቀሌ ከመቀሌም ወደ ወዳጁ ወደ ገብረ ናዝራዊ ጌፆ ደረሰ፡፡ በደረሰበትም ቦታ ለራሱ ማደሪያን ሠርቶ በመዓልትና በሌሊት መጻሕፍትን በማንበብ ይተጋል፤ እግዚአብሔር የተሰወረ የመጻሕፍትን ምስጢራቸውን ይገልጽለት ዘንድ በጾምና በጸሎት ይማለላል /ይለምናል/፡፡

፲፱ ወጾመ ፵ መዐልተ ወ፵ ሌሊተ እንዘ ኢይጥዕም ወኢምተኒ ዘእንበለ ሰንበታት ባሕቲቶን ከመይትከሠት ሎቱ ግብረተ ደብተራ ወተከሥተ ሎቱ በርእየ መንፈስ ቅዱስ ወኵሉ ንዋየ ግበሪሃ በከመ አርአዮ እግዚአብሔር ለሙሴ ከማሁ አርአዮ፡፡

፲፱ የድንኳንኑንም ሥራ ይገልጥለት ዘንድ ከሰንበት ቀናት በስተቀር ምንም ምን ሳይቀምስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ተገለጠለት የድንኳኗን ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳሳየው ለእርሱም እንዲሁ አሳየው፡፡

፳ ወካዕበ ጾመ ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ በከመ ቀዳሚ ሥርዐት ከመይትከሠት ሎቱ ሥነ ሕንጼሃ ለቤተ መቅደስ ዘገብረ ሰሎሞን ወተከሥተ ሎቱ በጸጋ እግዚአብሔር አምጣና ኑኃ ወግድማ ወአዘቅተ ጠፈራ አዕማደ ሳናጉግ ዘውስተ ኤልማ አርአያ ኪሩብ ዘውስተ ነቢተራ፡፡

፳ ዳግመኛም ሰሎሞን የሠራው የቤተ መቅደስ ሥራ ሕንፃ ውበት ይገልጽለት ዘንድ እንደ መጀመሪያው ሥርዐት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ በእግዚአብሔርም ጸጋ ወርዷ ቁመቷ፣ ስፋቷ፣ የጣራዋ መደምደሚያ፣ ምሰሶዎቿ፣ የኪሩብ አምሳል የሆነው ሁሉ ተገለጸለት፡፡

፷፩ ወሥዕለ በቍልት ዘውስቴታ ወድርኩኳት ወመአጽዊሃ ክልኤ ክልኤ ለለ አሐዱ ኆኅት ወሜላንታራ ዘውስተ ቀጸላሁ ወባሕር ዘብርት ዘይነብር ዲበ ዘበና ፲ወ፪ አልሕምተ ብርት ዘስብኮ ወሚኮኖት ዘየዐውዶ ከመ ማዕርት ወመስፈርተ ኵዲስ ወኪጥሮ ጋውሎስ ወኵሉ ንዋየ ግበሪሃ ለቤተ መቅደስ።

፷፩ የዘንባባው ሥዕል ሳንቃዎቿና መዝጊያዎቿ እያንዳንዱ መስኮት ሁለት ሁለት የሆኑት በጣራው ያለው ዘውድ በትከሻዋ ያለው ከብረት የተሠራው ባሕር ዐሥራ ሁለት የብረት ላሞች ምስል እንደመሸፈኛ ሆኖ የሚሠረው ሚካኖት የኵዲስና የኬጥሮ ጋውሎስ መስፈሪያ የቤተ መቅደስ አሠራርዋ ሁሉ ተገለጸለት።

፷፪ ወእምዝ ጾመ ፵ መዐልተ ወ፵ ሌሊተ ወተማሕለለ ይክሥት ሎቱ ሚጠተ ብርሃናት ወኑበሬ ኅዋኅወ ፀሐይ ዘሙፃኢሁ ወሙባኢሁ ወዑደታተ አቅማሪሁ።

፷፪ ከዚያም በኋላ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ፤ የብርሃናትን መመላስ፣ የፀሐይን መስኮቶች አቀማመጥ፣ መውጫውንና መግቢያውን የቍጥሩንም ዑደት ይገልጽለት ዘንድ ምሕላ ያዘ /ጸለየ/።

፷፫ ወተከሥተ ሎቱ በረድኤተ መንፈስ ቅዱስ ወእንዘ ይጼሊ በኑኀ ሌሊት ርእየ ምስጢራተ ሰማይ ዘሀሎ ጽሑፍ ውስተ መጽሐፈ ሄኖክ ወልደ ያሬድ።

፷፫ በመንፈስ ቅዱስም አጋዥነት ተገለጸለት ሌሊትም ሲጸለይ በያሬድ ልጅ በሄኖክ መጽሐፍ የተጽፎ ያለ የሰማይ ምስጢርን አየ።

፷፬ ርእየ ኅዋኅወ ፀሐይ ወመሳክወ ወእንዘ የዐውድ በዘይመጽእ ለሐበ ፀሐይ ወከመ ያውዒ ሠረገላተ።

፷፬ የፀሐይን መመላለሻና መስኮቶች ዙሮ በሚመለስበትም የፀሐዩ ሙቀት ሠረገላዎቹን እንደሚያቃጥል አየ።

፳፭ ወርአየ ሠረገላተ ነፋስ ዘይጸውርዎ መላእክት ዘይሜግብዎ ወኮበብ እንዘ ይመርሖ ወርእየ ሰሪቆቶ ዘከመ ያስተባሪ ለለአውራኂሁ አመ ወርኀሜናሰን ዘበራብዕ ወርኅ ኆኅተ እስከ ወርኃ አዴር፡፡

፳፭ በእርሱ ላይ የተሾሙ መላእክት የተሸከሙት የነፋስ ሠረገላዎችን አየ ኮከብም ይመራው ነበር፤ በየወሮቹም ከሚያዝያ ከአራተኛው ወር እስከ አዴር ወር እንዴት እንደሚፈራረቅ አየ፡፡

፳፮ ርእየ ዘከመ የሐጽጽ መዐልት እምሌሊት ወእም ወርኀ ተሰሪን ቀዳማይ ኮኑን ቀዳማይ በመስፈርተ ሑረቱ ለፀሐይ ርእየ ከመ ይፈደፍድ መዐልት እምሌሊት እምወርኀ ኒሳን እስከ ወርኀ ሐዜራን ርእየ ዘከመ ይዔሪ መዐልት ወሌሊት በወርኀ ኤሎል ወበወርኀ አዴር፡፡

፳፮ በታኅሣሥ ወር ቀኑ ከሌሊቱ እንደሚጐድል በመጀመሪያ በፀሐይ ምሕዋር አሰፋፈር መዓልቱ ከሌሊቱ እንደሚረዝም ከሚያዝያ ወር እስከ ወርኃ አዜራ ያለውን ሁሉ አየ፤ በመስከረምና በመጋቢት መዓልቱና ሌሊቱ እንደሚስተካከል አየ፡፡

፳፯ ርእየ ሚጠተ ብርሃናት ዘልደተ ወርኀ ወዘከመ ይመልእ ሐምስተ ብርሃን እምዕለተ ዕርቃኑ እስከ ዕለተ ገሀሁ ወዘከመ ይትወሀቦ ብርሃን በመስፈርት፡፡

፳፯ የብርሃናትን መመላለስና የጨረቃን ልደት ከብርሃን ከጐደለችበት ቀን ጀምሮ አምስት እጅ ብርሃን እንደሚመላ በመስፈሪያም ብርሃን እንደሚሰጠው አየ፡፡

፳፰ ርእየ ሑጸጻሁኒ ዘበሠለስቱ ትሕማሰ እምዕለተ ምልአተ ብርሃን እስከ ዕለተ ይተርፍ በከመ ዐውዱ፡፡ እስመ በመደልው ጥበቡ ለእግዚአብሔር ተሰርአ ዓለም፡፡

፳፰ በየሦስቱ ደረጃ ብርሃን ከመላበት ባዶ እስከሚቀርበት የብርሃኑን ምልአትና ጉድለት በዙሪያው እንዴት እንደሚስልበት አየ ዓለም በእግዚአብሔር የጥበብ መለኪያ ተሠርቶአልና፡፡

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳፱ ርእየ ሙያጤሁ ፍናዊሁ ወሰሪቆቶ ዘይትወላወል እምኖኅት ኀበ ኖኅት ወአኮ ከመ ፀሐይ ዘይሠርቅ በ፴ ጽባሕ ዘበአሐቲ ኖኅት አላ የዐውድ ኲሎ ኀዋኀወ በ፴ ጽባሕ ርእየ ኬክሩሳተ መዋዕል በ፬ ክፍል ወሐምስ ዘሚጠተ ፀሐይ ርእየ ከንትሮሳተ አዝማን ዘበ፬ ክፍል ዘኑባሬ ዓመት ዘበበ ፯ ወአሐቲ ዕለት፡፡

፳፱ የመንገዱን መመላለሻ አወጣጡን ከበር ወደ በር አመላለሱን አየ፤ እንደ ፀሐይ በሠላሳ ቀን በአንድ መስኮት ብቻ አይወጣም፤ በሠላሳው ቀን ሁሉ በሮቹን ይዞራል እንጂ፡፡ በአራት ክፍልና በአምስት የፀሐይ መመላለሻ የሚሆነውን የኬክሮስ ዘመን አየ፡፡ በየዘጠና አንድ ቀን የከንትሮስን ዘመን የዓመቱን አቀማመጥ አየ፡፡

፴ ርእየ መሳክወ ነፋሳት ፲ ዘመንገለ ጽባሕ ፲ ዘመንገለ ዐረብ ፲ ዘመንገለ ጽባሕ ፲ ዘመንገለ አዜብ፡፡

፴ በምሥራቅ በኲል ዐሥር በምዕራብ በኲል ዐሥር በሰሜን በኲል ዐሥር በደቡብም በኲል ዐሥር የነፋሳት መስኮቶቹን አየ፡፡

፴፩ ወሶበ ተከሥተ ሎቱ ዝንቱ ኲሉ ምስጢረ ሰማይ እንዘ ይጼሊ በሌሊት ከልሐ በዐቢይ ቃል ወይቤ ኦ ሄኖክ ከመዝኑ ውእቱ ብሩህ ምስጢረ ራእይከ ወከመዝኑ ውእቱ ከሡት ስዋሬ ኅቡኣቲከ

፴፩ ይህ ሁሉ የሰማይ ምስጢር በሌሊት እየጸለየ በተገለጠለት ጊዜ ከፍ ባለ ቃል ሄኖክ ሆይ የራእይህ ምስጢር እንደዚህ ብሩህ ነውን የምስጢርህስ መሰወር እንዲህ ግልጥ ነውን አለ፡፡

፴፪ አማንኬ ሐዋርያ ዘይቤ ኲሉ ዘኀጥአ ለጥበብ ለይስአል ኀበ ወሀቢ እግዚአብሔር ዘይሁብ ለኲሉ በስፉሕ እንዘ ኢይትዔየር ወኢይዘረኪ ወይትወሀብ ሎቱ፡፡ ያዕ.፩፥፭

፴፪ ሐዋርያ ጥበብን ያጣት ሰው ቢኖር ሳይገዳደር ሳይነፍግ ለሁሉ በሰፊው የሚሰጥ ለጋስ እግዚአብሔርን ይለምን ይሰጠዋል ያለው እውነት ነው፡፡ ያዕ..፩፥፭

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፫ ወዓዲ ወጠነ ከመይጹም ወይትመሐለል ፵ መዐልተ ወ፵ ሌሊተ ከመ ይክሥት ሎቱ ራእየ ትንቢቱ ለዳንኤል ነቢይ፡፡

፴፫ ዳመኛም የነቢዩ ዳንኤልን የትንቢቱን ራእይ ይገልጥለት ዘንድ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ይጾምና ይማለል ጀመር፡፡

፴፬ ወእምድኅረ ሰቡዕ መዋዕል እምዘወጠነ ጸዊመ መጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ኢኮነ ለከ መክፈልተ አእምሮ ፍካሬ ትንቢቱ ለዳንኤል ነቢይ እስመ ሀብተ ጸጋሁ ውእቱ ለናትናኤል፡፡

፴፬ ጾም ከጀመረ ከሰባት ቀን በኋላም ከሰማይ የነቢዩ ዳንኤልን የትንቢት ትርጉም የማወቅ ዕድል የአንተ አይደለም ይህን የመተርጐም ጸጋ የተሰጠው ለናትናኤል ነውና የሚል ቃል መጣ፡፡

፴፭ ወበጽባሕ ጸውዖ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለናትናኤል ወልዱ ወይቤሎ እስመ ሀብተ ጸጋ ተውህበ ለከ እምኀበ እግዚአብሔር ከመ ትፈክር ትንቢተ ዳንኤል ነቢይ፡፡

፴፭ በነጋም ጊዜ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ልጁ ናትናኤልን ጠርቶ የነቢዩ የዳንኤልን ትንቢት ትተረጉም ዘንድ ሀብተ ጸጋ ተሰጥቶሃል እኮን አለው፡፡

፴፮ ወእምዝ በርሀ ኅሊናሁ ከመ ማኅቶተ መብረቅ ወፈከረ ትንቢተ ለዳንኤል ነቢይ እምጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ፡፡

፴፮ ከዚያም በኋላ ልቡ እንደ መብረቅ ብልጭታ/ብርሃን/ በራለት የነቢዩ የዳንኤልንም ትንቢት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ተረጐመ፡፡

፴፯ ወተሠውጠ ላዕሌሁ መንፈሰ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል በከመ ተሠውጠ መንፈሱ ለሙሴ ላዕለ እያሱ መንፈሰ ኤልያስ ላዕለ ኤልሳዕ፡፡

፴፯ የአባታችን በጸሎተ ሚካኤልም መንፈስ፣ የሙሴ መንፈስ፣ በኢያሱ፣ የኤልያስም መንፈስ በኤልሳዕ ላይ እንዳደረ በእርሱ ላይ አደረ፡፡

፴፰ ስምዐ ኮነ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወነገሮሙ ለደቂቁ እንዘ ይብል ኅደረ ቃለ መጻሕፍት ውስተ ከርሥየ በፍቅረ እግዚእየ ወሶበ እጸርሕ ወእብል አባ ወአቡየ ፫ ጊዜ ወይጸርሕ በውስተ ነፍስየ እንዘ አፉየ ያረምም፡፡

፴፰ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ምስክር ሆኖ ለልጆቹ በጌታዬ ፍቅር የመጻሕፍት ቃል በልቡናዬ አደረ ብሎ ነገራቸው፡፡ ሦስት ጊዜም አባ አባቴ ብዬ በጮሁ ጊዜ አፌ ሳይገለጥ ዝም ብሎ ሳለ በነፍሴ ይጮኻል፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፻፱ ለለ ፍጻሜ ጸሎትየ ከመዝኒ ይትናገረኒ ወይሰጠወኒ እግዚእየ ዝ ቃል ኀደረ ላዕሌየ ወይጸርሕ ለለ መዋዕል ጊዜ ጸሎት፡፡

፻፱ በጸሎቴም መጨረሻ እንደዚህ ይነግረኛል፤ ጌታዬ ይመልስልኛል፡፡ ይህ ቃል በእኔ ስላደረ በጸሎት ጊዜ በየ ጊዜው ይሰማል፡፡

፺ ወእምዝ ኀለየ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ከመ ይትአጸው ኵሉ ዓለም በግዘቶሙ ለሐዋርያት በእንተ ዘይሁብ ክህነተ በሕልያን ጳጳስ፡፡

፺ ከዚህ በኋላ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል በመማለጃ /ጉቦ/ ክህነት በሚሰጥ ጳጳስ ምክንያት በሐዋርያት ግዝት ዓለም ሁሉ እንደሚዘጋ ዐሰበ፡፡

፺፩ ወሖረ ኀቤሁ ለአባ ዮሐንስ ጳጳስ ወተባረከ እምኔሁ ወይቤሎ ጳጳስ ዳኅንኑ አ ወልድየ በጸሎተ ሚካኤል ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እወ ዳኅን ወይቤሎ ጳጳስ በእንተ ምንት መጻእከ፡፡

፺፩ ወደ ጳጳሱ አባ ዮሐንስም ሔዶ ከእርሱ ተባረከ ጳጳሱም ልጄ በጸሎተ ሚካኤል ደኅና ነህን? አለው፡፡ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም አዎን ደኅና ነኝ አለው፡፡ ጳጳሱም መልሶ ስለምን መጣህ? አለው፡፡

፺፪ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ብየ ኑዛዜ በእንተ ትካዘ ርእስከ ወበእንተ ትካዘ ርእስየኒ ወተግኅሠ ኵሉ ሰብእ ወተርፉ ክልኤሆሙ፡፡

፺፪ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ስለ አንተና ስለ እኔ ጉዳይ ዐስብ አለኝ አለው፡፡ ሰው ሁሉ ሔዶ ሁለቱ ብቻ ቀሩ፡፡

፺፫ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለጳጳስ ኢሰማዕከኑ ዘይቤ ጴጥሮስ ርእሰ ሐዋርያት በመጽሐፈ ሲኖዶስ ምቱር ውእቱ ዘነሥአ ወዘወሀበ ክህነተ በሕልያን፡፡

፺፫ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ጳጳሱን የሐዋርያት አለቃ ጴጥሮስ በሲኖዶስ መጽሐፍ በመማለጃ ክህነትን የተቀበለና የሰጠ የተለየ ነው ያለውን አልሰማህምን አለው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፻፬ ወካዕበ ኢሰማከኑ ዘከመ አውገዘ ለሲሞን መሰርይ ሶበ አምጽአ ወርቀ ታሕተ እግሪሆሙ ለሐዋርያት እንዘ ይብል በሉ ኅበ ወደይኩ እዴየ ይረድ መንፈስ ቅዱስ

፻፬ ዳግመኛም እጄን በጫንሁበት መንፈስ ቅዱስ ይወርድ ዘንድ ተናገሩ ብሎ በሐዋርያት እግር ወርቁን አምጥቶ ባፈሰሰው ጊዜ ሲሞን መሠርይን እንዳወገዘው አልሰማህምን

፻፭ ወይቤሎ ጴጥሮስ ወርቅከሰ ወብሩርከ ምስሌከ ለይኩን ለሕርትምና ይመስለከኑ ዘበወርቅ ትሣየጦ ለጸጋ እግዚአብሔር እስመ ሕምዘ መሪር እሬእየከ ሐዋ.፰፥፲፱

፻፭ ጴጥሮስም ወርቅህና ብርህ ለጥፋት ይሁንህ የእግዚአብሔርን ጸጋ በወርቅ የምትገዛ ይመስልሀልን? አለው፤ በመራራ መርዝ ተመርዘህ አይሃለሁና፡፡ ሐዋ.፰፥፲፱

፻፮ ስማዕ ኦ አባ አይኑ ለማይ ለእመ ኮነ ሕሙገ የሐምግ ኲሎሙ ውሒዘ ማይ ወለእመ ኮነ ጽሩየ ይከውን ጽሩየ ኲሉ ውሒዘ አፍላግ፡፡

፻፮ አባቴ ሆይ የውኃ ምንጭ የደፈረሰ እንደሆነ የሚፈስሰው ውኃ ሁሉ ይደፈርሳል፡፡ ምንጩ ንጹሕ ከሆነ የውኃው ፈሳሽም ሁሉ የጠራ ይሆናል፡፡

፻፯ ወለእመ አንተ ቦእከ ውስተ ግዘቶሙ ለሐዋርያት ኲሉ ዓለም ይከውን ውጉዘ፡፡

፻፯ አንተ በሐዋርያት ውግዘት ብትገባ ሁሉም የተወገዘ ይሆናል፡፡

፻፰ ተምዐ ጳጳስ ወይቤ አንተኑ ትከውነኒ መምህረ አላ አንተ ተመሀር እምኔየ፡፡

፻፰ ጳጳሱም ተቆጥቶ አንተ ከእኔ ተማር እንጂ ለእኔ መምህር ትሆነኛለህን? አለ፡፡

፻፱ ወተፈጸመ እምኔሁ ቃለ እግዚአብሔር ዘይቤ በወንጌል አሌ ለከሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን እለተአጽዉ ቅድመ ገጹ ለሰብእ አንቀጸ መንግሥተ ሰማያት ለሊከሙኑ ኢትበውኡ ወለእለሂ ይበውኡ ትከልእዎሙ በዊአ፡፡ ማቴ.፳፫፥፲፬

፻፱ በወንጌል እናንተ ግብዞች ጸሐፍትና ፈሪሳውያን መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም ከመግባት ትከለክሏቸዋላችሁ ያለው የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ ላይ ተፈጸመ፡፡ ማቴ.፳፫፥፲፬

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፶ ወመጽሐፈ ሲኖዶስኒ ይብል ኤጲስ ቆጶሰ ዘይሜህር ዘእንበለ ሕግ ኢኮነ ኤጲስ ቆጶሰ አላ ሓሳዌ ክርስቶስ፡፡

፶ መጽሐፈ ሲኖዶስም ያለ ሕግ የሚያስተምር ኤጲስ ቆጶስ ኤጲስ ቆጶስ አይደለም በክርስቶስ ላይ የሚዋሽ ነው እንጂ ይላል፡፡

፶፩ ወካዕበ ይቤ በወንጌል አንትሙ ውእቱ ጼዉ ለምድር ወእመሰ ጼው ለስሐ በምንት እንከ ይቄስምዎ አልቦኬ እንዘ ዘይበቍዕ ዘእንበለ ዘይገድፍዎ አፍአ ወይከይድዎ ሰብእ በእገሪሆሙ አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም፡፡ ማቴ.፭፥፲፫

፶፩ ዳግመኛም በወንጌል እናንት የምድር ጨው ናችሁ ጨው አልጫ ከሆነ እንግዲህ በምን ያጣፍጡታል? እንግዲህ የሚጠቅመው የለም ሰዎች ወደ ውጭ አውጥተው ይጥሉታል በእግራቸው ይጠቀጥቁታል እንጂ የዓለም ብርሃን እናንት ናችሁ፡፡ ማቴ.፭፥፲፫

፶፪ ወዘንተ ኲሎ አእሚሮ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሖረ ኀበ ካህናተ ደብተራ ወተናገሮሙ ከመ ያብእዎ ኀበ ንጉሥ፡፡

፶፪ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ይህን ሁሉ ዐውቆ ወደ ካህናተ ደብተራ ሔደ ከንጉሡም ያገናኙት ዘንድ ነገራቸው፡፡

፶፫ ወካህናተ ደብተራ ነገርዎ ለንጉሥ ወአብእዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ጸልመት መንግሥትከ በግዘት እስመ ሐዋርያት ቀደሙ አውግዞ እመቦ ጥምቀተ አው ክህነተ ዘይሁብ ወዘይነሥእ በሕልያን፡፡

፶፫ የቤተ መንግሥት ካህናትም ለንጉሡ ነግረው አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን አስገቡት አባታችን በጸሎተ ሚካኤል መንግሥትህ በግዘት ጨለመች ሐዋርያት ጥምቀትም ቢሆን ወይም ክህነት በመማለጃ /ጉቦ/ የሚሰጥንና የሚቀበልን አስቀድመው አውግዘዋልና አለው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፺፬ | ወዝንቱሰ ጳጳስ አብዮ ትእዛዞሙ ናሁ ይሁብ ክህነተ በሕልያን ለእመ ጳጳስ ቦአ ውስተ ግዝቶሙ ለሐዋርያት ኲሎሙ እለ ተሰይሙ ወእለ ተጠምቀ በእዴሆሙ ውጉዛነ ይከውኑ ከማሁ ኲሉ ዓለም ቆመ ውስተ ግዘት፡፡ | ፺፬ | እነሆ ይህ ጳጳስ የሐዋርያትን ትእዛዝ ተላልፎ በጉቦ ክህነት ይሰጣል፤ ጳጳሱም በሐዋርያት ግዘት ከገባ በእጁ የተጠመቁና የተሾሙት ሁሉ የተወገዙ ይሆናሉ፤ እንደዚሁ ዓለሙ ሁሉ በውግዘት ውስጥ ይኖራል አለው፡፡ |
| ፺፭ | ወይቤሎ ንጉሥ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል አመ ይመጽእ ጳጳስ ነዐ አንተኒ ከመ ንትናገር ኅቡረ፡፡ | ፺፭ | ንጉሡም አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ጳጳሱ በመጣ ጊዜ በአንድነት እንናገርበት ዘንድ አንተም ና አለው፡፡ |
| ፺፮ | ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል በጽሐ ኀበ ንጉሥ ወአቡነ በጸሎተ ማካኤል ሖረ ህየ ወተናገሩ ንጉሥ ወጳጳስ እንዘ በባሕቲቶሙ በእንተ ዝንቱ ነገር፡፡ | ፺፮ | ከጥቂት ጊዜም በኋላ ጳጳሱ ወደ ንጉሡ ደረሰ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ከዚያ ሔደ፤ ንጉሡና ጳጳሱም ብቻቸውን ሆነው ስለዚህ ነገር ተነጋገሩ፡፡ |
| ፺፯ | ወይቤሎ ጳጳስ ለንጉሥ ዝንቱሰ በጸሎተ ሚካኤል ይፈቅድ ይሰአረነ ሊተ እምሢመትየ ወለከሰ እምንግሥትከ ስማዕ ኦ ወልድየ ዘእነግረከ አዘዝ ይእስርዎ ወይሰድዎ ምድረ ትግራይ፡፡ | ፺፯ | ጳጳሱም ንጉሡን ይህ በጸሎተ ሚካኤል እኔን ከሹመቴ አንተንም ከመንግሥትህ ሊሽረን ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ልጄ ሆይ የምነግርህን ስማኝ አስረው ወደ ትግራይ ይወስዱት ዘንድ እዘዝ አለው፡፡ |
| ፺፰ | ወይቤ ንጉሥ ይኩን በከመትቤ ወአዘዘ ይእሰርዎ ያብእዎ ወያብጽሕዎ ምድረ ሳርድ ወይሞቅሕዎ በጽኑዕ መዋቅሕት ወገብሩ ላእካነ ንጉሥ በከመ ተአዘዙ ወነበረ ህየ እሱረ ፪ ዓመተ፡፡ | ፺፰ | ንጉሡም አንተ እንዳልኸው ይሁን ብሎ በጽኑዕ ማሰሪያ አሰረው ወደ ሳርድ ያደርሱትና ያስገቡት ዘንድ አዘዘ፡፡ የንጉሡም መልእክተኞች እንደታዘዙ አደረጉ በዚያም ሁለት ዓመት ታስሮ ቆየ፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፶፱ ወእምዝ ወሰድዎ ምድረ ጽራዕ ወወሀብዎ ለዐቃቤ ሰዓት ለመካነ ቈራር ወይቤልዎ ንሥኦ ለዝንቱ መነኮስ ወእስሮ በጽኑዕ መዋቅሕት በከመ ትእዛዙ ለንጉሥ፡፡

፶፱ ከዚያም ወደ ጽራዕ ምድር ወሰዱት ቈራር በተባለ ቦታ ለተሾመ ዐቃቤ ሰዓትም ሰጡት ይህን መነኩሴ ወስደህ እንደ ንጉሡ ትእዛዝ በጽኑ ማሰሪያ እሰረው አሉት፡፡

፷ ወሰሚዖ ዘንተ ፈርሀ ዐቃቤ ሰዓት ወአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ተፈሥሐ በመዋቅሕቲሁ፡፡

፷ ዐቃቤ ሰዐቱም ይህን ሰምቶ ፈራ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ግን በእስራቱ ተደሰተ፡፡

፷፩ ወሰብአ መካንኒ አፍቀርዎ ፈድፋደ ወፈቀዱ ይፍትሕዎ እምዋቅሕቲሁ ወአበዮሙ እንዘ ይብል ንጉሥ ዘአሰረኒ አንትሙ ትፈትሑኑ ወአነ እሱር ፫ተ ዓመተ፡፡

፷፩ የሀገሩም ሰዎች እጅግ ወደዱት ከእስራቱም ሊፈቱት ወደዱ፤ ንጉሥ የአሰረኝን እናንተ ትፈታላችሁን? እኔ ሦስት ዓመት እታሰራለሁ ብሎ አይሆንም አላቸው፡፡

፷፪ ወእምዝ ሖሩ ሰብአ ሀገር ኀበ ሥዩመ ጽራዕ ወይቤልዎ ለምንት ይነብር እሱረ ዝንቱ ብእሴ እግዚአብሔር ወይቤሎሙ ሥዩመ ጽራዕ ፍትሕዎ በከመ ፈቀድክሙ ወፈትሕዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡፡

፷፪ ከዚህ በኋላ የሀገሩ ሰዎች በጽራዕ ወደተሾመው መስፍን ሔደው ይህ የእግዚአብሔር ሰው እንደታሰረ ለምን ይቀራል? አሉት፡፡ በጽራዕ የተሾመውም እንደወደዳችሁ ፍቱት አላቸው አባታችን በጸሎተ ሚካኤልንም ፈቱት፡፡

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምሳሌነ አሜን፡፡

ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፭

## ምዕራፍ አምስት

፩ ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል ፈቀደ ይሑር ኀበ ወልዱ ሳሙኤል ወእንዘ የሐውር በጽሐ ገብረ ናዝራዊ ፍቁረ ቤቱ ሀየ ወበጽባሕ በሳኒታ ሖረ ኀበ ወልድ ሳሙኤል ወተቀበሎ ሳሙኤል ወምስለ ደቂቁ በዐቢይ ፍሥሓ፡፡

፩ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ወደ ልጁ ሳሙኤል ሊሔድ ወደደ፡፡ ሲሔድም ወዳጁ ገብረ ናዝራዊ ደረሰና አብረው አደሩ፤ በማግሥቱም በነጋ ጊዜ ወደ ልጁ ሳሙኤል ሔደ፡፡ ሳሙኤልም ከልጆቹ ጋር በታላቅ ደስታ ተቀበለው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፪ ወእምዝ ይቤልዎ ደቂቁ ንፈቅድ ነኊደ ኢየሩሳሌም ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሀገሮሙሰ ለቅዱሳን ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ተዐገሡ ደቂቅየ በከመ ይቤ ዳዊት ትዕገሡ ወአጽንዑ ልበክሙ፡፡

፪ ከዚያም በኋላ ልጆቹ ወደ ኢየሩሳሌም መሔድ እንፈልጋለን አሉት አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም የቅዱሳን ሀገራቸው ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ናት ልጆቼ ዳዊት ታገሡ ልባችሁንም አጽኑ እንዳለ ታገሡ አላቸው፡፡

፫ ወአሐተ ዕለተ እንዘይቄድስ ቍርባነ ርእዩ አኃው እንዘ ይከውን ኀብስት ዘዲበ ጻሕል ሕፃነ ብሩሀ ወይሰክብ ዲበ ጠረጴዛ ወአብ ክቡር በጸሎተ ሚካኤል ያውሕዝ አንብዐ ከመ ነቅዐ ማይ ወይበኪ ወይኬልሕ በጸሎተ ቅዳሴ፡፡

፫ አንድ ቀንም ሲቀድስ በጻሕሉ ላይ ያለው ኀብስት የሚያበራ ሕፃን ሆኖ በመንበሩ ተቀምጦ ወንድሞች አዩ፡፡ ክቡር አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እንባውን እንደ ውኃ ምንጭ ያፈሳል በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜም አሰምቶ ያለቅሳል፡፡

፬ ወሕፃን ይስሐቅ እንዘ ይሰክብ ዲበ ምሥዋዕ ከመ ሕፃን ዘይሰክብ ወይትፌሣሕ በነጽሮ እሙ፡፡ ወሶበ በጽሐ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኀበ ጸሎተ ፈትቶ ኅብስት ኮነ ሕፃን ዘይከሥት መናቅዕቲሁ ወይሜጥዎ ገበዋቲሁ ከመ ይገሥሦ ለፈትቶ፡፡

፬ ሕፃኑም እናቱን በማየት እንደሚደሰት ሕፃን በመሠዊያው ላይ ሆኖ ይስቃል፤ አባታችን በጸሎተ ማካኤልም ኅብስቱን ከሚፈትትበት በደረሰ ጊዜ ሕፃኑ መለያያውን የሚገልጥና ለመፈተት ይዳስሰው ዘንድ ጐኑን የሚሰጠው ሆነ፡፡

፭ ወሶበ ይፌትት ሥጋሁ ለሕፃን ይከውን ውስተ እዴሁ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኅብስተ ቍርባን ዘልማድ ወገበዋቲሁኒ ለሕፃን ኮነ እንከ ያስተርኢ በከመ ህላዌሁ ዘትካት በሥጋ ልምልምት ሥርዐተ ሕፃን ወአልቦ ዐሠረ ተጠብሖ ውስቴቱ ወኢይከውን ንትጋ በእንተ ዘነሥአ እምኔሁ፡፡

፭ የሕፃኑንም ሥጋ በፈተተው ጊዜ በአባታችን በጸሎተ ሚካኤል እጅ እንደልማዱ ቅዱስ ቍርባን ይሆናል፡፡ የሕፃኑም ጐኖች እንደ ቀድሞው በሕፃን ሥርዐት በለመለመ ሥጋ ይታይ ነበር፤ የመታረድ ምልክትም አይታይበትም ነበር ከእርሱም ስለወሰደ አይጐድልም ነበር፡፡

፰ ወኮነ እንከ ዘይሠወጥ ደሙ ውስተ ጽዋዐ መድኀኒት ወእለ ርእዩ አኀው ፈርሁ እምነጽሮ ዝንቱ ምስጢር ወአልቦ ዘተናገሩ ፩ ምስለ ካልኡ ሶበ ተፈጸመ ጸሎተ ቅዳሴ ተሰወረ ሕፃን እምአዕይንቲሆሙ ለአኀው ወተረፈ ፍተታተ ኀብስት ዲበ ጻሕል ወደመ ወይንኒ ውስተ ጽዋዐ መድኀኒት፡፡

፰ ደሙም በመድኀኒት ጽዋው ውስጥ ይጨመር ነበር የተመለከቱትም ይህን ምስጢር ከማየታቸው የተነሣ ፈሩ፡፡ አንዱ ከሌላው ጋር ምንም አልተናገሩም፤ የቅዳሴው ጸሎት በተፈጸመ ጊዜ ሕፃኑ ከወንድሞች ዐይን ተሰወረ፣ ተረፈ ኀበስቱ በጻሕሉ ላይ ደሙም በጽዋ ውስጥ ነበር፡፡

፱ ወተመጠዉ አኀው እምስጢረ ቅድሳት በትፍሥሕት ዘምስለ ፍርሀት ወበሐሤት ዘምስለ ረአድ ወወፂኦሙ እምቍርባን ተሰአልዎ አኀው ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወይቤልዎ ብፅዕት ከርሥ እንተ ጾረተከ ወብፁዓት አጥባት እለ ሐፀናከ ቡርክት ይእቲ ሰዓት እንተ ባቲ ተፀነስከ ወቡርክት ዕለት እንተ ባቲ ተወለድከ፡፡

፱ ወንድሞችም ከፍርሀት ጋር በደስታ ከመንቀጥቀጥም ጋር በሐሤት ሥጋውና ደሙን ተቀበሉ፤ ወንድሞች ሥጋውንና ደሙን ከተቀበሉ በኋላ ወጥተው አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ጠየቁት እንዲህም አሉት፡፡ አንተን የተሸከመች ማሕፀን ብፅዕት ናት፤ አንተን ያሳደጉ ጡቶችም ብፁዓት ናቸው፤ የተፀነስህባት ሰዓት የተባረከች ናት የተወለድህባትም ዕለት የከበረች ናት፡፡

፲ ርኢከኑ ዮም ዘገብረ ለከ እግዚአብሔር ዘከመ ተወለጠ ኀብስተ ቍርባን ለከዊነ ሕፃን ፍሡሕ ርኢናሁ ሶበ ትገሥሥ እንዘ ይትፌሣሕ ወሶበ ትፌትቶ እንዘ ይስሕቅ ወይሜጥወከ ገበዋቲሁ በተባርዮ ዲበ ምሥዋዕ፡፡

፲ የቍርባኑ ኀብስት የሚደሰት ሕፃን በመሆን እንደተለወጠ እግዚአብሔር ያደረገልህን አየህን? እኛ ስትዳስሰው ሲደሰት ስትፈትተውም ሲስቅ አካሉንም በጻሕሉ ላይ ተራ በተራ ሲሰጥህ አይተናል፡፡

፱ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሊተሰ ኢያስተርአየኒ በአምሳለ ሕፃን ዘእንበለ በከዊነ ኅብስት ዘልማድ ወባሕቱ አንሰ እትሐዘብ ከመ ነበረ ኑፋቄ ውስተ ልብክሙ እንዘ ትብሉ ይክልኑ ኅብስት ከዊነ ሥጋሁ ለክርስቶስ ወወይንኑ ከዊነ ደሙ ወበእንተዝ አስተርአየክሙ በአምሳለ ሕፃን እንዘ ይጠባሕ፡፡

፱ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ለኔስ እንደተለመደው በኅብስት መልክ ነው እንጂ በሕፃን አምሳል አይታየኝምን? አላቸው፡፡ ነገር ግን እኔ ኅብስቱ የክርስቶስ ሥጋ መሆን ወይኑም ደሙ መሆን ይችላልን? ስትሉ በልባችሁ እንደተጠራጠራችሁ አስተዋልሁ፤ ስለዚህም በሕፃን አምሳል ሲሠዋ ታያችሁ አላቸው፡፡

፲ ወይቤልዎ ናስተበቍዐከ ከመ ኢይቀድስ ለነ ካልእ ዘእንበሌከ እምዝ ዳግመ ወይቤልዎ ካዕበ ንፈቅድ ንስእለከ ፩ ነገረ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል በሉ ተሰአሉኒ ዘፈቀድክሙ፡፡

፲ እነርሱም ከዛሬ ጀምሮ ከአንተ በስተቀር ሌላ ሰው እንዳይቀድስ እንለምንሃለን አሉት፡፡ ዳግመኛም አንድ ነገር ልንጠይቅህ እንወዳለን አሉት፤ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም በሉ የወደዳችሁትን ጠይቁኝ አላቸው፡፡

፲፩ ወይቤልዎ ቅዱሳን ነገርኮኑ ለንጉሥ በእንተ ዘአውሰበ ብእሲተ አቡሁ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወኢተናገርክዎ እምቅድመዝሰ እስመ በሙቃሔ ነበርኩ በማእሰር ጽኑዕ፡፡

፲፩ ቅዱሳኑንም የአባቱን ሚስት ስላገባ ለንጉሡ ነግረኸዋልን አሉት አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም በጽኑ ማሰሪያ ታስሬ በእስር ስለነበርሁ ከዚህ በፊት አልነገርሁትም አላቸው፡፡

፲፪ ወይቤልዎ ቅዱሳን ንገሮ ይእዜ ወኢትፍርሆ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አነ እነግሮ ወኢይፈርሆ ለእመ ሠምረ እግዚአብሔር ወለእመ ይሰምዐኒ ውእቱ፡፡

፲፪ ቅዱሳንም ዛሬ ንገረው አትፍራው አሉት አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም መልሶ እግዚአብሔር ቢፈቅድ እርሱም ቢሰማኝ እነግረዋለሁ አልፈራውም አላቸው፡፡

፲፫ ወይቤሉ ቅዱሳን ወለእመቦ ብእሲ ዘጠብአ ወዘለፎ ለንጉሥ እንዘ ይብል ኢይደልወከ ታውሰብ ብእሲተ አቡከ ወኢይከውኖ ስምዐ እመቀሠፍዎ አው ለእመ ኰነንዎ አው ለእመ አሰርዎ ወወሰድዎ አው ለእመ ቀተልዎ በእንተ ዝንቱ፡፡

፲፫ ቅዱሳኑም የአባትህን ሚስት ልታገባ አይገባህም ብሎ ንጉሡን የዘለፈውና ለመገሠጽም የጨከነ ሰው ቢኖር ቢገርፉት ወይም ቢያሰቃዩት አስረው ቢወስዱት ወይም ስለዚህ ነገር ምክንያት ቢገሉት ሰማዕትነት አይሆንለትምን? አሉት፡፡

፲፬ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ይከውኖ ስምዕ እወ ወባሕቱ ንጹም ወንጸሊ ወንትማሐለል ከመ ያክህለነ እግዚአብሔርጸዊረ ጻማ፡፡

፲፬ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል አዎን ሰማዕትነት ይሆንለታል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር መከራውን ሁሉ መሸከም እንዲያስችለን እንጹም እንጸልይ ምሕላም እንያዝ አላቸው፡፡

፲፭ ወእንዘ ነሐውር ኢንንሣእ ስንቀ ለፍኖትነ ወኢመስነቀተ ለሙዳየ ሲሳይነ ወኢመንጸፈ ለገበዋቲነ ወኢአሣእነ ለእገሪነ፡፡

፲፭ ስንሔድም ለመንገዳችን ስንቅ፣ ለምግባችንም መያዣ ከረጢት፤ /አቁማዳ/ ለጐናችን ምንጣፍ ለእግራችንም ጫማ አንያዝ፡፡

፲፮ ወኢጽዋዐ በዘንሰቲ ማየ ወኢጻሕለ በዘንበልዕ ጸብሐ ኢይንሣእ ወኢመኑሂ እምኔከሙ ዘእንበለ በትር ባሕቲታ ዘውስተ እዴሁ ዘበማዕተበ መስቀል ዘላዕሌሁ ወዘእንበለ መከርየ ሐጺን በዘንከሪ ምድረ ወንቀብሮ ለእመቦ ዘሞተ እምአኀዊነ፡፡

፲፮ ውኃ የምንጠጣበት ጽዋ በወጥ የምንበላበት ጻሕል አንያዝ ከእናንተ አንዱ ስንኳ በላዩ ላይ የመስቀል ምልክት ካለበት በእጁ ካለች መቋሚያ ብቻና ከወንድሞች አንዱ ቢሞት መሬቱን ቆፍረን ከምንቀብርበት የብረት መቆፈሪያ በስተቀር ሌላ አይያዝ፡፡

፲፯ ወሐሩ በዘከመዝ ግብር በጻማ ፍኖት እንዘ ይትመነደቡ ወቦ አመ ይበይቱ ጽዉማኒሆሙ ወቦ አመ ይትወከፍዎሙ፡፡

፲፯ በዚህም ሁኔታ በየመንገዱ እየተቸገሩ ሔዱ፤ ጾማቸውን የሚያድሩበት ጊዜ አለ ሰዎች የሚቀበሏቸውም ጊዜ አለ፤

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፫ ወይቤ አሐዱ እምደቂቁ ዘስሙ እንድርያስ ተስእልክዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወእቤሎ ተከሥተኑ ለከ እምኀበ እግዚአብሔር ኦ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ከመ ይወርድ ላዕሌነ ረድኤተ መንፈስ ቅዱስ ከመ ንጹር ሕማማተ ስምዕ በእንተ ትእዛዛቲሁ ወኲነኔሁ ወሕጉ ለእግዚአብሔር፡፡

፲፫ ከደቀ መዛሙርቱም መካከል አንዱ ስሙ እንድርያስ የሚባለው እንዲህ አለ፤ አባታችን በጸሎተ ማካኤልን ጠየቅሁት፤ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ሆይ ስለ እግዚአብሔር ትእዛዝ፣ ፍርድና ሕግም መከራውን ሁሉ እንሸከም ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ረድኤት በእኛ ላይ እንደሚወርድ ከእግዚአብሔር ተገለጠልህን? አልሁት፡፡

፲፬ ወይቤለኒ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወተከሥተ ሊተ ከመ ይወርድ ላዕሌነ መንፈስ ረድኤት፡፡

፲፬ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም የመንፈስ ቅዱስ ረድኤቱ በእኛ ላይ እንደሚወርድ ተገልጦልኛል አለኝ፡፡

፲፭ ወሶበ ተሰአሉኒ አኀው ወይቤሉኒ ለእመ ዘለፎ ለንጉሥ በእንተ ብእሲተ አቡሁ ይከውኖኑ ስምዐ ወእቤሎሙ እወ ይከውኖ ወውእተ ጊዜ ርኢኩ እንዘ ይወርድ መንፈስ ቅዱስ ዲበ ኲሎሙ፡፡

፲፭ ወንድሞችም የአባቱን ሚስት በማግባቱ ንጉሡን ቢዘልፈው ሰማዕትነት ይሆንለታልን ብለው በጠየቁኝ ጊዜ አዎን ይሆንለታል አልኋቸው ያን ጊዜም መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ላይ ሲወርድ አየሁ፡፡

፲፮ ወሖሩ ቅዱሳን ምስለ አቡነ በጸሎተ ማካኤል በረኀብ ወጽምዕ ወበኲሉ ዐጸባ ወበጽሑ እምሀገረ ትግራይ ኀበ ሀገረ ሴዋ እንተ ትሰመይ ሰወን እስመ ህየ ሀሎ ንጉሥ፡፡

፲፮ ቅዱሳንም ከአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ጋር በረኀብ፣ በጥም፣ በብዙ ችግር ሔደው ከትግራይ ሀገር ሰወን ከምትባል ሀገር ሴዋ ደረሱ፤ ንጉሡ ከዚያ ነበርና፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳፪ ወሶበ በጽሑ ቅዱሳን ኀበ ተዐይነ ንጉሥ ወመጽአ ብእሲ ዘይትዋረዶ ጋኔን እንዘ ይረውጽ ዕራቆ ገዲፎ አልባሲሁ፡፡

፳፪ ቅዱሳኑም ከንጉሥ ከተማ በደረሱ ጊዜ ጋኔን የሚጥለው ሰው ልብሱን ጥሎ ራቁቱን እየሮጠ መጣ፡፡

፳፫ ወይጐዩ ሕዝብ እምቅድመ ገጹ እምፍርሀተ እበዲሁ ከመ ኢያሕስም ላዕሌሆሙ ከመ ኢይፍቅአሙ፡፡

፳፫ ሕዝቡም ከእብደቱ የተነሳ ፈርተው በላያቸው ክፉ እንዳያመጣባቸው እንዳይገምሳቸውም ከፊቱ ይሸሹ ነበር፡፡

፳፬ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ አሐውር እትቀበሎ ለዝንቱ አብድ ከመ ይምሀረኒ ምዕዳነ በዘይከውነኒ፡፡

፳፬ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እኔ በሚጠቅመኝ ገንዘብ ምክሩን ያስተምረኝ ዘንድ ይህን እብድ ልቀበለው እሔዳለሁ አለ፡፡

፳፭ ወይቤልዎ ቅዱሳን ዘገደፈ ነፍሶ እምእንባዜ ልቡ እፎ ይምዕደከ ወዘይሰድዶሙ ለሰብእ በአብትር ወበአእባን እፎ ለከ ይትቀበለከ በቃለ ተግሣጽ፡፡

፳፭ ቅዱሳንም አእምሮው ከመታመሙ የተነሳ ራሱን የጣለ ይህ እንዴት ይመክርሃል፤ ሰዎችን በበትርና በድንጋይ የሚያባርራቸው አንተን በምክር ቃል እንዴት ይቀበልሃል አሉት፡፡

፳፮ ወይቤሎሙ በጸሎተ ሚካኤል ኢሰማዕክሙኑ ዘይቤ ጳውሎስ እስመ አብዳኒሁ ለዝ ዓለም ኀረየ እግዚአብሔር ከመ ያስተኀፍሮሙ ለጠቢባን፡፡ ፩ ቆሮ.፩፥፳፯

፳፮ በጸሎተ ሚካኤልም ጳውሎስ "እግዚአብሔር ጥበበኞችን ሊያሳፍር የዚህን ዓለም ሰነፎች መርጧልና ሲል የተናገረውን አልሰማችሁምን? አላቸው፡፡ ፩ኛ ቆሮ.፩፥፳፯

፳፯ ወካዕበ ኢሰማዕክሙኑ ዘይቤ ያዕቆብ ሐዋርያ አጋንንትኒ የአምኑ ወይደነግፁ፡፡ ያዕ.፪፥፲፱

፳፯ ሁለተኛውም ሐዋርያው ያዕቆብ አጋንንት ያምናሉ ይደነግጣሉም ያለውን አልሰማችሁምን? ያዕ.፪፥፲፱

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳፰ ወግብረ ሐዋርያትኒ ይቤ ወቦ እምአይሁድ እለ አኀዙ ይዑዱ ወይርቅዩ ወይጼውዑ ሎሙ ለአጋንንት እኩያን በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይቤልዎሙ ናምሕለክሙ በስሙ ለኢየሱስ ዘጳውሎስ ይሜህር በስሙ። ወእሉ እለ ከመዝ ይገብሩ አይሁድ እሙንቱ ደቂቀ ሊቀ ካህናት ዘስሙ አስቄዋ ወሰብዐቱ እሙንቱ።

፳፰ የሐዋርያት ሥራም እንዲህ ይላል "ከአይሁድም አዙረው የሚረጩ ነበሩ ከክፉዎች አጋንንት ላይም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ይጠሩ ነበር። ጳውሎስ ስሙን በሚያስተምርበት በኢየሱስ ስም እናማጽናችኋለን እያሉ እሊህ እንዲህ ያደርጉ የነበሩት አይሁድም አስቄዋ የሚባለው የሊቀ ካህናቱ ልጆች ናቸው፤ እነርሱም ሰባት ነበሩ።

፳፱ ወተሰጥዎሙ ውእቱ ጋኔን እኩይ ወይቤሎሙ በኢየሱስኒ አአምን ወለጳውሎስኒ አእምሮ አንትሙኬ እንከ መኑ አንትሙ።

፳፱ ያም ክፉ ጋኔን በኢየሱስ አምናለሁ፤ ጳውሎስንም ዐውቀዋለሁ፤ እንግዲህ እናንተ እነማን ናችሁ? ብሎ መለሰላቸው።

፴ ወአብደ ላዕሌሆሙ ውእቱ ጋኔን እኩይ ወኀየሎሙ ወሞኦሙ ወአቍሰሎሙ ወፈቀዮሙ ወሰደዶሙ እምውእቱ ቤት ግብ.ሐዋ. ፲፱፥፲፫

፴ ያ ክፉ ጋኔን የያዘው ሰውም ተነሣባቸው አየለባቸው፤ አሸነፋቸው ገምሶ አቍስሎ ከዚያ ቤት አስወጥቶ አባረራቸው። ግብ.ሐዋ. ፲፱፥፲፫

፴፩ ወበወንጌልኒ ይቤ ወተመይጡ እልክቱ ሰብዓ እንዘ ይትፌሥሑ ወይብልዎ አጋንንትኒ ይትኤዘዙ ለነ በስምከ ወገነዩ ለነ። ሉቃ.፲፥፲፯

፴፩ በወንጌልም "እነዚያ ሰባው መልእክተኞች ደስ ብሎአቸው ተመለሱና አጋንንት በስምህ ታዘዙልን ተገዙልንም አሉት አለ። ሉቃ.፲፥፲፯

፴፪ ወዘንተ ብሂሎ ሖረ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኀበ ውእቱ ብእሲ ዘይትዋረዶ ጋኔን ወይቤሎ ንግረኒ በቀኍዔተ ነፍስየ በከመ አንበበከ እግዚአብሔር።

፴፪ ይህንም ብሎ አባትችን በጸሎተ ሚካኤል ጋኔን ወደሚያሳብደው ወደዚያ ሰው ሔደና እግዚአብሔር እንዳናገረህ ለነፍሴ ጥቅም የሚሆነውን ንገረኝ አለው።

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፫ ወይቤሎ ውእቱ ጋኔን እንዘ ይዘፍን በእገሪሁ ወይጠፍሕ በእደዊሁ በጸሎተ ሚካኤል ጽናዕ በዘሀሎከ ወጥባዕ በዘኀለይከ ወተጋደል በእንተ ጽድቅ ወኢትትመየጥ ድኅሪተ፡፡

፴፬ ወአንከሩ ቅዱሳን በእንተ ምዕዳነ ጽድቁ ዘወፅአ እምአፉሁ ለአብድ በጽንዐ ሃይማኖቱ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡፡

ጸሎቱና ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

፴፫ ያም ጋኔን በእግሩ እየዘፈነ በእጁም እያጨበጨበ በጸሎተ ሚካኤል ሆይ ባለህበት ጽና ባሰብኸውም ጨክን ስለ ጽድቅ ተጋደል ወደ ኋላም አትመለስ አለው፡፡

፴፬ ቅዱሳንም በአባታችን በጸሎተ ሚካኤል የሃይማኖት ጽናት ከእብዱ አፍ ስለወጣው የእውነት ምክር አደነቁ፡፡

ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፮

፩ ወእምዝ ተሰምዐ ዜና ቅዱሳን ከመ መጽኡ ኀበ ዐምደ ጽዮን ንጉሥ ወአዘዞሙ ንጉሥ ለመኳንንቲሁ መለመሳፍንቲሁ አርእስተ ሐራሁ ከመ ይምጽኡ ኀቤሁ ተሰርጊዎሙ በትርሲተ ክብር መስተጽዕናነ ሠረገላት በትርሲተ አራሆሙ፡፡

፪ ወሰብአ አፍራስኒ በትርሲተ አፍራሲሆሙ ምስለ ንዋየ ሐቅሎሙ ዘድልው ለጸብዕ ወሰብአ አእጋርኒ በትርሲተ ወላቲዊሆሙ ወኲያኒዊሆሙ ወአቅስስቲሆሙ ወቆሙ ቅድሜሁ ርሱያኒሆሙ ወአዘዘ ይእስሩ ቅድሜሁ አናብስተ ግሩማነ ወመፍርሀነ፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

፩ ከዚህ በኋላ ቅዱሳን ወደ ንጉሡ ዐምደ ጽዮን እንደመጡ ዜናቸው ተሰማ፡፡ ንጉሡም መኳንንቱን መሳፍንቱን፣ የሠራዊቱን አለቆች በክብር ሽልመው በሠረገላ ጭነው ጦራቸውንና ሰይፋቸውን ይዘው ወደ እርሱ ይመጡ ዘንድ አዘዛቸው፡፡

፪ ፈረሰኞችም ለሰልፍ እንደተዘጋጁ ሆነው ከጦራቸው ጋር ፈረሶቻቸውን ሽልመው እግረኞችም ጋሻቸውንና ጦራቸውንና ቀስቶቻቸውን ሽልመው ሁሉም ተሸልሞ በፊቱ ቆሙ፤ የሚያስፈሩና የሚያስደነግጡ አንበሶችን በፊቱ ያስሩ ዘንድ አዘዘ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፫ | ወዘንተ ኲሎ ገብረ ንጉሥ ከመ ይፍርሁ መነኮሳት ወይኅድጉ ተዛልፎቶ | ፫ | ንጉሡም መነኮሳቱ ይፈሩና እርሱን መዝለፋቸውን ይተዉ ዘንድ ይህን ሁሉን አደረገ፡፡ |
| ፬ | ወውቱሂ ለብሰ ልብሰ ዘየኀይድ አዕይንተ ወወደየ ግርማ መንግሥት ዲበ ርእሱ ወአሕጋላተ ወርቅ ውስተ አቍያጻ እደዊሁ ወሎቱኒ ጥቀ አዳም ሞገሰ ሥኑ ወመፍርህ አካለ ግርማሁ ወላሕይ መላትሒሁ ጥቀ ዐበይት አዕይንቲሁ፡፡ | ፬ | እርሱም ዐይን የሚያንጸባርቅ ልብስን ለበሰ፤ ግርማ መንግሥቱን የማያሳይ ዘውዱን በራሱ ላይ አደረገ፤ የወርቅ መከዳውን በእጁ አጠገብ አስቀመጠ፤ እርሱ ደም ግባቱ እጅግ ያማረና ግርማውም የሚያስፈራ ነው፡፡ ጉንጮቹ ያማሩ ዐይኖቹም በጣም ታላላቅ ነበሩ፡፡ |
| ፭ | ወእምዝ አዘዘ ያምጽእዎሙ ለቅዱሳን ወያብጽሕዎሙ ውስተ መንግሥቱ፡፡ | ፭ | ከዚህ በኋላ ቅዱሳንን ወደ መንግሥቱ እንዲያመጧቸው አዘዘ፡፡ |
| ፮ | አብእዎሙ ሐራሁ ወዐቀምዎሙ ቅድሜሁ እንዘ የዐውዶሙ ነጸብራቀ ወልታሁ ወማዕገተ ኵያንዊሁ፡፡ | ፮ | ከዚያም ወታደሮቹ አስገብተው የጋሻው ነጸብራቅና የጦሩ ወጥመድ እየዞራቸው ከፊቱ ቆሙ፡፡ |
| ፯ | ወአውሥአ ንጉሥ ወይቤሎሙ ለቅዱሳን በእንተ ምንት ግብር መጻእክሙ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል በእንተ ኑዛዜ ጽድቅ ንትናገር ምስሌከ፡፡ | ፯ | ንጉሡም መልሶ ስለምን ነገር መጣችሁ? አላቸው፤ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እውነትን ስለማጽናት ከአንተ ጋር ልንነገር ነው አለው፡፡ |
| ፰ | ወይቤሎሙ ንጉሥ በሉ ንግሩኒ ወአውሥአ ወይቤ በጸሎተ ሚካኤል በዐቢይ ቃል ወይቤ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ወእምዝ ነገሮ ለንጉሥ በአንተ ፍጥረተ ዓለም፡፡ | ፰ | ንጉሡም በሉ እስቲ ንገሩኝ አላቸው፡፡ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ከፍ ባለ ቃል መልሶ እንዲህ አለ፤ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ከዚያም አያይዞ ስለ ዓለም ፍጥረት ለንጉሡ ነገረው፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፱ ወእምዝ ነገሮ በእንተ ልደተ አበው ወበእንተ ርደተ አይኅ ዘኮነ በእንተ ኅጣውኢሆሙ ለዕጓለ እመሕያው::

፱ ከዚያ በኋላ ስለ አበው ልደት፣ በሰው ልጆች ኀጢአት ምክንያት ስለወረደው የጥፋት ውኃም ነገረው::

፲ ወእምድኅረዝ ነገሮ በእንተ ዜና አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ዘከመ አፍቀሮሙ እግዚአብሔር በእንተ ዐቂበ ትእዛዛቲሁ ወካዕበ ነገሮ ዘከመ ገፍትዖሙ እግዚአብሔር ለሰዶም ወገሞራ በእንተ ኅጣውኢሆሙ ለእለ ይነብሩ ኀቤሁ::

፲ ከዚያም የአብርሃምን የይስሐቅን የያዕቆብንም ታሪክ ትእዛዙን ስለጠበቁ እግዚአብሔር እንደወደዳቸው ነገረው:: ዳግመኛም እግዚአብሔር በሚኖሩባቸው ሰዎች ኀጢአት ሰዶምንና ገሞራን እንደገለበጣቸው ነገረው::

፲፩ ወካዕበ ነገሮ ዘከመ ወሀበ ሕገ እግዚአብሔር ወፈለጠ ሎቱ ማእከለ ዘያነጽሑ ወማእከለ ዘያረኩሱ ወማእከለ ዘይበልዑ ወማእከለ ዘኢይበልዑ ማእከለ ዘአውሰቡ ወማእከለ ዘኢያውሰቡ እስመ ከመዝ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከሙ ብእሲ ኀበ ኩሉ ሰብኡ ወሥጋሁ ዘይከውን ኢይባእ ከመ ይክሥት ኀፍረቶ::

፲፩ ዳግመኛም ሕግን የሰጠ እግዚአብሔር በሚያረክሱና በማያረክሱ በሚበሉና በማይበሉ መካከል እንደ ለየ ነገረው:: ባገቡትና ባላገቡትም መካከል ያለውን ነገረው:: እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎታልና፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ ሰው ኀፍረተ ሥጋውን ይገለጥ ዘንድ ወደ ሥጋ ዘመዱ አይቅረብ::

፲፪ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወኀፍረተ አቡከ ወኀፍረተ እምከ ኢትክሥት እስመ እምከ ይእቲ ኢትክሥት ኀፍረታ ወኢትክሥት አፍረተ አቡከ እስመ አፍረተ አቡከ ውእቱ:: ዘሌ.፲፰፥፯

፲፪ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ:: የአባትህን ኀፍረተ ሥጋና የእናትህን ኀፍረተ ሥጋ አትግለጥ እናትህ ናትና ኀፍረተ ሥጋዋን አትግለጥ የአባትህን ሚስት ኀፍረተ ሥጋ አትግለጥ የአባትህ ኀፍረተ ሥጋ ነውና:: ዘሌ.፲፰፥፯

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፫ ወበካልእኒ ገጽ ይብል ዘሰከበ ምስለ ብእሲተ አቡሁ ኀፍረተ አቡሁ ከሠተ ሞተ ለይሙት ክልኤሆሙ ጊጉያን እሙንቱ፡፡

፲፫ በሌላም ክፍል ከአባቱ ሚስት ጋር የተኛ የአባቱን ኀፍረት ገልጧልና መሞትን ይሙት ሁለቱም በደለኞች ናቸውና ይሙቱ ይላል፡፡

፲፬ ጳውሎስኒ ይቤ እፎኑ ትፈቅዱ እምጻእ ከሙ በበትርኑ አው በተፋቅሮ ወበየውህት ፩ቆሮ. ፬፥፳፩

፲፬ ጳውሎስም እንዴት ሆኜ ወደ እናንተ ልመጣ ትወዳላችሁ? በጸብ ነውን ወይስ? በፍቅርና በልብ ቅንነት አለ፡፡ ፩ቆሮ. ፬፥፳፩

፲፭ እስመ ይሰማዕ በላዕሌክሙ ዝሙት ወዝሙትኒ ዘከመዝ ዘኢይገብርዎ አረሚ ጥቀ ሀሎ አ ዘአውሰበ ብእሲተ አቡሁ

፲፭ በእናንተ ላይ ዝሙት ይሰማል፤ እንደዚህ ያለው ዝሙትም አረማውያን እንኳ የማያደርጉት ነው፤ የአባቱን ሚስት ያገባ አለና፡፡

፲፮ ወአንትሙሰ ምስለዝኒ ዕቡያን ወበእንተዝ ለምንት ፈድፋደ ኢለሀውክምዎ ከመ ያእትት እምኔክሙ ዘገብረ ዘንተ ግብረ ወአንሰ እመ ኢሀለውኩ በሥጋየ ምስሌክሙ በመንፈስየ ሀሎኩ ምስሌክሙ፡፡ ወናሁ እኳንኖ ከመ ዘሀሎኩ ለዘገብሮ ለዝንቱ ግብር፡፡

፲፮ እናንተስ ከዚህም ጋር ቢሆን ትዕቢተኞች ናችሁ፤ ስለዚህ ይህን ያደረገው ከእናንተ ይለይ ዘንድ ለምን እጅግ ያላዘናችሁበት እኔ በሥጋዬ ከእናንተ ጋር ባልኖር በመንፈሴ ከእናንተ ጋር አለሁ፤ እነሆ ከእናንተ ጋር እንዳለሁ ሁኜ ይህን ሥራ የሠራውን እፈርድበታለሁ፡፡

፲፯ አንገሊገክሙ በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስለ መንፈስየ ወምስለ ኀይለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥውዎ ለሰይጣን ከመ ይሥርዎ ሥጋሁ ወትድኀን መንፈሱ በዕለተ ምጽአቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ፡፡ ፩ቆሮ. ፭፥፩

፲፯ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተሰብስባችሁ በእኔ ሥልጣን በጌታችን ኀይል ለሰይጣን አሳልፋችሁ ስጡት፤ ሥጋውን ጐድቶት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ቀን ነፍሱ ትድን ዘንድ፡፡ ፩ቆሮ. ፭፥፩

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፰ ስማዕ እንግርከ ዘከመ ፈጠረ እግዚአብሔር ኲሎ ፍጥረተ ወወሀበ ሕገ ለሰብእ ወሥርዐተ፡፡

፲፰ እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ እንደ ፈጠረ ለሰዎችም ሕግንና ሥርዐትን እንደሰጠ እነግርህ ዘንድ ስማ፡፡

፲፱ ወእምሰብእኒ ለክርስቲያን ይብለነ እግዚአብሔር ከመ ኢንንሣእ ክልኤተ አንስተ ወከመ ኢናጥሪ ዕቁባተ ወከመ ኢንሑር ኀበ ብእሲተ ብእሲ ወኲሉ ትእዛዘ እግዚአብሔር ተጸርአ በኀቤከ ወእምኲሉሰ ዘየዐቢ አውሰብከ ብእሲተ አቡከ ወካልአተሂ አንስተ ዘብዙኀ ኍልቆን፡፡

፲፱ ከሰዎችም ለእኛ ለክርስቲያኖች እግዚአብሔር ሁለት ሚስቶች እንዳናገባ፣ ዕቁባትም እንዳናስቀምጥ፣ ወደ ሌላ ሰው ሚስት እንዳንሔድ አዝዞናል፡፡ በአንተ ዘንድ ግን ሁሉም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ተሽሮአል፡፡ ከሁሉም የበለጠ ደግሞ የአባትህን ሚስት አግብተሃል፡፡ ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ሌሎች ሚስቶችንም ይዘሃል፡፡

፳ ሰገለሂ ወማሪተ ኢኀደገ ወይቤ ንጉሥ መኑ ይእቲ ብእሲተ አቡየ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ዘንመንገሣ ይእቲ ብእሲተ አቡከ ውድም ረአደ፡፡

፳ ጥንቆላንና ሟርትንም አልተውህም ንጉሡም የአባቴ ሚስት ማን ናት አለ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም የውድም ረአ/ፈ አባትህ ሚስት ዘንመንገሣ ናት አለው፡፡

፳፩ ወይቤ ንጉሥ ወኢኮነ አቡየ ውድም ረአደ ኢወለደኒ ወዘንተ ያመክኒ ንጉሥ እስመ ይብሉ ሰብእ ከመ አኀወ አቡሁ ቅድመ ሰገደ ሰከበ ምስሌሃ ለእሙ ወእምኔሁ ተወልደ ይብልዎ ወበእንተዝ ይቤ ኢወለደኒ ውድም ረአድ፡፡

፳፩ ንጉሡም ውድም ረአድ አባቴ አይደለም፣ አልወለደኝም አለ፡፡ ንጉሡም ይህን ያመካኘ ሰዎች የአባቱ ወንድም አስቀድሞ በስግደት ከእርሱ እናት ጋር ተኝቶ የተወለደ ነው ስለሚሉ ነበር ስለዚህ ውድም ረአድ አልወለደኝም አለ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳፪ | ወተምዐ ንጉሥ ዐቢየ መዐተ ወሶበ ርእዩ መላሕቅተ ሐራሁ ለንጉሥ ከመ ተምዐ አኀዙ ይዝብጥዎሙ ለቅዱሳን፡፡ | ፳፪ | ንጉሡም ታላቅ ቁጣን ተቈጣ፤ የንጉሡ ሠራዊትም እንደ ተቈጣ ባዩ ጊዜ ቅዱሳኑን ይደበድቧቸው ጀመር፡፡ |
| ፳፫ | ወኮነ ሐከክ ዐቢይ ወሁከት እስከ ኢያጻምዕ ፩ ቃለ ካልኡ እምብዝኀ ከላሕ፡፡ | ፳፫ | ከጩኸቱ ብዛት የተነሣ አንዱ የሁለተኛውን ቃል እስከማይሰማበት ድረስ ታላቅ ኹከትና ክርክር ሆነ፡፡ |
| ፳፬ | ተንሥአ ንጉሥ እመንበሩ ወነሥአ ኲናቶ ወአኀደኀሙ ለቅዱሳን እምእለ ይዘብጥዎሙ ወይቤሎሙ ለሐራሁ ሑሩ ንሥእዎሙ በበ፩ዱ ወኢይትራከቡ ፩ዱ ምስለ ካልኡ በዛቲ ሌሊት ወበጽባሕ አምጽእዎሙ ኀቤየ፡፡ | ፳፬ | ንጉሡም ከተቀመጠበት ጦሩን ይዞ ተነሣና ቅዱሳንን ከሚደበድቧቸው ሰዎች አስተዋቸው፡፡ ሠራዊቱንም ሒዱ እያንዳንዱን ውሰዷቸው በዚህችም ሌሊት አንዱ ከአንዱ ጋር አይገናኙ፤ ሲነጋ ወደ እኔ አምጧቸው አላቸው፡፡ |
| ፳፭ | ወወሰድዎሙ ሐራሁ ለንጉሥ ወቤቱ ቅዱሳን ሕሙያኒሆሙ ወእንዘ ይተግሁ ወይጼልዩ ኀበ እግዚአብሔር ወበሳኒታ አምጽእዎሙ፡፡ ኀበ ንጉሥ ወዐቀምዎሙ ቅድመ ንጉሥ፡፡ | ፳፭ | የንጉሡም ወታደሮች ወሰዷቸው፤ ቅዱሳንም እንደታሰሩ ወደ እግዚአብሔር እየተጉና እየጸለዩ አደሩ፡፡ በማግሥቱም ወደ ንጉሡ አምጥተው ከንጉሡ ፊት አቆሟቸው፡፡ |
| ፳፮ | ወሶበ ርእዮሙ ንጉሥ ነደ ልቡ በመዐት ወአዘዘ ይዝብጥዎሙ ወይቅሥፍዎሙ ለለ፩ መነኮሳት በበ፺ ጥብጣቤ ወውሕዘ ደሞሙ ከመ ማይ፡፡ | ፳፮ | ንጉሡም ባያቸው ጊዜ ልቡ በቁጣ ነደደ፤ እያንዳንዳቸውን መነኮሳት በሰባት ጅራፍ ይደበድቧቸውና ይገርፏቸው ዘንድ አዘዘ፡፡ ደማቸውም እንደ ውኃ ፈሰሰ፡፡ |
| ፳፯ | ወወፅአ እሳት ኀበ ተቀሥፉ መካን ወአንበልበለ ውስተ ዴዴሁ ለንጉሥ ወነበረ ከመዝ እንዘ ይነደድ መዐልተ ወሌሊተ፡፡ | ፳፯ | ቅዱሳን ከተገረፉበት ቦታ ላይም እሳት ወጣና በንጉሡ እጅ ተቀጣጠለ፤ እንዲህም እየነደደ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ቆየ፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳፰ | ወደንገፀ ንጉሥ በእንተ ውእቱ እሳት ወአዘዞሙ ንጉሥ ለሰራዊቱ ከመ ይቅድሑ ማየ ፈለግ ወይክዐዉ ላዕሌሁ ለእሳት፡፡ | ፳፰ | ስለዚያም እሳት ንጉሡ ደነገጠ፤ ንጉሡም ሠራዊቱን የወንዝ ውኃ እንዲቀዱና በእሳቱ ላይ እንዲያፈስሱበት አዘዘ፡፡ |
| ፳፱ | ወሶበ ከዐዉ ላዕሌሁ ሰራዊተ ንጉሥ አስተርአየ ኀበ ሠለስቱ ገጸ መካን፡፡ | ፳፱ | የንጉሡም ሠራዊት ውኃ ባፈሰሱበት ጊዜ እሳቱ በሦስት ቦታ ሲነድድ ታየው፡፡ |
| ፴ | ወዓዲ አዘዞ ንጉሥ ከመ ይክዐዉ ላዕሌሁ መብዝኀተ ሕዝብ፡፡ | ፴ | ዳግመኛም ብዙ ሕዝብ መጥተው እንዲያፈስሱበት አዘዘ፡፡ |
| ፴፩ | ወሶበ ከዐዉ ላዕሌሁ ደገመ ዓዲ አስተርአየ እሳት ኀበ ፯ቱ ገጸ መካን፡፡ | ፴፩ | ባፈሰሱበትም ጊዜ ዳግመኛ እሳቱ ባለበት ቦታ ሲቀጣጠል ታየ፡፡ |
| ፴፪ | ወእምዝ አዘዘ ንጉሥ ከመ ይሚጡ ውሒዘ ፈለግ ዐቢይ ከመ ያጥፍእዎ ለእሳተ መዐቱ ለእግዚአብሔር | ፴፪ | ከዚህ በኋላ ንጉሡ የእግዚአብሔርን የቁጣ እሳት ያጠፉት ዘንድ ትልቁን የወንዝ ውኃ በቦዩ እንዲመልሱት አዘዘ፡፡ |
| ፴፫ | ወእምዝ ተነስነሰ ውእቱ እሳት ውስተ ኲሉ ገጸ መካን ወትቤሎ ንግሥት ዘንመንገሣ ለዐምደ ጽዮን ንጉሥ ትክልኑ በማይ ከመ ታጥፍአ ለእሳተ ቅንዐቱ ለእግዚአብሔር፡፡ | ፴፫ | ከዚያም ያ እሳት በቦታው ሁሉ ተሰራጨ፡፡ ንግሥቲቱ ዛንመንገሣም ንጉሥ ዐምደ ጽዮንን የእግዚአብሔርን የቁጣ እሳት በውኃ ልታጠፋው ትችላለህን? አለችው፡፡ |
| ፴፬ | ወእምዝ ወፅአ ጽንጽንያ ፀዐዳ ወነሰኮሙ ለአፍራስ ወለአብቅልት ወኮነ ሞተ እንሰሳ ብዙኀ በንስከተ ውእቱ ጽንጽንያ፡፡ | ፴፬ | ከዚህ በኋላ ነጭ ዝንብ ወጥቶ ፈረሶቹንና በቅሎዎቹን ነከሳቸው በዚያ ዝንብ ንክሻም ብዙ እንስሳት ሞቱ፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፭ ወእምዝ ፈርሀ ንጉሥ ወተግኅሠ ጽሚተ በሌሊት ምስለ ሕዘቢሁ፡፡

፴፭ ከዚህ በኋላ ንጉሡ ፈርቶ ከሠራዊቱ ጋር ሌሊት በቀስታ ሸሸ፡፡

፴፮ ወእምዝ አዘዘ ንጉሥ ከመ ይስድድዎሙ ለቅዱሳን እንዘ ሙቁሓን እሙንቱ ምስለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወያዕርግዎሙ ውስተ ሀገረ ጻወን እንተ ትሰመይ ደራ እንተ አልባቲ ሙፃእ ወኢሙባእ ዘእንበለ ፩ዱ እስመ ጸድፍ ዐበይ ይእቲ፡፡

፴፮ ከዚያም ንጉሡ ቅዱሳንን እንደታሰሩ ከአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ጋር ከአንድ ቦታ በስተቀር መውጫና መግቢያ ወደ ሌለበት ደራ ወደምትባል የጻወን ተራራ ያወጧቸው ዘንድ አዘዘ ታላቅ ገደል ናትና፡፡

፴፯ ወእለሂ ይነብሩ ላዕሌሁ ተንባለት እሙንቱ ወኢያእመርዎ ለክርስቶስ ቀተልተ ነፍስ እሙንቱ እመ ይትቤቀል ንጉሥ ይፌኑ ኀቤሆሙ ከመ ይትበቀሉ ሎቱ፡፡

፴፯ በዚያም የሚኖሩት አሕዛብ ናቸው፡፡ ክርስቶስንም አያውቁትም፤ ነፍሰ ገዳዮች ስለሆኑ ንጉሥ ከተበቀለ እነርሱ ይገድሉለት ዘንድ ወደ እነርሱ ይልክ ነበር፡፡

፴፰ ወሶበ በጽሐ ኀቤሆሙ ሰበከ ሎሙ ወንጌለ መንግሥተ ሰማያት ወአብርሀ ሎሙ ከመ ዐምደ ብርሃን ወአምኑ በስብከቱ ወይቤሉ አጥምቀነ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፡፡

፴፰ ወደ እርሱም በደረሰ ጊዜ የመንግሥተ ሰማያት ወንጌልን አስተማራቸው፡፡ እንደ ብርሃን ዐምድም አበራላቸው፡፡ በስብከቱም አምነው በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቀን አሉ፡፡

፴፱ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሑሩ ንግርዎ ለንጉሥ እንዘ ትብሉ አመነ በክርስቶስ ወይቤልዎ ሰብአ ደራ መኑ ያበውአነ ኀበ ንጉሥ፡፡

፴፱ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ሒዱና በክርስቶስ አምነናል ብላችሁ ለንጉሡ ንገሩት አላቸው፡፡ የደራ ሰዎችም ወደ ንጉሡ ማን ያስገባናል? አሉት፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፵ | ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሑሩ ኀበ ካህናተ ደብተራ ውእቶሙ ይነግርዎ ለንጉሥ፡፡ | ፵ | አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ወደ ካህናተ ደብተራ ሒዱ እነርሱ ለንጉሡ ይነግሩታል አላቸው፡፡ |
| ፵፩ | ወሖሩ ተንባለተ ደራ በከመ ይቤሎሙ በጸሎተ ሚካኤል ወበጽሑ ኀበ ካህናተ ደብተራ ወይቤልዎሙ ንፈቅድ ንጠመቅ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፡፡ | ፵፩ | የደራ ተንባለትም አባታችን በጸሎተ ሚካኤል እንደነገራቸው ሔደው ወደ ካህናተ ደብተራ ደረሱ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ልንጠመቅ እንፈልጋለን አሏቸው፡፡ |
| ፵፪ | ወሖሩ ካህናተ ደብተራ ወነገርዎ ለንጉሥ ዘከመ ይቤልዎሙ ተንባላተ ደራ፡፡ | ፵፪ | ካህናተ ደብተራም ሔደው የደራ ተንባላት እንደነገሯቸው ነገሩት፡፡ |
| ፵፫ | ወአዘዘ ንጉሥ ያብእዎሙ ኀቤሁ ለእሙንቱ ተንባላት ወይቤሎሙ ንጉሥ መኑ መሀረክሙ ከመ ትእመኑ በክርስቶስ ከመ ትኩኑ ክርስቲያነ ወይቤልዎ ተንባላት ሀሎ ኀቤነ ፩ዱ ሙቁሕ መነኮስ ዘመጽአ እምዝየ ውእቱ ነገረነ፡፡ | ፵፫ | ንጉሡም እነዚያን ተንባላት ወደ እርሱ ያመጧቸው ዘንድ አዘዘ፡፡ ንጉሡም ክርስቲያን ትሆኑ ዘንድ በክርስቶስ እንድታምኑ ማን አስተማራችሁ? አላቸው፡፡ ተንበላቱም /አሕዛብ/ መልሰው ከዚህ ወደ እኛ የመጣ አንድ እስረኛ መነኩሴ አለ እርሱ አስተማረን አሉት፡፡ |
| ፵፬ | ወይቤ ንጉሥ በጸሎተ ማካኤል ውእቱ ዘአነ ሰደድክዎ እምዝየ በእንተ ዘሆከ ታዕካ መንግሥትየ | ፵፬ | ንጉሡም ቤተ መንግሥቴን ስለ አወከ ከዚህ እኔ ያሳደድሁት በጸሎተ ሚካኤል ነው አለ፡፡ |
| ፵፭ | ወናሁ በህየኒ አእመነ ብዙኀነ ሚ እግበሮ ለዝ ሀዋኪ ወይቤሎሙ ለተንባላት ሑሩ ንበሩ በሕገ አበዊክሙ ወተመይጡ እሙንቱ ተንባላት ሕዙናኒሆሙ ኀበ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡፡ | ፵፭ | እነሆ በዚያም ብዙዎችን አሳመነ ይህን አዋኪ /ሁከተኛ/ ምን ላድርገው? ተንባላቱንም ሒዱና በአባቶቻችሁ ሕግ ኑሩ አላቸው፡፡ እነዚያም ተንባላት እያዘኑ ወደ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ተመለሱ፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፶፯ ወይቤሎሙ ኢትሕዝኑ ደቂቅየ ሑሩ ርሑቀ ብሔረ ኀበ አህጉር ዘቦን አብያተ ክርስቲያን ወይሑር ወይንሣእ ፩ ፩ ጥምቀተ ወይትመጠዉ እምስጢር ቅዱስ ወተመይጡ ዝየ፡፡

፶፰ ሖሩ ወገብሩ በከመ አዘዞሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወነሢአሙ ጥምቀተ ወተመጢዎሙ እምስጢረ ቅድሳት ተመይጡ ኀቤሁ በፍሥሓ ወነበረ እንዘ ይሜህሮሙ ተግሣጸ እግዚአብሔር፡፡

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፯

፩ ወሀሎ ፩ዱ እምኔሆሙ ዘያፈቅሮ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ዘስሙ አብርሃም ወእምድኅረ ተጠምቀ ሰመዮ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አብርሃም

፪ ወአሐተ ዕለተ ይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እፈቅድ ታሥግር ሊተ ዓሣ ወትፈኑ ኀቤየ እስመ በጽሐ በዓለ ትስብእቱ ለመድኀኒነ፡፡

፶፯ እርሱም ልጆቼ አትዘኑ አብያተ ክርስቲያናት ወደ አሉባቸው ሩቅ ሀገር ሒዱ፡፡ አንዱም አንዱ ጥምቀትን ይጠመቅ ሥጋውንና ደሙንም ይቀበል አላቸው እነርሱም ከዚያ ተመለሱ፡፡

፶፰ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እንዳዘዛቸው ሔደው አደረጉ ተጠምቀው ሥጋውንና ደሙንም ተቀብለው በደስታ ወደ እርሱ ተመለሱ እርሱም የእግዚአብሔርን ተግሣጽ እያስተማራቸው ተቀመጠ፡፡

ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይኑር ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

፩ ከተጠመቁ በኋላ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ስሙን አብርሃም ብሎ የሰየመው አባታችን በጸሎተ ሚካኤል የሚወደው ሰሙ አብርሃም የሚባል አንድ ሰው ነበር፡፡

፪ አንድ ቀንም አባታችን በጸሎተ ሚካኤል መድኀኒታችን ሰው የሆነበት በዓል ደርሷልና ዓሣ አጥምደህ ወደ እኔ እንድትልክልኝ እፈልጋለሁ አለው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፫ | ወሖረ አብርሃም በከመ ይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ከመ ይኅሥሥ ዓሣ እስመ ርሑቅ ውእቱ ፈለገ ዓሣ ወእምዕፁብ ረከበ እም ፬ዱ ብእሲ ወፈነወ ፫ ዓሣ ጥቡሰ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡፡ | ፫ | አብርሃምም አባታችን በጸሎተ ሚካኤል እንዳዘዘው ዓሣ ሊፈልግ ሔደ ዓሣ የሚገኝበት ወንዝ ሩቅ ነበርና በብዙ ጭንቅም ከአንድ ሰው አግኝቶ ሦስት የተጠበሰ ዓሣ ለአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ላከለት፡፡ |
| ፬ | ወሶበ አጐንደየ አብጽሖ ይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለቅዱሳን በጽሐ ሰዓተ ድራር ንባእ ውስተ ቤተ ምርፋቅ ከመ ኢይኅልፍ ሰዓተ ድራር ዘማኅበር ዘሥርዐተ ቅዱሳን፡፡ | ፬ | ዓሣውንም ማድረስ ባዘገየ ጊዜ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ቅዱሳንን የራት መመገቢያው ሰዓት ደረሰ፤ በቅዱሳን ሥርዐት መሠረት የማኅበሩ የመመገቢያ ሰዓት እንዳያልፍ ወደ ምርፋቅ ቤቱ እንግባ አላቸው፡፡ |
| ፭ | ወሶበ ቦኡ ውስተ ቤት ዘአስተዳለዉ ማዕዳተ መጠነ ንዴቶሙ ወእንዘ ይጼልዩ ጸሎተ ማዕድ ሰሐቀ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እስመ አእመረ በመንፈስ ተነብዮ ዘኀደረ ላዕሌሁ ዘገብረ በውስተ ፍኖት እስመ ላእኩ ለአብርሃም ዘያመጽእ ሎቱ ዓሣ ኅብአ ማእከለ ዕፀው ፩ ዓሣ እምሠለስቱ ዓሣት ጥቡባት | ፭ | እንደችግራቸው ማዕድ ወደአዘጋጁበት ቤት በገቡ ጊዜ የማዕድ ጸሎት ሲጸልዩ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ፈገግ አለ በእርሱ ላይ ባደረ የትንቢት መንፈስ በመንገድ ያደረገውን ዐውቋልና ዓሣ የሚያመጣለት የአብርሃም መልእክተኛው ከተጠበሱት ከሦስቱ ዓሣዎች አንዱን ዓሣ በእንጨት መካከል ሰውሮታልና፡፡ |
| ፮ | ወይቤልዎ ቅዱሳን ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ምንትኑ አስሐቀከ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እስመ ቦ ዘሰረቀኒ ዘበውስተ ፍኖት ኀደገ ፩ ዓሣ ወአምጽአ ሊተ ፪፡፡ | ፮ | ቅዱሳንም አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ያሳቀህ ምንድን ነው? አሉት፡፡ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም በመንገድ ዓሣ የሰረቀኝ ሰው አለ፤ አንዱን ዓሣ ደብቆ ሁለት ዓሣት አምጥቶልኛልና አለ፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፯ | ወእንዘ ዘንተ ይትናገር በጽሐ ላእከ አብርሃም ወየቤሎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ይቤለከ ንሣእ እሎንተአ ዓሣተአ እስመአ በብዙኀአ መንሥሥአ ረከብኩአ ወበእንተዝ አጐንደይኩ ፈንዎቶአ፡፡ | ፯ | ይህንንም ሲነጋገሩ ከአብርሃም የተላከው ሰው ደረሰ፤ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን እነዚህን ዓሣዎች ተቀበል በብዙ ፍለጋ ስለአገኘኋቸው ስለዚህ መላኩን አዘገየሁ አለህ አለው፡፡ |
| ፰ | ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እግዚአብሔር ያብዝኅ በረከቶ ወይቤሎ ለላእክ ሑር በውስተ ፍኖት ወሶበ ትትመየጥ ኢይምሠጥከ፡፡ | ፰ | አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እግዚአብሔር በረከረቱን ያብዛ አለ፡፡ መልእክተኛውንም ሒድ በተመለስህ ጊዜ ግን በመንገድ እንዳይነጥቅህ አለው፡፡ |
| ፱ | ወኢሦጦ ውስተ ልቡ ውእቱ ወልድ ለዝነገር ወሶበ በጽሐ ኀበ መካን ዘኀብአ ውስቴቱ ዓሣ ጥቡሰ ሰፍሐ እዴሁ ለተመጥዎቱ፡፡ | ፱ | ያም ልጅ ይህን ነገር በልቡናው አላስገባውም የተጠበሰውን ዓሣ ከደበቀበት ቦታ በደረሰ ጊዜ ለማንሣት እጁን ዘረጋ፡፡ |
| ፲ | ወኮነ ውእቱ ዓሣ ጥቡሰ ከይሴ ዐቢየ ተሐውሰ ወአንሥአ ርእሶ ይንስኮ ለውእቱ ወልድ | ፲ | ያም የተጠበሰ ዓሣ ታላቅ ዘንዶ ሆኖ ያን ልጅ ሊነክሰው ተነሣቶ ራሱን አንቀሳቀሰ፡፡ |
| ፲፩ | ወጐየ ውእቱ ወልድ እምገጸ ውእቱ አርዌ ምድር ወእንዘ ይጐይይ ይጸርሕ ወይብል ርድኡኒ ቅዱሳን በጸሎተ ሚካኤል ርድአኒ ወሶበ ሰምዑ ዘንተ ጽራሐ ተሐውኩ ቅዱሳን በድራረ ማኀበር ወአመ ይቤሉ ምንትኑ ዝንቱ ጽራሕ ዘውስተ ሀገር፡፡ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ማካኤል ንዑ ንፃእ ከመ ንርአይ ኀይለ እግዚአብሔር፡፡ | ፲፩ | ያም ልጅ ከዚያ እባብ ፊት ሸሸ ሲሸሽም ቅዱሳን ርዱኝ በጸሎተ ሚካኤል ርዳኝ እያለ ይጮህ ነበር፡፡ ቅዱሳንም በማኅበራት ላይ ሳሉ ይህን ጩኸት በሰሙ ጊዜ ታወኩ፡፡ በሀገሩ ያለ ይህ ጩኸት ምንድን? ባሉ ጊዜ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል የእግዚአብሔርን ኀይል እናይ ዘንድ ኑ እንውጣ አላቸው፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፪ ወሰበ ወፅኡ በጽሐ ውእቱ ወልድ ወሐቀፎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡፡

፲፪ በወጡም ጊዜ ያ ልጅ ደረሰ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልንም አቀፈው፡፡

፲፫ ወይቤሎ መሰለኒ ከመ ሰብእ አንተ ዘከማየ ወሰረቁ እምውስተ ዓሣት ዘአምጻእኩ ለከ ወሰበ ተመየጥኩ እንሥእ ወናሁ ይዴግነኒ በከዊነ አርዌ ምድር፡፡

፲፫ አንተ እንደ እኔ ያለ ሰው መሰልኸኝ ስለዚህ ካመጣሁልህ ዓሣ ሰረቅሁ አለው ላነሣውም ልወስደውም በተመለስሁ ጊዜ እነሆ የምድር እባብ ሆኖ ይከተለኛል አለው፡፡

፲፬ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ ኅጥእ ወአባሲ ወባሕቱ ተግሣጸ እግዚአብሔር አደንገፀከ በዝንቱ አርአያ ግሩም፡፡

፲፬ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል እኔ በደለኛና ኀጢአተኛ ነኝ ነገር ግን የእግዚአብሔር ተግሣጽ አስፈሪ በሆነ በዚህ አርአያ አስደነገጠህ አለ፡፡

፲፭ ወባረከ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ላዕለ ውእቱ አርዌ ምድር እንዘ ይብል ተመየጥ በኀይለ ኢየሱስ ክርስቶስ ኀበ ዘትካት ህላዌከ ተመይጠ ውእቱ አርዌ ምድር ወኮነ ዓሣ ጥቡሰ፡፡

፲፭ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ያንን አውሬ በኢየሱስ ክርስቶስ ኀይል ወደ ቀደመ ተፈጥሮህ /አኗኗርህ/ ተመለስ ብሎ ባረከው ያም አውሬ ተመልሶ / ተለውጦ/ የተጠበሰ ዓሣ ሆነ፡፡

፲፮ ወአንከሩ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ወሰገዱ ታሕተ እገሪሁ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ፡፡

፲፮ ሁሉም ቅዱሳን አደነቁ እግዚአብሔርን አመሰገኑ ከአባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እግር በታች ሰገዱ፡፡

፲፯ ወይቤሉ ዐቢየ ነቢየ አንሥአ ለነ እግዚአብሔር ሐዋርያ ሐዲሰ አንሥአ ለነ እግዚአብሔር ብእሴ ሰማያዌ ወመልአከ ምድራዌ አንሥአ ለነ እግዚአብሔር ሐራዌ ዘይጸብእ በእንተ ሃይማኖት ወመስተቃትላነ ዘይትቃተል በሰይፍ ዘውእቱ ቃለ እግዚአብሔር አንሥአ ለነ እግዚአብሔር ወቦኡ ቅዱሳን ውስተ ማኅበሮሙ

፲፯ እግዚአብሔር ታላቅ ነቢያን አስሣልን፤ እግዚአብሔር ሐዲስ ሐዋርያን አስሣልን፤ ሰማያዊ ሰውን ምድራዊ መልአክን እግዚአብሔር አስነሣልን፤ ስለ ሃይማኖት የሚዋጋና የእግዚአብሔር ቃል በሆነ ሰይፍ የሚጋደል አርበኛን እግዚአብሔር አስነሣልን፤ አሉ ቅዱሳንም ወደ ማደሪያቸው ገቡ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፰ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለቅዱሳን ምንትኑ ዘንገብር በእንተ ዝንቱ ዓሣ ለእመ ንፈቅድ ንብልዖ አስተርአየነ በአርአያ ከይሲ ወለእመ ንፈቅድ ንግድፎ አስተርአየ መንክራተ እግዚአብሔር ላዕሌሁ፡፡

፲፱ ንዑኬ ናሕርሮ በእሳት ሥጋሁ ወአዕፅምቲሁ ወንጽዐጦ በቅብዕ ወንደዮ ውስተ ቀርን ከመ ይኩን ፈውሰ

፳ ይቤ ፩ዱ እምአዕረግ እምድኅረዝ ርኢኩ በአዕይንትየ እንዘ ይኔጽሩ ዕዉራን፤ ወይነጽሑ ልሙጻን በሥጋ ዓሣ

፳፩ ወተሰምዐ ዜና መንክራቲሁ ኀበ ንጉሥ ወአዘዘ ንጉሥ ከመ ያፍልስዎሙ እምህየ ለቅዱሳን ወያብእዎሙ ውስተ ባሕር ዐቢይ ዘስሙ ዝዋይ ወባሕሩኒ ዕሙቅ ውእቱ፤ በቅልየቱ ወርኅበቱ ወኢይበውእዎ ዘእንበለ በሐብል፡፡

፳፪ ወአብእዎሙ ውስተ ደሴት ኀበ ይነብሩ ውስቴቱ ዓረሚ እለ ኢይአምሩ ሕገ ወሥርዐተ ወይበልዑ ዘሕሩድ ወዘኢሕሩድ ወይበልዑ በህየኒ ወባዕዳነሂ አራዊተ እለ ኢይበልዑ ወነበሩ ህየ በጾም ወጸሎት በብዙኅ ምንዳቤ እንዘ ይትቀነዩ ለእግዚአብሔር በልብ ጽፉቅ ወበአንብዕ ውዑይ፡፡

፲፰ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ቅዱሳንን ስለዚህ ዓሣ የምናደርገው ምንድን ነው? ልንበላው ብንፈልግ በእባብ መልክ ታይቶናል ልንጥለውም ብንፈልግ የእግዚአብሔር ተአምር በእርሱ ላይ ተገልጧልና አላቸው፡፡

፲፱ ኑና ሥጋውንና አጥንቱን በእሳት እናሳርረው፤ በዘይትም አጣፍጠን ለድውያን ፈውስ ይሆን ዘንድ በቀንድ

፳ ከታላላቆቹ አንዱ ከዚህ በኋላ በእሳት በአሳረሩትና በዘይት በለወሱት የዓሣ ሥጋ ዕውራን ሲያዩ ለምጻሞችም ሲነጹ

፳፩ የተአምራቱም ዜና በንጉሡ ዘንድ ተሰማ ንጉሡም ቅዱሳንን ከዚያ አሰድደው ስሙ ዝዋይ በሚባል ታላቅ ባሕር ውስጥ ያስገቧቸው ዘንድ አዘዘ ባሕሩም በጥልቀቱና በስፋቱ በጣም ጥልቅ ነው ያለ ገመድም አይገቡበትም፡፡

፳፪ ቅዱሳንንም ሕግንና ሥርዐትን የማያውቁ አረማውያን ወዳሉበት ደሴት አስገቧቸው እነዚያም አረማውያን በዚያ የታረደውንና ያልተረደውን ሌሎችም የማይበሉ አራዊትን ይበሉ ነበር፡፡ ቅዱሳንም በጾምና በጸሎት በብዙም ችግር፣ በጠነከረ ልብና በሚያቃጥል እንባ ለእግዚአብሔር እየተገዙ በዚያ ተቀመጡ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፷፫ ወእምዝ አዘዘ ንጉሥ ከመ ያውፅእዎሙ እም ባሕር ወአያደ ዐዋዴ እንዘ ይብል እሉአ ቅዱሳን ይስብኩአ በአድያመ ሴዋአ ወይምሀሩአ፡፡

፷፫ ከዚያ በኋላ ንጉሡ ከባሕሩ ያወጥዋቸው ዘንድ አዘዘ፡፡ እሊህ ቅዱሳን በሴዋ አውራጃ ይስበኩ ያስተምሩም ሲል ዐዋጅ አስነገረ፡፡

፷፬ ወሰበኩ ቅዱሳን ውስተ ኵሉ ምድረ ሴዋ ወአኀደግዎው አምልኮ ጣዖት ወሐቲተ ማርያን ወኵሎ ተረፈ ጣዖት፡፡

፷፬ ቅዱሳንም በሴዋ ምድር ሁሉ አስተማሩ ጣዖት ማምለክን፣ ጠንቋይ መፈለግን፣ ለጣዖት መሠዋትን ሁሉ አስተዋቸው፡፡

፷፭ ወእምዝ ይቤሎ ለ፩ዱ እምደቂቁ መሃይምን ኀሥሥ ሊተ መካነ ጽምወ ወይቤሎ ውእቱ መሃይምን እወ አባ እገብር ፈቃደከ ወኀሠሠ ሎቱ መካነ ስውረ፡፡

፷፭ ከዚህ በኋላ ካመኑ ልጆቹ አንዱን ሰው የሌለበት ባዶ ቦታ ፈልግልኝ አለው፡፡ ያም ምእመን አባት አዎን ፈቃድህን አደርጋለሁ አለው ስውር ቦታንም ፈለገለት፡፡

፷፮ ወወሰዶ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኀበ ውእቱ መካን ምስለ ውኁዳን ደቂቁ ወለባዕዳንሰ ደቂቁ አዘዞሙ ይእትዉ ለለመካናቲሆሙ ይስብኩ ውስተ ምድረ ሴዋ ወንጌለ መንግሥተ ሰማያት፡፡

፷፮ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልንም ከጥቂት ልጆቹ ጋር ወደዚያ ቦታ ወሰደው ሌሎች ልጆቹን /ደቀ መዛሙርቱን/ ግን በየቦታቸው ሔደው የመንግሥተ ሰማያት ወንጌልን ይሰብኩ ዘንድ አዘዛቸው፡፡

፷፯ ወሰበኩ ደቂቁ በከመ ተአዘዙ አኅደግምሙ ለሰብአ ሲዋ ተማርዮ ወሰገለ ወኵሎ ተረፈ ጣዖት ወአርሐቁ እምኔሆሙ ዝሙተ ወትዕግልተ ወኵሎ ዘይጸልእ እግዚአብሔር፡፡

፷፯ ደቀ መዛሙርቱም እንደ ታዘዙ አስተማሩ፡፡ የሴዋንም ሰዎች ሟርትን ጥንቆላንና ለጣዖት መሠዋትን አስተዋቸው፤ ከእነርሱም ዝሙትን፣ ቅሚያን፣ እግዚአብሔር የሚጠላውን ሁሉ አራቁ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳፰ ወንጉሥሰ ሖረ ብሔረ ፀር ከመ ይጽብኦሙ ለዕልዋኒሁ ወሰምዐ ንጉሥ ከመ ተመይጡ ኀበ ትምህርቱ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወኀበ ትምህርቶሙ ለደቂቁ፡፡ አዘዘ ይእስርዎሙ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወለደቂቁ፡፡

፳፰ ንጉሡም ጠላቶቹን ይወጋ ዘንድ ወደ ጠላት ሀገር ሔደ፡፡ ንጉሡም ሰዎቹ ወደ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ትምህርት እንደ ተመለሱ ሰማ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልንና ደቀ መዛሙርቱን ያስሯቸው ዘንድ አዘዘ፡፡

፳፱ ወአሰርዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል እምድኅረ ነበረ ውስተ መካን ጽምው ፪ተ ዓመተ ወስመ ሀገሩኒ ናርእት ወአሲሮሙ አንበርዎ እስከ ይገብእ ንጉሥ እምጸብእ፡፡

፳፱ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልንም ሁለት ዓመት በብቸኝነት ቦታ ከተቀመጠ በኋላ አሰሩት፡፡ የሀገሩም ስም ናርእት ይባላል ንጉሡ ከሰልፍ እስኪመለስ ድረስ አስረው አስቀመጡት፡፡

፴ ወሶበ አተወ ንጉሥ እምጸብእ አዘዘ ንጉሥ ያምጽእዎ ምስለ ኲሎሙ ደቂቁ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡፡ ወእምዝ ጸንሖሙ በትግርምቱ ከመ ያፍርሆሙ በዕበየ መንግሥቱ፡፡

፴ ንጉሡም /ከጦርነት/ በተመለሰ ጊዜ፤ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ከሁሉም ልጆቹ ጋር ያመጡት ዘንድ አዘዘ ከዚህ በኋላ በትግርምቱና በመንግሥቱ ክብር ያስፈራቸው ዘንድ ጠበቃቸው፡፡

፴፩ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለደቂቁ ኢትፍርሁ ኦ ደቂቅየ እስመ ዝሰ ትግርምቱ ለንጉሥ አኮ እምኀበ እግዚአብሔር አላ እምኀበ ጸላኢ ውእቱ እስመ ዘይትገረም በምክረ ሰይጣን ይትመዋእ በኀይለ እግዚአብሔር፡፡

፴፩ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ደቀ መዛሙርቱን ልጆቼ ሆይ ይህ የንጉሥ ማስፈራቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም ከጸላኢ ነው እንጂ በሰይጣን ምክር የሚያስፈራ በእግዚአብሔር ኀይል ድል ይነሣልና አላቸው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፪ ወፈርሀ አብአቶሙ ንጉሥ ቅድሜሁ እስመ ቀዳሚ አደንገፅዎ በዘለፋሁ:: ወለአከ ኀቤሆሙ ንጉሥ እንዘ ይብል ለምንትአ ኢትጸልዩ ሊተአ በከመ ይደሉ አስተብቍዖ ለነገሥት::

፴፪ ንጉሥሙ ከፊቱ ለማስገባት ፈራ:: በመጀመሪያ በዘለፋ አስደንግጠውት ነበርና ንጉሡም ለነገሥታት መጸለይ እንደሚገባ ሁሉ ለእኔም ለምን አትጸልዩልኝም? አላቸው::

፴፫ ወለአከ ኀቤሁ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እንዘ ይብል ለኲሉኑአ ለዘነግሠ ይደልዎ አስተብቍዖ ወለኲሉኑአ ለዘነበረ ዲበ መንበረ ምኲናን ይብልዎ መፍቀሬ እግዚአብሔር አኮኑ ሙሴ ወአሮን ተቃወምዎ ለፈርዖን ወአውረዱ ላዕሌሁ ወለዕለ ሰብአ ግብጽ ፲ወ፪ መቅሠፍተ:: ዘፀ. ፯፥፲፬

፴፫ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ለነገሠው ሁሉ መጸለይ ይገባልን? ብሎ ወደ ንጉሡ ላከ:: በፍርድ ዙፋን ላይ የተቀመጠስ የእግዚአብሔር ወዳጅ ይባላልን ሙሴና አሮን ፈርዖንን ተቃውመውት በእርሱና በግብጽ ሰዎች ላይስ ዐሥራ ሁለት መቅሠፍት አውርደው የለምን:: ዘፀ. ፯፥፲፬

፴፬ ወሳሙኤልኒ ይቤሎ ለሳኦል እስመ አስተሐቀርከ ቃለ እግዚአብሔር ወኤልያስኒ ተዛለፎ ለአክአብ ወከልአ ዝናመ በመዋዕሊሁ ፫ ዓመተ ወ፮ አውራኀ::

፴፬ ሳሙኤልም ሳኦልን የእግዚአብሔርን ቃል አቃለሃልና አለው፡ ኤልያስም አክአብን ዘልፎ በዘመኑም ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ዝናምን ከልክልዋል::

፴፭ ወሖረ ላእክ ወነገሮ ለንጉሥ ከመ ይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወለአከ ንጉሥ ኀበ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እንዘ ይብል ለኀጥእሰ ኢትጸልዩ ይቤ እግዚአብሔር::

፴፭ መልእክተኛውም ሔዶ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል እንዳለው ለንጉሡ ነገረው ንጉሡም ወደ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል እግዚአብሔር ለኀጢአተኛ አትጸልዩ ይላልን? ብሎ ላከ::

፴፮ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወምትኑ ኀጥእ ዘእንበለ ከመ ይሚጦ እግዚአብሔር ውስተ ንስሓ

፴፮ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እግዚአብሔር ወደ ንስሓ እንዲመልሰው ነው? እንጂ ኀጢአተኛ ምንድን ነው አለ::

፴፯ ወይቤሎ ለላእክ ሑር በሎ ለንጉሥ ኢይፈርህ ትግርምተከ ወኢየሐዝን ሥቃያቲከ እመኒ አዘዝከ ከመ ይርግዙኒ በኲናት እዜከሮ ለሕዝቅኤል ወእመኒ አዘዝከ ይብልዑኒ ለአናብስት እዜከሮ ለዳንኤል እመኒ አዘዝከ ይደዩኒ ውስተ እቶነ እሳት እዜከሮሙ ለአናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል፡፡

፴፯ መልእክተኛውንም ሒደህ ለንጉሡ ማስፈራሪያህን አልፈራም፤ በምታመጣውም መከራ አላዝንም በለው አለው፡፡ በጦር እንዲወጉኝ ብታዝዝ ሕዝቅኤልን አስበዋለሁ፤ አንበሶች እንዲበሉኝ ብታዝዝም ዳንኤልን አስበዋለሁ፤ ወደ እሳት እንዲጥሉኝ ብታዘዝም አናንያን፣ አዛርያንና ሚሳኤልንም አስባቸዋለሁ፡፡

፴፰ ወእመኒ አዘዝከ ይውሥሩኒ በሞሥርተ ዕፅ እዜከሮ ለኢሳይያስ ወእመኒ አዘዝከ ይውግሩኒ በአእባን እዜከሮ ለኤርምያስ ወእመኒ አዘዝከ ይምትሩ ክሳድየ በመጥባሕት እዜከሮ ለዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ ዘቀተሎ ሄሮድስ በእንተ ሄሮድያዳ ብእሲተ ፊልጶስ እኁሁ፡፡

፴፰ በእንጨት መቁረጫ መጋዝ እንዲቆርጡኝ ብታዝዝም ኢሳይያስን አስበዋለሁ፤ በድንጋይም እንዲወግሩኝ ብታዘዝ ኤርምያስን አስበዋለሁ፤ በሰይፍ አንገቴን እንዲቆርጡኝም ብታዘዝ በወንድሙ ፊልጶስ ሚስት ምክንያት የገደለው የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ መጥምቅን አስበዋለሁ፡፡

፴፱ ወእመኒ አምጻእከ ላዕሌየ ካልኣተ ሥቃያተ እዜከሮሙ ለሐዋርያት ቅዱሳን ወለሰማዕት መዋዕያን እለ ጾሩ ሕማማተ ዘዘዚአሁ፡፡ ይመስለከኑ በትግርምትከ ይቀንይዎሙ ለቅዱሳን ዘእንበለ በትሕትና ወቀደምትኒ ነገሥት አኮኑ ይትማሐለሉ ሶበ መጽአሙ ትንሣኤ ፀር ጐድጕዶሙ ጾማዕቶሙ ለቅዱሳን ከመ ይርከቡ ረድኤተ በውስተ ጸብእ፡፡

፴፱ ከዚህ የተለዩ መከራዎችን በእኔ ላይ ብታመጣብኝም ልዩ ልዩ መከራዎችን የተቀበሉ ቅዱሳን ሐዋርያትንና አሸናፊዎች ሰማዕታትን አስባቸዋለሁ፤ ቅዱሳንን ያለትሕትና በማስፈራራት የሚገዙአቸው ይመስልሃልን? የቀደሙ ነገሥታትስ ጠላት በተነሣባቸው ጊዜ በጦርነት ርዳታን /አጋዥ/ ያገኙ ዘንድ የቅዱሳንን ዋሻ አንኳኩተው ይማፀኗቸው የለምን?

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፷ ወአንተሰ ትትጌረም ላዕለ ቅዱሳን ይመስለከኑ ዘትትበአስ ምስሌነ ምስለ ነዳያን አኮኑ ምስለ እግዚአብሔር ዘትትበአስ እስመ ላዕሌሁ ገደፍነ ነፍሰነ ወሥጋነ ወሰሚዖ ንጉሥ እምኅበ ላእካን ዘንተ ነገረ ፈርሀ ዐቢየ ፍርሀተ፡፡

፷ አንተ ግን በቅዱሳን ላይ ታስፈራራለህ፤ /ትዝታለህ/ ከእኛ ከነዳያን ጋር የምትጣላ ይመስልሃልን? ከእግዚአብሔር ጋር የምትጠላ አይደለምን? ነፍሳችንና ሥጋችን በእርሱ ላይ ጥለናልና ንጉሡም ከመልእክተኞቹ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ታላቅ ፍርሀትን ፈራ፡፡

፷፩ ወለአከ ኀቤሁ እንዘ ይብል ሥረይ ሊተ እምይእዜሰ እገብር ፈቃደከ ወካህናትኒ ይምጽኡ ኀቤከ ከመ ትንግሮሙ ቃለ ሕይወት ወለእመ ፈቀድከ እንተ ትንበር ኀቤየ ንበር እንዘ ትሜህር ወሊተኒ ንግረኒ ዘይበቊዐኒ

፷፩ ንጉሡም ይቅር በለኝ፤ ከዛሬ ጀምሮ ፈቃድህን አደርጋለሁ፤ ሲል መልእክተኛ ላከ፡፡ ካህናትም የሕይወትን ቃል ትነግራቸው ዘንድ ወደ አንተ ይመጣሉ፡፡ አንተም ከእኔ ዘንድ መኖር ብትወድ እያስተማርህ ተቀመጥ ለእኔም የሚጠቅመኝን ንገረኝ፡፡

፷፪ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል በኀጢአተ ሕዝብኒ ወበኀጢአተ መነኮሳትኒ አንተ ትትወቀስ ወይቤ ንጉሥ በእንተ ምንት እትወቀስ በእንተ ኀጢአተ መነኮሳት፡፡

፷፪ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም በሕዝቡና በመነኮሳቱ ኀጢአት አንተ ትወቀሳለህ አለው፡፡ ንጉሡም በመነኮሳቱ ኀጢአት ስለምን እወቀሳለሁ? አለ፡፡

፷፫ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለምንትኬ ይትራድኡ መነኮሳት ምስለ መበለታት መነኮሳትኒ ይንበሩ እንተ ባሕቲቶሙ እስመ ኢመፍትው ኀዲረ እሳት ወሣዕር ውስተ ፩ መካን፡፡

፷፫ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም መልሶ መነኮሳቱ ከሴቶች መበለቶች ጋር ለምን ይረዳዳሉ /ይቀመጣሉ/? መነኮሳትም ብቻቸውን ይቀመጡ እሳት ከሣር /ገለባ/ ጋር በአንድ ቦታ ማደር አይገባምና አለው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፺፬ ወእምዝ ይቤ ንጉሥ ይዑድ ዓዋዲ እንዘ ይብል ለአመ ቦ ዘተረክበአ መነኮስአ ይትበርበርአ ንዋዩአ ይትሐበልዎአ ሥዩማንአ ጥሪቶ ወኪያሁኒአ ያምጽእዎአ፡፡ ኅቤየአ ምስለ መበለቱአ እንተ ትረጽኦአ ከመ ይርከቡአ መቅሠፍቶሙአ በጥብጣቤአ ወእምዝ ተሰነአወ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወተሳለመ ንጉሥ ወአተወ ውስተ መካኑ፡፡

፺፬ ከዚህ በኋላ ንጉሡ ከመበለት ጋር እየኖረ የተገኘ መነኩሴ ቢኖር ገንዘቡ ይወሰድ ሹማምንትም ጥሪቱን ይዝረፉት፣ እርሱንም ከምትረዳው ከመበለት ጋር ወደ እኔ ያምጡት በጅራፍ መቀጫቸውን ያገኙ ዘንድ በማለት ዐዋጅ ነጋሪ ይዞር አለ ከዚህ በኋላ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ከንጉሥ ጋር ተስማማ ንጉሡም ተባርኮ ወደ ቦታው ተመለሰ፡፡

፺፭ ወካዕበ ነገርዎ ለንጉሥ እንዘ ይብሉ ዝንቱ መነኮስ ዘስሙ በጸሎተ ሚካኤል አግብአ ኲሎ ሰራዊተከ ውስተ ንስሓ ወይቤ ንጉሥ እለ መኑ እሙንቱ እለ ገብኡ ውስተ ንስሓ ወነገርዎ አስማቲሆሙ ለእድ ወለአንስት ወለሠየምት፡፡

፺፭ ዳግመኛም ስሙ በጸሎተ ሚካኤል የተባለው መነኩሴ ሠራዊትህን ሁሉ ወደ ንስሓ መለሳቸው ብለው ለንጉሡ ነገሩት፤ ንጉሡም ወደ ንስሓ የተመለሱት /ንስሓ/ የገቡት እነማን ናቸው? አለ የወንዶችንና የሴቶቹን የሹማምንቱንም ስም ነገሩት፡፡

፺፮ ወሀለወት አሐቲ ብእሲት ዘቀዲሙሰ ብእሲተ ንጉሥ ወድ ኅረሰ ወሀባ ለአሐዱ እምሐራሁ ወነገርዎ ለንጉሥ በከመ ነስሐት ወአበየቶ ሩካቤ ለብእሲሃ ወይቤ ንጉሥ ያምጽእዋ ኅቤየ ከመ አርኩሳ በምስካብየ ወተፈነወ ላእክ ኅቤሃ ከመ ያምጽኣ፡፡

፺፮ በመጀመሪያ የንጉሡ ሚስት የነበረች በኋላ ግን ከወታደሮቹ ለአንዱ የሰጣት አንዲት ሴት ነበረች እርሷ ንስሓ እንደ ገባች ከባልዋም ጋር ሩካቤን እንቢ እንዳለች ነገሩት፤ ንጉሡም በመኝታዬ አዋርዳት ዘንድ ወደ እኔ ያምጥዋት አለ፤ ያመጣት ዘንድ መልእክተኛ ወደ እርስዋ ተላከ፡፡

፺፯ ወሶበ በጽሐ ላእከ ንጉሥ ኀቤሃ ለአከት ይእቲ ኀበ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እንዘ ትብል ኦ አባ ርድአኒ በጸሎትከ ወወስክ ትጋሀ በዲበ ትጋሀከ እስመ ናሁ አዘዘ ንጉሥ ከመ ይሰዱኒ ኀቤሁ ከመ ያኀድገኒ ንስሓየ ወያርኵሰኒ በውስተ ምስካቡ፡፡

፺፯ የንጉሡም መልእክተኛ ወደ እርስዋ በደረሰ ጊዜ እርስዋም አባት ሆይ በጸሎትህ ርዳኝ በትጋትህም ላይ ትጋትን ጨምር ብላ ወደ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ላከች እነሆ ንጉሥ ንስሓዬን ሊያስተወኝና በመኝታውም ሊያወርደኝ ወደ እርሱ እንዲወስዱኝ አዝዞዋልና፡፡

፺፰ ወበጽሐ ላእክ ፍና ሠርክ ጊዜ ይበውኡ ቅዱሳን ውስተ ድራረ ማኅበር ወእንዘ ይጼልዩ ጸሎተ ማዕድ ነገርዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ከመ በጽሐ ላእክ ወአዘዘ ያብእዎ እምቅድመ ይጥዐሙ እመፍቅዶሙ ቅዱሳን እስመ ጥቀ ያፈቅርዋ ለይእቲ ብእሲት ወነገሮ ላእክ ውእተ መልእክታ፡፡

፺፰ መልእክተኛውም ቅዱሳን በማኅበር ወደ ሚመገቡበት ሲገቡ ወደ ማታ ደረሰ፡፡ የማዕድ ጸሎትም ሲጸልዩ መልእክተኛው እንደ ደረሰ ለአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ነገሩት፡፡ ቅዱሳንም ከምግባቸው ገና ሳይቀምሱ ያስገቡት ዘንድ አዘዘ፤ ያችን ሴት እጅግ ይወዳት ነበርና መልእክተኛውም መልእክቷን ነገረው፡፡

፺፱ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለቅዱሳን ወኢአሐዱሂ እምኔክሙ ኢይጥዐም እከለ ወማየ ወኢአሐዱሂ እምኔክሙ ኢይባእ ውስተ ማኅደሩ፡፡

፺፱ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ቅዱሳንን ከእናንተ አንዱ እንኳ እህል አይቅመስ ውኃም አይጠጣ፤ ከእናንተ አንዱም ወደ ቤቱ አይግባ አላቸው፡፡

፻ ወአሐዱሂ እምኔክሙ ኢይሁብ ንዋመ ለቀራንብቲሁ በዛቲ ሌሊት ወአብአሙ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወአዘዞሙ ይዕጥቁ ድርማንቀ፡፡

፻ ከእናንተ አንዱም በዚህች ሌሊት ለቅንድቦቹ እንቅልፍን እንዳይሰጥ ወደ ቤተ ክርስቲያንም አስገብቶ በመታጠቂያ እንዲታጠቁ አዘዛቸው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፺፩ ወካዕበ አዘዞሙ ያውፅኡ አልባሲሆሙ ወቆብዐቲሆሙ ወቆሙ ዕሩቃኒሆሙ ወተማሕለሉ ኵሎ ሌሊተ ቦ ዘይሰግድ በብረኪሁ መጠነ ኀይሉ ወቦ ዘያውሕዝ አንብዐ እምአዕይንቲሁ ከመ ነጠብጣበ ዝናም ወቦ ዘያወትር ቀዊመ ከመ ሐውልት ወካህናትኒ ተማሕለሉ እምሥርክ እስከ ነግህ እንዘ የዐጥኑ ምሥዋዐ በበዕብሬቶሙ፡፡

፺፩ ዳግመኛም ልብሳቸውንና ቆባቸውን እንዲያወልቁ አዘዛቸው፡፡ ራቁታቸውንም ቁመው ሌሊቱን ሁሉ ለመኑ፡፡ በኀይሉ መጠን የሚሰግድ አለ ከዐይኖቹም እንደዝናም ጠብታ እንባን የሚያፈስስ አለ፤ እንደ ሐውልትም ቁመትን የሚያበዛ አለ፤ ካህናቱም ከማታ እስከ ጧት መንበሩን በየተራቸው እያጠኑ ይለምኑ ነበር፡፡

፺፪ ወበይእቲ ሌሊት ደወየ ንጉሥ ዐቢየ ደዌ እስከ አልጸቀ ለመዊት ወይቤሎሙ ንጉሥ ለእሊአሁ ዝንቱ ደዌየ ኢኮነ እምኀበ ካልእ ዘመጽአ ኀቤየ ዘእንበለ እንበይነ ጸሎቱ ለበጸሎተ ሚካኤል በእንተ ዘአዘዝኩ ያምጽእዋ ለእንተ ተማሕፀነት ኀቤሁ ወይእዜኒ ትትመየጥ ኀበ ዘነበረት፡፡

፺፪ በዚያችም ሌሊት ንጉሡ ለሞት በሚያደርስ ከባድ በሽታ ታመመ ንጉሡም ወገኖቹን እንዲህ አላቸው፤ ወደ እርሱ የተማፀነችውን ሴት ያመጥዋት ዘንድ ስላዘዝሁ ከበጸሎተ ሚካኤል ጸሎት በስተቀር ይህ በሽታዬ /ሕማሜ/ ከሌላ የመጣ አይደለም፡፡ አሁንም ወደ ነበረችበት ትመለስ፡፡

፺፫ ወለአከ ኀበ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እንዘ ይብል ሥረይ ሊተ ኦ አባ ዘንተ ኵሎ ደዌ ዘረከበኒ በእንተ ዘአዘዝኩ ያምጽእዋ ለዘእንተ ተማሕፀነት ብከ ወይእዜኒ አዘዝኩ ትትመየጥ ኀበ ቀዳሚ ንብረታ፡፡

፺፫ ወደ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም አባት ሆይ ይቅር በለኝ ብሎ መልእክተኛን ላከ፡፡ ይህ ሁሉ ደዌ ያገኘኝ በአንተ የተማፀነችውን ሴት ያመጥዋት ዘንድ ስላዘዝሁ ነው፡፡ አሁንም ወደ ቀደመ አኗኗርዋ ትመለስ ዘንድ አዝዣለሁ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፺፩ | ወአፍራሰነ ዘፈነውኩአ ከመ ያጥፍዑ ቤቶሙ ለደቂቅከ ይእዜኒ አዘዝኩ ያውፅኡ ሎሙ ወአንተኒ አ አባ መሐረኒ ከመ እግዚአብሔር አቡከ መሓሪ:: | ፺፩ | የልጆችህን ቤት ያጠፉ ዘንድ የላክኋቸው ፈረሶችንም ያወጡላቸው ዘንድ አዝዣለሁ:: አንተም አባቴ ሆይ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ይቅር ባይ እንደ ሆነ ይቅር በለኝ:: |
| ፺፪ | ወለእመኒ አሕየወኒ እግዚአብሔር እምዛቲ ደዌ በጸሎትከ ቅድስት ወአነኒ አኀድር በሥርዐትከ | ፺፪ | በተቀደሰች ጸሎትህም እግዚአብሔር ከዚህች ደዌ ቢፈውሰኝ እኔም በሥርዐትህ እኖራለሁ:: |
| ፺፫ | ወፈነወ ንጉሥ ምስለ ውእቱ ላእክ ካህናተ ወዲያቆናተ ያስተብቍዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል | ፺፫ | ንጉሡም ከዚያ መልእክተኛ ጋር አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ይማልዱት ዘንድ ካህናትንና ዲያቆናትን ላከ:: |
| ፺፬ | ወሶበ ጸብሐ ብሔር አዘዞሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለመነኮሳት ከመ ይልበሱ አልባሲሆሙ ወይቅንቱ ቅናቲሆሙ ወይትቆብዑ ቆባዕቲሆሙ ወይትዐጸፉ አጽፎሙ:: | ፺፬ | ሰዓቱም በነጋ ጊዜ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል መነኮሳትን ልብሳቸውን እንዲለብሱ ትጥቃቸውን እንዲታጠቁ ቆባቸውንም እንዲያደርጉ ዐፅፋቸውንም እንዲጐናጸፉ አዘዛቸው:: |
| ፺፭ | ወእምድኅረዝ በጽሑ ላእካነ ንጉሥ ካህናት ወዲያቆናት ወነገርዎ ኲሎ ዘለአኮሙ ወአስተብቍዕዎ ከመ ይጸሊ ሎቱ ኀበ እግዚአብሔር በዘየሐዩ እምደዌሁ:: | ፺፭ | ከዚህ በኋላ የንጉሡ መልእክተኞች ካህናትና ዲያቆናት ደርሰው የላካቸውን ሁሉ ነገሩት:: ከበሽታውም በሚድን ገንዘብ ወደ እግዚአብሔር ይጸልይላት ዘንድ ማለዱት:: |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፺፱ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል መኑኬ ዘይገብሮ ለዝንቱ ኵሉ ዘእንበለ አንትሙ ደብተራ ዘትትበሃሉ ታስተብፅዕዎ ወትዌድስዎ ወትብልዎ መኑ ከማከ ኀያል ወመኑ ከማከ መዋኢ ወመኑ ከማከ ጸጋዊ ውስተ ኵሉ ወመኑ ከማከ ወሃቤ ምጽዋት፡፡

፺፱ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ደብተራ ከምትባሉ ከእናንተ በስተቀር ይህን ሁሉ የሚያደርገው ማን ነው? አላቸው፡፡ ታደንቁታላችሁ፤ ታመሰግኑታላችሁ፤ እንደ አንተ ያለ ኀያል ማን ነው? እንደ አንተ ያለ አሸናፊ ማን ነው? እንደ አንተ ያለ ለጋስ እንደ አንተስ ምጽዋት ሰጭ ማን ነው? ትሉታላችሁ፡፡

፻ ወሶበ ታስተበፅዕዎ ይዌስክ ኀጢአተ ዲበ ኀጢአት በከመ ይቤ ኢሳይያስ ሕዝብየ እለ ያስሕቱከሙ ወይደመስሱ ዐሠረ እገሪክሙ፡፡

፻ ባመሰገናችሁትም ጊዜ በኀጢአት ላይ ኀጢአትን ይጨምራል፡፡ ኢሳይያስ ወገኖቼን የሚያስቱ የእግራቸውንም ፍለጋ የሚያጠፉ አሉ እንዳለ፡፡

፻፩ ወይቤልዎ ካህናት ወሐራሁ ለንጉሥ አ አባ ንሕነኒ ንነብር በከመ ሥርዐትከ ወንጉሥኒ ይቤ እምከመሰ ሐየውኩ እምዝንቱ ደዌየ እገብር ከመ አዘዝከኒ፡፡

፻፩ ካህናቱና የንጉሡ ሠራዊትም አባት ሆይ እኛም እንደ ሥርዐትህ እንኖራለን፡፡ ንጉሡም ከዚህ በሽታ ከተፈወስሁ እንደ አዘዝኸኝ አደርጋለሁ ብሏል አሉት፡፡

፻፪ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አነሰ አእምር ከመ ኢይትመየጥ ወኢይኔስሕ እምኀጣውኢሁ ወባሕቱ ይፈውሶ እግዚአብሔር እምደዌሁ ከመ ኢይኩን ሞቱ በቃለ ዚአየ፡፡

፻፪ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እኔ ከኀጢአቱ ተመልሶ ንስሓ እንደ ማይገባ ዐውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ሞቱ በእኔ ቃል ምክንያት እንዳይሆን እግዚአብሔር ከበሽታው ይፈውሰው አላቸው፡፡

፻፫ ወይቤልዎ ካህናት ሀበነ ጸበለ እገሪከ ከመ ንሰድ ሎቱ በዘየሐዩ እምደዌሁ፡፡

፻፫ ካህናቱም ከደዌው በሚድን ነገር እንወስድለት ዘንድ የእግርህን ትቢያ ስጠን አሉት፡፡

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳፬ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኢይሁበክሙ ጸበለ እግርየ ወባሕቱ ሑሩ ወትረከብዎ ጥዑየ እምደዌሁ፡፡

፳፬ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም የእግሬን ትቢያ አልሰጣችሁም ነገር ግን ሒዱ ከደዌውም ተፈውሶ ታገኙታላችሁ አላቸው፡፡

፳፭ ወሖሩ ካህናት ወኩሎሙ ልኡካን ወረከብዎ ለንጉሥ ጥዑየ እምደዌሁ፡፡ ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

፳፭ ካህናቱና ሁሉም መልእክተኞች በሔዱ ጊዜ ንጉሡን ከደዌው ተፈውሶ አገኙት፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይኑር አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፰

## ምዕራፍ ስምንት

፩ ወእምድኅረዝ ነበረ በጸሎተ ሚካኤል ውስተ ውእቱ መካን እንዘ ይትጋደል በጽሙና ወይሜህሮሙ ለደቂቀ ወንጌለ መንግሥተ ሰማያት፡፡

፩ ከዚህ በኋላ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል በትርሕምት በዚያ ቦታ እየተጋደለ ለደቀ መዛሙርቱም የመግሥተ ሰማያት ወንጌልን እያስተማራቸው ተቀመጠ፡፡

፪ ወአሐተ ዕለተ ቦአ ውስተ ቤተ መቅደስ ከመ ይቀድስ ቍርባነ ወቦአ ዐቅራብ ውስተ መልበሱ ከመ ያዕቅፎ ወነደፎ ብዙኀ ንድፈተ፡፡

፪ አንድ ቀንም ይቀድስ ዘንድ ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ጊንጥ ያሰናክለው ዘንድ በልብሱ ውስጥ ገባ፡፡ ብዙ ጊዜም ነደፈው፡፡

፫ ወኢያፅርዐ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ቅዳሴ ቍርባን ወኢያብአ እዴሁ ውስተ ሕፅኑ ለኀሢሠ ዐቅራብ አላ ፈጸመ ቅዳሴ እንዘ ሰፉሓት እደዊሁ ወአስተሳተፎሙ ለሕዝብ ምስጢረ ቅድሳት ወእምድኅረ ፍጻሜ ቍርባን መድለወ ሥጋሁ ወሐጸት ነፍሱ ወመሰሎሙ ለቅዱሳን ከመ ሕማመ ደዌ ዘረከቦ ወኢያእመሩ ከመ ነደፎ ዐቅራብ ውስተ ሕፅኑ፡፡

፫ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ግን የቍርባኑን ቅዳሴ አላቋረጠም፡፡ ጊንጡንም ለመፈለግ እጁን ወደ ውስጥ አላስገባም፤ እጆቹን እንደ ዘረጋ ቅዳሴውን ፈጸመ እንጂ፡፡ ለሕዝቡም ሥጋውንና ደሙን ሰጣቸው፡፡ ከቍርባኑም ፍጻሜ በኋላ ሥጋው ጠወለገ፤ እስትንፋሱም ቀዘቀዘች፤ ለቅዱሳን ሕማም ያገኘው መስሏቸው ነበር፡፡ በውስጡም ጊንጥ እንደ ነደፈው ዐላወቁም፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፬ ወሶበ ፈነዉ እደዊሆሙ ለኀሚሠ ሥጋሁ ረከቡ ዐቅራበ ወረከቡ መካነ ሥጋሁ ኀበ ሐመመቶ እንዘ ያሕመለምል ሂጸተ ሕምዙ ለዐቅራብ ውስተ ሥጋሁ ለብእሴ እግዚአብሔር አስተብፅዑ ወአእኰቱ ትዕግሥቶ ለብእሲ ኄር፡፡

፬ ሥጋውንም ለመዳሰስ እጃቸውን በላኩ ጊዜ ጊንጥ አገኙ፡፡ በእግዚአብሔር ሰው በእርሱ የጊንጡ መርዙ እየተሰራጨ ያሳመማቸውን የተነደፈበትን ቦታ አገኙ፡፡

፭ እፎኬ መንክር ብዝኀ ትዕግሥቱ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወእፎ መንክር ገድለ ጻማሁ ዘይትፌቀር በኀበ ሰብእ ወይትመዘገን በኀበ እግዚአብሔር ኦ አባ ክቡር እፎ ኢሐመመተከ ዘነበ ዐቅራብ ወእፎ ኢያሕመመተከ በሂጸተ ሕምዙ ኦ አባ እፎ ተዐገሥከ ዘመጠነዝ ምንዳቤ እፎ አናኀከ እምጥንተ ቅዳሴ እስከ ፍጻሜ፡፡

፭ የአባታችን የበጸሎተ ሚካኤል የትዕግሥቱ ብዛት ምን ይደንቅ?! በእግዚአብሔር ዘንድ የተመሰገነ በሰውም ዘንድ የተወደደ የድካሙ ገድል እንዴት ይደንቅ? ክቡር አባት ሆይ የጊንጡ ጅራት እንዴት አላሳመመችህም በመርዙ መነደፍስ እንዴት አላሠቃየኸችህም አባት ሆይ ይህን ያህል መከራ እንዴት ታገሥህ? አባት ሆይ ከቅዳሴ መጀመሪያ እስከ መጨረሻው እንዴት አስረዘምህ?

፮ ኦ አባ ሦዕከ በቅዱስ ቍርባን ዘአምላክከ ከመ ትመጥዎሙ ለሕዝብ መድኀኒተ ነፍሶሙ ወሦዕከ ርእሰከ በትዕግሥተ ምንዳቤ ዘበሕማመ ዐቅራብ ወርገ መዐዛ ጽንሓሕከ እስከ ሰማይ ወበጽሐ ቅድመ መንበሩ ለአኀዜ ኩሉ፡፡

፮ አባት ሆይ ለሕዝቡ የነፍሳቸው መድኀኒት ትሰጣቸው ዘንድ የአምላክህን ቅዱስ ቍርባን ሠዋህ፡፡ መከራውንም በመታገሥ ራስህን ሠዋህ፤ በጊንጥ መነደፍ የተቀበልኸው መከራም የጽናሕ መዓዛ ሆኖ እስከ ሰማይ ዐረገ ሁሉን በያዘ በአምላክ መንበር ፊትም ደረሰ፡፡

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፯ ኦ አባ ውክፍተ ኮነት መሥዋዕትከ ከመ ስብሐተ ኪሩቤል ወከመ መዐዛ ዕጣን ዘሱራፌል ኦ አባ ሊቀ መምህራኒሃ ለኢትዮጵያ ኦ አባ መንኮሳ ለብሔረ አግዓዚ ኦ አባ ዘትትፌሣሕ በስደትከ ከመ ዘረከበ ምህርካ ብዙኀ ወትትሐሠይ በሙቃሔከ ከመ ዘየሐውር ውስተ ቤተ መርዓ፡፡

፯ አባት ሆይ መሥዋዕትህ እንደ ኪሩቤል ምስጋናና እንደ ሱራፌልም የዕጣን መዓዛ ተቀባይነትን አገኘች፡፡ አባት ሆይ የኢትዮጵያ የመምህራኖቿ አለቃ ነህ አባት ሆይ የኢትዮጵያ አባትዋ ነህ፡፡ አባት ሆይ በስደትህ ብዙ ምርኮ እንዳገኘ ሰው ትደሰታለህ ወደ ሰርግ ቤት እንደሚሔድ ሰውም በእሥራትህ ሐሤት ታደርጋለህ፡፡

፰ ኦ አባ ሶበ ትበውእ ውስተ ቤተ መቅደስ ይትዌለጥ ገጽከ ከመ ዘሰትየ ወይነ ከራሜ ወሶበ ትዌጥን ሰጊደ ታፈጥን ከመ ሩጻተ አፍራስ ኦ አባ ወሶበ ትሰፍሕ እደዊከ ለጸሎት ተኀጽብ ሥጋከ በነቅዐ እንብዕከ ወሶበ ትሜህርሂ ይትከዐው ሞገስ እምከናፍሪከ፡፡

፰ አባት ሆይ ወደ ቤተ መቅደስ በገባህ ጊዜ የከረመ ወይን እንደ ጠጣ ሰው ፊትህ ይለወጣል፡፡ ስግደትንም በጀመርህ ጊዜ እንደ ፈረስ ሩጫ ትፈጥናለህ፡፡ አባት ሆይ እጆችህንም ለጸሎት በዘረጋህ ጊዜ በእንባህ ፈሳሽ ምንጭ ሥጋህን ታጥባለህ ባስተማርህም ጊዜ ከከንፈሮችህ ሞገስ ይፈስሳል፡፡

፱ ኦ አባ ሶበ ትቀውም ውስተ ዐውደ ነገሥት ይውዒ ልብከ ከመ ድብ ሐራስ ወከመ ሐራውያ ሐቅል ለዋው ትዴግን በመዐት ከመ ጥሕረተ አንበሳ ወከመ ንቃወ አራዊት ወከመ ነምር ዘይቀንጽ እምእሙ ለተባእሶ ነአውት እለ ይረውድዎ፡፡

፱ አባት ሆይ በነገሥታቱ ዐደባባይ በቆምህ ጊዜ እንደ አራስ ጅብ ልብህ ይቃጠላል፡፡ እንደ በረሃ ሐራውያ በቁጣ እንደ አንበሳም ትከተላለህ፡፡ በግሳት እንደ አራዊት በጩኸት የሚከቡትን አንዳኞች ለመጣላት ከእናቱ ፈጥኖ እንደሚዘል ነምር ነህ፡፡

፲ ኦ አባ አልብከኑ ሥጋ ዘኢትፈርህ ሕማማተ ኦ አባ አልብከኑ ድካመ ሥቃያት በዐውደ ነገሥት ኦ አባ ዝክረኒ በጸሎትከ እስመ ጸሎተ ጻድቅ ትክል ወታሠልጥ፡፡ ያዕ.፭፥፲፮

፲ አባት ሆይ መከራዎችን የማትፈራ ሥጋ የለህምን? አባት ሆይ በነገሥታት ዐደባባይ ሥቃይን የማትፈራ የሥጋ ድካም የለብህምን አባት ሆይ በጸሎትህ አስበኝ የጻድቅ ሰው ጸሎት ትችላለች ግዳጅም ትፈጽማለችና ያዕ.፭፥፲፮

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፩ ወይእዜኒ ንግባእ ከመ ንንግር ዜናሁ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወአሐተ ዕለተ ይቤሎ አሐዱ መነኮስ በፍቅር ወበጽሙና ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለእመ ብከ መበለት ኢትንበር ምስሌከ።

፲፩ አሁንም የአባታችን የበጸሎተ ሚካኤልን ዜናውን እንናገር ዘንድ እንመለስ አንድ ቀንም አንድ መነኮስ አባት ሆይ በፍቅርና በጸጥታ በአንድ ቦታ እንቀመጥ አለው። አባታችን በጸሎተ ሚካኤል መበለት /መነኵሲት/ ካለች ከአንተ ጋር አትቀመጥ አለው።

፲፪ ወይቤሎ ውእቱ መነኮስ አልብየ መበለት ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እመሰ አልብከ መበለት ኢይደልወነ ንንበር ዝየ አላ ንትገኀሥ ውስተ ካልእ መካን ወገብረ ሎቱ ንስቲተ ጸማዕተ አቡነ

፲፪ ያም መነኩሴ መበለት የለኝም አለው። አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም መበለትስ ከሌለህ ከዚህ ልንቀመጥ አይገባንም አለው። ወደ ሌላ ቦታ እንሒድ እንጂ። አባታችን በጸሎተ ማካኤልም ትንሽ ዋሻ

፲፫ ወአሐተ ዕለተ እንዘ ኢሀሎ ውእቱ በጽሐት መበለት ወትቤ አብኡኒ ኀበ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወይቤልዎ ደቂቁ ኢይትከሃለኪ ከመ ትባኢ ኀቤሁ ወትቤሎሙ አነኒ ኢየሐውር። እምዝ መካን ዘእንበለ እትናዘዝ እምኀቤሁ በእንተ አበሳየ ወነገርዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ዘከመ ትቤ ይእቲ መበለት።

፲፫ አንድ ቀንም ያ መነኩሴ ሳይኖር መበለቲቱ መጣች ወደ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል አስገቡኝ አለች። ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ትገቢ ዘንድ አይቻልሽም አሏት። እኔም ከእርሱ ስለ ኀጢአቴ ሳልናዘዝ ከዚህ ቦታ አልሔድም አለቻቸው ያችም መበለት እንደ ተናገረች ለአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ነገሩት።

፲፬ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል በልዋ ንግርዮ ለዝ ቀሲስ ኩሎ ኀጢአተኪ ወነገሪቶ ይእቲ መለበት ኩሎ ኀጢአታ ወበከመ አማሰነ ድንግልናሃ ውእቱ መነኮስ ዘይቤ አልብየ መበለት።

፲፬ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ኀጢአትሽን ሁሉ ለዚህ ቄስ ንገሪው በሏት አላቸው። ያችም መበለት ኀጢአቷን ሁሉ ነገረችው መበለት የለኝም ያለው ያ መነኩሴም ድንግልናዋን እንዳ ፈረሰባት ነገረችው።

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፭ ወለአኮ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለውእቱ ቀሲስ ኀበ ይእቲ መበለት እንዘ ይብል ከመዝአ ነስሒአ ወከመዝአ ጹሚአ ወኢትግብኢአ ኀቤሁ እምዝ ዳግመ ለውእቱ መነኮስ፡፡

፲፭ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ያን ቄስ ወደዚያች መበለት ላከው እንደዚህ ሲል እንደዚህ ንስሓ ግቢ እንደዚህም ጹሚ ወደዚያም መነኩሴ ዳግመኛ እንዳትመለሽ፡፡

፲፮ ወአዘዘ ከመ ይሰድዋ ኀበ አባ ፊልጶስ ወልዱ ወለአከ ኀቤሁ እንዘ ይብል ንሥኣ ዕቀባ ለዛቲ በግዕት ዘአንገፍከዋ እምአፈ ተኵላ ወአንተኒ ዕቀባ በሥርዐተ ምንኲስና፡፡

፲፮ ወደ ልጁ አባ ፊልጶስም ይወስድዋት ዘንድ አዘዘ፡፡ ከተኩላ አፍ ያወጣኋት ይህችን በግ ጠብቃት ብሎ ወደ እርሱ ላከ አንተም በምንኩስና ሥርዐት ጠብቃት፡፡

፲፯ ወአተወ ውእቱ መነኮስ ወይቤሎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሀበኒ መበለትየ፡፡

፲፯ ያም መነኩሴ ገብቶ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን መበለቴን ስጠኝ አለው፡፡

፲፰ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኢትቤለኒኑአ ቀዲሙ አልብየ መበለት ወይእዜኒ ኢዐቀብከኒ መበለተከ፡፡

፲፰ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም አስቀድሞ መበለት የለኝም አላልኸኝምን አሁንም መበለትህን አላስጠበቅኸኝም አለው፡፡

፲፱ ወተምዐ ውእቱ መነኮስ ዐቢየ መዐተ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ምንትኑ ዘተግኀሠ እምኔከ ትትመዐዕ ላዕሌየ ጥቀ፡፡

፲፱ ያም መነኩሴ ታላቅ ቍጣ ተቈጣ፤ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም በእኔ ላይ ትቈጣ ዘንድ ከአንተ የተወሰደብህ ምንድን ነው? አለው፡፡

፳ ወሀሎ አሐዱ ዲያቆን ዘተምህረ ብሉየ ወሐዲሰ በኀበ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወውእቱኒ ሖረ ውስተ አሐዱ መካን ወይቤ አነ ቀሲስ ወሠርዐ ወቀደሰ ቍርባነ እንዘ ኢኮነ ካህነ ውእቱ፡፡

፳ ከአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ብሉይንና ሐዲስን የተማረ አንድ ዲያቆን ነበር፡፡ እርሱም ወደ አንድ ቦታ ሔዶ እኔ ቄስ ነኝ ብሎ ካህን ሳይሆን ቍርባን ሠርቶ ቀደሰ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | |
|---|---|---|
| ፳፩ | ወዜነውዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ዘከመ ገብረ ውእቱ ወአዘዞ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ከመ ይጸውዕዎ ወሰበ በጽሐ ኀቤሁ ተምዖ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡፡ | ለአባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ያ ዲያቆን ያደረገውን ነገሩት፡፡ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እንዲጠሩት አዘዘ፡፡ ወደ እርሱም በደረሰ ጊዜ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ተቈጣው፡፡ |
| ፳፪ | ወይቤሎ ለምንት ትገብር ከመዝ ወኢይትሐበሉ መላእክት ከመ ይግሥሡ ሥጋሁ ለክርስቶስ፡፡ | ለምን እንደዚህ አደረግህ? የክርስቶስ ሥጋ ይዳስሱ ዘንድ መላእክት እንኳን አይደፍሩም አለው፡፡ |
| ፳፫ | እፎ አንተ ደፈርከ እንዘ መሬታዊ አንተ ዘኢኮንከ ካህነ ወለእመ ተሰምዐ ዝንቱ ነገር ይዌግሩከ በእብን፡፡ | መሬታዊ ስትሆን ካህን ያይደለህ እንዴት ደፈርህ? ይህ ነገር ከተሰማ በድንጋይ ይወግሩሃል፡፡ |
| ፳፬ | ወይቤ ውእቱ ብእሲ አባ ክቡር ሀበኒ ንስሓ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ከመዝ ጹም ወከመዝ ነስሕ፡፡ | ያም ሰው ክቡር አባት ሆይ ንስሓ ስጠኝ አለ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል እንደዚህ ጹም እንደዚህም ንስሓ ግባ አለው፡፡ |
| ፳፭ | ወካዕበ ገብአ ኀበ ቀደሚ እበዲሁ ወሠርዐ ቍርባነ በዕለተ ትስብእቱ ለክርስቶስ፡፡ | ሁለተኛም ወደ ቀደመ በደሉ ተመለሰ፡፡ ክርስቶስ ሰው በሆነበት በዓልም ቍርባኑን ሠራ፡፡ |
| ፳፮ | ወዜነውዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል በከመ ገብረ ውእቱ ወአዘዘ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ከመ ይጸውዕዎ፡፡ | ያም ዲያቆን ያደረገውን ለአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ነገሩት አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ይጠሩት ዘንድ አዘዘ፡፡ |
| ፳፯ | ወይቤሎሙ ዑቁ ወኢትሳተፉ ምስሌሁ ኢ በቍርባን ወኢ በጸሎት | ከእርሱም ጋር በቍርባን ቢሆን በጸሎትም ቢሆን እንዳትሳተፉ ዕወቁ አላቸው፡፡ |
| ፳፰ | ወእምዝ ኀደግዎ ኵሉ ካህናትኒ ወዲያቆናት ወኵሉ ሕዝብ፡፡ | ከዚህ በኋላ ካህናትና ዲያቆናት ሕዝቡም ሁሉ ተለዩት፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳፱ | ወእምዝ ቦአ ሰይጣን ውስተ ልቡ ለውእቱ መነኮስ በከመ ቦአ ላዕለ ይሁዳ ሠያጤ እግዚኡ፡፡ | ፳፱ | ከዚህ በኋላ ሰይጣን በዚያ ጌታውን በሸጠ በይሁዳ ልብ እንደገባ በዚያ መነኩሴ ልብ ገባ/አደረ/፡፡ |
| ፴ | ወሖረ ውእቱ ዲያቆን ወተራከበ ለውእቱ መነኮስ ዘአማሰነ ድንግልናሃ ለመነኮሳዪት ወዝኩ ዘነገርነ ዜናሁ ቀዳሚ፡፡ | ፴ | ያም ዲያቆን ሐዶ የመነኩሴዋን ድንግልና ካፈረሰው መነኩሴ ጋር ተገናኘ፡፡ ይህም አስቀድመን ዜናውን የተናገርንለት ነው፡፡ |
| ፴፩ | ወነብሩ ክልኤሆሙ ተኳሉት ላዕለ በግዕ ወአንቅያት ላዕለ ርግብ ወአክይስት ላዕለ ብእሲ ንጹሕ ወአፍዖት ጸዋጋን ላዕለ መምህረ ሕግ ዘምሉአ በረከት፡፡ | ፴፩ | ሁለቱም ተኩላዎች በበጉ ላይ፣ ጭልፊቶችም በርግብ ላይ፣ እባቦች በንጹሕ ሰው ላይ የከፉ እፉኝቶች በረከትን በተመላ የሕግ መምህር ላይ አንድ ሆኑ፡፡ |
| ፴፪ | ወሖሩ ክልኤሆሙ ኀበ ንጉሥ ወአስተዋደይዋ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወይቤሉ ይረግመከ አ ንጉሥ አንዘ ይብል ዘአስጠሞ ለፈርዖን ወለ ሰራዊቱ ውስተ ቀላየ ባሕር ከማሁ ያሰጥሞ ለዝንቱ ንጉሥ ምስለ ሠራዊቱ ወሕዘቢሁ፡፡ | ፴፪ | ሁለቱም ወደ ንጉሡ ሔደው አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን አጣሉት ንጉሥ ሆይ ፈርዖንንና ሠራዊቱን በባሕር ያሰጠመው እንደዚሁ ይህን ንጉሥ ከሠራዊቱና ከሕዝቡ ጋር ያስጥመው እያለ ይረግምሃል ብለው ነገሩት፡፡ |
| ፴፫ | ወተምዐ ንጉሥ ወአዘዘ ያምጽእዎ አሲሮሙ ምስለ ደቂቁ እምኀበ ሀለዉ መካን፡፡ | ፴፫ | ንጉሡም ተቈጥቶ ካሉበት ቦታ ከልጆቹ /ደቀ መዛሙርቱ/ ጋር አስረው ያመጡት ዘንድ አዘዘ፡፡ |
| ፴፬ | ወአሰርዎሙ ወአ ብጽሕዎሙ ውስተ ዴዴ ንጉሥ ወለአከ ኀቤሁ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል እንዘ ይብል ለምንት ትረግሙኒ፡፡ | ፴፬ | አስረውም ከንጉሡ ደጅ አደረሰዋቸው ወደ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ለምን ትረግሙኛለችሁ? ብሎ ላከ፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፫ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ ኢረገምኩክ ወኢተመሀርኩኑ መጻሕፍተ እስመ ይቤ እግዚእነ ደኅርዎሙ ለእለ ይረግሙክሙ ወሠናየ ግበሩ ለእለ ይትዔገሉክሙ ማቴ. ፫፥፵

፴፬ ጳውሎስኒ ይቤ ለዘሂ ረገመከ ደኅሮ በሥርዐተ ምንኩስና ይብል እስከለሰይጣን ኢትርግሙ:: ወእመሰ እስከ ለሰይጣን ይኤዝዝ ኢረጊመ እፎኬ ለንጉሥ ይረግምዎ

፴፭ ወአብአ ንጉሥ ኀቤሁ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወይቤሎ እሉ እሙንቱ እለ ነገሩኒ ከመ ረገምከኒ ወዐቀሞሙ ቅድሜሁ ለክልኤቱ መነኮሳት እለ ዘከርኖሙ ቀዲሙ::

፴፮ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለንጉሥ ዝኒ ፩ዱ መነኮስ ዘአማሰነ ድንግልናሃ ለአሐቲ መበለት ወመጽአት ኀቤየ ወሰከየቶ::

፴፯ ወአዘዝክዋ ከመ ኢትግባእ ዳግመ ወኢትቅረብ ኀቤሁ ወሰደድክዋ ውስተ ካልእ መካን ወሎቱኒ ገሠጽክዎ በተግሣጸ ቅዱሳን ወአዘዝክዎ ከመ ኢይትመየጥ ኀበ ዘከመዝ ግብር::

፴፫ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እኔ አረገምሁህም መጻሕፍትን አልተማርሁምን ጌታችን የሚረግሙአችሁን መርቁ፤ ለሚቃወሟችሁም መልካም ነገርን አድርጉ ብሏልና:: ማቴ. ፫፥፵

፴፬ ጳውሎስም የሚረግምህን መርቀው በምንኩስና ሥርዐትም ሰይጣንንም እንኳ አትርገሙ ይላል:: ሰይጣንንስ እንኳ አለመርገምን የሚያዝዝ ከሆነ ንጉሥን እንዴት ይረግሙታል::

፴፭ ንጉሡም አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ወደ እርሱ አስገባው እንደ ረገምኸኝ የነገሩኝ እሊህ ናቸው አለው አስቀድመን የጠራናቸው ሁለቱ መነኮሳትንም ከፊቱ አቆማቸው::

፴፮ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ለንጉሡ ይህ አንዱ መነኩሴ የአንዲቱን መበለት ድንግልናዋን አፍርሶ ወደ እኔ መጥታ የከሰሰችው ነው አለው::

፴፯ ዳግመኛም እንዳትገባ ወደ እርሱም እንዳትቀርብ አዘዝኋት:: ወደ ሌላም ቦታ ሰደድኋት:: እርሱንም በቅዱሳን ተግሣጽ ገሠጽኩት ወደዚህም ሥራ እንዳይመለስ አዘዝሁት::

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፺ | ወዝኒ ካልኡ ነበረ ኅቤየ በሥርዐተ ዲቁና ወሖረ ኀበ ካልእ መካን ወይቤ ቀሲስ አነ ዘኢኮነ ቀሲስ ወሠርዐ ቍርባነ ወነገሩኒ በእንቲአሁ ከመ ገብረ ዘንተ ሎቱኒ ገሠጽክዎ ወተማዕክዋ፡፡ | ፺ | ይህም ሁለተኛው በዲቁና ሥርዐት ከእኔ ጋር ነበር ወደ ሌላ ቦታ ሔዶ ቄስ ሳይሆን ቍርባን ሠርቶ ቀደሰ ስለ እርሱም ይህን ሁሉ እንዳደረገ ነገሩኝ እርሱንም ገሠጽሁትና ተቈጣሁት አለው፡፡ |
| ፺፩ | ወውእቱኒ አምነ ከመ ገብረ ዘንተ በቅድመ ቀሳውስት ወዐቀምክዎ በንስሓ እምግብረ ክህነት ወእምድኅረዝ ተመይጠ ኀበ ቀደሚ እበዲሁ፡፡ | ፺፩ | እርሱም ይህን እንዳደረገ በቀሳውስት ፊት አመነ፡፡ ከክህነትም ሥራ በንስሓ አገድሁት ከዚህ በኋላ ወደ ቀደመ በደሉ ተመለሰ፡፡ |
| ፺፪ | ወእምዝ አዘዝክዎሙ ለእለ ይነብሩ ምስሌሁ ከመ ኢይሳተፍዎ በጸሎት ወበእንተዝ መጽኡ ኀቤከ ከመ ያስተዋድዩኒ በሐሰት፡፡ | ፺፪ | ከዚህ በኋላ ከእርሱ ጋር ያሉትን በጸሎት እንዳይተባበሩ አዘዝኋቸው ስለዚህ በሐሰት ሊያጣሉኝ ወደ አንተ መጡ፡፡ |
| ፺፫ | ወይቤ ንጉሥ ሑር ወሥርዖሙ በከመ ፈቃድከ ወግበር ላዕሌሆሙ ቀኖና በከመ ሥርዐትከ በከመ ተአምር አንተ፡፡ | ፺፫ | ንጉሡም ሒድ እንደወደድህ ሥራባቸው እንደምታውቀው እንደሥርዐትህም ቀኖና ሥራባቸው አለ፡፡ |
| ፺፬ | ወወሀቦ ሰላመ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወተሰነአወ ምስለ ንጉሥ ወአተወ ውስተ መካኑ፡፡<br>ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስለ ኲልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡ | ፺፬ | አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ሰላምታ ሰጥቶት ከንጉሡም ጋር ተስማምቶ ወደ ቦታው ተመለሰ፡፡<br>ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ሕዝበ ክርስቲያን ጋር ይኑር ለዘለዓለሙ አሜን፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

## ምዕራፍ ፱

## ምዕራፍ ዘጠኝ

፩ ወአሐተ ዕለተ በጽሐ ኀቤሁ ናትናኤል ወልዱ ዘየዐቢ እምኲሎሙ ደቂቁ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወአምጽኡ ለነ ምዝረ እምቤተ እግዚእ ክብራ አኀትየ ከመ ንሳተፍ ምስለ ናትናኤል ወልድየ፡፡

፩ ከዕለታትም አንድ ቀን ከሁሉም ደቀ መዛሙርቱ የሚበልጠው ተማሪው ናትናኤል ወደ እርሱ መጣ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ከልጄ ከናትናኤል ጋር እንሳተፍ ዘንድ ከእኅቴ እግዚእ ክብራ ቤት ጠጅ አምጡልን አለ፡፡

፪ ወአምጽኡ ሎቱ ምዝረ በንስቲት ጽዋዕ እስመ ኢረከቡ ካልአ ዘውስተ ቤት ዘእንበሌሁ

፪ በቤት ውስጥ ከእርሱ በቀር ሌላ ስላላገኙ በትንሽ ጽዋ ጠጅ አመጡለት፡፡

፫ ወነሥአ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ካልአ ጽዋዐ ወከፈሎ ለውእቱ ምዝር ኀበ ክልኤሆሙ ወመልአ ውስተ አፉሆን ወአስተባዝኆን በጸሎቱ ከመ ቅብዐ መበለት ዘመልአ ኲሎ ንዋየ ልሕኲት ዘውስተ ቤት በትእዛዘ ኤልሳዕ ነቢይ፡፡ ፪ነገ.፬፥፩

፫ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ሌላ ጽዋ አምጥቶ ያን ጠጅ ከሁለት ከፈለው በጽዋዎቹም አፍ መላ በጸሎቱም በነቢዩ ኤልሳዕ ትእዛዝ በቤቷ ገላው ዕቃ ሁሉ እንደ መላ እንደ መበለቲቱ ዘይት አበዛው፡፡ ፪ነገ.፬፥፩

፬ ወአሐተ ዕለተ እንዘ ሀለዉ ኀቡረ በስደቶሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወዘአማኑኤል መምህረ ወለቃ ወእንዘ ያስተዳልዉ ሎሙ ኀብስተ ሠርኮሙ አርዳኢሆሙ፡፡ በውስተ ማኅበዝ ወማሰነት ኀብስተ ዘአማኑኤል ወኢሠነየት ወኀብስተ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሠናየ ጥቀ ኮነ ዘይኤድም ለአዕይንት፡፡

፬ ከዕለታትም አንድ ቀን አባታችን በጸሎተ ሚካኤልና የወለቃ መምህር ዘአማኑኤል በስደት በአንድነት ሳሉ ደቀ መዛሙርቶቻቸው የሠርክ ምግባቸውን ሲያዘጋጁላቸው የዘአማኑኤል ዳቦ ጠፋች ደስም የማታሰኝ ሆነች፡፡ የአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ዳቦ ግን ለዐይን ደስ የሚያሰኝ እጅግ ያማረ ሆነ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳፯ ወይቤሎ ረድአ ዘአማኑኤል ለረድአ በጸሎተ ሚካኤል አቡነ ሀበኒ ዘአስተዳለውከ ለመምህርከ እስመ መምህርየ መዐትም ወለእመ ርእየ ዘንተ ኅብስተ ሙሱነ ይትመዐዕ ላዕሌየ ወይኴንነኒ፡፡

፳፯ የዘአማኑኤል ደቀ መዝሙርም የአባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ደቀ መዝሙር መምህሬ ቁጡ ነውና ለመምህርህ ያዘጋጀኸውን ስጠኝ ይህን የተበላሸ ዳቦ ያየ እንደ ሆነ በእኔ ላይ ይቈጣል ይቀጣኛልም አለው፡፡

፳፰ ወይቤሎ ረድአ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለረድአ ዘአማኑኤል ንሣእ በከመ ትቤ እስመ መምህርየሰ ዕጉሥ በመንፈስ ውእቱ ወወደይዎ ለኅብስተ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ውስተ መሶበ ዘአማኑኤል ወለኅብስተ ዘአማኑኤል ወደይዎ ውስተ መሶበ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡፡

፳፰ የአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ደቀ መዝሙርም የዘአማኑኤል ደቀ መዝሙርን መምህሬ በመንፈስ ትዕግሥተኛ ነውና እንዳልህ ውሰድ አለው፡፡ የአባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ዳቦ በዘአማኑኤል መሶብ የዘአማኑኤልንም ዳቦ በአባታችን በጸሎተ ሚካኤል መሶብ ጨመሩት፡፡

፳፱ ወእምዝ ፍና ሠርክ አቅረቡ ሎሙ ድራረ በበመሶቦሙ ወሶበ ፈቀደ ከሣቶታ ለመሶብ ዘዘአማኑኤል አበየት ተፈትሖተ እስመ ኅብስተ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሀሎ ውስቴታ ወጥቀ አጥቅዐዋ በኀይል ከመ ያርሕውዋ ወአበየቶሙ፡፡

፳፱ ከዚህ በኋላ በምሽት ጊዜ ምግባቸውን በየመሶባቸው አቀረቡላቸው የዘአማኑኤልንም መሶብ ለመክፈት በፈለገ ጊዜ አልከፈት አለች የአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ዳቦ በውስጥዋ አለና በኀይልም ይከፍትዋት ዘንድ መላልሰው መታ መታ አደረጓት እንቢ አለቻቸው፡፡

፴ ወይቤሎ ለረድኡ ዘአማኑኤል አይኑ ጌጋይ ዘገበርከ ዘአበየተኒ ተፈትሖ መክድነ መሶብየ፡፡

፴ ዘአማኑኤልም ደቀ መዝሙሩን የመሶቡ መክደኛ አልከፈት ያለችን የሠራኸው በደል ምንድን ነው አለው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፱ ወይቤሎ ረድኡ ፩ አበሳ አበስኩ በፍርሀተ ዚአከ ሶበ ማሰነ ኀብስተ ዚአከ በውስተ ማኀበዝ ወእቤሎ ለዝንቱ ካልእየ ሀበኒ ኀብስተ መምህርከ ከመ ኢይትመዐዕ ላዕሌየ መምህርየ ወሀበኒ በከመ ሰአልክዎ እትሐዘብ በእንተዝ አበየ ተፈትሖ፡፡

፱ ደቀ መዝሙሩም አንተን በመፍራት አንድ በደል በደልሁ አለው የአንተ ዳቦ በምጣዱ ውስጥ በተበላሸ ጊዜ ይህን ጓደኛዬን መምህሬ እንዳይቆጣኝ የመምህርህን ዳቦ ስጠኝ አልሁት፡፡ እርሱም እንደ ለመንሁት ሰጠኝ ስለዚህ አልከፈት ያለ ይመስለኛል አለው፡፡

፲ ወይቤ ዘአማኑኤል ይትባረክ እግዚአብሔር ዘይገብር መንክራተ በላዕለ ቅዱሳኒሁ ወእምዝ ይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ንሣእ ኀብስተከ ዘወሀበከ ፍትሐ እግዚአብሔር፡፡

፲ ዘአማኑኤልም በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ተአምራትን የሚያደርግ እግዚአብሔር ይመስገን አለ፤ ከዚህ በኋላ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል የእግዚአብሔር ፍርድ የሰጠኽን ኅብስትህን ውሰድ አለው፡፡

፲፩ ወሶበ ባረከ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ተፈትሐት በጊዜሃ በከመ ልማድ ወእለ ርእዩ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር፡፡

፲፩ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም በባረከ ጊዜ እንደተለመደው ተከፈተች ያዩትም ሰዎች እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡

፲፪ ወበአሐዱ እመዋዕል ይቤሎሙ ንጉሥ ለሐራሁ በምንትኬ ዘይዜኀሩ መነኮሳት ላዕሌየ፡፡

፲፪ ከዕለታትም አንድ ቀን ንጉሡ ሠራዊቱን እሊህ መነኮሳት በእኔ ላይ የሚኮሩ በምንድን ነው አላቸው፡፡

፲፫ ይመስለከሙ እለ ውስተ አድባር ወምኔታት ዘእንበለ በውሒዘ አፍላግ ወአንቅዕታተ ማያት ዘይበውእ ውስተ አዕጻዳቲሆሙ ወቦቱ ይሰቅዩ አትክልተ ወቦቱ ይዘርዑ አሕማላተ ወቦቱ ያረውዩ ስጉርተ ወሰማተ ወእምዝ ጸጊቦሙ ይወፅኡ ከመ ይትበአሱ፡፡

፲፫ በአድባራትና በገዳማት ያሉ መነኮሳት በቦታቸው በሚፈስሰው አማካኝነት አትክልታቸውን ያጠጣሉ፤ በእርሱም አዝርዕትን ይዘራሉ፤ ሽንኩርቱን ያጠጣሉ፤ ከዚህ በኋላ በጠገቡ ጊዜ ሊጣሉ ይወጣሉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፬ | ወአዘዘ ይምጽኡ ይጸውዑ ሎቱ ጽኑዓነ ሐራ እለ ይትለአክዎ ለስደተ ቅዱሳን ወአዘዞሙ ለእሙንቱ ሐራ እንዘ ይብል ሑሩ ሰድዎሙ ለቅዱሳን ምስለ በጸሎተ ሚካኤል፡፡ ዘየሀውኮ ለመንግሥትየ፡፡ | ፲፬ | ቅዱሳንን ለማሳደድ የሚያገለግሉት ጠንካሮች ወታደሮችን ይጠሩለት ዘንድ አዘዘ እነዚያንም ወታደሮች መንግሥቴን ከሚያውክ ከበጸሎተ ሚካኤል ጋር እነዚህን ቅዱሳን ውሰዷቸው ብሎ አዘዛቸው፡፡ |
| ፲፭ | ወአብጽሕዎሙ ውስተ ብሔር ይቡስ ኅበ ዘኢይትረከብ ማይ መጠነ አሐቲ ዕለት፡፡ | ፲፭ | አንድ ቀንም ተጉዘው ውኃ ከማይገኝበት ቦታ አደረሷቸው፡፡ |
| ፲፮ | ወእምዝ ወሰድዎሙ ለእሙንቱ ቅዱሳን ውስተ ብሔር ርሑቅ ወሶበ በጽሑ ኀበ ውሒዘ ፈለግ ይቤልዎሙ እለ የአምሩ ግእዘ ብሔር ቅድሑ ማየ እምውስተ ዝ ፈለግ ወኢትረክቡ እንከ እምድኅረዝ፡፡ | ፲፮ | ከዚህ በኋላ እነዚያን ቅዱሳን ወደ ሩቅ ሀገር ወስደዋቸው ከፈሳሽ ወንዝም በደረሱ ጊዜ የአገሩን ሁኔታ የሚያውቁ ሰዎች ከዚህ ወንዝ ውኃ ቅዱ ከዚህ በኋላ ውኃ አታገኙም አሏቸው፡፡ |
| ፲፯ | ወበሳኒታ ሶበ ትትነሥኡ ነግሀ ትበጽሑ ዝየ ጊዜ ስድስቱ ሰዓት ወሶበ በጽሐ ጊዜ ስድስቱ ሰዓት በጽሑ ህየ ወሶበ የዐርብ ፀሐይ ቀድሑ ማየ ቅዱሳን እምውስተ ውእቱ ፈለግ ወሰትዩ ኀበ መካን ዘአብጽሕዎሙ፡፡ | ፲፯ | ነገ በጥዋት ከተነሣችሁ ከዚያ ስድስት ሰዓት ትደርሳላችሁ፤ ስድስት ሰዓትም በደረሰ ጊዜ ከዚያ ደረሱ ፀሐይም ሲጠልቅ ከያዙት ከዚያ ወንዝ ውኃ ቀድተው ካደረሷቸው ቦታ ሁነው ጠጡ፡፡ |
| ፲፰ | ወበሳኒታ ሶበ ኀሐ ብሔር ተበሀሉ በበይናቲሆሙ ንዑ ንሑር ውስተ ፈለግ ከመ ኢይኩን ተመይጦትነ በምሴተ ጽልመት፡፡ | ፲፰ | በማግሥቱም በነጋ ጊዜ እርስ በርሳቸው መመለሻችን በጨለማ እንይሆን ኑ ወደ ወንዝ እንሂድ ተባባሉ፡፡ |
| ፲፱ | ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ማካኤል ተዐገሡ ደቂቀየ ወአጽንዑ ልበክሙ እስመ ትሬእዩ ኀይለ እግዚአብሔር፡፡ | ፲፱ | አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ልጆቼ ሆይ የእግዚአብሔርን ኀይል ታያላችሁና ታገሡ ልባችሁንም አጽኑ አላቸው፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳ ወሶበ ኮነ ረፋዲተ ሖረ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኀበ ኵኵሕ ዘያረስኖ ለእግር እምላህበ ፀሐይ እስመ መርቄ ብሔሩ ወጸለየ ዲቤሁ ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት ወእንዘ ይጼሊ አጽለቅለቀ ውእቱ ኵኵሕ ወተነቅለ እምኔሁ መጠነ ዐቢይ ገበታ፡፡

፳ ረፋድም በሆነ ጊዜ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ከፀሐይ ሙቀት የተነሣ እግርን ወደሚያቃጥለው ዐለት ሔደ፡፡ ሀገሩ ቈላ ነውና ከዐለቱም ላይ ሆኖ በሦስት ሰዓት ጸለየ፡፡ ሲጸልይም ያ ዐለት ተነዋወጠ ታላቅ ገበታ የሚያህል ድንጋይም ተፈነቀለ፡፡

፳፭ ወውሕዘ ማይ ብዙኀ ወምስለ ማዩ ውሕዙ ዓሣት ዐበይት ወአዘዘ አቡነ በጸሎተ ማካኤል ከመ ይጸውዕዎሙ ለሐራ ንጉሥ፡፡

፳፭ ብዙ ውኃ መነጨ፤ ከውኃውም ጋር ታላላቅ ዓሣዎች ተገኙ፤ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልንም የንጉሡን ወታደሮች እንዲጠሯቸው አዘዘ፡፡

፳፪ ወሶበ በጽሑ ይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እግዚእከሙ ሐዘነ በእንተ ማይ ዘዝዕብ ይስትዮ አምጽአነ ዝየ ከመ ኢንስተይ ወእግዚአብሔር ለሲሳይነ ኀለየ ወሠርዐ ለነ ማዕደ ዓሣት አኮ ዘተሠግሩ እም ወሓይዝተ አፍላግ አላ ዘመጽኡ እማየ መንክራቲሁ ዘነቅዐ እምኵኵሕ፡፡

፳፪ በደረሱም ጊዜ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ንጉሣችሁ ጅብ ለሚጠጣው ውኃ አዝኖ ውኃ እንዳንጠጣ ወደዚህ አመጣን፤ እግዚአብሔር ግን ለምግባችን አሰበልን፤ የዓሣ ማዕድንም ሠራልን፤ ይኸውም ከሚፈስሰው ወንዝ የተያዙ አይደለም፤ ከዐለት ከመነጨው ከተአምራቱ ውኃ የተገኙ ናቸው እንጂ፡፡

፳፫ ምንተኑ ይኄሊ እግዚእከሙ ወኀበ አይቴኑ ይሰድደነ ኀበ ኢይበጽሕኑ እግዚአብሔር ወኀበ አይኑ ይወስደነ ኀበ ዘኢሀሎ መለኮተ አምላክ እስመ ጽሑፍ ዘይብል "ውስተ ኵሉ በሐውርት መለኮቱ" መዝ.፻፪፡፳፪

፳፫ ጌታችሁ ምን ያስባል ወዴየትስ ይሰድደናል እግዚአብሔር ወደማይደርስበት ነውን ወዴየትስ ቦታ ይወስደናል የአምላክ ግዛት ከሌለበት ነውን? ግዛቱ በሀገሩ ሁሉ ነው የሚል ጽሑፍ አለና መዝ.፻፪፡፳፪

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳፬ ወካዕበ ጽሑፍ ዘይብል አይቴኑ አሐውር እመንፈስከ ወአይቴ እጐይይ እምቅድመ ገጽከ እመኒ ዐረጉ ውስተ ሰማይ ህየኒ አንተ ወእመኒ ወረድኩ ውስተ ቀላይ ህየኒ ሀሎከ ወእመኒ ነሣእኩ ክንፈ ከመ ንስር ወሰረርኩ እስከ ማኀለቅተ ባሕር ህየኒ እዴከ ትመርሐኒ ወታነብረኒ የማንከ መዝ.፻፴፰፥፯

፳፬ ሁለተኛም “ከመንፈስህ ወዴት እሔዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ ወደ ጥልቁም ብወርድ አንተ በዚያ አለህ እንደ ንስርም ክንፍን ብወስድ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር በዚያ እጅህ ትመራኛለች፡፡ ቀኝህም ታኖረኛለች” የሚል ጽሑፍ አለ መዝ.፻፴፰፥፯

፳፭ ወሐሩ እሙንቱ ሐራ ንጉሥ ወነገርዎ ዘከመ ርእዩ ኵሎ መንክራተ በኀይለ ጸሎቱ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡፡

፳፭ እነዚያም የንጉሥ ወታደሮች ሔደው በአባታችን በጸሎተ ሚካኤል የጸሎት ኀይል የአዩትን ተአምራት ሁሉ ነገሩት፡፡

፳፮ ወፈርሀ ንጉሥ ሶበ ሰምዐ ዘንተ ወአዘዘ ከመ ይፈንውዎሙ ወይሑሩ ኀበ ፈቀዱ ወነበሩ ቅዱሳን ኀዳጠ መዋዕለ ኀበ መንክራቲሆሙ፡፡

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን

፳፮ ንጉሡም ይህን በሰማ ጊዜ ፈራ ወደ ወደዱት ቦታ ይሔዱ ዘንድ እንዲሰድዋቸውም አዘዘ፡፡ ቅዱሳንም ተአምራት በተደረገበት ቦታ ጥቂት ጊዜ ቆዩ፡፡

ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይኑር ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፲

፩ ወእምድኅረዝ አንሥአ ምንስወ ጸላኢ ውስተ ልበ ንጉሥ ከመ ያሕስም ዲበ ቅዱሳን ወአዘዘ በኵሉ ሕዘቢሁ እንዘ ይብል አምጽእዎሙአ ለቅዱሳንአ ለእለ ሀለዉአ ውስተኵሉ አህጉረ መንግሥትየአ፡፡

## ምዕራፍ ዐሥር

፩ ከዚህ በኋላ ጠላት /ዲያብሎስ/ በቅዱሳን ላይ ክፉ ሥራ ይሠራ ዘንድ በንጉሡ ልብ ክፉ ዐሳብን አስነሣ እኔ በምገዛው ሀገር ሁሉ ያሉ ቅዱሳንን አምጧቸው ብሎ በሕዝቡ ሁሉ ትእዛዝ አስተለለፈ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፪ | ወአብጽሕዎሙ ለቅዱሳን ወበጽሐ ዘአማኑኤልሂ ምስለ ደቂቁ ወአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወእምዝ ይቤሎሙ ንጉሥ ኅበሩ ምስሌየ በቊርባን ወበጸሎት ወእመኅበርክሙ ምስሌየ እሁበክሙ አድባራተ ለሐኒጸ ምኔታት ወአድባረሂ ትገብርዎሙ፡፡ | ፪ | ቅዱሳንን ሁሉ አመጧቸው ዘአማኑኤልም ከልጆቹና ከአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ጋር ደረሰ፤ ከዚህ በኋላ ንጉሡ በቊርባንና በጸሎት ከእኔ ጋር ተባበሩ /አንድ ሁኑ/ አላቸው፡፡ ከእኔም ጋር ከተባበራችሁ ገዳማትን የምታንጹባቸው ቦታዎችን እሰጣችኋለሁ የራሳችሁ አድባራትም ታደርጓቸዋላችሁ፡፡ |
| ፫ | ወካዕበ እሁበክሙ ወርቀ ወብሩረ ዘይበቊዕ ለመቅደስክሙ ወለመፍቅደ ቤተ ክርስቲያንክሙ ስርናየ ወዲበጋተ ለመክድነ ምሥዋዒክሙ ወለሞጣሕተ ካህናቲክሙ አባዕረኒ በዘትትጌበሩ ወአልሕምተ በዘትሴሰዩ ሐሊበ፡፡ | ፫ | ዳግመኛም ለቤተ መቅደስ ሥራ የሚበቃ ወርቅና ብርን እሰጣችኋለሁ፤ ለቤተ ክርስቲያኑም ማገልገያ ግብሩን ለመንበሩ መጋረጃ ግምጃውን ለካህናቱ ልብሰ ተክህኖ የምታርሱባቸውን በሬዎችና ወተት የምትጠጡላቸውን ላሞዎች እሰጣችኋለሁ፡፡ |
| ፬ | ወእመሰ አበይክሙ ኅቢረ ምስሌየ አዘዘ ሊቀ ጳጳሳት እስድድክሙ ኅቤሁ ሑሩኬ ምድረ ግብጽ በረኃብ ወበጽምዕ ወበውስተ ፍኖትኒ ሀለዉ ፈያት እለ ይቀትሉ ነፍሰ፡፡ | ፬ | ከእኔ ጋር መተባበርን እንቢ ካላችሁ ግን ወደ እርሱ እሰዳችሁ ዘንድ ሊቀ ጳጳሱ አዝዘዋል፤ ስለዚህ ወደ ግብጽ በረኃብና በጥም ሒዱ በመንገድም ነፍስ የሚገሉ ሽፍቶች አሉ፡፡ |
| ፭ | ወይቤሉ ደቂቀ ዘአማኑኤል ነኀብር ንሕነሰ ምስሌከ ወንገብር ፈቃደከ በከመ አዘዝከነ ንጉሥ ወወሀቦሙ ንጉሥ ወርቀ ወብሩረ ወአልባሰ ወአልሕምተ ወነሢኦሙ አተዉ ለለመካኖሙ ዘአማኑኤልሰ አቡሆሙ አበየ ዘንተ ወተሰደ ባሕቲቱ፡፡ | ፭ | የዘአማኑኤል ደቀ መዛሙርትም እኛ ከአንተ ጋር እንተባበራለን፡፡ ንጉሥ እንዳዘዝኸንም ፈቃድህን እናደርጋለን አሉ ንጉሡም ወርቅና ብር፣ ልብሶችና ላሞችን ሰጣቸው እነርሱም ተቀብለው እየቦታቸው ሔዱ፡፡ መምህራቸው ዘአማኑኤል ግን ይህን አልፈልግም ብሎ ብቻውን ተሰደደ፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፮ ወለአቡነ በጸሎተ ሚካኤልሂ ለአከ ኀቤሁ ዐበይተ መኳንንተ ወመሳፍንተ እንዘ ይብል ኀበሩ ምስሌየ ወእመሰ አበይከ ሑር ኀበ ሊቀ ጳጳሳት ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እወ አሐውር በፍኖተ ኢየሩሳሌምኒ ኢታፍርሀኒ በልዎ ለእግዚእክሙ

፮ ወደ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ታላላቅ መኳንንትንና መሳፍንትን ከእኔ ጋር ተባበሩ /ተስማሙ/ ብሎ ላከ፡፡ ኣይሆንም /እንቢ/ ካልህ ግን ወደ ጳጳሳቱ አለቃ ሒድ፤ አባታችን በጸሎተ ማካኤልም አዎን እሔዳለሁ፤ በኢየሩሳሌምም መንገድ አታስፈራራኝ በሉት ጌታችሁን አለ፡፡

፯ ወይቤሎሙ ካዕበ ላእከ ንጉሥ ለቅዱሳን ወለክሙኒ ይቤለክሙ ንጉሥ ወኢትሙቱአ በረኀብ ወበጽምዕ እንዘ ትነግዱአ ኢየሩሳሌምአ እስመ ሀየአ ሀለዉአ ቀተሊልተ ነፍስአ ዘውስተ ፍኖትአ እለ ያክሕዱአ ክርስቲያነአ ፈያትአ እለ ኢየአምርዎአ ለክርስቶስአ፡፡

፯ ዳግመኛም የንጉሡ መልእክተኛ ቅዱሳንን እናንተንም ወደ ኢየሩሳሌም ስትሔዱ በረኀብና ጥም እንዳትሞቱ አላቸው፡፡ በዚያ በመንገድ ክርስቶስን የማያውቁ ክርስቲያንን የሚያስክዱ ነፍሰ ገዳዮች አሉና ይላችኋል ንጉሥ አልዋቸው፡፡

፰ ወእመሰ ኀበርክሙአ ምስሌየአ እሁበክሙ ወርቀ ወብሩረአ አልሕምተአ ወኩሎ ጥሪተአ ወይቤልዎ ቅዱሳን ለላእክ ወርቅከ ወብሩርከ ወኩሉ ጥሪትከ ምስሌከ ለይኩን ለሕርትምና፡፡

፰ ከእኔ ጋር ከተባበራችሁ ግን ወርቅና ብር ላሞችንና ጥሪቱን ሁሉ እሰጣችኋለሁ ቅዱሳንም መልእክተኛውን ወርቅህና ብርህ ጥሪትህም ሁሉ ከአንተ ጋር ለጥፋት ይሁንህ አሉት፡፡

፱ ወዘንተ ብሂሎሙ ተለውዎ ለመምህሮሙ ወአንከሩ ኩሎሙ ሰራዊተ ንጉሥ በእንተ ጥብዐቱ ለአቡነ በጸሎተ ማካኤል ወበእንተ ጥብዐተ ደቂቁ፡፡

፱ ይህንም ብለው መምህራቸውን ተከተሉት የንጉሡም ሠራዊት ስለ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ጽናትና ስለ ልጆቹ ጥንካሬ አደነቁ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲ ወሖረ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እንዘ ያነብብ ዘንተ መዝሙረ ወይቤ እግዚአብሔር ያበርህ ሊተ ያድኅነኒ ምንትኑ ያፈርሀኒ እግዚአብሔር ምእመና ለሕይወትየ ወምንትኑ ያደነግፀኒ ወአንበበ ዘንተ መዝሙረ እስከ ተፍጻሜቱ። መዝ.፳፯፥፩

፲ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ይህን መዝሙር እያነበበ ሔደ። እግዚአብሔር ያበራልኛል፤ ያድነኛልም፤ ምን ያስፈራኛል? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው ምን ያስደነግጠኛል" አለ ይህንም መዝሙር እስከ መጨረሻው አነበበ። መዝ.፳፯፥፩

፲፩ ወበጽሐ ውስተ መካን ዘየኀድር ውስቴቱ ወቤተ ህየ ምስለ ደቂቁ ወመጽኡ ህየ ኀቤሁ ሠራዊተ ንጉሥ ወመኳንንት ወመሳፍንት ወኲሉ አርእስተ ሐራሁ ለንጉሥ ወተሰኣልዎ ለብእሴ እግዚአብሔር።

፲፩ ከሚያድርበትም ቦታ ደረሰ በዚያም ከልጆቹ ጋር አደረ። በዚያም የንጉሡ ሠራዊት፣ መኳንንትና መሳፍንትና የሠራዊቱ አለቆች ሁሉ መጥተው የእግዚአብሔርን ሰው ጠየቁት።

፲፪ ወኀደረ እንዘ ይነግሮሙ ኲሎ ሌሊተ ወይቤሎሙ ኢትፍርሁ ተበርብሮ ንዋይክሙ ሙቃሔ እደዊክሙ ወእገሪክሙ ወተቀሥፎ ዘባንክሙ ወተጠብሖ ወዓዲ ኢትፍርሁ ለእመ ቀተሉክሙ እስመ በድንክሙ ኢትኀደግ ለክሙ በዝየ ወነፍስክሙ ይሰክዮ ለዘቀተለክሙ ቅድመ እግዚአብሔር ወአልቦ እንከ ሥልጣነ ሞት ላዕሌክሙ።

፲፪ ሌሊቱን ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ሲነግራቸው አደረ፤ የገንዘባችሁን መዘረፍ፣ የእጃችሁንና የእግራችሁን መታሰር፣ የጀርባችሁን መገረፍ፤ የሥጋችሁን መታረድ፤ አትፍሩ ዳግመኛም ቢገድልዋችሁ አትፍሩ፤ ሥጋችሁ በዚህ ዓለም ይቀራል ነፍሳችሁ ግን የገደላችሁን በእግዚአብሔር ፊት ይከሰዋልና፤ በእናንተ ላይ ሞት ሥልጣን የለውም።

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፫ ወዘንተ ብሂሎ ሖረ ምስለ ደቂቁ እንዘ ይነድእዎሙ ሐራ ንጉሥ ወአብጽሕዎሙ በሀገረ አረሚ ኀበ ቀተልተ ነፍስ እለ ኢየአምርዎ ለእግዚአብሔር፡፡

፲፫ ይህን ብሎ የንጉሡ ሰራዊት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እየነድዋቸው ሔደ እግዚአብሔርን የማያውቁ ነፍሰ ገዳዮች አረማውያን ወዳሉበት ቦታ አደረስዋቸው፡፡

፲፬ ወእምድኅረዝ ወሰድዎ ምድረ ትግራይ ወአብጽሕዎ ኀበ መኰንን ወመኰንን አንበሮ ኀበ ካልእ መካን ዘይሰመይ ገረአልታ ወለካልኣንሂ ደቂቁ አንበርዎሙ ምድረ ጽራዕ ወገብት፡፡

፲፬ ከዚህ በኋላ ወደ ትግራይ ወሰዱት ወደ ገዢውም አደረሱት ገዢውም ገረአልታ በሚባል ቦታ አስቀመጠው ሌሎች ልጆችን ደግሞ ጽራዕና ገብቶት በሚባል ቦታ አስቀመጥዋቸው፡፡

፲፭ ወነበሩ ቅዱሳን በጾም ወበጸሎት ወበዐቢይ ትሕርምት ወውእቱሂ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ነበረ እንዘ ይዌስክ ጾመ ዲበ ጾም ወሰጊደ በዲበ ሰጊድ ወጻማ በዲበ ጻማሁ ወትጋሀ በዲበ ትጋሁ፡፡

፲፭ ቅዱሳንም በጾምና በጸሎት በታላቅም ትርሕምት ኖሩ፡፡ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም በጾም ላይ ጾም በስግደትም ላይ ስግደት በተጋድሎ ላይ ተጋድሎ በትጋትም ላይ ትጋት እየጨመረ ኖር፡፡

፲፮ ወእምዝ በጽሐ ላእከ ንጉሥ ኀበ መኰንን ወይቤ ያምጽእዎ ለበጸሎተ ሚካኤል ከመ ንንግሮ መልእክተ ንጉሥ፡፡

፲፮ ከዚህ በኋላ የንጉሡ መልእክተኛ ወደ ገዢው ደረሰና የንጉሡን መልእክት እንነግረው ዘንድ በጸሎተ ሚካኤልን ያምጡት አለ፡፡

፲፯ ወአብጽሕዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ወይቤ ላእከ ንጉሥ ሰላም ለከአ ይቤለከአ ንጉሥ ንሣእአ ዘንተ ወርቀአ ወብሩረአ፡፡

፲፯ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልንም በአደረሱት ጊዜ የንጉሡ መልእክተኛ ንጉሡ ሰላም ለአንተ ይሁን፡፡ ይህን ወርቅና ብር ውሰድ ብሎሃል አለ፡፡

፲፰ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለላእከ ንጉሥ በቅድመ መኰንን ለምንት ሊተ እነሥእ ወርቀ ወብሩረ ኢኮንኩ ቀደሙኒ በእንተ ዝንቱ ተሰደድኩ እስመ ይኄይሰኒ ለመነኮስ እንበር በንዴትየ፡፡

፲፰ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም የንጉሡን መልእክተኛ በገዢው ፊት ወርቅና ብር ለእኔ ምንድን ነው? ቀድሞስ ስለዚህ ተሰድጄ የለምን? ለመነኩሴው ለእኔ በችግር ልኖር ይገባኛልና፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፱ ወይቤሎ ላእከ ንጉሥ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል እመሰ አበይከ ነሢአ ንዋይ ሑር ሀገረ ኢየሩሳሌም ይቤለከ ንጉሥ፡፡

፲፱ የንጉሡም መልእክተኛ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ገንዘቡን አልቀበልም ካልህ ንጉሡ ወደ ኢየሩሳሌም ሒድ ብሎሃል አለው፡፡

፳ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አሆ አሐውር አነ በትእዛዝክሙ በከመ ትቤሉኒ ወጸበለክሙኒ ዘተለወኒ እነግፍ ለክሙ መልበስየ ዘዲበ ሥጋየ ወዐጽፊ ዘዲበ ዘባንየ ወቆብዕኒ ዘዲበ ርእስየ እገድፍ በቅድሜክሙ፡፡

፳ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እሺ እንዳላችሁኝ በትእዛዛችሁ እሔዳለሁ የተከተለኝንም ትቢያ አራግፍላችኋለሁ፤ በሥጋዬ ላይ ያለ ልብሴን፣ በጀርባዬ ያለ መጐናጸፊያዬን በራሴ ላይ ያለ ቆቤን በፊታችሁ እጥልላችኋለሁ፡፡

፳፩ ለምንት አኀፍር ቀዊመ ዕርቃንየ አነኑ እኄይስ እምእግዚእየ ወአምላኪየ እስመ ውእቱ ቆመ ዕራቁ ቅድመ ዐውደ ሰቃልያን ወዘንተ ብሂሎ አርመመ፡፡

፳፩ ለምን ዕራቁቴን መቆምን አፍራለሁ፡፡ እኔ ከጌታዬና ከፈጣሪዬ እበልጣለሁን እርሱ በሰቃዮች ዐደባባይ ዕራቁቱን ቆሞልና ይህን በሎ ዝም አለ፡፡

፳፪ ወይቤሎ ለላእከ ንጉሥ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሑር ውስተ መካንከ ወሖረ ላእከ ወነገሮ ለንጉሥ ወሶበ ተፈጸመ ጾመ ፵ ሖረ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኀበ ዴዴ ንጉሥ ምስለ ደቂቁ ወምስሌሁ መሳፍንት ዘአምጽአሙ፡፡

፳፪ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም የንጉሡንም መልእክተኛ ወደ ቦታህ ሒድ አለው መልእክተኛውም ሔዶ ለንጉሡ ነገረው አርባው ጾም /ዐቢይ ጾም/ በተፈጸመ ጊዜ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ከልጆቹ ጋር ወደ ንጉሡ ደጅ ሔደ፡፡ ያመጣቸውም መስፍን ከእርሱ ጋር ነበር፡፡

፳፫ ወለአከ ንጉሥ ኀበ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እንዘ ይብል ከመ አብእከሰ ኀቤየአ እፈርህአ ከመ ኢትዘልፈኒአ በከመ ዘለፍከኒ ቀዳሚ ወባሕቱ አ አባ አስተበቍዐከ ከመ ትኅበር ምስሌየ ወእመሰ አበይከ ሑር ኢየሩሳሌም፡፡

፳፫ ንጉሡ ወደ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል እንዲህ ሲል መልእክተኛ ላከ፡፡ ወደ እኔ አስገባህ ዘንድ ከዚህ በፊት እንደዘለፍከኝ እንዳትዘልፈኝ እፈራለሁ፡፡ ነገር ግን አባት ሆይ ከእኔ ጋር ትተባበር ዘንድ እለምንሃለሁ፡፡ አይሆንም ካልህ ግን ኢየሩሳሌም ሒድ፡፡

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፳፬ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ ምስሌከኒ ኢየኀብር ወኀበ ኢየሩሳሌምኒ ኢየሐውር፡፡

፳፬ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እኔ ከአንተ ጋር አልተባበርም ወደ ኢየሩሳሌምም አልሔድም አለ፡፡

፳፭ ወለእመሰ ፈቀድከ እሑር ኢየሩሳሌም አምጽኡ ለላእከ ዘፈነወ ሊቀ ጳጳሳት እስረኒ ሊተኒ ወሎቱኒ በሙቃሔ ወፈንወነ ህየ፡፡

፳፭ ወደ ኢየሩሳሌም እንድሔድስ ከወደድህ የጳጳሳቱ አለቃ የላከውን መልእክተኛ አምጣውና እኔንም እርሱንም በሰንሰለት አሰረህ ወደዚያ ላከን፡፡

፳፮ ወይቤ ንጉሥ ኢየአስረክሙ ለከሂ ወሎቱሂ አላ ለሊከ ሑር በእገሪከ

፳፮ ንጉሡም አንተንም እርሱን አላሰራችሁም ራስህ በእግርህ ሒድ እንጂ አለ፡፡

፳፯ ወይቤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ ኢየሐውር እምዝ ደዴከ ወእፈቅድ ፍትሐ ኩነኔ ሞት እምኔከ እመሂ በኩናት ወእመሂ በመጥባሕት እስመ ይኄይሰኒ መዊት እምነቢር ዘእንበለ ፍሬ እስመ ለዘይጸውም ጾሞ አብጠልከ ወለዘይሰግድ ሰጊደ ከላእከ ወተዐጸዋ ምኔታት ወአድባራት በዕብሬተ መንግሥትከ፡፡

፳፯ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እኔ ከዚህ በደጅህ አልሄድም ከአንተም የሞት ፍርድን እፈልጋለሁ በጦርም ቢሆን፣ በሰይፍም ቢሆን ያለፍሬ ከመኖር ሞት ይሻለኛልና የሚጾመውን ጾሙን አስቀርተሃል የሚሰግደውንም ስግደቱን ከልክለሃልና ገዳማትና አድባራት በዘመነ መንግሥትህ ተዘግተዋልና፡፡

፳፰ ወለአከ ንጉሥ ኀቤሁ እንዘ ይብል እቱአ ኦ አባ ውስተ ማኅደርከ ከመ ኢትሙት በቊር ወበአስሐትያ ወአስተብቊዕዎ ደቂቁ ቅዱሳን እንዘ ይብሉ ንእቱ ኦ አቡነ ውስተ ማኅደርነ ከመ ኢንማስን በምንዳቤ ቊር ወበአስሐትያ፡፡

፳፰ ንጉሡም አባቴ ሆይ በብርድና በውርጭ እንዳትሞት ወደ ቤትህ ግባ ብሎ ላከበት ቅዱሳን ደቀ መዛሙርቱም አባታችን ሆይ በብርድና በውርጭ እንዳንሞት ወደ ቤታችን እንግባ ብለው ማለዱት፡፡

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳፱ | ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ይኩን ፈቃድከሙ ወአተወ ምስሌሆሙ ውስተ ማኅደሩ ወአምጽአ ሎቱ መስፍን ድራረ ወአበዩ አቡነ በጸሎተ ሚካኤለ ወይቤሎ መስፍን ምንተ ገበርኩ አ አባ:: | ፳፱ | አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ፈቃዳችሁ ይሁን ብሎ ከእነርሱ ጋር ወደ ቤቱ ገባ፤ መስፍኑም ራት አመጣለት፤ አባታችንም በጸሎተ ሚካኤልም አልበላም አለ፤ መስፍኑም አባት ሆይ ምን ሠራሁ? አለው:: |
| ፴ | ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንተሰ ምንተሂ ኢገበርከ ወባሕቱ ከመ ኢይትሜካሕ ንጉሥ በንዋየ ዚአከ ወአስተብቍዖሂ ካዕበ ወአበዮ ወሖረ ውእቱ መስፍን ወነገሮ ለንጉሥ:: | ፴ | አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም አንተስ ምንም አልሠራህ ነገር ግን ንጉሡ በአንተ ገንዘብ እንዳይመካ ነው አለው ሁለተኛም ለመነው አይሆንም አለው ያም መስፍን ሂዶ ለንጉሡ ነገረው:: |
| ፴፩ | ወለአከ ንጉሥ ኀበ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል እንዘ ይብል የሀቡከሙ እክለ ሲሳየከሙ ከመ ትግብርዎ በከመ ፈቀድከሙ:: | ፴፩ | ንጉሡም ወደ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል እንደ ወደዳችሁ ትሠሩት ዘንድ ለምግባችሁ እህል ይስጧችሁ ብሎ ላከ:: |
| ፴፪ | ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኢንፈቅድ እክለከ እስመ ይኄይሰነ መዊት በረኀብ እምተሴስዮ እክለ ዚአከ:: | ፴፪ | አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም የአንተን እህል አንፈልግም የአንተን እህል ከመመገብ በረኀብ መሞት ይሻለናልና አለው:: |
| ፴፫ | ወሰሚዖ ንጉሥ ዘንተ ተምዐ ወአዘዘ ከመ ኢያቅርቡ ኀቤሆሙ ኢእደ ወኢአንስተ ከመ ኢይሀብዎሙ ዘይበልዑ:: | ፴፫ | ንጉሡም ይህን ሰምቶ ተቈጣ ወንዶችንም ሴቶችንም ወደ እነርሱ እንዳይቀርቡ የሚበሉትም እንዳይሰጥዋቸው አዘዛቸው:: |
| ፴፬ | ወይቤ እምከመ ረከቦሙ ዐጸባ ወረኀብ ይትመጠዉ:: እምእዴየ ወእሙንቱሂ አጥብዑ ከመ ኢይትመጠዉ እምእዴሁ:: | ፴፬ | ችግርና ረኀብ ካገኛቸው ከእጄ ይቀበላሉ አለ፤ እነርሱም ከእጁ ላለመቀበል ጨከኑ:: |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፫ ወረከብዎ ሐራሁ ለንጉሥ ለአሐዱ መነኮስ እንዘ ይጸውር ሐምለ ዘነሥአ በሤጡ ወወሰድዎ ወአብጽሕዎ ኀበ ንጉሥ ወአዘዘ ከመ ይዝብጥዎ በጥብጣቤ ወሞተ ውእቱ መነኮስ እንዘ ይዘብጥዎ።

፴፫ የንጉሡም ወታደሮች አንዱን መነኩሴ በዋጋ የገዛውን ጎመን ተሸክሞ አገኙት ወስደው ወደ ንጉሡ አደረሱት፤ በጅራፍም እንዲገርፉት አዘዘ ያም መነኩሴ እየገረፉት ሳለ ሞተ።

፴፬ ወካዕበ አዘዘ ንጉሥ ከመ ይሰድዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ምድረግሎ ማከዳ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንሰ ኢየሐውር ወእምዝ አዘዘ ንጉሥ ከመ ይንሥእዎ በኀይል ምስለ ደቂቁ ወነሥእዎሙ በኀይል።

፴፬ ዳግመኛም ንጉሡ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ወደ ገሎ ማከዳ ይወስዱት ዘንድ አዘዘ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም እኔ ከዚህ አልሔድም አለው ከዚህ በኋላ ንጉሥ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በኀይል /በግድ/ እንዲወስዱት አዘዘ በግድም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወሰድዋቸው።

፴፭ ወሖረ ውእቱኒ በሰላመ እግዚአብሔር ምስለ ደቂቁ ወእንዘ የሐውር ፩ ዕለተ ቀደሞሙ በፍኖት እምኲሎሙ ደቂቁ።

፴፭ እርሱም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በእግዚአብሔር ሰላም ሔደ። አንድ ቀንም ሲሔድ ሁሉንም ደቀ መዛሙርት ቀደማቸው።

፴፮ ወሶበ በጽሑ ይቤሎሙ ምንትኑዝ በላዕሌክሙ ወይቤልዎ ደቂቁ ንስቲት ሐሪጽ ዘይከውን ድራረ ለሕሙማን።

፴፮ በደረሱም ጊዜ በእናንተ ያለው ይህ ምንድን ነው? አላቸው። ለሕሙማን ራት የሚሆን ትንሽ ዱቄት ነው አሉት።

፴፯ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንትሙኑ ትኄይሱ ኀልዮ ሲሳይ ለሕሙማን እምአቡሆሙ ዘበሰማያት። ወነሥአ ኲሎ ጾረ ዘውስተ መትከፍቶሙ ወገደፈ ወስተ ምድር ኢኀደገ ሎሙ ኢሐሪጸ ለደራር ወኢመስነቅተ ለፍኖት ኢጸሕለ በዘይበልዑ ወኢጽዋዐ በዘይሰትዩ።

፴፯ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ከሰማያዊ አባታችሁ ይልቅ ለሕሙማን ምግብ በማሰብ እናንተ ትሻላላችሁን አላቸው በትከሻቸው የተሸከሙትን ሁሉ ይዞ ወደ ምድር ጣለው። ለእራት የሚሆን ዱቄትን በመንገድ የሚይዙበትን ከረጢትም ቢሆን የሚበሉበትን ጻሕልና የሚጠጡበትን ጽዋም አልተወላቸውም።

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፵ ወኢያትረፈ እምነ ኲሉ ቄሳቁሲሆሙ ዘእንበለ ምርጉዝ ዘውስተ እደዊሆሙ ወመከርየ ሐጺን በዘይቀበሩ ምውታኒሆሙ ወአዘዘ ይቅድምዎ ወዘንተ ገብረ ከመ ኢያንሥኡ ዘገደፈ

፵ በእጃቸው ካለ በትርና ሙታንን ከሚቀብሩበት የብረት መቆፈሪያ በስተቀር ምንም አላስቀረም፤ ቀድመውትም እንዲሔዱ አዘዘ፤ የጣለውን እንዳያነሡ ይህን አደረገ፡፡

፵፩ አንከርዎ ለዝ ብእሴ እግዚአብሔር ዘገደፋ ለነፍሱ ኀበ እግዚአብሔር ወእግዚአብሔር ተወከፋ ለነፍሱ ከመጽንሓሐ ዕጣን ሣቀያ ለነፍሱ በጾም ወበትሕርምት በቀዊም ወበሰጊድ በከዊነ ስምዕ ወበቅሥፈታት፡፡

፵፩ ነፍሱን በእግዚአብሔር የጣላት ይህን የእግዚአብሔር ሰው አድንቁት እግዚአብሔርም ነፍሱን እንደ ዕጣን መሥዋዕት ተቀበላት ነፍሱን በጾም፣ በትርሕምና፣ በመቆም፣ በስግደት፣ ሰማዕት /ምስክር/ በመሆን በግርፋትም አሠቃያት፡፡

፵፪ ወበቤተ መቅደስኒ ይተግህ ከመ መላእክት እምቅድመ ቅኔ ወበገብረ ሌሊትኒ ይሰግድ ይውሕዝ ሐፉ ከመ አንቅዕተ ማያት፡፡

፵፪ በቤተ መቅደስም የቅኔ ማኅሌቱ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት እንደ መላእክት በትጋት ያመሰግናል በሌሊትም ሲሰግድ ወዙ እንደ ፈሳሽ ውኃ ይወርዳል፡፡

፵፫ ወእምዝ ይወፅእ እምቤተ መቅደስ ወይበውእ ውስተ ቤተ መንደድ፡፡ ወይነሥእ ፍሕመ በመውስደ እሳት ወይወዲ ውስተ ማዕጠንት ወየዐጥን እንዘ የዐውድ ምሥዋዐ ወጸሎተ ዕጣን ይደግም በአፉሁ ወያርሕስ በነቅዐ አንብዑ ዐውደ ምሥዋዕ፡፡

፵፫ ከዚህ በኋላ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ እሳት ወደሚነድበት ይገባል፤ በእሳት መውሰጃም ፍሕሙን ወስዶ በማዕጠንቱ ጨምሮ መሠዊያውን እየዞረ ያጥናል፤ ጸሎተ ዕጣንም በአፉ ይደግማል፤ በእንባውም መሠዊያውን ያርሰዋል፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፺፬ ወዲበ ጸሎተ ዕጣን ይዌሰክ አንብቦ መዝሙር ዘ፻፲ወ፰ እንዘ ይብል አሌፍ ብፁዓን እለ ንጹሓን እስከ ተፍጻሜቱ፡፡

፺፬ በጸሎተ ዕጣንም ላይ መቶ ዐሥራ ስምንተኛውን መዝሙር "በመንገዳቸው ንጹሓን የሆኑ" እያለ እስከ መጨረሻው ይጸልያል፡፡

፺፭ ወካዕበ ይሰግድ በከመ ቀዳሚ ወየዐጥን እንዘ ይበኪ ወይትማሐለል ወከመዝ ይገብር ፲ወ፪ ጊዜ ወእምዝ የሐውር ኀበ ምስካበሙ ለቅዱሳን ወይቤሎሙ ጥቅዑ ደወለ ከመ ይትጋብኡ ለቅኔ ገብረ ሌሊት፡፡

፺፭ ዳግመኛም እንደ መጀመሪያው ይሰግዳል እያለቀሰም ያጥናል ዐሥራ ሁለት ጊዜም እንደዚህ ያደርጋል፤ ከዚህ በኋላ ቅዱሳን ወደተኙበት ይሔዳል ለማኅሌቱ አገልግሎት ይሰበሰቡ ዘንድ ደወል ደውሉ ይላቸዋል፡፡

፺፮ ወውእቱሰ ይበውእ ውስተ ጸማዕቱ ወይበይት እንዘ ይግዕር ከመ መጸብሐዊ ወእንዘ ይዘብጥ እንግድዓሁ በኀይል ወይበኪ ከመ ዘማዊት ዘሐጸበት እገሪሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ በአንብዓ ወለለ ጽባሑ ይነድድ ልቡ በፍቅረ አምላኩ፡፡

፺፮ እርሱ ግን ወደ ዋሸው ገብቶ እንደዚያ ቀራጭ እየጮኸና ደረቱንም እየደቃ ያድራል በእንባዋ የጌታችን ኢየሱስን እግር እንዳጠበች ዘማዊትም ያለቅሳል፤ በየ ቀኑም ልቡ በአምላኩ ፍቅር ይቃጠላል፡፡

፺፯ ወአልቦ አመ ይቄርር ወለለዕለቱ ይትኄየል ከመ ይባእ እንተ መቃዐን ውስተ ገድለ ቅድሳን በጸዊም ዘምስለ ትርሕምት ወበቀዊም ዘምስለ ሰጊድ በከዊነ ስምዕ ዘምስለ ቅሥፈታት በከዊነ ሐዋርያ ዘምስለ ስብከት በከዊነ ነቢይ ምስለ ራእየ ኅቡኣት

፺፯ የሚቀዘቅዝበትም ጊዜ አልነበረም፡፡ ከትርሕምት ጋር በመጾም ከስግደትም ጋር በመቆም፣ ከግርፋትም ጋር ምስክር በመሆን፣ ከስብከትም ጋር ሐዋርያ በመሆን፤ ምስጢራትን ከማየት ጋር ነቢይ በመሆን፣ ጭንቅ /ከባድ/ ወደ ሆነ የቅዱሳን ገድል ይገባ ዘንድ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፵፰ ወይነግሮሙ ለአኀው ይኩን ዘሀሎ ከመ ዘሀለወ ወሎሙኒ ይነግሮሙ ዘገብሩ ኀጣውኢሆሙ፡፡

፵፱ ወይቤሎሙ አንተ ዘንተ ገበርከ ወከመዝ ነስሐ ከመዝ ጹም ወእሙንቱሂ ይፈርህዎ በኀበ ኢሀሎ ከመ ዘሀሎ ምስሌሆሙ ወይሬስይዎ ከመ ዘይሬእዮሙ፡፡

ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምሳሌነ ለዓለም ዓለም አሜን፡፡

፵፰ ለወንድሞችም ይሆን ዘንድ ያለውን እንደ ሆነ ይነግራቸዋል ለእነርሱም ያደረጉትን ኀጢአት ይነግራቸዋል፤

፵፱ አንተ ይህን አድርገሃል እንደዚህ ንስሓ ግባ እንደዚህም ጹም ይላቸዋል፡፡ እነርሱም ባልነበረበት ጊዜ እነርሱ ጋር እንዳለ በመቁጠር ይፈሩታል እንደሚያያቸውም ያደርጉታል፡፡

ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ለዘላለሙ ይኑር አሜን፡፡

## ምዕራፍ ፲፩

፩ ወይእዜኒ ንግባእ ኀበ ዜና ነገር ከመ ንዜኑ ዘከመ አብጽሕዎ ምድረ ግሎ ማኪዳ፡፡

፪ ወሶበ በጽሐ ተቀበልዎ ቅዱሳን በፍሥሓ ወበሐሤት ወዘውእቱ አስማቲሆሙ ማርቆስ ወክርስቶስ አምነ ወአባ ሲኖዳ ወማማስ፡፡

፫ ወሶበ ርእይዎ ተፈሥሑ ፈድፋደ ወይቤሎ ማማስ አነ አርእየከ በአተ ኰኵሕ ኀበ ትገብር ለከ ጾማዕተ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል በል ምርሐኒ ወአርአዮ ውእቱ በአተ ኰኵሕ ወተፈሥሐ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ሶበ ርእያ ለይእቲ በአተ ኰኵሕ ወደቂቁሰ ጸልእዎ፡፡

## ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

፩ አሁንም ወደ ግሎ ማኪዳ ምድር እንዳደረሱት እንናገር ዘንድ ዜናውን ወደ መናገር እንመለስ፡፡

፪ በደረሰም ጊዜ ቅዱሳን በፍጹም ደስታ ተቀበሉት፤ ስማቸውም ይህ ነው ማርቆስ፣ ክርስቶስ አምነ አባ ሲኖዳ እና ማማስ፡፡

፫ ባዩትም ጊዜ እጅግ ደስ አላቸው ማማስም ማደሪያ የምሠራበት የዐለት ዋሻ እኔ አሳይሃለሁ አለው አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም በል አሳየኝ አለው እርሱም የድንጋዩን ዋሻ አሳየው አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ያችን የድንጋይ ዋሻ ባያት ጊዜ ደስ አለው፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ጠሉት፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፬ ወይቤልዎ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኀድግ አባ ዘተ መካነ እስመ ሕስምት ይእቲ ወጽንዕት ንኅሥሥ ለከ ካልአ መካነ ዘይኤድም ለዐይን፡፡

፬ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልንም አባታችን ሆይ ይህችን ቦታ ተው መጥፎ ናትና ለዐይን ደስ የሚያሰኝ ሌላ ቦታ እንፈልግልህ አሉት፡፡

፭ ወይቤሎሙ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ወዝየ አኀድር እስመ ኀረይክዋ ወአኀዘ ይቅሪ ይእተ ኰኵሐ ወደቂቁኒ ወቀሩ ምስሌሁ እንዘ የሐዝኑ በልቦሙ፡፡

፭ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም ይህች ለዘለዓለሙ ማረፊያዬ ናት፤ በዚህ እኖራለሁ፤ መርጫታላሁና አላቸው፤ ያንም ድንጋይ ይወቅር ጀመር ደቀ መዛሙርቱም በልባቸው እያዘኑ ከእርሱ ጋር ጠረቡ፡፡

፮ ወበዕለተ ዐርብ ለአከ ኀበ ቅዱሳን ማርቆስ ወክርስቶስ አምነ ወአባ ሲኖዳ እንዘ ይብል ሰኑየ በነግህ ንዑአ ምስለ ደቂቅክሙአ ከመ ትክርዩአ መቃብርየ፡፡

፮ ዓርብ ቀንም ቅዱሳን ወደ ሆኑ ማርቆስና ክርስቶስ አምነ ወደ አባ ሲኖዳም መቃብሬን ትቆፍሩ ዘንድ ከተማሪዎቻችሁ ጋር ሰኞ በጥዋት ኑ ብሎ ላከ፡፡

፯ ወበሳኒታ በሰንበተ አይሁድ ወፅአ አፍአ ከመ ይርአይ ሀገረ ወምስሌሁ ወልዱ ዕንባቆም ወረከቡ መቃብረ ሐዲሰ እንዘ ይወፅእ በድን እምውስቴቱ፡፡

፯ በማግሥቱም በቀዳሚት ሰንበት ሀገር ያይ ዘንድ ወደ ውጭ ወጣ፤ ከእርሱም ጋር ደቀ መዝሙሩ ዕንባቆም ነበር ከውስጡ በድን የሚወጣበት አዲስ መቃብርን አገኙ፡፡

፰ ወይቤሎ ዕንባቆም ኢጼአከኑ አባ ወይቤሎ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንተሂ ጌሠመ ትገድፎ ለአቡከ ውስተ መቃብር ወይቤሎ ዕንባቆም ወልዱ ለመቃብርኑ ኢንበቀ፡ዐከ አ አባ፡፡

፰ ዕንባቆምም አባት ሆይ አልሸተተህምን? አለው አባታችን በጸሎተ ሚካኤልም አንተም ነገ አባትህን ወደ መቃብር ትጥለዋለህ አለው፤ ደቀ መዝሙር ዕንባቆምም አባት ሆይ ለመቃብርም ሳንሆንህ እንቀራለን አለው፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፱ | ወዘንተ ነገረ እምድኅረ ተበሃሉ ገብኡ ኀበ ማኅደሪሆሙ ወበሳኒታ ዕለተ እሑድ ወዐለ እንዘ ይምዕዶሙ ለደቂቁ በመጽሐፈ ነቢያት ወኤፍሬም | ፱ | ይህን ነገር ከተባባሉ በኋላ ወደየቤታቸው ገቡ፤ በማግሥቱም እሑድ ቀን ደቀ መዛሙርቱን በነቢያት መጽሐፍና በኤፍሬም ውዳሴ ሲመክራቸው ዋለ፡፡ |
| ፲ | ወእንዘ ይምዕዶሙ ይበኪ ወይግዕር ወሶበ መስየ ጸለየ በአስተርክቦ እስከ መንፈቀ ሌሊት ወእስከ ንቅወተ ደርሆ፡፡ | ፲ | ሲመክራቸውም ያለቅስና ይጮህ ነበር በመሸም ጊዜ እስከ ሌሊት እኩሌታና እስከ ዶሮ ጩኸት ተንበርክኮ ጸለየ፡፡ |
| ፲፩ | ወእምዝ ይቤሎ ለአሐዱ ረድእ ዘስሙ አቤል ነዐ ንረድ ውስተ በአት ወእምዝ ወፅአ እኂዞ ምርጉዘ ወቦአ ውስተ በኣት ወጸለየ በከመ ያለምድ፡፡ | ፲፩ | ከዚህ በኋላ ስሙ አቤል የሚባል አንዱን ደቀ መዝሙርና ወደ ዋሻው እንውረድ አለው ከዚያም ምርጉዙን ይዞ ወጣ ወደ ዋሻውም ገብቶ እንዳስለመደ ጸለየ፡፡ |
| ፲፪ | ወእምዝ ይቤሎ ለውእቱ ረድእ ሑር ጸውዖሙ ለአኀዊከ ወእምደኀረዝ ዐተበ ገጾ በትእምርተ መስቀል ወዐተባ ለገጸ መካን እንተ ፬ ገበዋቲሃ፡፡ | ፲፪ | ከዚህ በኋላ ያን ደቀ መዝሙር ሒድ ወንድሞችህን ጥራቸው አለው ከዚህ በኋላ በመስቀል ምልክት ፊቱን ዐማተበ ቦታውንም በአራቱ መዓዝን ባረካት፡፡ |
| ፲፫ | ወእምዝ ሰፍሐ እደዊሁ ወእገሪሁ ወመጠወ ነፍሶ ውስተ እደ ፈጣሪሁ ወሞተ ዘእንበለ ጻዕር በከመ ይቤ ዳዊት ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር፡፡ | ፲፫ | ከዚህ በኋላ እጁንና እግሩን ዘረጋ፡፡ ነፍሱንም በፈጣሪው እጅ ሰጠ፡፡ ዳዊት የጽድቅ ሰው ሞት በእግዚአብሔር ፊት ክቡር ነው እንዳለ ያለ ጻዕር ሞተ፡፡ |
| | መዝ.፻፲፭፥፮ | | መዝ.፻፲፭፥፮ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፬ | ወወፅአት መንፈሱ ንጽሕት እምነ ንጽሕት ሥጋ ወነገደት ኀቤሁ ለመኰንነ ጽድቅ ከመ ይንሣእ አክሊለ ስምዕ በእንተ ቅሥፈታቲሁ ወአክሊለ ንጽሕ በእንተ ድንግልናሁ ወአክሊለ ክህነት በእንተ መዐዛ ትምህርት፡፡ | ፲፬ | ንጽሕት ነፍሱ ከቅድስት ሥጋው ስለ ግርፋቱ የሰማዕትነት አክሊልን፣ ስለ ድንግልናውም የንጽሕና አክሊልን፣ ስለ ትምህርቱ መዓዛም የክህነት አክሊልን ይቀበል ዘንድ ወደ እውነት ፈራጅ ሔደች፡፡ |
| ፲፭ | ትትፌሣሕ ፍጹመ በሐሤት ተስፋሃ ዘዚአሃ እስመ አልቦ ዘተርፋ እምገድለ ቅዱሳን፡፡ | ፲፭ | ቅዱሳን ከተቀበሉት መከራ የቀረባት የለም ተስፋ አድርጋው በኖረች ሐሴት ፈጽሞ ደስ ይላታል፡፡ |
| ፲፮ | ንግባእኬ ኀበ ጥንተ ዜና ሞቱ ወሶበ በጽሑ ደቂቁ ረከብዎ ዘከመ ሞተ፡፡ | ፲፮ | ወደ ቀደመ የዕረፍቱ ዜና እንመለስ ደቀ መዛሙርቱ በደረሱ ጊዜ እንዳረፈ አገኙት፡፡ |
| ፲፯ | ወድቁ ውስተ ምድር ወከልሑ እንዘ ይብሉ ኦ አባ ኦ አባ ዕንቊ ክቡር እፎ ተገደፍከ በገጸ ገዳም አባ አባ ወርቅ ንጡፍ ወብሩር ጽሩይ እፎ ተዘገብከ ውስተ በአት ጽይዕት ኦ አባ አባ መልአክ ዘበምድር መኑ ለጐሞ ለአፉከ ወመኑ አጽርአ ለስብሐተ ከናፍሪከ፡፡ | ፲፯ | በግንባራቸውም ወደ መሬት ተደፍተው እንዲህ እያሉ አለቀሱ፡፡ አባት ሆይ አባት ሆይ አንተ የከበረ ዕንቊ ስትሆን እንዴት በበረሃ ወደቅህ? አባት ሆይ አባት ሆይ ንጹሕ ወርቅ የጠራም ብር ስትሆን በምትሸት ዋሻ እንዴት ተሰበሰብህ አባት ሆይ አባት ሆይ ምድራዊ መልአክ ስትሆን አፍህን ማን ዘጋው? የከንፈሮችህንስ ምስጋና ማን አስቀረው፡፡ |
| ፲፰ | ኦ አባ አባ መኑ ይነግረነ እም ይእዜ ኀጣውኢነ ዘገበርነ በኀቡእ ወይጌሥጸነ ከመ ንትመየጥ፡፡ | ፲፰ | አባት አባት ከዛሬ ጀምሮ በስውር የሠራነውን ኀጢአት ማን ይነግረናል፡፡ እንመለስስ ዘንድ ማን ይገሥጸናል፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፱ | አባ አባ መኑ ሐዋርያ ዘይሰብክ እምይእዜ በዐውደ ነገሥት ወይከውን ላቲ ቀዋሚ ለቤተ ክርስቲያን፡፡ | ፲፱ | አባ አባት ሆይ ከዛሬ በኋላ በነገሥታት ዐደባባይ የሚሰብክ፣ ለቤተ ክርስቲያንም ጠበቃ የሚሆንለት ሐዋርያ ማን ነው? |
| ፳ | አባ አባ ሰማዕተ ክርስቶስ መኑ እምይእዜ ዘይቀንዕ በእንተ ዐቂበ ትእዛዝ ወይትወከፍ ሕማማተ በእንተ ሕጉ ወሥርዐቱ፡፡ | ፳ | አባ አባት ሆይ ከዛሬ ጀምሮ የክርስቶስ ምስክር የሚሆን ትእዛዙስ ስለ መጠበቅ የሚቀና፣ ስለ ሕጉና ስለ ሥርዐቱም መከራን የሚቀበል ማን ነው? |
| ፳፩ | አባ አባ አበ መነኮሳት መኑ ይምዕዶሙ ለባሕታውያን ወይሔውጾሙ ለገዳማውያን፡፡ | ፳፩ | የመነኮሳት አባት አባት ሆይ ባሕታውያንን ማን ይመክራቸዋል? ገዳማውያንንስ ማን ይጐበኛቸዋል / ይጠይቃቸዋል/? |
| ፳፪ | አባ አባ ዐምደ ሃይማኖት መኑ ያጸንዓ ለቤተ ክርስቲያን በዘ ኢትትነሡት አረፍታ ወዘኢያንቀለቅል ቀመራ፡፡ | ፳፪ | አባት አባት ሆይ የሃይማኖት ምሰሶ ነህ የቤተ ክርስቲያንን ግድግዳዋ እንዳይፈርስ ጣራዋም እንዳይነዋወጥ ማን ያጸናታል? |
| ፳፫ | አባ ኖላዊ መኑ ይሬዒ አባግዒከ ውስተ ቤተ ነቢያት ወያአትዎን ውስተ አጸደ ሐዋርያት፡፡ | ፳፫ | አባት መልካም እረኛ ነህ በነቢያት ቤት በጎችህን ማን ይጠብቃቸዋል በሐዋርያትስ በረት የሚያስገባቸው ማን ነው? |
| ፳፬ | አባ አባ ተቅዋመ ማኅቶት መኑ ያበርህ እምይእዜ ውስተ ምድረ ኢትዮጵያ፡፡ | ፳፬ | አባ አባት ሆይ የብርሃን መቅረዝ ነህ እንግዲህ በኢትዮጵያ የሚያበራ ማን ነው? |
| ፳፭ | አባ አባ ንጹሕ ከመ ሐሊብ አባ አባ ጥዑም ከመ መዐር አባ አባ ምዑዝ ከመ ዕፍረት ዘአልበስጥሮስ፡፡ | ፳፭ | አባ አባ እንደ ወተት ንጹሕ ነህ አባ አባ እንደ መዐርም የምትጣፍጥ ነህ፡፡ አባት አባት እንደ አልባስጥሮስ ሽቱም መዓዛህ ጣፋጭ ነው፡፡ |

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳፪ | አባ አባ ሞሉአ በረከት ከመጠለ አርሞንኤም ዘይወርድ ዲበ አድባረ ጽዮን፡፡ | ፳፪ | አባ አባ በጽዮን ተራራ እንደሚወርድ እንደ አርሞንኤም ጠልም በረከትን የተመላህ ነህ፡፡ |
| ፳፯ | አባ አባ ፍሡሕ ዘያስተፌሥሕ ቃላቲሁ እምወይን፡፡ | ፳፯ | አባ አባት ሆይ ደስ የተሰኘህ ነህ፡፡ ቃልህም ከወይን ይልቅ ደስ ያሰኛል፡፡ |
| ፳፰ | አባ አባ መምህር ዘይጸብት እምቃለ መጻሕፍት ወከሣቴ ኅቡኣተ ኦሪት ወነቢያት፡፡ | ፳፰ | አባት አባት በመጻሕፍት ቀል የምትዋኝ በኦሪትና በነቢያት የተሰወረውን ምስጢርም የምትገልጽ ነህ፡፡ |
| ፳፱ | ወፈጺሞሙ ሰቈቃወ ቀበርዎ ደቂቁ ምስለ ፬ቱ እደው ጻድቃን ወቅዱሳን ውስተ በኣተ ኰኵሕ ዘወቀረ ለሊሁ ከመ ትኩኖ ጾማዕተ፡፡ | ፳፱ | ልቅሶአቸውንም ከፈጸሙ በኋላ ጻድቃንና ቅዱሳን ከሆኑ አራት ሰዎች ጋር ማረፊያ ትሆነው ዘንድ ራሱ በጠረባት የድንጋይ ዋሻ ቀበሩት፡፡ |
| ፴ | ናስተበፅዓ ለይእቲ ኰኵሕ እስመ ተመሰለት በበኣተ ካእበት ዘገራህተ ኤፍሮን ኬጥያዊ ዘተቀብሩ ውስቴቱ አብርሃም ይሰሐቅ ወያዕቆብ፡፡ | ፴ | ያችን ዐለት እናመሰግናታለን አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብም በውስጡ በተቀበሩበት ድርብ ክፍል ባላት በኬጢያዊው በኤፍሮን እርሻ ትመሰላለችና፡፡ |
| ፴፩ | ካዕበ ተመሰለት በኰኵሐ ኮሬብ ዘአስተርአየ በውስቴታ መዕዘሪሁ ለእግዚአብሔር እንተ ስቍረተ ኰኵሕ፡፡ ዘፀ.፴፫፥፳፩ | ፴፩ | ሁለተኛም የእግዚአብሔር ጀርባ በተሰነጠቀ ዐለት በታየባት በኮሬብ ዐለት ትመሰላለች ዘፀ.፴፫፥፳፩ |
| ፴፪ | ወዓዲ ተመሰለት በኰኵሐ እንተ ሰጠቃ ኤርምያስ ወወደየ ውስቴታ ንዋየ ግበሪሃ ለደብተራ ወእምዝ ኮነቶ ከመ ግልወተ ሐጺን፡፡ | ፴፪ | ዳግመኛም ኤርምያስ በሰነጠቃት የደብተራ ኦሪትንም ንዋያተ ቅድሳት ባስቀመጠበት ዐለት ተመሰለች ከዚህ በኋላ እንደ ብረት መሸፈኛ ሆነችው፡፡ |

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፴፫ ወካዕበ ተመሰለት በኰኵሕ ዘአድያመ ግብጽ ዘተሥዕለ እራኀ እግዚእ ዲቤሃ ከመ ዘጽቡር ናሁ ዐሠረ እዴሁ እስከ ዮም፡፡

፴፫ ዳግመኛም በግብጽ አውራጃ ባለች የጌታችን መሐል እጅ በጭቃ እንደሚሣል በተሣለበት ዐለት ተመሰለች እነሆ የእጁ ምልክት እስከ ዛሬ አለ፡፡

፴፬ ንግባእ እንከሰ ንንግር ዘከመ ነበሩ ቅዱሳን ውስተ ይእቲ መካን በሐዘን ወበብከይ እስመ ፈላስያን እሙንቱ ወኢያእመሩ ግእዘ ብሔር ወሰብአ ሀገርኒ እኩያን ጥቀ እሙንቱ ወአልቦሙ ምሕረተ እግዚአብሔር ውስተ ልቦሙ፡፡

፴፬ ቅዱሳን በዚያች ቦታ በኀዘንና በልቅሶ እንደነበሩ እንናገር ዘንድ እንመለስ፡፡ ስደተኞች ናቸውና የሀገሩንም ጠባይ ዐያውቁም፤ የሀገሩም ሰዎች እጅግ ክፉዎች ነበሩ የእግዚአብሔርም ምሕረት በልባቸው አልነበራቸውም፡፡

፴፭ ወእምድኅረ ጉንዱይ መዋዕለ ዓመታት ፈቀዱ ደቂቀ ከመ ያፍልስዎ ኀበ ካልእ መካን በጽሚት፡፡

፴፭ ከብዙ ዓመታት በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ዐፅሙን ወደ ሌላ ቦታ በስውር ሊያፈልሱት ወደዱ፡፡

፴፮ ወሶበ አውፅኡ አዕፅምቲሁ ዘየብሳ ብዙኀ ቆሙ ወኢተክሀሎሙ ከመ ያብእዎ ውስተ ሳጹን እስመ ነዊኀ አጥብአ ወአኀዘ አቀኍይዖጸ እገሪሁ ከመ ይእጽፍ አብራኮ ወእምዝ ውሕዘ ደም ዐቢይ ከመ ዘሕያው ብእሲ፡፡

፴፮ የደረቁ ዐፅሞቹንም ባወጡ ጊዜ ብዙ ሰዓት ቆሙ ወደ ሳጥኑም ማስገባት አልተቻላቸውም ረጅም ነውና አንድ ሰውም ጉልበቱን ያጥፍ ዘንድ የእግሩን መገጣጠሚያ አጥብቆ ያዘ፡፡ ከዚያም በሕይወት እንዳለ ሰው ብዙ ደም ፈሰሰ፡፡

፴፯ ወአንከሩ ቅዱሳን በእንተ ዘውሕዘ ደም እምዐፅም ዘበልየ ወለውእቱ ብእሲ ተምዕዎ እስመ ደፈረ ዐጼፈ ዐፅመ አብራኪሁ ለሰማዕተ ክርስቶስ፡፡

፴፯ ቅዱሳንም ከቆየው ዐፀም ስለፈሰሰው ደም አደነቁ፡፡ ያንም ሰው ተቈጡት የክርስቶስ ሰማዕት የጉልበቶቹን ዐፅም ለማጠፍ ደፍሮአልና፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፴፰ | መንክርኬ ግብረ እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ ወእምድኅረ ሞቱሙሂ የዐቢ ሞገሶሙ እምዘ በሕይወቶሙ፡፡ | ፴፰ | የእግዚአብሔር ሥራ በቅዱሳን ላይ ድንቅ ነው፤ ከሞቱም በኋላ ባለሟልነታቸው በሕይወታቸው ከነበራቸው ባለሟልነት ይበልጣል፡፡ |
| ፴፱ | አማንኬ ዘይቤ ዳዊት ብዙኅ ሕማሞሙ ለጻድቃን ወእምኩሉ ያድኅኖሙ እግዚአብሔር እግዚአብሔር የዐቅብ ኲሎ አዕፅምቲሆሙ ወኢይትቀጠቀጥ አሐዱ እምውስቴቶሙ መዝ.፴፫፥፲፱ | ፴፱ | ዳዊት "የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፡፡ እግዚአብሔርም ከሁሉ ያድናቸዋል፤ እግዚአብሔር አጥንቶቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል፤ ከእነርሱም አንዱ አይሰበርም" ያለው እውነት ነው፡፡ መዝ.፴፫፥፲፱ |
| ፵ | ወእምዝ አፍለሱ አዕፅምቲሁ ለሰማዕት ውስተ ካልእ መካን ወአንበሩ ህየ እስከ ምጽአቱ ለአባ ያዕቆብ ዐቢይ ጳጳስ ዘኢትዮጵያ ወአዘዘ ውእቱ ከመ ያምጽኡ ሎቱ አዕፅምቲሁ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡፡ | ፵ | ከዚህ በኋላ የሰማዕቱን ዐፅም ወደ ሌላ ቦታ አፈለሱት /ወሰዱት/ እስከ ኢትዮጵያ ጳጳስ አባ ያዕቆብ መምጣትም ከዚያ አስቀመጡት፤ እርሱም የአባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ዐፅም ያመጡለት ዘንድ አዘዘ፡፡ |
| ፵፩ | ወሶበ አብጽሑ ሎቱ ተፈሥሐ ዐቢየ ፍሥሓ ወአንፈርዓጸ ከመ ሕፃን ዘይትፌሣሕ ሶበ ይሬእያ ለእሙ ወገብረ ላዕሌሁ በጸሎተ ቅዳሴ ዘይደሉ ላዕለ አዕፅምተ ሰማዕት፡፡ | ፵፩ | በመጡለትም ጊዜ ታላቅ ደስታ ደስ አለው እናቱን ባያት ጊዜ እንደሚደሰት ሕፃንም ዘለለ፡፡ ለሰማዕታት ዐፅም የሚገባውን የቅዳሴ ጸሎትም አደረገለት /አደረሰለት/፡፡ |
| ፵፪ | ወተቀደሰ ለለአሐቲ እመናቅዐ አዕፅምቲሁ ለሰማዕት በበመሌሊቱ እንዘ ይደግም ጸሎተ ቅዳሴ ወየአትም በቅብዐ ዘይቶን፡፡ | ፵፪ | የሰማዕቱንም ዐፅም መለያያ እያንዳንድዋን በየአካሉ ጸሎተ ቅዳሴ እየደገመ በሜሮንም ቅባት እያተመ /እየቀባ/ ተቀደሰ፡፡ |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፺፫ ወእምዝ ባረኮሙ ለደቂቁ ወይቤሎሙ ኀበ ሀሎ ዝ ዐፅም ኢይኩን ውስቴቱ ሞተ ብድብድ ወኢኀጢአ እክል ወኢአባረ ዝናም ወዘንተ ብሂሎ ባረከ ሖረ ወአተወ ብሔሮ፡፡

፺፫ ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ይህ ዐፅም ባለበት የመቅሠፍት ሞት የእህል እጦት፣ የዝናም እጥረት አይሁን ብሎ ባረካቸው ይህንም ብሎ ከባረከ በኋላ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

፺፬ ወእምአሜሃ አልቦ ዘኮነ ወኢምንተኒ እስከ ዮም ኀበ ሀሎ አዕፅምቲሁ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኢሞተ ብድብድ ወኢኀጢአ እክል ወኢአባረ ዝናም እስመ ጸጋ እግዚአብሔር ይተልዎ ኀበ አፍለስዎ ወኀበ አንበሩ ሥጋሁ፡፡

፺፬ ከዚያ ቀን ጀምሮ የአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ዐፅም ባለበት እስከዛሬ ድረስ የመቅሠፍት ሞት፣ የእህል እጦት የዝናም እጥረት /መታጣት/ ምንም አልሆነም /አልተከሠተም/ ዐፅሙን በወሰዱበትና ባስቀመጡበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ ይከተለዋልና፡፡

፺፭ እስመ ኀይለ መለኮት የዐውዶ በአመ ይቤ መጽሐፍ እስመ በጸሎተ ጻድቅ ትድኀን ወኢትማስን ሀገር በአማን ረከበት መድኀኒተ ዛ ሀገር ባሕርየ ክቡረ ዘብዙኀ ወዕጹብ ሤጡ፡፡

፺፭ የመለኮት ኀይል ይከበዋልና መጽሐፍ በጻድቅ ሰው ጸሎት ሀገር ትድናለች አትጠፋምም እንዳለ ይህችም ሀገር በእውነት የከበረ ዋጋውም እጅግ የበዛ መድኀኒትን አገኘች፡፡

፺፮ ወአዘዘ አባ ያዕቆብ ከመ ያንብሩ አዕፅምቲሁ በሳጹን ወኢይድፍንዎ በመሬት ውስተ ምድር

፺፮ አባ ያዕቆብም ዐፅሙን በሳጥን እንዲያስቀምጡት ከመሬትም በታች በአፈር እንዳይቀብሩት አዘዘ፡፡

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፵፺ ወተዝካረ ዕረፍቱሰ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ኮነ ፳ወ፩ ለወርኀ አጺፍ ሐምሌ በሐሳበ ግብጽ ወኢትዮጵያ ወበሐሳበ ሮምሰ አመ ፳ወ፫ ለወርኀ ኤዩሉሰ ወበሐሳበ ዕብራውያንሂ ወርኀ ትሙዝ እስመ ኅብረ ሡርቀ ክልኤሆሙ ዘሮማይስጥ ወዘዕብራይስጥ ወዕለቱሰ ሰኑይ እምድኅረ ንቅወተ ደርሆ፡፡

፵፺ የአባታችን በጸሎተ ሚካኤል የዕረፍቱ መታሰቢያ በግብጽና በኢትዮጵያ አቈጣጠር ሐምሌ ሃያ አንድ ቀን በሮማውያን አቈጣጠር በኤዩሉስ ወር በሃያ አምስተኛው ቀን በዕብራውያን አቈጣጠር ተሙዝ በተባለ ወር ነው፡፡ የሁለቱ የሮማውያንና የዕብራውያን የወራቸው ዕለት ገጥሞ /አንድ ሆኖ/ ነበርና ዕለቱም ሰኞ ከዶሮ ጮኸት በኋላ ነው፡፡

፵፰ ወንሕነኒ ንግበር ተዝካረ ለዘመጠነዝ ነቢይ ከመ ነቢያት ወለዘመጠነዝ ሐዋርያ ከመ ሐዋርያት ወለዘመጠነዝ ሰማዕት ከመ ሰማዕታት ወበዘመጠነዝ መምህር መስተጋድል ከመ ተዝካረ ጻድቃን ቅዱሳን፡፡

፵፰ እኛም እንደ ነቢያት የነቢይን ያህል እንደ ሐዋርያትም የሐዋርያትን ያህል እንደ ሰማዕታትም የሰማዕትን ያህል እንደ ቅዱሳን ጻድቃን መታሰቢያም የመምህራን ያህል ክብር ያለው የእርሱን መታሰቢያ እናድርግ፡፡

፵፱ እስመ ገድለ ኲሎሙ ቅዱሳን ይትረከብ በኀቤሁ፡፡ ወከመ ነቢያት ትንቢት ወከመ ሐዋርያት ስብከት ወከመ ሰማዕት ትዕግሥት ወከመ ጻድቃን ገድል፡፡ ወከመ ደናግል ንጽሕ ወከመ ካህናት ተልእኮ በንጽሕ ወከመ ገዳማውያን ጽሙና ወከመ ሰማዕታት ብሕትውና፡፡ ወኲሎሙ ቅዱሳን ገድሎሙ ወሃይማኖቶሙ ኢተርፈ እምኔሁ ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ አሜን፡፡

፵፱ የሁሉም ቅዱሳን ገድል በእርሱ ዘንድ ይገኛልና እንደ ነቢያት ትንቢት እንደ ሐዋርያትም ስብከት፣እንደ ሰማዕታት ትዕግሥት እንደ ጻድቃንም ተጋድሎ፡፡ እንደ ደናግል ንጽሕና እንደ ካህናት በንጽሕና ማገልገል እንደ ገዳማውያን ብቸኝነት፣ እደ ባሕታውያንም ብሕትውና በእርሱ ዘንድ ይገኛልና፡፡ የሁሉም ቅዱሳን ገድላቸውና ሃይማኖታቸው አልቀረበትምና፡፡
ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይኑር አሜን፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| ምዕራፍ ፲፪ | ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት |
|---|---|
| ፩ ኦ ሀገረ ሰግላ እፎ ረከብኪ ዘመጠነዝ ዕንቈ ዘየኀቱ ሥኑ ምስብዒተ እምፀሐይ ዘተወደሰ በአፈ እግዚኡ እንዘ ይብል ገብርየ ወምእመንየ ዘምስለ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ማኅደርከ ይኩን፡፡ | ፩ ሀገረ ሸገላ ሆይ በፈጣሪው አንደበት አገልጋዬና ታማኙ ሆይ ማደሪያህ ከጴጥሮስና ከጳውሎስ ጋር ይሁን ተብሎ የተመሰገነ ከፀሐይ ሰባት እጅ የሚያበራ እንደዚህ ያለውን ዕንቊ እንዴት አገኘሽ፡፡ |
| ፪ ወዘመጠነዝ ክብር ወብዕል ዘተወፈዩ እምኀበ እግዚአብሔር በአይቴ ኮነ ማኅደሮሙ ለጴጥሮስ ወለጳውሎስ ሊተሰ ይመስለኒ ሶበ እኄሊ ሰሚዕየ ዘይቤሎሙ በወንጌል አመ ተሰአሎ ጴጥሮስ ለእግዚእነ እንዘ ይብሎ ንሕነ ኀደግነ ኵሎ ወተሎናከ ምንተ እንከ ንረክብ፡፡ | ፪ ይህን ያህል ክብርና ሀብት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበሉ የጴጥሮስና የጳውሎስ ማደሪያቸው በየት ይሆን? ለእኔ ግን በወንጌል ጴጥሮስ ጌታችንን እኛ ሁሉን ትተን ተከተል እንግዲህ ምን እናገኛለን? ብሎ በጠየቀው ጊዜ ያለውን ሰምቼ ሳስብ ይመስለኛል፡፡ |
| ፫ ወይቤሎሙ እግዚእነ አማንየ እብለክሙ አንትሙሰ እለ ተሊለውክሙኒ አመ ዳግም ልደት አመ ይነብር ወልደ ዕጓለ እመሕያው ዲበ መንበረ ስብሐቲሁ አንትሙኒ ትነብሩ ዲበ ዐሠርቱ ወክልኤቱ መናብርት ወትኴንኑ ዐሠርተ ወክልኤተ ነገደ እስራኤል፡፡ ማቴ.፲፱፥፳፰ | ፫ ጌታችንም እንዲህ አላቸው እውነት እላችኋለሁ የተከተላችሁኝ በዳግም ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በተቀመጠ ጊዜ እናንተም በዐሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ በዐሥራ ሁለቱም ነገደ እስራኤል ትፈርዳላችሁ ፡፡ ማቴ.፲፱፥፳፰ |
| ፬ ወህየ ይሄሉ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል በከመ ቃሉ ለእግዚእነ ዘይቤሎ ምስለ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ይኩን ማኅደርከ | ፬ አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ማደሪያህ ከጴጥሮስና ከጳውሎስ ጋር ይሁን እንዳለው እንደ ጌታችን ቃል በዚያ ይኖራል፡፡ |

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፭ | ወበእንተ ዐሥራትሂ ተሰእልዎ ወይቤልዎ ካዕበ ዘይገብር ተዝካረ ወይትመሐፀን በጸሎትነ ወይጽሕፍ መጽሐፈ ገድልነ ምንት ዐስቡ:: | ፭ | ስለ ዐሥራትም ዳግመኛ መታሰቢያችን የሚያደርግ፣ በጸሎታችንም የሚማፀን፣ የገድላችን መጽሐፍ የሚጽፍ ዋጋው ምንድን ነው ብለው ጠየቁት:: |
| ፮ | ወይቤሎሙ ይኀልፍ ምሳሌከሙ በግህደት በደኅሪት ዕለት ወሎቱኒ ኢያሕጸጾ ምንተኒ እምኔሆሙ ኢማኅደረ ወኢክብረ ወኢዐሥራተ በከመ ወሀበ ማኅደረ ምስሌሆሙ ወከማሁ ይጸግዎ ዐሥራተ:: | ፮ | በመጨረሻው ቀን ከእናንተ ጋር በግልጽ ይለፍ አላቸው:: እርሱንም ከእነርሱ በምንም አላሳንሰውም በቤትም ቢሆን በክብርም ቢሆን በዐሥራትም ቢሆን ከእነርሱ ጋር ማደሪያ እንደሰጠው እንዲሁም ዐሥራት ይሰጠዋል:: |
| ፯ | ወከመ አሥመርዎ እሙንቱ ውእቱኒ አሥመሮ ወበከመ ኀደጉ እሙንቱ ኵሎ ዓለመ ውእቱኒ ከማሆሙ ኀደገ ዓለመ ወኵሎ ዘውስቴቱ:: | ፯ | እነርሱ ደስ እንዳሰኙት እርሱም ደስ አሰኘው:: እነርሱ ዓለሙን ሁሉ እንደተዉ፤ እርሱም እንደ እነርሱ ዓለሙንና በውስጡ ያለውንም ሁሉ ተወ:: |
| ፰ | ወበከመ ኢነሥኡ ስንቀ ለፍኖት በከመ ትእዛዙ ለመድኀኒነ እንበለ በትር ባሕቲታ ውእቱኒ ኢነሥአ ምንተኒ እንበለ በትር ወማዕተበ እድ ባሕቲታ:: | ፰ | በመድኀኒታችን ትእዛዝ ከበትር በስተቀር ለመንገድ ስንቅ እንዳልያዙ እሱም ያለ በትርና በእጁ ከሚባርክባት መስቀል በቀር አልያዘም:: |
| ፱ | ወበከመ ተለወ ዐሠሮሙ ወዴገነ ፍኖቶሙ ከማሆሙ ረከበ ማኅደረ ወዐሥራተሂ ወኢየሐጽጽ እምኔሆሙ | ፱ | ፍለግቸውን እንደ ተከተለና በመንገዳቸውም እንደ ሔደ እንደ እነርሱ ማደሪያ ገና ዐሥራትን ዐገኘ ከእነርሱም አያንስም:: |

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲ ወለዝንቱሰ አብ ብእሴ አምላክ ብፁዓዊ አቡነ ክቡር ሐዋርያዊ በጸሎተ ሚካኤል ኢይትዌዳዕ ነገረ ግብሩ ወጻማ ገድሉ፡፡

፲ የዚህ የእምላክ ሰው፣ ብፁዕ ክቡር ሐዋርያ በጸሎተ ሚካኤል የሠራው ሥራና የተጋደለው ገድል አይፈጸምም፡፡

፲፩ ወንሕነኒ ፍቁራን ለእመ ኢተከህለነ ተሊወ ዐሠሮሙ ወተወክፎ ጻማሆሙ ወንግበር ተዝካሮሙ ለቅዱሳን በአምጣነ ይትከሀለነ እንዘ ንትአመን በጸሎቶሙ እስመ ጸሎተ ጻድቅ ትክል ወታሠልጥ እስመ ባቲ ብዙኀ በቊዔት

፲፩ የተወደዳችሁ ሆይ እኛም ፍለጋቸውን መከተልና ተጋድሎአቸውንም ካልተቻለን በጸሎታቸው አምነን በሚቻለን መጠን የቅዱሳንን መታሰቢያ እናድርግ የጻድቅ ሰው ጸሎት ትችላለች ግዳጅም ትፈጽማለችና ብዙ ጥቅም አላትና፡፡

፲፪ በከመ ጽሑፍ በወንጌል "ዘተወክፈ ነቢየ በስመ ነቢይ ዐሰበ ነቢይ ይነሥእ ወዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻድቅ ዐሰበ ጻድቅ ይነሥእ"፡፡

፲፪ በወንጌል እንደተጻፈ በነቢይ ስም ነቢይን የተቀበለ የነቢይን ዋጋ ያገኛል፤ በጻድቅ ስም ጻድቅን የተቀበለ የጻድቅን ዋጋ ያገኛል፡፡

፲፫ ወዘአስተየ ለአሐዱ እምእሉ ንኡሳን ጽዋዐ ማይ ቈሪር ባሕቲቶ በስመ ረድእየ አማን እብለክሙ ኢየሐጕል ዐስቦ አማን ኢየሐጕል ዐስቦ ዘይገብር ተዝካሮሙ ለጻድቃን ወለሰማዕት፡፡ ማቴ.፲፥፵፩

፲፫ ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ በደቀ መዝሙሬ ስም ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ ያጠጣ እውነት እነግራችኋለሁ ዋጋውን አያጣም፡፡ የጻድቃንንና የሰማዕታትን መታሰቢያቸውን የሚያደርግ በእውነት ዋጋውን አያጣም፡፡ ማቴ.፲፥፵፩

፲፬ ሰምዑ ኦ አኀው ለፈራሄ እግዚአብሔር ዘከመ ይሤኒ ደኀሪቱ ወይትባረክ ዕለተ ሞቱ ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር መዝ.፻፲፭፥፮

፲፬ ወንድሞች ሆይ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ፍጻሜው እንደሚያምርለት የሞቱም ዕለት እደሚባረክ ስሙ የጻድቅ ሰው ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው መዝ.፻፲፭፥፮

፲፭ አማን ክቡረ ኮነ ሞቱ ለዝንቱ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ለባሴ ንጽሕ ኖትያዊ ዘኀደፈ ሐመሮ በመቃድፈ መስቀል ዘኢያስጠሞ መዋግደ ዓለም ዘብዙኀ ማዕበሉ።

፲፭ በእውነት ንጽሕናን የለበሰ የዚህ የአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ሞቱ የከበረ ሆነ፣ ማዕበሉ ብዙ የሆነ የዓለም ሞገድ ያላሰጠመው መርከቡን በወንጌል መቅዘፊያ ያሻገረ ዋናተኛ ነው።

፲፮ ይሰምይዎ ነቢየ ወሚመ ሐዋርያ አው መነኮሰ ወዝኩሉ ይትረከብ ላዕሌሁ ለብእሴ እግዚአብሔር አቡነ በጸሎተ ሚካኤል።

፲፮ ነቢይ ይሉታል ወይም ሐዋርያ ወይም መነኩሴ ይህ ሁሉ በእግዚአብሔር ሰው በአባታችን በጸሎተ ሚካኤል ይገኛል።

፲፯ ዐምደ ሃይማኖት ዘኢይንሕል ወመሠረት ዘኢያንቀለቅል ብእሲ አዛል መሰተጋድል ኀያል ብዙኀ ገድል አያተኑ እዜኑ ዕበዩ ለአቡየ መምህረ ሕግ ዘበአማን ወንጹሕ ከመ ዕጣን ወፍሡሕ ከመ ወይን ዘይንእዳሁ ዐብያተ ክርስቲያናት ዘአሰርገዎን በስብሐታት።

፲፯ የማይፈርስ የሃይማኖት ዐምድ /ምሰሶ/ የማይነዋወጥ መሠረት ነው፤ የሚጋደል ጐልማሳ ገድሉ የበዛ ኀያል ነው። እውነተኛ የሕግ መምህር እንደ ዕጣን ንጹሕ፣ እንደ ወይንም ደስ የሚያሰኝ በምስጋና ያስጌጣቸው አብያተ ክርስቲያናት የሚያመሰግኑት የአባቴን ክብሩን ስንቱን እናገራለሁ።

፲፰ ኦ አባ ክቡር እፎ ይሤኒ ሰሚዐ ዜናከ ወይጥዕም እመዐር ወሦከር ወያስተፌሥሕ ልበ ወያጸሉ አእዛነ ወያጸልል አዕፅምተ ወያሠርሮ ለኀሊና ከመ ዘስተየ ወይነ ከራሜ።

፲፰ ክቡር አባት ሆይ ዜናህን መስማት እንዴት ያምራል፤ ከመዐርና ከስኳርም ይጣፍጣል፣ ልብን ያስደስታል፤ ጆሮን ያዘነብላል፤ አጥንትን ያለመልማል፣ የከረመ ወይን እንደ ጠጣ ሰውም ኀሊናን ያበርረዋል፤

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፱ ስብሐት ለአብ ለዘአሥረቀ ለነ ዘንተ ኮከበ መብርሄ ወሰጊድ ለወልድ ለዘአጽንዖ በገድሉ ከመ ይኩነነ መራሔ አኰቴት ለመንፈስ ቅዱስ ዘጸገወነ ኪያሁ መምህረ እመዋቅሕቲሁ ለጸላኢ ፈታሔ ዘሎቱ ይደሉ ውዳሴ ወስባሔ ዘከደነ ዓለመ ለሱራኄ፡፡

፲፱ ይህን የሚያበራ ኮከብ ላወጣልን ለአብ ምስጋና ይገባል መሪ ይሆነን ዘንድ በገድሉ ላጸናው ለወልድ ስግደት ይገባል፤ ከጠላት ማሰሪያ የሚፈታ እርሱን ለሰጠን ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል፤ ዓለምን በብርሃን ለአለበሰ ለእርሱ ክብር ምስጋና ይገባል፡፡

፳ ስብሐት ለአብ ለዘጸገወነ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አበ መነኮሳት ተላዊሆሙ ለሐዋርያት ዕጉሥ በምንዳቤ ወበቅሥፈታት ወለወልድ ስግደት ዘአጥብዖ ለዝንቱ ብፁዓዊ አቡነ ለከዊነ ሰማዕት አኰቴት ወባርኮት ለመንፈስ ቅዱስ ቡሩክ ወእኩት በአፈ ሰብእ ወመላእክት ወበኩሉ ፍጥረታት በምድር ወበሰማያት በባሕር ወበቀለያት፡፡

፳ የመነኮሳት አባት የሐዋርያት ተከታይ፣ በችግርና በግርፋት የሚታገሥ አባታችን በጸሎተ ሚካኤልን ለሰጠን ለአብ ምስጋና ይገባል፤ ሰማዕት ለመሆን ይህን ብፁዕ አባታችን ላጸናው በወልድም ስግደት ይገባል፤ በሰውና በመላእክት አንደበት፣ በፍጥረታትም ሁሉ፣ በምድርና በሰማያት በባሕርና በቀላያት ለሚመሰገንና ለሚከበር ለመንፈስ ቅዱስም ክብር ምስጋና ይገባል፡፡

፳፩ ዘአንገፎ ለዝንቱ ብእሲ እመሥገርት ነዓዊት ከመ ይኩን ኖላዌ አባግዕ ወአባግዕት ወከማሁ ለነኒ ያንግፈነ እምአፈ ተኲላ በኀይለ ጸሎቱ ቅድስት፡፡

፳፩ የአባግዕና የአባግዕት /ምእመናንና ምእመናት/ ጠባቂ ይሆን ዘንድ ይህን ክቡር አባት ከተጠመደች ወጥመድ ያዳነው እንዲሁ እኛንም ቅድስት በሆነች በጸሎቱ ኀይል ከተኲላ /ሰይጣን/ አፍ ያድነን፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፷፪ ለዘተጋባእነ ሀየ በዛቲ ዕለት ያስምዐነ ቃለ ፍሥሓ ወሐሤት ከመ ንግበር ተዝካሮ በአምጣነ ይትከሀለነ በቊርባን ወበስብሐት፣ በጸሎት ወግናይ በስግደት በመዝሙር ወበማኅሌት በከመ ትብህለ በዳዊት ዝክረ ጻድቅ ለዓም ይሄሉ ዝክረ ጻድቅ በውዳሴ፡፡

፷፪ በዚህች ዕለት በዚህ ቦታ የተሰባሰብን እኛን በሚቻለን መጠን መታሰቢያውን በቊርባን በምስጋና በጸሎት በክብርና በስግደት፣ በመዝሙርና በማኅሌት እናደርግ ዘንድ የደስታንና የሐሴትን ቃል ያሰማን በዳዊት የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል የጻድቅ መታሰቢያ በምስጋና ነው እንደተባለ፡፡

፷፫ ኦ እንጦንስ መንፈሳዊ ዘፈታሕከ ለበግዐ ምስጢር ተመሲሎ ሕፃነ እንዘ ያከሞሲስ ወይሜጥወከ ይምኖ ወጽግሞ ወመጠውኮሙ ለደቂቅከ ወከፈሎሙ ርስተ ሀብተ ጸሎትከ እስከ ነጸርዎ ገሀደ በዐይነ ሥጋ ወከማሁ ይክፍለነ ርስተ በረከተ ጸሎትከ እለ ንፈትዋ ለበረከትከ፡፡

፷፫ ሕፃንን በመምሰል ፈገግ እያለ የምስጢር በግን የፈታኸው ቀኙንና ግራውን የሰጠህ ለልጆችህም የሰጠሃቸው የጸሎትህም ሀብት በዐይነ ሥጋ እስኪያዩት ድረስ ርስት አድርጎ የሰጣቸው መንፈሳዊ አባት እንጦንስ ሆይ እንዲሁ በረከትህን ለምንፈልጋት የጸሎትህ በረከት ርስትን ያድለን፡፡

፷፬ ኀበ ተገብረ ተዝካርከ ወኀበ ተነበ መጽሐፈ ገድልከ ሀየ ይኩን ሣህል ወምሕረት እስመ ድልው ለኀዲር በረከተ ኖሎት በላዕለ አርድእት ባርከነ አባ ባሕረ ጥበባት ንስር ሰራሪ ልዑለ ስብከት ተናጋሪ በኀይለ መለኮት ጸባቲ በዐቅለ ባሕረ መጻሕፍት፡፡

፷፬ መታሰቢያህ በተደረገበት የገድልህም መጽሐፍ በተነበበት በዚያ ይቅርታና ምሕረት ይሁን፡፡ የመምህራን / እረኞች/ በረከት በደቀ መዛሙርት ላይ ለማደር የሚገባ ነውና የጥበባት ባሕር አባት ሆይ ባርከን በራሪ ንስር ስብከትህ ከፍ ያለ በመለኮት ኀይል የምትናገር በመጻሕፍት የባሕር ጥበብ የምትዋኝ ሆይ ባርከን፡፡

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፷፫ አ ዳግማይ ጳውሎስ ልሳነ ዘርብ ሰሚዐ ዜና ገድልከ ዘይኤድም ለልብ ወዘተውህበ ለከ ዘመዊዕ ኮከብ፡፡

፷፫ እንደ በገና መምቻ አንደበትህ ያማረ ዳግማዊ ጳውሎስ ሆይ የገድልህን ዜና መስማት ለልብ ደስ የሚያሰኝ ነው የአሸናፊነትም ኮከብ የተሰጠህ ነህ፡፡

፷፬ አ አባ አበ ሕዝብ ወአሕዛብ ወለመነኮሳት መክብብ፤ ኍልቈ ሰጊድከ ከመ ነጠብጣብ ዘያዘነግአ ለልብ ገጸ መካን ኀበ ሰገድከ ዘትኤምቆ ከመ ግብ፤ መንክራቲከ ለነጊር ዕጹብ፤ ዘዐደውኮ ለባሕረ ዓለም ርሒብ፤ ዘኢዐገተከ መሣግሪሁ ርቡብ፡፡

፷፬ አባት ሆይ የአሕዛብና የሕዝብ አባት የመነኮሳትም አለቃ ነህ፤ የስግደትህ ብዛት ልብን የሚያዘነጋው እንደ ዝናም ጠብታ ነው፡፡ የሰገድህበትም ቦታ እንደ ጉድጓድ ይጐደጉዳል፡፡ ተአምራትህ ለመናገር ድንቅ ነው፡፡ ኀላፊውን የዓለም ባሕር የተሻገርኸው የተዘረጋ ወጥመድ ያላጠመደህ ነህ፡፡

፷፭ አ አባ ንሥአነ ዐሥራተ እምወልደ አብ፤ አመ ይትገብር ለኅሩያን ከብካብ፤ ወአመ ይሰደዱ ፳ አክላብ አመ ይውኀጦሙ፤ ዘአንብዕ አስራብ፤ አዕድወነ እንተ መጽብብ ከመ ንባእ ምስሌከ ውስተ መርኅብ

፷፭ አባት ሆይ ከአብ የባሕርይ ልጅ ዐሥራት አድርገህ ተቀበለን፤ ለተመረጡት ሠርግ በሚደረግ ጊዜ አምስቱም ውሾች በሚሰደዱ ጊዜ የእንባ ጐርፍ በሚወጣቸው ጊዜ ከአንተ ጋር ወደ ሰፊው እንገባ ዘንድ ከጠባቡ አሻግረን፤

፷፮ ወሶበ በጽሐ ፍልሰቱ ለአቡነ ጸሎተ ሚካኤል ጸውዖ ለአሐዱ ረድኡ እንዘ ይብል ነዐ ንሑር ውስተ በኣት ወዐተበ ፬ ገበዋቲሁ ለበኣት ወሰፈሖ እደዊሁ ወእገሪሁ መጠወ ነፍሶ ውስተ እደ ፈጣሪሁ፡፡

፷፮ የአባታችን የበጸሎተ ሚካኤል ዕረፍቱ በደረሰ ጊዜ አንዱን ደቀ መዝሙር ወደ ዋሻ እንሒድ ዘንድ ና ብሎ ጠራው፡፡ መቋሚያውንም ይዞ ወደ ዋሻው ገባ፤ የዋሻውንም አራቱን መዓዘን ባረከ፤ እጆቹንና እግሮቹን ከዘረጋ በኋላ ነፍሱን በፈጣሪው እጅ ሰጠ፡፡

# ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፷፱ ተፈጸመ መጽሐፈ ገድሉ ለአቡነ ትሩፍ በጸሎተ ሚካኤል ወኮነ ዕረፍቱ አመ፳ወ፩ ለወርኀ ሐምሌ፡፡

፸ ወስብሐት ለእግዚአብሔር ለዝላፉ ለዓለመ ዓለም አሜን፤ አሜን፤ አሜን ለይኩን ለይኩን ለይኩን፡፡

፸፩ ዘንተ መጽሐፈ ለዘጸሐፈ ወለዘአጽሐፈ ለዘአንበበ ወለዘተርጐመ ወለዘሰምዐ ቃላቲሁ ኀቡረ ይምሐሮሙ እግዝአብሔር በመንግሥተ ሰማያት፡፡

ወያሰምዖሙ ቃለትፍሥሕት ወሐሤት በእንተ ሰእለታ ለእግዝእትነ ሙዳየ ሰእለታት

በጸሎቱ ወአስተብቍዖቱ ለአቡነ በጸሎተ ሚካኤል አበ መነኮሳት ይመሐረነ ክርስቶስ ንጉሠ ስብሐት በዝ ዓለም ወበዘይመጽእ ዓለም፡፡

ወላዕሌነ ይኩን ሣህል ወምሕረት እስከ እስትንፋስ ደኀሪት አመ ይመጽእ ጸባኦት በግርማ መንግሥቱ ፍጽምት ወአመ በአደዊሁ ይትገበር ጸሎት፡፡

፷፱ ፍጹም የሆነ የአባታችን የበጸሎቱ ሚካኤል ገድል ተፈጸመ ዕረፍቱም ሐምሌ ሃያ አንድ ቀን ነው፡፡

፸ ዘወትር ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን አሜን አሜን ይሁን ይደረግ፤ ይጽና፡፡

፸፩ ይህን መጽሐፍ የጻፈውን ያጻፈውን፣ ያነበበውን፣ የተረጐመውን፣ ቃሉንም የሰማውን በአንድነት እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ይቅር ይበላቸው፡፡

የጸሎት መዝገብ በሆነች በእመቤታችን አማላጅነት የደስታና የሐሴት ቃልን ያሰማቸው፡፡

የመነኮሳት አባት በሆነ በአባታችን በጸሎተ ሚካኤል አማላጅነትና ጸሎት የክብር ባለቤት ንጉሥ ክርስቶስ በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም ይቅር ይበለን፡፡

የመነኮሳት አባት በሆነ በአባታችን በጸሎተ ሚካኤል አማላጅነትና ጸሎት የክብር ባለቤት ንጉሥ ክርስቶስ በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም ይቅር ይበለን፡፡ በእኛም ላይ እስከ መጨረሻይቱ እስትንፋስ ይቅርታና ምሕረት ይሁን ፡፡

## ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

ወአመ ያረፍቆሙ እንዘ ይቀንት አመ ይደለው ለጻድቃን ትፍሥሕት ወአመ ይሰድዶሙ አፍአ ለከለባት፣ ኀበ ፈለገ እሳት ወኀበ ጸናፌ ጽልመት፡፡

የሠራዊት ጌታ እርሱ ፍጽምት በሆነች በመንግሥቱ ግርማ በመጣ ጊዜ በእጁ /በሥልጣኑም/ ጸሎት በተደረገ ጊዜ ታጥቆ ባስቀመጣቸው ጊዜ ለጻድቃን ደስታ በተዘጋጀ ጊዜ ውሾችንም ወደ ውጭ በሰደዳቸው ጊዜ ውሾችንም ወደ እሳት ባሕርና ጽኑ ጨለማ ወዳለበት ወደ ውጭ በሰደዳቸው ጊዜ ፡፡

ወአመ ያስተርኢ ዘክቡት ቅድመ ገጹ ለብሑት ወአመ ይትከወሱ ኀይለ ምድር ወሰማያት እመ ያንበሰብሱ መባርቅት፤ ወይሐወኩ ነፋሳት፣ ወአመ ይነጽፉ ባሕር ወቀላያት፣ ወኵሉ ለለ፩ አመ ይትሐተት፡፡

ሥልጣን ባለው በእርሱ ፊት የተሰወረው በተገለጠ ጊዜ የምድርና የሰማይ ኀይል በናወጸ ጊዜ መባርቅት /በተከለጨለጩ/ በተመላለሱ ጊዜ ነፋሳትም በታወኩ ጊዜ ባሕርና ቀላያት በደረቁ ጊዜ እያንዳንዱ ሁሉ በተመረመረ ጊዜ፡፡ በእኛ ላይ ይቅርታና ምሕረት ይሁን፡፡

አመ ያጕብእ ኵሉ ጾሮ በእይቲ ዕለት ቅድስት አመ ያጠብሑ ክልኤቱ እልሕምት ለምሳሐ ፲ ምእት ዓመት ይክፍለነ ሀልዎ በደብረ ጽዮን ቅድስት ለዓለመ ዓለም አሜን አሜን ወአሜን፡፡

ቅድስት በሆነች በዚያች ዕለት ሁሉም ሥራውን በመለሰ ጊዜ ሁለቱ ላሞች በአንድ ሺህ ዓመት ምሳሌ በተሠጠው ጊዜ ቅድስት በሆነች በደብረ ጽዮን /የጽዮን ተራራ/ መኖርን ለእኛ ያድለን፡፡ ለዘለዓለሙ አሜን ይሁን ይደረግ፡፡

# መልክአ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፩ ሰላም ለእግዚአ ክብራ ዘኢያፅርዐት መሐላ፣ ዘምስለ ምታ ማርቆስ ማኅደረ ፍሥሐ ወተድላ፣ ሚካኤል መልአክ እንተ በአክናፍ ጸለላ፣ ሶበ ውሕዘ እንተ ቅድሜሁ አንብዐ አዕይንት ሄላ፣ እስመ እም ንጹሕ ካህን ተፀንሰ ዕጓላ፡፡

፪ ሰላም ለፅንሰትከ ዘአንጸፍጸፈ ጽሙና ወለልደትከ ዓዲ በብሥራተ መልአክ ወዜና በጸሎተ ሚካኤል ሀበኒ ወጸግወኒ ጥዒና፣ ነፍስየ ጊዜ ዕረፍት ከመ ኢትርአይ ሙስና፣ በእደ ሚካኤል ሴስየኒ አውሪደከ መና፣

፫ ሰላም ለዝክረ ስምከ ከመ ስቴ መዐር ጥዑም፣ ወለሥዕርትከ ዓዲ በቅብዐ መንፈስ ልምሉም፣ በጸሎተ ሚካኤል ጻድቅ እንተ አልብከ ንዋም፣ በጾም ወበቀኖና ከመ እንተ አብ ወእም ለመነኮሳት አበው ዘኮንኮሙ ዖም፡፡

፬ ሰላም ለርእስከ ለእንጦንዮስ አምሳሉ፣ ወለገጽከ ሰላም ዘይበርህ ሥነ ጸዳሉ፣ በአምሳለ ፀሐይ ወወርኅ ወከመ ከዋክብት ዘላዕሉ፣ ደቂቅከ መነኮሳት እለ ገዳማተ ኤሉ፣ በጸሎተ ሚካኤል አቡነ ባርከነ ይብሉ፡፡

፭ ሰላም ለቀራንብቲከ ዘኢለመደ ድቃሰ፣ ወለአዕይንቲከ ካዕበ ለንዋመ ሥጋ ዘኢኀሠሠ በጸሎተ ሚካኤል ዘኮንከ ማኅደረ አምላክ መቅደሰ፣ ጸገወነ ለአግብርቲከ መንፈሰ ልቡና ቅዱሰ፣ በእንተ ቀኖና ወጾም ዘይጥዒ ነፍሰ፡፡

፮ ሰላም ለአእዛኒከ አእዛነ መንፈስ ዘኮና፣ ወለመላትሒከ ልሑይ ዘኢሰሰለ ብርሃና፣ በጸሎተ ሚካኤል ክቡር ተወካፌ ሕግ ዘደብረ ሲና፤ ረኀበ ሶበ ርኀብከ ዘተሴሰይከ መና፣ በይነ ዘረሰይከ ምግበከ ቀኖና፡፡

፯ ሰላም ለአዕናፊከ መዓዛ ቅዳሴ ዘአጼነዋ፣ ወለከናፍሪከ ሰላም ዘኢነበበ ዕልዋ፣ በጸሎተ ሚካኤል ሕፃን ዘአንፈርዓጽከ ከመ ጣዕዋ፣ በገዳም ከመ ሀሎከ በአምሳለ አዳም ወሔዋ፣ አምጣነ ዘበዝኀ ደቂቅከ ነዋ፡፡

፰ ሰላም ለአፉከ ምዕራገ ጸሎት ማዕዳ፣ ወሰላም እብል ለአስናኒከ ጸዓዳ፣ በጸሎተ ሚካኤል ሢመኒ ለመንግሥተ ሰማይ በዐውዳ፣ ድርሳነከ እስመ አቅረብኩ በፍቅረ ልቡና ሠሌዳ፣ በገጸ ፈጣሪ ልዑል ኢይኩን እንግዳ፡፡

# መልክአ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፱ ሰላም ለልሳንከ ወለቃልከ ናዛዜ ለእስትንፋስከ ምሉእ እስትንፋሰ መንፈስ ከመ ተከዜ፣ በጸሎተ ሚካኤል አቡነ እስእለከ ይእዜ፣ በይነ ዘአቅረብኩ ለእንተ መዋዕል ወጊዜ፣ እምልቡናየ ይሴስል እንባዜ፡፡

፲ ሰላም ለጉርዔከ መዓዛ በረከት ዘጥዕመ ወለከሣድከ ስርግው አስኬማ መላእክት ፍጹመ፣ በጸሎተ ሚካኤል ጻድቅ እንተ መነንከ ዓለመ፣ አስተዐጽብ ቅድስናከ ወኂሩተከ ዳግመ፣ ወለመነኮሳት አበው ዘኮንኮሙ እመ፡፡

፲፩ ሰላም ለመትከፍትከ ስርግወ አነዳ፣ ወለዘባንከ ስፉሐት ዋዕያተ ፀሐይ ውሉዳ፣ በጸሎተ ሚካኤል ባዕል ለግብረ ቀኖና አጸዳ መዓዛ ገድልከ ዘይጼኑ በምድረ በዳ፣ ውስተ ደብረ ግሸ ሕንፃከ ያመጽኡ ጋዳ፡፡

፲፪ ሰላም ለእንግድአከ አስኬማ መላእክት ዘሐቀፈ፣ ወለሕፅንከ ዓዲ ዘኢፈተወ መንጸፈ፣ በጸሎተ ሚካኤል ዘኮንከ ለግብረ ቀኖና ምዕራፈ፣ ያስተፌሥሕ ሕዙነ ልብ ዜና ገድልከ ጽሑፈ ወድርሳንከ ካዕበ ያስተዐጽብ ዘልፈ፡፡

፲፫ ሰላም ለአእዳዊከ ጽፉሐት ለሰጊድ፣ ወለመዛርዒከ ጽኑዕ ከመ እንተ ዘብርት ዓምድ፣ በጸሎተ ሚካኤል ክቡር ዘውገ መላእክት አንጋድ፣ አኅልፈኒ በጸሎትከ አምባሕረ ሞገድ፣ ወእም መከራሃ ለሲዖል ዘግርምት ዐውድ፡፡

፲፬ ሰላም ለኩርናዕከ ኩርናዐ አናብስት ዘተመሰላ መለእመትከ ሰላም ዘዕፍረተ ገነት ተድላ፣ በጸሎተ ሚካኤል ቀዳሲ ለድንግለ ሙሴ ወዕጓላ፣ አድኅነኒ በኪዳንከ እም አፈ አንበሳ ወተኩላ፣ ወአስተብቍዕ ካዕበ በጽኑዕ መሐላ፡፡

፲፭ ሰላም ለእራኀቲከ ኀብስተ ቀኖና ዘአኀዛ፣ ወለአጻብዒከ ዓዲ ለፍትወተ ዓለም ዘአውገዛ፣ በጸሎተ ሚካኤል ዘኮንከ በአምሳለ ኀያል ወሬዛ፣ ነፍሰ እንቲአየ ከመ ኢትሑር ትኩዛ፣ ጊዜ ፀኣታ ፍጡነ ናዝዛ ናዝዛ፡፡

፲፮ ሰላም ለአጽፋረ እዴከ እንተ ላዕሌሆን ዘሠረጸ፣ ወለገቦከ ሰላም ለንዋመ ሥጋ ተግሣጸ በጸሎተ ሚካኤል ህልው ለደብረ ግሼ በውስተ ሕንፃ፣ ደቂቅከ በይነ ዘበዝኁ ከመ ውሳጤ ባሕር ዘሆፃ፣ በጽድቅከ አባ ኲለሄ ሐውፃ፡፡

# መልክአ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፲፯ ሰላም ለከርሥከ ኀብስተ ቀኖና ዘተሴሰየ፤ ወለልብከ ሰላም ባሕርየ መለኮት ዘኀለየ፤ በጸሎተ ሚካኤል ጻድቅ ዘተመነይከ ሠናየ፤ ለጾም ወለቀኖና ሶበ ረሰይከ ንዋየ፤ ደቂቅከ ነዋ ተወልዱ ዝየ።

፲፰ ሰላም ለኩልያቲከ ለግብረ ቀኖና ዘያንሶሱ፤ ወለኀሊናከ ዓዲ ለጽድቀ ሃይማኖት ሞገሱ፤ በጸሎተ ሚካኤል ነቢይ ከመ መስፍነ ሕግ ኢያሱ፤ ደቂቀ መሃይምናን ረደኤተከ ይኅሥሡ፤ ኀበ ተድላ ገነት ዘሀሎከ ምስሌከ ፈለሱ።

፲፱ ሰላም ለኅንብርትከ ኀንብርተ መንፈስ ረቂቅ ወለሐቌከ ቅኑት ቅናተ ድንጋሌ ዘሠቅ፤ በጸሎተ ሚካኤል ኢዮብ ዘትዕግሥትከ ርሑቅ፤ ዜናከ ሶበ ተሰምዐ እንተ በዐረብ ወሠርቅ፤ ሕንፃ መቅደስከ ዘመልኡ ደቂቅ።

፳ ሰላም ለአቍያጺከ አዕማደ ቀኖና ወጾም፤ ወለአብራኪከ በሰጊድ ዘኢረከቦን ሕማም፤ በጸሎተ ሚካኤል ያዕቆብ ሰዋስወ ብርሃን ቅውም፤ ዘነጸርከ በምድረ ግሸ ዘአስተርአየ በቅድም፤ ሰዋስወ ብርሃን ይእቲ ማርያም።

፳፩ ሰላም ለአእጋሪከ ወለሰኰናከ ልዑል፤ ወለመከየድከ ዘኮና ወከየደ ምሕረት ወሣሕል፤ በጸሎተ ሚካኤል ኤልያስ መገሥጸ ዘማ ኤልዛቤል፤ ጸሎትከ በጊዜ በጽሐ እም ኢትዮጵያ ደወል፤ እስመ እምድሩ ተሰደ ሙስና ወሐጕል።

፳፪ ሰላም ለአፃብዒከ ከመ ዕንቈ ባሕርይ ዘንዕዱ፤ ወለ አጽፋረ እግርከ ጽዱላት ገዳማተ ኲሎን ዘዖዱ፤ በጸሎተ ሚካኤል ዘኮንከ ከመ መላእክት አሐዱ፤ ቅዱሳን መነኮሳት ታሕተ እግርከ ሰገዱ።

፳፫ ሰላም ለቆምከ በአምሳለ መልአክ ቆሙ፤ ወለመልክአከ ሰላም ዘተሳተፈ ለመልአከ ምሕረት ዕበየ ስሙ፤ በጸሎተ ሚካኤል አብ ከመ እም ኮንከሙ፤ ሶበ መጽኡ መነኮሳት ለተከለ ሃይማኖት ወልዶሙ፤ ጻማ ቅዱሳን ኢትክሉ ዘተቤ ቀዲሙ።

፳፬ ሰላም ለፀአተ ነፍስከ ዘተለዐለ ክብሩ ወለበድነ ሥጋከ ኤም በጕሎ ማከዳ ማኅደሩ፤ በጸሎተ ሚካኤል ጻድቅ ለእግዚአብሔር ፍቁሩ፤ ሶበ ሐወጸከ ዘምስለ ማርያም መጾሩ፤ ዕበየ ክብርከ መላእክት አንከሩ።

# መልክአ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፺፭ ሰላም ለግንዘተ ሥጋከ በእደ ትጉሃን አርድእት፣ ወለመቃብሪከ ሰላም እንተ ደብረ ጕሎ ማከዳ ስፍሕት፣ በጸሎተ ሚካኤል ክቡር በድንግልና ንጽሕት፣ ድርሳነከ በተአምኖ እስመ አቅረብኩ በግብት፣ ወኢትትሐየየኒ ለኀጥእ ገብርከ ትሑት፡፡

፺፮ ሰላም ለፍልሰተ ሥጋከ እምውሳጤ ገዳም ስፉሕ፣ በፈቃደ አምላከ ልዑል እምድኅረ አዝማናት ነዊኅ፣ በጸሎተ ሚካኤል አቡነ በትዕግሥት ብዙኅ አስተዐፅብ ዜና ገድልከ በቃለ ኖላዊ ትጉህ፣ አምጣነ ተረክበ ሥጋከ ንጹሕ፡፡

፺፯ ሰላም ሰላም ወሰላም ለፍልሰተ ሥጋከ መአድም፣ እምውሳጤ ገዳም ዘቅድም፣ በጸሎተ ሚካኤል ትጉህ ዘተሐውር በጊዜ ንዋም፣ ፍጹመ ሶበ በጻሕከ ውስተ ደብረ ግሼ ገዳም፣ እንተ ለምሕረት ወሣህል ወረደ ዝናም፡፡

፺፰ ሰላም ለከ በጸሎተ ሚካኤል አቡነ ፍቁረ ማርያም እምነ፣ ወበእንተዝ ገብርከ እስእለከ ፍጡነ ከመ ትጽሐፍ ስመ ዚአየ በኪዳንከ እሙነ እስመ ረሰይኩከ ኪያከ መድኅነ፣

፺፱ ሰላም ለከ በጸሎተ ሚካኤል ሰማዕት አበ ብዙኃን መነኰሳት፣ በግብረ ቀኖና ወጾም ውስተ ደብረ ግሸ ጾማዕት፣ ወበእንተዝ ሰመይኩከ ዘውገ መላእክት፣ በዘተሰርገውከ አስኬማ ቅድስት፡፡

፻ ተወከፍ ዘአቅረብኩ ድርሳነ በረከት ሠናይ፣ ለመልክአቲከ ኲሎን በቃለ ግናይ፣ በጸሎተ ሚካኤል ሐዋርያ ወዘበነቢያት ነቢይ፣ ከመ ትኅድር በላዕሌየ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ርሡይ፣ እስመ ተማሕፀንኩ ገብርከ ነዳይ፡፡

፻፩ አባ ጸሊ በእንቲአየ ቅድመ መንበሩ ለእግዚእነ ሰላም በጸሎተ ሚካኤል አቡነ ፍቁረ ማርያም እምነ፣ በእንተዝ እስእለከ ገብርከ ፍጡነ፣ ከመ ትጽሐፍ ስመ ዚአየ በኪዳንከ እሙነ፣ እስመ ረሰይኩከ ኪያከ መድኅነ፡፡

፻፪ ሰላም ለከ በጸሎተ ሚካኤል ሰማዕት አበ ብዙኃን መነኮሳት፣ በግብረ ቀኖና ወጾም ውስት ደብረ ግሼ ጾማዕት ወበእንተዝ ተሰመይከ ዘውገ መላእክት፣ በይነ ዘተረሰይከ አስኬማ ቅድስት፣

## መልክአ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል

፻፫ ሰላም ለከ በጸሎተ ሚካኤል አበ መነኮሳት ኵሎሙ፤ በግብረ አስኬማ ወቆብዕ እንተ ወለድኮሙ፤ ውሉደ ዛቲ ምኔት ይስእሉከ በስሙ፤ ሶበ መጽኡ ውሉዱከ ኀበ ሀሎከ ቀዲሙ፤ ጻማ ቅዱሳን ኢትክሉ አኮኑ ትብሎሙ፡፡

፻፬ አድባር ድኁኃን ዘይቤ ሰሎሞን፤ ሊተሰ ይመስለኒ ነፍሳተ ጻድቃን፤ በጸሎተ ሚካኤል ካህን መከብበ ኵሎሙ ቅዱሳን፤ እንዘ ይሜህር ቃለ ዘበአማን፡፡

፻፭ ዐምደ ሃይማኖት ግሩም ውስተ ቤተ መቅደስ ዘይቀውም፤ በጸሎተ ሚካኤል ካህን መከሥተ አፉሁ መዓር ጥዑም፤ አመ አፍለሱ አዕፅምቲሁ በጕንዱየ ዓም፤ ሶበ አዕጸፉ አብራኪሁ አንጸፍጸፈ ደም፡፡